የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ምሁራን፣ ስለዚህ መጽሐፍ ምን ይላሉ?



"በብሉይም ሆነ በሐዲስ ኪዳን፣ ሐሰተኛ ነቢያት እንደ ነበሩ፣ እውነተኞቹም በጽኑ እንደተፋለሟቸው ቅዱስ መጽሐፍ በማያሻማ ሁኔታ ይነግረናል። ለዚህ ምክሩ ብዙ ቢሆንም፣ 'ነቢይ ነኝ የምትለውን ሆኖም ሐሰተኛ...እንዲሁም ሐዋርያ ሳይሆኑ ሐዋርያት ነን የሚሉ...' ከተለኘው አገላለጽ የተለየ ዋቢ ማስብ አስፈላጊ አይደለም።

በቀደምቶቹና በእኛ መካከል የዘመን ልዩነት ያለ ቢሆንም፣ ቃሉን በተመለከተ ግን የመርሕ ክፍተት እንዳለ ጨርሶ መታሰብ የለበትም። ከዚህ የተነሣ፣ ሐሰተኞችን ይልቁንም ራሳቸውን የቅዱስ ቃሉ መለኪያ ዘንግ አደረገው በመፈረጅ፣ ቅዱሳንን አያሳቱ ያሉትን ሐራጥቃዎች በእውነተኛው ቀናና መፋስም ያስፈልጋል። ተስፋዬም ከዚህ የተለየ ዐላማ የለውም። እኛም ወደዚህ መስመር እንድንዘልቅ አባቶች በቀደዱት ትልም ላይ እንድንንዘ ይጠራናል።"

——ጻድቁ አብዶ (መጋቢ)
የወቅቱ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ጎብረት ፕሬዚደንት

.....

"ለእምነት መቆም የሁሉም ክርስቲያን አቋም ሊሆን ይገባል። ክርስትናን የመጠበቅ፣ ትክክለኛውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት በዘመናት ሳይበረዝና ሳይከለስ ለራስ ተጠቅሞ ለሌላው የማስተላለፍ ኃላፊነት፣ ክርስቲያን ነኝ ብሎ የሚያምን ሁሉ ተግባር መሆን አለበት። ወንድማችን ዶክተር ተስፋዬ ሮበሌ በዚህ መጽሐፉ የሚነግረን (የሚሞግተን)፣ 'ለእምነታችሁ ልትጋደሉ ይገባችኋል' ይህ የእውነተኛ ክርስቲያን መገለጫ አንዱ ገጽታ ነውና' የሚለውን ነው። እስቲ ይህን መጽሐፍ አንብበን ከያለንበት፣ ምናልባትም ከተኛንበት አንንቃ!"

——ቴምድሮስ በየነ
የመሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ፕሬዚደንት

"ባለፉት ሁለት ዐሥርት ዓመታት፣ በአገራችን በኢትዮጵያ ክእምነት ነጻነትና ክወንጌል ሥርጭት አኳያ፣ የተለየና አዎንታዊ ሁኔታ ተፈጥሮ መቆየቱ ለሁላችንም ግልጽ ነው። ይህ እንደ ተጠበቀ ሆኖ፣ ክቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ አያደገ የመጣው አንዳንድ የእግዚአብሔር ቃል አውነት ጥሰት፣ የአስተምህሮት ግድፈትና የሐሰተኛ ነቢያት መበራከት፣ የወንጌሳውያን አብያተ ክርስቲያናትን አሳሳቢ ክሆነ ደረጃ ሳይ እያደረሳቸው ይገኛል። የወንድማችን የዶክተር ተስፋዩ ሮበሌ፣ 'አባይ ነባይ' መጽሐፍ እነዚህን የቃሉ መሠረት የሌሳቸውን የኑፋቄ ትምህርቶች፣ ክመሠረታቸው አንሥቶ በጥልቀትና በስፋት በመግለጽ፣ ተገቢውን መልስ የሚሰጥ እጅግ ጠቃሚና ወቅታዊ የሆነ መጽሐፍ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። በዚህ ጉዳይ ሳይ እስከአሁን ተጽፈው ካነበብኋቸው መጽሐፍ መካከል፣ ጥልቀት ያለውና ዕውቀት ያገኘሁበት መጽሐፍ ይህ ነው ማለት እችላለሁ። 'አባይ ነባይ' መጽሐፍ በአሁኑ ወቅት እየታየ ሳለው ወቅታዊ ችግር፣ በጉዳዩ ግራ ለተጋቡና አውነቱን መረዳት ለሚሹ ክርስቲያኖች ሁሉ እሉተማሪ፣ ጠቃሚና አስተዋጽኦው የጉሳ መሆኑን ልገልጽ እወዳለሁ።"

——ንጉሤ ተፈራ (ዶክተር)
ሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን

.....

"ከመጽሐፍ ቅዱስ ቅንብብ አኳያ ሲታዩ ሽውራራ፣ ወልካፋና አሳች የሆኑ አስተምህሮዎች በዘመኛ መልካቸው፣ እንደ ጭንቀር እየተስፋፉ ነው። የቤተ ክርስቲያንንም አቋምና ጤና እየሸረሸሩ ይገኛሉ። እኒህ አስተምህሮዎች ክቅዱሳት መጻሕፍት የተጣጣመ መለኪያነት አንጸር አይዩ፣ ዝንፈታቸውን ደግሞም የክርስትና መሠረታዊ ትምህርት ጉሻሚና ተቀናቃኝነታቸውን፣ ለአማኒው ማኅበረሰብ ማሳየትና አግባብ የሆነውን ትምህርት ማስጨበጥ፣ ባሳደራነትን ወይም ዐቃቢነትን መወጣት ነው።

እነሆ ዛሬ ደግሞ፣ ወንድማችን ዶክተር ተስፋዩ ሮበሌ፣ 'አባይ ነባይ' በሚል ርእስ አዘጋጅቶ ያቀረበልን ዐይነተኛ መጽሐፍ ታዳጊ ነው። እግዚአብሔር ይባርከው! ጸጋውን አሁንም በጥበብና በማስተዋል ያብዛለት! ተስፋዩ መዐልት ክሌሊት ሊያነብና ሊጽፍ በቀሳሉ የማይበገር አእምሮውን ሳስብ አገረማለሁ። ጸጋ ያበዛለት እግዚአብሔር አምሳክን አመሰግናለሁ፣ አከብራለሁ። ለበረከት ይበለው!"

——ሰለሞን ከበደ
የቀድሞው ዓለም ዐቀፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር የሰሜን ምሥራቅ አፍሪካ፣ ኋሳ ሳይ ደግሞ የአፍሪካ ዳይሬክተር
የቀድሞው የመሠረተ ክርስቶስና የአብያተ ክርስቲያናት ኅብረት የቦርድ ሰብሳቢ

"ወንድማችን ዶክተር ተስፋዩ ሮበሌ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አቋም እንድንይዝ ተማጽኖ በማቅረብ፣ በምርምር የተደገፈ፣ በምዕራፍ በምዕራፉ ማጠቃሻ የታገዘ በሳል መጽሐፍ አቅርቦልናል።

በአገራችን በኢትዮጵያም ሆነ አበሾች በተዘሩበት ልዩ ልዩ የዓለማችን ክፍሎች፣ ወንጌሳዊውን ክርስትና አምነት አየሞገተ ያለውን አንግዳ ልምምድና ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት በመጽሐፍ ቅዱሱ አስተምህሮ በማረመ ረገድ፣ ይህ መጽሐፍ ትልቅ ድርሻ አለው።

ንባቡ ትዕግስትን የሚጠይቅ፣ እምነትን ብቻ ሳይሆን ቋንቋን ለመማር ትልቅ ዕድል የሚሰጥ በመሆኑ፣ አእምሮችን በአዳዲስ ቃሳት፣ እምነታችንን በመጽሐፍ ቅዱሳዊው እውነት ለማስታጠቅ፣ ወገባችንን ጠበቅ አድርገን በማዕዱ እንሳተፍ። ረቂቁን ቀምሼ አንደ ጣመኝ አልሸሸጋችሁም።"

——ንይሉ ቸርነት (ዶክተር/መጋቢ)
የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ኅብረት ቤተ ክርስቲያን በሎስ አንጀለስ—መጋቢ
የኢትዮጵያ ወንጌሳውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት በለሜን አሜሪካ
የቦርድ ፕሬዚደንት

.....

"ሐሰት አውነት በሚገለጽበት ቃሳት ተሸፋፍና በአደባባይ እየታወጀች ብዙዎችን ባሳተችበት ትውልድና ዘመን መኖር፣ እውነትን እጥብቀው ለያዙና ለሚወዱ ሁሉ የመንፈስ ብስጭትን ያስክትሳል። ክዚህም በተነሣ፣ በጌታ ጸጋ የእውነት ወዳጆች የሆኑ ቅዱሳን፣ በጸሎት አልፍኖቸው የአውነት አምሳክ እግዚአብሔር ይህን በእርሱ ሳይ የተቃጣውን የክፋት ምክር ስንፍና እያደረገ፣ የሳቱትን ሁሉ እንዲታደግና የዘመናችን ቤተ ክርስቲያን ከሳተችበት እንድትመለስ በመማጸን ሳይ ሰመሆናቸው እርግጥ ነው።

ወንድማችን ተስፋዬ ሮበሌ፣ 'አባይ ነባይ' በሚለው በዚህ መጽሐፉ፣ ያቀረበው መልእክት እግዚአብሔር የቅዱሳንን ጸሎት የመለስበት አንዱ መልስ ነው ብዬ ሰመናገር እውዳለሁ። የዚህ መጽሐፍ መልእክት የሳቱት እንዲመለሱ፣ አውነትን የያዙት ጸንተው እንዲቆሙ፣ ቤተ ክርስቲያንም ክስሕተትና ክአሳኞች ተጠብቃ ምዕመኖችዋን የምትጠብቅበት የጌታ የጸጋው መሣሪያ እንዲሆን ጸሎቴ ነው። 'ልጆቼ በአውነት እንዲሄዱ ክመስማት ይልቅ የሚበልጥ ደስታ የለኝም' (3ዮሐንስ 4)"

——ዮሴፍ መኮንን (መጋቢ)
የአብ ጸጋ ቤተ ክርስቲያን፣ ሲልቨር ስፕሪንግ ሜሪላንድ

አባይ ነባይ!

መፍቀሬ ነቢያትን እንዴት ማከም ይቻላል?



ወርኀ ጎሮር 2017 ዓ.ም

ከዶክተር ተስፋዬ ሮበሌ

THE EVANGELICAL SOCIETY FOR APOLOGETICS (TESFA)
ATLANTA GEORGIA
ተስፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር
አትላንታ፣ ጆርጂያ

ርእስ—አባይ ነባይ መፍተሬ ነቢያትን እንዴት ማዘም ይቻላል?
ጸሓፊ— ዶክተር ተስፋዬ ሮበሌ
አሳታሚ—ተስፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር
©መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው 2017 ዓ.ም

ያለ አሳታሚው ፈቃድ አባዝቶ ማሳተምም ሆነ፣ የተወሰነን ክፍል በተለያዩ መንገዶች ማራባት/ማባዛት፣ ከጥበቅ የተከለከለ ነው። በማንኛውም መልኩ መረጃ ለመውሰድ ከተፈለገ፣ በትክክል ሥርዐቱን ጠብቆ ሊጠቀስ፣ በጎዳግ መዘክር ሊመሳከት ይገባዋል።

የዘመን አቈጣጠርን በተመለከተ "እንደ ጕርጕሮሳውያን" ወይም "እንደ ኢትዮጵያውያን" የዘመን ቀምር እያልን ተጠቅመናል። የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት፣ የኢትዮጵያ የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር በኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር1954 ዓ.ም ካሳተመው ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ትርጉም እንዲሁም የኢንተርናሽናል የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር በ1993 ዓ.ም ካሳተመው የአዲሱ መደበኛ ትርጉም ነው።

የዚህ መጽሐፍ የተወሰኑ ምዕራፎች፣ ከ17 ዓ.ም በፊት ጸሓፊው፣ "ዐበይት መነሻቃን" በሚል ርእስ ባዘጋጀው መጽሐፍ ላይ ታትመዋል። ነገር ግን እነዚህ ምዕራፎች ከርእስ ጕዳዩ አንዲሰናሰኑ እንዲሁም በሮበብ ዙሪያ እንዲያወነጥኑ መሐራ ተደርጓል።

ጥያቄ፣ አስተያየትም ሆነ ሒስ ካለም፣ ለጸሓፊው በሚከተለው አድራሻ ይጻፉ፦—
ተስፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር *The Evangelical Society For Apologetics*

የመልእክት ሣጥን ቍጥር 23045	*271 Village Drive,*	*P.O. Box 23045*
ክድ 1000	*Loganville, GA. 30052*	*Code, 1000*
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ	*USA*	*Addis Ababa, Ethiopia*

Title—Prophecy, False Prophets, and Christian Apologetics
Publisher—The Evangelical Society For Apologetics

©Copyright 2017—Dr. Tesfaye Robele
All rights reserved. No part of this publication may be reproduced, stored in a retrieval system, or transmitted in any form or by any means-electronic, mechanical, photocopying, or other wise-without the prior written permission of the publisher and copyright owner.
Comments, questions, and criticisms of this book are welcome. Please address all correspondence to the author at the following address:
The Evangelical Society For Apologetics
271 Village Drive,
Loganville, GA. 30052
The United States of America

ምስጋና



ይህ መጽሐፍ ተዘጋጅቶ ሰንበብ እንዲበቃ—ከፅንሰቱ እስከ ልደቱ አጅግ በርካታ ሰዎች፣ ትልቅ ዕገዛ አድርገዋል።

በወቅቱ የተፈጠረውን ችግር አስመልክቶ፣ በልቤ የተጫረውን ውጥን ወደ ገቢር እንዲቀይር ያበረታታችኝ እንዲሁም የጎተመቱን ወጪ ሙሉ ሰሙሉ የሸፈነችው፣ በአክላንድ ካሊፎርኒያ የምትገኘው የአቤንኤዘር ቤተ ክርስቲያን ነች። ከዚህ በተጨማሪ የመጽሐፉ ምርቃት (*Book Signing*) በዚሁ በካሊፎርኒያ ልሳነ ምድር (*Bay Area*) እንዲደረግ ዕቅዱን በመንደፍ፣ ገቢራዊነቱን በመከታተል እንዲሁም ተዛማጅ ወጪዎችን በመሸፈን የወንጌል አጋርነታን አሳይታለች።

ላለፉት ሃያ አምስት ዓመታት የክርስትናን መሠረተ እምነት ከአስተምህሮአዊ ከጥቃት ለመከላከልም ሆነ፣ የምሥራቹን ወንጌል ለማጽናት ዐቅሜ የፈቀደውን ጥረት ያደረግሁ ይመስለኛል። ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ደረጃ ይህ ዐይነቱ ውስጠት የሚነካ ፍቅር፣ ዐጥንት የሚያለመልም አብሮነት፣ እንዙሮ የሆነን ልብ የሚገጥም ወጌሻነት፣ "ዐቅብቱ አምነት የአኔም ጎሳፌነትና ሥራ ነው" የሚል የባለዐደራነት መንፈስ ገጥሞኝ አያውቅም—በጭራሽ! በርግጥ መውተርተሬ በልዑል አምላክ ፊት አንዳች ፋይዳ ካለው፣ የእናንተ አይዞህ ባይነት አንደ ምን ታላቅ ሳያሆን ይችላል[1]? አቤንኤዘር—አምላክነ እግዚአብሔር ረዳአነ *(1ሳሙ 7÷12)*።

እንደ አቤንኤዘር ሁሉ ፍቅራቸውን በገቢር ያሳዩኝ በርካታ ወገኖች አሉ። ከዚህ የተነሣም ቊጭ ብዬ መጻፍ ችያለሁ። የሥራው ባለቤት ልዑል እግዚአብሔር፣ ለጤናማው ወንጌል ያላችሁን ቀናኢነት አትረፍርፎ ይባርክ። የስማቸው ዝርዝር እነሆ:—

- ወንድም በርሄ በርሄና ቤተ ሰቡ (አንቲያክ፤ ካሊፎርኒያ)
- ወንድም ሳሙኤል በየነና ቤተ ሰቡ (አክላንድ፤ ካሊፎርኒያ)
- ወንድም ግዮን ደሌና ቤተ ሰቡ (አክላንድ፤ ካሊፎርኒያ)
- ዶክተር ዘነበ አስፋውና ቤተ ሰቡ (አስተን፤ ቴክሳስ)
- ዶክተር ዳግም ታደሰና ቤተ ሰቡ (አክላንድ፤ ካሊፎርኒያ)
- ወንድም አክሊሉ ባምቦሬና ቤተ ሰቡ (ዴንቨር፤ ኮሎራዶ)
- ዶክተር ቶማስ ባህሩና ቤተ ሰቡ (አክላንድ፤ ካሊፎርኒያ)
- ወንድም አበበ ተዘራና ቤተሰቡ (ሰን ፍራንሲስኮ፤ ካሊፎርኒያ)

---

[1] እነሆ ይህ መጽሐፍ ታትሞ ለንባብ መቅረቡ ሳያንስ፣ ተቋርጦ የነበረው በሥነ ምግባር ላይ ትኩረት የሚያደርገው የአራት ቅጽ ተከታታይ መጻሕፍት ሥራ እንዲሁም በክርስቲያናዊ ዐቅብቱ እምነት ላይ የሚዘጋጁት ባለአራት ደርብ መጻሕፍት፣ እነሆ ሥራቸው ተጀምሯል። ይህ ደግሞ፣ "በአንድ ጠጠር ሁለት ወፍ" የሚባለውን "ነባር ተአምር" በሁለት ዕጥፍ በልጦታል።

- ዶክተር ሃይማኖት ዘአማኑኤልና ቤተ ሰቡ (ኤልክሪጅ፤ ሜሪ ላንድ)
- ወንድም ዳንኤል ጳውሎስ (አትላንታ፤ ጆርጂያ)
- ወንድም ሰሎሞን ሳህሌና ቤተሰቡ (ሮክቪል፤ ሜሪላንድ)
- ወንድም ሞገሥ ታምሬና ቤተሰቡ (ኦክላንድ፤ ካሊፎርኒያ)
- ወንድም አፈወርቅ ነጋሽና ቤተሰቡ (አይንግስ ሚልስ፤ ሜሪላንድ)
- ወንድም ኤርምያስ ላቀውና ቤተ ሰቡ (ዋሽንግተን ዲሲ)
- ወንድም ኤልያስ ሚደቅሳና ቤተ ሰቡ (ኦክላንድ፤ ካሊፎርኒያ)
- ቤሪያ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በዴንቨር (ዴንቨር፤ ኮሎራዶ)
- የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ኅብረት ቤተ ክርስቲያን በሎስ አንጀለስ

የነገረ መለኮትና የሥነ ጽሑፍ አርትዖቱን ሥራ የከወኑት:—

- ወንድም አማረ መስፍን (አራዳ ጊዮርጊስ፤ ኢትዮጵያ)
- መጋቢ ዮሐንስ መሐመድ (ፌር ፋክስ፤ ቨርጂኒያ)

ሙግቶቼን ሚዛናዊ በሆነ መልክ እንዳደራጅ ያበረታቱኝ:—

- ወንድም ምኒልክ አስፋው (ፎርትዎርዝ፤ ዳላስ)
- ወንድም ዘሪሁን ጎይሉ (ሻርሌት፤ ኖርዝ ካሮላይና)

መጽሐፉን ጊዜ ሰጥተው በማንበብ፣ አስተያየታቸው በዚህ መጽሐፍ ላይ እንዲወጣ የፈቀዱልኝ:—

- መጋቢ ጻድቁ አብዶ (አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ)
- ዶክተር ንጉሤ ተፈራ (አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ)
- ጋሻ ሰሎሞን ከበደ (ስሚርና፤ ጆርጂያ)
- መጋቢ ዶክተር ጎይሉ ቸርነት (ሎስ አንጀለስ፤ ካሊፎርኒያ)
- መጋቢ ዮሴፍ መኮንን (ሲልቨር ስፕሪንግ፤ ሜሪላንድ)
- ወንድም ቴዎድሮስ በየነ (አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ)

የሆህያት ግድፈትንና ስሕተትን የሰቀሙት:—

- ዶክተር በቀስ ብርሃኑ (ሞንትጎመሪ ቪሌጅ፤ ሜሪላንድ)
- ወንድም አፈወርቅ ካራ (ሽሮ ሜዳ፤ አዲስ አበባ)
- እኅት ጸባኦት ሰሎሞን (ስሚርና፤ ጆርጂያ)
- ዶክተር ገዛኸኝ በቀስ (ቦን፤ ጀርመን)

የመጽሐፉን ሽፋን ያሳመረው:—

- ወንድም ሐዋርያው ጴጥሮስ (አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ)

ስባተሉ ወገኖች መጽሐፉን በማንበብ በድምፅ የቀረጸው:—

- ወንድም ነጋ ፈለቀ (አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ)

የሚያበረታቱኝና ሁል ጊዜ በጸሎት ጌታ ፊት የሚያቀርቡኝ ብዙ ናቸው። የጥቂቶቹ ስም እነሆ፦—

- እኅት ተናኜ ጥላሁን (ሸካጎ፣ ኢልኖይ)
- ወንድም ወንድወሰን ባሕሩ (አታዋ፣ ካናዳ)
- መጋቢ ታምራት በዳኔ (ሮቸስተር፣ ኒው ዮርክ)
- ዶክተር ዮሴፍ መንግሥቱ (ሰንደን፣ እንግሊዝ)
- ወንድም ግዮን ደሴ (አክላንድ፣ ካሊፎርኒያ)
- ጋሼ በዛብህ ወርቅነህ (ሲልቨር ስፕሪንግ፣ ሜሪላንድ)
- ወንድም ቴዎድሮስ በሻ (አርሊንግተን፣ ቨርጅኒያ)
- ወንድም ንዋይ ጸጋዬ (ኮልፌ፣ አዲስ አበባ)
- እኅት አስቴር ፍቅረ ማርያም (ኮልፌ፣ አዲስ አበባ)
- ወንድም ማርቆስ ታምራት (ሬስተን፣ ቨርጅኒያ)
- ወንድም ወሰኑ ዳርጌ (ሄርደን፣ ቨርጅኒያ)
- መጋቢ ይሄይስ ሽፈራው (ደስስ፣ ቨርጅኒያ)
- ዶክተር ግርማ በቀሰ (ቶሮንቶ፣ ካናዳ)
- ወንድም መንግሥቱ ታምሬ (ኦንሌ፣ ሜሪላንድ)
- ወንድም ኤርምያስ ወሰኑ (ሲልቨር ስፕሪንግ፣ ሜሪላንድ)
- ዶክተር አሸናፊ ማርዬ (አትላንታ፣ ጆርጂያ)
- ጋሼ ደሻቸው መኖር (አትላንታ፣ ጆርጂያ)
- ወንድም ደስታ ደምሌ (ሳን ሆዜ፣ ካሊፎርኒያ)
- ዶክተር ወይታ ወዛ (አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ)
- ወንድም ስሎሞን አጅጉ (አትላንታ፣ ጆርጂያ)
- መጋቢ መስፍን ታደሰ (አትላንታ፣ ጆርጂያ)
- መጋቢ ተስፋዬ ጎይሌ (አርሊንግተን፣ ቨርጅኒያ)
- መጋቢ ጣዕመ ደስታ (ዴንቨር፣ ኮሎራዶ)
- ወንድም መስፍን ጎይሌ (አትላንታ፣ ጆርጂያ)
- ወንድም ዮናስ ደመወዝ (ዴንቨር፣ ኮሎራዶ)
- መጋቢ ኤርምያስ አማኑኤል (ዴንቨር፣ ኮሎራዶ)
- መጋቢ አንዳሻው ከልክሌ (ዴንቨር፣ ኮሎራዶ)
- ወንድም ናጆ ተሰማ (ቪይስተን፣ ቴክሳስ)
- ወንድም ጌታሁን መሳይ (ግራንድ ራፒድስ፣ ሚሽገን)
- እኅት ዓለም ፀሓይ ፍሬሕይወት (ግራንድ ራፒድስ፣ ሚሽገን)
- ዶክተር ጥበበ አሸቱ (አናርበር፣ ሚሽገን)
- እኅት ዮሚ አማ (ዴንቨር፣ ኮሎራዶ)
- እኅት ሩት ይልማ ብርሃኑ (ዴንቨር፣ ኮሎራዶ)
- እኅት ሸዋ ዳዲ (ግራንድ ራፒድስ፣ ሚሽገን)
- ወንድም ሳሙኤል ገብረ ሚካኤል (ዴንቨር፣ ኮሎራዶ)
- ወንድም ዘላለም መንግሥቱ (ላስቬጋስ፣ ኔቫዳ)
- ወንድም ዱራሳ መርጋ (ግራንድ ራፒድስ፣ ሚሽገን)
- ወንድም እዮስያስ አሸናፊ (ትሮይ፣ ኒው ዮርክ)
- ወንድም ጴጥሮስ ክፈተው (ግራንድ ራፒድስ፣ ሚሺገን)
- ወንድም ቶኒ መሓሪ (ግራንድ ራፒድስ፣ ሚሽገን)
- ዶክተር ዓለሙ ፊጤ (ቢልቪል፣ ሚሽገን)
- መጋቢ ዳኜ ቱሉ (አስተን፣ ቴክሳስ)
- ዶክተር ወንድአፈራሁ አድነው (መከኒላ፣ አዲስ አበባ)
- ወንድም አበጀ በላይ (ጋርላንድ፣ ቴክሳስ)
- ወንድም ክፍሌ ዐቢይ (ዳላስ፣ ቴክሳስ)
- ወንድም ጌትነት ዓለም (ኖርዝ ሾር፣ ዋሽንግተን)
- ዶክተር ምስግና ፍሥሓ (መከኒላ፣ አዲስ አበባ)
- አትላንታ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ወንድሞችና እኅቶች
- የቤሪያ ቴሌ ኮንፍራንስ አገልጋዮች

በዐቅብተ እምነት አገልግሎት አብረውኝ ለተጠመዱ የተሰፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር ባልንጀሮቼና ባልደረቦቼ፦—

- ቄስ ሙሉጌታ ታደሰ (ዓለም ባንክ፣ ኢትዮጵያ)
- ወንድም አፈወርቅ ካራ (ሽሮ ሜዳ፣ ኢትዮጵያ)
- ወንድም መኮንን አዳሙ (ኮልፌ፣ ኢትዮጵያ)
- ወንድም ናሆም ዳዊት (መከኒላ፣ አዲስ አበባ)
- ወንድም አንተነህ ደምሌ (አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ)
- ወንድም ጎይሉ በቀሰ (ሽሮ ሜዳ፣ ኢትዮጵያ)
- ወንድም አማረ መስፍን (አራዳ ጊዮርጊስ፣ ኢትዮጵያ)

ጌታ ይባርካችሁ!

ክብር ሁሉ ለእግዚአብሔር ይሁን!

"A wretched poor and helpless worm on thy kind arms I fall"

ተስፋዬ ሮበሌ

ሶጋንቪል፣ ጆርጂያ

ጠቦን ጥር 2018 ዓ.ም

እንደ ኮርኮሮሰውያኑ የክመን ቀመር

መቅድም

ደር ድንበርና ትልም



የመጽሐፉ ቀዳማይ ተደራስያን፣ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ክርስቲያኖች ናቸው። ነገር ግን ለልበ ሰፊ ካቶሊካውያንም ሆነ ኦርቶዶክሳውያን የሚሆን እርባና አይጠፋውም። መጽሐፉ ረቂቅና ውስብስብ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የሚተች ባይሆንም እንኳ፣ በአስተምህሮ ጉዳይ ላይ ሒስ የሚሰነዝር የዐቅብተ እምነት መጽሐፍ መሆኑ፣ ባተሌ (ሥራ ብዙ) አንባቢዎች የተፈለገው ያህል ላይጠቀሙበት ይችላሉ። በርጋታና በማስተዋል ከተነበበ፣ ቡቲያይ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን በውይይት መልክ ከተጠና፣ በጭብጡ

ላይም ሆነ፣ ኮታ ገጠም በሆኑ ርእሰ ጉዳዮች ላይ፣ “ችግር የሚፈታ ባለንጣ ‘ሚረታ” ትንተና የሚገኝበት ይመስለኛል[2]።

አንዳንድ ወገኖች መጽሐፉ ሊያካትታቸው የሚገቡ ሁነኛ ጉዳዮችን አላካተተም፣ በተቃራኒው መካተት የማያስፈልጋቸውን ርእስ ጉዳዮች ይዟል የሚል፣ ወቀሳ አዘል አስተያየት ሰጥተዋል። ሌሎች ደግሞ የቀረቡት ሙግቶች ሒሳዊ ጉልበታቸውና የትንታኔ ምጥቀታቸው በተፈለገው መጠን “አልተፋፋመም” ባይ ናቸው። አነዚህ አስተያየቶች እንደየሰዉ አተያይ የሚወለኑ አንጻራዊ (ግላዊ) ምልከታዎች ይመስሉኛል። አንዳንዱ፣ “አጥጋቢ” ነው የሚለውን ጉዳይ ሌላው ሰው፣ “ለረሀብ ማስታገሻ” አንኳ አይበቃም ይላል። አንዱ፣ “ሰፊ ቦታ” ተሰጥቶታል የሚለውን ጉዳይ፣ ሌላው “ጠባብ” ነው ሊል ይችላል። አንዳንዶች፣ “ጥራዝ ነጠቅ” የሚሉትን ሙግት ሌሎች “ጥራዝ ጠለቅ” ሊሉት ይችላሉ። አንዷ እኅት፣ “ጠንካራ” የምትለውን ሌላዋ አኅት፣ “ደካማ” ልትለው ትችላለች። እነዚህ ገለጻዎች ማንጻሪያ የሚሆን ነባራዊ ማገናዘቢያ ከልተበጀላቸው በቀር፣ በራሳቸው አንጻራዊ ገለጻዎች ናቸው።

አኔ ይህን መጽሐፍ ለማዘጋጀት ስወጥን፣ ዐላማ ያደረግሁት፣ “ዘመነኞቹ አባይ ነባዮች ተሳስተዋል የምልበት ዐቢይ ምክንያት ምንድን ነው?”፣ “ይህንን ችግር ነባራዊ በመሆነ መንገድ ማለትም ቅዱሳት መጻሕፍትን ማገናዘቢያ ባደረገ መልኩ ምላሽ መሰጠት አንዴት ይቻላል?”፣ “ችግሩ ትልቅ አደጋ ሳያስከትል እንዴት እልባት ይበጅለት?”፣ “ቤተ ክርስቲያን አባሎችዋን ‘ከተጋረጠው አደጋ ከተወረወረው ቀጋ’ አንዴት ትጠብቅ?” የሚሉትን ወሳኝ መጠይቆች መመለስን ነው[3]። በዚህ አንጻር ሊታይ መጽሐፉ የሚሞግትባቸው ጭብጦች፣ አግባብነት ያላቸው ይመስሉኛል። ይህ ማለት ግን፣ መካተት የነበረባቸው ርእሰ ጉዳዮች ሁሉ ተካተዋል ማለቴ እንዳልሆነ ግለጽ ሊሆን ይገባዋል። አኔ የታዩኝ በዚህ መጽሐፍ የተካተቱት ነጥቦች ናቸው። ሌሎች ወገኖች ከዚህ ጋር ተዛማጅ የሆኑ፣ ነገር ግን የተለዩ ርእሶች ላይ ጠቃሚ ሥራ ሊያዘጋጁ እንደሚችሉ አገምታለሁ። ችግሩ ፈርጀ ብዙ ስለሆነ፣ መፍትሔውም ከብዙ አንጻር ተሰናድቶ አንዲቀርብ የግድ ይላል። ስለዚህ ይህ መጽሐፍ፣ “አንድ ለእናቱ” ቢጤ አይደለም፣ ሊሆንም አይችልም።

የትንታኔ ደረጃውን በተመለከተ፣ ተሳቢ ላደርግኋቸው ተደራስያን ይህ አቀራረብ ሚዛናዊ ነው የሚል እምነት አለኝ። ወደ ፊት ወገኖች በሚሰጡኝ አስተያየት፣ አቀራረቡን ለተደራስያኑ ተስማሚ እንዲሆን ማድረግ ይቻላል፣ ተጨማሪ ርእሰ ጉዳዮችንም ስማካተት ሙከራ ይደረጋል።

አንድ ጠያቂ፣ “አንተ ያለአባይ ነባይና ያለመናፍቃን ሥራም የለህ እንዴ?” ብሎኛል። መልሴ፣ “አዎ! አዎ የለኝም” ነው፣ ለአኔና “ለግብረ አበሮቼ” የአባይ ነባይና የመናፍቅ ጉዳይ፣ ከሙሉ ሥራ በላይ ነው። ይህ ምን ማለት እንደ ሆነ፣ በዚህ መጽሐፍ የተወሰነ መልስ ተሰጥቶታል። እንግዲያው መጠየቅ የሚወዱ ሰዎች፣ ለመልሱም መትጋት አለባቸውና—በጥሙና ይነቡ!

ሌላ አስተያየት ሰጪ፣ “በአባይ ነባይ ጀምረህ መናፍቃንንም ከአባይ ነባዮች ባላነሰ ምናልባትም በበለጠ መልኩ ቦታ ሰጥተኻቸዋል” የሚል አሳብ ሰንዝሯል። እውነት ነው! ይህ ታዲያ በምንም ዐይነት መልኩ የዐላማ መሳከር ላይሆን፣ የተወራራሽነት ጥያቄ ነው። ምክንያቱም በአባይ ነባዮችና በመናፍቃን መካከል ያለው ልዩነት፣ የመጠን እንጂ የይዘት አይደለም። ሁሉም መናፍቃን የአባይ ነባይነት ጠባይ አላቸው፤ አባይ ነባይ ሁሉ ግን መናፍቅ አይደለም። ስለዚህ በአንዱ ላይ የሚሰነዘረው ትችት፣ በመጠን ካልሆነ በቀር በይዘት አንድ ነው፤ የአንዱም ምላሽ ለሌላው መልስ ይሆናል—መቶ በመቶ። አንዱን የምንከላከልበት ዘዴ ሌላውንም

---

[2] የጥናት መምሪያውን የሚፈልጉ ወገኖች፣ ከጸሓፊው በነጻ ማግኘት ይችላሉ።

[3] አንዳንድ ወንድሞች አባይ ነባዮቹ ቡተሰያየ ጊዜ ያስተላለፉቸውን የድምፅ-ከምስል (የቪዲዮ) ስብከትና ትምህርት በመስማት፣ በአሰተምህሯቸው ላይ ሒስ እንድሰነዘር አሳብ ቀርበዋል። ያን ማድረጉ ስለተት ባይሆንም፣ ችግሩን ከሥር መሠረቱ የሚፈታው አካሄድ አልመሰለኝም። ከዚህ ይልቅ አባይ ነባዮቹ ተሳቢ የሚያደርጓቸውንና አዘውትረው የሚያነሧቸውን ስሑት ትምህርቶችን ለቅሞ በማውጣት፣ እነዚህ ትምህርቶች ለምን ስሕተት እንደሚሆኑ መሞገት የተሻለ አካሄድ ነው የሚል እምነት አለኝ።

የምንከላከልበት ዘዴ ነው። ለዚህ ነው ይህ መጽሐፍ ሁለቱንም አቀላቅሎ የሚመታው።

አንድ ወዳጄ፣ በመጽሐፉ መጨረሻ ላይ፣ "የማጠቃለያ አሳብና ምክር ቢቀርብ ጥሩ ነው" የሚል አስተያየት ሰጥቶኛል። ይህ አስተያየት የቀረበው፣ መጽሐፉ ወደ ማተሚያ ቤት ሊላክ ከሁለት ጀንበር ያነስ ጊዜ ሲቀረው ነው። ምናባቴ ላድርግ ጥሩ አስተያየት ቢሆንም፣ በጊዜ ጥበት ላስተናግደው አልተቻለኝም። አግዚአብሔር ፍቃዱ ሆኖ መጽሐፉ ለሁለተኛ ጊዜ የሚታተም ከሆነ፣ ይህን እንዲሁም ሌሎች መሰል አስተያየቶችን ለመመለስ ሙከራ አደርጋለሁ።

አንዳንድ ወገኖች፣ "የጎዳማ መዘክሩ በየቦታው ላይ መነስነሱ፣ ፍስቶ አሳቡን ያደነቃቅፋል" የሚል እምነት አላቸው። ሌሎች ደግሞ ከዚህ ጋር በሚቃረን መልኩ፣ ሁሉን ነገር በዐቢይ ጽሑፉ ላይ ማካተት ዝርዝር መረጃ የማይፈልጉ ሰዎችን ያሰለቻል፤ ስለዚህ ዝርዝሩን ለትጉ አንባብያን ወደ ጎዳማ መዘክሩ ወስዶ፣ ቦቢይ መግቱን በዋናው ክፍል ላይ ብቻ መወሰን ተገቢ ነው ይላሉ። እኔ የሁለተኛው አካሄድ ተመችቶኛል። ስለዚህም መጽሐፉን ያደራጀሁት በዚያ መልክ ነው—ሌላም ጊዜ ይህንኑ አካሄድ ነው የምከተለው። አብዛኛው ሰው ምን ይላል የሚለው ግን፣ መጽሐፉ ለንባብ ቀርቦ በሂደት የሚጣራ ጉዳይ ይሆናል።

መጽሐፉ በሚሞግትበት ርእሰ ጉዳይ ላይ ሁሉ፣ ሰው ሁሉ መቶ በመቶ ይስማማል የሚል እምነት የለኝም—ቢስማማ ግን አሰየው ነው። ነገር ግን የምሞግትለት አስተምህሮ ጭብጥ፣ ክነባሩ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት አስተምህሮ ጋር ሙሉ ለሙሉ ግጣም መሆኑን መግለጽ አወዳለሁ።

በመጽሐፉ ላይ ጉልኅ የሆነ የአቀራረብም ሆነ የአስተምህሮ ስሕተት ቢገኝ ወይም ሌላ ቦይነት ችግር ቢስተዋል፣ የስሕተቱ ሙሉ ተወቃሽ አኔው ጸሓፊው እንጂ፣ ተሰፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር፣ አርታኢያኑ፣ የገንዘብ ዕገዛ ያደረጉ አብያተ ክርስቲያናት፣ ግለሰቦች ወይም ደግሞ አስተያየት ሰጪዎቹ አይደሉም። በተለያየ ምክንያት ያላካተትኋቸው፣ ያሳሳትኋቸው፣ ያገደፍኋቸው አንዲሁም ያልተቀበልኋቸው አስተያየቶች ይኖራሉና።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር!

ከአንባቢዎቹ
የመጽሐፉ መታሰቢያነት



ከውነተኛውን ወንጌል በመስበክና በመኖር የረጅም ጊዜ አብነቶች (በዕውቀቴና በዐቅራቢያዬ ከሚገኙቱ መካከል)፦—

ጋሼ ማሞ ገብረ መስቀል
ከኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን
ጋሼ መኩ ሻመና (መጋቢ)
ከኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን
ጋሼ ሰሎሞን ከበደ
ከኢትዮጵያ መሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን
ጋሼ ፈቃዱ ተሰማ (መጋቢ)
ከጲሶን ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን
ጋሼ አታላይ ዓለም (ፕሮፌሰር)
ከኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን
ጋሼ ንጉሤ ተፈራ (ዶክተር)
ከኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን
ጋሼ ደምሴ ማደ
ከኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን
ጋሼ ተስፋ ወርቅነህ (መጋቢ/ዶክተር)
የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ጎባረት ቤተ ክርስቲያን ዊይስተን ቴክሳስ
ጋሼ መለሰ ወጉ (ዶክተር)

ማውጫ



ቃለ አራርሆ—— *1*

እነሆ ልመናዬ፡— ለርቱዕ ነቢይ፣ ለአባይ ነባይ!

ቃለ አንክሮ!—— *5*

በዳራ የመጽሐፉ መክፈቻ የሆነውን ይህን ክፍል በጥሙና ያንብቡ

አንተ ሊቅ...ተጠየቅ!

ክፍል አንድ—— *33*

የመሠረታዊ ቃላት ፍካሬና እማሬ

ክፍል ሁለት—— 53

ስለ አባይ ነባዮችና ስለ መናፍቃን መነጋገር ለምን አስፈለገ?

ክፍል ሦስት—— 63

"በሌላው ላይ ልትፈርድ አንተ ማን ነህ?"

ክፍል አራት—— 77

"አምላክ በቀባው ላይ እጅህን አታንሣ!"

ክፍል አምስት—— 95

"ፍጹም የሆነ እውነት እስከሌለ ድረስ፣ ፍጹም የሆነ ነገረ መለኮት ሊኖር አይችልም!"

ክፍል ስድስት—— 115

ነቢያትና ነቢይነት በቅዱሳት መጻሕፍት

ክፍል ስባት—— 149

መርገም ከምዝላት፣ ክእንጅላት...ይተላለፋልን?

ክፍል ስምንት—— 201

ክርስቲያን አጋንንት ይገቡበታልን?

ክፍል ዘጠኝ—— 223

በአባይ ነባዮችና በመናፍቃን ተዘወትረው የሚታዩ ባሕርያት የትኞቹ ናቸው?

ክፍል ዐሥር—— 263

"በኢየሱስ ክርስቶስ ስም" ማለት ምን ማለት ነው?

ክፍል ዐሥራ አንድ—— 291

የአባይ ነባዮችና የመናፍቃን መበራከት ምስጢር ምንድን ነው?

ክፍል ዐሥራ ሁለት—— *303*

የአባይ ነባዮችንና የመናፍቃንን ዕድገት ለመቀነስ
ልንወስዳቸው የሚገቡ ርምጃዎች የትኞቹ ናቸው?

ክፍል ዐሥራ ሦስት—— *313*

ጸረ-ተምህሮታዊነት፣ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን
አብያተ ክርስቲያናት አብሾ፣ እርሾና ጌሾ

ኪነበቡ የሚገባቸው መጻሕፍት—— *331*

ቃለ አራርሆ

እነሆ ልመናዬ:— ***ለርቱዕ ነቢይ፣ ለአባይ ነባይ!***



"ነ**ቢይ**" የግእዝ ቃል ሲሆን፣ የአማርኛ እቻው "ነባይ" ነው! አማርኛ የራሱን ቃል ገድሎ፣ የሴማዊ ጐረቤቱን የግእዝን ቃል በቋሚነት ለምን እየተጠቀመ እንደሚገኝ፣ በውል የማውቀው አንዳችም ነገር የለኝም። አማርኛ ግእዝን በመኳያነት (ማለትም እንደ ዙል፣ እንደ ሽቱ፣ እንደ እንሾሽላ) ከመጠቀምም ባሻገር፣ ለሙያዊ ቃላት ቅመራ፣ በዋና ግብዐትነት እየተጠቀምንበት እንደምንገኝ ግን ይታወቃል።

አማርኛ ነባይን አግድፎ/ጥሎ፣ ነቢይን ያስነሣበት አግባብ ምን እንደ ሆነ፣ ቢያንስ ዛሬ በቊርጥ መናገር ባልችልም! በቊርጥ ማድረግ የምችለው ነገር ግን ይኖረኛል፤ ይኸውም ቃሉን ለዚህ መጽሐፍ ርእስ አድርጎ በመጠቀም፣ ለሚች ቃል ትንሣኤ ሕይወት መስጠት!

“አባይ” ማለት ዋሸ ማለት ነው! ስለዚህ “አበየ” ማለት “ዋሸ፣ ቀላመደ፣ ጠማማ ነገር ቀና ነው ብሎ መለከረ፣ ቀጠፈ” ማለት ነው። በሌላ አማራጭ ትርጕመ “አበየ” ማለት፣ “እንቢ” ወይም “አሻፈረኝ አለ” ማለትም ይሆናል። “አብዮት” የሚለው ቃል የመነጨው፣ ከዚህ ዘር አንቀጽ ነው። “አብዮተኛ” ማለት አሻፈረኝ ባይ ማለት ነው (በፖለቲካ ጭቆና ላይ ብቻ ሳይሆን፣ በሃይማኖት ኑፋቄና በሐራጥቃዎች[1] ላይ “ዘራፍ!” የሚል ሁሉ፣ አብዮተኛ የሚለው ቃል የሚወክለው ይመስለኛል። በዚህ አግባብ ሲታይ እኔም ሆንሁ ሌሎች ቀዋምያነ ቤተ ክርስቲያን/ዐቅብተ እምነቶች፣ አብዮተኛ መባላችን አግባብ ይሆናል። እንደ ትልቅ ክብርም እንመለከተዋለን! ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ትስብእት/ለው በመሆን አይሞቱ ሞት የሞተበትን ይህን ክቡር እንዲሁም ዘላለማዊ ዐላማ፣ በንቃት ከመጠበቅና ከማስጠበቅ በላይ፣ ስብዐዊ ፍጡር ምን ሌላ ክብር ሊኖረው ይችላል?)።

ከቋንቋ ባሕርይ የምንማረው፣ ቃላት ስምምነትን መሠረት ማድረጋቸውን ነው። ዐልጋን ዐልጋ ብሎ ለመለየም፣ በሬን በሬ ብሎ

[1] ሐራጥቃ ማለት ሐሰተኛ ማለት ነው። ኑፋቄ ከሚለው ቃል ጋር በተለዋዋጭነት ጥቅም ላይ ይውላል። አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ ገጽ 462 ይመለከቷል።

ለመጥራት፣ አንዳችም ምክንዮአዊ[2] ምክንያት የለንም። በስያሜው ላይ ስንስማማ ግን ተግባዐት ይፈጠራል። ቋንቋ መግባቢያ ነው የሚባለው፣ በዚህ ምክንያት ነው። የቋንቋ አስፈላጊነት አሳብን በትክክል ማሻገሩ አንዲሁም ምስል የመከሠት ምትሐታዊ ችሎታው ነው[3]።

እንግዲህ እኔ በዚህ አግባብ ተደራሲዎቼን አንድ ሁነኛ ጥያቄ መጠየቅ እፈልጋለሁ። በትልቅ አክብሮት ትልቅ ልመና ማቅረብ እሻለሁ። ይኸውም “ነባይ” የሚለውን የአማርኛ ቃል፣ በብዙ መልኩ በክርስቶስ የተጉናጸፍንውን መልካም ስምና ዘላለማዊ ተልኣኮ ያጕደፉብንን አባዮች/ዋሾዎች፣ ከስማቸው በፊት ያኖሩትን (ማለትም “ነቢይ”) የሚለውን የማዕረግ ስም በመጉረድ/በመቀረጥ፣ “ነባይ”

[2] “አመክነየ” ምክንያት ሰጠ፣ ምክንያት አቀረበ ከሚለው የግእዝ ቃል የመጣ ነው። “ምክንዮአዊ” ወይም “አመክንዮአዊ” ማለት፣ ምክንያትን ማቅረብ በእንግሊዝኛው “reason” የሚለውን ቃል የሚተካ ሲሆን፣ ሥነ አመክንዮ ደግሞ የምክንያትን ባሕርዮትና ሕግጋት የሚያጠናውን የሳይንስ ዘርፍ (በእንግሊዝኛው logic) የሚያመለክት ነው።

[3] በዚህ አግባብ ሲታይ ቃላት ብቻ ሳይሆኑ፣ ሰዋሰውም ነባራዊ (objective) መሠረት ሊኖረው የሚችል አይመስለኝም። በተለያዩ ምክንያቶች የአንድ ቃል ትርጕም እየተቀየረ ወይም እየሞተ እንደሚሄደው ሁሉ (“ቋንቋ ይወለዳል፣ ያድጋል፣ ይሞታል” የሚባለውን አባባል ልብ ይሏል)፣ ሰዋሰዋዊ ሕግጋትም በዚሁ መልክ እየተቀየሩ፣ ሕገ ወጥ አነጋገሮች እየተበራከቱ፣ ሕገወጡቹ ወደ ሕጋዊነት እየተቀየሩ ይሄዳሉ። ስለዋሰው ሕግጋት፣ “እሞታለው” ማለት ስሕተት የሚሆነው፣ በዚህ ምክንያት ይመስለኛል—ከሰውነው ጋር እየተሰወጠ መሄድ የግድ ነው። “ቋንቋ ሰምምነት ነው” የሚለው ጉዳይ እጅግ በርካታ እንድምታዎች የሚኖረው ለዚህ ነው። የሰዋሰው ሕግጋትን ባለማወቅ ለሚፈጠረው የተግባቦት ችግር፣ “ሰዋሰው የውል ሰምምነት ነው” የሚለው አነሄድ ሰበብ መሆን አይችልም። ስለዚህ ሰዋሰውን ላለማክበር ሰንካሳ ተገን እንዳነደረገው እንዘንጥት።

የሚለው ቃል አሉታዊ እንድምታ *(derogative connotation)* ይዞ እንዲወከላቸው ብናደርግ[4]።

ይህ አካሄድ ያስፈለገበት ጣምራ ምክንያት አለ፦ ***አንደኛ***፣ ቤተ ክርስቲያን የመሰከረችላቸውን፣ በምግባራቸውም ሆነ በአስተምህሮአቸው ንጽሕና የታወቁትን እውነተኛ ነቢያት ከአጥፊዎቹ ለመለየት ይጠቅማል። አልሚውም አጥፊውም በአንድ ስም መጠራት በጭራሽ የለባቸውም። ***ሁለተኛ***፣ አጥፊዎቹ በቤተ ክርስቲያን ላይ እያመጡ ያሉትን ትልቅ ኪሳራ ግምት ውስጥ በማስገባት፣ የምግባራቸውን አኩይነት የአስተምህሮአቸውን ስሑትነት በይፋ ለመኮነን ይበጃል። እነርሱ ለማጥፋት ከደፈሩ፣ እኛ እነርሱን በትክክል የሚወክል ስም ዳቦ ቁርሶ ለማውጣት፣ ፈራ ተባ ማለት በፍጹም የለብንም። እነርሱ ለመሳሳት ከደፈሩ፣ እኛ ስሕተታቸውን በትክክል የሚጠቅስ ስያሜ ለመቀመር፣ የሚያለጋን አንዳችም ምክንያት ሊኖር አይችልም። እንግዲያው ቀና አስተምህሮና ንጹሕ ሕይወት ያላቸውን "ነቢያት" እንላለን፣ ስሑት አስተምህሮና አግድም ዐደግ ሕይወት የሚከተሉትን ደግሞ፣ "ነባይ" ብለን እንጠራቸዋለን! አንግዲያው ልመናዬ ይኸው ነው። ***ለርቱዕ***[5] ***ነቢይ***፣ ***ለአባይ ነባይ!***

[4] "ቋንቋ ስምምነት ነው" የሚለውን ፍልስፍና የተከተለ አስተያየት ነው።

[5] "ርቱዕ" ማለት ቀጥተኛ፣ ትክክል፣ ንጹሕ፣ እውነተኛ...ማለት ነው።

ቃለ አንክሮ!

ዐደራ የመጽሐፉ መክፈቻ የሆነውን ጽሀን ክፍል በሞሙና ያንብቡ

አንተ ኪቅ...ተጠየቅ!



በአባይ ጠንቂይ አባዜ የተለከፈን ለው፣ ከሱሱ መገላገል እጅግ ሲበዛ አስቸጋሪ ነው። አንድ ዘመዴ አባይ ጠንቂይ ዘንድ መሄድ ትወዳለች። በዚህም ምክንያት እናቶች ለቡና ሲለበስቡ፣ ስሟን እየጠሩ፣ "አዬዬ...ሉስ ሆኖባታል! ካዳሚ ከመሆን ባሻገር አንዳችም ተስፋ የላት" ይላሉ። አባይ ጠንቂይ ብቻ ሳይሆን፣ አባይ ነባያም የለመደ ለው ቦመሉ ቶሉ አይለቀውም።

"ዐዋቂ"[6] ዘንድ መሄድ ሉስ እንደ ሆነባት ዘመዴ፣ "ተስፋ የለውም!" ባይባል እንኳ፣ እንዲህ ዐይነቱን ጠባይ ማረቅ[7] ሲበዛ አድካሚ ነው፣ ቶሎ መሳቀቅ አይችልም።

የሠላሳ ሁለት ዓመት የክርስትና ሕይወቴ በግልጽ ያስተማረኝ ነገር ቢኖር፣ በመናፍቃን ትምህርት የተተበተበን ሰው እንዲሁም በመፍቀሬ ነባይ የተነደፈን ሰው፣ ከልማዱ መመለስ እንዲሁም ልቡን ወደ ቃለ እግዚአብሔር ማቅናት፣ የረጅም ጊዜ ኖሎታዊ[8]/ምጋቤያዊ ጥረት ይፈልጋል። ዛሬ በርካታ ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱሳቸውንም ሆነ መንፈሳዊ መጻሕፍትን ለማንበብ የሚቸገሩት፣ በዚህ ዐይነቱ ችግር ውስጥ ስለ ወደቁ ነው። ነባይ ዘንድ ሄዳ፣ "ጌታ እንዲህ ይልሻል" የምትባልን እኅት፣ "የቆሮንቶስን መጽሐፍ አጥኚ፣ ሥነ ትርጓሜን ተማሪ" ማለት ሲበዛ አስቸጋሪ ነው። "አምላክ ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ምን አላቸው፣ ይህስ ጉዳይ ከእኔ ነባራዊ ሁኔታ ጋር እንዴት ይመሳከራል" ከሚለው ብርቱ አሳብ ጋር ለምን ትታገላለች? እንደ አሸን ከፈሉ ነባዮች መኻል አንዱ ዘንድ ብር ብላ ብትሄድ በእድራሻዋ፣ "መልእክት ተክ" ያደርጉሳታል። እነርሱ ዘንድ ሄዶ "ባዶ እጁን" የተመለሰ ማን ነው? በጻጉሯ ቍጥር እንደሚያሸክሚት አያጠራጥርም። ስለዚህ ቅዱሳት መጻሕፍትን እያነበቡና አያስነበቡ ከመኖር፣ "አምላክ በዚህ ደቂቃና ሰዓት እንዲህ እያለሽ ነው..." የሚለው አካሄድ፣ ከብዙ አንጻር ድካምንም ሆነ ጊዜን ይቀንሳል። ይህ ጉዳይ ሰዎች መንፈሳዊ መጻሕፍትን አንዳይመረምሩ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን እንዳያጠኑ፣

[6] እናቶች አባይ ጠንቋይን "ዐዋቂ" ሲሉ ነው የሚጠሩት።

[7] አረቀ ማለት ጠባይን በምክር ቡጉግጽ...እንዲስተካከል አደረገ፣ ዕርጥበት ያለውን እንጨት በእሳት ሰብለቦ አቃና፣ ያጋደለውን የአህያ ወይም የኢጋሰስ ጭነት አስተካከለ ማለት ነው።

[8] ኖለወ (ጠበኰ፣ አስማራ)፣ ኖላዊ (እረኛ)፣ ኖሎት (እረኞች)።

በብዙ መልኩ ጋሬጣ እንደ ሆነባቸው ስንቶች አስተውለነው[9] ይሆን[10]?

ለዚህም ነው፣ "ከይሖዋ ምስክሮች" ወይም "ከሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" ለምች ጋር አንድ ሳምንት የቆየ ሰው፣ ረጅም ዓመት በቤተ ክርስቲያን ያስቈጠረውን አማኝ፣ በአንድ ደቂቃ ውስጥ አምነቱን በማስጣል ሙልጩን የሚያወጣው (ካልሆነ ክፉኛ አንዲደናገረው)። በአገር ቤት የተሠሩ ጥናቶች አንደሚናገሩት፣ ከመቼውም የታሪክ ጊዜ ይልቅ በርካታ ሰዎች ወደ፣ "ይሖዋ ምስክሮችና" ወደ "ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" እየጐረፉ ነው[11]። ለዚህ ዐቢይ ምክንያቱ ደግሞ፣ ሰዎች ስመሠረተ እምነታቸውም ሆነ ስታሰ እግዚአብሔር፣ ፍጹም መኃይማን የመሆናቸው ሐቅ ነው።

አምላክ ነቢያትን ለቤተ ክርስቲያን እንደሚሰጥ፣ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ ማስተማሩ አሙን ነው። ዛሬ ነቢያት የሉም ወይም አምሳክ ለቤተ ክርስቲያን ነቢያትን አልሰጠም ማለት የሚቻል አይመስለኝም። አኔም ሆንሁ እኔ የማውቃቸው የነገረ መለኮት ለምች፣ "ዛሬ የተአምራት ስጦታዎች የሉም" የሚል አንዳችም አምነት የለንም[12]። በመሠረቱ ተአምራዊ ስጦታዎች ዛሬ በቤተ ክርስቲያን አይሠሩም የሚል፣ ኢትዮጵያዊ የነገረ መለኮት ለው መኖሩን፣ በእውነቱ እኔ በግሌ አሳውቅም። የሚያሳዝነው ግን፣ "ወደ ቃሉ እንመለስ" የምንል ለምች፣ የጸጋ ስጦታዎችን አንደምንቃወም፣

[9] የአማርኛ ለወለው ዐዋቂዎች፣ "አስተውለነው" አይባልም፣ "አስተውለንው" እንጂ ይላሉ (የሰዋስው መግታቸው ምን ያህል አሳማኝ ነው የሚለው የሰዋስው መጻሕፍት ርእስ ነው)። ይህ መጽሐፍ ይህን አካሄድ ተከትሏል። ለዚህ እንደ ጸሓፊ ስሕተት እንዳይታይ ለማለት ነው።

[10] የማንበብ ልማዳችን ምን ያህል አሳዛኝና አሳፋሪ እንደ ሆነ የሚያሳይ ጎጽጽራዊ ጥናት፣ በዚህ መጽሐፍ መጨረሻ ማለትም በክፍል ዐሥራ ሦስት ላይ ቀርቧል።

[11] ተስፋዬ ርነሌ፣ *ዐበይት መናፍቃን* (ኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን፣ 1994 ዓ.ም)።

[12] በክፍል ስድስት ላይ ለፊ ማብራሪያ ተሰጥቧል።

መንፈሳዊነት እንደማይገባን በብዙዎች ዘንድ ይታሰባል። ይህ ፍጹም አግባብነት የሌለው ክስ ነው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መጋቢዎች፣ አስተማሪዎች፣ ዲያቆናት ወዘተ እንደሚያስፈልጉ ሁሉ፣ ነቢያትም ያስፈልጋሉ የሚለው የአኔም ሆነ፣ የእብዛኞቹ የነገረ መለኮት ሰዎች አቋም ነው[13]። ስለዚህ የቅዱሳት መጻሕፍት አስተምህሮም ሆነ ሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን ይከበር የሚሉትን በዚህ መልክ ጥላሸት በመቀባት፣ ሥርዐት አልበኝነትንና የተሳሳቱ ትምህርቶችን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማስገባት ትክክል አይደለም፤ ነውርም ነው።

[13] በኢትዮጵያውያን የነገረ መለኮት ሰዎች ዘንድ ያለው ልዩነት፣ "ዛሬ ነቢያት አሉ ወይስ የሉም?" በሚለው ዙሪያ ላይሆን፣ "የነቢይነት አገልግሎት ምን ዐይነት ባሕርይ አለው?" በሚለው ነጥብ ላይ ነው። የነቢይነት ስጦታ ልክ እንደ ማስተማር፣ እንደ መስበክ፣ እንደ መጋቢነት ወዘተ ሰጦታ ነው። ከዚህም የተነሣ የተሰጠውን ግለሰብ "ነቢይ" ብሎ በማዕረግ ሰም መጥራት አግባብ ነው የሚለው አንደኛው ወገን ሲሆን፣ ሌሎቹ ደግሞ ስጦታው ለአንድ ግለሰብ የሚሰጥ ላይሆን፣ ዳግም ሰተወሰዱ ክርስቲያኖች ሁሉ "የተሰጠ" ነገር ግን እግዚአብሔር መልእክት ሲኖረው፣ ከነባኤው መኻል አንዱን ሰው በመጠቀም አሳቡን ለቤተ ክርስቲያን ይገልጻል ባሮች ናቸው (ይህ ሰው ምናልባት ዲያቆን ወይም አስተማሪ ወይም ዘማሪ ወዘተ ሊሆን ይችላል—ሳኦል ንጉሥ ሆኖ ሳለ ትንቢት ተናግሯል፣ ትንቢት መናገሩ ግን "ነቢይ" አላሰኘውም፣ ስለዚህ ትንቢት የተናገረ ሁሉ ነቢይ አይደለም፤ እንዲሁም አምላክ ያሻውን ሰው ባሻው ጊዜ እየነጠቀ ያናግራል—1ሳመ. 19÷23-23)። የሁለተኛውን አካሄድ የሚከተሉ ሰዎች፣ የመግታቸው ቁጥጥ እንደሚከተሰው ነው—ዳጸጋ ስጦታዎችን፣ "እንደ ፈቀደ" የሚሰጠው እግዚአብሔር ራሱ ሆኖ ሳለ፣ ትንቢትን ግን ክርስቲያን ሁሉ እንዲሻው/እንዲፈልገው ማሳሰቢያ ተሰጥቶአል። እንዲያውም ሐዋርያው ጳውሎስ "ሁላችሁም ትንቢትን እንድትናገሩ እፈልጋለሁ" ሲል እንሰማለን። ይህ የሚያሳየን ሕዝበ ክርስቲያኑ ሁሉ፣ ይህ ጉዳይ በሕይወቱ እውን እንዲሆን ዕለት ዕለት ስጦታውን መሻት/መጸለይ ይኖርበታል ባሮች ናቸው። እንዲያውም አንዳንዶች፣ ትምህርተ ወንጌል ወይም ስብከተ ወንጌል የሚያቀርቡ አገልጋዮች፣ ጌታ መልእክታቸውን ልዩ በሆነ መልክ በመጠቀም የእያንዳንዱን ግለሰብ ሕይወት ትንቢታዊ በሆነ መንፈስ እንዲነካ፣ በዚህ መንፈስ መጸለያና ስብከታቸውን ማቅረብ አለባቸው ባሮች ናቸው።

ይህ እንዳለ ሆኖ ግን፣ በዕለት ተዕለት ኑሮ ውስጥ፣ ክርስቲያኖች በቅዱስ ቃሉ መሪነት አንጂ፣ በነቢያት ትንቢት መንቀሳቀስ የለባቸውም። ትክክለኛ ነቢያት ናቸው በሚሏቸው ሰዎች ዙሪያ መደራጀት፣ ቤተ ክርስቲያን መትከል ስሕተት ነው።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮና ቀኖና መሠረት ቤተ ክርስቲያንን ለመትከል ጽላት/ታቦት ወሳኝ ጉዳይ ነው። በሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ አንብሮተ እድ (የሲቃነ ጳጳሳቱን ሹመት) የተቀበለ ካህን በሌለበት፣ ቤተ ክርስቲያን መትከል በፍጹም አይቻልም። በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ነባር አስተምህሮ ግን፣ ዳግም የተወለዱ ለዎች ሁለትም ሦስት ሆኖው በቃሉ ዙሪያ ቢሰበሰቡ፣ እምላክ በመካከላቸው ይገኛል (ማቴ. 18÷20፤ 28÷20፤ 1ቆሮ. 5÷4)፤ በቃሉ ዙሪያ በመደራጀት ባሻቸው ቦታ ቤተ ክርስቲያንን መቄርቄር ይችላሉ። በመካከላችን የፈሉት አባይ ነባዮች ግን፣ ይህን ነባርና ቋሚ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያንን ትምህርት በማፍረስ፣ ለዎችን በራሳቸው ማንነትና አስተሳሰብ ዙሪያ እያደራጁ ነው። እኛ የአምላክን ቀጥተኛ ድምፅ እነግራችኋለን፤ ክአምላክ ጋር በቀጥታ አናነናኛችኋላን እያሉን ነው። ይህ ደግሞ ካቶሊካዊታ ቤተ ክርስቲያን ክምትለውም ይልቅ፣ ሥር የለደደው ኑፋቄ ነው። ክዚህ ባለፈም፣ "ቤተ ክርስቲያን የምትመራው በባለ ራእይ ነው" በሚለው የአስተዳደር አካሄዳቸው፣ የቤተ ክርስቲያንን ጥሪት ወደ ግል ካዝናቸው እንዲያፈልሱ፣ ጥሩ መሸለክ ፈጥሮላቸዋል። ይህ ደግሞ በአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ላይሆን፣ በየቦታው በሚተክሏቸው ድርጅቶች ሁሉ ላይ እውን እየሆነ የሚገኝ ነው።

አንዲያውም አዚም እዚያም የሚክፍቷቸውን ቤተ ክርስቲያናት፣ "ኢንተርናሽናል" (ዓለም ዐቀፍ) የሚል እንግሊዝኛ ስያሜ ሊያስገበጣቸው አየታየ ነው። ይህ ኢንተርናሽናል ቤተ ክርስቲያን የሚለው ስያሜ ትልቅ ምስጢር አንደ ተሸከመ ስንቶች

ተረድተነው ይሆን? ቤተ ክርስቲያን ዘላለማዊና ዓለም ዐቀፋዊ ተልእኮ ያላት ብትሆንም፣ የምታገለግለው ግን በአንድ አጥቢያ/ቀዬ ተወስነው የሚኖሩትን ለምች ነው። ቤተ ክርስቲያን ዓለም ዐቀፍ ተልእኮ (ማለትም በየዓለማቱ ለሚኖር ለው ሁሉ የሚሆን ታላቅ የምሥራች) አላት ማለት፣ መሪዎቿ በየዓለማቱ ላሉት ሰዎች ሁሉ ኖላውያን (መጋቢያን) ናቸው ማለት በጭራሽ አይደለም። ከሕዝቡ ጋር አየኖረ ሕዝቡን የማይመራና የሕዝቡን ኑሮ አየተጋራ ቃል አግዚአብሔር የማያስተምር ለው፣ በምን አግባብ መጋቢ ነኝ ሊል ይችላል? መጽሐፍ ቅዱስ አብያተ ክርስቲያናትን በአጥቢያ ለይሚቸው በቀዬ አደራጅታቸው የምንመለከተው በዚህ አግባብ ነው—ሮም፣ ቆሮንቶስ፣ ገላትያ፣ ኤፌሶን፣ ፊልጵስዩስ፣ ተስሎንቄ፣ ለምርኔስ፣ ጴርጋሞን፣ ትያጥሮን፣ ለርዴስ፣ ፊላድልፍያ፣ ሎዶቅያ ወዘተ። እነዚህ ሁሉ በሚገኙበት አካባቢ የሚጠሩ፣ የአካባቢውን ኗሪ የሚያገለግሉ አጥቢያዎች ናቸው።

አባይ ነባሮች በአንድ ለው ዙሪያ ፍጹም የተማከለ አስተዳደር *(Absolute centralization)* መከተላቸው፣ አጅግ ዐምባ ገነናዊ በሆነ አመራር ሕዝቡን ለጥ ለጥ አድርገው እንዲገዙ ዕድል ለጥቶአቸዋል። ይህ ፈላጭ ቈራጭ አሳሄድ የሥልጣን ተጠያቂነት እንዳይኖራቸው ማድረጉ ብቻ ሳይሆን፣ በተለያዩ ቦታዎችና በተለያዩ የዓለም ክፍሎች የሚተከሏቸው አጥቢያዎች፣ የገንዘብ ፈለጓቸው ባለራአይ ወደ ተባለው ግለሰብ እንዲያነጣጥር አድርጓል[14]።

[14] በቅርቡ የእንግሊዝ መንግሥት፣ ዴቪድ አይዴፖ *(David Oyedepo)* የተባለ አባይ ነባይ፣ ወደ እንግሊዝ አገር እንዳይገባ፣ እግር ጥሎት ቢገባ ግን በቀጥታ ከርቸሌ እንዲወረወር፣ ግለሰቡ በሌለበት ጥብቅ ዋራንት (ብያኔ) አስተላልፎበታል። ለዚህ ዋነኛው ምክንያት፣ ግለሰቡ ናይጀሪያ ሆኖ በእንግሊዝ አገር የቁረቁራቸው አጥቢያዎች፣ ገንዘባቸውን ሁሉ በግለሰቡ ካዝና ውስጥ በመክተታቸው ነው። የሚከተሉትን ድረ ገጾች ይመለከቷል፡—
http://saharareporters.com/2014/10/16/bishop-oyedepo-banned-entering-uk-over-church-corruption
http://www.nairaland.com/1954675/bishop-oyedepo-banned-uk-over
http://pointblanknews.com/pbn/exclusive/uk-banned-entry-bishop-oyedepo/

እንግዲያው ቅዱሳት መጻሕፍት የአምላክ አፈጮተ ቃል ናቸው ብለን የምናምን ለምች፣ ሕዝበ ክርስቲያኑን ወደ ቅዱስ ቃሉ የመመለስ እንዲሁም ቤተ ክርስቲያንን ከቀን ጅቦች[15] በንቃት የመጠበቅ ትልቅ ኀላፊነት ወድቆብናል። ይህ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ድርሻ ብቻ ሳይሆን፣ እያንዳንዱ ክርስቲያን ከአምላክ የተሰጠው ኀላፊነት ነው፤ እግዚአብሔር በቀጠረው ጊዜ ደግሞ "ኀላፊነትህን የት አደረስኸው?" ማለቱ አይቀርም።

በለሜን አሜሪካ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን መጋቢዎች፣ "ሕዝቡ መጽሐፍ ቅዱስንም ሆነ ድጋፍ ሰጪ መጻሕፍትን ማንበብ አይወድም፤ ተቸግረናል" ይሉኛል። ማንበብ የመጥላቱ ምክንያት ምን እንደ ሆነ ግን፣ ብዙዎች በውል መርምረው የደረሱበት

ቤተ ክርስቲያን በአትራፊ ድርጅት ለም ሳትመዘገብ፣ ሀብቷ በቀጥታ ወደ ግለሰቦች ካዝና እንዲገባ መደረጉ፣ በእንግሊዝ ብቻ ሳይሆን፣ በየትኛውም አገር ሕግ ወንጀል ነው። ልብ በሉ ዴቪድ አይዴፖን ጨምሮ በርካታ የዓለማችን የናጠጡ ቱጃር ስባኪያን፣ የእምነት እንቅስቃሴ አራማጅ አባይ ነባይ ስባኪዎች ናቸው።
http://dailypost.ng/2017/07/31/seven-nigerians-make-list-top-20-world-richest-pastors-see-list/
http://gazettereview.com/2016/02/richest-pastors-in-world/

በኢትዮጵያ የሚገኙትም አባይ ነባሮች ይህንኑ አካሄድ እንደሚከተሉ፣ አገር ያወቀው ዐሓይ የሞቀው እውነት ነው። እንዲያውም በቅርቡ በለሜን አሜሪካ ይህንኑ አካሄድ በማራባት በተለያዩ ግዛቶች/ስቴቶች "የድርጅታቸውን" ተከላ እያካሄዱ ነው። የሚያሽከረክሯቸው መኪኖች፣ የሚኖሩባቸው መኖሩያ ቤቶች... የብልጥግናቸውን ለፋትና ጥልቀት፣ ዘተወለነ ደረሻም ቢሆን ያመላክታል። ሠርቶ መክበር አግባብ ቢሆንም፣ የቤተ ክርስቲያንን ሀብት በዚህ መልክ መዝረፍ ግን፣ ትልቅ ስሕተት እንዲሁም ትልቅ ወንጀል ነው። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን በለሚ እየተካሄደ ያለውን ወንጀል የማስቆም፣ መልካሙን ለሚን የሚያጐድፉ ለምችን የመጋፈጥ ትልቅ ኀላፊነት ወድቆባታል። አልያ በዚህ መልክ የሌቦች ጉሬ ሆና፣ "የዓለም ፍጬው የዓለም ብርሃን" ነኝ ማለት አትችልም። ይህን ምፀት አውነት ነው ብሎ የሚቀበል ዘመናዊ ለው ሊኖር አይችልም፣ አይገባምም።

[15] ጅብ በውድቅተ ሌሊት መዝጊያ ገንጥሎ፣ መክት ዘንጥሎ፣ ጠቦት አንጠልጥሎ እንደሚሄድ ይታወቃል። ይህ ያለና የነበረ ክሥተት ነው። በጠራራ ዐሓይ መግለጥና መስለብ ግን፣ እነዞ ዘመነኞቹ አባይ ነባሮች ለዓለማችን ያስተዋወቁት አዲስ ግኝት ሆኗል።

እያመሰለኝም። አባይ ነባይ ከምዕመኑ ቍጥር በላይ ሆኖ በፈላበት በዚህ ዘመን፣ ስው እንዴት አድርጎ ቃለ አግዚአብሔርን ያነባል? ምን ይሁን ብሎ ቅዱሳት መጻሕፍትን ይመረምራል? ለሕይወት ተሐድሶና ለሥነ ምግባር ፍልስፍና ለምን ይጨነቃል? ባይሆን ጊዜውን ስማኅበራዊ የመገናኛ ብዙኃን እንዲሁም መሰል መዝናኛዎች ስጥቶ፣ የዕስት ተዕስት አዋዋሉን በተመለከተ ለአባይ ነባዮች ገንዘብ አየከፈለ "ጸጋቸውን" ቢጠቀም አይቀልም? እንግዲያው በስሜን አሜሪካ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን መጋቢዎች፣ በውል ያላስተዋሉት ምስጢር ይህ ነው።

ዕስት በዕስት "እምላክ እንዲህ ይልሃል..." መባል የለመደ ስው፣ ለምን ብሎ መጽሐፍ ቅዱሱን ያነባል? ክርስቲያን ቅዱሳት መጻሕፍትን የሚያነበው መለኮታዊ ዕውቀት ለመቅሰም ብቻ ሳይሆን፣ መለኮታዊ ምሪት ለማግኘት ጭምር ነው። አምላክ አፍ ለአፍ፣ ዕስት በዕስት ይናገረኛል የሚሉ፣ ዐይነ ደረቅ ቄርጦ ቀጥሎች ምዕመኑን እንደ ጭስ አፍነውት፣ በምን ቀዳዳ ቃለ እግዚአብሔርን የማጥናት ትንፋሽና ብርታት ሊያገኝ ይችላል? ብዙዎች በውል ያላስተዋሉት ትልቁ እንቈቅልሽ ይህ ነው። ወገን፣ ታዲያ ችግሩን በውል የማታውቅለትን ምዕመን እንዴት ልታገለግለው ትችላለህ?

"ክርስቲያኖች ሁሉ ካህናት ናቸው፤ ከዚህም የተነሣ ያለ አንዳች መካከለኛ[16]፣ ክርስቶስ ኢየሱስ ዘንድ በቀጥታ መቅረብ ይችላሉ፤ አምላክን ማናገር ይችላሉ..." የሚለውን ትምህርት በማመናችን፣ ክካቶሊክና ከኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ተለይተን ነበር። ዛሬ ግን የታሪክ ምፀት ወድቆብን፣ አባይ ነባዮችን የየቀን ካህን አድርገን ሹመናል። አባይ ነባይ፣ "የየቀን ውሎህን ወለል አድርጌ እነግርሃለሁ" የሚለው ትውልድ፣ ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር የመሚገናኝ ዐቅም፣ ክየት ሊያመጣ ይችላል? መጽሐፍ ቅዱስ ክሌጅ በመሄድ በኮረ ጽሑፋትን ለመመርመር ብርታቱን ክየት ሊያገኝ

[16] ክርስቶስ ኢየሱስ የእኛርሱ መካከለኛ ብቻ ሆኖ።

ይችላል? የሕይወት ፍልስፍናውን ስማጥለል ሊቃውንትን መጻሕፍት በምን ጉልበቱ ይመረምራል? መጠይቃዊ ሕይወትንስ የጉዞ መስመሩ እንዴት ማድረግ ይቻለዋል? ይህን አንቈቅልሽ በትክክል ሳንፈታና ሳናስፈታ፣ ትውልዱን በትክክል ማገልገል እንችላለን ማለት፣ ሊበዛ ዘበት ነው! ይህን ሁነኛ ጥያቄ በትክክል የማይመልስ አገልግሎት፣ ስትውልዱ ነቀርሳ ፍቱን መድኒት ሊያመጣ አይችልም።

ከጽኑ ባርነት...ወደ አስደናቂ ዐርነት!

ሀ. የባህል ዕዳ ወድቆብናል!

ወፍ እንዳንገሯ...

በወንድማማቾቹ በዮሐንስ አድማሱና በዶክተር ዮናስ አድማሱ ጸሓፊነትና አርታዒነት (እንደ ቅደም ተከተሉ)፣ ተዘጋጅቶ ለንባብ የቀረበልን፣ "የቀኝ ጌታ ዮፍታሔ ንጉሤ አጭር የሕይወቱና የጽሑፉ ታሪክ"፣ በዚህ ረገድ የባህላችንን ዕዳ ጠቆም አድርጎ ያስፈበትን እንዲት አጽቅ ልጥቀስ[17]። የዚህ ንዑስ ክፍል አጥር ጥር እንደሚከተለው ነው፦—

ንጉሥ ሚካኤል ዕስተ እሑድ ግንቦት 23 ቀን 1906 ዓ.ም ዘንቡሠ ጽዮን ተብለው ደሴ ላይ የንጉሥነት ዘውድ ደፉ። ማኅበረ ኤልያስ ለንጉሥ ሚካኤል የላከውን መልእክት አድርሰው እንዲሁም

[17] ዮሐንስ አድማሱ፣ *ቀኝ ጌታ ዮፍታሔ ንጉሤ አጭር የሕይወቱና የጽሑፉ ታሪክ 1887-1939*፣ አርታዒ. ዶክተር ዮናስ አድማሱ (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ 2004 ዓ.ም)፣ ገጽ 12-17። መጽሐፉ ዮፍታሔ በማኅበረ ኤልያስ የመመረጡ እንዲ ምክንያት፣ የንግግር ችሎታው እንደ ሆነ እንዲህ ሲል ይገልጻል፣ "ምንም በዕድሜ ሊጋ ቢሆን እንደቡቱ የረታ፣ ድፍረትን ከፊሲዋ ጋር ያስተባበረ አስተዋይ፣ ቢናገር የማያሳፍር ጽሩይ፣ የነገሩትን መልእክት ስተት አድርጎ የሚናገር ትብ፣ የነገር ብልት ያወቀ ረቂቅ፣ ንባቡን ከምስጢሩ፣ ምስጢሩን ከንባቡ አስማምቶ፣ በጥቂት ንባብ ብዙ ምስጢር አከናውኖ ስማቅረብ የሚችል ንግግር ዐዋቂ፣ እንደበተ መልካም ወሣት ነበረ" ገጽ 17።

የመልእክቱን ውጤት ይዘው ወደ ኤልያስ እንዲመለሱ ዮፍታሔ ንጉሤን፣ መሪ ጌታ ጀምበሬ ኪዳነ ማርያምንና ከቀኝ ጌታ ኑሬ ተስፋዬን ንጉሥ ሚካኤል ዘንድ ወደ ደሴ ላካቸው[18]።

"እነዚህ መልእክተኞች ወደ ደሴ ለመሄድ ከኤልያስ የተነሡት፣ ሐምሌ በባተ በዐሥራ አራተኛው ወይም በዐሥራ አምስተኛው ቀን ነበረ። ክረምት ስለ ነበረ በዝናቡ፣ በጭቃው፣ በውሃው ምላት ምክንያት መንገዱ አላፈጠናቸውም"[19]። የመንገዱ መራዘም፣ ይዘውት የወጡት ስንቅ እንዲያልቅ ምክንያት ሆነ። በዚህ ምክንያት እነዚህ ሰዎች ወደ ደሴም ሲሄዱ ሆነ፣ ከደሴ ወደ ኤልያስ ሊመለሱ፣ ብዙ የመንገድና የስንቅ ችግር እንዳጋጠማቸው የመጽሐፉ ጸሓፊ ይገልጸሉ[20]። እንግዲህ የነገሩ ዚቅ (ቁም ነገር) የሚጀምረው እዚህ ጋ ነውና በጽሐፉን በቀጥታ ልጥቀስ፡—

"ወደ ደሴ ሲሄዱ አንድ ቦታ ላይ ስንቅ አለቀባቸው። ይህንም ያጋጠማቸውንና እሱንም የመሰለውን ችግር ለመወጣት የሚከተለውን ያደርጉ ነበር። በመንገዳቸው ባጋጠማቸው መንደር ጉራ ብለው መጽሐፍ ገላጮች መሆናቸውን ሲናገሩ፣ አንዲት ሴት ቤታ አግብታ አስተናገደቻቸው። መሪ ጌታ ጀምበሬ መጽሐፍ ገላጭ ሆነው፣ ዳዊታቸውን ገልጠው ክህቧን እንደሚያዩ እያገላበጡ ምኑንም ምኑንም ሲቀላብጡ ዮፍታሔ በወረቀት ላይ ይጽፍ ነበር። ወንዶቹ ከሥራ ከመመለሳቸው በፊት ለመሸሽ ፈልገው ጥፊቱን ለሴትዮዋ ለመስጠት ቢፈልጉ፣ የተጻፈበት ቀለም እልደርቅ ቢል፣ 'ስጣት በወንገቷ ላይ ይደርቃል' ብለው መሪ ጌታ ጀንበሬ ቀለዱ"[21]።

ይህቺ አንቀጽ የአንድ መጽሐፍ ጥራዝ ቁም ነገር የተሸከመች ይመስለኛል[22]። ልብ እንበል፣ እነዚህ ሰዎች በማኅበረ ሰቡ ዘንድ እጅግ የተከበረ ሙያ ያላቸው፣ የሕዝበ ኤልያስ አምባላደር

[18] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 12።

[19] ዝኒ. ከማሁ፣ ገጽ 13።

[20] ዝኒ. ከማሁ።

[21] ዝኒ. ከማሁ፣ ገጽ 13-14።

[22] የመልእክተኞቹ ችግር አፈታት፣ የሕዝቡ ንጽርኮ ዓለም፣ የአርኤር ዘይቤ ወዘተ።

የመሆን ክብር የተጐናጸፉ፣ አገር ወክለው ሕዝብ መስለው ንጉሥ ዘንድ የሚቀርቡ፣ በወቅቱ በነበረው የአነዋወር (የአኗኗር) ስልት ሊቀ ሊቃውንት የሚባሉ ሰዎች ናቸው። ሆኖም ግን በክፉ ቀናት አህል መብላት የቻሉት የሕዝብ መልእክተኛ ነን፣ የቅዱሳት መጻሕፍት መምህራን ነን፣ የቤተ ክህነት አገልጋዮች ነን፣ የእግዚአብሔር እንግዶች ነን ወዘተ ብለው አይደለም። "መጽሐፍ ገላጭ ነን" ብለው እንጂ[23]። ለምን ይህን አካሄድ መረጡ ብንል፣ መልሱ እጭር ቀጭን ነው። ሕዝቡ እጁ የሚፈታው ለክህብ ቄጣሪ እንጂ፣ ለወንጌል አብሣሪ መቼ ሆነና። ለቃላተኛ እንጂ፣ ለብልሃተኛ ምን ቀኣብ አለውና። በምጥ ወቅት በችግር ጊዜ፣ እነዚህ ሰዎች የተጐናጸፏቸው ማኅበራዊ፣ አአምሮአዊና ሃይማኖታዊ ስኬቶች ሁሉ የእንቧይ ካብ ነው የሆኑት። እንደ ኒሻን ያንዣረገዝቸው ስኬቶች፣ ኮርማን እንጀራ ለማብላት፣ እንድ ጣሳ ውሃ ለማጠጣት ብቃት አልነበራቸውም። ማኅበረሰቡ የሚፈልገው ክህብ ቄጣሪ እንጂ ፊደል ቄጣሪም ሆነ ፊደል አስቄጣሪ አይደለም።

ባህላችን መፍቀሮተ ነባይ ክፉኛ የተጣባው ባህል ነው። እኛ ኢትዮጵያውያን፣ ደንቃራ፣ ቡዳ፣ ሰላቢ፣ ሚርተኛ፣ ጦስ፣ ጥንቁላ፣ ሞራ ገላጭ፣ ጠጠር በታኝ፣ እንደርቢ፣ ጠፍር አቀ-ም፣ ሙታን ጥራ፣ ጋኔን ጐትት...እያለ በሚመሰጥር (ምስጢራዊ ትርጉም በሚያነፈንፍ) ማኅበረሰብ ውስጥ በዝማ ተወልደን አድገን፣ በዚያው ክልል ተርመጥምጠን የምንሞት ነን። ታዲያ የአአምሮ ምርምርና መንፈሳዊነት አንዴት ሊታረቁልን ይችላሉ? አአምሮን የለጠን አምላክ የሰጠንን አአምሮ ፈጽመን ጨልጠን እንድንጠቀምበት ይፈልጋል ብለን እንዴት ልናስብ አንችላለን[24]?

[23] "መጽሐፍ ገላጭ" የሚባሉት፣ መጽሐፍን እያዩ የለዎችን ክህብ ማለትም ዕጣ ፈንታ እንነግራለን የሚሉ አባይ ጠንቋዮች ናቸው።

[24] ምንልባት አንዳንድ ሐያስያን፣ "ይህ ገለጻ የእኔን ባህልና የእኔን አካባቢ በትክክል የሚወክል አይደለም" ወይም "እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ከስማንያ በላይ ቋንቋዎችና ከአንድ መቶ በላይ ብሔሮች ባለብት አገር፣ ይህ ጅምላ ፍረጃ ሚዛናዊነት ያጉደለዋል" የሚል አስተያየት ሊለነዘሩ ይችላሉ። ይህ ትችት በሚከተሉት

ሰው ሁሉ የራሱ የሆነ መቅድመ ልባዊ *(presupposition)* አለው[25]። ከሊቅ አስከ ደቂቅ፣ ከትልቅ አሰከ ትንሽ የመቅድመ ልባዊ ሰለባ ነው። ከዚህም የተነሣ ነው የለው ልጅ፣ "ወና ቤት አይደለም" የሚባለው። የተማረውም ያልተማረውም፣ የቅድመ ግንዛቤው ሰለባ መሆኑ በጭራሽ አጠያያቂ አይደለም። ቤተ ለቤ፣ አለተዳደጌና ባህሌ በአስተላለቤና በማንነቱ ላይ የራሱ የሆነ ተጽእኖ አሳደረገም ማለት የሚችል ለብአዊ ፍጡር የለም፤ ቢልም አብለት ነው፤ ትልቅ ሽፍጥ ነው። ሁላችንም የአስተዳደጋችን ነጻብራቅ ነን—በጥሩም ሆነ በመጥፎ ጐኑ አስተዳደጋችን አሻራውን የነቀለብን "ንቅሳታም" ነን።

የተማረው ካልተማረው የሚለይበት ሁነኛ አካሄድ ግን አለው። ይኸውም የተማረ ሰው የመቅድመ ልባዊን ብርቱ ጣጣ በውል ይገነዘባል። "የመቅድመ ልባዊ ሰለባ ሆኛለሁን?" ሲል ራሱን ዕለት ዕለት ይጠይቃል። መንገዱን በጥብቅ ይሰልሳል። መሠረተ እምነቱን ይመረምራል። "በርግጥ ይህን ለማመኔ መረጃዬ ምንድን

አግባቦች ስሕተት ነው፦— *(1)* ልክ ነው ኢትዮጵያ የብዙ ቋንቋዎችና የበርካታ ብሔረሰቦች አገር ናት። ይህ ማለት ግን ኢትዮጵያዊ ባህል፣ ኢትዮጵያዊ ቀለም የለም ማለት አይደለም። ሰላለ ነው "የናይጀሪያውያን ባህል"፣ "የአሜሪካኖች ባህል"፣ "የኢትዮጵያውያን ባህል" ወዘተ የምንለው። በእነዚህ አገሮች ግን በርካታ ቋንቋዎችና በርካታ ብሔረሰቦች መኖራቸው እሙን ነው። ይህ መሆኑ ግን፣ የአገራቱ መለያ የሆነ ባህል ወይም "ገዢ አስተሳሰብ" የለም ወደሚለው ድምዳሜ የሚያደርሰን አይደለም። *(2)* ከላይ የኢትዮጵያውያን ባህል ጥንቁሳና ምስጠራ ከፋኛ ይጫነዋል ለሚለው መግት የቀረበው ናመና/ማሳያ፣ ከቦታ ቦታ፣ ከጊዜ ጊዜ በመጠንና በዐይነት ሊለያይ ይችላል፤ ምናልባትም በአንዳንድ አካባቢዎች ጨርሶውኑ *መገለጫው* ላይሆን፣ ሌላ መገለጫ ሊኖረው ይችላል። ይህ ማለት ግን ያ ዐይነት አስተሳሰብ ጨርሶውኑ የለም ወደሚለው ድምዳሜ ለያደርሰን አይችልም። ስለዚህ ስለባህል ሥነ ሰብ *(Cultural anthropology)* ጥናት ስናወራ፣ ናመናዎቻችን፣ "ጅምላ ጨራሽ" ተደርገው ሊወሰዱ አይገባም። "የጅምላ ጭፍጨፋ" የሚለው ሐሰ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችለው፣ ያ ዐይነቱ አስተሳሰብ በሌላ አካባቢ ላለመኖሩ፣ አጥጋቢና አሳማኝ መረጃ ሲቀርብ ብቻ ነው።

[25] "መቅድመ ልባዊ" ወይም "ቅድመ ግንዛቤ" *(presupposition)* የምንለው፣ ሰዎች በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ስለአንድ ነገር ወይም ስለአንድ ድርጊት ያሳቸው አተያይ ነው።

ነው?" ሲል ከራሱ ጋር በብርቱ ይሚገታል። ተጸራሪ ድምዳሜዎችን በቅን መንፈስ ያገናዝባል። እውነት የምትወስደኝ ማንኛውም ቦታ እሄዳለሁ፣ የምታጠጣኝን ጽዋ እጠጣለሁ የሚል ኪዳን ያቆማል (በዚህ መልኩ ንቅሳቱን ማደብዘዝ፣ ከበረታም ማጥፋት ይችላል)። ያልተማረው ግን ሰለባ መሆኑን አያውቅም፣ ነጻ ነኝ አንዳለ ጀሮውን እንደ በሳ ባርያ በግዙት ምድር በባርነት ይሞታል።

የኢትዮጵያውያን አስተዳደግና ባህል አጅግ መጥፎ ጐኑ፣ የሁሉ መስፈሪያ ሊሆን የሚገባውን አእምሮንና ትሩፋቱን የማስጣል ነያል ጉልበቱ ነው። ሰዎች አእምሮአቸውን አንዳይጠቀሙበት ማድረጉ ነው። በተለይ መንፈላውያን ነን የምንል ሰዎች፣ አእምሮን በጮሪጥ ነው የምናየው። አእምሮን የለጠን አምላክ፣ "የአእምሮ ነገር በቃኝ" ብሎ አንደ ተንገፈገፈ ነው የምናስበው። እንዲያውም ምክንዮአዊ ባልሆነ ጐዳና በመሄድ አእምሮን ተጸርረን መቆማችንን፣ እንደ ትልቅ መንፈላዊ ጀብዱ[26] እናየዋለን። "አምንታዊ ነገር ተናገር! በውጅ!" የሚለው የብልጽግና ወንጌል አስተምህሮ፣ ለዚህ ችግር ትልቅ ድጋፍ ይሁን እንጂ የበቀልንበት ዐፈር ምስጠራ ይበዛበታል[27]። ምናልባትም ይህ ትምህርት ሥር የለደደው ለባህላችን የተመቸ ጥፍጥና ስላለው ይሆናል።

---

[26] ይህ ቃል ከኦሮሚፋ እንደ ተገኘ፣ ከእኔና ከአንድዩ በቀር ማን ያውቃል? (ዐደራ ለፈጣታ የቀረበ ነው)።

[27] ይህን ስሑት አስተምህሮ ከንቱነት በትክክል ለማወቅ፦— ተሸመ ነጋሽ፣ *አስክመጣ ድረስ*። ግርማዊ ቡሽ፣ *የብልጽግና ወንጌል*። እንዲሁም ምኒልክ አሰፋውና ተስፋዬ ርነሌ፣ *የእምነት ወይስ የክህደት እንቅስቃሴ* በሚል ርእስ ያዘጋጁትን መጻሕፍት ይመለከቷል። የሚከተሉት የእንግሊዝኛ መጻሕፍት በአስተምህሮው ላይ ጠንካራ ትችት ያቀረቡ ናቸው፦— *Hank Hanegraff, Christianty in Crisis (Eugene, Ore.: Harvest House, 1993). Robert M. Bowman Jr, The Word Faith Controversy: Understanding the Health and Wealth Gospel* (Grand Rapida: Baker, 2001). *Gordon D.R. McConnell, A Different Gospel: A Historical and Biblical Analysis of the Modern Faith Movement.* (Peabody, Mass.: Hendrickson Publisher, 1995). *D. Fee, The Disease of the Health and Wealth Gospel* (Costa Mesa, Calif The World for Today, 1979).

መጽሐፍ ቅዱስ አምላለ መለኮት ናችሁ ሲለን፣ አምላለ መለኮትነታችን የአለምሮ ጎይላችን አንደ ሆነ፣ ስንቶች አስተውለንው ይሆን? አንድ ባልንጀራዬ፣ "ከሰው ልጆች መኻል፣ አንስላን የመሰለ አንደ ኢትዮጵያውያን ማን አለ?" ይላል። አውነቱን ነው—ወገኖቼ በብዙ አንጻር ደመ ነፍላውያኑን አንስላት ለመምለላችን አንዳችም ጥያቄ የለውም። ጅል አስተላለብ ሁሉ ጐጀውን የሚሠራብን ፍጡር ሆነናል፤ ብልጣብልጥ አንደ መናጀ ያሻው ቦታ በጀማ አፍሶ የሚወስደን ሰዎች ሆነናል።

ባህላችን፣ አስተዳደጋችን "በሕይወቱና በአስተላለቤ ውስጥ አንዳችም ተጽአኖ አላደረገም" ብንል ትልቅ እብለት፣ ትልቅ ቅጥፈት ይሆንብናል። ባይሆን በምን መልኩ ከተጽአኖው ዐርነት ልወጣ አችላለሁ የሚለው ጉዳይ ትድግናችንን ያፈጥነዋል። የወደቀ ለው ከመነሣቱ በፊት መውደቁን ማመን አለበትና። ችግሩን ሊያመላክት የሚችል አስረጅ ላቅርብ።

በአንድ ወቅት፣ ታምራት ገለታ የተባለ አባይ ጠንቋይ፣ የአገሪቱ መነጋገሪያ ሆኖ ነበር። ከግለሰቡ ቋሚ ደንበኞች መኻል፣ ስመ ጥር ምሁራን፣ ድምፃውያን፣ ፖለቲከኞች፣ ሙዚቀኞች፣ ነጋዴዎች ወዘተ አንደ ነበሩ፣ መንግሥት ንብረቱን አግቶ ዘብጥያ በወረወረው ጊዜ ይወጡ የነበሩ ጋዜጦች ነግረውናል። አንዲያውም አንዳንድ አንስት ምሁራን (የዩኒቨርሲቲ አስተማሪዎች)፣ የግለሰቡ ካዳሚና ዕጣን አጫሽ አንደ ነበሩ የሰማን ቀን፣ በአውነቱ ከትከት ፍርስ ብለን ነው የላቅንው፤ የተላለቅንው። አንዳንድ ስመ ጥር ዘፋኞች፣ የዘፈን ስንኝ በዚሁ ግለሰብ ማስቋጠራቸውን[28] የሰማን ጊዜማ ሠርግና ምላሽ ነው የሆነልን።

ነገር ግን ከጊዜያዊ ላቅና ተረብ ባለፈ፣ "ይህ አንዴት እውን ሊሆን ቻለ?" "በሃያ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን የሚኖር፣ በሳይንስና በፍልስፍና አላት የተሟሸ ሰው፣ ይህ ዐይነቱን ፋቡላ (የጥንት የግሪካውያን የአንስላ ተረት) አውነት ነው ብሎ አንዴት

[28] "የሐመሉ ፊረስ" የሚለው የአንዲት አንስት ዘፈን፣ የዚህ ሰው ድርሰት ነው የሚሉ አስተያየቶች ነበሩ።

ሊያምን ቻለ? በሃያ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን የሚኖር ሰው በዚህ መጠን አአምሮውን ሊነሣው አንዴት ይችላል?" የሚሰውን ብርቱና ዋነኛ ጥያቄ ብዙዎቻችን አልጠየቅንም። የጠየቅንም ሰዎች ወደ አስተንትኖቱ አልሄድንም[29]። ነገሮችን እየመሰጠሩ የመመልከቱ አዘምሞት የአኛ የመንፈላውያኑ ብቻ ላይሆን፣ ኢትዮጵያዊ በሚባለው ማላ ውስጥ ባለ ፍጥረት ሁሉ ላይ፣ በጉልኅ የሚታይ ችግር ነው።

የአኛን የኢትዮጵያውያን ምስጠራዊ ባህል፣ ከአሜሪካኖቹ ምክንዮአዊ ባህል ጋር አናነጻጽረው—በደምላላው። "አሜሪካስ ጋት/ጎት ታለንት" *"America's Got Talent"* በተባለው የተሰጥኦ ማላያ ዐውደ ትይእንት ላይ፣ አንደ ትንግርት የሚታዩ በርካታ ከሥተቶችን አየታዘብን ነው። በተሰይ የሰውን አአምሮ የማንበብ *"Mind Reader"* ክሂሎት[30] አስን የሚሉ ሰዎች፣ የሚያደርጉት ነገር ዐይናችንንና ጆሮአችንን አንድንጠራጠር የሚያደርጉ ናቸው። ከጉባኤው ማኻል አንድ ሰው አስቁሞ፣ "አንቺ *መ*ያሽ ማስተማር ነው"፣ "አንተ ሰው በዚህ መድኀኒት አለ፤ የመድኀኒቱ የመጠቀሚያ ጊዜ *(expiration*

[29] ግለሰቡ ከርቸሌ በወረደበት በአሁኑ ወቅት እንኳ፣ አንዳንድ ሰዎች ከአውሮፓና ከሰሜን አሜሪካ ግለሰቡ ወደ ታሰረበት አስር ቤት በመሄድ፣ "አገልግሎቱ ተጠቃሚ" እንደ ሆኑ ሰምቻለሁ። ግለሰቡ የቦታ እንጂ የምግባር ለውጥ እንዳያመጣ ያደረገው፣ "አገልግሎቱ" በኢትዮጵያውያን ዘንድ ሊኖሮ የማይችል ተፈላጊነት ያለው ጮማ ሥራ ሆኖ በመገኘቱ ነው። "ሰው በሠለጠነት አገሮች እየኖረ እንዴት እንደዚህ ያስባል?" ይባል ይሆን። መልሱ ከባድ አይደለም። የኢትዮጵያዊነት ሥሪት—ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያዊነትን ከነመሉ ክብሩም ሆነ ከነመሉ ግብሩ ጋር በአንድ ጠቅልሎ ተቀብሎታል። መለየት፣ መርጦ መውሰድ የሚለው ጉዳይ አያሠራም። በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ምድር ትልቅ የባህል አብዮት ካልተካሄደ በስተቀር፣ ይህ ዐይነቱ ዕድል ነጋሪ ስኬት አብላሪ ሥራ ተወዳዳሪ ሳያገኝ በመሪነቱ ይቀጥላል። ለአውነት ሳይሆን ለኽድ የደሩ ብልጣብልጦችም፣ በመጻኢው ዘመን ብዙ ንዋያ እንደሚለበስበት አያጠራጥርም።

[30] አማረ መስፍን፣ "ክህሎት" አይባልም፣ "ሆዘ አንቀጹ 'ክሂሎ' ስለኾነ፣ ግዛዊ ስመ 'ክሂሎት' መባል አለበት" ባይ ነው። እንግዲያው፣ አኔ ማን ሆኜ ይህን ትንታኔ ልጻፈ?

date) አንዲህና እንዲያ ነው" ይላሉ[31]። አነዚህ ሰዎች ወደ ኢትዮጵያውያን ቤተ ክርስቲያን ብቅ ብለው፣ በየትንግርቱ መኻል፣ "አሜን"፣ "ኢየሱስ"፣ "ሃሌሉያ"... የሚሉትን ሰማያዊ ቃላት አንደ ቅመም በተን በተን ቢያደርጉበት፣ ለመርዶ ነጋሪ የሚሆን ሰው የሚተርፍልን አይመስለኝም። መንጋውን በትምህርት ሳይሆን፣ በዝማሬና በዋዛ ፈዛዛ ያቆየ መጋቢ፣ አጁን አጨብጭዐ አንደሚቀር ማንም ሰው መጠራጠር ያሰበት አይመስለኝም[32]።

እዚህ ጋ ልንጠይቀው የሚገባን ወሳኝ ጥያቄ፣ ይህ ጉዳይ ሰምን በአሜሪካውያኑ (በአውሮፓውያኑ) አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ አይታይም?[33] የትአይንቱ ተዋንያን ነገሩን፣ "ችሎታ" ("ታለንት" *"talent")* በሚለው ቃል (ቅጥር) ብቻ ሊወስኑት ለምን ፈለጉ? ለምን

---

[31] *YouTube* ላይ፣ *"America's Got Talent Mind Reader"* ብለው ይፈልጉ።

[32] አንድ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ፣ የአንድ አባይ ነባይን ስም ጠቅሶ፣ "ያ ሰው ወደ አህባቢያችን ሊመጣ ነው ምን ይሻላል?" አለኝ፣ በትልቅ ፍርሓት በትልቅ ሥጋት ተውጦ። "ዐየር ላይ የተከልኻቸው ለምች በየት አቅጣጫ መንፈስ እንዳሰባቸው የሚወስነው ንፋሱ ስለሆነ፣ 'ንፋስ ሆይ አነፋፈስህ ውዴት ነው? ጉልበትህስ ምን ያህል ነው?' ብሰህ ሰምን አትጠይቀውም? 'ደጉንፋስ' አኳኋኑን በዝርዝር እንደሚነግርህ አትጠራጠር። ስለዚህ ጥያቄው መሰንዘር ያለበት ለእኔ ሳይሆን፣ ለሚመለከተውና ሕዝቡን በወደራ ለሰጠኸው ክፍል ነው፤ ስለዚህ እኔን ለቀቅ አያ ንፋስን ጠበቅ" አልሁት። ጠያቂዬ ኾደ ሰፊ ነው፣ በአስተያየቱ ባይደሰት እንኳ፣ ቅያሜ እንዳላደረበት ግን እምነት አለኝ። ዞሮ ዞሮ፣ መልእክቱ ቢሆን ወደ አንጀቱ ባይሆን ወደ ወንጉቱ በማድረሴ ደስተኛ ሆኛለሁ። በየከተማው ቤተ ክርስቲያን አንጻለሁ የሚለው ይህ ጉዳኛ አባይ ነባይ፣ ኮንፍራንስ ያካሂድባቸዋል በተባሉ ቦታዎችና ቀናት ላይ፣ በርካታ መጋቢያን "የፈውስ፣ የኀይልና የመነቃቃት ኮንፍራንስ" ጠርተው ነበር—"ከእኛስ ቤት ምን ጠፍቶ!" ለማለት። ምን ያርጉት፣ ንፋሰ (አሸዋ) ላይ የተከሏቸውን ምዕመናን፣ ከአውራቂስ ንፋስ ለማስመለጥ በተርሴስ ንፋስ ይሸሽጓቸው እንጂ *(ሐሥ. 27÷14፤ መዝ. 48÷7)*። ከአውራቂሱ ይልቅ ተርሴሱ ሞገደኛ እንደ ሆነ ማን ማን በነገራቸው። ዞሮ ዞሮ ትኮሱ የወረት (የገንዘብ) እንጂ የእውነት መቼ ሆነና። እኔ ታዲያ ዐቃቤ እምነት እንጂ፣ ዐቃቤ ወረት ማን አደረገኝ?—ገላ. 1÷10።

[33] ቢያንስ እኔ አይቼም ሆነ ሰምቼ አላውቅም።

መንፈሳዊ ሽማ በማኮናጸፍ፣ "መገለጥ"፣ "ትንቢት" የሚል ሲያሜ አላብሰው ቤተ ክርስቲያን አላገኙትም?

በሳይንሱ ዓሰም፣ አንዳንድ ሰዎች ሰድሰተኛ ወይም ሰባተኛ የስሜት ሕዋስ አንዳላቸው ይነገራል (ለምሳሌ *Telepathy, Precognation)*። "አንዲህ ዐይነቱ ሰው በኢትዮጵያውያን መካከል ቢኖር፣ ተጨማሪ የስሜት ሕዋሱን በመጠቀም ሩቅ ያሰውን ከሥተት ቢያውቅ ወይም ያሰብንውን ነገር ቢነግረን ወይም ደግሞ ሰሰ መጻኢው ጊዜ ቢተነብይ፣ ጉዳዩን ከክሂሎት/ክችሎታ ጋር ብቻ አያይዘን አንመሰክተዋለን?" አይመሰለኝም[34]። በወዲያ ያለችው ቤተ ክርስቲያን ጽላት ልትቀርጽሰት፣ በወዲህ ያለነው ደግሞ ልናጥንለት ልናደገድግለት የማንችልበት አንዳችም ምክንያት የለም—ይኸው በአነዚህ ሰዎች ዙሪያ እየተደራጀንና ቤተ ክርስቲያን አያነጽን አይደለም አንዴ? አንግዲያው ነገሮችን መንፈሳዊ የማድረግ፣ ከአአምሮ ምርመራ የማራቅ፣ ምርምርና መንፈሳዊነት አንደሚቃረኑ ማሰብ፣ የባህላችንና የንጽሮተ ዓለማችን ቅኝት ነው።

ባላ'ገር ልበ ገር

በብዙ ኢትዮጵያውያን ዘንድ፣ አግዚአብሔር ጸሎቱን የሚሰማለት ልበ አግዚአብሔር (ልበ ንጹሕ) ተደርጎ የሚታሰበው፣ በዘመናዊ ትምህርት ገፍቶ የሄደ ሳይሆን፣ ከክተማ ርቀው በሚገኙ ጠረፍ መንደሮች ውስጥ የሚኖር፣ አንዳችም የትምህርት ንፋሰ ያልነፈሰበት፣ ለሳይንስና ሰቴክኖሎጂ ፍጹም ባይተዋር የሆነን... ሰው ነው። የተማረ የተመራመረ፣ ጥያቄ የሚያበዛ፣ ትንታኔ የሚወድ...ሰው መንፈሳዊ አይደለም እንዲያውም የአምላክ ባላጋራ አድርጎ የሚሰፍር ሞገደኛ የሆነ አድፋጭ አለተሳሰብ አለ። አንድ

---

[34] ይህ ጽሑፍ እነዚህ ነገሮች አሉ ወይስ የሉም፣ ምንጫቸው እግዚአብሔር ነው ወይስ አይደለም ወዘተ የሚሰውን ምርመራ ታሳቢ አላደረገም። ዐላማዬ፣ "ይህ ዐይነቱ ክሥተት በርግጥ ቢኖር *(if...)* ነገሩን መንፈሳዊ ሳናደርገው ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ ብቻ እናብራራዋልንን?" የሚለውን ጉዳይ ለአንባቢያኑ ሚዛናዊ ፍርድ በማቅረብ የምዕራባውያኑን ባህል ከእኛ ጋር ማነጻጸር ነው።

ወዳጄ፣ “ኦርጋኒክ ምግብና ኦርጋኒክ መንፈሳዊነት በገጠሩ የአገራችን ክፍል ብቻ ነው የሚገኘው” የሚለው አባባሉ፣ አአምሮና መንፈሳዊነት ጠበኞች እንደ ሆኑ ታሳቢ ያደረገ ንግግር ነው። ይህ እንግዲህ የአስተሳሰባችን ድርና ማግ፣ ዋልታና ማገር ነው። ባህላችን ምርምርንና መንፈሳዊነትን ዐይንና ናጫ፣ እሳትና ጭድ አድርጎ የሚመለከት ባህል ነው። በዚህ ብቻ አይቆምም አንዲያውም ወደ ሌላው ጽንፍ በመሄድ፣ ጥንቁላንና ምስጠራን በብርቱ ይጠቅሳል።

ትምህርት አልጠናሽ ያለት፣ ችግሯን የምታያይዘው ከዐይነ ጥላ ጋር ነው። በፍቅር ብትነደፍ መስተፋቅር ሠርተውብኛል የሚል ጥርጣሬ ይገባታል። የቀለም ተቀብዖ ያለው ሲገኝ፣ ችሎታውን የምናያይዘው ከመተት ጋር ነው—አስደግሟል! በለስ የቀናው፣ ሠርቶ የተሳካለት ሰው ቢገኝ፣ አንደ ስላቢ ይታያል። በአጠቃላይ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ከመናፍስቱ ዓለም ጋር ያልተነካካ ነጻ መሬት ያለ አይመስልም።

ይህ ነው የበቀልንበት ዐፈር፣ ያደግንበት ማላ[35]። የሰው ልጅ የባህሉ ውጤት መሆኑ እሙን ነው። ነገር ግን ባህል ከሰው ተራ አውሮዶ፣ ደመ ነፍሳውያኑ አንስሳት መንደር ሊቀለቅለን፣ “ምን አየሆነ ነው?” እንዴት አንልም ጃል? ወደድንም ጠላንም፣ ባህላችን ጥንቁላና ምስጠራ በአያሌው የተጫነው ባህል ነው።

ባህላችን የአአምሮ ምርምርን የመጸየፉን ጉዳይ በውል የተረዱ ሰዎች፣ ትውልዱን ዐርነት ለማውጣት፣ “የአአምሮ ምርምር ከተት” ሊያውጁ ይገባል። የኢትዮጵያውያን ጉባኤ፣ የኖሳውያን ሰባኤ የሊቃውንት ምክር የጠቢባን ዝክር ብቻ ይህ ዐይነቱን ችግር ከሥር መሠረቱ ነቅሎ ይጥላል። አለያ ግን የችግሩን ፍሬ እንጂ፣ ችግሩን

[35] ስለ ባህል ተጽእኖ ስምግት፣ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ያለው የምስጠራ አካሄድ የባህል ተጽእኖ ብቻ ነው አያልሁ እንዳልሆነ ግን ልብ ይሏል። ምጣኔ ሀብታዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ እንዲሁም ሌሎች ፊርጀ ብዙ ጉዳዮች በዚህ ውጤት ላይ የራሳቸው የሆነ ተጽእኖ ሊያስከትሉ ይችላሉ። ስለዚህ ባህል ለዚህ ዝርክርክ ጉዳይ ዋነኛው ጠይም ከዋናዎቹ መንኳል ነው ማለቴ፣ ብቸኛው ሰበብ ነው ማለቴ እንዳልሆነ እንዲታወት እፈልጋለሁ።

ከሥር መሠረቱ ነድሎ መጣል አይቻለንም። ምን ሆነ ከሚለው ይልቅ፣ “እንዴት ወይም ስምን አንደዚያ ሊሆን ቻለ?” የሚለው ምርምር ወደ መፍትሔ የሚወስደን ትክክለኛ አቅጣጫ ነው። ይህ ሲሆን ብቻ፣ ትውልድን ከባህሉ ዕዳ ዐርነት ማውጣት ይቻላል።

እንግዲያው ኢትዮጵያ የሚገኝ ነባይ ዘንድ ደውሎ፣ “እንዲህ አድርግ!” መባል የሰመደ ወንድም ወይም ብርቱ ጉዳይ ሲኖራት ብር ብላ ኢትዮጵያ በመሄድ፣ “ጌታ አገሴን አግቢ ይልሻል!” መባል ዮተስማመደች አጎት፣ አምላክ ሕያው በሆነው ቅዱስ ቃሉ፣ እኔን በግሌ ያናግረኛል የሚል እምነት ሊያድርባት አይችልም። አሁንማ “ነቢያቱ” አዚሁ አሜሪካ አየመጡ፣ በየቦታው ቤተ ክርስቲያን በመትከል፣ በራሳቸው ዙሪያ አያደራጇቸው ያሉ ይመስላል።

ለ. የአስተምህሮ ችግር መጥቶብናል!

ላለፉት ሃያ ዓመታት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን፣ የተለያዩ የስሕተት ትምህርቶች ማራገፊያ ወደብ ሆናለች። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በዝርዝር ለማየት እንደምንሞክረው የተለያዩ የስሕተት ትምህርቶች በተለይ ደግሞ ከምዕራቡ ዓለም የሚነሡ ኑፋቄዎች መዳረሻ፣ የአፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው።

በዚህ ረገድ፣ “የአምነት አንቅስቃሴ” *(Word of Faith Movement)* በመባል የሚታወቀው መናፍቃዊ ትምህርት፣ አሁን ለምናየው ዝርክርክ አካሄድና ለአባይ ነባሮች መበራከት ትልቁን ድርሻ ይወስዳል። እልባት ካልተበጀለት ባህላችን ባልተናነስ መልኩ አጅግ ትልቅ ውድመት አስከትሏል—በማስከተልም ላይ ይኖራል። አንድም ጉበዝ አንኳን ከሩጫው ሊገታው ከፍጥነቱ ሊያበርደው የቻለ አያመስልም።

የእንቅስቃሴው ዕውቅ መምህራን የጻፏቸው አብዛኞቹ መጻሕፍት፣ በአማርኛ ቋንቋ ተተርጉመው ስንባብ ቀርበዋል። ዛሬ በዚህ አስተምህሮ ያልተበከለ አባይ ነባይ ማግኘት አጅግ አስቸጋሪ

ነው—የበሽታው መጠንና ዐይነት ቢለያይም አንኳ[36]። ይህን እንቅስቃሴ ከሌሎቹ መናፍቃዊ ትምህርቶችም ይልቅ አጅግ አደገኛ የሚያደርገው፣ ጴንጤቈስጣዊ ጭንብል አጥልቆ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናትን ዐርማ አያውለበለበ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዘው ብሎ መግባቱ ነው። ዛሬ በርካታ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች፣ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የዚህ ትምህርት ለለባ ናቸው። የእንቅስቃሴውን ዕውቅ መምህራን መጻሕፍት በማጥናት፣ አስተምህሮውንና አስተምህሮው የሚያዘውን ልምምድ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ናቸው።

ማንኛውም ምግባር የራሱ የሆነ ፍልስፍናዊ ወይም ነገረ መለኮታዊ መሠረት አለው፣ ዐየር ላይ የሚበቅል አንዳችም አረም አንደሌለ ሁሉ፣ ፅንሰ አሳብን መሠረት ያላደረገ ትንቢት ሊኖር አይችልም። ለዚህም ነው፣ "ትምህርት ምግባርን አለከትሎ ይሄዳል፤ ግብር ፍልስፍናን ይጠቅሳል" የሚባለው። መጥፎ ትምህርትን የተቀበለ ለው፣ መጥፎ ፍሬ ማፍራቱ አይቀሬ ነው። የእግዚአብሔር ቃል፣ "ከአሾኽ ወይን፣ ከኵርንችትስ በለስ ይለቀማልን? አንዲሁ መልካም ዛፍ ሁሉ መልካም ፍሬ ማፍራት ወይም ክፉ ዛፍ መልካም ፍሬ ማፍራት አይቻለውም" *(ማቴ. 7÷16-18)* ሲል፣ ለመጥፎ ፍሬ ምክንያቱ መጥፎ ትምህርት ወይም መጥፎ ፍልስፍና አንደ ሆነ የሚያሳይ ነው። ስለዚህ የመከር ጊዜን አየጠበቁ የክፉን

[36] በአሜሪካን አገር የሚገኙ አንዳንድ ቤተ ክርስቲያናትና መጋቢዎች፣ የዚህ ትምህርት ቀዳማይ አስፋፊ እንደ ሆኑ ብዙ ስዎች የሚያውቁ አይመስሰኝም። *(1)* በኢትዮጵያ የሚገኙ የእምነት እንቅስቃሴ አራማጆችን በገንዘብ የሚደግፉ፣ *(2)* በበዓለ ሢመታቸው ላይ በመገኘት ግለሰቦቹን የሚያበረታቱ፣ *(3)* እንቅስቃሴውን የሚያስፋፉ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶችን በገንዘብ የሚደጉሙ እንዲሁም *(4)* በኢትዮጵያ የሚገኙ የእንቅስቃሴው ሰባኪያን፣ ወደ አሜሪካን አገር በመጋበዝ በመድረካቸው ላይ የሚያሰብኩ፣ እነዚህ ግለሰቦች እንዲሁም እነርሱ የሚመሯቸው ቤተ ክርስቲያናት ናቸው። ይህ ደግሞ ችግሩ ምን ያህል ሥር እንደ ሠደደና እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ እንደ ደረሰ በጉልኅ የሚያሳይ ነው። የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ጎብረት በቅርቡ አያሳየን ያለውን ጥንካሬ ገፍቶበት፣ እነዚህንም ስዎች ያመክራል ይዘክራል አሻፈረኝ በሚሉትም ላይ መግለጫ ያወጣል ብለን እናምናለን።

ዛፋ፡ አኵይ ፍሬ ከመልቀም/ከመቍረጥ ይልቅ፣ መጥፎነቱን ከምንጩ ማከም ዘላቂና አማራጭ የሌለው መፍትሔ ነው።

በዓለማችን የሚገኙ የሃይማኖት ተቋማት ሁሉ፣ አምላክ ተናግሮናል በሚሉ አባይ ነባዮች የተቈረቈሩ መሆናቸውን ለንቶች አናውቅ ይሆን። ይህ ደግሞ የነባዮችን ጉዳይ በክፍተኛ ጥንቃቄ መያዝ አንደሚያለፈልግ በግልጽ የሚያሳይ ይመስለኛል። ስለዚህ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዘልቆ የገባውን ይህን እንዲሁም መሰል መናፍቃዊ ትህርቶች በቅዱሳት መጻሕፍት አለተምህሮ በጽናት ልንፋለማቸው ይገባል።

በግልም ሆነ በጀማ (በቤተ ክርስቲያን ደረጃ) መንፈሳዊ ተሐድሶ የሚመጣው፣ ወደ ቅዱስ ቃሉ በመመለስ፣ ቃሉን የሕይወታችንና የአስተምህሮአችን አልፋና ዖሜጋ በማድረግ ብቻ ነው። ይህ አካሄድ ለቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን፣ ለአገርም ዕድገት ትልቅ ዕገዛ አለው። ቅዱሳት መጻሕፍት ለምዕራባውያኑ ሥልጣኔ ፈር ቀዳጅና ፋና ወጊ ተደርገው ይታያሉ። በአውሮፓ የተነሣው የኢንዱስትሪ አብዮት መሠረቱ ከክርስትና በተለይ ደግሞ ከፕሮቴስታንቱ ተሐድሶ እንቅስቃሴ ስንቶች በለከነ ልብ አስተውሰነው ይሆን?

በዓለም ላይ ለታዩ አውነተኛ የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶዎች መሠረቱ፣ ቅዱስ ቃሉ ነው። የአምላክ አፈ ምት[37] ቃል ነው የምንለው መጽሐፍ ቅዱስ ነው፣ ለትምህርታችንና ለአስተሳለባችን መልህቅ መሆን የሚገባው። የፕሮቴስታንቱ የተሐድሶ ንቅናቄ፣ "ቅዱሳት መጻሕፍት ብቻ" *(Sola Scriptura)* የሚለውን ዐላማ፣ ለአምስት መቶ ዓመት ያውለበለበው፣ ለውጡ የተመራው በቅዱሳት

[37] እንደ ክርስቲያናዊው አስተምህር፣ ቅዱሳት መጻሕፍት በመንፈስ ቅዱስ አነሣሽነትና መሪነት የተጻፉ መጻሕፍት ስለሆኑ፣ የአምላክ አፈ ምት ቃል *(Inspired Word of God)* ናቸው እንላለን። እነዚያ የአምላክ አገልጋዮች/ባሮች፣ አምላክ ያሳያቸውን (በራእይ፣ በህልም)፣ የገለጸላቸውን (ዕውቀት፣ ክሃሎት)፣ የነገራቸውን (በድምፅ፣ በምልክት) ወዘተ በደንብል ቅጠል ወይም በእንስሳ ቈዳ ላይ ጽፈው አኑረውልናል።

መጻሕፍት አማካይነት በመሆኑ ነው። ይህም ቀዳማይ ቦላማ ነው፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን ከማጥናትም በላይ፣ በዓለማችን የሚገኙትን ስመ ጥር ዩኒቨርሲቲዎች አንዲቄረቄሩ ምክንያት የሆነው። ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን መጋቢዎችና አገልጋዮች ቃሉን ማንበብም ሆነ ማስነበብ፣ መተንተንም ሆነ ማስተንተን፣ ቀዳማይ ሥራቸው ሊያደርጉ ይገባል የምለው። የጌታ አገልጋዮች፣ የቃሉ አገልጋዮች ናቸውና። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ምስጠራን የሚያበረታቱና አእምሮአዊ ፋይዳዎችን የሚያጣጥሉ ስዎችንም ሆነ አስተምህሮዎችን በግልጽ መቃወም ይኖርባታል። ቃሉን የሰጠን አምላክ ነው አእምሮንም የሰጠን። አውነተኛ መንፈሳዊነትና እውነተኛ ምርምር እርስ በርስ ሊቃረኑ አይችሉም። "በአእምሮ መታደስ መለወጥ" ለሚለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ አሳብ፣ ከዚህ ውጪ ሌላ የትርጓሜ አማራጭ ልናበጅለት አንችልም (ሮሜ 12÷2፣ ኤፌ. 4÷23-24፣ 5÷17፣ ቈላ 1÷9፣ 3÷10)።

የመጽሐፉ የሙግት ቢጋር

ይህ መጽሐፍ፣ በዘመናችን ነቢይ በሚል ቅጽል (የማዕረግ ስም) የሚጠሩ ነባዮች፣ የትንቢትና የፈውስ ስጦታ ተሰጥቶናል የሚሉ አብዛኞቹ ለምች፣ ነገረ መለኮታዊ አሳቦታቸው (ሥሪታቸው) ምን እንደ ሆነና፣ ይህስ አስተሳሰብ ከቅዱሳት መጻሕፍት አስተምህሮ ጋር በማነጻጸር ብያኔ ይሰጣል።

ይህን ጭብጥ ለመተንተን ይህ መጽሐፍ የሚከተሉትን አራት አካሄዶች ተከትሏል፦—

(1) ዘመነኞቹ አባይ ነባዮች ምናልባትም ሁሉም ማለት በሚቻል ደረጃ፣ ታሳቢ የሚያደርጓቸው ስሑት የነገረ መለኮት አስተሳሰብ *(theological presuppositions)* አሏቸው። ለእነዚህ የተሳሳቱ መቅድመ ልባዊዎች ቅዱሳት መጻሕፍትን ማገናዘቢያ ባደረገ መልኩ ምላሽ መስጠት፣ ክርስቲያኑ ማኅበረተሰብ የነባዮቹ ትንቢት ስሑት አንደ ሆነ በቀላሉ አንዲያውቅ ያስችለዋል።

አንድ አስረጅ ልጥቀስ። "መርዕድ" በተባለ ስም በፌስቡክ ላይ የተለጠፈ የአንድ ግለሰብ ትንቢት፣ "የክርስቶስ ምጽአት የሚሆነው፣ ኢትዮጵያውያን ወደ ዓለም ሁሉ ተበትነው የምሥራቹን ወንጌል ሲሰብኩ ነው" የሚል ሐሳብ ተካቶበታል[38]። ይህ ትንቢት "ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ልዩ ናቸው" የሚለውንና በብዙዎች ዘንድ የሚነገረውን የጀማ ነገረ መለኮት ታሳቢ ያደረገ ትንቢት ነው።

አንድ ናይጄሪያዊ ክርስቲያንና አንድ ኢትዮጵያዊ ክርስቲያን፣ በአምላክ ዘንድ አኩል ናቸው። ኢትዮጵያዊውን የተቤዠው ክቡር የክርስቶስ ደም ናይጄሪያዊውን ተቤዠቶታል። ጌታ የኢትዮጵያን አብያተ ክርስቲያናት በሚወድበት መንገድ የኬኒያን አብያተ ክርስቲያናት ይወዳል። ወይም ደግሞ ክርስቶስ ኢየሱስ ስኢትዮጵያውያን ወይም ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብቻ የከፈለው፣ ተጨማሪ ዋጋ የለም። ናይጄሪያውያን ክርስቲያኖች ከድነቱ በረከት የጎደለባቸው አንዳችም ነገር ሊኖር አይችልም። ስለዚህ አቶ መርዕድ ኢትዮጵያውያንን የፍጻሜ ዘመን ቀዳማይ ተዋናይ፣ የዓለም መድኀኒት ናቸው የሚለው ትንቢቱ፣ ክርስቶስ በአይሁድና በአሕዛብ መካከል የነበረውን የጥል ግርግዳ አፍርሷል፣ ከአሁን በኋላ አይሁዳዊ የለም፣ አሕዛብም የለም፣ ክርስቶስ ኢየሱስ ከነገድ ሁሉ፣ ከቋንቋም ሁሉ፣ ከሕዝብም ሁሉ ዋጅቷል ከሚለው ከምሥራች ወንጌል ጋር በጽኑ ይቃረናል (ሮሜ 10÷12፣ 3÷22:29:30፣ ገላ. 3÷28፣ ቈላ. 3÷11፣ 1ጢሞ 2÷5፣ ራእ 7÷9፣ 14÷6)።

"ኢትዮጵያውያን ልዩ ሕዝቦች ናቸው" የሚለው አስተሳሰብ በአብዛኛው የመነጨው፣ "መጽሐፍ ቅዱስ ኢትዮጵያን ከ40 ጊዜ በላይ ጠቅሷታል" ከሚለው ያረጀ ያፈጀ ትምህርት ይመስለኛል። በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ መጠቀሳችን፣ ጥንታውያን ሕዝቦች

[38] የነባዩ ትንቢት ብዙ ዝርክርክ ነገር ቢኖርበትም፣ እኔ በዚህ ቦታ የጠቀስሁት የጉዳዩን ጭብጥ የሚያዋህልኝን አሳብ ብቻ ነው። በዚህ አጋጣሚ፣ እኔ ግለሰቡን በአፀደ ሥጋም ሆነ በአፀደ ፈስቡክ (በፈስቡክ ባልንጀርነት) አለማወቄን መግለጽ እፈልጋለሁ። ስለዚህ ስሙን መጥቀሴ፣ እንደ ግል ጥላቻ መታየት የለበትም።

መሆናችንን አንጂ፣ በክርስቶስ ድነታዊ ሥራ ውስጥ ልዩ ቦታ መያዛችንን በጭራሽ አመላካች አይደለም[39]።

ኢትዮጵያ የሚለው ስም በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ከተጠቀሰው ዕጥፍ በላይ የግብፃውያን፣ የአሶራውያን፣ የባቢሎናውያን፣ የግሪካውያን፣ የሮማውያን ስም ተጠቅሷል። ነገር ግን ከኢትዮጵያውያን በስተቀር፣ አነዚህ ጥንታውያን ሕዝቦች፣ አኛ በክርስቶስ ወጂዊ ሥራ ውስጥ ልዩ ቦታ አሰን የሚል አሳብ ሲያነሡ አይታይም። በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ተደጋግመው መጠቀሳቸውም ያንን አያመለክትምና። አምላክ አንድን ብሔር ወይም ሕዝብ ልዩ በሆነ መልኩ ይመሰከተዋል የሚል ነገረ መለኮት፣ በሊቃውንቱም[40] ሆነ በመጻሕፍቱ አንዳችም ስፍራ የለውም። አስራኤል ልዩ ቦታ አላት የሚለው የነገረ መለኮት አካሄድ አንኳ፣ ዛሬ በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት የለውም። በሐዲስ ኪዳን፣

[39] "ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች" (መዝ 68÷31፤ 87÷4፤ ኢሳ 18÷7፤ 19÷19፡21፤ 45÷14፤ ሶፎ 3÷10፤ ሐሥ 8÷27) የሚለውም ክፍል ቢሆን፣ ኢትዮጵያ በክርስቶስ ድነታዊ ሥራ ውስጥ ልዩ ቦታ እንዳላት ወይም በዘመነ ፍጻሜ ውስጥ በአገር ደረጃ ሚናዋ ትልቅ እንደ ሆነ የሚገልጽ አሳብ የለነዘረ፣ አንድም የነገረ መለኮት ለው የሚገኝ አይመለኝም። እንዲያውም አንዳንድ የትርጓሜ መጻሕፍት በዚህ ክፍል ላይ የሰጡትን አስተያየት ያነበበ ሰው፣ በዚህ ክፍል ሊያፍር እንጂ ደረቱን ሊነፋ አይችልም። ከዚህ በተጨማሪ ኢትዮጵያ የሚለው ስያሜ የዛሬዋን ሱዳን፣ ኤርትራን፣ ኬኒያን፣ ጅቡቲን እንዲያውም አንዳንዶች የመንንና ደቡብ አፍሪካን ይጨምራል በሚል ይሞግታሉ። ያም ሆነ ይህ ግን፣ ምድራቱም ሆነች የምድራቱ ነዋሪ ኢትዮጵያውያን፣ በክርስቶስ ድነታዊ ሥራ ውስጥ ልዩ ቦታ አላቸው የሚለው አስተሳሰብ በዘመነ ሐዲስ፣ ከመንፈሳዊ ዘረኝነት ተለይቶ የሚታይ አይመስላኝም። ምናልባትም በፖለቲካው ውስጥ ከምናየውም ዘረኝነት ይልቅ ይህ አስተሳሰብ ነውጠኛ ይመስለኛል። ጌታ በክቡር ደሙ ያፈረሰውን ግድግዳ መልሶ የሚገደግድ ከፋፋይ ነገረ መለኮት ነውና!

[40] በአንድ ወቅት አብሮ አሁን ደብዛው እየጠፋ ያለው *Classical Dispensationalism* አስተሳሰብ፣ ዛሬ በነገረ መለኮቱ ዓለም እምብዛም ተቀባይነት የለውም። የአስተምህሮው አራማጅ የነበሩ ሰዎች ራሳቸው፣ አስተምህሮውን በመቃወም ጽፈዋል። ለምሳሌ *Criag A. Blaising, Darrell L. Bock, Robert L. Saucy* መጻሕፍት ይመለከታል።

ክርስቶስ በአይሁድና በአሕዛብ መካከል የነበረውን ልዩነት ለአንዴና ለዘላለም አፍርሶታልና (ሮሜ 3÷22፡29፡30፤ ቁላ 3÷11፤ 1ጢሞ 2÷5፤ ኤፌ 2÷18-22)። ከዚህም የተነሣ አምላክ ስምችን የሚያውቀው በክርስቶስ ቤዛዊ ሥራ ብቻ አንጂ፣ በተወለዱበት ወይም ዜጋ በሆነበት አገር አይደለም። ስለዚህ በክርስቶስ የድነት ዓለም ውስጥ፣ ዜግነት ወይም የትውልድ ሐረግ አንዳችም ቦታ የለውም። ስለዚህ ይህ አንድን ሕዝብ ልዩ የሚያደርግ የነገረ መለኮት አስተሳሰብ ስሕተት ነው። ይህ አስተሳሰብ አንዳለን አንድ ናይጀሪያዊ ክርስቲያን ወይም አሜሪካዊ ባልንጀራችን ቢያውቅ፣ ምን የሚለማው ይመስላችኋል? ጌታ አኔና አንተን በደሙ ዋጅቶናል ብለንው ዞር ብለን፣ ኢትዮጵያዊ በመሆኔ ግን በድነት ታሪክ ውስጥ እኔ ከአንተ የተሻለ ቦታ አለኝ ማለት ከስሕተትም በተጨማሪ ነውር አይደለምን?

አኔ ይህን ናሙና በዚህ ቦታ የጠቀስሁበት ሁነኛ ዐላማ፣ የነባሮቻችንን የተሳሳተ ትንቢት ለመለየት፣ አብዛኞቹ ነባሮች ታላቢ ያደረጓቸውን፣ ነገር ግን በቅዱሳት መጻሕፍት አንዳችም ድጋፍ የሌላቸውን ትምህርቶች አንድ በአንድ ነቅሶ በማውጣት (ቢያንስ በብዛት የተለመዱትን)፣ ክርስቲያኑ ማኅበረሰብ አንዲያውቃቸው ለማስተዋወቅም ባሻገር፣ ለምን ስሕተት አንደ ሆኑ በስፋት ይሞግታል። አነዚህን ስሑት አስተሳሰቦች ከማስተዋወቅም ባሻገር፣ ለምን ስሕተት አንደ ሆኑ በስፋት ይሞግታል። አነዚህን ስሑት አስተሳሰቦች በውል ካወቅናቸው በአባይ ነባይ የመታሰል ዕድሳችን በእጅጉ ይቀንሳል፤ ምናልባትም ሳያውቁ በስሕተት አንቅስቃሴውን የተቀላቀሱ አባይ ነባሮችን መታደግ ያስችለናል[41]።

[41] አነዚህ አባይ ነባሮች፣ በየጊዜው የሚሰብኳቸውን ስብከቶችና ትምህርቶች፣ እንደ "ፌስቡክ" እና "ዩቲውብ" ባሉ የመገናኛ ብዙኃን ላይ አዘወትረው ይለጥፋሉ። አድናቂያቸውም ሆነ ተቃዋሚው ክፍል በሚያየውና በሚሰማው ጉዳይ ላይ የበኩሉን አስተያየት ይሰጣል። አስተያየቶቹ በአብዛኛው ዘለፋና ቁጣ የሞላባቸው መሆናቸው ብቻ ሳይሆን፣ በአካሄድም ደረጃ ቢሆን አነርሱ ይዘውት በቀረቡት አጀንዳ ላይ መወያየት ትክክል አልመሰለኝም። ምክንያቱ አራት ነው፡— *(ሀ)* ይህ አካሄድ አነርሱ እንድንወያይ በሚፈልጉት አርቲ ቡርቲ አጀንዳ ላይ ብቻ ትኩረት

(2) አባይ ነባዮች መተቸት የለብንም፣ አስተምህሮአችን መመዘን የለበትም በማለት ራሳቸውንና ትምህርታቸውን ከምዘና የሚደብቁባቸውን ቋሚ ዘዴዎች ማላወቅ፣ ክርስቲያኑ ማኅበረሰብ በእነዚህ አነጋገሮች እንዳይታለል ማሠልጠን የመጽሐፉ ዐላማ ነው። ለምሳሌ፣ "እንዳይፈረድብህ አትፍረድ"፣ "ጌታ በቀባው ላይ እጅህን አታንሣ"፣ "ለምችን ስም አየጠሩ ማውገዝ ስሕተት ነው"፣ "የሚያደርጉትን ሁሉ የሚያደርጉት በኢየሱስ ስም ስለሆነ ክክፉ መንፈስ ነው ማለት አይቻልም" ወዘተ።

(3) ይህ መጽሐፍ፣ ቤተ ክርስቲያን በየጊዜው የሚያቈጠቍጡ ኑፋቄዎችን እንዴት በፍጥነት መለየት እንደምትችል የሚረዳንን ዘዴ ያስታጥቃል። ከፀሓይ በታች ያሉትን የአባይ ነባይ ትንቢቶችን ሁሉ መርምረን አንዘልቅም። ነገር ግን ብዙዎቹ የሚስቱባቸውን ነጥቦች

እንድናደርግ፣ ክቡር ጊዜያችንንና ጕልበታችንን እንድንፈጅ ምናልባትም እንድንጨርስ ያደርገናል። ይህ ደግሞ እነርሱ አጀንዳ ለፈጪ፣ ክርስቲያኑ ማኅበረሰብ ደግሞ አጀንዳ ተቀባይ አድርጎታል። (2) ይህ ዐይነቱ ውይይት አቀራረብን ብቻ መሠረት ያደረገ ስለሆነ፣ አባይ ነባዮቹ ታሳቢ ያደረጓቸውን አስተምህሮዎች ሥር ነቀል በሆነ መልኩ የመመለስ ዐቅም አይኖረውም። አጀንዳው የተቀረጸው በመሠረታዊ ጕዳይ ላይ ስላልሆነ። (3) በአስተምህሮ ጕዳይ ላይ እንኳ ብንወያይ፣ እነዚህን የድምፅ-ከምስል (የቪዲዮ) መረጃዎች የሚቈጣጠሩት እነርሱ ስለሆኑ፣ ባሻቸው ጊዜ ሊያጠፏቸው ስለሚችሉ፣ እማኝ አድርገን ልንወያይባቸውም ሆነ ልንጽፍባቸው ያስቸግራል። እንደዚያ አላደረግንም፣ በዚያ መልክ አላስተማርንም ወዘተ ቢሉ ምንም ዐይነት ማስረጃ (ማመሳከሪያ) በእጃችን ሊቀርልን አይችልም። መረጃዎቹን ቀድቶ ማስቀመጥ (download) ከተቻለ ግን፣ ጥናት ለማካሄድና ሐሰ ለመስንዘር ለሚፈልጉ ሰዎች ጠቀሜታው ታላቅ ነው። ጥናት በማጥናት ዐቅቤ እምነታዊ ምላሽ ለሚሰጡ ለምች፣ መረጃዎቹን ቀድቶ (download) መስጠት (ማስተላለፍ) ትልቅ ዕገዛ ነው። የኮምፒውተር ዕውቀት ያላቸው ወገኖች፣ ይህ ዐይነቱን መረጃ እየቀዱ (download) እንዲያስቀምጡ አበረታታለሁ። (4) የእነርሱን ድምፅ-ከምስል (ቪዲዮ) መረጃዎች ለውይይት በሚል ሒሳብ በየፌስቡኩ ላይ መለጠፍ፣ ተደማጭነታቸውንና ዕውቅናቸውን የሚያስፋው ይመስለኛል። ስለዚህ ይህ አካሄድ ቤተ ክርስቲያንን የሚጐዳ በእንጻሩ ደግሞ እነርሱን የሚጠቅም ነገር ከማድረግ መቈጠብ ያለብን አይመስላችሁም?

ማወቅ፣ ስሕተቱን ቶሎ ከመለየትም ባሻገር ለአፋጣኝ መፍትሔ ያዘጋጀናል።

የአባይ ነባዮችና የመናፍቃን አካሄድ በብዙ መልኩ አንድ ዐይነትና ተወራራሽ ስለሆነ፣ በመጽሐፉ ውስጥ እነዚህን ቃላት ቡተደጋጋሚነት ተጠቅመናል። ልዩነታቸውን በተመለከተ ግን የቃላት አማራና ፍካሬ በሚሰው በቀጣዩ ክፍል፣ ሰፊ ማብራሪያ ቀርቦአል።

(4) ባለማወቅ የተሳሳቱ አባይ ነባዮች ከተሳሳተው መንገዳቸው እንዲመለሱ የሚያስችል፣ መሠረታዊ ትምህርት ያለጨብጣል። በተሰይ ለስሕተት የተጋለጡ ትምህርቶችን በመጠቀም ትክክለኛውን ትምህርት ያመላክታል። ቤተ ክርስቲያን በእነዚህ አስተምህሮዎች ላይ ቆማ፣ የአባይ ነባይ አካሄድ የነበራቸውን ግለሰቦች፣ ነገር ግን ለመመለስ ፈቃደኛ የሆኑትን፣ እንዴት በአስተምህሮ ግራዋ በማጠብ፣ በደቀ መዝሙርነት ወይራ በማጠን፣ ከበከላቸው የኑፋቄ አተላ እንዴት ማጽዳት እንደሚቻል፣ ፍንጭ ጠቋሚ ነገሮችን ያስተዋውቃል።

ስጦታ ልዩ ልዩ ነው! እንዳንዱ እንደ እኔ መጻፍ ይቀናዋል። እንዳንዱ ደግሞ ማንበብና ማስነበብ ይሆንለታል። እንዳንዱ ጥሩ ሰባኪና አስተማሪ ነው! እንግዲያው እኔ በአምላክ እርዳታ፣ የዐቅሜን ያህል ጥረት አድርጌ ይህን መጽሐፍ በእጃችሁ አድርሻለሁ፣ ይህን በማድረጌም ክርስቲያናዊ ኀላፊነቴንና አምላካዊ ዐደራዬን በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ፈቅ ያደረግሁ ይመስለኛል፣ እናንተም እንደ ተልእኮአችሁና እንደ ተውህዖአችሁ፣ የመጽሐፉን አስተምህሮና ዐላማ ለሌሎች አንድታዳርሱ በማክበር አጠይቃለሁ። ተቀናጅቶ የመጣብንን ተግዳሮት በተቀናጀ መልክ ብቻ ነው ልንፋለመው የምንችለው። ምንም ያህል ጕልበት የታደልን ለምች ብንሆን፣ በተናጠል ትልቅ ለውጥ ልናመጣ አንችልም። ነገር ግን ጌታ የሰጠንን ገንዘብ፣ ዕውቀት፣ የተመቻቸ ሁኔታ...ብናስተባብር መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትናን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዳግም መመሥረት፣ የደከመውንም ማጐልበት እንችላለን።

መቼም በአባይ ነባይ ያልተንገበገበ፣ የምንጓደድበትን ክቡር እምነታችንን፣ በዚህ መጠን ሲሳለቁበት በማየት ያልተቆጨ ክርስቲያን ያለ አይመስለኝም። እንግዲያው አሁን የምንንጨረጨርበት ሰዓት ሳይሆን፣ የማንበብና የማሰነበብ፣ የመተንተንና የማሰተንተን ጊዜ ነው። አለማወቅን በዕውቀት የምንበቀልበት ጊዜ ነው። የትምህርት ንፋሰን በጤናማ አስተምህሮ የምንመክትበት ወቅት ነው! ጠንክረን ክሠራን በአግዚአብሔር ጸጋና ኀይል፣ ኀፍረታችንን ሙሉ ለሙሉ ልንቀሰብሰው እንችላለን። አንዲያውም ከኪሳራችንን ልምድ የምንቀስምበት ትልቅ ቤተ ሙክራ በማድረግ፣ ወደ ፊት በሰፋት ሕዝባችንን ለማገልገል ትልቅ በር ሊክፍትልን ይችላል።

- "መጻሕፍትንና የአግዚአብሔርን ኀይል አታውቁምና ትሰታላችሁ" (ማቴ 22÷29)። "ኢየሱስም መልሶ አንዲህ አላቸው:— ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ...ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉና፣ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን አንኳ አሰኪያሰቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ" (ማቴዎስ 24÷4:24-25)።
- እነርሱም ክበጉ ደም የተነሣ፣ ከምሰክራቸውም ቃል የተነሣ ድል ነሡት፣ ነፍሳቸውንም አሰክ ሞት ድረስ አልወደዱም። (ራእ. 12÷11)።
- "የለውንም ሐሳብ፣ በአግዚአብሔርም ዕውቀት ላይ የሚነሣውን ክፍ ያለውን ነገር ሁሉ አናፈርሳለን፣ በክርስቶስም ለመታዘዝ አእምሮን ሁሉ አንማርካለን" (2ቆሮንቶስ 10÷5)።

ክፍል አንድ

የመሠረታዊ ቃላት ፍካሬና እማሬ



ይህ መጽሐፍ ትንታኔና ሙግት በሚያቀርብባቸው ርእሰ ጉዳዮች ላይ፣ ወሳኝ የሆኑ መሠረታዊ ቃላት ምን ትርጉም አንደሚወክሉ፣ ቋንቋዊና ነገረ መለኮታዊ አንድምታቸው አሰክ ምን አንደሚዘልቅ ይመረምራል[1]። ለቋንቋው ስያሜ በዋቢነት የምንጠቅሰው የቋንቋ

[1] "ፋካሬ" የግእዝ ቃል ሲሆን፣ "ተረጐመ፣ ፈታ፣ አፍታታ፣ ዘረዘረ፣ መረመረ" ማለት ነው (አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ 722)። ቋንቋን ወደ ቋንቋ ለመመለስ "ትርጓሜ" ስንል፣ ቅኔ፣ ህልም፣ ረቂቅ የሆነ ሐሳብን ለመተንተን እንዲሁም ሌላ ሐበአ ነገር ለመተርጐም "ፋካሬ" የሚለውን ቃል እንጠቀማለን። "እማሬ" የግእዝ ቃል ነው፤ ትርጉሙም ማመልከት፣ ይኼ ብሎ በጣት መጠቁም ማለት ነው (አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ 228)። እኔ በምጽፋቸው ጽሑፎች ውስጥ ፋካሬን በቀጥታ

መጸሕፍትን ሲሆን፣ ለነገረ መለኮቱ ደግሞ የነገረ መለኮት መዝገበ ቃላትን እንጠቀማለን።

ሀ. ቋንቋዊ ፍካሬ

ነባይ

- ነቢይ፣ የሚለው ቃል "ነበየ" ከሚለው ዘር አንቀጽ የሚወጣ ሲሆን፣ "ነበየ" ማለት፣ ነቢይ ኾነ፣ ትንቢት ተናገረ ማለት ነው[2]።
- ነባዪ[3]፦— በቍሙ[4]፣ የሚተነብይ፣ ተንቢ ነባቢ፣ ትንቢት ያደረበት፣ ራእይ የሚያይ ትንቢት የሚናገር፣ ለባሕ. መምህር[5]።
- ነቢያዊ[6]፦— የነቢይ ወገን፣ ነቢይ፣ ረድ ደቀ መዝሙር፣ ሀብተ ነቢይ የተለጠው፣ እንደ ኢያሱና እንደ ኤልሳዕ ያለ[7]።
- ነቢይ፣ ወደ ፊት ሊሆን፣ ሊመጣ ወይም ሊደርስ የሚችለውን ነገር አስቀድሞ የሚናገር የእግዚአብሔር ሰው[8]።

ትርጒሙ ማለትም ትንታኔ፣ ሐተታ የሚለውን አሳብ በሚወክል መንገድ የተጠቀምሁበት ሲሆን፣ እማሬን ግን የትንታኔው ፋይዳ፣ የትርጒሙ እንድምታ፣ በእንግሊዝኛ *significance* የሚለውን አሳብ እንዲይዝልኝ በማለብ ነው።

[2] አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፣* (ገጽ 620)።

[3] እርባታው እንደሚከተለው ነው—አንስታይ ነጠላ "ነባዪት"፣ ተባዕት ብዙ "ነባይያን"፣ አንስታይ ብዙ "ነባያት"።

[4] "በቍሙ" ማለት በቀጥታ ትርጒሙ ማለት ነው። በእንግሊዝኛው *literal* የምንለውን ይጐዳኛል።

[5] ዝኒ ከማሁ።

[6] እርባታው— አንስታይ ነጠላ "ነቢያዊት"፣ ተባዕታይ ብዙ "ነዚያውያን" አንስታይ ብዙ "ነቢያት"።

[7] ዝኒ ከማሁ።

[8] *አማርኛ መዝገበ ቃላት፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፣* አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የካቲት 1993፣ ገጽ 280።

- ነቢይ፣ በቍሙ ያለፈውንና የሚመጣውን ዐውቆ የሚናገር ሰው፣ ብቃት ያለው። ነባይ ዐማርኛ፣ ነቢይ ግእዝ ነው[9]።
- ነቢየ ሐሰት፣ ያላየውን አየኹ፣ ያልሰማውን ሰማኹ የሚል የሐሰት ነቢይ[10]።
- ነቢየ ጽድቅ፣ የአውነት ነቢይ[11]።

ነቢይ ግእዝ ሲሆን፣ ነባይ ደግሞ የአማርኛ አቻው ነው። በአጭሩ አባይ ነባይ ማለት ሐሰተኛ/ዋሾ ነቢይ፣ እምላክ ያልሰጠውን ሰጠኝ፣ ያልነገረውን ነገረኝ እያለ የሚቀሳምድ ማለት ነው።

ነገርን ነገር ያነሣዋል እንዲሉ፣ ከዚህ ጋር ተያያዥ የሆነ አንድ ነገር እግረ መንገዴን ጠቀም አድርጌ ባልፍስ? "የሞክሼ ሠሀያት ልዩነት የትርጉም ልዩነት ያመጣል" የሚባለው ጉዳይ፣ በዚህ ቦታ ደምቆ ይታያል። "አብይ" ማለት የሚያብል የሚዋሽ ማለት ሲሆን፣ "አበየ" ከሚለው ዘር አንቀጽ የሚሠርጽ ነው። በአንጻሩ "ዐቢይ" የሚለው ቃል "ዐበይት" ከሚለው ዘር አንቀጽ የሚወጣ፣ "አንጋፋ" በእንግሊዝኛው *"Major"* የሚለውን ቃል የሚዳበል ነው። ስማቸው "ዐቢይ" ተብሎ የሚጠራ ለዎች፣

[9] ደስታ ተክለ ወልድ፣ *ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት፣* ገጽ 832። ደስታ ተክለ ወልድና ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ነባይ መሠረቱ አማርኛ ነው ወይስ ግእዝ በሚለው ጉዳይ ላይ ልዩነት ያላቸው ይመስላል። አለቃ ኪዳነ ወልድ፣ በቍርዮ ሥሪቱ ግእዝ ነው ባይሉም፣ እርባታውን ያዘጋጁት የግእዝን አካሄድ ተከትለው ነው። ደስታ ተክለ ወልድ ግን በግልጽ፣ "ነባይ ዐማርኛ፣ ነቢይ ግእዝ ነው" ብለውናል። በዚህ ጉዳይ ላይ አስተያየት የጠየቅኋቸው ትልቁ የቋንቋ ሊቅ፣ አቶ እድጉ ረታ "ነባይ" ግእዝ ነው የሚል አቋም አላቸው። "እርባታው ግእዝን መከተሉ ሥሪቱ ግእዝ መሆኑን አመላካች አይደለም፣ በዚህ ረገድ ብዙ አፈንጋጭ ቃላት አሉ" ባይ ናቸው አቶ እድጉ። እኝህን ትልቅ ኦርቶዶክሳዊ ሊቅ በቅርቡ በሞት ማጣታችን፣ እኔን ጨምሮ ብዙዎች ተጐድተናል። እግዚአብሔር አምላክ ለቤተሰባቸው መጽናናትን ይስጥ።

[10] ዝኒ ከማሁ።

[11] ዝኒ ከማሁ።

በአልፋው “እ” ከጸፉ፣ “ዋሸ” በመሆን ትርጉም እንደሚሰት ልብ ይሏል።

“ሠረቀ” የተባሉ ሰው፣ በስርቆሽ ተከሰው የፍርድ ቤት መጥሪያ ይላክላቸዋል። መጥሪያውን አልቀበልም ይላሉ። ኋላ በፖሊስ ተይዘው ችሎት እንዲቀርቡ ይደረጋል። ፍርድ ቤቱ “ለምን መጥሪያውን አልተቀበልህም?” ቢላቸው፣ “ስሜ ስላልሆነ”። “ስምህ ማነው?” “ሠረቀ”። “ታዲያ መጥሪያው ላይ የተጻፈው፣ ስሜ አያደለም እንዴት ትላለህ?”። “ክቡር ፍርድ ቤት፣ ‘ሰረቀ’ ተብሎ በአሳቱ ‘ሰ’ ከተጻፈ፣ ስርቆሽ ወይም ሌብነት ነው፤ ያ ደግሞ በጭራሽ የእኔ ስምም ሆነ የእኔ ግብር አይደለም። ነገር ግን በንጉሡ ‘ሠ’ ከተጻፈ ወጣ ማለት ነው፤ ‘ሠረቀ ብርሃን’—‘የብርሃን መውጣት’ እንዲሉ”። “ስለዚህ ስሜ ሠረቀ እንጂ ሰረቀ አያደለም”። “እንዲያውም ክቡር ፍርድ ቤቱ ነገሩን በውል ሳያጣራ፣ እንድከላከልም ዕድል ላይሰጠኝ፣ ስርቀኻል በሚል ድምዳሜ ላይ ደርሶ ደብዳቤ በመላኩ፣ ጉዳዩ በለበር ችሎት ያታይልኝ” ሲሉ እሸፈረኝ አሉ የሚባል ወግ ሰምቻለሁ[12]። የጥንት የእማርኛና የግእዝ ቋንቋ ሲቃውንት፣ በሞከሼ ሆህያት ትልቅ ቅኔ ይዘርፉ እንደ ነበር ይነገራል። እንዳንድ ሰዎች ግን፣ የፊደል ገበታው ማጠር እለበት የሚል እሳብ ይሰነዝራሉ። ይህ ዐይነቱ እስተያየት “የሞከሼ ሆህያት ልዩነት የትርጉም ልዩነት ያመጣል” የሚለውን እንዲሁም የፊደል ገበታው የሰፋበትን ሁነኛ ምክንያት በአግባቡ ያለመረዳትን የሚያመለክት ይመስለኛል። ትልቁ የግእዝ ቋንቋ ሊቅ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣

የፊደልን ገላ ደርሶ ለመቊረጥ፣
ሐኪም መሆን ያሻል በአፋ በውስጥ።

[12] “ሰአለ” (ለመነ) እና “ሠዓለ” (ሥዕል ሣለ) የዚህ ቢጤ ነው።

ይላሉ። ውስጠ ምስጢሩን በወግ ሳይረዱ፣ በእማርኛ ላይ እስተያየት መስጠት እግባብ አይደለም ለማለት ተፈልጎ ነው[13]።

ይህ ሁሉ፣ ርእስ ለማብራራት የቀረበ ትንተና መሆኑ፣ አንዳንዶችን እንደሚያበሳጭ እገምታለሁ! በተለይ ደግሞ፣ “ሐሰተኛ ነቢያት—ሐሳውያን ነቢያት” የሚለው መደበኛ ቃል፣ ርእሱን ሙሉ ለሙሉ የሚወክለው ከሆነ፣ “ይህ ሁሉ ዙሪያ ጥምጥም ለምን አስፈለገ ሲባል ይችላል። ጥሩ ጥያቄ ነው ስንክሳሩ ያስፈለገበት ሁለት ዐቢይ ምክንያት አለ። እንደኛ የመጽሐፉ ርእሰ ሥነ ጽሑፋዊ ለዛ እንዲኖረው፣ እንብቡኝ አንብቡኝ የሚል መስህብ እንዲላበስ ከመሻት የመጣ ነው። ሁለተኛ በመግቢያው ላይ እንደ ገለጽሁት የዘመኑን ሐሰተኛ ነባዮች በትክክል የሚወክላቸውን ቃል መቀመሩ ድርጊቱን የመቃወሚያ እንዱ መንገድ መስሎ ስለታየኝ ነው[14]። እንግዲያው ጉዳዩ በዚህ መልክ ይታይልኝ።

መፍቀሬ የሚለው ቃል “ፍቁር” ከሚለው የግእዝ ዘር እንቀጽ የሚወጣ ሲሆን ትርጉሙም፣ “ወደደ፣ ተቀበለ፣ አከበረ፣ አስከበረ” ማለት ነው። ቃሉ በሁለት መንገድ በተገናኘ ይነገራል፤ እንደኛው “አፍቃሮ” ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ “መፍቀሬ” የሚለው ነው፤ ሁለቱም ይሰዳል፤ እማኝ ካስፈለገ አለቃ ኪዳነ ወልድን መጥቀስ እችላለሁ (ገጽ 731)። (ምሳሌ:—“እፍቅሮ ለእግዚ አምላክከ”፣ “መፍቀሬ ሰብእ”፣ “መፍቀሬተ ዝሙት” እንዲሉ)።

“አባይ ነባይ” እንደሚለው ቃል ሁሉ፣ “ጉፋቄ” የሚለውንም ቃል አብዝተን ስለምንጠቀም ቃሉ ምን አሳብ እንደሚሸከም፣ ነገረ መለኮታዊ እንድምታው ምን እንደ ሆነ እንመልከት።

[13] ዶክተር አምሳሉ አክሊሉ ያዘጋጇት መለስተኛ መጽሐፍ፣ በዚህ ረገድ ትልቅ ጥቅም አላትና አማርኛውን በወጉ ማወቅ የሚፈልጉ በተለይ ደግሞ የጽሑፍ ችሎታና ፍላጎት ያላቸው ሰዎች እንዲመለከቷት እመክራለሁ።

[14] ምናልባት ሦስተኛው ምክንያት በዚህ ታሪካዊ አጋጣሚ፣ የአማርኛ ችሎታዬን “በስ!” እንድትሉልኝስ ፈልጌ ቢሆን? መጠርጠር አይከፋም።

ኑፋቄ

- ነፈቅ፤ (ነፈቀ፤ ይነፍቅ፤ ይንፈቅ)፤ መንፈቅ መሰንጠቅ፤ አስተካክሎ መክፈል መለየት[15]። (ዘር አንቀጽ ነው)።
- መናፍቅ፤ (ቅት ቃን ቃት)፤ ናፋቂ፤ አናፋቂ፤ የሚጠራጠር፤ ጠርጣሪ አጠራጣሪ፤ ሃይማኖቱ ሕጹጽ የኾነ፤ ምሉዕና ፍጹም ትክክል ያይደለ፤ መንፈቁን አምኖ መንፈቁን የሚክድ[16]።
- ኑፋቄ፤ (ያት)፤ በቍሙ፤ መክፈል፤ መከፈል፤ ክፍያ አከፋፈል ጥርጥር፤ ጥርጠራ፤ ምንታቄ[17]።

እንደ አለቃ ኪዳነ ወልድ ከፍሌ፤ ኑፋቄ የሚለው ቃል "ነፈቅ" ከሚለው የግእዝ ቃል የወጣ ሲሆን፤ ትርጕሙም አንድን ነገር አስተካክሎ ለሁለት መክፈል፤ ማመንታት ወይም መጠራጠር፤ አምነተ ለንካላ መሆን፤ ግማሹን አምኖ ግማሹን መካድ በአጠቃላይ ሃይማኖቱ ሕጹጽ (ጕደሎ) የሆነ ማለት ነው።

ኑፋቄ የሚለው ቃል ከግእዝ የመጣ ቢሆንም፤ የአማርኛ ፍቺውን መመርመር፤ የቃሉ አማራጭ ትርጕም አስከምን ድረስ እንደ ሆነ ለማወቅ፤ የአማርኛ መዝገበ ቃላትንም መመልከት በብዙ ጕኑ ጠቃሚ ነው። ከሣቴ ብርሃን ተሰማ፤ *የዐማርኛ መዝገበ ቃላት*፤ ቃሉን በሚከተለው መልክ ይፈታዋል።

- ነፈቀ፤ ዐመትን ዕለትን ወርን ከፈለ፤ ለየ ወይም አንድ ሙሉ የኾነ ነገርን ከኹለት ከፈለ ወይም የብርቱካንን፤ የሎሚን አካል ከፍልፋዮች በየከፍላቸው ለየ።
- ነፈቀ፤ ከሃይማኖት ወጣ፤ ተጠራጠረ፤ መናፈቅን፤ ከሓዲን ኾነ ነፈቀ።

[15] የኪዳነ ወልድ ክፍሌ፤ *መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ* (ገጽ 645-646)።
[16] ዝኒ. ከማሁ።
[17] ዝኒ. ከማሁ።

የአማርኛው ገለጻ በአብዛኛው ከግእዙ ጋር አንድ ዐይነት ቢሆንም "ከሃይማኖት መውጣት፤ ከሓዲ መሆን" የሚለውን ትርጕም ጨምሮአል። በአጠቃላይ ኑፋቄ የሚለው ቃል ቋንቋዊ አጠቃቀሙ፦—

> "አንድን ነገር ለሁለት አስተካክሎ መክፈል፤ ማመንታት ወይም መጠራጠር፤ ግማሹን አምኖ ግማሹን በመካድ፤ አምነተ ለንካላ ወይም ከሓዲ መሆን" ማለት ነው።

ለ. ነገረ መለኮታዊ እማሬ

ኑፋቄ ወይም መናፍቅ ለሚለው ቃል የእንግሊዝኛ አቻ ቃላት ክልት *(cult)* እና ሔረሲ *(heresy)* የሚሉት ናቸው (ለመጀመሪያው ቃል ኑፋቄ ለሁለተኛው ደግሞ ሐራጥቃ/ሕርጥቅና)። ክልት የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል ክልተሰ ከሚለው የላቲን ቃል የተወረሰ ሲሆን፤ ትርጕሙም፦— "ማምለክ ወይም ለመለኮት ክብርን መስጠት"[18] ማለት ነው። የላቲን ቨልጌት ቃሉን ለእውነተኛው አምላክም ሆነ ለጣዖታት የሚቀርበውን አምልኮ በሚያሳይ መልኩ ተጠቅሞበታል። ለምሳሌ በሐዋርያት ሥራ 17÷23 ላይ የአቴና ለዎች ለሚያመልኳቸው ጣዖታት ይቀርብ የነበረውን አምልኮ ሲያመላክት፤ በቍጥር 25 ላይ ደግሞ፤ "ሕይወትንና እስትንፋስን ሁሉንም ለሁሉ" ለሚለጠው ልዑል እግዚአብሔር የሚውለውን አምልኮና ክብር ለማላየት ቃሉ ጥቅም ላይ ውሎ እንመለከታለን[19]። ይህ ትርጕም እኛ ልንጠቀምበት ካለብነውና ዛሬ አየተሠራበት ካለው አጠቃቀም ብዙ የራቀ ስለሆነ፤ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ አንጠቀምበትም።

ሔረሲ የሚለው ቃል፤ "ሔረሲስ" ከሚለው የግሪክ ቃል የተወረሰ ሲሆን ትርጕሙም፤ "ምርጫ" ወይም "የተመረጠ" ማለት ነው። ቃሉ በአዲስ ኪዳን ግሪክ ጥቅም ላይ የዋለው፤ "ክፍፍል" በሚለው ትርጕሙ ነው (የሐሥ. 24÷14፤ 1ቆሮ. 1÷1-19፤ ገላ. 5÷19-

[18] *Alan W. Gomes, Unmasking the Cults (Grand Rapids: Zondervan, 1955)* በገጽ 7 ላይ. ከCharlton T. Lewis and Charles Short, *A Latin Dictionary (Oxford: Oxford University Press, 1879, Impression of 1984) S.V. "colo" 370.* ጠቅሶ እንደ ጻፈው።
[19] *Gomes,* ገጽ 7።

20 ይመለከቷል።) የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ሔረሲ የሚለውን ቃል ትገለገልበት የነበረው፣ መሠረታዊ የሆኑትን ክርስቲያናዊ አስተምህሮዎችን ለሚቃወም ግለሰብ ወይም አንቅስቃሴ ሲሆን፣ ክርስቲያኖች ክእንዲህ ዐይነቱ ሰው ወይም ንቅናቄ መራቅ ወይም መለየት እንዳለባቸው በሚገልጽ መልኩ ገብቶአል[20] (የሐሥ. 24÷14 ይመለከቷል።) ስለዚህ ሔረሲ ማለት፣ መሠረታዊ የሆነውን ክርስቲያናዊ ትምህርት መካድ ስለሆነ፣ ከልት ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይ ትርጉም ይጋራል።

በአንግሊዝኛ ቋንቋ የተዘጋጁ አንዳንድ የነገረ መለኮት መጻሕፍት ክልትና ሔረሲ ክሚባሉት ቃላት በተጨማሪ፣ አክልት *(Occult)* እንዲሁም ሴክት *(Sect)* የሚሉትን ቃላት ሲጠቀሙ ይስተዋላል። ክዚህ የተነሣም ስለ እነዚህ ቃላት በትንሹም ቢሆን መነጋገሩ አግባብነት ይኖረዋል።

አክልት የሚለው ቃል አክልትስ *(Occultus)* ከሚለው የላቲን ቃል የመጣ ሲሆን ትርጉሙም፣ "የተደበቀ" ወይም "ምስጢር" ማለት ነው። የአማርኛ ጽሑፎች ለዚህ ቃል የሚሰጡት ትርጉም የተለያየ ሲሆን (አስማተኛ፣ ድግምተኛ፣ መተተኛ፣ ጠንቋይ፣ ቃላተኛ፣ መናፍስት ጠሪ፣ ዕድል ነጋሪ) አብዛኞቹ የሚስማሙበት ቃል ግን "ጥንቈላ" የሚለውን ነው። አንዳንድ መጻሕፍት አንደሚያስተምሩት ጥንቈላ (አክልት) በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች የሚከፈል ሲሆን፣ እነዚህም *(1)* መናፍስት ጠሪነት *(2)* ዕድል ነጋሪነት እንዲሁም *(3)* አስማት ናቸው[21]። እነዚህም ነገሮች የሚከናወኑት ሞራ በመግለጥ፣ ጠጠር በመጣል ወዘተ ባሉ መንገዶች ነው።

አሜሪካን ሄሪቴጅ የሚባለው የአንግሊዝኛ መዝገበ ቃላት፣ "ሴክት" የሚለውን ቃል፣ "ለፊና ትልቅ ክሆነው ሃይማኖት

[20] *Bowman, Orthodoxy and Heresy,* ገጽ 50።

[21] *George A. Mather and Larry a. Nichols. Dictionary of Cults, Sects, Religions and Occult (Grand Rapids: Zondervan, 1993)* ገጽ 212። ድግምት ወይም ምትሐት ልንለው እንችላለን።

ተገንጥሎ የወጣ ንዑስ ሃይማኖታዊ አካል" ሲል ይፈታዋል[22]። ብዙ የትምህርተ መለኮት መዝገበ ቃላት፣ "ሴክት" የሚለውን ቃል የሚጠቀሙበት ክርስቲያኖች ሆነው የሃይማኖት ባለ ሥልጣናትን የማያቀበሉ አንዲሁም ክቤተ ክርስቲያን ራሳቸውን ያገለሉ፣ ነገር ግን ጥሰውት የሄዱት ቤተ ክርስቲያን አጓድሎታል የሚሉትን ትምህርት አጠንክረውና ለጥጠው የሚሰብኩትን ነው[23]።

የነገረ መለኮት ሊቃውንት ኑፋቄ ወይም መናፍቅ ለሚለው ቃል የሚሰጡት ትርጉም ለየቅል ቢሆንም እብዛኞቹ የሚስማሙበት የሚከተሰውን ነው፦—

> "ከክርስትና አምነት የወጡ መናፍቃን ራሳቸውን ክርስቲያን ብለው የሚጠሩ፣ በመሪዎቻቸው ወይም በድርጅቶቻቸው የተሰጠውን የተወሰነ አስተምህሮአዊ ሥርዐት የሚከተሉ፣ ይህም አስተምህሮአዊ ሥርዐት ክሥልሳ ስድስቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅዱሳት መጻሕፍት የተቀዳውን የክርሰትና አምነት መሠረታውያን እስተምህሮዎች መኻል አንድ ወይም ከአንድ በላይ ትምህርት የሚክዱትን መናፍቃን ብለን አንጠራቸዋለን"[24] የሚለውን ነው።

ሐ. የነገረ መለኮት እማሬው ትንተና

በዚህ መጽሐፍ "ኑፋቄ" የሚለውን ቃል የምንጠቀመው በሂንቋዊ ፍቺው ሳይሆን፣ በነገረ መለኮታዊ አጠቃቀሙ ስለሆነ፣ ትንታኔው ይበልጥ ግልጽ እንዲሆን የትንታኔው ቃል ወይም ሐረግ

[22] *American Heritage Dictionary, Second college Edition (Boston: Houghton Mifflin, 1985,)* ገጽ 1108።

[23] *Bryan Wolson, "sect" in The Westminister Dictionary of Christian Theology, ed. Alan Richardson and John Bowden (Philadelphia: Westminister, 1983)* ገጽ 532።

[24] *Gomes* ገጽ 7።

ምን ዐይነት ነገረ መለኮታዊ ትርጕም ወክሎ እንደሚገኝ ወደ መመልከቱ እንዝለቅ[25]፦—

1. "ከክርስትና እምነት የወጡ መናፍቃን..."

መናፍቃን በአስተምህሮ ምክንያት ከእናት ቤተ ክርስቲያናቸው እፈንግጠው የወጡ ናቸው። ይህም፦— መናፍቃን በቀደምትነት ከተመሠረተው እምነት ያፈነገጡ መሆናቸውን ይገልጻል። እኛ አሁን የምንነጋገረው ከክርስትና እምነት ስለወጡት መናፍቃን ያኸውም በቀደምትነት ከተመሠረተው እምነት ያፈነገጡ መሆናቸውን ያሳያል። ለምሳሌ በአስልምና ውስጥ ሉፊዎችና ጥቁር ሙስሊሞች (የእስላም ሕዝብ *[Nation of Islam]* በመባል ይታወቃሉ) የአስልምና ሃይማኖት መናፍቃን በመባል ይጠራሉ። እነዚህ እንቅስቃሴዎች ወይም ኅብረቶች ራሳቸውን ሙስሊም እያሉ ቢጠሩም እንኳ፣ ከመሠረታዊ የአስልምና ትምህርት የራቀ አስተምህሮ ያላቸው ናቸው።

"ከክርስትና እምነት የወጡ መናፍቃን" የሚለውን ሐረግ የተጠቀምንበት ዋነኛ ምክንያት፣ ብዙ ሰዎች መናፍቃን የሚለውን ቃል የሚጠቀሙት እንደ አስልምና ባሃኢዝም ወዘተ ያሉትን ሃይማኖት በሚያመለክት መልኩ ስለሆነ እንዲሁም፣ "የክርስትና እምነት መናፍቃን" የሚለው ሐረግ በክርስትናና በመናፍቃን መካከል ጉልሕ የሆነ ልዩነት መኖሩን ለማመልከት ነው።

2. "...ራሳቸውን ክርስቲያን ብለው የሚጠሩ..."

መናፍቃንን፣ መናፍቃን ከሚያለኟቸው መስፈርቶች ውስጥ "ራሳቸውን ክርስቲያን ብለው የሚጠሩ" የሚለው አንደኛው ነው። ምንም እንኳ አስልምና ከክርስትና ጋር የሚቃረን እጅግ በርካታ

[25] በጎላማ መዘክሩ ላይ ልዩ መግለጫ ካልቀረበ በቀር፣ የመናፍቃን ነገረ መለኮታዊ ትንተና የተወሰደው ከሚከተለው መጽሐፍ ነው፦— *Alan W. Gomes, Unmasking the Cults (Grand Rapids: Zondervan, 1995)*።

ትምህርት ቢኖረውም፣ ራሱን ክርስቲያን ብሎ ስለማይጠራ በመናፍቃን ጕራ ሊፈረጅ አይችልም። አስልምና ራሱን የቻለ፣ ከክርስትና እምነት ጋር የሰማይና የምድር ያህል የተራራቀ የኅልማችን ሃይማኖት ነው።

"የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን"፣ "የይሖዋ ምስክሮች"፣ "የሞርሞን እምነት" ምናልባትም "የእምነት እንቅስቃሴ" በመባል የሚታወቀው አስተምህሮ፣ "ከክርስትና እምነት የወጡ መናፍቃን" ብለን ልንጠራቸው እንችላለን፤ ምክንያቱም ራሳቸውን ክርስቲያን እንዲያውም በምድር ላይ እነርሱ ብቻ እውነተኛ ክርስቲያኖች እንደ ሆኑ ያስባሉና።

ወንጌልን የሚቃወም ማንኛውም ሥርዐተ እምነትና ንጽሮተ ዓለም፣ ስዎችን በመጽሐፍ ቅዱስ ራሱን ከገለጠው እምላክ ስለሚያርቃቸው ስሕተት ነው። ነገር ግን ክርስቲያን ነን እያሉ መሠረታዊውን የክርስትና እምነት የሚቃወሙትን ብቻ መናፍቃን እንላቸዋለን።

3. "...በመሪዎቻቸው ወይም በድርጅቶቻቸው የተሰጠውን የተወሰነ አስተምህሮአዊ ሥርዐት የሚከተሉ..."

እንዳንድ የመናፍቃን ድርጅቶችና እንቅስቃሴዎች ለምሳሌ "የእምነት እንቅስቃሴ"፣ "የእግዚአብሔር ልጆች"፣ "የዩኒፊኬሽን ቤተ ክርስቲያን" የተወሰኑ ነባዮቻቸውን "ባለ ሥልጣን ነቢያት" ናቸው በማለት የእውነት ምንጭ እድርገው ይቀበሏቸዋል።

እንዳንድ መናፍቃዊ እንቅስቃሴዎች ደግሞ፣ እውነትን የማግኘትና ስዎችን በእውነት የመምራት ሥልጣን የድርጅቶቹ ብቻ እንደ ሆነ ያስባሉ። ለምሳሌ፣ "የይሖዋ ምስክሮች" የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር በመባል የሚታወቀውን ድርጅት የሚመሩት የአመራር አካላት ("ልባምና ታማኝ ባሪያ" በመባል ይታወቃሉ) "ወቅታዊ የሆነውን መንፈሳዊ ምግብ ያወርዳሉ"

ተብሎ ስለሚታመን ስድርጅቱ እመራር እካላት ትምህርት፣ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መገዛት ይጠበቅባቸዋል።

4. "...ይህም አስተምህሮአዊ ሥርዐት ከሥልሳ ስድስቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅዱሳት ጽሑፎች የተቀዳውን..."

ክርስቲያናዊ ትምህርት መመሥረት ያለበት፣ የእግዚአብሔር ሥልጣናዊ ቃል በሆኑት በሥልሳ ስድስቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅዱሳት መጻሕፍት ብቻ ነው። እንዳንድ መናፍቃን በእነዚህ መጻሕፍት ላይ መጻሕፍትን ይጨምራሉ፣ ይህ ጉዳይ እነርሱ ከጨመሩት መጻሕፍት ውጪ፣ መጽሐፍ ቅዱስ በቂ እንዳልሆነ ወይም የእነርሱ መጻሕፍት መጽሐፍ ቅዱስን እንደሚተኩ ወይም ደግሞ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እንደሚስተካከሉ ማመናቸው ብቻ ሳይሆን፣ ዐልፎ ተርፎም እነዚህ መጻሕፍት በ66ቱ ቅዱሳት ጽሑፎች ላይ ጥላቸውን እንዲጥሉ ይደረጋል—መጽሐፍ ቅዱስ የሚብራራው ከእነዚህ መጻሕፍት እንጻር ነው። እንዳንዶች ደግሞ የእፈታት ሥርዐቱን ይጥሳሉ።

5. "...ከክርስትና እምነት መሠረታውያን አስተምህሮዎች መሻል አንድ ወይም ከአንድ በላይ ትምህርት የሚክዱትን..."

የክርስትና እምነት መሠረታዊ አስተምህሮ የሚባሉት፣ ክርስትናን ክርስትና የሚያሰኙት ትምህርቶች ናቸው። ለዚህም ነው ዋልተር ማርቲን፣ "በአጭሩ ኑፋቄ ማለት፣ ርቱዕ[26] ከሆነው የክርስትና አስተምህሮ ዐበይት ትምህርቶችን የሚክድ ማለት ነው"[27] የሚለው።

[26] "ርቱዕ" ማለት ቀጥተኛ ወይም ትክክለኛ ማለት ነው።

[27] *Walter R. Martin, Rise of the Cults (Santa Ana, Calif: Vision House, 1977), 11.*

መሠረታዊ የሚባሉት ክርስቲያናዊ አስተምህሮዎች፣ የእምነቱ ጽኑ አዕማድ ናቸው። እነዚህም አስተምህሮዎች ትምህርተ ሥላሴ፣ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው መሆኑን፣ ክርስቶስ በአካለ ሥጋ ከሙታን እንደ ተነሣ፣ ክርስቲያኖችም በዚሁ መንገድ ከሙታን የሚነሡ መሆኑን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የፈጸመው የድነት ሥራ ብቻ ለድነት ዋስትና መሆኑ እንዲሁም ድነት በጸጋ አማካይነት በእምነት መሆኑ ናቸው። እነዚህ የክርስትና እምነት መሠረታውያን ባሕርያት ናቸው። ከእነዚህም መሠረታውያን ትምህርቶች ማፈንገጥ ኑፋቄ ነው። እነዚህ አስተምህሮዎች ክርስትና ያለፈበት ታሪካዊ ዐሰት መሆናቸውን ቃለ እግዚአብሔር ያስተምረናል (ማቴ. 28÷19፤ ዮሐ. 8÷24፤ 1ቆሮ. 15፤ ኤፌ. 2÷8-10)። እንደ ቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት፣ እነዚህን መሠረተ እምነቶች ክዶ የዘላለምን ሕይወት ተስፋ ማድረግ አይቻልም።

እንዳንድ ጊዜ ሰዎች መሠረታዊ የሆነውን ክርስቲያናዊ አስተምህሮ፣ ከደቃቅ (ከንዑስ) ትምህርቶች ጋር ይቀይጡታል፤ ይህ ግን ስሕተት ነው። ሰምሳሌ:— አንድ ሰው፣ "በወጎኒ የነበሩ ነፍሳት" (1ጴጥ. 3÷19) ማን እንደ ሆኑ በሚሰጠው ገለጻ ሊሳሳት ይችላል፤ ይህ ስሕተት ግን እንደ ትልቅ ስሕተት ሊቈጠር ግለሰቡንም መናፍቅ ሊያሰኘው አይችልም፤ ትንታኔው ከመሠረታዊው የክርስትና ትምህርት ጋር አስካልተቃረነ ድረስ።

መ. አባይ ነባይ ነገረ መለኮታዊ አማራውና ፍካሬው

መናፍቃንን በአስተምህሮአቸው በትክክል መግለጽ እንደ ቻልነው፣ በዙሪያችን እንደ እንጉዳይ የፈሉትንም አባይ ነባዮች በትምህርታቸውና በምግባራቸው በትክክል መግለጽ የምንችል ይመስለኛል። እንግዲያው አብዛኞቹ አባይ ነባዮች ላይ የሚስተዋሉትን ነገረ መለኮታዊና ምግባራዊ አካሄድ ነቅሶ በማውጣት፣ "አባይ ነባይ" ሰሚለው ሐረግ፣ ነገረ መለኮታዊ ይዘቱንና እጠቃቀሙን እንወስን።

1. የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናትን መሠረተ እምነት እንከተላለን የሚሉ

መናፍቃን የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናትን መሠረተ እምነት በይፋ በመካድ የራሳቸውን ሃይማኖታዊ ድርጅት ክፍተው የሚንቀሳቀሱ ሲሆኑ፣ አብዛኞቹ አባይ ነባዮች ግን፣ በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ተስግስገው የሚገኙ ናቸው።

የራሳቸውም ሃይማኖታዊ ድርጅት ክፍተው የሚንቀሳቀሱት እንኳ፣ ራሳቸውን የሚገልጹት የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናትን አስተምህሮ እንደሚከተሉ አድርገው ነው። በዚህ አግባብ፣ መናፍቃን የውጭ ወራሪ ሲሆኑ፣ አባይ ነባዮች ደግሞ የውስጥ ቦርቧሪ ናቸው ማለት የሚቻል ይመስለኛል።

አንዳንዶቹ ደግሞ ክእናት ቤተ ክርስቲያናቸው ተደብቀው፣ በግለሰቦች ቤት ውስጥ ስዎችን እየሰበሰቡ ይተነብያሉ፤ ይገልጣሉም። በዚህ ወቅት የሚሰበሰበውም ስጦታ፣ በአባይ ነባዮቹ ኪስ በቀጥታ እንዲገባ ይደረጋል።

በአምልኪቸውም ወቅት በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የሚዘመሩ መዝሙሮችን ይጠቀማሉ። እንዲያውም አንዳንዶቹ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ዕውቅ ዘማሪዎችን በየመድረክቻቸው አብዝተው በመጋበዝ በስፋት ይታወቃሉ። ይህ ደግሞ መዝሙር የሚወደውን ወጣት ትውልድ በቀላሉ የሚማርክ አካሄድ ነው። በመዝሙር ታጅሎ የሚቀርብለት ትምህርትና ሥነ ምግባር ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያለመሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ጋር የሚጻረር እንዲሁም ኢሥነ ምግባራዊ የሆነ ነው።

የአምልክ ዘይቤያቸውም ክብዙ አንጻር ከወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት የሰንበት አምልክ ዘዬ ጋር ተቀራራቢ ነው።

2. ትንቢቶቻቸውና ተኣምራቶቻቸው ስሕተት እንደ ሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠባቸው

እነዚህ አባይ ነባዮች በተለያዩ ጊዜያት ይሆናሉ በሚል የጊዜ ሰሌዳ ጠቅሰው፣ የተናገሩባቸው ትንቢቶች እውነት ሲሆኑ አልታዩም። ይልቁንም "ትንቢቶቻችሁ ስምን እውን ሲሆኑ አልታዩም?" የሚሰውን መሠረታዊ ጥያቄ አናንቀው ሲያልፉ፣ አለያም ጉዳዩ ስምን አውን አንዲልሆነ ማብራሪያ ስመስጠት፣ የሦዕመኑ መንፈሳዊ ዕድገት እንደማይመጥን ሲናገሩ ተደምጠዋል። አንዳንዶቹ ደግሞ፣ ትንቢቱ በአንዳንድ ስውር ምክንያቶች፣ አምላክ አዙን አንዳይሆኑ እንዳደረገ ይናገራሉ[28]።

ፈውስቸውም ቢሆን በግርግር እንጂ፣ ዕውቅና ባለው ሐኪም የተረጋገጠ አይደለም። በአንድ አካባቢ ነዋሪዎች ዘንድ በህመሙ የሚታወቅ ስው ከበሽታው ሲፈወስ አልታየም። ክውስጥ ደዌ ተፈውሳችኋል የተባሉትም ስዎች፣ በበሽታቸው አስከ ወዲያኛው አንዳንቀላፉ በርካታ መረጃዎች አየወጡ ነው።

3. አብዛኞቹ አባይ ነባዮች "የእምነት እንቅስቃሴ" አስተምህሮን የሚከተሉ ናቸው

አብዛኞቹ አባይ ነባዮች፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ "የአምነት አንቅስቃሴ"[29] አስተምህሮ በመባል የሚታወቀውን

---

[28] ትንቢቶቹ እውነት ሆነው ቢገኙ እንኳ፣ የትንቢቶቹ እውን መሆን ከአምላክ ለመገኘታቸው ዋስትና ሊሆን አይችልም።

[29] በእንግሊዝኛው *Word of Faith Movement* ወይም *Prosperity Gospel* በመባል የሚታወቀው እንቅስቃሴ ነው። የእንቅስቃሴው መሥራች *E.W. Kenyon* ሲሆን፣ አስተምህሮውን በማስፋፋት ረገድ በቀዳሚነት የሚጠቀሰው *Kenneth Hagin Sr.* ነው። በአሁኑ ጊዜ ይህን አስተምህሮ በማሠራጨት አገር እያጠፉ ያሉት የሚከተሉት ስዎች ናቸው ከእነዚህም ውስጥ የአንዳንዶቹ መጻሕፍት በአማርኛ ተተርጉሞ ለንባብ ቀርቧል—*Kenneth Copeland, Benny Hin, Robert Tilton, Marilyn Hickey, Paula White, Joyce Meyer, Paul and Jan Crouch, John Avanzini, Jerry Savelle, Morris Cerullo, Oral Roberts, TD Jakes, Brian Houston-Hillsong, Joel Osteen, Rod Parsley, Robert Morris, Carl Lenz, Rodney Howard-Browne, Peter*

ትምህርት የሚክተሉ ናቸው። ስዚህም ነው፣ "ቃል አወጣብሃለሁ"፣ "ቃል ዐውጅብሃለሁ"፣ "መርገምህን አስብራለሁ"፣ "ቱጃር ትሆናለህ"፣ "በሽታ አይነካህም"፣ "ሥራ ታገኛለህ"፣ "በእምነት እንጂ በላብህ ጥረህ ግረህ አትበላም"፣ "አንተ በአምላስ መለኮት የተፈጠርህ ትንሽ አምላክ ነህ" ወዘተ በሚለው ንግግራቸውና ትምህርታቸው በስፋት የሚታወቁት። እነዚህ ንግግሮችና ትምህርቶች ደግሞ "የአምነት አንቅስቃሴ" በመባል ክሚታወቀው መናፍቃዊ ትምህርት በቀጥታ የተቀዱ፣ አሰያም ትምህርቱ ትክክል ነው የሚሰውን ታሳቢ ያደረጉ አስተሳሰቦች ናቸው።

4. የአንድ ሰው ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ የሚክተሉ

የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት የተለያዩ አስተዳደራዊ ሥርዐቶችን የሚክተሉ ቢሆንም[30]፣ በአባይ ነባዮቹ የሚመሩ አብዛኞቹ ቤተ ክርስቲያናት ግን ባለ ራእይ፣ የአግዚአብሔር ሰው፣ ሐዋርያ፣ ነቢይ፣ መሥራች ወዘተ በሚባሉት ግለሰቦች አምባገነናዊ አስተዳደር የሚተዳደሩ ናቸው። ብዝኃዊ አስተዳደር እንክተላስን የሚሉት እንኳ፣ የሽማግሌዎች ቦርድ ተጠሪነቱ ለጠቅላላው ጉባኤ ሳይሆን ለድርጅቱ መሥራች ግለሰብ ነው።

በርካታ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ቢኖሯቸው እንኳ፣ እያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ተጠሪነቱ ለመሥራቹ ወይም "ለባለ ራእዩ" ግለሰብ እንጂ፣ ለጎብረት አመራር አይደለም።

Popoff, Juanita Bynum የዚህ አስተምህሮ ታዋቂ አፍሪካውያን መምህራን ደግሞ፣ *Chris Oyakhilome, David Oyedepo, Victor Atokolo,* በአስተምህሮው ላይ ሰፊ ማብራሪያ ከፈለጉ የዚህ መጽሐፍ ጸሓፊ፣ የእምነት ወይስ የክህደት እንቅስቃሴ በሚል ርእስ ከወንድም ምኒልክ አስፋው ጋር ያዘጋጀውን መጽሐፍ ይመለከታል። በዚህ መጽሐፍ መጨረሻ ዋቢ መጻሕፍት በሚሰው ዝርዝር ውስዋ በእንቅስቃሴው ላይ ሐስ የሚስነዘሩ በርካታ መጻሕፍት በዝርዝር ቀርበዋል። እነዚህን መጻሕፍትን እንዲመለከቷቸው ክልብ እናበረታታልን።

[30] ሥልጣን ተዋረዳዊ አስተዳደር፣ የፕርስቢቴሪያን ወይም የፌድራል አስተዳደር፣ ማነበረ ምዕመናዊ አስተዳደር፣ ኢጥንኛ አስተዳደር ናቸው።

5. የቤተ ክርስቲያኒቱ ሀብት ሀብታቸው የሆነ

ብዙዎቹ አባይ ነባዮች በቤተ ክርስቲያኒቱ ባንክና በራሳቸው ሃለብ መካክል ወይም በራሳቸው ሀብትና በቤተ ክርስቲያኒቱ ሀብት መካክል ቅንጣት ታህል ልዩነት የለም። የቤተ ክርስቲያኒቱ ገንዘብና ሀብት፣ ከቤተ ክርስቲያኒቱ ሀብት በቀጥታ ወደ ግለሰቦቹ ሀብት እንዲፈስ ይደረጋል። በዚህ አንጻር ሲታይ እነዚህ ቤተ እምነቶች የግል ድርጅቶች እንጂ፣ የቤተ ክርስቲያንን አስተዳደራዊ ሥርዐት የሚክተሉ ሃይማኖታዊ ተቋማት አይደሉም።

ለዚህም ነው በርካታ አባይ ነባዮች የቅንጦት ልብሶችን የሚለብሱት፣ እንደ ትንግርት የሚታዩ መኪናዎችን የሚነዱት፣ የተንጣለለ ሕንፃዎች ውስጥ የሚኖሩት። መቼም በምዕራቡ ዓለም እንደ ክዋክብት የሚታዩ የፊልም ተዋንያንና ባለሀብቶች በአለባበስ እነዚህን አባይ ነባዮች መስተካክል የቻሉ አይመስልም።

እንዲያውም በቅርቡ ሀብታቸው ገደቡን ስላለፈ፣ "ሽልማት" በሚል ሽፋን፣ ለአንዳንድ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ድርጎ መስፈር ጀምረዋል። ይህ ደግሞ የብዙዎችን ልብ ለመክፋፈል ትልቅ መሣሪያ የሆነ ይመስላል—"ብቻቸውን አይበሉም፣ በልተው ያበላሉ"፣ "የአምላክ ባለሟሎች ናቸው"... የሚሉ ደጋፊዎችን እንዲያገኙ ረድቷቸዋል[31]።

6. ዕውቅና በሌላቸው የነገረ መለኮት ተቋማት ውስጥ የተማሩ

ብዙ አባይ ነባዮች ዕውቅና በሌላቸው ትምህርት ቤቶች ውስጥ የተማሩ ናቸው። አንድ የትምህርት ተቋም ደረጃውን የጠበቀ

---

[31] ምናልባት ቤተ እምነቶችም ሆነ የአብያተ ክርስቲያናት ጉባረት፣ "ሽልማት" ሚባለው ጉዳይ ላይ በስፋት መምከር፣ የአቋም መግለጫም ማውጣት ሳያስፈልጋቸው የሚቀር አይመስሰኝም።

የትምህርት ተቋም ነው የሚባለው፣ ቢያንስ የሚከተሉትን መሠረታውያን መመዘኛዎች አሟልቶ ሲገኝ ነው፦— *(1)* በተቋሙ ውስጥ የሚያስተምሩ መምህራን፣ ዕውቅና ባለው ኮሌጅ፣ ዩኒቨርሲቲ ወይም ሌሚነርየም የተማሩ መሆናቸው፣ *(2)* የተማሪዎቹ ቅበላ ደረጃውን የጠበቀ መሆኑ (ለምሳሌ ተማሪዎቹ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በትክክል ማጠናቀቃቸው፤ አንዲሁም ለኮሌጅ ትምህርት የሚመጥን ነጥብ ማግኘታቸው)፣ *(3)* ለመማር ማስተማሩ ሂደት አመቺ የሆነ ሕንፃ ያላቸው መሆኑ፣ *(4)* የመማሪያ መጻሕፍቱ ደረጃቸውን የጠበቁ መሆናቸው (ለምሳሌ ጸሓፍያኑ ዕውቅና ባላቸው ተቋማት የተማሩ መሆናቸው፣ በሌሎችም መለል ትምህርት ቤቶች ውስጥ በመማሪያነት የሚያገለግሉ መጻሕፍት መሆናቸው ወዘተ)፣ *(5)* የትምህርት ቤቱ መርሓ ትምህርት (ካሪኩለም) ከመለል ተቋሞች አንጻር ደረጃውን የጠበቀ መሆኑ፣ *(6)* ደረጃቸውን በጠበቁ መጻሕፍት የተደራጀ፣ ቍጭ ብሎ ለማጥናት የሚያስችሉ ዕቃዎች (ወንበር፣ ጠረጴዛ) ተሟልተው የሚገኙበት ቤተ መጻሕፍት ያለው መሆኑ፣ *(7)* የሙሉ ጊዜ ተማሪዎችን ቢያንስ በዲፕሎማ ለሁለት ተከታታይ ዓመታት የሚያስተምር፣ ለመጀመሪያ ዲግሪ ቢያንስ አራት ዓመት የሚያስተምር ወዘተ መሆኑ፣ *(8)* ዕውቅና ከሚሰጥ ማዕከል ዕውቅና ያገኙ ወይም ዕውቅና ለማግኘት በሂደት ላይ ያለ ወይም ደግሞ ዕውቅና የተሰጠው የትምህርት ተቋም ዕውቅና የሰጠው የትምህርት ማዕከል መሆን ይኖርበታል[32]።

[32] *Accreditation Council of Theological Education in Africa—ACTEA* በአፍሪካ የነገረ መለኮት ትምህርት ቤቶችን ዕውቅና የሚሰጥ ዕውቅ ተቋም ነው። ይህ ተቋም በኢትዮጵያ ለሚገኙ በርካታ የነገረ መለኮት ትምህርት ቤቶች ዕውቅና ሰጥቷል። አንዳንዶቹም ዕውቅና ለማግኘት ከተቋሙ ጋር በመሥራት ላይ ናቸው። በዚህ ተቋም ዕውቅና ባገኙ የነገረ መለኮት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የተማሩ ስዎች፣ በሰሜን አሜሪካና በአውሮፓ በሚገኙ ዕውቅ ዩኒቨርስቲዎችና ሴሚናሪዎች ውስጥ በቀጥታ የድኅረ ምረቃ ወይም የዶክትሬት ዲግሪአቸውን መማር ይችላሉ። ስለዚህ በዚህ አጋጣሚ፣ ወላቶች ደረጃውን ባልጠበቀ የትምህርት ተቋም ውስጥ በመማር ዕድሜያቸውን በከንቱ እንዳያባክኑ መምከር እወዳለሁ።

በግጥሪቱ ኢትዮጵያ እንዲሁም በከተሞች አካባቢ የሚገኙ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች፣ ይህን መስፈርት አንዳማያሟሉ እሙን ነው። ነገር ግን አነዚህ የትምህርት ተቋማት ዲግሪ ወይም የማስተርስ ድግሪ እንሰጣለን የሚሉ ሳይሆን፣ አገልጋዮቻቸው መሠረታዊውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጠንቅቀው በማወቅ ለአገልግሎት የሚያዘጋጁ ማዕከላት ናቸው። ይህ አንዳለ ሆኖ የቃለ ሕያውት፣ የመሠረተ ክርስቶስና የመካነ ኢየሱስ አብያተ ክርስቲያናት ከላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉና ደረጃቸውን የጠበቁ የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጆችን እንደ ከፈቱ ዐውቃለሁ። ምናልባትም ሌሎች ይህንኑ መንገድ ተከትለው ይሆናል። አነዚህ ተቋማት ደግሞ አዲስ አበባ ለሚገኙ የድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤቶች፣ ተማሪን በማቅረቡ ረገድ ትልቅ አስተዋጽአ እያደረጉ ናቸው።

ብዙ አባይ ነባሮች ነገረ መለኮትን በኮሌጅ ደረጃ እንደ ተማሩ ያገልጻሉ። አንዲያውም አንዳንዶቹ ትምህርታቸው አስከ ድኅረ ምረቃ እንደሚዘልቅ በኩራት ሊያስረዱ ይሞክራሉ። ነገር ግን የተማሩባቸው ትምህርት ቤቶች፣ እንደ አነርሱ በአንድ አባይ ነባይ የተከፈተ፣ የገንዘብ ትርፍ ለማግኘት ሆነ ተብሎ የተቋቋመ፣ ነፋቂያዊ ትምህርታቸውን በአገራቱ ውስጥ ለማሰፋፋት በሚፈልጉ ግለሰቦችና ድርጅቶች የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግለት፣ አልያም ደግሞ፣ በ"ከማን አንሼ" መንፈስ የተደራጀ የትምህረት ተቋም ነው[33]።

[33] በዚህ በለሜን አሜሪካ፣ "ዲፕሎማ ሚልስ" *(Diploma Mills* "የዲፕሎማ መፍጨምቾች") የሚባሉ በርካታ ትምህርት ቤቶች አሉ። አንዲያውም አነዚህ ትምህርት ቤቶች፣ በአሜሪካን መንግሥት የሚታወቁት ወይም የምዝገባ ፈቃድ የወሰዱት እንደ ትምህርት ተቋም ሳይሆን፣ እንደ አትራፊ ድርጅት ነው። በጥቂት ወራት ውስጥ፣ ለው ያሻውን ዐይነት ድግሪ ዐትመው በመሰጠት፣ ብዙዎችን በድግሪ "አንበሽበሸዋል"። ከአነዚህ የትምህርት ተቋማት የተፈለገውን ያህል ደረጃ ያለው ዲፕሎማ ለማግኘት ትልቁ ቅድመ ሁኔታ፣ ድግሪውን የሚፈልገው ለው፣ የተጠየቀውን ገንዘብ ማዘጋጀት መቻሉ ብቻ ነው። ከአነዚህ ትምህርት ቤቶች የመጀመሪያ ድግሪ፣ የማስተርስ ድግሪ አንዲያውም የዶክትሬት ድግሪ የሸመቱ በርካታ ኢትዮጵያውያን አንዳሉ ስንቶች ያውቁ ይሆን? ከዚህም የተነሣ ብዙ

በዚህ ቦታ ልብ ልናደርገው የሚገባን አንድ ሁነኛ ነገር አስ ይኸውም መናፍቅ የምንለው መሠረታዊውን የክርስትና ትምህርት የሚያገድፈውን ሲሆን፣ አባይ ነባይ ግን ዐበይት የሚባሉትን ክርስቲያናዊ ትምህርቶች ላይክድ ይችላል።

ኢትዮጵያውያን አንድ ወይም ሁለት ዓመት በሚሰጥ ደረጃውን ያልጠበቀ ትምህርት "ዶክተር" የሚለውን ማዕረግ ተጐነጽፈዋል። አንዳንድ ሰዎች ሆነ ብለው የድግሪ አንዲሁም "የተምፌአለሁ" ጥማታቸውን ለማርካት፣ ከእነዚህ ትምህርት ቤቶች ድግሪ ሸምተዋል፤ አንዳንዶቹ ደግሞ ሳያውቁ የእነዚህ ድርጅቶች ሰለባ ሆነዋል። ይህ ጉዳይ በአሜሪካን መንግሥት ጭምር ትልቅ የመወያያ ጉዳይ እንደ ሆነ አየተነገረ ነው። በዐቅብተ እምነት እንዲሁም ሕዝብን በማንቃት ዙሪያ የሚሠሩ የመገናኛ ብዙኃን፣ በእነዚህ ግለሰቦች ላይ ጥናት በማድረግ ነገሩን ይፋ ቢያወጡ፣ የትምህርት ተቋማት ጥራታቸውን አንዲጠብቁ ከማስቻሉም ባሻገር፣ ወደ ፊት ለምች በሰሕተት ወይም በድፍረት ወደ እነዚህ ተቋማት በመሄድ ዕውቅና አንዳያሸምቱ ያስጠነቅቃቸዋል። የእነዚህን ትምህርት ቤቶች ዝርዝር ወይም ስለእነዚህ ትምህርት ቤቶች አስተማማኝ መረጃ የምትፈልጉ ሰዎች፣ የተለያዩ ድረ ገጾችን አንዲመለከቱ እንመክራለን።

ለምሳሌ:— https://www2.ed.gov/students/prep/college/diplomamills/diploma-mills.html

https://www2.ed.gov/students/prep/college/diplomamills/index.html

https://www.geteducated.com/college-degree-mills/161-college-degree-or-diploma-mill

https://en.wikipedia.org/wiki/Diploma_mill

https://www.consumer.ftc.gov/articles/0206-college-degree-scams

https://www.nytimes.com/2015/05/18/world/asia/fake-diplomas-real-cash-pakistani-company-axact-reaps-millions-columbiana-barkley.html

ክፍል ሁለት

ስለ አባይ ነባዮችና ስለ መናፍቃን መነጋገር ለምን አስፈለገ?



ይህን መጽሐፍ መጻፍ ያስፈለገው፣ ስለአባይ ነባዮችና ስለ መናፍቃን አስተምህሮ እንዲሁም አካሄድ በጥንቃቄ መመርመር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው። በዚህ ረገድ ያሉትን ዋና ዋና ምክንያቶች በአስላ መልክ አንመልከት:—

1. መጽሐፍ ቅዱስ ለስሕተት እንቅስቃሴዎች ትልቅ ትኩረት ሰጥቶአል

የነገረ መለኮት ሊቃውንት፣ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ከሚያስተምሩአቸው ትምህርቶች ውስጥ ስለ አባይ ነባዮችና ስለመናፍቃን የተሰጠው ትምህርት፣ ከአጠቃላዩ ትምህርት ሦስት አራተኛውን ቦታ እንደሚይዝ ያስረዳሉ። ይህ አውነት ቅዱሳት መጻሕፍት ስለስሕተት አስተማሪዎችና ስለትምህርታቸው ምን ያህል ትኩረት አንደ ሰጡና አኛም ሰጕዳዩ ትልቅ ትኩረት በመስጠት ማጥናት አንዳለብን ያስገነዝበናል (ዮሐ 10÷12፤ ማቴ. 7÷15፤ 24÷11፤ ማር. 13÷22፤ ማቴ. 5÷19፤ 15÷9፤ 1ጢሞ. 1÷7፤ 4÷2፤ 1ጴጥ. 3÷15፤ ማቴ. 12÷34:39፤ ማቴ. 13÷15፤ 21÷23-25፤ 27:28፤ 33፤ ማቴ. 15÷14)።

2. ክርስቲያኖች እምነታቸውን ከስሕተት አስተማሪዎች የመጠበቅ ሙሉ ኀላፊነት አለባቸው

ሐዋርያት፣ "ወዳጆች ሆይ፣ ስለምንካፈለው ስለ መዳናችን ልጽፍላችሁ አጅግ ተግቼ ሳለሁ፣ ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለተሰጠ ሃይማኖት እንድትጋደሉ እየመከርኋችሁ አጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ" (ይሁዳ 3)። "በአናንተ ስላስ ተሰፋ ምክንያት ለሚጠይቁአችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ፤ ነገር ግን በየዋህነትና በፍርሃት ይሁን" (1ጴጥ. 3÷15) ይሉናል። በትምህርታቸውና በስብከታቸውም የአባይ ነባዮችንና የመናፍቃንን ትምህርት ይኮንኑ ነበር (ሐሥ. 2÷14-41፤ 3÷12-26፤ 4÷8-12፤ ሐሥ. 6÷8-10፤ 7÷1-60፤ 13÷8-12: 16-46፤ 14÷1-4፤ 17÷1-4፤ 16-34)።

የእምነት አባቶች የምሥራቹን ቃል ከሚሸቃቅጡ አባይ ነባዮችና መናፍቃን ጠብቀው ለአኛ አንዳስተላለፉልን፣ አኛም

ለአናማውን ወንጌል ጠብቀን የማቆየት ዐደራ አለብን። ይህ ደግሞ የሚሆነው አስተምህሮአቸውን በሚገባ መርምረን ስናውቅ ብቻ ነው።

3. በከፍተኛ ፍጥነት በመስፋፋት ላይ ያለውን የስሕተት ትምህርት ጤናማ በሆነ አስተምህሮ መመከት (መገደብ) ያስፈልጋል

በርካታ አባይ ነባዮችና መናፍቃዊ አንቅስቃሴዎች የተጀመሩት፣ በዐሥራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን አንደ ሆነ መረጃዎች ይገልጻሉ። አንዲያውም ይህ አኛ ያለንበት ዘመን፣ "መንፈስ ግን በግልጥ:— በኋለኞቹ ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንትን ትምህርት አያደመጡ፣ ሃይማኖትን ይክዳሉ" (1ጢሞ. 4÷1) የሚለው ትንቢት የተፈጸመበት ጊዜ ይመስላል።

አባይ ነባዮችና መናፍቃን ከስናፍጭ ቅንጣት በአጅጉ ከሚያንስው አቶም (atom) ያነስ ጅማሬ ቢኖራቸውም፣ የአቶም ቦምብ ከሚያስከትለው ውድመት የበለጠ ጥፋት እያመጡ ነው። ስለዚህ አማኞች፣ "ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም መጥተዋልና" (1ዮሐ. 4÷1) የሚለውን ቃል በማጤን ማንነታቸውን ሊያውቁ፣ እንደ አግዚአብሔርም ቃል ሊቃወሟቸው ይገባል።

ከኒቂያ ጉባኤ በፊት የነበሩ አበው (ለምሳሌ:— ዮስጦስ ሰማዕት፣ ሔራኔሞስ፣ ቀሌምንጦስ ዘአስክንድርያ፣ ጠርጡልያኖስ) አምነታቸውን ከአይሁዶች፣ ከጣያት አምላኪዎች፣ ከኖስቲኮች አንዲሁም በዘመናቸው ከተነሡት መናፍቃዊ ትምህርቶች ሁሉ ጠብቀዋል።

በመካከለኛው ዘመን የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ታስተምረው የነበረውን ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት በመቃወም፣ ጤናማውን አስተምህሮ ያቀበሉንን የተሐድሶ መሪዎች በዚህ ቦታ ልንዘክራቸው ይገባል። ስለዚህ በከፍተኛ ፍጥነት በመሠራጨት ላይ ያለውን

የስሕተት ትምህርት፣ ጤናማ በሆነው አስተምህሮ መመከት የጊዜው አንገብጋቢ ጥያቄ ነው።

4. የስሕተት አስተማሪዎች ወደ ክርስቶስ መምጣት አለባቸው

አባይ ነባዮችም ሆነ መናፍቃን እንደ ማንኛውም ሰው መዳን ያስፈልጋቸዋል። ወደ ጠፉ ሰዎች መሄድ ደግሞ የክርስቲያኖች ሁሉ ኀላፊነት ነው። እግዚአብሔር ዐደራ ሰጥቶናል። ያም ዐደራ ስለሰዎች ሁሉ እውነተኛውን የምሥራች ቃል መንገር ነው። አባይ ነባዮች እውነተኛው የድነት መንገል አያስፈልጋቸውም ያለው ማነው?

አንድ ሐኪም የሕመምተኛውን በሽታ ከተረዳ በኋላ፣ ስበሽታው የፈውስ መድኀኒት እንደሚስጠው ሁሉ፣ እኛም በዘመናችን ያሉትን አባይ ነባዮችና መናፍቃን ወደ ክርስቶስ ማምጣት የምንችለው የአስተምህሮአቸውን ጠማማነት በሚገባ ስናውቅ ብቻ ነው።

5. ቤተ ክርስቲያን አባሎቿን ከስሕተት አስተማሪዎች መጠበቅ አለባት

ቤተ ክርስቲያን አባሎቿን ከተሳሳተ ትምህርት የመጠበቅ ሙሉ ኀላፊነት አለባት። ኀላፊነትና ተጠያቂነት ደግሞ እጅ ለእጅ ተያይዘው የሚሄዱ ነገሮች ስለሆኑ፣ ዛሬ የተሰጠን ኀላፊነት ነገ እንደሚያስጠይቀን መገንዘብ ይገባናል።

ቤተ ክርስቲያን አባሎቿን ከስሕተት ትምህርትና እንቅስቃሴ መጠበቅ የምትችለው፣ የመናፍቃንን ከንቱ ትምህርት ስለአባሎቿ ገላልጣ ስታሳይ ብቻ ነው።

ዛሬ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ሕዝባቸውን ከአባይ ነባዮች ጉባኤ መጠበቅ አልቻሉም። "እየመጡ ነው አትሄዱ" የሚል ቀጭን ትእዛዝ ቢያወጡ እንኳ የሚሰማቸው አልተገኘም። ዐየር ላይ

የተከልንውን ሕዝብ፣ ንፋስ እንዳያንቀሳቅሰህ ልንለው አንችልም። በእንጻሩ እውነትን በትክክል የተረዳ ክርስቲያን እውነት በሚመስሉ ተረቶች ይሞኛል ማለት አይቻልም። ስለዚህ ዋስትናችን መጽሐፍ ቅዱስን ማስተማር፣ ምክንዮአዊ ምርምርን ማጐልበት...ብቻ ሰዎች ከእውነት ጋር ተጣብቀው ለመኖራቸው ዋስትና ነው።

6. መጥፎ አስተምህሮ አገርንና ሕዝብን ይጐዳል (ያንቅዛል)

ትምህርት፣ ምግባርን አስከትሎ ይሄዳል። መጥፎ ትምህርትን የተቀበለ ሰው መጥፎ ፍሬ ያፈራል። የእግዚአብሔር ቃል፣ "ከእሾኽ ወይን፣ ከኩርንችትስ በለስ ይሰቀማልን? አንዲሁ መልካም ዛፍ ሁሉ መልካም ፍሬ ማፍራት ወይም ከፉ ዛፍ መልካም ፍሬ ማፍራት አይቻለውም" (ማቴ. 7÷16-18) የሚለው ስለዚህ ነው።

መጥፎ አስተምህሮ አገርንና ሕዝብን ይጐዳል። "አንድ ክርስቲያን ሥራን በመሥራት ላይሆን የሚፈልገውን ነገር አንደ ሆነለት (እንደሚሆንለት) በማመኑ ብቻ የሚሻውን ነገር ያገኛል" የሚለውን የእምነት እንቅስቃሴ መምህራንን ትምህርት የተቀበሉ ከ20 በላይ የአዲስ አበባ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች፣ በዩኒቨርሲቲው የሚያቆያቸውን ውጤት ማምጣት ባለመቻላቸው ከትምህርት ቤቱ መባረራቸውን አንድ መንፈሳዊ ድርጅት አስታውቋል[1]። ይህ ስቤተ ክርስቲያንም ሆነ ለአገር ትልቅ ጉዳት ነው። በቅርቡ በአባይ ነባዮች አማካይነት ቤተ ክርስቲያን ምን ያህል እየታመሰች እንዳለች ሁላችንም የምናውቀው ጉዳይ ነው። ይህ ጉዳይ የጨቅላ ክርስቲያኖችን ሕይወት ምን ያህል እንደሚጐዳ እንዲሁም ለወንጌል ሥርጭት ምን ያህል አንቅፋት እንደሚሆን መገመት አያዳግትም።

---

[1] የዩኒቨርስቲ ክርስቲያን ተማሪዎች ኅብረት ጋር የሚሠራው *EvaSu*፣ ከ15 ዓመት በፊት ይህን ጉዳይ ይፋ አድርጎ ነበር።

7. ሐሰተኛ መምህራንን በተመለከተ የምናጠናው ትምህርት እምነታችንን ያጠናክረዋል

አባይ ነባዮችም ሆኑ መናፍቃን ተሳስተዋል እንድንል የሚያደርገን፣ መሠረታዊ የሆኑትን የቃሰ እግዚአብሔር ትምህርቶች ባስመቀበላቸው ነው። አንድ ክርስቲያን ራሱንም ሆነ ቤተ ክርስቲያኑን ከአባይ ነባዮችና ከመናፍቃን እንቅስቃሴ ስመጠበቅ እንዲሁም የተሳሳቱ ስዎችን ወንጌል እንዲደርሳቸው በሚል የሚያደርገው ጥናት፣ መሠረተ እምነቱ ምን እንደሆነና ስምን በዚያ መልኩ ማመን እንዳስፈስገው በትክክል እንዲያውቅ ይረዳዋል።

8. ቤተ ክርስቲያን ከሐሰተኛ መምህራን ትምህርት መቅሰም አለባት

አባይ ነባዮችም ሆኑ መናፍቃን ሐሰተኞች ስለሆኑ፣ "ከእነርሱ የምንማረው አንዳች ነገር የለም" ብሎ ማስብ ቂልነት ነው። የስሕተት መምህራን ስዎችን የሚስቡበት፣ ትምህርታቸው እውነት ባይሆንም እንኳ፣ ስዎች የሚፈልጉት ነገር አነርሱ ዘንድ ስለሰ ነው።

አባይ ነባዮችም ሆኑ መናፍቃን ከፍተኛ ትኩረት የሚስጡት በቤተ ክርስቲያን ደካማ ጉኖች ላይ ስለሆነ፣ ለአነርሱ ዕድገት ምክንያት የሆኑትን ነገሮች መመርመር፣ ቤተ ክርስቲያን ድካሟን አሻሽላ መቅረብ እንድትችል ያግዛታል። ይህ ደግሞ ሲሆን የሚችለው አነርሱን በቅርበት ማጥናት ስንችል ብቻ ነው።

9. እግዚአብሔር በተጠንቀቅ እንድንቆም ይፈልጋል

የተስያዩ ስዎች መሠረተ እምነታችንን በተመለከተ እጅግ አስቸጋሪ የሚባሉ ጥያቄዎችን ይጠይቁናል። እነዚህን ጥያቄዎች በአጥጋቢ መንገድ መመለስ የምንችለው፣ በጥያቄዎቹ ላይ አስፈላጊ የሆኑ ዝግጅቶችን/ጥናቶችን ማድረግ ስንችል ብቻ ነው። "በእናንተ ስላስ ተስፋ ምክንያትን ስሚጠይቁዋችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት

ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ፣ ነገር ግን በየዋህነትና በፍርሓት ይሁን" (1ጴጥሮስ 3÷15)።

እንዲያውም መልስ ከመስጠትም ባስፈ፣ ከንቱ አስተሳስቦችንና አስተምህሮችን በትክክለኛው ትምህርት ከሥር መሠረታቸው ነቅለን እንድንጥላቸው መጽሐፍ ቅዱስ ያሳስበናል፣ "የስውንም ሐሳብ፣ በእግዚአብሔርም ዕውቀት ላይ የሚነሣውን ከፍ ያስውን ነገር ሁሉ እናፈርሳለን፣ በክርስቶስም ለመታዘዝ አእምሮን ሁሉ እንማርካለን" (2ቆሮንቶስ 10÷5)። ይህ ደግሞ እንዲያው በግብታዊነት እውን የሚሆን ጉዳይ አይደለም። የረጅም ጊዜ ዝግጅትንና ጥናትን ይፈልጋል (ትክክለኛውን መረጃ ማወቅ እንዲሁም ይህን ትክክለኛ መረጃ በተሳካ መልኩ በስዎች ልብ ማደረስን)።

እንዲያውም ሐዋርያው ጳውሎስ ወንጌልን እንዳጸናና እንድመክት፣ በእምላክ ተመርጫለሁ ይላል (ፊልጵ 1÷7:16)። በተመሳሳይ መልኩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ ለመምከርና ለመውቀስ የሚያስችል ዕውቀት ገንዘባቸው እንዲያደርጉ ያሳስባል (ቲቶ 1÷9፤ 2ጢሞቴዎስ 2÷24-25)። ይሁዳ በመልእክቱ ላይ ሕዝበ ክርስቲያኑ ሁሉ፣ ለስ ወንጌል እንዲጋደል ጥሪ ያቀርባል (ይሁዳ 3)። ከእነዚህ ምንባባት በትክክል የምንማረው ሐቅ፣ ዐቅብተ እምነት ትልቅ የሆነ አእምሮአዊ እንዲሁም የሥነ ልቡና ዝግጅት የሚፈልግ ጉዳይ እንደ ሆነ ነው።

አሉታዊ ንግግሮች

መሠረተ እምነታችንን እንዳናጸና፣ ራሳችንን ከመናፍቃን እንቅስቃሴ እንዳንጠብቅ፣ በስሕተት እንቅስቃሴ ውስጥ ያሉትን ስዎች ወደ ጤናማው መሠረተ እምነት እንዳንጠራ፣ በአጠቃላይ ዐቅብተ እምነትን የጉዞ መስመራችን እንዳናደርግ አከል

የሚፈጥሩብን በርካታ ንግግሮች/አስተሳሰቦች አሉ። በዚህ ረገድ ተዘውትረው ስሚደመጡ ሦስት ንግግሮች መልስ ልስጥ።

1. "ወንጌል የእግዚአብሔር ኀይል ነው፤ የእግዚአብሔርን ኀይል ልታግዝ አንተ ማነህ?"

እርግጥ ነው ወንጌል የእግዚአብሔር ኀይል ነው። ወንጌል ሕያው እንዲሁም የሚሠራ ትልቅ ኀይል አለው (*መዝ. 119፤ 2ጢሞ. 3÷16፤ ዮሐ. 17÷17፤ ዕብ 4÷12*)። ነገር ግን የወንጌል ኀያል ጕልበት በስዎች ሕይወት ውስጥ የሚሠራው፣ ስዎች የእምላክ ቃል መሆኑን አምነው ሊቀበሉ ነው (*ሮሜ 10÷17፤ 2ጢሞ 3÷15፤ መዝ 19÷7*)። ስዎች አምነው አንዲቀበሉ ደግሞ፣ ትክክለኛነቱን ማብራራትና የተጻራሪ ምልክታዎችን ከንቱነት መግለጽ ማሳየት የግድ ይላል። ስዚህ ነው ወንጌል አንድንሰብከው፣ አንድናስተምረው፣ አንድንኖረው የሚጠይቀው።

2. "ፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔርን ነገር ሊረዳ አይችልም፤ ታዲያ አንዴት ልታስረዳው ትሞክራለህ?"

"አባይ ነባዮችም ሆኑ መናፍቃን ድነት ያልገባቸው ፍጥረታውያን ስዎች ናቸው። ፍጥረታዊ ሰው ደግሞ የወንጌልን እውነት በጭራሽ የማይረዳ ከሆነ፣ ጥረታችን ዋጋ ቢስ ነው" የሚሉ ስዎች አሉ። መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ሰፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት ነውና አይቀበለውም፤ በመንፈስም የሚመረመር ስለ ሆነ ሊያውቀው አይችልም" (*1ቆሮ. 2÷14*) ማለቱ እሙን ነው። ነገር ግን ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ክፍል "አይቀበለውም" (ዴኮማይ δέχομαι) እንዲሁም "ሲያውቀው" (ጊኖስኮ γινώσκω) አይችልም ሊል፣ የቅዱሳት መጻሕፍትን አውነት "ገንዘቡ ሊያደርግ አይችልም" በሚለው ትርጕመ አነዚህን ሁለት ቃላት

በተለዋዋጭነት ተጠቅሚል። በሌላ ምንባብ ሐዋርያው የእግዚአብሔር ነገር ለስዎች ሁሉ ሊታወቅ እንደሚችል ገልጿል (*ሮሜ 1÷20*)። ፍጥረታዊ ሰው ችግሩ ያለመረዳት ሳይሆን ያለመቀበል ነው። ምክንያቱም ወንጌል የምግባር ለውጥን፣ ንጹሕ ሕይወትን የሚፈልግ ጕዳይ መሆኑ፣ ስዎች የተረዱትን ነገር ተግባራዊ እንዳያደርጉ አክል ሊፈጥርባቸው ይችላል። ነገር ግን የተረዱትን መቀበል እንኳ ቢሆን፣ የእምላክ እርዳታ ከታከለበት ስዎች ወንጌልን ያቀበላሉ። ክርስቲያኖች የምሥራቹን ቃል ለፍጥረት ሊሰብኩ፣ የሥራው ባለቤት የሆነው መንፈስ ቅዱስ፣ ስዎች በሚስሙት የወንጌል ቃል ወደ ራሱ ይጠራቸዋል። ሁላችንም ቢሆን ወንጌልን የተቀበልንው በዚህ መልክ አይደለምን?

3. "እውነትን መስበክ እንጂ፣ የሐሰት ትምህርት ምን እንደሚመስል ማስተማር ፋይዳ የለውም!"

"የባንክ ሠራተኞች ከጤናማው ብር ጋር የዕለት ተዕለት ትርርብ ስላላቸው፣ ሐሰተኛ ኖቶችን በፍጥነት የማወቅ ክሂሎት አላቸው"። የሚለውን የቀየ አባባል በመጠቀም፣ ስለሐሰተኛ እስተማሪዎች ማጥናት አያስፈልግም ወደሚለው ድምዳሜ ሊደርሱ ይታያል። ልክ ነው ጤናማውን አስተምህሮ በትክክል ማወቃችን፣ የተሳሳተውን ትምህርት በቀላሉ ለመለየት ይረዳናል።

ነገር ግን የዐቅብተ አምነት ቀዳማይ ዐላማ፣ ትክክለኛውን ትምህርት ከተሳሳተው ትምህርት እንዴት መለየት አንደምንችል ማሳወቅ ብቻ እይደለም። ነገር ግን የእነዚህ ስዎች ስሕተት ምን እንደ ሆነ፣ ለምንስ ሊሳሳቱ አንደ ቻሉ፣ ወደ ትክክለኛው መሠረተ እምነትም እንዴት ልናመጣቸው እንደምንችል፣ ስዎች ወደዚያ እንቅስቃሴ እንዳይሄዱ ምን ዐይነት ጥንቃቄ ማድረግ ይገባናል ወዘተ በሚሉ ፈርጀ ብዙ ተዛማጅ ጕዳዮች ላይ ጥናት የሚያደርግ

የትምህርት ዘርፍ ነው። እነዚህን ስዎች በወንጌል ለመድረስ እንዲሁም ክርስቲያኑ ማኅበረሰብ ራሱን ከአንቅስቃሴው እንዲጠብቅ ለማለታጠቅ፣ የመናፍቃኑንና የአባይ ነባዮቹን አስተምህሮ፣ የሥነ ትርጓሜ አካሄዳቸውን፣ ታሪካቸውን፣ የአስተዳደር መዋቅራቸውን፣ የቃላት አጠቃቀማቸውን ወዘተረፈ በጥልቀት ማወቅ ይለፈልጋል። ለለዚህ ትክክለኛውን ነገር ማወቅ ብቻ የዐቅብተ አምነትን መሠረታውያን ተልእኮዎች እንድንፈጽም ሊረዳን አይችልም።

ስለዚህ ይህ ዐይነቱ አስተያየት የዐቅብተ እምነትን ሥራና ተልእኮ በትክክል ካለማወቅ የሚለነዘር ግልብ ትችት ነው። በዐቅብተ እምነት አገልግሎት ብዙ መናፍቃንና አባይ ነባዮች ወደ ትክክለኛው መሠረተ አምነት መጥተዋል። ከመጥፎ ምግባራቸው ተመልሰዋል። ንጹሕ መሠረተ እምነት ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ ተደርጓል። ይህ ሁሉ እውን በሆነበት ሁኔታ፣ የዐቅብተ አምነትን አገልግሎት አያስፈልግም ማለት ስሕተት ነው።

ክፍል ሦስት

"በኤላው ላይ ልትፈርድ አንተ ማን ነህ?"



ምዕራባውያን፣ *"first things first"* ማለት ይወዳሉ። በሽርክቱ ሲተረጉም፣ "ዋነኛውን ጉዳይ፣ ዋነኛ አድርገህ በአፋጣኝ ከውነው" እንደ ማለት ነው[1]። በዚህና በቀጣዮቹ ተከታታይ ክፍሎች፣ ዐቅብተ አምነትን ከነሙሉ ጓዙ ተግባራዊ እንዳናደርገው ማለትም መሠረተ እምነታችንን ከጥቃት እንዳንከላከል፣ የምሥራቹን ወንጌል እንዳናውጅ፣ ከወንጌል ተጻራሪ ሆነው የቆሙትን ምልከታዎች ከሥር መሠረታቸው እንዳናመክን ጋሬጣ የሚሆኑብንን መሰናክሎች፣

[1] ይህ ቁም (የቃል በቃል) ትርጉም ሳይሆን፣ ሐሳብ ተሻጋሪ ትርጉም ነው።

የትምህርት ዘርፍ ነው። እነዚህን ለምች በወንጌል ለመድረስ እንዲሁም ክርስቲያኑ ማኅበረሰብ ራሱን ከእንቅስቃሴው እንዲጠብቅ ለማስታጠቅ፣ የመናፍቃኑንና የእባይ ነባዮቹን እስተምህሮ፣ የሥነ ትርጓሜ እካሄዳቸውን፣ ታሪካቸውን፣ የእስተዳደር መዋቅራቸውን፣ የቃላት እጠቃቀማቸውን ወዘተረፈ በጥልቀት ማወቅ ይስፈልጋል። ስለዚህ ትክለኛውን ነገር ማወቅ ብቻ የዐቅብተ እምነትን መሠረታውያን ተልእኮዎች እንድንፈጽም ሊረዳን እይችልም።

ስለዚህ ይህ ዐይነቱ እስተያየት የዐቅብተ እምነትን ሥራና ተልእኮ በትክክል ካለማወቅ የሚለነዘር ግልብ ትችት ነው። በዐቅብተ እምነት እገልግሎት ብዙ መናፍቃንና እባይ ነባዮች ወደ ትክለኛው መሠረተ እምነት መጥተዋል። ክመጥፎ ምግባራቸው ተመልሰዋል። ንጹሕ መሠረተ እምነት ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ ተደርጓል። ይህ ሁሉ እውን በሆነበት ሁኔታ፣ የዐቅብተ እምነትን እገልግሎት እያስፈልግም ማለት ስሕተት ነው።

ክፍል ሦስት

"በኬላው ላይ ልትፈርድ አንተ ማን ነህ?"



ምዕራባውያን፣ *"first things first"* ማለት ይወዳሉ። በሽርክቱ ሲተረጉም፣ "ዋነኛውን ጉዳይ፣ ዋነኛ እድርገህ በእፋጣኝ ከውነው" እንደ ማለት ነው[1]። በዚህና በቀጣዮቹ ተከታታይ ክፍሎች፣ ዐቅብተ እምነትን ክነሙሉ ዓዙ ተግባራዊ እንዳናደርገው ማለትም መሠረተ እምነታችንን ክጥቃት እንዳንከላከል፣ የምሥራቹን ወንጌል እንዳናውጅ፣ ክወንጌል ተጻራሪ ሆነው የቆሙትን ምልክታዎች ክሥር መሠረታቸው እንዳናመክን ጋሬጣ የሚሆኑብንን መሰናክሎች፣

[1] ይህ ተም (የታል በታል) ትርጉም ሳይሆን፣ ሐሳብ ተሻጋሪ ትርጉም ነው።

ከመንገድ ገለል እናደርጋቸዋለን[2]። እንግዲያው ወደዚያው እንዝለቅ፦—

ለው ፍጹም አይደለም። ማናችንም ብንሆን፣ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ እንስታለን፣ እንሳሳታለን። "ለው ሆኖ አይለት አንጨት ሆኖ አይጤስ የለም" የሚለው አገርኛ ቢሂል፣ ይህን የለውን ልጅ የፍጽምና ረሀብ፣ በርኅራኄ የሚያስታውስ ይመስለኛል። ለው ሁሉ የሚለት/የሚሳሳት ቢሆንም፣ ባለማወቅ ልለት እችላለሁ በሚል

[2] አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ምሁራን *apologetics* የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል፣ "ምክቱ እምነት" ብለው ተርጉመውታል (ነባሩ ትርጉም የግሪኩን ቃል "ወንጌልን መመከት" ብሎታል። ጥሬ ቃሉ በዚህ መንገድ መተርጉሙ፣ ለመ.ያዊ ግልጋሎት የዋለው ቃል በዚህ መንገድ ለመተርጉሙ ምክንያት የሚሆን አይመስለኝም)። እኔ ይህ ቃል አስተምህሮውን በትክክል የሚወክለው አይመስለኝም። ምናልባትም፣ "ሳይቮገር ጤፍ ብድር" እንዳሆን እፈራለሁ። በስፋት እየተሠራበት ያለው ዐቅብተ እምነት የሚለው ቃል፣ የጥናቱን ዘርፍ በትክክል የሚወክለው ከሆነ፣ አዲስ ቃል መቀመሩ አስፈላጊ አይደለም። ምክንያቱም የዐቅብተ እምነት የጥናት ዘርፍ፣ የክርስትናን አስተምህሮ ከጥቃት መመከት ብቻ ሳይሆን፣ ከክርስትና ጋር የሚጻረሩ ክንቱ ምልከታዎችንም መቃወም፣ የጥናቱ ሌላው ክፍል ነው። ዐቅብተ እምነት በሁለት ወገን የተሳለ ሰይፍ ነው። የምክቱው ወገን፣ አሉታዊ ዐቅብተ እምነት፣ በእንግሊዝኛው *negative apologetics* ተብሎ የሚጠራ ሲሆን፣ የማጥቃቱ ወገን ደግሞ፣ አዎንታዊ ዐቅብተ እምነት *positive apologetics* በመባል ይታወቃል። በዚህ አንጻር ሲታይ "ምክቱ እምነት" የሚለው ቃል፣ ሐሳቡን በግማሽ እንጂ በሙሉ የሚወክል አይደለም። ከዚህ በፊት እየተሠራበት የሚገኘው "ዐቅብተ እምነት" የሚለው ቃል ግን፣ "ምክቱ እምነት" ከሚለው በብዙ መልኩ በብዙ የተሻለ ነው። ምክንያቱም ዐቅብተ እምነት የሚለው ቃል፣ አሉታዊውንም ሆነ አዎንታዊውን ዐቅብተ እምነት የመወከል ዐቅም አለውና። በዚህ አንጻር "ዐቀበ" የሚለው ቃል ምን ያህል ባለጸጋ እንደ ሆነ እዩልኝ፦— "ዐቀበ፣ የሚጠብቅ፣ ጠባቂ፣ ተመልካች፣ ከልካይ ... ጠንቅቆ ማየት፣ መመልከት፣ መገመገም፣ ማቆየት፣ ማዘግየት፣ መመልከት ... አስጠበቀ፣ ዘበኛ አቆመ፣ ዐደራ ሰጠ"። ተገብሮ/ተደራጊ ግሥ ሲሆን ደግሞ፣ "አዕቀበ፣ አስጠበቀ፣ በበኛ አቆመ...ተጠነቀቀ" (አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሉ ገጽ 703-704 ይመለከቷል)። ጥንታውያኑም ሊቃውንት ይህንኑ ቃል ነው የሚጠቀሙት፣ "ካህናት ዐቃቢያነ ሕጉ ለእግዚ"።

ራሱን ለትችት በማጋለጥ፣ ከስሕተቱ ለመማር የሚፈልገው ግን አድማ ጥቂቱ ነው።

እንድ ለው ሌላውን ለው በተለያየ ምክንያት ሊተች ይችላል። አንዳንዱ ባላንጣውን/ወደረኛውን ለማሳጣት በሚል ለትችት ይነሣል። አንዳንዱ ደግሞ አውነትን ከመሻት፣ ለጽድቅ ከመቄርቈር እንዲሁም ገለሰቡን ለማስተካከል ከመፈለግ እኳያ፣ በቅን ልቡና ሙግቱን ያደራጃል። አንዳንዱ ርእሰ ጉዳዩን በውል ካለማስተዋል/ካለመረዳት በተሳሳተ ግንዛቤ ለሐሰ ይጣደፋል። እንዳንዱ ከሙግቱ ጭብጥ ይልቅ፣ ሙግቱ የቀረበበት መንገድ ወይም የቋንቋ እጠቃቀም ለትችት እንዲከለፈለፍ ያደርገዋል።

አንዳንዱ ልታይ ባይ ነው። ችሎታውን ለማሳየት፣ "እኔም አለሁ" ለማለት ትችት/ሙግት ያደራጃል። ይህ ዐይነቱ ለው፣ ሙግቱ የትኛውንም አቅጣጫ ቢከተል (ማለትም ትክክልም ቢሆን ወይም ባይሆን) ግድ የለውም። ዐላማው አስተያየት በመስጠት ሀልዎቱን ማሳወቅ፣ ዕውቅናን ማግኘት እንጂ፣ እውነትን ማሳየት አይደለምና። አለሁ የሚለውን ዐላማውን ከዳር ካደረሰ ተረጋግቶ ይቀመጣል።

ለትችት ልብን መክፈት ትልቅ ብልኀነት ነው። እሳውቃለሁ፣ አስተምራለሁ በሚባልበት መድረክ ላይ ማወቅ፣ መማር እለና። አእምሯዊ ዕድገቱ ያልተቀጨ ለው፣ ራሱን ለትችት አሳልፎ በመስጠት እውነትን ገንዘብ ያደርጋታል። ትላልቅ የትምህርት ተቋማት ትችትን፣ ሙግትን፣ ግምገማን፣ ውይይትን ለተማሪዎቻቸው በማስተማሪያነት የሚያቀርቡት በዚህ እግባብ ነው።

ለምች እኛን ለማላጣትም ሆነ፣ እኛን ለማረም ወይም ደግሞ በሌላ ስውር ዐላማ የትችት ደፍ ሊያዘንቡብን ይችላሉ። "ይህ ለው ለምን ለትችት ተነሣብኝ?" የሚለውን ምርምር ገታ እድርገን፣

"ትችቱ አግባብነት አለው ወይስ የለውም?"፣ "እውነትን መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም?" በሚሉት መሠረታውያን ነጥቦች ላይ ትኩረት ብናደርግ እንለመልማለን—እውነት ታለመልማለችና። አንዳንድ ጊዜ ለምች እውነት ኖሯቸው እንኳ፣ ሌላኛውን ወገን ለማሳጣት ወይም ደግሞ በሌላ አኩይ ምክንያት ትችት/ሒስ ለመስንዘር ሊነሡ ይችላሉ። የትችት/የሒስ ትክክለኛነት ከልብ ተነሣሥቶት *(motive)* ጋር አንዳችም ግጣም የላትም የሚባለው በዚህና በዚህ መለሱ ምክንያት ነው። የለውን የልብ ተነሣሥቶት *(motive)* በትክክል የሚያውቅ፣ ልብና ኩላሊትን የሚመረምረው ትልቁ እግዚአብሔር ብቻ ነው። እኛ የለምችን ልብ በመመርመር፣ የልብ መነሣሣታቸው ከዚህ ወይም ከዚያ የመነጨ ነው ለማለት ዐቅም የለንም። ግምት ልናቀርብ እንችላለን፤ ግን ፍርጥም ያለ ድምዳሜ ላይ መድረስ ያስቸግራል። ግምታችን በየትኛውም አንጻር ቢወድቅ ግን (ግለሰቡ ትክክለኛ ፍላጎት ኖሮት ወይም ትክክለኛ ያልሆነ መሻት ተገን አድርጎ ይነሣ) እርሱ ለሙግቱ ግብዐት ብዙ ፋይዳ የለውም። ትልቁ ቁም ነገር ትችትን/ሒስን በራሱ መመርመር፣ ትክክለኛነቱ እስከ ምን ድረስ ነው የሚሰውን ማጣራት የአስተንትኖው ዋነኛ ክፍል ነው።

የእኛ የኢትዮጵያውያን ባህል ትችትን የሚፈራ፣ ሒስን የሚጸየፍ ይመስለኛል። ከሙግቱ ይልቅ፣ "እንተ ማን ሆነህ ነው እኔን የምትተች" የሚለው ንግግርና አስተሳሰብ ቶሎ ይባርቅብናል፤ ብዙ ጉዳትም ያደርሳል። ይህ ደግሞ ከሙግቱ ይልቅ በሙግቱ እቅራቢና በሙግቱ ሐያሲ/ተቺ ማንነት ላይ የሚያነጣጥር ነው።

ሙግትን መጥላትና ግለሰብን መጥላት ፍጹም የተለያዩ ጉዳዮች ናቸው። የእኔ ሙግትና ትንታኔ ከወጪ ቀሪ "ቆሻሻ" ሊሆን ይችላል። ያ ማለት ግን፣ እኔ እንደ ግለሰብ "ቆሻሻ" ነኝ ማለት

አይደለም። ሙግቱ ተሳሳተ ማለት፣ እኔ እንደ ሰው ስሑት ነኝ ማለት እይደለም። ሙግትን ማበሻቀጥ ግለሰቡን ማበሻቀጥ አይደለም። ሙግትን መጣል ሙግቱን ይዞ የቀረበውን ሰው መጣል ማለት እይደለም። ስለዚህ የያዝነውን አሳብ ከእኛ ማንነት (ኑባሬያዊ ማንነት) መለየት ይኖርብናል።

እውነት የእኛን እስተሳሰብ ስትነቅፍ፣ ልንደሰት እንጂ ልንከፋ አይገባም። በመሠረቱ ስንሚገት/ስንከራከር እውነት በእኔ እንጻር ነው ያለችው፣ የአንተ ሙግት/ጭብጥ ስሕተት ነው እያልን እኮ ነው። እውነትን መውደድና ሐሰትን መጥላት ደግሞ ተገቢ ነው። እኔ "የይሖዋ ምስክሮችን" ትምህርት አምርሬ እጠላለሁ፣ ምክንያቱም አስተምህሮአቸው ስሕተት ነው ብዬ ስለማምን። እንደ ሰው፣ "የይሖዋ ምስክሮችን" መጥላት ግን ስሕተት ነው፤ ላደርገውም አያገባም። ይልቁንም የተሳሳተ እስተምህሮ ሰለባ በመሆናቸው ምክንያት ልንራራላቸው ያስፈልጋል። ስወዳቸው እኮ ነው በትክክል ላገለግላቸው የምችለው። ሐኪም በሽታን "እይወድም" በሽተኛውን ስለሚወድ ግን በሽታውን ሰማጥፋት የሞት ሽረት ትግል ያደርጋል። በአጠቃላይ አንድን ፅንሰ ሐሳብ፣ አስተምህሮውን ትክክል ነው ብለው ከሚያስቡ ለምች ወይም ትምህርቱን ከሚያራምዱ ሰምች ሰይተን ማየት ይኖርብናል።

ዐውቆ አጥፊና የዘመኑ አባይ ነባይ ትችትን እንደ ጦር ነው የሚፈራው። ሌባ ሌብነቱ ሲታወቅበት የሚሰማውን ስሜት ለመረዳት፣ አንደ እርሱ ሌባ መሆን አያስፈልግም። የደመ ነፍስ ሰውቀት *(a priori knowledge)* ይህ ዐይነቱን ጉዳይ በትክክል ያጣራልና። የሚሠራ ሰው እንደሚሰሳት እሙን ነው፣ መሳሳቱም ሲነገረው ለመታረም ክብዙ አንጻር ፈቃደኛ ይሆናል፣ ዐላማው አወነትን ወደ ለምች ልብ ማድረስ ነውና። ነገር ግን ለማታለል

ታጥቆ የወጣን ሰው፣ ማታለሉ ሲታወቅበት መበሳጨቱ አይቀርም። ይህ ዐይነቱ ለው ማታለል የአእምሮ ፍልስፍናው ብቻ ሳይሆን፣ ማንነቱ ሆኗልና በዚህ አግባብ "ሌባ" የሚለው ቃል ግብሩን ብቻ ሳይሆን ማንነቱንም ይጠቅሳል።

አባይ ነባሮችም ሆኑ ደጋፊዎቻቸው፣ "አንተ ማን ስለሆንህ ነው በሌላው ላይ የምትፈርድ"፣ "እንዳይፈረድብህ አትፍረድ"፣ "አስተዋይ ግን ዝም ይላል"፣ "አምላክ በጸሎት አንጂ በውይይት አይገኝም"፣ "ጌታ በመንፈስ አንጂ፣ በአእምሮ አይታወቅም" ወዘተ በሚሰው ንግግራቸው፣ በስፋት የሚታወቁ ይመስለኛል። ይህ ዐይነቱ ንግግር በአብዛኛው አውነተኛ ምርመራንና ሐቀኛ ምዘናን አጥብቆ ይጠላል። ሰዎች እነዚህን ንግግሮች የሚናገሩት፣ ራሳቸውን ከምርመራ ስመደበቅ ሊፈልጉ እንደ ሆነ መገመት አንችላለን። ስዚህ ዐይነቱ የአትመርምሩኝ መደበቂያዎች ጥሩ ምላሽ ካልሰጠን፣ የሐሰት መጫወቻ ነው የምንሆነው። ስለዚህ ይህንንና ይህን መሰል ጥያቄ በወኑ መመርመር፣ ክርስቲያናዊ ዐቅብተ እምነትን በትክክል ስመክወን ትልቅ ድርሻ አለው፣ ምክንያቱም ይህን መለሉ አነጋገር፣ በብዙ መልኩ አለምሮንም ሆነ አንደበትን ሸብፀ የመያዝ ጽኑ ጎያል ጉልበት አለውና።

በዚህ ክፍል፣ "አንዳይፈረድብህ አትፍረድ"፣ የሚለው ሐሳብ፣ ለአትመርምሩኝ መደበቂያ ሊሆን በፍጹም አንደማይችል እንዲሁም ምን ዐይነት መልእክት እንዲያስተላልፍ ታስቦ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ግልጋሎት ላይ እንደ ዋለ እንመረምራለን።

ሀ. በሌላው ላይ መፍረድ ስሕተት የሚሆንባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

በራስም ሆነ በሌሎች ሰዎች ላይ መፍረድ ስሕተት የሚሆንበት አግባብ አንዳለ ሁሉ፣ ትክክል የሚሆንበትም አካሄድ አለ። በዚህ ምዕራፍ ይህ የግራና ቀኝ አካሄድ አግባብነቱ ምን አንደ ሆነ አንመለክታለን[3]።

1. በግብዝነት የተሰጠ ፍርድ ውጉዝ ነው!

በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፣ በአንዲት አጥቢያ ደብር ውስጥ የቤተ ክርስቲያኒቱን ንብረት በበላይነት የሚቁጣጠር ካህን፣ "ገበዝ" ወይም "ቁስ ገበዝ" በመባል ይጠራል። በዚህ ረገድ "ሰዎች ስግብዝና ይሾማሉ" ሲባል፣ ስገንዘብና ለንብረት አስተዳደር ዐቃቤ ንዋይ ሆነው ይተከላሉ ማለታችን ነው። አኔ ግን "ግብዝ" ወይም "ተገበዘ" የሚለውን ቃል የተጠቀምሁት በዚህ ትርጉሙ ሳይሆን፣ አርሱ ራሱ በወደቀበት ተመሳሳይ ስሕተት አንዳንዴም በበረታ ስሕተት ራሱን ትክክል አድርጎ በማቅረብ፣ በሌሎች ላይ ሒስ የሚስነዝረውን ሰው በሚያሳይ ትርጉሙ ነው።

አንድ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ "ነውረኛ"[4] በሚባል ነጢአት ወድቆ፣ ምናልባትም መውደቁን ሰዎች በይፋ ተረድተው፣

---

[3] አንዳንድ መረጃዎችን ከሚከተለው መጽሐፍ ወስጃለሁ፣ *Robert M. Bowman, Jr., Orthodoxy and Heresy: A Biblical Guide to Doctrinal Discernment, (Grand Rapids, Mi.: Baker, 1992).*

[4] ቅዱሱ መጽሐፍ እንደሚል፣ የነጢአት ሁሉ ዋጋው ዘላለማዊ ሞት ነው፤ በዚህ አገባብ ነጢአት ሁሉ እኩል ነው ማለት እንችላለን። ቢያንስ በእኛ ማኅበራዊ መስተጋብር ውስጥ፣ ነጢአት ሁሉ እኩል ውድመት ያስከትላል ማለት የሚቻል አያመስለኝም። መሳደብና መገደል እንዴት አንድ ሊሆን ይችላል። "የሥነ ምግባር መርሖ" በሚለው መጽሐፍ፣ ይህን ጉዳይ በስፋት ስመመርመር መክሬ አድርጌ አለሁ።

በውድቀቱ ማግሥት፣ "ቅድስና ሰአግዚአብሔር" በሚል ርእስ ስብከተ ወንጌል አዘጋጅቶ፣ "ተቀደሱ!" እያለ እሳት ልሶ አሳት ጮርሶ ቢናገር፣ ድርጊቱ ብዙዎችን አንደሚያበሳጭ እሙን ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ቋንቋ፣ "ግመል አየዋጡ ትንኝ ማጥራት" (ማቴዎስ 23÷24) ወይም "በሌላው ያሰውን ጉድፍ እያመሰከቱ በራሳቸው ዐይን ያሰውን ምሰሶ ያለመመልከት" (ማቴዎስ 7÷3) የሚባሰው ዐይነት ይሆንብናል።

ይህ ዐይነቱን የሥነ ምግባር ስብከት ተቀባይነት የሚያሳጣው፣ ግለሰቡ ራሱን እያመጻደቀ፣ ሌላውን ሰጽድቅ መጥራቱ ነው። ነገር ግን "ወገኖቼ አኔም ሆንሁ እናንተ በዚህ ረገድ ወድቀናል!" ቢል የመጀመሪያውን ያህል ላያንገፈግፈን ይችላል። አንደ ግብዝነትም ላንቁጥረው እንችላለን። "ትንኝን እያጠሩ ግመልን የሚውጡ" (ማቴ 23÷24) ስዎች ግብዝነታቸው ያስቄጣን እንጂ፣ ንግግራቸው ወይም ስብከታቸው በራሱ ስሕተት ላይሆን ይችላል[5]። ሰዚህም ነው፣ ጌታ "ሰሕዝቡና ሰደቀ መዛሙርቱ አንዲህ ብሎ የነገራቸው፣ ጻፎችና ፈሪሳውያን በሙሴ ወንበር ተቀምጠዋል። ስሰዚህ ያዘዙአችሁን ሁሉ አድርጉ፣ ጠብቁትም። ነገር ግን አየተናገሩ አያደርጉትምና አንደ ሥራቸው አታድርጉ" (ማቴ. 23÷1-3)። ከዚህ የምንማረው አንድ ሰው በግብዝነት ትችት መስንዘሩ ምኞት ቢነሣንም እንኳ፣ ትችቱ ግን በራሱ ስሕተት ላይሆን ይችላል። አንዳንድ ጊዜ አግዚአብሔር ግብዝ የሆኑ፣ ልቡናቸው ንጹሕ ያልሆነ ስዎችን በመጠቀም ሊመክረን፣ ሊዘልፈን ይችላልና ሁል ጊዜ የሚተላሰፈውን መልእክት ከአስተላላፊው ማንነትና ምግባር ሰይተን ጉዳዩን መመልከት ይኖርብናል። በዚህ ረገድ ሐዋርያው ጳውሎስ የሚሰውን አናንብብ፡—

[5] ንጹሕ/ነቀፋ አልቦ ሕይወት ስስበከተ ወንጌል ወሳኝ የሚሆነው በዚህ አግባብ ነው (ማቴ 7÷1-5)።

"አንዳንዶች ከቅንአትና ከክርክር እንኳ ሌሎች ግን ከበጎ ፈቃድ የተነሣ ክርስቶስን ይሰብኩታል፤ እነዚህ ወንጌልን መመከቻ ለማድረግ አንደ ተሾምሁ ዐውቀው በፍቅር ይሰብካሉ፤ እነዚያ ግን በእሰራቴ ላይ መከራን ሊያመጡብኝ መሰሎአቸው፣ ለወገናቸው የሚጠቅም ፈልገው፣ በቅን አሳብ ሳይሆኑ ስለ ክርስቶስ ያወራሉ። ምን አስ ቢሆንም በሁሉ ጎዳና፣ በማመካኘት ቢሆን ወይም በቅንነት ቢሆን ክርስቶስ ይሰበካል ስለዚህም ደስ ብሎኛል" (ፊልጵ 1÷15-18)።

ሰዎች በተለያዩ ምክንያቶች ክርስቶስን ይሰብካሉ፤ አንዳንዶች ከበጎ ቅንአት፣ ሌሎች ደግሞ በጳውሎስ ሳይ መከራን ሰማምጣት በመፈለግ፣ አንዳንዶች ደግሞ ምድራዊ ጥቅም በመሻት ስብከተ ወንጌልን ያካሄዳሉ። ሐዋርያው ግን የልብ ፍላጎታቸውን አንጂ ስብከተ ወንጌላቸውን አልነቀፈም። አንዲያውም መሻታቸው ሞልቶ በሐዋርያው ሳይ መከራ ቢመጣ እንኳ፣ ስብከተ ወንጌላቸው ግን ትክክል መሆኑን ይገልጻል። ሙግት ለማዋቀር የተነሣንበት አሳብ ጠማማ መሆኑ፣ ሙግቱ ጠማማ ነው ወደሚል ድምዳሜ ሊያደርሰን አይገባም።

አንዳንድ ሰዎች፣ "ለው ሁሉ ፍጽምና የለውምና በሌሎች ሰዎች ላይ ሒስ መሰንዘር አግባብነት ይጐድለዋል" ይላሉ። ልክ ነው ማናችንም ብንሆን ፍጹምነትን የተጐናጸፍን ሰዎች አይደለንም። የሃግባራችን ብልሹነት ግን፣ በሌላው ላይ የምንስነዝረውን ሒስ/ትችት ስሉት አያደርገውም።

ልብ ልንሰው የሚገባን ሌላም ነጥብ አስ፤ ይኸውም፡— "በሌላው ላይ አትፍረድ" የሚሉን ሰዎች ራሳቸው፣ በአኛ ላይ እየፈረዱብን መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል። "አትፍረድ" የሚለው ተግሣፃቸው ራሱ ፍርድ ነው። ይኸውም "ንግግርህ ትክክል ወይም አግባብ አይደለምና አደበህ ጨምተህ ተቀመጥ" ማለት ነው።

በሌላው ላይ መፍረድ ስሕተት ከሆነ፣ እነርሱስ በእኛ ላይ፣ "አትፍረድ ዝም ብለህ ተቀመጥ" የሚል ፍርድ ለምን ይለጣሉ። በዚህ ረገድ "አትፍረድ" የሚለው አነጋገር በራሱ ፍርድ መሆኑ መታወቅ አለበት።

የዚህ ቢጤ የሆነ ሌላ አነጋገርም ገጥሞኛል። ሰሞኑን በፌስቡክ ውይይት መኻል እንዱ፣ "እስተዋይ የሚሆን ዝም ይሰል" (አሞ. 5÷13) የሚለውን ክፍል ከመጽሐፍ ቅዱስ በመጥቀስ፣ ውይይታችንን እንድናቆም መከረን። "ስነፍ ዝም ቢል ጠቢብ ሆኖ ይቁጠራል፤ ከንፈሩንም የሚቈልፍ ባለ አእምሮ ነው ይባላል" (ምሳሌ 17÷28) የሚለውን ክፍል መጥቀስ ፈልጌ ፈራሁ፤ ነቀፋ እንዳይመስልብኝ። ከዚያ መዝሙር 32÷3 ሳጥ አድርጌ አወጣሁ። ክፍሱ፣ ይህን እውነት ዝም የምል ከሆነ፣ "ዐጥንቶቼ ይበላሻሉ" የሚል ሐሳብ አለው። በእውነትና በሐሰት መኻል እንድንበይን ለዳኝነት ተቀምጠን ዝም ማለት እንዴት ይቻለናል? ሐሰት እገር ሲያጠፋ፣ እውነት ማቅ ሲለብስ "ዝምታ ጌጥ" ሊሆንልን እንዴት ይችላል? እኛ ክርስቲያኖች "አፍቃሬ እውነት ወአፍቃሬ ሚራክ[6]" ነን እያለን፣ ሐሰት እንደ ንዳድ እየተንቀለቀለ አገር ምድሩን ሲበሳ፣ ያለማለቀም ውርደት እንጂ ክብር ሊሆንልን አይችልም።

"እንዳችም አለተያየት ያለመስጠት" ትክክለኛ አካሄድ ከሆነ፣ "እስተያየት እትስጡ" የሚለው አስተያየት ራሱ ስሕተት ነው[7]—ንግግሩ ራሱን ይቃወማልና። ወደድንም ጠላንም ከፍርድ ሙሉ ለሙሉ ልንታቀብ እንችልም፤ ልንታቀብም አይገባንም።

እንድን ሰው ስሕተቱን ጠቅሰን ክጥፋቱ የማንመልሰው ከሆነ፣ ቢያንስ ባለማወቅ በሰሕተቱ ይቀጥላል። ራሱንም ሆነ አገርን

[6] ሚራክ ማለት ጥበብ ማለት ነው።

[7] እኔ ይህን ነው ጨቤ ጥቅስ የምለው። ክፍሉ ከሚናገርበት ሐሳብ አየወጨቁ ለሳላጉቸው የሚጠቀሙትን ለሥች ዐቅም በፊቱደው ሁሉ ማስቆም ይኖርብናል።

ይጐዳል። ልጆቻችን ሲያጠፉ የምንመክራቸው፣ ቢያሰፈልግ የምንቀጣቸው ከስሕተት መመለስ ትክክለኛ አካሄድ ስለሆነ እንጂ፣ እንባቸውን ማየት ፈልገን አይደለም። ክርስቲያኖች የእውነት አምባሳደሮች ነን የምንል ከሆነ ስሕተትን እያየን ዐይናችንን ልንሸፍን፣ ጆሮአችንን ልንከድን፣ አፋችንን ልንዘጋ እንችልም። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ሐሳችን ግብዝነት እንዳይበክለው አስጠነቀቀን እንጂ አትፍረዱ አሰለንም።

2. ግልብ የሆነ ፍርድ ውጉዝ ነው!

"ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ቅን ፍርድ ፍረዱ እንጂ፤ በመልክ አትፍረዱ" (ዮሐ. 7÷24) የሚለው አነጋገሩ፣ ፍርድን ሁሉ ገደል የሚከትት አይደለም። ርእሰ ጉዳዩን በጥልቀት የመረመረ ፍርድ ትክክል ሲሆን፣ ጉዳዩን ከላይ ሳዩ በግልቡ በመመልከት ወደ ሐሰ መክነፍነፍ ግን ትክክል አይደለም።

ከላይ ለማየት እንደ ሞከርነው ግብዝነት ያለበት ፍርድ/ሐስ ትክክል በእንጻሩ ደግሞ ስሕተት ሲሆን ይችላል፣ ግልብ ትችት ግን ዘየትኛውም ጊዜ፣ በማናቸውም ሁኔታና ዐታ ስሕተት ነው።

3. ዐቅምን ያላገናዘበ ፍርድ ውጉዝ ነው!

ከሰብአውያን ችሎታና ዐቅም በላይ የሆኑ በርካታ ርእሰ ጉዳዮች አሉ። ለምሳሌ፣ "ድነት ያገኘ ለው ማን ነው" የሚል ጥያቄ የሰበአውያን ክልል አይደለም። ይህ ዐይነቱ ብያኔ የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ድርሻና ኀላፊነት ብቻ ነው (ዮሐ. 5÷22-23፤ ሐሥ. 17÷31)። ስለዚህ በዚህ ጉዳይ ሳይ የሚሰጥ ፍርድ ዐቅሙን ያላገናዘበ፣ መስመሩን የሳተ ነው። ይህ ማለት ግን ሰዎች ወደ ድነት እንዲመጡ የማሳሰብ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት አድርገን ድነትን የመተንተን ዐቅም የለንም ማለት አይደለም። እኛ መንገዱን

የመጠቆም ዐቅም አንዲሁም ኀላፊነት ተሰጥቶናል። የመንገደኛውን ማንነት ማለትም ድነት አለው ወይስ የለውም የሚለውን ጉዳይ የማወቅ ችሎታ ግን አልተሰጠንም፤ መንገዱን እናውቃለን እንጂ መንገደኛውን ልናውቅ አንችልም። ጌታ የምጽአቱን ቀን በተመለከተ፣ "ይህ ለእናንተ አልተሰጣችሁም" ማለቱ አእምሮአዊ ዐቅማችን ውሱን መሆኑን የሚያሳይ ነው።

ሌላው መሠረታዊ ባልሆኑ ክርስቲያናዊ ጉዮች ላይ ፍርድ መስጠት አስፈላጊ አይደለም። ለምሳሌ ሐዋርያው ጳውሎስ፣ ስንበትን ስለማክበር እንዲሁም ሥጋ ወይስ አትክልት እንብላ በሚለው ጉዳይ ላይ፣ ምርር ክርር ያለ ሒስ/ትችት ውስጥ መግባት እንደማይገባን ነግሮናል (ሮሜ 14÷1-23)። ይህ ማለት ግን ጉዳዩን በጨዋ ደንብ መነጋገር አያስፈልግም ማለቱ አይደለም። በአጠቃላይ ክክልላችን እንለፍ ስንል፣ በክልላችን/ዐቅማችን በሚፈቅደው መጠን ፍርድ እንስጥ እያልን እንደ ሆነ ልብ ይሏል።

ለ. በሌላው ላይ መፍረድ ስሕተት የማይሆንባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

ክላይ (1) ግብዝ የሆነ፣ (2) ግልብ የሆነና (3) የሰብአውያንን ዐቅም ያላገናዘበ ፍርድ ስሕተት ነው ብለናል። በአንጻሩ ደግሞ የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች በማሞት ውስጥ ያካተተ ፍርድ ትክክል/አግባብ ነው።

1. እውነቱን ከውሸት ሠናዩን ከእኩይ የሚለይ ፍርድ ቅቡል ነው!

ቅዱሳት መጻሕፍት አንዲህ ዐይነቱን ብያኔ አንድናደርግ በአጽንኦት ያሳስቡናል። ይህንንም በግለሰብ ደረጃ ብቻ ሳይሆን፣ አንደ ቤተ ክርስቲያን በጀማ እንድናደርግ ይጠበቅብናል (ሮሜ 12÷2:9፤

1ቆሮ 12÷10፤ 14÷2፤ 1ተሰ 5÷19-22)። እነዚህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንባባት፣ እውነተኛ አስተርአዮን/መገለጥን፣ ሐሰተኛ ከሆነው መገለጥ መለየት አስፈላጊ ጉዳይ እንደ ሆነ በአጽንኦት ያሳስባሉ።

በመንፈስ ቅዱስ ተነድተናል፣ በእግዚአብሔር ተልከናል የሚሉ ነባዮች፣ ትንቢታቸውና ግልጠታቸው፣ ቀኖናዊ በሆኑት የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት መመዘን፣ መገናዘብ፣ መነጻጸር ሃንድ ይኖርበታል (ሐሥ. 17÷11፤ 2ቆሮ 2÷1፤ 3÷2፤ 1ዮሐ 4÷1-2፤ ይሁዳ 17)።

2. ንስሓ በማይገቡ ኀጥኣን ላይ የሚተላለፍ ፍርድ ቅቡል ነው!

ሐዋርያትም ሆኑ ክርስቶስ ነውረኛ የሆኑ ምግባሮችን የሚፈጽሙ ክርስቲያኖች ከክርስቲያናዊ ኅብረት መታገድ እንዳለባቸው፣ በተግሣጸ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መውደቅ እንዳለባቸው አስገንዝበዋል (ማቴ. 18÷15-18፤ 1ቆሮ 5÷9-13)። ምክንያቱም ይህ ዐይነቱ ምግባር የቤተ ክርስቲያንን ንጽሕና እንዲሁም ክርስቶስ የሞተለትን ክቡር ዐላማ ያክፋፋልና። ግለሰዐቹን በተግሣጸ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መጣል፣ የዘላለማዊ ዕጣ ፈንታቸውን የሚወስን አይደለም። ይልቁንም ተመክረው ተዘክረው እንዲመለሱ እንዲሁም ሌሎች የእነርሱን እኩይ አካሄድ እንዳይከተሉ ለማስገንዘብ ጭምር እንጂ። ይህ ደግሞ ለቤተ ክርስቲያን እንዲሁም ተግሣጹ ለወደቀበት ለው የሚጠቅም አካሄድ ነው።

3. ኑፋቄን በሚያስተምሩ ሰዎች ላይ የሚተላለፍ ፍርድ ቅቡል ነው!

ቅዱሳት መጻሕፍት ኑፋቄንና የኑፋቄ መምህራንን ያለአንዳች ማቅማማት በጽናት እንድናወግዝ በግልጽ ያስተምሩናል

(ሮሜ. 16÷17፤ ገላ 1÷6-9፤ 2ጢሞ 3÷16-4÷4፤ ቲቶ 3÷10-11)። እንዲያውም ኑፋቄን የሚያስፋፉ ሰዎችን በስም ጠቅሶ ማውገዝ አስፈላጊ የሚሆንበት ጊዜ አለ (2ጢሞ. 2÷17፤ 1ጢሞ. 1÷20፤ ነህ. 2÷19)።

ውሃ መስሎት መርዝ የሚጠጣን ሰው፣ ድርጊቱን በፍጥነትና በተቻለ መንገድ ሁሉ ማስጣል ትክክለኛ አካሄድ ነው። አውነተኛው ወንጌል የድነት መሠረት የሆነውን ያህል፣ ጠማማ ትምህርት ደግሞ የሲኦል አበጋዝ ነውና።

እንግዲያው መጽሐፍ ቅዱስ አትፍረዱ አላለም፣ ይልቁንም ፍርድ ተገቢ እንደ ሆነ፣ ተገቢ የሆነውም ፍርድ ግልብነት የሌለበት፣ ዐመፃን ያልተከተለ፣ ግብዝነት ያልተጣባው . . . በአንጻሩ እውነትን ያማከለ፣ ጽድቅን የተከተለ፣ ምርመራን መሠረት ያደረገ . . . ሊሆን ይገባዋል።

- "ቅን ፍርድ ፍረዱ እንጂ፣ በመልክ አትፍረዱ"
  (ዮሐንስ 7÷24)
- ፍርዳችሁ ያለግብዝነት ይሁን
  (ማቴዎስ 7÷15)
- "በፍርድ ዐመፅን አታድርጉ፣ ለድኻ አታድላ፣ ባለጠጋውንም አታክብር፣ ነገር ግን ለባልንጀራህ በአውነት ፍረድ"
  (ዘሌዋውያን 19÷15)
- "አፍህን ክፈት፣ በአውነትም ፍረድ" (ምሳሌ 3÷19)

ክፍል አራት

"አምላክ በቀባው ላይ እጅህን አታንሣ!"



አንዳንድ የበሽታ ዐይነቶች በአንድ የተወሰነ አካባቢ፣ በስፋትና በመጠን ተስፋፍተው አንደሚገኙ ይነገራል። በቀዝቃዛ አካባቢ ብቻ የሚገኙ በሽታዎች አንዳሉ ሁሉ፣ ሞቃት በሚባለው የምድር ወገብ አካባቢ በስፋት ተዛምተው የሚገኙ የበሽታ ዐይነቶችም አሉ። ለምሳሌ የሕክምናው ማኅበረሰብ፣ በመጠንና በዐይነት በምድር ወገብ አካባቢ ተስፋፍተው የሚገኙትን በሽታዎች፣ "በረሓማ በሽታዎች" *(tropical diseases)* ይላቸዋል።

ኑፋቄን በመቀመምና አባይ ነባዮችን አሠልጥኖ በማሠራጨት ረገድ፣ አሜሪካንን የሚተካከል የዓለማችን አገር ያለ አይመስለኝም። በእኔ ስሌት (ግምት እንደ ሆነ ልብ ይሏል) ዘጠና ከመቶ የሚሆኑት የክርስትና እምነት አባይ ነባዮችና መናፍቃን፣ መነሻቸው ምድረ አሜሪካ ነው—"የይሖዋ ምስክሮች"፣ "የሞርሞን እምነት"፣ "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን"፣ "የእምነት እንቅስቃሴ"፣ "ስባተኛ ቀን አድቬንቲስት"፣ "ክርስቲያን ላይንስ"፣ "አርምስትሮንጋውያን"፣ "ክርስቶ ዳልፊያንስ"...። እነዚህ አደገኛ ኑፋቄዎች በስፋት ተስፋፍተው እንዲሁም ተልቅ ውድመት አስከትለው የሚገኙት ግን፣ ባላደጉት ወይም በማደግ ላይ በሚገኙ አገሮች ነው።

ለዚህ ምክንያቱ እጅግ ብዙ ሲሆን፣ አስተምህሮውን በማስፋፋት ረገድ የገንዘብ ዐቅም መኖር፣ ሥነ ጽሑፍን በመሣሪያነት መጠቀም፣ ትምህርቱ በሚሠራጭባቸው አካባቢዎች ያለው ስው በቅዱላት መጻሕፍትም ሆነ በአጠቃላይ ዕውቀት ያለው ብስለት ደካማ መሆኑ እንዲሁም የእንግሊዝኛ ቋንቋ እንደ ሮማውያኑ ዘመን፣ የዓለም መነጋገሪያ ቋንቋ መሆኑ አሳብን በቀላሉ በሌላው ስው ልብ የማድረስ ችሎት እንዲኖር አድርጓል። እነዚህ እንግዲህ ከምክንያቶቹ መኻል ይመስሉኛል[1]።

በአንድ አካባቢ በመጠንና በዐይነት ፈልተው ከሚገኙ መናፍቃዊ ትምህርቶች መኻል፣ "ቅባት" የሚባለው የዚያ ወገን ነው። ይህ አስተምህሮ የተቀመመው በቀዝቃዛው ዓለም *(temperate climates)* ማለትም በምዕራባውያኑ አገሮች እንዲሁም በምዕራባውያኑ ቢሆንም፣ በብዛትና በፍጥነት በመስፋፋት ትልቅ ውድመት ያመጣው ግን፣ በመከረኛዋ አፍሪካ በተለይ ደግሞ፣ በኢትዮጵያ፣ በናይጀሪያ፣ በዩጋንዳና በደቡብ አፍሪካ ነው።

[1] የሥነ ጽሑፍን ጉልበት በተመለከተ፣ "ዐረ ተምህሮታዊነት የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት አብሾ፣ እርሾና ጌሾ" የሚለውን የመጨረሻ ክፍል ይመለከቷል።

ይህ ትምህርት ብዙ ፈርጅ አለው። በዚህ ክፍል ይህን ከተዘራ ያልታረመ ትምህርት፣ በቃለ እግዚአብሔር እንፈትሸዋለን። ይህን ማድረግ እንብዛም አድካሚ አይደለም። ስለቅባት የሚሰጠው ትምህርት በርካታ ጓዝ እንዲሁም አውዳሚ ቅርንጫፎች ያሉት ቢሆንም፣ የትምህርቱን ግራና ቀኝ ለመመርመር ግን ከብዙ አንጻር አስቸጋሪ አይደለም—ትምህርቱ ያስከተለውን ውድመት ያህል ሙስብስብ ተፈጥሮ የለውምና። በክርክሩ ዐቢይ ጭብጥ ላይ ብቻ ትኩረት ማድረግ፣ በሚከተሉት አምስት ነጥቦች ላይ እንወያያለን፣ ይኸውም:—

(1) የተለያዩ የቅባት ዐይነቶች አሉን?

(2) ቅባት ደረጃ አለውን?

(3) ቅባት ከአንዱ ሰው ወደ ሌላው ሰው ይተላለፋልን?

(4) "ዕጥፍ ቅባት" የሚባል ነገር አለን?

(5) "እግዚአብሔር በቀባው ላይ እጅህን አታንሣ!" ማለት ምን ማለት ነው?

ጉዳዩን በዚሁ ቅደም ተከተል ከመመልከታችን በፊት፣ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ቅባት የሚያስተምረውን ትምህርት በቅኝታዊ ዳሰሳ እንመልከተው።

ብሉይ ኪዳን

በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት፣ መቀባት/ቅባት የሚለውን አሳብ ለመወከል ሁለት የዕብራይስጥ ቃላት ግልጋሎት ላይ ውለው እናገኛለን። አንደኛው "ማሺያኽ" (מָשִׁיחַ) ሲሆን፣ ሌላኛው ደግሞ "ዛዒት" (מָיְשׁ) ነው—በአማርኛ "ዘይት" መባሉ፣ የሌማዊ ቋንቋዎችን ተወራራሽ ጠባይ አመላካች አይመስላችሁም?

የመጀመሪያው የዕብራይስጥ ቃል፣ ሃይማኖታዊ ሥርዐትን አመላካች ሲሆን፣ ሁለተኛው ቃል ደግሞ የመካከለኛውን ምሥራቅ

የፀሓይ ሐሩር ለመከላከል እንዲሁም ተከለ ሰውነትን ለመጠበቅና ለማስዋብ በአካል ላይ የሚፈለውን መዋቢያ ቅባት ያመለክታል (መዝ. 104÷15፤ ማቴ. 6÷17፤ ሩት 3÷3፤ 2ሳሙ 12÷20፤ ሕዝ. 16÷9)[2]።

ቅባት በሃይማኖታዊው ሥርዐት ውስጥ እውን ሆኖ የምናየው ከንጉሥ ዳዊትም በፊት እንዲያውም በመላው የብሉይ ኪዳን ምንባባት ውስጥ ነው (ዘሌ. 4÷3፤ 1ሳሙ. 2÷10፤ ኢሳ. 45÷1፤ ዘዳ. 28÷40፤ ሩት 3÷3፤ 2ሳሙ. 12÷20፤ 14÷2፤ 2ዜና 28÷15፤ ሕዝ. 16÷9፤ ሚኪ. 6÷15፤ ዳን. 10÷3)[3]። ይህ ሃይማኖታዊ እንድምታ ያለው ቃል፣ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ስባ ሁለት (72) ጊዜ ጥቅም ላይ ውሎ እናገኘዋለን።

በብሉይ ኪዳን ምንባባት፣ አንድ ሰው ተቀባ (በዕብራይስጥ ማሺያኽ) የሚባለው ቃል የሚከተሉትን ትርጉሞች ወክሏል:—

1. ለተለየ ዐላማ ወይም ተግባር መሾም/መለየም። ይህም መንፈስ ቅዱስን መቀበልንና ለእግዚአብሔር አገልግሎት ብቁ መሆንን የሚያመለክት ነው (ለምሳሌ የሚከተሉትን ምንባባት ይመለከቷል፣ ካህናት—ዘፀ. 28÷37፤ 40÷13:15፤ ዘሌ. 6÷22፤ ዘኍ. 35÷25፤ ነገሥታት—1ሳሙ. 9÷16፤ 10÷1፤ 15÷1፤ 16÷3:13 ነቢያት—1ነገ. 19÷16፤ ኢሳ. 61÷1)።
2. የእግዚአብሔርን ግርማ ሞገስ ማግኘት (መዝ. 23÷5፤ 92÷10)።
3. የእግዚአብሔር ሥልጣን ወይም መንፈስ፣ በተቀባው ግለሰብ ላይ መሆን (1ሳሙ. 16÷13፤ ኢሳ. 61÷1፤ 2ነገ. 9÷11-13)።

[2] James Swanson, *Dictionary of Biblical Languages With Semantic Domains: Hebrew (Old Testament)*, electronic ed. (Oak Harbor: Logos Research Systems, Inc., 1997).

[3] ዝኒ. ከማሁ።

እንግዲያው በብሉያት አንድ ሰው ተቀባ ሲባል፣ ተመረጠ፣ ተሾመ፣ ተለየ (ተቀደሰ)፣ እንዲሁም ለተጠራበት (ለተሾመበት) ሥራ ብቃትን፣ ክሂሎትን፣ ውክልናን ተጕናጸፈ ማለት ነው።

ሐዲስ ኪዳን

በብሉያት፣ "ማሺያኽ" (מָשִׁיחַ) አንዲሁም "ዛዪት"(זַיִת) የሚሉትን የዕብራይስጥ ቃላት ተክቶ ግልጋሎት ላይ የዋለው፣ "ካሪዝማ" (χρῖσμα) የሚለው የግሪክ ቃል ነው[4]። ይህም ቃል በሐዲስ ኪዳን የሚከተሉትን ትርጉሞች ይዞ ጥቅም ላይ ውሏል:—

1. ለውሳኔ ለማስዋብ ወይም ለመንከባከብ ሲባል ለዎች አካላቸውን የሚቀቡት ቅባት (ማቴ 6÷17፤ ሉቃ. 7÷46፤ አንዲሁም የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል ሩት 3÷3፤ ሚኪ 6÷15፤ መዝ 23÷5)።
2. ለእንግዳ የሚደረግን ጥንቃቄና ክብር ለማሳየት (ማቴ. 26÷7፤ ሉቃ. 7÷38)።
3. አስከሬንን መቀባት (ማር. 14÷8)።
4. ድውያን/በሽተኞች ይፈወሱ ዘንድ ጸሎት ለማድረግ (ያዕ. 5÷14፤ ማር. 6÷13)።
5. መንፈስ ቅዱስ በአንድ ሰው ላይ አንዳደረ/እንደ ኖረ ለማሳየት (2ቆሮ. 1÷21፤ 1ዮሐ 2÷20:27)።
6. ጌታ ኢየሱስን ለማሳየት (መዝ. 2÷2፤ ዳን. 9÷25:26፤ ኢሳ. 61÷1፤ ዮሐ. 1÷41፤ 4÷25-26፤ ሐሥ. 9÷22፤ 17÷2:3፤ 18÷4:28፤ ዮሐ 1÷32:33፤ ሐሥ. 4÷27፤ 10÷38)።
7. ሕዝበ ክርስቲያኑ (አማኞች ሁሉ) የተቀበሉትን መንፈስ ቅዱስ ለማመልከት (2ቆሮ. 1÷21፤ 1ዮሐ 2÷20:27)።

[4] James Swanson, *Dictionary of Biblical Languages With Semantic Domains: Greek (New Testament)*, electronic ed. (Oak Harbor: Logos Research Systems, Inc., 1997).

በሐዲስ ኪዳን ግሪክ መቀባት የሚለው ቃል፣ ክርስቲያኖችን በሙሉ በሚያሳይ ትርጉሙ ነው ጥቅም ላይ ውሎ የምናገኘው፦—

- "እናንተም ከቅዱሱ ቅባት ተቀብላችኋል፤ እንዲሁም ደግሞ ሁሉን ታውቃላችሁ" "καὶ ὑμεῖς *χρῖσμα* ἔχετε ἀπὸ τοῦ ἁγίου καὶ οἴδατε πάντες"[5] *(1ዮሐንስ 2÷20)*።
- "እናንተም ከአርሱ የተቀበላችሁት ቅባት በእናንተ ይኖራል" "καὶ ὑμεῖς τὸ *χρῖσμα* ὃ ἐλάβετε"[6] *(1ዮሐንስ 2÷27)*።
- "የአርሱ ቅባት ስለሁሉም ነገር ያስተምራችኋል" "τὸ αὐτοῦ *χρῖσμα* διδάσκει ὑμᾶς"[7] *(1ዮሐንስ 2÷27)*።
- "በክርስቶስ ከእናንተ ጋር የሚያጸናንና የቀባን እግዚአብሔር ነው" "ὁ δὲ βεβαιῶν ἡμᾶς σὺν ὑμῖν εἰς Χριστὸν καὶ *χρίσας* ἡμᾶς θεός"[8] *(2ቆሮንቶስ 1÷21)*።

በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ነቢያት፣ ነገሥታትና ካህናት ለአገልግሎት ሲለዩ/ሲመረጡ ይቀቡ እንደ ነበር፣ ይህም የመንፈስ ቅዱስ አብሮነት አብሯቸው እንዳለ የሚያሳይ ነው። በብሉይ ኪዳን መንፈስ ቅዱስ ያድር/ይኖር የነበረው፣ በእነዚህ አገልጋዮች ውስጥ ብቻ ነበር።

በሐዲስ ኪዳን ግን ይህ ፍጹም ተቀይሮ እንመለከታለን። ይኸውም መንፈስ ቅዱስ በሕዝበ ክርስቲያኑ ሁሉ በተናጠልም ሆነ በጋራ ከመኖሩ ባሻገር፣ መንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ያለደረገው ሰው

[5] *Kurt Aland, Matthew Black, Carlo M. Martini et al., The Greek New Testament, Fourth Revised Edition (With Morphology), 1Jn 2:20:27 (Deutsche Bibelgesellschaft, 1993; 2006).* አማርኛ ትርጉምና ግሪክኛ አጽንኦት የእኔ።

[6] ዝኒ ከማሁ። አማርኛ ትርጉምና ግሪክኛ አጽንኦት የእኔ።

[7] ዝኒ ከማሁ። አማርኛ ትርጉምና ግሪክኛ አጽንኦት የእኔ።

[8] *Kurt Aland, Matthew Black, Carlo M. Martini et al., The Greek New Testament, Fourth Revised Edition (With Morphology), 2 Co 1:21 (Deutsche Bibelgesellschaft, 1993; 2006).* አማርኛ ትርጉምና የግሪክኛ አጽንኦት የእኔ።

ክርስቲያን አንዳልሆነ ወይም ዳግም ልደት አንዳላገኘ ተገልጿል። መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ሕይወት የሚኖረው ደግሞ ስዘላለም ነው (ሮሜ. 8÷9፤ ዮሐ. 14÷16፤ ኤፌ 1÷13-14፤ 4÷30፤ 2ቆሮ. 1÷22፤ 1ቆሮ. 6÷19-20፤ 3÷16፤ ቈላ 1÷27)። ክርስቲያን በነጠሊት ሲወድቅ መንፈስ ቅዱስ ያዝናል ወይም የመንፈስ ቅዱስ ብርሃን ይዳፈናል (ኤፌ. 4÷30፤ 1ተስ. 5÷19)። ነገር ግን "በነጠሊታችን ብንናዘዝ ነጠሊታችንን ይቅር ሊለን ከዐመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው" (1ዮሐ. 1÷9)።

በብሉይ ኪዳን ግን መንፈስ ቅዱስ በተቀቡት አገልጋዮቹ ላይ አንካ የሚኖረው በጊዜያዊነት ነበር (ስምሌ ንጉሥ ሳያል 1ሳሙ. 16÷14 ንጉሥ ዳዊት 1ሳሙ. 16÷13፤ ከመዝሙር 51÷11 ጋር ያነጻጽሯል፤ ባስልኤል ዘፀ. 31÷2-5፤ መሳ. 15÷14፤ 1ዜና 12÷18፤ መዝ 51÷11፤ ሕዝ. 11÷5)።

የተሳሳቱ ግንዛቤዎች

ብሉያትም ሆኑ ሐዲሳት ስለ መቀባት ከሚናገሩት ምንባባት የምንማረው ቁም ነገር መኻል ዋነኞቹ፦— *አንደኛ፣* በሐዲስ ኪዳን ትባቱና ቀቢው መንፈስ ቅዱስ ሲሆን፣ መቀባት ደግሞ ስአግዚአብሔር መለየታችንንና የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ መሆናችንን አመልካች ነው። በብሉይ ኪዳን ያልተቀባ አገልጋይ አንደ ሌለ ሁሉ፣ በሐዲስ ኪዳንም ያልተቀባ ክርስቲያን የለም።

ሁለተኛ፣ በሐዲስ ኪዳን ቀቢውም ሆነ ቅባቱ ራሱ መንፈስ ቅዱስ ነው[9]። በአንጻሩ ስምችን በመቀባት ለበሽታ መጸለይ አግባብ ቢሆንም፣ በስምች ዐናት ላይ ዘይት አያፈስሉ ለአገልግሎት ተለይታችኋል የሚለው አካሄድ ግን ከሐዲስ ኪዳን ትምህርት ጋር

[9] እነዚህ ክፍሎች 1ዮሐ. 2÷20፡27፤ 2ቆሮ. 1÷21፤ ሉቃ. 4÷18 ከሚከተሉት ምንባባት ጋር ያነጻጽሯል ዘፀ. 29÷7፤ 40÷9፤ 2ነገ. 9÷6 ነገር ግን ለበሽተኛ የሚደረግ ጸሎት ከዚህ ጋር መቀላቀል የለበትም ያዕ. 5÷14።

በጭራሽ አብሮ የሚሄድ አይደለም። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ይህ ዐይነቱን እንግዳ ትምህርት የማስቆም ኀላፊነትና ሕዝቡን የማንቃት ግዴታ አለባት.[10]። በዚህ አግባብ ዘይት በማፍሰስ ስዎችን የሚቀቡ እንዲሁም "ጌታ፣ በዚህ ቤተ ክርስቲያን ስዎችን ትቀባልኛለህ ብሎኛል" የሚሉ፣ የአባይ ነባዮች ትምህርት ወይም ትንቢት መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደሉም።

ሦስተኛ፣ በብሉይ ኪዳን የቤተ መቅደስ ዕቃዎች ይቀቡ የነበረ ቢሆንም፣ በሐዲስ ኪዳን ግን ቍሳቍስ አይቀባም። ምክንያቱም በሐዲስ ኪዳን፣ መንፈስ ቅዱስ የሚኖረው ስው በሠራስት ቍስ ወይም ቤተ መቅደስ ሳይሆን፣ የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ናችሁ በተባሉት ክርስቲያኖች ውስጥ ነው።

አራተኛ፣ ሕዝበ ክርስቲያን ሁሉ ክርስቶስ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኙ አድርጎ ሲቀበል በመንፈስ ቅዱስ የተቀባ ስለሆነ፣ "እገሌ የተቀባ ስባኪ ነው"፣ "የተቀባ ዘማሪ ነው" ወዘተ የሚሉት አነጋገሮች መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደሉም፤ ስሕተት ናቸው።

አምስተኛ፣ ቅባት እንደ ጸጋ ስጦታ የሚለያይ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ ልዩ ልዩ የጸጋ ስጦታዎች እንዳሉ ቢያስተምርም፣ ልዩ ልዩ መቀባቶች/ቅባቶች አሉ የሚል ትምህርት የለውም። እንዲያውም አማኞች ሁሉ የተቀቡት ቅባት አንድ ዐይነት ቅባት ነው። መጠኑም አንድ ነው። ስለዚህ ዕጥፍ ቅባት፣ ወፍራም ቅባት ወይም ደግሞ ወርቃማ ቅባት፣ ብርማ ቅባት...የሚለው ትምህርት

[10] በቅርቡ አንድ ግለሰብ፣ "ዓመቱ ላይጠናቀቅ በሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን አምስት ስዎችን ትቀባልኛለህ" የሚል ትንቢት ሲነገረው የሚያሳይ ቪዲዮ ተመለከትሁ። በመሠረቱ ያ ግለሰብ እስከ ዛሬ ድረስ፣ ወደ ሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ዝር ማለት የቻለ አይመስለኝም። የሆነው ሆኖ ግን እየበሩ አንት "ሰነቢይነት፣ አንተ ለወንጌላዊነት...ተቀብተሃል" አያሉ በሰዎች ዐናት ላይ ዘይት ማፍሰስ የወንጌል ትምህርት አይደለም። የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናትም ትውፊት አይደለም። ይህ እውነት ከሆነ፣ "እየዞርህ ትቀባልኛለህ" የሚለው ትንቢት ከእግዚአብሔር ሊሆን በፍጹም አይችልም።

ስሕተት ነው። ክስሕተትነቱም ባሻገር በእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ ድነት አግኝተዋል በተባሉት አማኞች መካል ልዩነት የሚያበጅ፣ አማኞችን የሚያበላልጥ ነውረኛ ትምህርት ስለሆነ በግልጽ ሊወገዝ ይገባዋል።

ሰድስተኛ፣ የተቀባ *("The Anointed One")* የሚለው ሙያዊ ቃል በተጸውዖ ስምነት የሚያመለክተው፣ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ብቻ ነው (ሉቃስ 2÷26)። ስለዚህ ስዎችን "የተቀባ" አያሉ መጥራት ወይም ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን "የተቀባው" ብሎ መስየም ትክክል አይደለም።

1. የተለያዩ ዐይነት ቅባቶች አሉን?

መጽሐፍ ቅዱስ፣ አንድ ዐይነት ቅባት እንጂ፣ የተለያዩ ዐይነት ቅባቶች እንዳሉ አያስተምርም። በቅባት የተመሰለውም መንፈስ ቅዱስ አንድ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ልዩ ልዩ አገልግሎት (1ቆሮንቶስ 12÷5)፣ ልዩ ልዩ አሠራር (1ቆሮንቶስ 12÷6)፣ ልዩ ልዩ ስጦታ (1ቆሮንቶስ 12÷4) እንዳለ ይናገራል እንጂ፣ የተለያዩ ዐይነት ቅባቶች አሉ አይልም። ወርቃማ፣ ብርማ፣ ወዘተ የሚሉት ገለጻዎች በጸንስ ክሐዲስ ኪዳን አስተምህሮና ከሐዲስ ኪዳኑ የአግዚአብሔር ሕዝብ አንጻር ድርሳነ ፈጠራ ናቸው።

በመንፈስ ቅዱስ የተቀባ ነው (2ቆሮንቶስ 1÷21፤ 1ዮሐንስ 2÷20፡27)፣ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ነው (ዮሐንስ 14÷16፤ 1ዮሐ 2÷20፡27)፣ በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቀ ነው (ሐሥ. 1÷4-5፤ ሉቃስ 3÷3፡16፤ 1ቆሮ 12÷13)፣ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የሆንነው (ዮሐ. 13÷10፤ 15÷3፤ ሮሜ 8÷9፤ ዮሐ. 3÷5) አንዲሁም በመንፈስ ቅዱስ የታተምነው ዳግም በመወለድ የእግዚአብሔር ልጆች ስለሆንን አንጂ ((ዮሐንስ 7÷37-39፤ ኤፌሶን 1÷13፤ ገላትያ 3÷2፤ 2ቆሮንቶስ 1÷22፤ ኤፌሶን 4÷30)፣ በጽድቅ ከሌሎች ስለተሻልን፣ በዕውቀት ከሌሎች ስለበለጥን፣ በጥንካሬ ጽኑአን ስለሆንን ወዘተረፈ አይደለም። በእግዚአብሔር ቸርነት፣ በክርስቶስ ቤዛዊ ሥራ እንዲሁም በመንፈስ

ቅዱስ ርዳታ ብቻ ክርስቲያን ሆነናል፤ ለአገልግሎት ተሹመናል። በአጠቃላይ ክርስቲያኖች የተቀቡበት ቅባት በዐይነት *(quality)* ይለያያል የሚለው ትምህርት ስሕተት ነው።

2. ቅባት ደረጃ አለውን?

ቅባት ደረጃ አለው፤ ከዚህም የተነሣ አያደገ ይሄዳል የሚለውን ትምህርት የሚያስተምሩ ሰዎች፣ ለትምህርታቸው ግብዐት የሚጠቀሙት የዳዊትን ታሪክ ነው። እግዚአብሔር አምላክ፣ ዳዊትን ለመጀመሪያ ጊዜ የቀባው በቤተ ልሔም በቤተሰቡ ፊት በነቢዩ ሳሙኤል አማካይነት ነበር *(1ሳሙ. 16÷12-13)*። ሁለተኛ ጊዜ በይሁዳ ሰዎች ላይ ይነግሥ ዘንድ ዳግመኛ ተቀባ *(2ሳሙ. 2÷4-7)*። አዚህ ጋ ልብ ልንለው የሚገባን ነጥብ፣ ዳዊት በይሁዳ ሰዎች ላይ ንጉሥ ይሆን ዘንድ የተቀባው፣ በእግዚአብሔር ትእዛዝ እንዲሁም በነቢይ ወይም በካህን አማካይነት አልነበረም *(2ሳሙ. 2÷7)*። በሁለተኛ ሳሙኤል 5÷3 ላይ ዳዊት ከእስራኤል ሽማግሌዎች ጋር ቃል ኪዳን ሲያቆም፣ በመላው እስራኤል ላይ ንጉሥ ይሆን ዘንድ የእስራኤል ተወካይ የሆኑት ሽማግሌዎች ሊቀቡት እንመለከታለን። እንደ ሁለተኛው ጊዜ ሁሉ፣ በዚህም ወቅት እግዚአብሔር እንዲቀቡት ሲያዝ እንዲሁም ታዋቂ ካህን ወይም ነቢይ ሊቀባው አንመለከትም።

ከእነዚህ ምንባባት በግልጥ የምንረዳው ሐቅ ዳዊት፣ በእግዚአብሔር ትእዛዝ በዕውቅ የእግዚአብሔር ነቢይ ለንጉሥነት የተቀባው አንድ ጊዜ ብቻ እንደ ሆነ ነው *(1ሳሙ. 16÷12-3)*። መጀመሪያ ከተቀባ በኋላ፣ እግዚአብሔር ደጋግማችሁ ቀቡት አላለም።

በሁለተኛ ሳሙኤል 2÷4-7 ላይ የምናነበው በጓዳ በቤተሰቦቹ ፊት የተቀባው ዳዊት፣ በይሁዳ ሰዎች ላይ ንጉሥ ይሆን ዘንድ የተቀባው ንግሥናውን ይፋ ለማድረግ ብቻ ነው። በሁለተኛ ሳሙኤል 5÷3 ላይ በእስራኤል ሽማግሌዎች ፊት የተቀባው በመላው እስራኤል

ላይ ንጉሥ መሆኑን ለመግለጽ የተካሄደ ሥርዐተ ሲመት ነው። ስለዚህ የዳዊት ታሪክ፣ "መቀባት ደረጃ" አለው ለሚለው የቡና ጠሪ፣ አንዳችም ድጋፍ አይሰጥም፤ ፍንጭ ጠቋሚ ነገርም አይገኝበትም።

አንድ አማኝ መንፈስ ቅዱስ በውስጡ ማደር በሚጀምርበት ቀን ተቀብቶአል። ስለዚህ ቅባት ደረጃ በደረጃ የሚቀቡበት ሂደት አይደለም (ሮሜ 8÷9፤ 2ቆሮ. 1÷22-23)።

3. ቅባት ይተላለፋልን?

ቅባት አጅ በመጫን፣ የተቀባ ሰው በቆመበት ምስባክ (አትሮኖስ ወይም ዐውደ ምሕረት) ላይ በመቆም፣ የተቀባ ሰው የጸለየበትን ጨርቅ፣ ውሃ፣ ሳሙና፣ ዘይት፣ በመቀባት ይተላለፋል የሚለው ተረት፣ ለቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት ሲበዛ እንግዳ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ሞላባቸው"፣ "ወረደባቸው" ወዘተ ይላል እንጂ፣ "ተላለፈባቸው" አይልም። ቅባት ይተላለፋል የሚሉ ሰዎች ለትምህርታቸው መደገፊያ የሚያደርጉት ጥቅስ፣ በዘጕልቁ ምዕራፍ 11 ላይ ያለውን ምንባብ ነው። ነገር ግን ከፍሉ ቅባት ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው ይተላለፋል የሚል አንዳችም አሳብ የለውም።

በመሠረቱ በከፍሉ ምንባብ ላይ፣ "መንፈስ ቅዱስ" እንጂ፣ "ቅባት" የሚል አንዳችም ቃል አናገኝም። መንፈሱንም ቢሆን፣ ከሙሴ ወስዶ ለሰባዎቹ የሰጠው ራሱ እግዚአብሔር እንጂ፣ ሙሴ እጁን ስለጫነ፣ ሙሴ በቆመበት ስፍራ ስለቆመ፣ ሙሴ የጸለየበትን ፊልፎቅ በአምነት ስለነካ ወይም በሌላ መንገድ አይደለም። መንፈስ ቅዱስን ለሰዎች የሚሰጠው ልዑል እግዚአብሔር ብቻ ነው።

እግዚአብሔር ቅባትን "ለማስተላለፍ" ከላይ የጠቀስናቸውን መንገዶች ሲጠቀም በፍጹም አናይም። በዚህ ምዕራፍ በቍጥር 26 እስከ 30 ባለው ምንባብ በኢልዳድና በሞዳድ ላይ፣ "መንፈስ ወረደባቸው" ይላል። ይህም የመንፈስ ቅዱስ ሰጪ ልዑል

አግዚአብሔር እንደ ሆነ፣ በቀጥታ ከእምላክ ወደ አገልጋዮቹ የሚወርድ እንደ ሆነ የሚገልጽ አንጂ፣ የሚተላለፍ እንዳልሆነ ይገልጻል። መንፈስ ቅዱስ አይቄነጠርም፣ አይባዛምም። አንዱ አንደ ነዳጅ ማጠራቀሚያ "ዴፖ" ሆኖ፣ ከአርሱ እየተቄነጠረ ለሌላው ሰው እይሰጥም። መንፈስ ቅዱስ ጌታን ባመነ ሰው ሁሉ ውስጥ ያድራል። እራት ነጥብ።

የኢየሱስ ክርስቶስን የጽድቅ ሥራ እምነው የሚቀበሉ ሰዎች፣ የእርሱ ጽድቅ የእነርሱ ጽድቅ ሆኖ እንደ ሚቄጠርሳቸው መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል። የአዳም ኀጢአት አዳማውያን ወደ ሆኑ የሰው ልጆች ሁሉ እንደ ተላለፈ፣ በዚህም ምክንያት ሰዎች በግብር ኀጢአታቸው ብቻ ሳይሆን በጥንተ አብሶ (በውርስ ኀጢአት) ለሞት ተሳልፈው ተሰጥተዋል። ነገር ግን ክርስቶስ ኢየሱስ የትኪ ሞት በመሞት ይህን ቤዛዊ ሥራ እምነው የተቀበሉ ሁሉ፣ የክርስቶስ ጽድቅ ጽድቃቸው ሆኖ ይቄጠርሳቸዋል። ይህ በነገረ መለኩቴ ዓለም በእንግሊዝኛው *"imputation"* በመባል ይታወቃል[11]።

የአምነት እንቅስቃሴ መምህራን *"impartation"* የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል (በቍመ መስጠት ወይም ማቀበል ማለት ነው) በመጠቀም፣ "ቅባቴን ሳጋባብህ"፣ "ስጦታዬን ሳስተላልፍብህ" ወይም ደግሞ "ስተወለነ ጊዜ የእኔ ስጦታ በእንተ ዘንድ ይደር" የሚለውን አሳብ ሲናገሩ ይደመጣል። የጸጋ ስጦታዎችን መስጠት የእግዚአብሔር ዘሳለማዊ ፈቃድና ችሎታ ብቻ ነው። በዚህ ዐይነቱ ተግባር ውስጥ እንዳችም የሰዎች ድርሻ የለበትም።

ሐዋርያው ጳውሎስ፣ "መንፈሳዊ ስጦታ እንዳክፍላችሁ ሳያችሁ አናፍቃለሁና" ወይም "የአግዚአብሔርን ወንጌል... አናካፍላችሁ ዘንድ" ሲል ጌታ በሰጠው ጸጋ ሊያገለግላቸው መፈለጉን

[11] የሐዲስ ኪዳን ግሪክ አብዛኛውን ጊዜ "ሎጊዚዮማይ" "λογίζομαι" ሲለው፣ ዕብራይስጡ ደግሞ በአብዛኛው፣ "ራጻሕ" חָשַׁב ይሰዋል ዘሌ. 7÷18፤ 17÷4፤ 2ሳሙ. 19÷19፤ ሮሜ 5÷12-19፤ ከፊልሞና 1÷18-19 ጋር ያነጻጽሯል።

የሚያሳይ እንጂ፣ የእርሱን ስጦታ ሊቄንጥርሳቸው፣ ስጦታ እንካችሁ ብሎ ሊሰጣቸው እንዳሰበ የሚያሳይ አይደለም አሳብ የለም (አባክዎን የሚከተሉትን ክፍሎች ከዐውዳቸው ጋር በጥሙና ይመርምሯቸው ሮሜ 1÷11፤ 1ተሰሎ. 2÷8፤ ኤፌ. 4÷28፤ 1ጢሞ. 6÷18)።

4. ሁለት ዕጥፍ ቅባት አለን?

ሁለት ዕጥፍ ቅባት አለ የሚለውን ተረት የሚያስተምሩ አባያ ነባዮች፣ እዘውትረው የሚጠቅሱት የኤልያስንና የኤልሳዕን ታሪክ ነው (2ነገሥት 2)። እስገራሚው ሐቅ፣ ይህም ክፍልም ቢሆን ስለ ቅባት የሚናገረው እንዳችም ነገር ያለመኖሩ ነው፣ እንዲያውም "ቅባት" የሚለው ቃል በክፍሉ ውስጥ ተጠቅሶ እንመለከትም። ክዚህ ይልቅ ክፍሉ "ቅባት" ሳይሆን "መንፈስ" የሚለውን ቃል ነው የሚጠቀመው። በክፍሉ ውስጥ፣ "ሁለት ዕጥፍ" የሚለው ቃል የነባበት የራሱ የሆነ ታሪካዊ አግባብ አለው።

ነገሩ እንዲህ ነው፣ በብሉይ ኪዳን የበኩር ልጅ የአባቱን ዕጥፍ ንብረት በመውረስ ከሌሎቹ ወንድሞቹ የተሻለ ዕድል የሚያገኝበት አግባብ ነበረው (ዘዳግም 21÷15-17)። ኤልሳዕ የኤልያስን "ዕጥፍ መንፈስ" መፈለጉ፣ ኤልያስን በመተካት የነቢያት መሪ ለመሆን መፈለጉን የሚያሳይ ነው። ኤልሳዕ ሁለት ዕጥፍ መንፈስ መሻቱ፣ የኤልያስን ቦታ ለመተካት ያለውን ጉጉት/ፍላጎት የሚያሳይ እንጂ፣ "ሁለት ዕጥፍ ቅባት" አለ የሚል አሳብ ለማስተላለፍ አይደለም። ይህ ነው እንግዲህ መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበትን ባህላዊና ሥነ ጽሑፋዊ ዐውድ ተክትሎ መተርጎም ወሳኝ ጉዳይ ነው የሚባልበት እግቡ[12]።

[12] በትርቡ ወንድማችን ምኒልክ አስፋው፣ *መጽሐፍ ቅዱስና የትርጓሜ ስልቱ ቅዱሳት መጻሕፍት እንዴት ይነበቡ? እንዴት ይተርጐሙ? እንዴት ይተግበሩ?* በሚል ርእስ ያዘጋጀው መጽሐፍ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን መተርጎም የራስ የሆነ

፭. "እግዚአብሔር በቀባው ላይ እጅህን አታንሣ!" ማለት ምን ማለት ነው?

"እጅህን አታንሣ" ማለት ምን ማለት ነው የሚለውን ነጥብ ቅድሚያ ለጥተን መነጋገር ያስፈልጋል። "እግዚአብሔር በቀባው ላይ እጅህን አታንሣ" የሚሉ ዐውደ ምንባባት በሙሉ፣ በሌላው ሰው ላይ አካላዊ ጥቃትን ማድረስን እንጂ፣ ሥነ ልቡናዊ ጉዳትን ወይም የግለሰብን አስተምህሮ መመርመርን የሚያሳዩ አይደሉም። እነሆ ክፍሎቹን በሙሉ ይመልከቱ፦—

> "8. አቢሳም ዳዊትን፣ "ዛሬ እግዚአብሔር ጠላትህን በእጅህ ላይ ጥሎታል፤ አሁንም እኔ አንድ ጊዜ በጦር ወግቼ ከመሬት ጋር ላጣብቀው፣ መድገምም አያስፈልገኝም" አለው። 9. ዳዊት ግን አቢሳን እንዲህ አለው፣ "አትግደለው! እግዚአብሔር በቀባው ላይ እጁን አንሥቶ ከበደል ነጻ የሚሆን ማን ነው? 10. ሕያው እግዚአብሔርን! እግዚአብሔር ራሱ ይቀሥፈዋል፤ ወይም ቀኑ ደርሶ ይሞታል፤ ወይም በጦርነት ይሞታል። 11. እግዚአብሔር በቀባው ላይ እጁን ከማንሣት እግዚአብሔር ይጠብቀኝ! ነገር ግን በራስጌው አጠገብ ያለውን ጦርና የውሃ መያዣውን ያዝና እንሂድ..." 15. ዳዊትም እንዲህ አለ፣ "አንተ ብርቱ ሰው ነህ? በእስራኤልስ ዘንድ አንተን የሚመስል ማን ነው? እነሆ፣ አንድ ሰው ንጉሡን ጌታህን ሰመግደል መጥቶ ነበር፤ ታዲያ አንተ ንጉሥ ጌታህን ያልጠበቅኸው ሰለምንድን ነው? 16. ያደረግኸው መልካም አይደለም፤ ሕያው እግዚአብሔርን! አንተና ሰዎችህ ሞት ይገባችኋል፤ እግዚአብሔር የቀባውን ጌታችሁን አልጠበቃችሁምና። አሁ፣ ተመልከት፣ በራስጌው የነበሩት የንጉሡ ጦርና የውሃ መያዣ የት አሉ?" 23. እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ሰው እንደ ጽድቁና እንደ ታማኝነቱ ይክፈለው። እኔ ግን ዛሬ እግዚአብሔር አንተን በእጄ አሳልፎ ሰጥቶኝ ሳለ እግዚአብሔር በቀባው ላይ እጄን አላነሣሁም። 24. እነሆ፣ ዛሬ ሕይወትህ በፊቱ እንደ ከበረች ሁሉ፣ የእኔም ሕይወት በእግዚአብሔር ዘንድ የከበረች ትሁን፤ ከመከራም ሁሉ ያድነኝ።" *(1ሳመ.ኤል 26)*

ሕግ እንዳሰው በትክክል የሚያስተምር ነው። ማንኛውም ክርስቲያን ይህን መጽሐፍ እንዲያነብ ክልተ አበረታታሰሁ።

"1. ሳኦል ከሞተ በኋላ፣ ዳዊት አማሌቃውያንን ድል አድርጎ በመመለሱ፣ በጺቅላግ ሁለት ቀን ቈየ። 2. በሦስተኛውም ቀን የተቀደደ ልብስ የለበሰ፣ በራሱም ላይ ትቢያ የነሰነሰ አንድ ሰው ከሳኦል ሰፈር መጣ። ወደ ዳዊት እንደ ደረሰም፣ ወደ መሬት ሰጥ ብሎ በአክብሮት እጅ ነሣ። 3. ዳዊትም፣ "ከወዴት መጣህ?" ሲል ጠየቀው። እርሱም፣ "ከእስራኤላውያን ሰፈር ሸሽቼ መምጣቱ ነው" በማለት መለሰለት። 4. ዳዊትም፣ "ምን ነገር ተፈጠረ?" ሲል ጠየቀው። እርሱም "ሰዎቹ ከጦርነቱ ሸሽተዋል፤ ብዙዎቹ ወድቀዋል፤ ሞተዋል፤ ሳኦልና ልጁ ዮናታንም ሞተዋል" አለ። 5. ከዚያም ዳዊት ወሬውን የነገረውን ወጣት፣ "ሳኦልና ልጁ ዮናታን መሞታቸውን እንዴት አወቅህ?" ሲል ጠየቀው። 6. ወሬ ነጋሪው ወጣትም እንዲህ አለ፣ "ድንገት ወደ ጊልቦዓ ተራራ ወጥቼ ነበር፤ እዚያም ሳኦል ጠሩን ተደግፎ ሳለ፣ ሠረገሎችና ፈረሰኞች ተከታትለው ደረሱበት፤ 7. ወደ ኋላውም ዞር ሲል እኔን ሰላየ ጠራኝ፤ እኔም፣ 'ምን ልታዘዝ' አልሁ። 8. "እርሱም፣ 'አንተ ማን ነህ?' ሲል ጠየቀኝ፣ "እኔም 'አማሌቃዊ ነኝ' ብዬ መለስሁለት። 9. "ከዚያም፣ 'እኔ በሞት ጣር ውስጥ እኛለሁ፤ ነፍሴ ግን አልወጣችም፤ እባክህ በላዬ ቆመህ ግደለኝ' አለኝ። 10. "መቼም ከወደቀ በኋላ እንደማይተርፍ ሰላወቅሁ፣ በሳዩ ቆሜ ገደልሁት፤ በራሱ ላይ የነበረውን ዘውድና የክንዱን አንባር ወስጀ እነሆ፣ ለጌታዬ አምጥቻለሁ።" 11. ከዚያም ዳዊትና አብረውት የነበሩት ሰዎች ሁሉ ልብሳቸውን ቀደዱ። 12. ስሳኦልና ለልጁ ሰዮናታን፣ ለእግዚአብሔር ሰራዊትና ለእስራኤል ቤት አዘኑ፣ አለቀሱ፣ እስከ ማታም ድረስ ጾመ። የወደቁት በሰይፍ ነበርና። 13. ዳዊትም ወሬውን ያመጣለትን ወጣት፣ "ከየት ነው የመጣኸው?" ብሎ ጠየቀው። እርሱም፣ "እኔ የአንድ መጻተኛ አማሌቃዊ ልጅ ነኝ" ብሎ መለሰ። 14. ዳዊትም፣ "ታዲያ እግዚአብሔር የቀባውን ለማጥፋት እጅህን ሰታነሣ እንዴት አልፈራህም?" ሲል ጠየቀው። 15. ዳዊትም ከጕልማሶቹ አንዱን ጠርቶ፣ "በል ቅረብና ውደቅበት" አለው። እርሱም መታው፣ ሞተም። 16. ዳዊትም፣ "እግዚአብሔር የቀባውን ገድያለሁ' ስትል የገዛ አፍህ መሰክሮብሃልና፣ ደምህ በራስህ ላይ ይሁን" አለው።" *(2ሳመ.ኤል 1)*

"የቀባኋቸውን አትንኩ፣ በነቢያቴም ላይ ክፉ አታድርጉ።"

(መዝሙር 105÷15)

“21. ማንም እንዲጨሙናቸው አልፈቀደም፣ ስለ እነርሱም ነገሥታትን
ገሠጸ፤ 22. እንዲህ ሲል፣ “የቀባኋቸውን አትንኩ፣ በነቢያቱ ላይ ክፉ
አታድርጉ።” (1ዜና 16)

ከእነዚህ ምንባባት በግልጽ የምንመለከተው፣ “እግዚአብሔር በቀባው ላይ እጅህን አታንሣ” የሚለው ገለጻ፣ በግለሰቡ ላይ እካላዊ ጥቃት ማድረስን የሚከለክል እንጂ፣ አስተምህሮአዊ ምዘናን ወይም የተተነበዩ ትንቢቶችን ከቃለ እግዚአብሔር ጋር ማመሳከርን የሚከለክል አይደለም። ስለዚህ አስተምህሮን፣ ትንቢትን፣ ትምህርትን፣ ስብከትን ወዘተ ለመገምገም ስንነሣ፣ ግምገማውን እንድናቆም የሚጠቀለው ይህ ጥቅስ፣ አእምሮአዊ ምርምርን ወይም ፍተሻን በጭራሽ የሚከለክል አይደለም።

አንደኛ ዜና 16÷15-21 እንዲሁም በመዝሙር 105÷6-14 ባሉት ክፍሎች፣ የተቀቡ የተባሉት ርእሳነ አበው ማለትም አብርሃም፣ ይስሐቅና ያዕቆብ ናቸው። የተቀባውን የአብርሃምን ሚስት ሣራን፣ ሚስቱ እድርጎ ሊወስድ ያሰበው አቢሜሌክ፣ የአብርሃምን ውሸት መርምሮ እንዳይደርስ አልተከለከለም። በዘፍጥረት 20÷7 ላይ፣ አብርሃምን “ነቢይ” ሊለው እንመለከታለን፤ በአንጻሩ በቍጥር 9-10 ባለው አቢሜሌክ የአብርሃምን ውሸት መርምሮ እንደ ደረሰበት፣ አብርሃምም የመዋሸቱ ምክንያት ምን እንደ ነበር ከ11-13 ባለው ክፍል ሊናዘዝ እንመለከታለን።

መጽሐፍ ቅዱስ የእምላክ ነቢይ የሆነ ለው ትንቢቱ ከቅዱሳት መጻሕፍት አንጻር እንዲመዘን ያስጠነቅቃል (ዘዳ. 13÷1-5፤ 18÷20-22)። በተለይ በመጨረሻው ዘመን፣ ሐሰተኛ አስተማሪዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን ሾልከው በመግባት ብዙዎችን እንደሚያሳስቱ በግልጽ ተነግሮናል። ታዲያ ይህ ዐይነቱ አደጋ በውስጣችን እንዳለ በግልጽ በተነገረበት ቦውድ፣ ትንቢት ልተንብይ ነገር ግን ትንቢቱ የአምላክ አፊምተ ቃል በሆነው በመጽሐፍ ቅዱስ አይፈተሽ ማለት እንዴት ትክክል ሊሆን ይችላል (ሮሜ 16÷17፤ 1ጢሞ. 1÷3፤ ቲቶ 1÷11፤ 3÷10-11)?

ማጠቃለያ

በቅርቡ እምስት መቶኛ ዓመት የልደት በዓሉን ያከበረው፣ የፕሮቴስታንቱ ዓለም የወንጌል ተሐድሶ ንቅናቄ፣ ልዩ መታወቂያው ከነበሩ ዐይነተኛ ባሕርያት መካል፣ “ቅዱሳት መጻሕፍት ብቻ የአስተምህሮአችን ሁሉ ማዕከላት ናቸው” ከዚህም የተነሣ፣ “አስተምህሮዎች ሁሉ በእምላክ ቃል መመዘን የግድ ይኖርባቸዋል” አንዲሁም “ክርስቲያን፣ ያለአንዳች መካከለኛ በእምላክ ፊት በቀጥታ መቅረብ ይችላል” የሚሉት አስተምህሮዎቹ ነበሩ። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ከቅዱላት መጻሕፍት ውጪ ያሉ አስተሳሰቦች ቤተ ክርስቲያንን ወረው እንዲሁም ካቶሊካዊቷ ቤተ ክርስቲያን፣ “ለምች አምላክ ፊት የመቅረብ ዕድል የሚያገኙት በካህናት አማካይነት ብቻ ነው”፣ “የቅዱላት መጻሕፍትን አስተምህሮ የሚበይነው ሊቀ ካህናቱ ብቻ ነው” የሚለውን ትምህርት በጽኑ ለመቃወም ነበር። እንደ መራሕያን ተሐድሶዎች፣ እያንዳንዱ አማኝ የንጉሥ ካህን ነው። ክርስቲያን ቅዱላት መጻሕፍትንም ያለአንዳች መካከለኛ በግሉ አንብቦ፣ መሠረታዊውን ትምህርት ማወቅ ይችላል።

“የአባይ ነባዮችና የመናፍቃን አስተምህሮአዊ ባሕርይ” በሚለው ክፍል ላይ በስፋት እንደ ምንመለከተው፣ መናፍቃን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላትን በመጠቀም፣ ኢመጽሐፍ ቅዱላዊ ትምህርት እንደሚያስተምሩ ነው። አባይ ነባዮችና መናፍቃን የአነርሱን ተፈላጊነት ለማላቅ እንዲሁም ክርስቲያኑ ማኅበረሰብ ያለአነርሱ አንዳችም ፋይዳ እንደሌለው እንዲቈጥር፣ የአነርሱን አገልግሎትና ለብአና የሚያደምቁ በርካታ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ።

“ቀባት” የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል በመጠቀም አንዱት አድርገው ኢመጽሐፍ ቅዱላዊ የሆነ ባዕድ ትምህርት በማሾለክ የመጽሐፍ ቅዱስን መሠረታውያን ትምህርቶች አንደሚቀወሙ በዚህም ክፍል ለማየት ችለናል።

መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ እንደሚያስተምረው፣ ሁላችንም በኀጢአት ምክንያት ከአግዚአብሔር ጸጋ ወድቀን የነበርን፣ ነገር ግን በእምላክ ዘላለማዊ ምሕረት፣ በክርስቶስ ቤዛዊ ሥራና በመንፈስ

ቅዱስ ርዳታ የአምላክ የጸጋ ልጆች የመሆን ሥልጣን ያገኘን ሰዎች ነን። የሆነውን ሁሉ መሆን የቻልነው በአግዚአብሔር ቸርነት ብቻ ነው። ይህን የተሳሳተ የቅባት ትምህርት፣ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በስፋት ያስተማሩት ስመ ጥር እንዲሁም አንጋፋ የሚባሉ ሰባኪያንና መጋቢያን ናቸው። አነዚህ ግለሰቦች ይህን ትምህርት በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ያስተምሩት እንጂ፣ አስተምህሮው ግን ትልቅ ውድመት አንዳስከተለ በማስከተልም ላይ እንደሚገኝ ግልጽ ነው።

እንደ ቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት፣ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙ አድርጎ የተቀበለ ማንኛውም ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ተቀብቶአል። ቅባት አምላካችን አግዚአብሔር እንደ ቸርነቱ መጠን ለልጆቹ የሚሰጠው እንጂ፣ ግለሰቦች ለአማኞች የሚያከፋፍሉት ሸቀጥ አይደለም። አንዱን ክርስቲያን ከሌላው የሚያልቁ፣ በክርስቲያኖች መካከል አጅግ አስፈላጊና አስፈሳጊ ያልሆነ ክርስቲያን የሚል ስሜት የሚፈጥሩ ትምህርቶችን ሁሉ ያስአንዳች ማቅማማት፣ በጽናት መቃወም አለብን። አኛ በአምላክ ቸርነት ብቻ ድነት ያገኘን የአግዚአብሔር የጸጋ ልጆች ነን። ይህ የክርስትና ትምህርት መሠረት ነው።

> "በክርስቶስም ከአናንተ ጋር የሚያጸናንና የቀባን አግዚአብሔር ነው፤ ደግሞም ያተመን፣ የመንፈሱንም መያዣ በልባችን የሰጠን አርሱ ነው" (2ቆሮ. 1÷21-22)።
>
> "አናንተስ ከአርሱ የተቀበላችሁት ቅባት በአናንተ ይኖራል" (1ዮሐ. 2÷27)።
>
> "አናንተም ከቅዱሱ ቅባት ተቀብላችኋል፤ ሁሉንም ታውቃላችሁ" (1ዮሐ. 2÷20)።

ክፍል አምስት

"ፍጹም የሆነ እውነት እስከሌለ ድረስ፣ ፍጹም የሆነ ነገረ መለኮት ሊኖር አይችልም!"



በመናፍቃንና በአባይ ነባዮች ተወዳጅ የሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች እንዳሉ ሁሉ፣ ተወዳጅ የሆኑ አስተሳሰቦች/አነጋገሮችም አሉ። በእነዚህ አነጋገሮች ተወግቶ የወደቀው ሰው፣ ከዐውዳቸው ተፈልቅቀው ክወጡ የመጽሐፍ ቅዱስ ጩቤ ምንባባት ከተወጋው ሰው የሚተናነስ አይመስለኝም። በዚህ ምዕራፍ ትክክለኛ/መልካም

የሚመስሉ፣ በየመገናኛ ብዙኃኑና በማኅበራዊ ሚዲያዎች ላይ በብዛት የሚደመጡ ምርመራን፣ ፍተሻን፣ ምዘናን፣ የሚቃወሙ አባባሎችን አእምሮአዊ ይዘት እንመረምራለን።

- "ፍጹም/ነባራዊ የሆነ እውነት አለከሌለ ድረስ፣ ፍጹም የሆነ ነገረ መለኮትም ሊኖር አይችልም!"
- "እውነት ነባራዊ ነች የሚለው ሐሳብ መቻቻልን ያጠፋል!"
- "የእኔን የነገረ መለኮት ላትወደው ትችላለህ፣ ግን የአንተን አቋም ልትጭንብኝ አይገባም!"
- "ኑፋቄ አውነት የማይሆነው፣ ለሕተት ነው ብለን ካስብን ብቻ ነው!"
- "ሰው እንደ እምነቱ ነው፣ ያድነኛል እንዲሁም ያዋጣኛል ብሎ ያመነው ነገር ያድነዋል፣ ያዋጣዋልም!"

እነዚህ ጥያቄዎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ፣ "ፍጹም ወይም ነባራዊ የሆነ እውነት አለ?" በሚለው ጭብጥ ላይ የሚያጠነጥኑ ናቸው። ለለዚህ ጥያቄዎቹን በትክክል እንዲሁም አጥጋቢ በሆነ መንገድ ለመመለስ፣ "እውነት ምንድን ነው?" "ፍጹማዊ/ነባራዊ የሆነ እውነት ለመኖሩ ማስረጃው ምንድን ነው?" "ፍጹማዊ/ነባራዊ እውነት መኖሩስ ነባራዊ የሆነ ነገረ መለኮት አለ አንድንል ያደርገናልን?" በሚሉት ጥያቄዎች ዙሪያ እንነጋገር።

በርግጥ እውነት ነባራዊ ነችን?

አውነት ምንድን ነው? ነባራዊ የሆነ አውነት አለ ወይስ እንደ ተመልካቹ ፍላጎትና አተያይ ወይም ደግሞ እንደ ማኅበረሰቡ ባህልና ትውፊት ወይም ደግሞ ግለሰቡ ልደርስበት አፈልጋለሁ ከሚለው ውጤት አኳያ የሚወሰን አንጻራዊ ምልከታ ነው?

ይህ እኛ እየኖርንበት ያለነው የታሪክ ወቅት፣ አውነት ነባራዊ አይደለችም በሚለው አቋሙ፣ ድኅረ ዘመናዊ ዓለም *(Postmodern Age)*[1] የሚል ስያሜ ወጥቶለታል። ይህም "አውነት ምንድን ነው?"፣ "በጊዜ፣ በቦታና በሁኔታ የማይወሰን ነባራዊ *(objective)* አውነት አለን?"፣ "በተለይ በሃይማኖትና በሥነ ምግባር የጥናት ዘርፎች ውስጥ፣ ነባራዊ የሆነ አውነት ሊገኝ ይችላልን?" ለሚለው ጥያቄ ብዙ ሰዎች አሉታዊ ምላሽ ስለሚሰጡ ነው። ጥንታውያን ሊቃውንት አውነት ምንድን ነች በሚለው ጉዳይ ላይ አይወያዩም/አይወዛገቡም ነበር ማለት አይደለም። ነገር ግን በርካታ ሰዎች፣ "አውነት አንጻራዊ ነች" የሚለውን አስተሳሰብ ከመቀበላቸውም በላይ፣ በዕለት ተዕለት ሕይወታችን ውስጥ ይኸው ፍልስፍና ይመንዘር ማለት የጀመሩት ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ነው።

በመሠረቱ አውነት የሚባል ነገር ከሌለ፣ ይህን መጽሐፍ ማዘጋጀትም በጭራሽ አያስፈልግም። አንድ ሰው "አውነት የለም" ብሎ ሊከራከር፣ "አውነት የለም" የሚለው ይህ ንግግሩ ራሱ በምን አግባብ አውነት ሊሆን ይችላል? ለዚህ ነው አውነት ነባራዊ አይደለችም የሚለው አተያይ፣ ራሱን በራሱ የሚቃረን *(self-defeating/self-stultifying)* አነጋገር ነው የሚባለው። አጸፋውን ኋላ እመለሰበታለሁ፣ ነገር ግን አሁን ጉዳዩን ከመሞገቴ በፊት፣ አንጻራዊ

---

[1] "ድኅረ" የሚለው ቃል፣ "ድኅር" ወይም "ደኃሪ" ከሚለው የግእዝ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም "መቁየት፣ መዘግየት፣ ማፈግፈግ፣ ወደ ኋላ ማለት፣ ወደ ኋላ መቅረት፣ መጨረሻ፣ ተከታይ" ማለት እንደ ሆነ፣ አለቃ ከዳነ ወልድ ይገልጻሉ (ገጽ 344-345)። "አድኅሪ" ማለትም ኋላ ቀር እንዲሁም "ዳኃራዊ" በእንግሊዝኛው *"background"* እንዲሁም "ደኅርት ማስረጃ" *(secondary source)* የሚሉትን አሳቦች በሚወክል መልክ ግልጋሎት ላይ እንዲውል የተደረገው በዚህ መልክ ነው። ድኅረ ዘመናዊ *("post modernism")* ወይም ድኅረ ምረቃ *("post graduation")* እየተባለ፣ ድኅረ *(post)* በባዕድ መነሻነት *(prefix)* ተጭኖ ጥቅም ላይ ሲውል ከዘመናዊነት በኋላ፣ ከምርቃት በኋላ የሚለውን ትርጉም ይወክላል።

(relative) እንዲሁም ነባራዊ *(objective)* የሚሉትን መደዊ ቃላት የትርጉማቸውን ዳር ድንበር ልበይን።

አንጻራዊ *(relative)* እንዲሁም ነባራዊ *(objective)* የሚሉትን ቃላት ለማብራራት የተወሰኑ ዐረፍተ ነገሮችን ልጠቀም:—

(1) "ወንድም ዮናስ ፋንታ ቶኒክ መጠጣት ይወዳል"

(2) "ሱሉልታ የኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ ነች"

የመጀመሪያው ዐረፍተ ነገር ዮናስ ስለተባለ ግለሰብ የሚናገር ነው። ግለሰቡ በፋንታ ቶኒክ ላይ ያለውን አመለካከት ይገልጻል። ስለዚህ ዐረፍተ ነገሩ ስለ ፋንታ ቶኒክ *(object)* ሳይሆን፣ ዮናስ ስለተባለው ግለሰብ *(subject)* የሚናገር ነው። ይህ አንጻራዊ *(relative)* እውነት ነው። ማንኛውም ሰው ፋንታ ቶኒክ የመውደድና ያለመውደድ ሙሉ መብት አለው። ይህ የግለሰቡ የግል ፍላጎት ነው። ማንም ሰው፣ "ምን ነካህ ጃል አንዴት ፋንታ ቶኒክ ትወዳለህ?" ሊባል አይችልም። ነገር ግን:—

(3) "ዮናስ ፋንታ ቶኒክ አልኮል መጠጥ ነው የሚል አቋም አለው"

ቢባል፣ "መብቱ ነው" ወይም "ትክክል ነው/አንዳሻው" ልንል አንችልም። ምክንያቱም "በፋንታ ቶኒክ ውስጥ የአልኮል ይዘት አለ ወይስ የለም?" የሚለው ጉዳይ የሚበየነው፣ በአንድ ሰው ግላዊ ፍላጎት ሳይሆን፣ ፋንታ ቶኒክ ይዞ በሚገኘው የንጥረ ነገር ይዘት ብቻ ነው። ስለዚህ የመጀመሪያው ዐረፍተ ነገር ትክክል ነው ወይስ ትክክል አይደለም የሚለው ጉዳይ የሚወሰነው በግለሰቡ ፍላጎት ሲሆን፣ "ሱሉልታ የኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ ነች" የሚለው ግን የሚበየነው፣ በእኔ ፍላጎት ሳይሆን፣ ከተማዋ የኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ ነች ወይስ አይደለም በሚለው ነባራዊ ሐቅ ነው። ስለዚህ

በዚህ አግባብ ቁጥር ሁለት ነባራዊ እውነት እንጂ አንጻራዊ አይደለም።

እንግዲያው ግብረገብን ወይም ሃይማኖትን በተመለከተ ያለው እውነት አንጻራዊ ነው ወይስ ነባራዊ/ፍጹማዊ ነው የሚለውን ጉዳይ ለማብራራት ሦስት ተጨማሪ ዐረፍተ ነገሮችን እንመልከት።

(4) "2+2=4"

(5) "መስረቅ ትክክለኛ ምግባር ነው"

(6) "የዘላለም ሕይወት ለማግኘት በክርስቶስ ኢየሱስ ቤዛዊ ሥራ ማመን ያስፈልጋል"

የተራ ቁጥር 4 እውነትነት ወይም ውሸትነት የሚወሰነው፣ እንደ ተራ ቁጥር አንድ በግለሰብ (በማኅበረሰብ፣ በባህል ወዘተ) ፍላጎት አይደለም። እኛ ወደድንም ጠላን፣ እሜሪካ ሆንን አዲስ አበባ፣ ክዛሬ አንድ ሺህ ዓመት በፊትም ሆነ እሁን "2+2" የሰሌቱ ውጤት "4" ብቻ ነው።

እንግዲያው ሥነ ምግባራዊ ፋይዳዎች (ለምሳሌ አትግደል፣ አትስረቅ፣ አትዋሽ ወዘተ) ማለትም ቁጥር 5 እንዲሁም ሃይማኖታዊ አስተምህሮዎች (ማለትም ቁጥር *6)* የአውነት ፋይዳቸው *(truth value)* የሚወሰነው፣ እንደ ምግብ ጣዕም በግለሰብ (በማኅበረሰብ፣ በባህል ወዘተ) ፍላጎት ነው የሚለው አቋም/አመለካከት ግብረገባዊ አንጻራዊነት ይባላል።

ግብረገባዊ ፋይዳዎች (እትግደል፣ አትስረቅ፣ አትዋሽ ወዘተ) ወይም ሃይማኖታዊ አስተምህሮዎች ("የዘላለም ሕይወት ለማግኘት፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ቤዛዊ ሥራ ማመን ያስፈልጋል") እንደ ምግብ ጣዕም በግለሰብ ወይም በማኅበረሰብ ወይም በባህል ይወሰናሉ የሚለው አቋም ግብረገባዊ አንጻራዊነት ሲባል፣ ግብረገባዊ ፋይዳዎችና ሃይማኖታዊ አስተምህሮዎች እንደ ሒሳብ ስሌት በጊዜ፣

በቦታና በሁኔታ እያወሰኑም የሚሰው ደግሞ ነባራዊነት/ፍጹማዊነት ይባላል። እንግዲያው ግብረገባዊና ሃይማኖታዊ እስተምህሮች በአንድ ባህል፣ ወይም ግለሰብ፣ ወይም ማኅበረሰብ ወዘተ የማይወስኑ ከሆነ፣ እነዚህ ነገሮች በምን እንጻር ይገናዘቡ ወይም እውነት ራሱ ምንድን ነው?

አንድ ነገር "ትክክል ነው" ወይም ደግሞ "ስሕተት ነው" ወዘተ ለማለት ነገሩን የምናነጻጽርበት ማገናዘቢያ *(frame of reference)* የግድ ያስፈልጋል። ረጅም እጭር፣ ትልቅ ትንሽ፣ ጠንካራ ደካማ፣ ፈጣን ዘገምተኛ ወዘተ የሚሉት ቅጽሎች/ገለጻዎች ትርጉም የሚኖራቸው፣ ማነጻጸሪያ/ማገናዘቢያ ነጥብ ወይም መሠረት ሲኖር ነው። አሰያ ትርጉም ሊኖራቸው አይችልም። እንደ ፍጹማውያን/ነባራውያን ሃይማኖታዊ አስተምህሮዎች እንዲሁም ግብረገባዊ ፋይዳዎች በባህል፣ በስዎች በጎ ፈቃድ፣ በማኅበረሰብ ፍላጎት ወዘተ የማይገናዘቡ ከሆነ፣ አንድን ምግባር ከምን እንጻር መዝነን ነው ትክክል ወይም ስሕተት ማለት የምንችለው የሚለው ነጥብ እውነት ማለት ምን ማለት ነው የሚለውን ጉዳይ ማብራራት የግድ ይላል።

በፍልስፍናውም ሆነ በሌላው የጥናት ዘርፍ እውነት በአብዛኛው የምትብራራው፣ እኔ በግርድፉ (በሽርክቱ)፣ "ጉድኝታዊ የእውነት ንድፈ ሐሳብ" በምለው፣ ምዕራባውያኑ ፈላስፎች *Correspondence Theory of Truth* በሚሉት ነባቤ ቃል ነበር። አሁን ግን በአብዛኛው[2] ተቀባይነት ያለው፣ ከዚህ ተጻራሪ ከሆኑት የእውነት ንድፈ ሐሳቦች መኻል አንዱ ነው። ከዚህ ውጪ ያሉት ንድፈ

[2] "በአብዛኛው" የሚለው ገለጻ ብዛትን ወይም ቁጥርን እንጂ ዐይነትን/ጥራትን አመልካች እንዳልሆነ ልብ ይሏል።

ሐሳቦች ወይም ነባቤ ቃላት እውነትን እንደ ምግብ ጣዕም ጎሊናዊ *(subjective)* የሚያደርጉ ናቸው።

ጉድኝታዊ ወይም ዝምደታዊ የእውነት ንድፈ ሐሳብ *(The Correspondence Theory of Truth)* አንድ ዐረፍተ ነገር ወይም ንግግር እውነት የሚሆነው፣ ዐረፍተ ነገሩ ከገሐዱ ዓለም *(reality)* ጋር ጥምረታዊ ወይም ጉድኝታዊ ትስስር *(correspond)* ሲያበጅ ነው[3]። ጉዳዩን ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ የተወሰኑ ሙያዊ ቃላትን ሳብራራ፦—

1) እውነት ተሸካሚ *(Truth-bearer)*

እውነት ተሸካሚ የምንለው፣ የእውነት ፋይዳው *(truth value)* እውነት አለያም ሐሰት የሆነውን ዐረፍተ ነገር ብቻ ነው። "ኢትዮጵያ በምሥራቅ አፍሪካ የምትገኝ አገር ናት" የሚለው ዐረፍተ ነገር እውነት ተሸካሚ ይባላል።

2) እውነት ፈጣሪ *(Truth-maker)*

እውነት ፈጣሪ የምንለው እውነት ተሸካሚው እውነት እንዲሆን የሚያደርገው ነገር ማለት ነው። "ኢትዮጵያ በምሥራቅ አፍሪካ የምትገኝ አገር ናት" የሚለው እውነት ተሸካሚ እውነት የሚሆነው፣ በገሐዱ ዓለም *(reality)* ኢትዮጵያ በምሥራቅ አፍሪካ የምትገኝ አገር ስትሆን ብቻ ነው። ይህ "እውነት" እኛ እውነትን ከመረዳት ችሎታችን ጋር የሚያያዝ አይደለም። እኛ ይህን ጉዳይ ዐወቅን አላወቅን ጉዳዩ እውነት ነው። ለምሳሌ የጂኦግራፊ ትምህርት ያልተማረ ሰው ይህን ሐቅ ባይረዳም ወይም ካርታዎችን እንዴት ማንበብ እንዳለበት ባያውቅም፣ ጉዳዩ ግን እውነት ነው።

[3] *Truth is what corresponds to its referent.*

2) ጉድኝታዊ መስተጋብር *(Correspondence Relation)*

ስለዚህ ጉድኝታዊ መስተጋብር የምንለው፣ በአውነት ተሸካሚውና በአውነት ፈጣሪው መካከል ያለ አንድነት ነው[4]።

ስለዚህ አውነት ማለት እንደ ነገርየው የሆነ ንግግር ማለት ነው[5]። ከነሐዱ ዓለም ጋር ጉድኝት ያለው ስንል፣ ቁሳዊ ለሆኑም አንዲሁም ቁሳዊ ላልሆኑ አሳቦች *(ideas)* ማለታችን ነው። በሁለቱም መንገድ ነባራዊነት *(reality)* ያለ ሊሆን፣ አውነት *(truth)* ደግሞ ከአውነታው ጋር አንድ የሆነ ወይም ጉዳዩን በትክክል የሚወክል ጉዳይ ማለት ነው። ሐሰት ማለት ደግሞ ከነባራዊው ዓለም *(reality)* ጋር አንድ ያልሆነ ማለት ነው[6]።

አውነት ነባራዊ ነች

አውነት ነባራዊ/ፍጹማዊ ለመሆኗ አነሆ ማስረጃዎ:—

1. አውነት አንጻራዊ ከሆነች፣ "አንጻራዊነት አውነት ነው" የሚሉ አንጻራውያን አውነት አንጻራዊ ከሆነች ይህ አውነት ለምች ሁሉ እንዲቀበሉት የሚገባ አውነት ሳይሆን፣ የተናጋሪው የግል አስተያየት ነው። አውነትን መሠረት ያላደረገን የግል አመለካከት መቀበል የሚኖርብን አንዳችም ምክንያት አይኖርም። "አንጻራዊነት አውነት አለ፣ የሚለው ጉዳይ አንጻራዊ በሆነ መልኩ አውነት ነው የሚባል ከሆነ" የተናጋሪውን አመለካከት መቀበል የሚኖርብን አንዳችም ምክንያት አይኖርም። ምክንያቱም ይህ አነጋገር ማዕከለ ውጋጅነት ሕግ *(Law of Excluded Middle)* የሚባለውን መሠረታዊ የሥነ አመክንዮ ሕግ ይጋጫልና።

[4] *Truth is what corresponds to its referent.*

[5] *Truth is "telling it like it is"*

[6] *It tells it like it is not, misrepresenting the way things are.*

2. አንጻራዊነት ትክክል ከሆነ፣ ዓለማችን በተቃርኖ የተሞላች ትሆናለች። ለአኔ አውነት የሆነው ነገር ለሌላው ሐሰት ከሆነ፣ ተቃራኒ ነገሮች አውነት ሊሆኑ ነው ማለት ነው። ለምሳሌ የሚከተሉትን ቦረፍተ ነገሮች አንመልከት። ሀ) "በማቀዝቀዣው ውስጥ ሥጋ አለ"። ለ) "በማቀዝቀዣው ውስጥ ሥጋ የለም" የሚሉት ሁለት ዐረፍተ ነገሮች በአንድ ጊዜ፣ በተመሳሳይ ትርጉማቸው አውነት ሊሆኑ ነው ማለት ነው። ይህ ተቃርኖ ነው።

3. አውነት አንጻራዊ ከሆነች፣ አንድም ሰው ሊሳሳት፣ አንድም ሰው ትክክል ሊሆን አይችልም። አንዲያውም ትክክልና ስሕተት የሚባሉ ነገሮች ሊኖሩ አይችሉም። ምክንያቱም በምን መስፈርት ተሳስተሃል፣ በምንስ መስፈርት ትክክል ነህ ይባላል? አውነት በለምች ፍላጎትንና ምልከታ የሚለያይ ጉዳይ ከሆነ፣ አውነትና ስሕተት የሚባሉ ነገሮች ሊኖሩ አይችሉም።

4. አንጻራዊነት አውነት ከሆነ፣ ትምህርት ሊኖር አይችልም። ትምህርት አዳዲስ መረጃዎችን ገንዘብ ማድረግ ብቻ ሳይሆን፣ የተሳሳቱ መረጃዎችንም ማስተካከል ወይም ማስወገድ ነው። አንዳችም አውነት ወይም ሐሰት ከሌለ፣ ትምህርት ሊኖር አይችልም።

5. በአንድ ነገር ላይ ያለን ዕውቀት ፍጹም ላይሆን ይችላል፣ ዕውቀት/መረዳት ወደ ፍጽምና እያደገ የሚሄድ ጉዳይ ነውና። ይህ ግን አውነት ነባራዊ አይደለችም ማለት ስሕተት ነው። ፍጹም አርግጠኞች የምንሆንባቸው ነገሮች አንዳሉ ሁሉ፣ ፍጹም

እርግጠኛ የማንሆንባቸው ነገሮችም አሉ (ለምሳሌ “3+2=5” የሚለው ስሌት ውጤት ትክክል መሆኑን ፍጹም እርግጠኞች ነን። እኔ ሬሳ ላለመሆኔ እርግጠኛ ነኝ። ምክንያቱም “ሬሳ እይደለሁም” ብዬ እየተናገርሁ ሬሳ ልሆን እልችልም። “ክብ-አራት ማዕዘን” የሚባል ነገር እንደ ሌለ እርግጠኛ ነኝ፣ ምክንያቱም አንድ ነገር “ክብ ነው” ስንል በውስጡ አራት ማዕዘን እይደለም እያልን ነውና። ለዚህ ይህ አነጋገር እርስ በርሱ የሚቃረን ንግግር ነው)። ፍጹም የሆነ እውነት የለም የሚሉ ለምች፣ የእውነትን ባሕርዮት እውነትን ከምናውቅበት ሂደት ጋር ይቀላቅሉታል። እውነትን የምናውቅበት መንገድ ሊለያይ ወይም ጠንካራ ወይም ደካማ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን መንገዱ በመጠንና በዐይነት መለያየቱ፣ የእውነት ፋይዳውን አይቀይርም። ለምሳሌ “አዲስ እበባ የኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ ነች” የሚለውን ጉዳይ ለማስረዳት እጥጋቢ ማስረጃ የለኝም ማለት፣ እውነታው በጭራሽ አይታወቅም ማለት አይደለም። የማስረጃ መኖርና ያለመኖር የእውነት ፋይዳውን አይቀይረውም። ቀለም እይለዬ የሆነ ለው፣ “አረንጓዴ ቀለም ምን እንደ ሆነ አላውቅም” ለላለ አረንጓዴ የሚባል ቀለም የለም ማለት አይቻልም። እኛ እውነታውን የማወቅ ችሎታ ማግኘታችንም ሆነ ያለማግኘታችን እውነታውን ሀልዎት ቅንጣት ታህል አይቀይረውም።

6. አንዳንድ ለምች “ጥሩ”፣ “መጥፎ”፣ “ትልቅ”፣ “ትንሽ”፣ “እውነት”፣ “ውሸት”፣ ወዘተ የሚባሉ ነገሮች ንጽጽርን ታሳቢ ያደረጉ መሆናቸው፣ ፍጹም የሆነ እውነት የለም እንድንል አያስችለንም። ለምች ከሂትለር ጋር ሊነጻጸሩ ጥሩ ከእማሆይ ትሬዛ ጋር ሊነጻጸሩ ደግሞ መጥፎ/እኩይ ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ

ጉዳይ ግን ፍጹማዊ የእውነት መለፈርት የለም እንድንል እያደርገንም። እኔ ከታላቅ ወንድሜ ጋር በቁመት ተነጻጽሬ ላንስ፣ ከታናሽ ወንድሜ ጋር ደግሞ ተነጻጽሬ ልበልጥ እችላለሁ፤ ነገር ግን ከአንዱ ጋር ተነጻጽሬ ማነሴና ከሌላው ጋር ተነጻጽሬ መብለጤ ፍጹም የሆነ እውነት ነው። ይህ ዐይነቱ ጉዳይ ፍጹም የሆነ እውነት የለም እንድንል የሚያደርገን እይደለም።

7. “እውነት የማይቀያየር ቢሆን ኖሮ፣ አዲስ እውነት አይገኝም ነበር” የሚሉ ለምች አሉ። “አዲስ” ለንል፣ አዲስ የሆነው ለእኛ እንጂ፣ ጉዳዩማ ድሮም የነበረ ነው። ለምች እውነትን ፈልገው ያገኙ እንጂ፣ እውነትን ሊፈጥሩ አይችሉም። “ወርኀ ጎዳር 2017 ዓ.ም የተፈጠረ ወይም የተወለደ እውነት” የሚባል ነገር የለም። ነገር ግን በዚህ ቀን በርካታ እውነታዎች ሊታወቁ ይችላሉ። ይህም እውነት በየትኛውም ቦታና ጊዜ ውስጥ እውነት ነው። እውነት በአንድ የተወለነ ወቅት ሊወለድ፣ ሊሞት፣ ሊያረጅ እያችልም። በአንድ ጊዜ እውነት ነው የሚባል ነገር፣ በማናቸውም ጊዜ እውነት ነው። ኒውተን ከመወለዱም በፊት የመሬት ስበት ነበር። ግለሰቡ ቀመሩን ዐወቀ ማለት ፈጠረ ማለት አይደለም፤ አገኘ እንጂ።

8. በእንድ ነገር ላይ ያለን ዕወቀት ጠንካራ እይደለም ማለት፣ እውነት ፍጹማዊ አይደለችም ማለት አይደለም። ሳይንሳዊ ግኝቶች ከአሮጌው እውነት ወደ አዲሱ እውነት የሚካሄዱ ሽግግሮች ሳይሆኑ፣ ለምች በርእሰ ጉዳዩ ላይ ያላቸው ዕውቀት እየኮሰበተ መሄዱን የሚያሳዩ ናቸው። ፍጹማውያን ነን ማለት

ስለ እውነት ፍጹም የሆነ ወይም የተሟላ ዕውቀት አለን ማለት አይደለም።

9. እውነት አትቀየርም። እኛ በእውነት ላይ ያለን ዕውቀት ያልተሟላ ሊሆን ይችላል። በጊዜ ውስጥም እየጠራ ሊመጣ ይችላል። ይህ መሆኑ ግን እውነት ትቀያየራለች ማለት አይደለም። የሰዎች ሥነ ዕውቀት መቀያየሩ (በእውነታው ላይ ያላቸው ዕውቀት መለዋወጡ) የኑባሬው እውነትነት ይቀያየራል ማለት አይደለም።

10. የለምች እምነት፣ እውነታውን አይቀይረውም። አንድ ሰው በየዋህነት *(sincerely)* አንድን ነገር ሊያምን ይችላል። ግለሰቡ ጉዳዩን በዚህ መልክ ማመኑ ጉዳዩን እውነት ሊያደርገው አይችልም። አንድ ሰው መሬት አንደ ለፊድ ጠፍጣፋ ነች ብሎ በየዋህነት ሊያምን ይችላል። በየዋህነት ማመኑ ጉዳዩን እውነት ሊያደርገው አይችልም።

11. አንድ ነገር እውነት ከሆነ፣ ከአርሱ በተቃራኒ ያለው ሐሳብ ስሕተት ነው ማለት ነው። ትምህርተ ሥላሴ አውነት ከሆነ፣ ከዚህ ውጪ ያለው ትምህርት ስሕተት ነው ማለት ነው። ትምህርተ ሥላሴ አውነት ከሆነ፣ ከዚህ ትምህርት ጋር ተቃራኒ አስተሳሰብ ያላቸው፣ "ይሖዋ ምስክሮችም" ሆኑ "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" እማንያን ተሳስተዋል ማለት ነው። በአንድ ወቅት በአንድ ጉባኤ፣ "ክርስትና እውነት ነው፤ በአንጻሩ ደግሞ ከአርሱ ጋር የሚቃረኑ ትምህርቶች ሁሉ ስሕተት ናቸው" የሚለውን ንግግሬን ያልወደደልኝ አንድ ሰው፣ "ጽንፈኛ ነህ"

አለኝ። እኔ የአንተን አስተሳሰብ ባለመቀበሌ ጽንፈኛ መሆኔ እውነት ነው። አንተም የእኔን አስተሳሰብ ባለመቀበልህ ጽንፈኛ ነህ ማለት ነው እልሁት። ጽንፈኛ የሚለው ቃል በዚህ መልኩ የሚተረጐም ከሆነ፣ ሁላታችንም ጽንፈኞች ነን። አንድ ነገር እውነት ከሆነና የአርሱ ተቃራኒው ሐሰት ከሆነ፣ አኔ ወይም ደግሞ ይህ ግለሰብ ተሳስተናል ማለት ነው። ለዚህም ነው እውነት አግልሌ *(exclusive)* ባሕርይ አላት የሚባለው።

12. የለምች አምንታዊም ሆነ አሉታዊ ዐዋጅ፣ ነባራዊ የሆነውን እውነታ አያቀይረውም፤ ሊቀይረውም አይችልም። በርካታ አባይ ነባዮችና የእምነት እንቅስቃሴ አራማጆች፣ "ቃል አውጥቼብሃለሁ!"፣ "ተናግሬብሃለሁ!"፣ "ዐውጀብሃለሁ!" ወዘተ ይላሉ። የእነርሱ ዐዋጅ ወይም አምንታዊም ሆነ አሉታዊ ንግግር እንዳችም ፋይዳ የለውም። ቅዱሳት መጻሕፍትም የለምች ንግግር አውነታውን ይቀይራል የሚል አንዳችም ትምህርት የለውም[7]። ለምሳሌ አንድ ሰው፣ "መሬት ጠፍጣፋ ነች" የሚል ቃል ከአፉ ለሳወጣ፣ መሬት ጠፍጣፋ ልትሆን አትችልም። አብርሃምና ሣራ "መካን ነን/ልጅ የለንም" ማለታቸው፣ ይስሐቅ እንዳይወለድ አልከለከለም። የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን፣ "ሀብታም ነኝና ባለጠጋ ሆኛለሁ አንድም ስንኪ እያስፈልገኝም" ማለቷ፣ እንዳለችው እንድትሆን አልረዳትም። ይልቁንም አምላክ፣ "ጕስቁላና ምስኪንም ድኻም፣ ዕውርም፣ የተራቈትህም መሆንህን ስለማታውቅ" ሊላት እንመለከታለን (ራእይ 3÷17)።

---

[7] ለበለጠ ማብራሪያ፣ የዚህ መጽሐፍ ጸሓፊ፣ "*የእምነት ወይስ የክህደት እንቅስቃሴ*" በሚል ርእስ ከወንድም ምኒልክ አስፋው ጋር የተዛጋጀውን መጽሐፍ ይመለከታል።

ዘካሪያስ በስተርጅናው ልጅ ያገኘው፣ አምነታዊ ዐዋጅ በማወጁ አይደለም። እንዲያውም ኤልሳቤጥ እወልዳለሁ የሚል እምነት እንኳ እንዳልነበራት መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ነገር ግን ይህ አሉታዊ ምልከታዋ/ዐዋጅዋ ልጅ እንዳታገኝ አልከለከላትም። ከላይ ለማየት እንደ ሞከርንው እውነት በገሐዱ ዓለም ያለን ነገር አለ ማለት ሲሆን፣ ስሕተት ደግሞ የሌለን ነገር አለ ማለት ነው። ዛሬ እንደ አንጉዳይ በዙሪያችን የፈሉት አባይ ነባዮች ይህንን ሐቅ ነው አየተጻረሩ ያሉት።

13. እውነት ባህል ዘለል ነች። እንድ ነገር እውነት ከሆነ በማንኛውም ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታ ውስጥ ላሉ የሰው ልጆች አውነት ነው ማለት ነው። በዚህ አግባብ ሲታይ፣ የኢትዮጵያውያኖች ሂሳብ፣ የአሜሪካኖች ፊዚክስ፣ የአንግሊዞች ሥነ ምግባር፣ የግሪኮች ሥነ አመክንዮ የሚባል ነገር የለም። አውነታውን መጀመሪያ ያገኘው ሰው የተወሰነ አገር ዜግነት አለው ማለት፣ ግኝቱም የዚያ አገር ባልደረባ ነው ማለት አይደለም። እንዳንድ ሰዎች ይህ የምዕራባውያን ፍልሰፍና፣ የአሜሪካኖች ነገረ መለኮት ወዘተ ነው ይላሉ። እንድ ፍልሰፍና ወይም ነገረ መለኮት በአንድ አካባቢ ሊገኝም ሆነ ሊያብብ ይችላል፣ ይህ ማለት ግን አውነታው ቀዬአዊ/ቀበሌያዊ ነው ማለት አይደለም።

14. አንዳንድ ሰዎች እውነት ነባራዊ ነው ብለው የሚያምኑ ሰዎች ግትሮች ናቸው ይላሉ። ነገር ግን እንጻራውያንም ቢሆኑ የአኛን ተቀበሉ በማለታቸው ግትር ናቸው ማለት ይቻላል። ስለዚህ ወቀሳው በሁለቱም ወገኖች ላይ የሚወድቅ ነው። ነገር ግን ሊጠየቅ የሚገባው ጥያቄ፣ "ፍጹማውያን ግትር የሆኑት በምን

ላይ ነው?" እንዲሁም "አንጻራውያን የሙጥኝ ያሉት ምኑን ነው?" በሚለው ጉዳይ ላይ ነው። ፍጹማውያን በአውነት ላይ ግትር ሲሆኑ፣ አንጻራውያን ደግሞ በሐሰት ላይ የሙጥኝ ብለዋል። ስለዚህ ወቀሳው "ግትር ለምን ሆንህ?" የሚለው ሳይሆን፣ "በምን ላይ ግትር ሆንህ?" የሚለው ነው—በአውነት ወይስ በውሸት።

15. ብዙ ሰዎች ፍጹማውያን ጠባብ ናቸው ይላሉ። *4+4* መልሱ *8* ብቻ ነው። ሌሎች አጅግ በርካታ አማራጮች የስሌቱ ትክክለኛ ምላሽ ሊሆኑ አይችሉም። ስለዚህ *8* ብቻ የሙጥኝ ማለት ጠባብ አያለኝም። ይህ ጉዳይ ጠባብ የሚያሰኝ ከሆነ፣ ጠባብ መሆኔ ትክክል እንዲሁም አግባብ ነው። ለዎች ሁሉ እንደ አኔው ጠባብ መሆን ይኖርባቸዋል።

እውነት ነባራዊ መሆኗ፣ ነገረ መለኮትም ነባራዊ እንዲሆን የግድ ይላል!

ነገረ መለኮታዊ አውነት ከሌለ፣ አጅግ ተጻራሪ የሆኑ ሃይማኖቶች ሁሉ በአንድ ዐይን ሲታዩ ነው ማለት ነው። ለምሳሌ ክርስትና፣ "የዘላለም ሕይወት የሚገኘው በክርስቶስ ኢየሱስ ቤዛዊ ሥራ አማካይነት ብቻ ነው" ይላል። በአንጻሩ ደግሞ የይሁዲ ሃይማኖት ይህንን አስተምህሮ አይቀበልም። ሃይማኖቶች ሁሉ ትክክል ከሆኑ፣ ይህ አርስ በርሱ የሚቃረን ዐዋጅ ትክክል ነው አንደ ማለት ነው። አውነት አርስ በርሷ ትጻረራለች ብሎ ማሰብ፣ እውነት የለም" ብሎ ከማመን ጋር እንድ ዐይነት ነው።

ማናቸውም ዐይነት አስተምህሮች፣ አሉታዊም ሆነ አምንታዊ ውጤት አላቸው። በአብዛኛው እውነት የሆነ ነገር አምንታዊ ውጤት ሲያስከትል፣ ሐሰት የሆነ ነገር ደግሞ አሉታዊ ውጤት ያመጣል።

አውነትን "ወግጂልኝ!" ካልናት፣ ሐሰት መግነኑ አይቀሬ ነው። ብርሃንን ለማስወገድ ከወደድን፣ ጨለማን መጥላት አንችልም። ሥነ ምግባራዊ የሆነ አውነት ከሌለ አትግደል፣ አትስረቅ፣ አትዋሽ ወዘተ የሚሉት የሥነ ምግባር ሕግጋት አንዳችም ትርጉም አይኖራቸውም። መግደል፣ መዝረፍ፣ አስገድዶ መድፈር፣ መዋሸት፣ ስሐተት የማይሆንበት አገር ቢኖር፣ በዚህ አገር መኖር የሚፈልግ ሰው ይኖራልን? አውነትን መጥላት ለላምን መጥላት ብቻ ሳይሆን ሕይወትንም መጥላት ነው።

"አውነት ነባራዊ ነች የሚለው ሐሳብ መቻቻልን ያጠፋል!"

አንዳንድ ሰዎች አውነት ነባራዊ ነች ብሎ ማመን ጽንፈኝነት እንደ ሆነ እንዲሁም መቻቻል አንዲጠፋና ጽንፈኝነት አንዲያቈጠቍጥ ያደርጋል ይላሉ። ለዚህ ዐይነቱ ፍርደ ገምድል ንግግር ምክንያት የሚሆነው፣ መቻቻል ለሚለው ፅንሰ ሐሳብ የምንሰጠው ትርጓሜ ነው። አንዳንድ ሰዎች መቻቻል የሚለውን ሐሳብ የሚመለከቱት ተቃራኒ ነገሮች ሁሉ አውነት ናቸው በሚለው ትርጓሜ ነው። ተቃራኒ ነገሮች አውነት አንደማይሆኑና ሊሆኑም አንደማይችሉ ተመልክተናል። ተቃራኒ ነገሮች አውነት የሚሆኑ ከሆነ፣ ተቻቻሉ ለሚለው ሐሳብ ተቃራኒው አትቻቻሉ እስከ ሆነ ድረስ ሁለቱም ሐሳቦች ትክክል ሊሆኑ ነው ማለት ነው።

አንዳንዶች መቻቻልን የሚፈቱት ደግሞ፣ የሌላውን ሰው ሐሳብ በጥያቄ ውስጥ ካለማስገባት ጋር አያይዘው ነው። ይህም ትንተና ትክክል አይደለም። ቅዱሳት መጻሕፍት፣ "ሁሉን መርምሩ መልካሙን" ያዙ ከሚለው ምክራቸው ጋር የሚጻረር ነው ዘዳግም *13÷1-5*፤ *1*ዮሐንስ *4÷1*፤ ገላትያ *1÷8*፤ *2*ቆሮንቶስ *11÷13*)።

ታላቁ ፈላስፋ ሶቅራጥስ፣ "የሰው ልጅ የማይመረመረውን/የማይመረምረውን ሕይወት ሊኖረው አይገባም" የሚለው አነጋገሩ ሁሉን መመርመር ተገቢ መሆኑን ብቻ ሳይሆን፣ የሰው ልጅ ግዴታም እንደ ሆነ የሚያሳስብ ነው። አገርኛውን ብሂል አንዳሻሽለው ከተፈቀደልኝ፣ "ያልመረመረ ተመነጠረ" ብል ተገቢ ነው።

ስሕተት በሆነ ነገር የገንዘብና የሕይወት መሥዋዕትነት የሚከፍሉ ሰዎች፣ ምርምርን የሕይወት መስመራቸው ባለማድረጋቸው ምክንያት በራሳቸው ላይ የሚያመጡት የጥፋትን መቅሠፍት ነው። አምላለ መለኮት የሆኑ የሰው ልጆች እንደ ደመ ነፍላውያኑ እንስላት በዋል ፈለስ ሕይወት ሊኖሩ አይገባቸውም። አእምሮን የሰጠን አምላክ፣ አእምሮን ጥለን እንድንከንፍ በፍጹም፣ በፍጹም በፍጹም አይፈልግም።

መቻቻል የሚለው ፅንሰ ሐሳብ ራሱ አውነት መኖሯን አንዲሁም አውነት ነባራዊ ባሕርይ እንዳላት ታሳቢ ያደረገ ነው። አውነት ከሌለና ሁሉም ነገር አውነት ወይም ሐሰት ካልሆነ፣ "መቻቻል" የሚለው ቃል አንዳችም ትርጉም አይኖረውም። "ቻለው" ልባል የምችለው የሚከብደኝን ነገር ግን በትዕግሥት ልሸከመው የሚገባኝን ነገር ነው።

መቻቻል እውነትን መካድ ሳይሆን፣ እውነትን አምኖ/ተቀብሎ በአንጻሩ በማይመች ሁኔታ ውስጥ ትዕግሥትን ተላብሶ መኖር ነውና። መጽሐፍ ቅዱስ እውነትን በፍቅር ያዟት የሚለው ንግግሩ ይህ ዐይነቱን ሁኔታ ታሳቢ ባደረገ ይመስለኛል።

“አንተ በነገረ መለኮት አንጻራዊነት ላታምን ትችላለህ፤ የአንተን አቋም ግን ልትጭንብኝ አይገባም!”

ልክ ነው፣ “የአኔ ዐይነት ነገረ መለኮታዊ አቋም ይኑርህ” ብሎ በሰዎች ላይ አካላዊም ሆነ የሥነ ልቡና ጫና ማምጣት ስሕተት ነው። የሰው ልጅ የመለሰውን የማመን ሙሉ መብት ሊሰጠው ይገባል። ትክክል ነው ብሎ ያመነበትም አቋም፣ የሚያስከትለውን እምንታዊም ሆነ አሉታዊ ውጤት፣ በሙላት የመቀበል፣ ኀላፊነትም የመውሰድ ግዴታ አለበት።

የአንተን ዐይነት አላብ አንዲኖረኝ አታስገድደኝ የሚሉ ሰዎች ግን፣ እነርሱም የአነርሱ ዐይነት አመለካከት አንድንይዝ ጫና ሊያደርጉብን አይገባም። ከዚህም የተነሣ፣ ቤተ ክርስቲያን፣ “ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ የተሰጠውን ሃይማኖት” የመስበክና በዚህም አስተምህሮ ሥር የማይኖሩትን የመምከር፣ የመገሠጽ፣ አሻፈረኝ ያሉትን የማባረር ግዴታ አለባት (ይሁዳ 3፤ ማቴዎስ 18÷15-17፤ 1ቆሮንቶስ 5÷1-2)። ይህን መሠረተ እምነቷን፣ ተግባራዊ አንዳታደርግ መከልከል በፍጹም የለባትም።

ብዙ ክርስቲያኖች ይህ ዐይነቱን ንግግር ሲናገሩ ይደመጣል። ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነ አመክንዮ *(Logic)* በመጠቀም፣ “አኔ በግሌ ክርስቶስ አዳኝ አንደ ሆነ አምናለሁ፤ ነገር ግን አንተ አላምንም የምትል ከሆነ ትክክል ነህ”። ወይም “እኔ ክርስትና ትክክል ነው ብዬ አምናለሁ፤ አንተ ደግሞ ከዚህ በተቃረነ መልኩ ክርስትና ትክክል አይደለም ማለትህ ትክክል ነው” ማለት ይቻላልን? ነገሩን ከሃይማኖታዊ ንግግር አውጥተን ወደ ሥነ ምግባር በመውሰድ፣ “አኔ በግሌ አስገድዶ መድፈርን እቃወማለሁ፤ ነገር ግን አንተ አስገድደህ መድፈር የምትፈልግ ከሆነ መብትህ ነው” ማለት

ይቻላልን? አውነት ነባራዊ ከሆነች፣ የምናደርገው ውይይት ሁሉ እውነት በማን ዘንድ ነው ያለችው የሚለውን ጉዳይ ለማወቅ ትልቅ ጠቀሜታ አለው።

በዚህ አንጻር ውይይት ወይም ትምህርት ተገቢ ጉዳይ ነው። እውነት አንጻራዊ ነች የሚሉ ሰዎች፣ እውነት አንጻራዊ እንዳልሆነች፣ በማከበር አንነግራቸዋለን። ምክንያቱም እውነትን ወግድ ብለው ሐሰትን ገንዘባቸው አድርገዋልና። ቤተ ክርስቲያን እውነትን የምታውጀው፣ አምላለ መለኮት የሆነ የሰው ልጅ የሐሰት ሰለባ እንዳይሆን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ አስከ ምድር ዳርቻ ሄዳችሁ ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ የሚለው አውነት ዐርነት ስለሚያወጣ፣ ሐሰት ደግሞ ከዚህ ተቃራኒ በሆነ ሁኔታ ውሰጥ መቀመቅ ስለሚከት ነው።

በአውነትና በሐሰት መኻል የሚገኝ ሌላ ነጻ ክልል አስከሌለ ድረስ፣ ሰዎች አውነትን አልቀበልም ካሉ ሐሰትን መቀበላቸው አይቀሬ ነው። በዚህ አግባብ አውነት አይጫንብኝ ያሉ ሰዎች ሐሰት ሊጫንባቸው የግድ ነው። ከሁለት አንዱ መጫኑ የማይቀር ከሆነም (ከአውነት ወይም ከሐሰት ውጪ ሌላ ሦስተኛ አማራጭ ከሌለ[8]) ከሐሰት ይልቅ እውነት ቢጫንብን አይሻለንምን?

“ነፋቂ እውነት የማይሆነው፣ ስሕተት ነው ብለን ካሰብን ብቻ ነው!”

ይህ አውነት ነባራዊ አይደለችም ይልቁንም በሰዎች አስተሳሰብ የምትወለን ነች የሚለውን አቋም ታሳቢ ያደረገ ንግግር

[8] የአውነት ዋጋዋ አውነት ወይም ሐሰት አንጂ፣ ሌላ ሦስተኛ አማራጭ ሊገኝ አይችልም፤ መስረቅ ወይም ያለመስረቅ፣ መግደል ወይም ያለመግደል፣ ክርስቶስን ማመን ወይም ያለማመን... ከዚህ ውጪ ሦስተኛ አማራጭ ሊቀርብ አይችልም። ይህ አውነት ከሆነ አንዱን አልቀበልም የሚል ሰው ሌላውን መቀበሉ የግድ ነው። ከሁለት አንዱ መጫኑ የማይቀር ከሆነ፣ ከአውነት ጋር መወገን አይሻልምን?

ነው። ይህ ደግሞ ስሕተት እንደ ሆነ ከላይ በስፋት ለማየት ሙክራ አድርገናል። የእኛ አስተሳሰብ የእውነት ዋጋዋን ሊቀይር አይችልም። "እኔ ክርስቶስ ጌታ ነው" ብል ወይም ባልል፣ የእኔ አነጋገር ወይም አቋም ጌትነቱን ሊለጠውም ሆነ ሊነፍገው አይችልም፣ "ለምኽ ሁሉ ሐሰተኛ ቢሆኑ እግዚአብሔር ግን እውነት ሆኖ ይኖራል" (ሮሜ 3÷4)። መግደል እኔ ትክክል ነው ወይም ትክክል አይደለም ስላልሁ በእኔ ንግግር የእውነት ፋይዳው ሊቀየር አይችልም። ወይም የአንድ ማኅበረሰብ ወግና ትውፊት የእውነት ዋጋውን ሊወሰን አይችልም። የእኛ ሥነ ዕውቀት *(epistemology)* መለያየት የኑባሬውን *(ontology)* ማንነት ቅንጣት ታህል ሊቀይረው አይችልም።

ክፍል ስድስት

ነቢያትና ነቢይነት በቅዱሳት መጻሕፍት



እኔ ወደ ክርስትና የመጣሁት፣ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት መምህራን በተለምዶ፣ "የተአምራት/የኀይል ስጦታዎች"[1] በመባል የሚታወቁ የጸጋ ችሮታዎችን በተመለከተ፣ ተቃራኒ እንዲሁም የክረረ አቋም በሚያራምዱበት ታሪካዊ ወቅት ነው።

[1] ትንቢት፣ ልሳን፣ ፈውስ።

ነው። ይህ ደግሞ ስሕተት እንደ ሆነ ከላይ በስፋት ለማየት ሙከራ አድርገናል። የእኛ አስተሳሰብ የእውነት ዋጋዋን ሊቀይር አይችልም። "እኔ ክርስቶስ ጌታ ነው" ብል ወይም ባልል፣ የእኔ አነጋገር ወይም አቋም ጌትነቱን ሊሰጠውም ሆነ ሊነፍገው አይችልም፣ "ሰዎች ሁሉ ሐሰተኛ ቢሆኑ እግዚአብሔር ግን እውነት ሆኖ ይኖራል" (ሮሜ 3÷4)። መግደል እኔ ትክክል ነው ወይም ትክክል አይደለም ስላልሁ በእኔ ንግግር የእውነት ፋይዳው ሊቀየር አይችልም። ወይም የአንድ ማኅበረሰብ ወግና ትውፊት የእውነት ዋጋውን ሊወስን አይችልም። የእኛ ሥነ ዕውቀት *(epistemology)* መሰያየት የኑባሬውን *(ontology)* ማንነት ቅንጣት ታህል ሊቀይረው አይችልም።

ክፍል ስድስት

ነቢያትና ነቢይነት በቅዱሳት መጻሕፍት



እኔ ወደ ክርስትና የመጣሁት፣ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት መምህራን በተሰምዶ፣ "የተኣምራት/የኀይል ስጦታዎች"[1] በመባል የሚታወቁ የጸጋ ችሮታዎችን በተመሰከተ፣ ተቃራኒ እንዲሁም የከረረ አቋም በሚያራምዱበት ታሪካዊ ወቅት ነው።

[1] ትንቢት፣ ልሳን፣ ፈውስ።

በአገራቱ ውስጥ ይንቀሳቀሱ የነበሩትና በኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት አስተምህሮ ውስጥ፣ ትልቅ የሆነ አሻራቸውን ትተው የሄዱት የምዕራባውያኑ ሚስዮናዊ ተቋማት፣ ለምሳሌ የኤስ. አይ. ኤም. *(S.I.M)*፣ የሉተራን፣ የባፕቲስት እንዲሁም የሜኖናይት ሚስዮናውያን፣ የተላምራት ስጦታዎች በዛሬዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አያሠሩም፤ አንዳች ፋይዳዊ ጠቀሜታም የላቸውም የሚል አቋም ነበራቸው[2]። ነገር ግን በስዊድናውያን የተቋረቋሩት፣ የአዋሳው ፊላደልፊያ ሚሽንና የመርካቶው ፊንላንድ (ፊኒሽ) ሚሽን፣ ከዚህ ተቃራኒ የሆነ አቋም ነበራቸው። እነዚህ ሚስዮናውያን ተቋማት፣ በካሪዝማዊና በጴንጤቆስጣዊ[3] አቋም ስለነበራቸው፣ የተላምራት ስጦታዎች ለዛሬዋ ቤተ ክርስቲያን ተስጥተዋል፣ በቤተ ክርስቲያን ቀዳማይ ተልእኮ[4] ውስጥም አውናዊ ፋይዳ አላቸው የሚል አቋም ያራምዱ ነበር።

በተለይ በቀደምት ሚስዮናውያን አገልግሎት ጌታን የተቀበሉና በእነርሱም እግር ሥር ቁጭ ብለው ለዓመታት ነገረ መለኮትን የተማሩት፣ ኢትዮጵያውያን የነገረ መለኮት ተማሪዎች፣ የተላምራት ስጦታን በተመለከተ መረር ከረር ያለ አቋም ያራምዱ

[2] ለምሳሌ የኤስ. አይ. ኤም ሚስዮናውያን ከአንድ ቤተ እምነት ወይም አንድ የተወሰነ የነገረ መለኮት ነባቤ ቃል ከሚያራምድ የትምህርት ተቋም የመጡ አይደሉም። ነገር ግን አብዛኞቹ ሚስዮናውያን የተላምራት ስጦታዎች በዛሬዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አያስፈልጉም አንዳች ፋይዳም የላቸውም የሚል አቋም ነበራቸው።

[3] *Charismatic and Pentecostal.*

[4] የቤተ ክርስቲያን ቀዳማይ ተልእኮዎች የሚባሉት፦— *(1)* ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ መስበክ፣ *(2)* የዳነውን ማነበረሰብ በዕውቀትና በምግባር ማነጽ፣ *(3)* አምልኮተ እግዚአብሔር ማስፋፋድ፣ *(4)* ሠናይ ግብሮችን በማነበረሰብ ውስጥ በማከናወን፣ ክርስቲያን የዓለም ብርሃንና ጨው መሆኑን ለዓለም ማሳየት ናቸው።

ነበር—በመደገፍም ሆነ በመቃወም[5]። እንዲያውም ተቃዋሚው ወገን፣ አንቅስቃሴውን ከክፉ መንፈስ አሠራር ጋር አያይዞ የሚመለከትበትም ጽንፍ ነበር።

ጴንጤቆስጣዊ ልምምድን ያበረታቱ የነበሩት አብያተ ክርስቲያናት፣ በርካታ አባል መስብሰብ የቻሉት በዚህ ወቅት ይመስለኛል። ከሉተራን፣ ከቃለ ሕይወት፣ ከመካነ ኢየሱስ፣ ከመጥምቃውያን አብያተ ክርስቲያናት በርካታ አገልጋዮች፣ "መንፈስ ቅዱስ በሙላት ወደሚሠራባት ቤተ ክርስቲያን ኑ" የሚሰውን ጥሪ በመከተል፣ ብዙዎች አናት ቤተ ክርስቲያናቸውን በመተው ወደ ጴንጤቆስጣውያኑ አብያተ ክርስቲያናት ይጉርፉ አንደ ነበር አስታውሳለሁ—በተለይ ደግሞ ወደ ሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያንና ወደ መሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን[6]።

በርካታ ኢትዮጵያውያን አገልጋዮች ነገረ መለኮትን የመማር ዕድል ያገኙት፣ ጴንጤቆስጣዊ ባልሆኑ ሚስዮናውያን በቁረቁሯቸው የነገረ መለኮት ተቋማት ነው—ከአገር ውጪም ሆነ በአገር ውስጥ።

[5] በጊዜ ብዛት ግን በብዙዎች ዘንድ ይታይ የነበረው ይህ የከረረ አቋም፣ እየጠየመ (እየላላ) መምጣቱ እሙን ነው። ምክንያቱም ብዙዎቹ ኋላ በመጣው አማኝ፣ "የመንፈስ ቅዱስ ተቃዋሚ"፣ "መንፈስ ቅዱስን የማይቀበል"፣ "ደረቅ" ወዘተ የሚል መታወቂያ ቅጥር ስለተሰጣቸው፣ አቋማቸውን ማለሳለስ የግድ ሆኖባቸዋል። የተላምራት ስጦታዎች ዛሬ የሉም የሚለው አቋማቸው ስሕተት ነው የሚል አቋም ቢኖረኝም እንኳ፣ ስያሜው ግን እጅግ የተሳሳተ ምናልባትም እጅግ አደገኛ መሆኑን ማንም ሰው ሊክደው አይገባም። ምክንያቱም ግለሰቦቹ የተላምራት ስጦታዎች የሉም የሚለው አቋማቸው፣ የሥላሴ ሦስተኛ አካል የሆነው መንፈስ ቅዱስ የለም ወይም መንፈስ ቅዱስ ዛሬ በራሱ መንገድ ሥራውን አይሠራም የሚል እምነት የላቸውምና።

[6] መሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን የቁረቁሩት ሜኖናይት ሚስዮናውያን የተላምራት ስጦታዎች ዛሬ የሉም የሚል አቋም ቢኖራቸውም፣ ኋላ ግን ይህን አቋም በማለሳለሳቸው፣ ቤተ ክርስቲያኒቱ ጴንጤቆስጣዊ እንቅስቃሴን ከሚደግፉ ቤተ ክርስቲያን አንዱ ሆናለች።

ኋላ አብዛኞቹ አብያተ ክርስቲያናት የተኣምራት (የጎይል) ስጦታዎች በሚባለው ዙሪያ ያላቸውን አቋም በይፋ በማስተካከል፣ አንቀጻ ሃይማኖታቸውንም በመከለስ፣ የጴንጤቁስጤ ልምምዱን በይፋ ተቀላቅለዋል።

የተኣምራት ስጦታዎች የሉም፣ አስፈላጊነትም የላቸውም የሚሉ ሰዎች ያነሡ የነበረው ክርክር አንድ ጭብጥ ነገር ግን ሁለት ገጽ ያለው ሙግት ነው። ይኸውም፦— *(1)* የብሉይና የሐዲስ ኪዳን ቀኖናዊ መጻሕፍት ተጠናቀው በእጃችን በገቡበት በዚህ ወቅት፣ የትንቢት ስጦታ ዛሬም አስ የምንል ከሆነ፣ መጽሐፍ ቅዱስ የአምላክ ሥልጣናዊና ብቸኛ ቃል ነው የሚለውን አቋማችንን ገደል ይከትብናል የሚለው አንዱ ሲሆን፣ *(2)* እነዚህ ስጦታዎች አሉ ከተባለ፣ ሰዎች ስቃለ እግዚአብሔር ያላቸው ጥማት ይቀንላል፣ ተኣምር ናፋቂዎች በመሆን ስቅዱስ ቃሉ ያላቸው ቦታ ይመናመናል የሚለው ደግሞ ሁለተኛው ገጽ ነው[7]። ምናልባት በእነዚህ ሁለት አቋሞች መካል ወዲህና ወዲያ የሚዋዥቁ፣ መካል ስፋሪዎችን በሦስተኛው ጐራ ልንይዛቸው እንችላለን።

ይህ በኢትዮጵያ የነበረው ልዩነት፣ በአሜሪካን የነገረ መለኮት ተቋሞችም ውስጥ በስፋት የነበረና ነባብያነ መለኮቶች በሁለት ወግነው ስዘመናት ሲጠዛጠዙበት የኖረ፣ አሁን ግን ደብዛው እየጠፋ ያለ የነገረ መለኮት አቋም ልዩነት ነው[8]። አየቀረበ ያለው የመጽሐፍ ቅዱስ መረጃ አላላመነንም ከሚሉ ከጥቂት ግለሰቦች በስተቀር፣ በዚህ ረገድ የነገረ መለኮቱ ቤት በአንድ ታዛ ሥር እየተስባሰበ ነው ቢባል፣ አብለት የሚሆን አይመስለኝም።

[7] ኋላ ለእነዚህ መከራከሪያዎች ረዛብ ማለታገሻ መልስ ለመስጠት እሞክራለሁ።

[8] በእንግሊዝኛው *Cessationism* ይባላል።

ለምሳሌ እኔ የተማርሁበት ካልቪን ሴሚናርየም *(Calvin Theological Seminary)* የጎይል ስጦታዎች የሉም የሚለውን አቋማቸውን በይፋ ከቀየሩ የትምህርት ተቋማት መካል አንዱ ነው[9]። ወደ ኢትዮጵያ የመጡ አሜሪካውያን ሚስዮናውያን በብዛት ተምረውበታል የሚባለው የዳላስ የነገረ መለኮት ሴሚናርየም *(Dallas Theological Seminary)*፣ የተኣምራት ስጦታዎች ቆመዋል የሚለውን አቋሙን አለላልሷል። በእነዚህ ተቋማት ያስተምሩ የነበሩ አንዳንድ መምህራን፣ የተኣምራት ስጦታዎች ዛሬ አሉ በሚለው አቋማቸው ከማስተማር ሥራቸው ተባረው ነበር[10]።

ዛሬ በሰሜን አሜሪካ የሚገኙ፣ ስመ ጥር ሲቃውንት አንዲሁም አብዛኞቹ የነገረ መለኮት ተቋማት፣ የተኣምራት ስጦታዎች በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን ቆመዋል የሚል አቋም የላቸውም። ይልቁንም የተኣምራት ስጦታዎች አሉ አንዲሁም ስዛሬዋ ቤተ ክርስቲያን ትልቅ ጠቀሜታ አላቸው የሚለውን አቋም በስፋት በማስተጋባት ላይ ናቸው[11]።

[9] የትምህርት ቤቱን አቋም ይፋ ካደረጉ ለነዶች መካል የሚከተለውን ለነድ አንዲሁም ድረ ገጽ ይመለከታል፦—

https://www.calvinseminary.edu/wp-content/uploads/forums/07fall.pdf

Calvin Theological Seminary Forum Fall 2007.

የተኣምራት ስጦታዎች ዛሬም አሉ የሚለው አቋም፣ በእንግሊዝኛው *Continuationism/nonCessationism* ይባላል።

[10] ለምሳሌ በዳላስ ሴሚናሪየም የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ፕሮፌሰር የነበረው *Professor Jack Deere.*

[11] ታዋቂው የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ምሁር ክሬግ ኪነር፣ *Craig S. Keener, Spirit Hermeneutics: Reading Scripture in Light of Pentecost, (Grand Rapids, MI.: Eerdmans, 2016)* ቡተለላለው መጽሐፉ ጴንጤቁስጣዊ አቋም እንዲሁም ልምምድ ያላቸውን እጅግ በርካታ ስመ ጥር ሲቃውንት ዘርዝሮአል። እነዚህ ሲቃውንት እጅግ ስመ ጥር በሚባሉ የዓለማችን ዩኒቨርስቲዎችና ሴሚነሪዎች ውስጥ ደርዛዊ ነገረ መለኮትን፣ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍትን፣ ፍልስፍናን

በሁሰቱ ጉራዎች (ማስትም የተአምራት ስጦታዎች እሱ ወይስ የሱም) የሚቀርቡትን ሙግቶችና አፀፋዊ ምላሾች በመተንተን፣ እናንተንም ሆነ ራሴን አላደክምም። ይህ መጽሐፍ ይዞ ከተነሣው ጭብጥ አኳያም፣ ይህን ውይይት በዚህ ቦታ ይዞ መቅረቡ ፋይዳ ያለው አልመሰለኝም። ባይሆን ይህን መሰል ውይይት የሌላ መጽሐፍ ወይም መጣጥፍ ጭብጥ አድርጌው ብቅ ልል እችላለሁ—ልዑል እግዚአብሔር ፈቃዱ ከሆነ፣ ዕድሜውንና ጤንነቱን ከሰጠኝ። ይህ እንዳለ ሆኖ ግን፣ የተአምራት ስጦታዎች ዛሬ መኖራቸውን የሚያስተምሩ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንባባትን ከመዘርዘርም በላይ፣ የሱም የሚሉ ሰዎች ከሚያቀርቧቸው ሙግቶች መኻል ተገቢ ስፍራ ሊሰጣቸው የሚገባቸውን ሰማብራራት ሙከራ እደርጋለሁ[12]።

የውይይቱ ጭብጥ

በዘመነ ብሉይም ሆነ በዘመነ ሐዲስ፣ ነቢይነት በወንዶች ብቻ የተወሰነ የእገልግሎት ዘርፍ እይደለም። ሰምሳሌ የሙሴ እኅት ማርያም ነቢዪት እንደ ነበረች ይታወቃል (ዘፀ. 15÷20)። እንዲሁም ዲቦራ (መሳ. 4÷4)፣ ሕልዳና (2ነገ. 22÷14-20፣ 2ዜና 34÷22)፣ ኖዓድያ (ነህ. 6÷14 እንዲሁም ኢሳ. 8÷3 ይመለከቷል) ነቢያት[13] እንደ ነበሩ እናነባለን። በሐዲስ ኪዳንም ሴት ነቢያት እንደ ነበሩ እናነባለን። ሰምሳሌ ሐና (ሉቃ. 2÷36) እንዲሁም የፊልጶስ እራት ሴት ልጆች ነቢያት ነበሩ (ሐሥ. 21÷9)። ትንቢት መናገር ስሴቶችም ሆነ ሰወንዶች እኩል የሚሰጥ ስጦታ እንደ ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል (ሐሥ 2÷17)።

በእስራኤል ምድር በጥምረት የሚያገለግሉ የነቢያት ጎበረቶች እንደ ነበሩ ፍንጭ ጠቋሚ ምንባባትን እናገኛለን (1ሳሙ. 10÷5፣ 1ነገ. 18÷4)። እነዚህም ነቢያት የነቢያት ልጆች በመባል ይጠሩ እንደ ነበረ እናነባለን (2ነገ. 2÷3፡5፡7፣ 4÷38)።

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ወደ ነቢያት እንዴት እንደሚመጣ ማብራሪያ አይሰጠንም። ነገር ግን እግዚአብሔር ፈቃዱን በተለያየ መንገድ ለነቢያቱ እንደሚገልጽ ይናገራል፣ ለምሳሌ በራእይ (1ሳሙ. 3÷1፡15፣ 2ሳሙ 7÷17፣ ኢሳ. 1÷1፣ ሕዝ. 11÷24)፣ በህልም (ዘኍ 12÷6)።

የተነሣንበትን ዐላማ ከዳር ማድረስ እንችል ዘንድ፣ የምንነጋገርባቸውን ርእሰ ጉዳዮች መምረጥና መወሰን የግድ ይሆናል። ስለዚህም በዚህ ክፍል በሚከተሉት ርእሰ ጉዳዮች ላይ ብቻ፣ በዚሁ ቅደም ተከተል እንነጋገራለን፡—

የሚያስተምሩ ናቸው። ይህ ባለፉት ሠላሳ ዓመታት፣ በዚህ ረገድ ያለው ለውጥ ምን ያህል ከፍተኛ እንደ ሆነ በግልጽ የሚያሳይ ይመስለኛል።

[12] በነገረ መለኮት ተቋማት አብረውኝ የተማሩ አንዳንድ ባልንጀሮቼ የተአምራት ስጦታዎች ዛሬ የሉም የሚል ጠንካራ አቋም ነበራቸው። ነገር ግን ዛሬ እነዚህን ሰዎች ጨምሮ አንዳችም ኢትዮጵያዊ የተአምራት ስጦታዎች ቆመዋል የሚል አቋም ያለው ሰው እኔ በግሌ አላውቅም። አንዳንድ ስም አጥፊዎች፣ "ተስፋዱ እነዚህ ስጦታዎች አንዳሉ አይቀበልም" የሚል ወሬ እንደሚያናፍሱ ሰምቻለሁ። ይህ ግን ፍጹም ስሕተት ከመሆኑም ባሻገር፣ በታሪኬ ውስጥ እንደዚያ ዐይነት አቋም ኖሮኝ አያውቅም፣ ምናልባት ከስም አጥፊዎቹ በላይ እኔ የእነዚህ ስጦታዎች ተከላይ ሆኜስ ቢሆን?

[13] አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ "ነቢያን" ተባዕት ብዙ፣ "ነቢያት" ደግሞ አንስታይ ብዙ ነው ይላሉ፣ ገጽ 620። ይህ ትክክል ከሆነ፣ ነቢይ ነቢያን፣ ነቢዪት ደግሞ ነቢያት ይሆናል ማለት ነው። በተለምዶ ግን "ነቢያት" የሚለውን አንስታይ ብዙ፣ ተባዕት ብዙ አድርገን ስንጠቀም ኖረናል፣ አይ አለማወቅ። በዚህ ጽሑፍ የተከተልሁት አለቃ ኪዳነ ወልድን ሳይሆን፣ የተለመደውን ጀማ አካሄድ ነው። "ነቢያት" አንስታይ ብዙ ነው ብል ማን ያምናል? "ልማድ ሲለሰነን ቀኖና ይሆናል" ይላል ይህ ነው።

1. ነቢያትና ነቢይነት በብሉይ ኪዳን
2. ነቢያትና ነቢይነት በሐዲስ ኪዳን
3. ትንቢትና ዐሥሩ መሠረታውያን
4. ዛሬ የተአምራት ስጦታዎች የሉምን?
5. የዛሬዎቹ ነቢያት የመሳሳት ፈቃድ ተሰጥቶአቸዋልን?

1. ነቢያትና ነቢይነት በብሉይ ኪዳን

ሐዲስ ኪዳን ስለነቢይነት ስጦታና አገልግሎት የሚያስተምረውን ትምህርት በትክክል ለመረዳት፣ ብሉይ ኪዳንን መቃኘቱ ከብዙ አንጻር ውይይታችንን ያደላድለዋል[14]።

(1) **የብሉይ ኪዳን ነቢያት የአምላክ ወኪሎች ናቸው!**

የብሉይ ኪዳን ነቢያት፣ የእግዚአብሔር ወኪሎች ወይም አምባሳደሮች ነበሩ። እግዚአብሔር ለሙሴ የሚከተለውን ተስፋ ሰጥቶታል፣ "በል አሁን ሂድ፣ እኔ እንድትናገር አደርግሃለሁ፣ የምትናገረውንም አስተምርሃለሁ አለው" (ዘፀ. *4÷12*)። "ከወንድሞቻቸው መካከል እንደ አንተ ያለ ነቢይ አስነሣላቸዋለሁ፣ ቃሌን በአፉ አደርጋለሁ፣ የማዘውንም ሁሉ ይነግራቸዋል" (ዘዳ. *18÷18*)። ለኤርምያስም እንዲህ ሲል ተስፋ ሰጥቶታል፣

[14] ልዩ መግለጫ ካልቀረበ በቀር፣ "ነቢያትና ነቢይነት በብሉይ ኪዳን" በሚለው ክፍል ውስጥ ያሉት ሐሳቦች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተወሰዱት ከሚከተሉት አራት መጻሕፍት ነው፦ *Wayne Grudem, The Gift of Prophecy in the New Testament and Today, (Wheaton, Illinois: Crossway Books, 2000). Jack Deere, The Beginner's Guide to the Gift of Prophecy, (Bloomington, Minnesota: Chosen Books, 2001). D. A. Carson, Showing the Spirit: A Theological Exposition of 1 Corinthians, 12-14, (Grand Rapids, Mi.: Baker, 1987). Jack Deere, Surprised by the Power of the Spirit: Discovering How God Speaks and Heals Today, (Grand Rapids, MI.: Zondervan, 2010).*

"እግዚአብሔርም እጁን ዘርግቶ አፌን ዳሰሰና እንዲህ አለኝ፣ 'አነሆ፣ ቃሌን በአፍህ አኑሬአለሁ'" (ኤር. *1÷9*)። ሕዝቅኤልን የሾመው እንዲህ ሲል ነው፣ "እነርሱ ዐመፀኛ ቤት ስለሆኑ፣ ቢሰሙም ባይሰሙም አንተ ቃሌን ንገራቸው" (ሕዝ. *2÷7*)።

በዚህም መልክ የእግዚአብሔርን መልእክት ለሰዎች ይናገሩ ነበር፣ "የእግዚአብሔርም መልእክተኛ ሐጌ፣ በእግዚአብሔር መልእክት ሕዝቡን እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ፣ ይላል እግዚአብሔር ብሎ ተናገረ" (ሐጌ *1÷13*፤ አብድዩ *1÷1*)። እግዚአብሔር መልእክቱን፣ "በነቢዩ በናታን እጅ ላከ" (*2ሳሙ 12÷25*)። እግዚአብሔር ንጉሥ ሕዝቅያስን ለመታደግ በነቢዩ ኢሳይያስ አማካይነት መልእክት ላከ (*2ነገ. 20÷4-6*)።

በርግጥም አውነተኛ ነቢይ የሚባለው፣ "እግዚአብሔር በእውነት የለደደው" ነቢይ ብቻ ነው (ኤር. *28÷9*)። አባይ ነባይ ደግሞ፣ እግዚአብሔር፣ "በስሜ ሐሰተኛ ትንቢትን ይናገሩላችኋልና፣ እኔም አልላክኋቸውም" የሚላቸው ናቸው (ኤር. *29÷9*፤ ሕዝ. *13÷6*)።

(2) **የብሉይ ኪዳን ነቢያት ቃላቸው የአምላክ ቃል ነው!**

የብሉይ ኪዳን ነቢያት አምላክ አሳብ ለጥቂቱ የሰጣቸውን ጭብጥ በራሳቸው መንገድ የሚያብራሩ ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ፣ አምላክ አፋቸውን የተዋሳቸው ሰዎችም ነበሩ። የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል፦—

- "እንግዲህ አሁን ሂድ፣ እኔም ከአፍህ ጋር እሆናለሁ፣ የምትናገረውንም አስተምርሃለሁ አለው" (ዘፀ. *4÷12* እንዲሁም *24÷3*)።

- “በሰዓምም ባላቅን፣ እነሆ ወደ አንተ መጥቼአለሁ፤ በውኑ አሁን እንዳችን ነገር አናገር ዘንድ እችላለሁን? እግዚአብሔር በአፌ የሚያደርገውን ቃል እርሱን አናገራለሁ አለው” (ዘኍ. *22÷38* እንዲሁም *23÷5:16*)።
- “ከወንድሞቻቸው መካከል እንደ አንተ ያለ ነቢይ አስነሣላቸዋለሁ፤ ቃሌንም በአፉ አደርጋለሁ፤ ያዘዝሁትንም ቃል ሁሉ ይነግራቸዋል” (ዘዳ. *18÷18* እንዲሁም ቍጥር *21-22*)።
- “እግዚአብሔር እጁን ዘርግቶ አፌን ዳሰሰ፤ አግዚአብሔርም አነሆ ቃሌን በአፍህ ውስጥ አኑሬአለሁ...አለኝ” (ኤር. *1÷9*)።
- “እነርሱም ዐመፀኛ ቤት ናቸውና፤ ቢሰሙ ወይም ባይሰሙ ነቢይ በመካከላቸው እንዳለ ያቃሉ” (ሕዝ. *2÷7* እንዲሁም *3÷17*)።

በዚህም አግባብ ነው የብሉይ ኪዳን ነቢያት፣ በአንደኛ መደብ ነጠላ ተውላጠ ስም፣ “እኔ እግዚአብሔር ... እንዲህና እንዲያ አደርጋለሁ” የሚለውን ንግግር እምላክን ወክለው ይናገሩ የነበረው፣ “አኔም አግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቃለህ” (*1ነገ. 20÷13*)፣ “እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ ከእኔም ሌላ ምንም የለም፤ ከእኔም በቀር አምላክ የለም፤ በፀሓይ መውጫና በምዕራብ ያሉ ከእኔ በቀር ማንም ሌላ እንደ ሌለ ያውቁ ዘንድ አስታጠቅሁህ፤ አንተ ግን አላወቅኸኝም፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ ከእኔም ሌላ ማንም የለም” (ኢሳ. *45÷5* እንዲሁም የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል:— *2ሳሙ 7÷4-16*፤ *1ነገ. 20÷13:42*፤ *2ነገ. 17÷13*፤ *19÷25-28:34*፤ *21÷12-15*፤ *22÷16-20*፤ *2ዜና. 12÷5*)። ከእነዚህ መረጃዎች በግልጽ የምንማረው፣ እነዚህ ንግግሮች የእምላክ ቃል እንጂ፣ የነቢያቱ አስተያየት ናቸው ብሎ የሚያስብ አንድም እስራኤላዊ የለም። ለዚህም ነው የብሉይ ኪዳን ነቢያት፣

“የሰራዊት አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል...” የሚለውን ንግግር የትንቢታቸው መነሻ ያደርጉ የነበረው።

ነቢያት የእግዚአብሔር አፍ ናቸው፣ “በእግዚአብሔር አፍ ላይ ዐምፀሃልና፤ አምላክህም አግዚአብሔር ያዘዘህን ትእዛዝ አልጠበቅህምና...በእግዚአብሔር አፍ ላይ ያመፀ ያ የእግዚአብሔር ስው ነው፤ እግዚአብሔር እንደ ተናገረው ቃል፣ አግዚአብሔር ስአንበሳ አሳልፎ ሰጥቶታል፤ ሰብሮም ገድሎታል አለ” (*1ነገ. 13÷21:26*)። የእስራኤል ሕዝብ የነቢያቱን ቃል የሚያስታውስው፣ “በባሪያውም በነቢዩ በአሒያ አንደ ተናገው አንደ እግዚአብሔር ቃል...” በሚለው ሁኔታ ነበር (*1ነገ. 14÷18*፤ *16÷12*፤ *2ነገ. 9÷36*፤ *14÷25*፤ *17÷23*፤ *24÷2*፤ *2ዜና 29÷25*፤ *ዕዝ. 9÷10-11*፤ *ነህ. 9÷30*፤ *ኤር. 37÷2*፤ *ዘካ. 7÷7:12* ወዘተረፈ)። ይህም የነቢያቱ አፍ የእግዚአብሔር አፍ፣ የነቢያቱም ቃል የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን የሚያጸና ነው።

(3) የብሉይ ኪዳን ነቢያት የኪዳኑ ጠባቂዎች ናቸው!

ነቢያት የኪዳኑ መልእክተኞች ናቸው[15]። ይኸውም አስራኤል ከአምላኪ ጋር የገባችውን ኪዳን እንድታስብ፣ ስትሳሳት እንድትመለስ፣ ስትበድል ንስሓ እንድትገባ፣ በዐመፅ ከጸናች ደግሞ ቅጣት አንደሚጠብቃት የሚያሳስቡ ናቸው (ለምሳሌ የሚከተሉትን ምንባባት ይመለከቷል:— *2ዜና 24÷19*፤ *ነህ. 9÷26:30*፤ *ኤር. 7÷25*፤

[15] ይህን ሐሳብ ያገኘሁት ከሚከተለው መጽሐፍ ነው:— ምኒልክ አስፋው ፍቅረ ሥላሴ፣ *መጽሐፍ ቅዱስና የትርጓሜ ስልቱ፣ ቅዱሳት መጻሕፍት እንዴት ይነበቡ? እንዴት ይተርጐሙ? እንዴት ይተግበሩ?* (ምኒልክ አስፋው፣ ግራንድ ራፒድስ ሚሺገን፣ *2017* ዓ.ም)፣ *268-301*።

ሚል. 4÷4-6)። የአንድ አገር አምባሳደር ያልተላከውን አንደማይናገር ሁሉ፣ ነቢያትም አምላክ ያላዘዛቸውን አያደርጉም፤ አይናገሩም።

ብዙ ጊዜ ነቢያት ትንቢት አንደሚተነብዩ አድርገን ብቻ ነው የምናስበው፤ ይህ ግን ከብሉይ ኪዳን ነቢያት አገልግሎት አንጻር ስሕተት ነው። ነቢያት የዐላፊውንና የአሁኑን ጊዜ ነባራዊ ሁኔታ በመጥቀስ ዘለፋም ሆነ ማበረታቻ ያቀርባሉ። ነቢያት፣ አስራኤል የኪዳኗን አምላክ ስትተው በኪዳኑ ቃል ላይ ስታምፅ ለንስሓ ይጠሯታል፤ እንድትመለስ ይጋብዟታል። በአልሸኘነቷ የምትጸና ከሆነ ደግሞ፣ ቅጣት አንደሚጠብቃት ይገልጹላታል። ከዚህ አንጻር ሲታይ የብሉይ ኪዳን ነቢያት የሕጉ መምህራንና ጠባቂዎች/ጉበኞች ናቸው።

(4) የብሉይ ኪዳን ነቢያትን ያለመቀበል፣ እግዚአብሔርን ያለመቀበል ነው!

የብሉይ ኪዳን ነቢያት የሚያስተላልፉትን ቃል መቀበል አምላክን መቀበል፣ በአንጻሩ ደግሞ የንግግራቸውን ዝርዝር አሳብ እንኳ ያለመቀበል፣ አምላክን ያለመቀበል ነው። ምክንያቱም ነቢያቱን የሚልከው ራሱ አግዚአብሔር ነውና። አነርሱንም ያለመታዘዝና ያለማመን አምላክን ያለመታዘዝና ያለማመን ነው (ዘዳ. 18÷19፤ 1ሳሙ. 8÷7፡18፡23፤ 1ነገ. 20÷36፤ 2ነገ. 25÷16፤ ኢሳ. 30÷12-14፤ ኤር. 6÷10-11፡16-19 ወዘተ)።

የነቢያት ትንቢት በአስራኤል ማኅበረሰብ ውስጥ ትልቅ ስፍራ አንዳላቸው ሁሉ፤ ትንቢታቸው ሐሰት ሆኖ ከተገኘ ግን፣ አይቀጡ ቅጣት አንዲቀጡ የሕጉ መጽሐፍ በአጽንኦት ያዛል (ዘዳ. 18÷1-22፤ 13÷1-18፤ 1ነገ. 18÷19፤ 22÷28፤ መሳ. 3÷5-7 ወዘተ)። ትልቅ ሥልጣን

ትልቅ ጥፋት ያስከትላል፤ ትልቅ ጥፋትም ትልቅ ቅጣትን የግድ ይላል።

(5) የነቢያቱ ቀዳማይ አገልግሎት ሕጉን ማስተማር፣ መምከርና ማስጠንቀቅ ነው!

የብሉይ ኪዳን ነቢያት ቀዳማይ አገልግሎት የሕጉን መጽሐፍ ማስተማር አንዲሁም ሕዝቡ ከሕጉ መጽሐፍ ሲርቅ ማስጠንቀቅና በንስሓ እንዲመለስ ማድረግ ነው[16]።

> "አብርሃም የተመረጠው፣ "የምድር ነገዶች ሁሉ በእርሱ እንዲባረኩ" (ዘፍ 12÷3) ነው። የእስራኤል መመረጥና የሕጉ ሞግዚት መሆን ከዚህ ተልእኮ ጋር በእጅጉ ይዛመዳል። እስራኤል በዙሪያዋ ባለው ዓለም ሥርዐት እንድትዋጥ ላይሆን በዙሪያዋ ላለው ዓለም ብርሃን እንድትሆን ተመርጣ ነበር። "ከአሕዛብ ሁሉ የተመረጠ ርስት ትሆኑኛላችሁ፤ እናንተም የካህናት መንግሥት የተቀደሰም ሕዝብ ትሆኑኛላችሁ" (ዘጸ 19÷5-6)። ሕዝቡ ሕጉን መተላለፉ ብቻ ሳይሆን ከሕጉ እንድምታ ጨርሶ መራቁ ያልተጠበቀ ቢመሰልም ውጤቱ አሳታዊ ነበር። በተሰይ ከኢያሱ ሞት በኋላ የሕዝቡ መረን መውጣት (ሞልጥ ብሎ መጥፋት) የተመረጠበትን ዐላማ ለአደጋ አጋልጧል። በመጽሐፈ መሳፍንት ውስጥ፣ "ሰው ሁሉ በፊቱ መልካም መስሎ የታየውን ያደርግ ነበር" (17÷6፤ 21÷25) የሚለው

---

[16] ይህን እንዲሁም የሚከተለውን ነጥብ ቃል በቃል የወሰድሁት፣ ከወዳጄ ከምኒልክ አስፋው መጽሐፍ ነው። ዕንስ ሐሳቡም ሆነ አቀራረቡ፣ እኔ ላቀርበው ከምችለው በብዙ መልኩ የተሻለ ስለሆነ፣ ዐጮል ካክቹ እጅጅ እንዳይል፣ ቃል በቃል ጠቅሼዋለሁ። ምኒልክ አስፋው ፍቅረ ሥላሴ፣ *መጽሐፍ ቅዱስና የትርጓሜ ስልቱ፣ ቅዱሳት መጻሕፍት እንዴት ይነበቡ? እንዴት ይተርጐሙ? እንዴት ይተግበሩ?* (ምኒልክ አስፋው፤ ግራንድ ራፒድስ ሚሽን፤ 2017 ዓ.ም)።

ነለጻ እሰራኤል በጥቂት ዓመታት ውስጥ ከወዴት እንደ ወደቀች ያሳያል"[17]።

"የትንቢት መጻሕፍቱ አብዛኛው ክፍል የሚያወሳው ስለ መጪው ዘመን ሳይሆን ስለ እስራኤል መታዘዝና አለመታዘዝ በዚህም በሕዝቡ ላይ ስለ መጣውና ስለሚመጣው ፍርድ ነው (ኢሳ 1÷2-9፤ ኤር 2÷4-8፤ ሕዝ 3÷16-18፤ ሆሴ 14÷1-2)"[18]።

"ከሁሉ በላይ ግን ሕዝቡ አምላኩን እግዚአብሔርን ሲተውና እርሱንም መፍራት ችላ ሲል ምን ያህል ክፉና መራራ ነገር እንደ ፈጸመ፡ መግለጽና መገለጡንም መጠቆም ነው (ኤር 2÷19)"[19]።

"የይሁዳ ንጉሥ የአሞጽ ልጅ ኢዮስያስ ከነገሠበት ከዐሥራ ሦስተኛው ዓመት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ሃያ ሦስት ዓመት ሙሉ የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ መጣ፤ ደጋግሜም ነገርኋችሁ፤ እናንተ ግን አልሰማችሁም። እግዚአብሔር አገልጋዮቹን ነቢያትን ሁሉ ደጋግሞ ወደ እናንተ ላከ፤ ሆናም አልሰማችሁም፤ ትኩረትም አልሰጣችሁ። እነርሱም እንዲህ አሉ፤ እንግዲህ ሁላችሁ ከክፉ መንገዳችሁና ከክፉ ሥራችሁ ተመለሱ. . . ሌሎቹን አማልክት አትከተሉ (ኤር. 25÷3-6)[20]።

(6) ነቢያት ቀዋምያነ እግዚአብሔር (ዐቃቤ እምነቶች) ነበሩ!

"በካት ደህ.ልና ዳንኤል ሄይስ፣ 'ነቢያት የእግዚአብሔር ዐቃቤ ሕግ ነበሩ' ይላሉ[21]። ነቢያት በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል በመቆም ለሕዝቡ

[17] ምኒልክ አበራው ፍቅረ ሥላሴ፤ *መጽሐፍ ቅዱስና የትርጓሜ ስልቱ፤ ቅዱሳት መጻሕፍት እንዴት ይነበቡ? እንዴት ይተርጐሙ? እንዴት ይተግበሩ?* (ምኒልክ አበራው፤ ግራንድ ራፒድስ ሚሽገን፤ 2017 ዓ.ም)፤ ገጽ 273።

[18] ዝኒ. ከማሁ፤ 270-271። ከ*J. Scott Duvall and J. Daniel Hays, Grasping God's Word: A Hands-On Approach to Reading, Interpreting, and Applying the Bible (Grand Rapids: Zondervan, 2001) 357-360.* ጠቅሶ እንደ ጸፈው።

[19] ዝኒ. ከማሁ።

[20] ዝኒ. ከማሁ።

[21] ዝኒ. ከማሁ፤ 278። ከ*Duvall and Hays, Grasping God's Word,* 361. ጠቅሶ እንደ ጸፈው።

በናንተም የእግዚአብሔር ጠበቆችም ነበሩ። ሕዝቡ መንገዱን በመሳት ወደ ጣዖታት ዘወር ሲል እየወቀሱ ይከሱታል። እግዚአብሔርና ሕዝቡ እንደማይነጣጠሉ ሁሉ ኪዳኑና ሕዝቡም አይነጣጠሉም። ነቢያቱ ይህን መሠረታዊ ትስስር ነበር ለሕዝቡ የሚያስታውቁት፤ 'መንገዳቸውን እንድታውቅና እንድትፈትን በሕዝቤ መካከል ፈታኝ አድርጌሃለሁ' (ኤር 6÷27)።"[22]

"አብርሃም ሂሼል እንደሚለው የነቢያቱ፤ 'ጆሮ' እግዚአብሔርን ሲያዳምጥ 'ዐይናቸው' ሕዝቡን ይመለከት ነበር።[23] እንግዲህ ነቢያት መልእክተኞች ብቻ ሳይሆኑ ከሳሾችም ነበሩ። በአንድ በኩል ይመክራሉ፤ በሌላ በኩል ይወቅሳሉ፤ በአንድ በኩል ያውጃሉ በሌላ በኩል ክስ ያቀርባሉ። የነቢያቱ ዐዋጅ ብዙ ገጽታዎች ቢኖሩትም በሦስት ዐቢይ ክፍሎች መወቃለል ይችላል። እነርሱም *1)* ንስሐ፤ *2)* ፍርድ እና *3)* ተስፋ ናቸው።"[24]

2. ነቢያትና ነቢይነት በሐዲስ ኪዳን[25]

በሁለቱ ኪዳናት መካከል፤ ማለትም በብሉይ ኪዳን የመጨረሻዎቹ ነቢያት በሚባሉት ሐጌ፤ ዘካርያስና ሚልክያስ[26]

[22] ዝኒ. ከማሁ፤ 278-279።

[23] ዝኒ. ከማሁ፤ 279፤ ከ*Abraham J. Heschel, The Prophets: An Introduction (New York: Harper & Row Publishers, 1962) 21.* ጠቅሶ እንደ ጸፈው፡

[24] ዝኒ. ከማሁ፤ 278-79።

[25] ልዩ መግለጫ ካልቀረበ በቀር፤ "ነቢያትና ነቢይነት በሐዲስ ኪዳን" በሚለው ክፍል ውስጥ ያሉት ሐሳቦች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተወሰዱት ከሚከተሉት አራት መጻሕፍት ነው፡— *Wayne Grudem, The Gift of Prophecy in the New Testament and Today, (Wheaton, Illinois: Crossway Books, 2000). Jack Deere, The Beginner's Guide to the Gift of Prophecy, (Bloomington, Minnesota: Chosen Books, 2001). D. A. Carson, Showing the Spirit: A Theological Exposition of 1 Corinthians, 12-14, (Grand Rapids, MI.: Baker, 1987). Jack Deere, Surprised by the Power of the Spirit: Discovering How God Speaks and Heals Today, (Grand Rapids, MI.: Zondervan, 2010).*

እንዲሁም በሐዲስ ኪዳን የመጀመሪያው ነቢይ መጥምቁ ዮሐንስ[27] መካከል የአራት መቶ ዓመት ገደማ ክፍተት እንዳለ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ይገልጻሉ (ማቴ. 11÷9፤ ሉቃ. 1÷76)። እንዳንድ ሰዎች ይህን ወቅት፣ "የጸጥታው ዘመን" ሲሉት አንዳንዶች ደግሞ፣ "በኪዳናት መካከል" *(Intertestamental Period)* ይሉታል። "የጸጥታው ዘመን" የሚለው ገለጻ የሚያሳየው፣ በዚህን ወቅት እንድም ታዋቂና ተአማኒ የብሉይ ኪዳን ነቢይ በምድረ እስራኤል ስላልተነሣ፣ ትንቢትም እንዳልተናገረ የሚገልጽ ነው።

ሐዋርያው ጴጥሮስ በዓለ ኀምሳ ቀን፣ ብሉያት በግልጽ የተናገሩለት የመሲሑ ዘመን፣ በአሕዛብ ላይ መንፈስ ቅዱስ በመውረዱ አሮጌው ዘመን እንደ ጠባ፣ አዲሱ ዘመን እንዳ ባተ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ አበሠረ (ሐሥ 2÷17)። ይህም አምላክ በብሉያት የተናገረው ትንቢት ፍጻሜ መሆኑን ጴጥሮስ ገለጸ፣

> "16. ነገር ግን ይህ በነቢዩ በኢዩኤል እንዲህ ተብሎ የተነገረ ነው፤ 17. 'እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ በመጨረሻው ቀን፣ መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈሳለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁ ትንቢት ይናገራሉ፤ ጕልማሶቻችሁ ራእይ ያያሉ፤ ሽማግሌዎቻችሁ ሕልም ያልማሉ። 18. በዚያ ጊዜ በወንዶችና በሴቶች አገልጋዮቼ ላይ፣ መንፈሴን አፈሳለሁ፤ እነርሱም ትንቢት ይናገራሉ። 19. በላይ በሰማያት ድንቅ ነገሮችን፣ አሳያለሁ፤ በታች በምድርም ምልክቶችን አሰጣለሁ፤ ደምና እሳት፣ የጢስም ጭጋግ ይሆናል። 20. ታላቅና ክቡር የሆነው የጌታ ቀን ከመምጣቱ በፊት፣ ፀሓይ ወደ ጨለማ፣ ጨረቃም ወደ ደም ይለወጣሉ። 21. የጌታን ስም፣ የሚጠራ ሁሉ ይድናል።'" (ሐሥ. 2)።

[27] አንዳንዶች መጥምቁ ዮሐንስ የብሉይ ኪዳን ነቢይ ነው የሚል አቋም አላቸው።

የነቢያት አገልግሎት በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እጅግ ተስፋፍቶ እንደ ነበረ እንመለከታለን። ከኢየሩሳሌም ወደ አንጾኪያ ከተጓዘው የነቢያት ጉባኤ መካከል፣ "ከእነርሱም እንዱ አጋቦስ የተባለው ተነሥቶ በዓለም ሁሉ ታላቅ ራብ እንደሚሆን መንፈስ ቅዱስ አስመልክቶት ተናገረ፤ ይህም በቀላውዴዎስ ቄሳር ዘመን ተፈጸመ" (ሐሥ. 11÷28)። በእንጾኪያ፣ በቂሳርያ፣ በሮም፣ በቆሮንቶስ፣ በኤፌሶን፣ በተሰሎንቄ ወዘተ የሚያገለግሉ ነቢያት እንደ ነበሩ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል (ሐሥ. 13÷1፤ 21÷8-9፤ 19÷1-7፤ ሮሜ 12÷6፤ 1ቆሮ. 12÷7-11፤ 14÷1-40፤ ኤፌ. 2÷20፤ 2÷11፤ 1ጢሞ 1÷18፤ 1ተሰሎ. 5÷19-22)።

የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት፣ ክርስቲያኖች የትንቢት ስጦታ አጥብቀው መሻት እንዳለባቸው ያሳስባል (1ቆሮ 14÷1)። የስጦታውም ቀዳማይ ዐላማ አማኙን ማነጽ፣ ማበረታታትና ማጽናናት ነው (1ቆሮ 14÷3)። በሌላ አገላለጽ የትንቢት ስጦታ ጉባኤን የሚያንጽ ታላቅ ሰጦታ ነው።

> "1. ፍቅርን ተከታተሉ፤ መንፈሳዊ ስጦታዎችን፣ በተለይም ትንቢት የመናገርን ስጦታ በብርቱ ፈልጉ። 2. በልሳን የሚናገር ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው አይናገርምና፤ ምስጢር የሆነውን በመንፈስ ስለሚናገር የሚረዳው የለም። 3. ትንቢትን የሚናገር ግን ለማነጽ፣ ለማበረታታትና ለማጽናናት ለሰው ይናገራል። 4. በልሳን የሚናገር ራሱን ያንጻል፤ ትንቢትን የሚናገር ግን ቤተ ክርስቲያንን ያንጻል። 5. ሁላችሁም በልሳን ብትናገሩ እወዳለሁ፤ ከዚህ ይልቅ ግን ትንቢትን ብትናገሩ እወዳለሁ። ቤተ ክርስቲያን እንድትታነጽ በልሳን የሚናገር ሰው የተናገረውን ካልተረጐመ፣ በልሳን ከሚናገር ይልቅ ትንቢትን የሚናገር ይበልጣል" (1ቆሮ 14)።

የትንቢት አገልግሎት ለሚያምኑ ሰዎች መታነጽ ብቻ ሳይሆን፣ የማያምኑ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ለመምጣት ምክንያት ሊሆን ይችላል።

"24. ነገር ግን ሁሉም ትንቢት በመናገር ላይ ሳሉ፣ አንዳች ወይም የሚጠይቅ ወይም የማያምን ሰው ቢገባ፣ በሁሉ ይወቀሣል፣ በሁሉ ይመረመራል፣ 25. በልቡም የተሰወረው ነገር ይገለጣል፣ እንዲሁም፣ 'እግዚአብሔር በርግጥ በመካከላችሁ ነው' በማለት በግንባሩ ተደፍቶ ለእግዚአብሔር ይሰግዳል"። (1ቆሮ 14)።

ትንቢት ለማስተማርና ለማበረታታትም እንደሚውል ሐዋርያው ጳውሎስ ገልጾአል (1ቆሮ. 14÷31)። የትንቢት ስጦታ ስዎች ስሙሉ ጊዜ አገልግሎት እንደ ተጠሩ ይፋ አድርጓል (ሐሥ. 13÷13)። በክርስቲያኖች ላይ ሊመጣ ያለውን እደጋ ያጋልጣል (ሐሥ. 21÷4;10-13)፣ ትንቢት በሚነገርበት ጊዜ የጉባኤው ድርሻ ትንቢቱን በአልልታና በሆታ ማዳመቅ ሳይሆን፣ በማስተዋል መመርመር እንደ ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ያስጠነቅቃል (1ቆሮ. 14÷29)። ምንም እንኳ ሴቶች በጉባኤ ማስተማር አለባቸው ወይስ የለባቸውም (1ቆሮ. 14÷33-35)፣ የሚለው ጉዳይ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራንን በእጅጉ የሚያወዛግብ ርእስ ቢሆንም፣ ሴት ነቢያት በጉባኤ ትንቢት ማቅረብ እንደሚችሉ ግን በግልጽ ይናገራል (ሐሥ. 2÷17-18፤ 21÷9፤ 1ቆሮ. 11÷5)[28]። ነቢያት ጠባያቸውንና ንግግራቸውን መግራት የሚችሉ (1ቆሮ. 14÷32) እንዲሁም ስሳምን እጥብቀው የሚከተሉ ስዎች ሊሆኑ ይገባል (1ቆሮ. 14÷33)። ነቢያት ለቀኖናዊ መጻሕፍት አስተምህሮና ሥነ ምግባር ከሙሉ ልብ ሊገዙ ይጠበቃል፣

"36. የእግዚአብሔር ቃል የወጣው ከእናንተ ነውን? ወይስ የደረሰው ወደ እናንተ ብቻ ነውን? 37. ማንም ነቢይ ነኝ የሚል ወይም መንፈሳዊ ስጦታ አሰኘ የሚል ቢኖር፣ ይህ የጻፍሁላችሁ የጌታ ትእዛዝ መሆኑን ይወቅ፤ 38. ይህን የማያውቅ ቢሆን ግን እርሱም አይታወቅ" (1ቆሮ. 14÷36-38)።

[28] ባይሆን የወንድ ነቢያትን ትንቢት በአደባባይ መገምገም ይችላሉ ወይስ አይችሉም የሚለው ጉዳይ ሳያከራክር አይቀርም።

የትንቢት አገልግሎት ቤተ ክርስቲያን የሚያሳድገውን ያህል፣ ክርስቲያኖችንም የሚያንጸውን ያህል፣ ስወንጌል ሥርጭት የሚጠቅመውን ያህል ትልቅ የሆነ ጥፋትም ሊያመጣ ይችላል። ስለዚህ ትንቢቱ ክአምላክ ነው ወይስ እያደለም የሚለው ጉዳይ በእንክሮ ሊመረመር ይገባዋል።

"ወዳጆች ሆይ፣ መንፈስን ሁሉ አትመኑ፣ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር መሆናቸውን መርምሩ፣ ምክንያቱም ብዙ ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም ወጥተዋልና።" (1ዮሐንስ 4÷1)።

ትክክለኛ ትንቢት መሠረታውያኑን ክርስቲያናዊ ትምህርቶች የሚቃረን ሳይሆን እነዚህን መሠረተ እምነቶች የሚያጸና ነው። እንዲያውም የእንድ ትንቢት እውነተኝነት እንዱ ማረጋገጫ፣ ክመሠረታውያን ክርስቲያናዊ አስተምህሮዎች ጋር ምን ያህል ይጣጣማል የሚለው ነጥብ ነው፣

"2. የእግዚአብሔርን መንፈስ በዚህ ታውቃላችሁ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደ መጣ የሚቀበል መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው፤ 3. ኢየሱስን የማይቀበል መንፈስ ግን ከእግዚአብሔር አይደለም፣ እንደሚመጣ የሰማችሁት የክርስቶስ ተቃዋሚ መንፈስ ይህ ነው፣ አሁንም እንኳ በዓለም አለ" (1ዮሐንስ 4)።

"7. ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደ መጣ የማያምኑ ብዙ አሳዮች ወደ ዓለም ወጥተዋል። እንዲህ ያለ ማንኛውም ስው አታላይና የክርስቶስ ተቃዋሚ ነው። 8. እናንተም የደከማችሁበትን ዋጋ እንዳታጡ፣ ነገር ግን ሙሉ ሽልማት እንድትቀበሉ ስራሳችሁ ተጠንቀቁ። 9. በክርስቶስ ትምህርት የማይኖርና ከትምህርቱ የሚወጣ ሁሉ አምላክ የለውም፣ በክርስቶስ ትምህርት የሚኖር ግን አብም ወልድም አለው። 10. ማንም ወደ እናንተ ቢመጣ፣ ይህንንም ትምህርት ባያመጣ በቤታችሁ አትቀበሉት፣ ስላምም አትበሉት፣ 11. የሚቀበለው ሰው፣ የክፉ ሥራው ተባባሪ ይሆናልና" (2 ዮሐንስ)

እውነተኛ ትንቢት ዐይነተኛ መለያው ክርስቶስን ማክበሩ ነው፤

"እኔም ልሰግድለት በእግሩ ሥር ተደፋሁ፤ እርሱ ግን፣ ኑተው! ይህን አታድርግ! እኔም ከአንተና የኢየሱስን ምስክር ከያዙት ወንድሞችህ ጋር አገልጋይ ነኝ፤ ለእግዚአብሔር ስገድ፤ የኢየሱስ ምስክር የትንቢት መንፈስ ነውና" አለኝ" *(ራእ. 19÷10)*።

3. ትንቢትና ዐሥሩ መሠረታውያን

በሐዲስ ኪዳን፣ ስለ ትንቢት ስጦታ ማወቅ የሚኖርብን ዐሥር መሠረታውያን ቁም ነገሮች የሚከተሉት ናቸው[29]፦—

1) የትንቢት ስጦታ ዛሬም በዘመናችን እንዳለ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይናገራል *(1ቆሮ 13÷8-12፤ ሐሥ. 2÷17-18)*።

2) እውነተኛ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር የትንቢት ስጦታ እንዲሰጣቸው መሻት/መፈለግና መጠየቅ አለባቸው *(1ቆሮ 14÷1፡5፡39፤ 14÷13)*።

3) ምንም እንኳ ክርስቲያኖች እምላክ ይህን ስጦታ እንዲሰጣቸው የመጠየቅ መብት ቢኖራቸውም፣ የነቢይነት

[29] እነዚህ ዐሥር መሠረታውያን ነጥቦች፣ ከሚከተሉት አራት መጻሕፍት የተውጣጡ ናቸው፦— *Wayne Grudem, The Gift of Prophecy in the New Testament and Today, (Wheaton, Illinois: Crossway Books, 2000). Jack Deere, The Beginner's Guide to the Gift of Prophecy, (Bloomington, Minnesota: Chosen Books, 2001). D. A. Carson, Showing the Spirit: A Theological Exposition of 1 Corinthians, 12-14, (Grand Rapids, Mi.: Baker, 1987). Jack Deere, Surprised by the Power of the Spirit: Discovering How God Speaks and Heals Today, (Grand Rapids, MI.: Zondervan, 2010).*

ስጦታ ለሕዝበ ክርስቲያን ሁሉ የሚሰጥ ስጦታ አይደለም *(1ቆሮ 12÷29)*[30]። እምላክ ስጦታውን የሚሰጠው፣ እንደ ሉዓላዊ ፈቃዱ ማለትም እርሱ እንዳሻው/እንደ ፈቀደው ብቻ ነው *(1ቆሮ 12÷11፤ ዕብ 2÷4)*።

4) እግዚአብሔር በሉዓላዊ ፈቃዱ በለጠን ስጦታ ደስተኛ መሆን እንጂ፣ በሌላው ስጦታ መቅናት በፍጹም አይገባም *(1ቆሮ. 12÷14-19)*።

5) እምላክ የትንቢት ስጦታን የለጠው ለግለሰብ ጥቅም ሳይሆን፣ ለቤተ ክርስቲያን መታነጽ ነው። ዋነኛ ዐላማውም እማኞችን ማበረታታት፣ ማጽናናት፣ መምራት ነው *(1ቆሮ 14÷3፡24-25፡ 24-25፤ ሐሥ. 21÷4፤ 16÷6-10)*። ስለዚህ ስጦታውን ለግለሰቦች የንዋይ ጥቅም መሰብሰቢያ ማዋል ስሕተት ነው፤ ይህ ዐይነቱን ድርጊት፣ ዐቅም በፈቀደ ሁሉ፣ ከሙሉ ልብ ልናወግዘው ይገባል።

6) የነቢያት መልእክት በቅዱስ ቃሉና በበለሰ መንፈሳዊ ዕውቀት ዘወትር መመርመር አለበት *(1ተሰሎ. 5÷19-21፤ 1ቆሮ. 14÷29፡36-38፤ ቈላ. 1÷9፤ 3÷15፤ 2ተሰሎ. 2÷1-3፤ ኤፌ. 5÷15-17፤ ሮሜ. 12÷1-2፤ ፊልጵ. 1÷9-10፤* እንዲሁም የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል—ሕዝ. 13÷9፤ ኤር. 23÷16፤ ሉቃ. 6÷24፤ ማቴ. 24÷24፤ 16÷11-12፤ 7÷15-202፤ ጢሞ. 4÷3-

[30] አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ መምህራን ስጦታው ስሕዝበ ክርስቲያን ሁሉ የተሰጠ *(potentiality)* ነገር ግን አምላክ በፈለገው ጊዜና ቦታ ክክርስቲያኑ መ'ካል አንዱን ስው ነጥቆ *(actuality)* የሚጠቀምበት ስጦታ ነው ባይ ናቸው።

4፤ ሐሥ. 20÷28-30፤ 2ጴጥ. 3÷14-18፤ 1ዮሐ. 4÷1-6፤ 2ጴጥ. 1÷12-21፤ 2÷1-22፤ ቲቶ 1÷6-16)።

7) ትንቢት በመንፈስ ቅዱስ አነሣሽነት እውን የሚሆን ስጦታ ነው (1ቆሮ. 14÷30። ሉቃ. 7÷39፤ 22÷64፤ ዮሐ. 4÷19)።

8) ትንቢት በመንፈስ ቅዱስ አነሣሽነት እውን የሚሆን ስጦታ ቢሆንም፣ የቅዱሳት መጻሕፍት አስተምህሮና ትንቢት ብቻ በማነኛውም ቦታና ጊዜ ስሚኖሩ ስዎች የተሰጠ የአምላክ አፊዎተ ቃል ነው (1ቆሮ. 2÷13፤ 2ጢሞ. 3÷16፤ 2ጴጥ. 1÷20-21፤ ሐሥ. 3÷18)።

9) በአምላክ አነሣሽነት እውን የማይሆኑ፣ ተፈጻሚነትም የሌላቸው ትንቢቶች ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ የተወገዙ ናቸው (ዘዳ. 18÷20፤ ሕዝ. 13÷9፤ ኤር. 23÷16፤ ሉቃ. 6÷24፤ ማቴ. 24÷24፤ 16÷11-12፤ 7÷15-202፤ ጢሞ. 4÷3-4፤ ሐሥ. 20÷28-30፤ 2ጴጥ. 3÷14-18፤ 1ዮሐ. 4÷1-6፤ 2ጴጥ. 1÷12-21፤ 2÷1-22፤ ቲቶ 1÷6-16)።

10) የሁሉ ነገር ማስሪያ ፍቅር ነውና የጸጋ ስጦታዎችን መጠቀም የሚኖርብን በፍቅር ነው (1ቆሮ. 14÷1:12:26÷37፤ 2÷14)።

4. ዛሬ የተኣምራት ስጦታዎች የሉምን?

እግዚአብሔር አምላካችን፣ የተኣምራት ስጦታዎችን ዛሬም ለቤተ ክርስቲያን እንደሚስጥ የሚናገሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችንና ሙግቶችን በአጭሩ አንዳስስ[31]:—

1) እነዚህ የተኣምራት ስጦታዎች፣ በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በስፋት አገልግሎት ላይ ውስዋል (ስምሳሌ በሮሜ—ሮሜ 12፤ በቆሮንቶስ—1ቆሮ 12-14፤ በስማርያ—ሐሥ. 8፤

---

[31] ካልተሳሳትሁ በቀር የተኣምራት ስጦታዎች ዛሬ የሉም የሚሉ ስዎች (cessationist) ተወዳጅ መግታቸውን የሚቀዱበት አንዲሁም አዘወትረው የሚጠቅሱት የሚከተለውን መጽሐፍ ነው:— Richard B. Gaffin, Jr., *Perspectives on Pentecost*, (Phillipsburg, New Jersey: Presbyterian & Reformed, 1979). ምናልባት የመጽሐፉን ሙግት በዚህ መልክ ማቅረብ የሚቻል ይመስለኛል (እኔ በምወደው የሙግት አወቃቀር a three step syllogism):—

Premise 1: ተኣምራት አንድን ክሥተት ስማጽናት ወይም ትክክለኝነቱን ስማስረገጥ ግልጋሎት ላይ የሚውሉ ናቸው፣

Premise 2: ዛሬ ልዩ መገለጥ አያስፈልግም፣

Conclusion: ተኣምራት ዛሬ እውን አይሆኑም።

በርካታ ጸሓፍያን የዚህን መጽሐፍ መግት ተቃውመው ጽፈዋል። በጉዳዩ ላይ ስፊ ጥናት ማድረግ የሚፈልጉ ስዎች የሚከተሉትን መጻሕፍት ሊመለከቱ ይችላሉ። *Craig S. Keener, Miracles: The Credibility of the New Testament Accounts, (Vol I & II) (Grand Rapids, MI.: Baker, 2011). D. A. Carson, Showing the Spirit: A Theological Exposition of 1 Corinthians, 12-14, (Grand Rapids, MI.: Baker, 1987). Craig S. Keener, Gift and Giver: The Holy Spirit for Today, (Grand Rapids, MI.: Baker 2001). Wayne Grudem, The Gift of Prophecy in the New Testament and Today, (Wheaton, Illinois: Crossway Books, 2000). Jack Deere, The Beginner's Guide to the Gift of Prophecy, (Bloomington, Minnesota: Chosen Books, 2001). Craig S. Keener, Spirit Hermeneutics: Reading Scripture in Light of Pentecost (Grand Rapids, MI.: Eerdmans, 2016). Jack Deere, Surprised by the Power of the Spirit: Discovering How God Speaks and Heals Today, (Grand Rapids, MI.: Zondervan, 2010).*

በቂሳርያ—ሐሥ. 10፤ በአንጾኪያ—ሐሥ 13፤ በኤፌሶን—ሐሥ 19፤ በተሰሎንቄ—1ተሰሎ 5፤ በገላትያ—ገላ 3)።

2) ክሐዋርያ ውጪ በርካታ ስዎች ተአምራት የማድረግ ስጦታ አንደ ነበራቸው መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይናገራል፤ ስምሳሌ:—

- ጌታ የላካቸው ሰባዎቹ ደቀ መዛሙርት (ሉቃ. 10÷9;19-20)። በበዓለ ኀምሳ ቀን መቶ ሃያ ስዎች ክሐዋርያቱ ጋር አንደ ነበሩ ተዘግቧል። የዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያትን ቊጥር ስናቀናንስ 108 ስዎች የበዓለ ኀምሳ ተአምራዊ ክሥተት ተካፋዮች ነበሩ ማለት ነው።
- እስጢፋኖስ (ሐሥ. 6-7)።
- ፊልጶስ (ሐሥ. 8)።
- ሐናንያ (ሐሥ. 9)።
- በአንጾኪያ የነበሩ ክርስቲያኖች (ሐሥ. 13)።
- ስሙ ያልተጠቀስ የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ስው (ሐሥ. 19÷6)።
- በቂሳርያ የነበረች አኅት (ሐሥ. 21÷8-9)።
- በገላትያ የነበረ ወንድም (ገላ. 3÷5)።
- በሮሜ የነበሩ ክርስቲያኖች (ሮሜ. 12÷6-8)።
- በተሰሎንቄ የነበሩ ክርስቲያኖች (1ተሰሎ. 5÷19-20)።

3) ስቤተ ክርስቲያን መታነጽ የሚጠቅሙ/የሚያስፈልጉ ስጦታዎች ሁሉ ቤተ ክርስቲያን ያስፈልጋታል (1ቆሮ.12÷7፤ 14÷3;6)።

4) ታዋቂው የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ሲቅ ዲ.ኤ ካርሰን፤ በዚህ ርእስ ላይ በጻፈው መጽሐፍ ላይ አንዲህ ብሏል፤

"መንፈስ ቅዱስ የሐዲስ ኪዳን ዘመን መጀመሩን ለማብሰር አይደለም በመጀመሪያው ጊዜ የመጣው። ነገር ግን በአዲስ ኪዳን አብሮን ሊኖር አንጂ። በበዓለ ኀምሳ ቀን ብቻ አይደለም የመጣው፤ ነገር ግን ክዘመነ በዓለ ኀምሳ እስከ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት አንጂ"[32]።

5) በአንደኛ ቆሮንቶስ 1÷7 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ፤ "ስለዚህ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን መገለጥ በጕጕት በመጠባበቅ ላይ ሳላችሁ፤ ማንኛውም መንፈሳዊ ስጦታ አይጐድልባችሁም" የሚል ማረጋገጫ ቢሰጥም እንኳ፤ የተአምራት ስጦታዎች ዛሬ የሉም የሚሉ ስዎች፤ አንደኛ ቆሮንቶስ 13÷8-12 ያለውን ምንባብ በመጥቀስ፤ "ፍጹም የሆነው እስኪመጣ" የሚለው ሐረግ፤ የሐዲስ ኪዳን ቀኖና መጠናቀቅ አመላካች ነው። የመጨረሻው የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍ ተጽፎ ሲጠናቀቅ፤ የተአምራት ስጦታዎች ይሻራሉ የሚል ትንታኔ ያቀርባሉ።

"8. ፍቅር ከቶ አይወድቅም፤ ነገር ግን ትንቢት ቢሆን ይሻራል፤ ልሳንም ቢሆን ይቀራል፤ ዕውቀትም ቢሆን ይሻራል። 9. ምክንያቱም የምናውቀው በከፊል ነው፤ ትንቢት የምን ናገረውም በከፊል ነው። 10. ነገር ግን ፍጹም የሆነው ሲመጣ በከፊል የነበረው ይሻራል።" (1ቆሮ. 13)።

ነገር ግን ይህ ትንታኔ የአንደኛ ቆሮንቶስን ዐውድ በጭራሽ የተከተለ አይደለም። (1) የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች፤ "ፍጹም

[32] *D.A. Carson, Showing the Spirit: A Theological Exposition of 1 Corinthians 12-14, (Grand Rapids, MI.: Baker, 1987), 155.*

የሆነው እስኪመጣ" የሚለውን ሐረግ ከቀኖና ማለትም ከሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ጋር አይይዘው መረዳታቸውን የሚገልጽ እንዳችም ማስረጃ የለም። (2) ሐዋርያው ይህ ሐረግ የሐዲስ ኪዳን ቀኖና እመላክች መሆኑን ለመግለጽ ፈልጎ ቢሆን ኖሮ ስለጉዳዩ ከዚህ የተሻለ ማብራሪያ ያቀርብ ነበር። (3) ሐዋርያው እያለ ያለው የጸጋ ስጦታዎች ይሻራሉ፤ ይህ የሚሆነውም ደግሞ፣ እርሱ እኛን እንደሚያውቀን እኛ እርሱን በምናውቅበት ቀን ነው፤ ይኸውም እኛ አርሱን ፊት ለፊት ስናየው ነው፣ "እሁን የምናየው በመስተዋት ውስጥ እንደሚታይ በድንግዝግዝ ነው፤ በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያዋለን። አሁን የማውቀው በከፊል ነው፤ በዚያን ጊዜ እኔ ራሴ ሙሉ በሙሉ የታወቅሁትን ያህል ዐውቃለሁ" (13÷12 እንዲሁም የሚከተለውን ክፍል ይመለከቷል 2ቆሮ. 3÷18)። ይህ ማለት ደግሞ የጸጋ ስጦታዎች እስከ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ድረስ አብረውን እንደሚኖሩ የሚያሳይ ነው። ይህ እውነት ከሆነ ደግሞ የተአምራት ስጦታዎች ዛሬ የሉም ብሎ ማለት ትክክል አይሆንም። (4) እግዚአብሔር የጸጋ ስጦታዎችን ለአማኙ ማኅበረሰብ የሚሰጠው እንዳችን ሌላውን እንድንጠቅምበት እንጂ፣ በጭራሽ እንድንጐዳበት አይደለም። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን አሳብ በእንደኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 12 እስከ 14 ባለው ክፍል እንዴት እንዳሥፈበተው እንመልከት።

የጸጋ ስጦታዎችን በመጠቀም ሌላውን መጉዳት፣ ጌታ ስጦታዎችን ከሰጠበት ዐቢይ ምክንያት ጋር በቀጥታ ይቃረናል። ፍቅርን ማዕከል ያላደረገ ስጦታ ዋጋ ቢስ ነው (13÷1-3)። የፍቅር ቀዳማይ ግቧ ደግሞ ስዎችን ማነጽ ነው (13÷4-7)። ስጦታዎች ለዚህ ምድር ብቻ ስለሆኑ ጊዜያውያን

ናቸው። ፍቅር ግን ዘላለማዊ ነው (13÷8-13)። ከሁሉ የተሻለውንም ስጦታ ማለትም ፍቅርን እጥብቀን ልንሻ ይገባል፤ ምክንያቱም ፍቅር ዘወትር ስዎችን ያንጻልና (12÷31፤ 14÷1)። እንዲያውም ሐዋርያው በአንደኛ ቆሮንቶስ ውስጥ የምንታዘበው የፍቅርን ባሕርይና (13÷4-7) ቆሮንቶሳውያኑ የሚታይባቸውን ጠባይ ነው፤ ይኸውም ስስት፣ ትዕቢት ወዘተ (3÷3፤ 4÷6-7፡18፤ 5÷2)። በሌላ አገላለጽ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የሎዶቅያን ቤተ ክርስቲያን የምትመስል ነበረች ማለት ይቻላል (ራእ. 3÷14-22)።

ከአንደኛ ቆሮንቶስ ኮታ ገጠም ዐውድ እንዲሁም ስፊ ዐውደ ምንባብ በግልጽ የምንማረው ነገር፣ ሐዋርያው ፍጹም የሆነው ሲመጣ የሚለው ሐረግ የክርስቶስን ምጽአት ወይም እኛ ክርስቶስን ፊት ለፊት ስናየው የጸጋ ስጦታዎች አስፈላጊነት ይቋረጣል እያለ እንጂ፣ ስለ ቀኖና ማለትም የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ተጽፈው ስለመጠናቀቃቸው የሚናገር አይደለም። ለዚህም ነው ብዙዎቹ ሊቃውንት፣ "ፍጹም የሆነው አስኪመጣ" የሚለው ሐረግ የክርስቶስን ዳግም ምጽአት ያሳያል በሚለው ሐሳብ የሚስማሙት።

6) የተአምራት ስጦታዎች ዛሬ የሉም የሚሉ እንዳንድ ስዎች፣ ተአምራትና ምልክቶች ያስፈለጉት የወንጌልን አስተምህሮ ለማጽናት ነው፤ ይህ ደግሞ በኢየሱስና በሐዋርያቱ ሕይወት አውን ስለሆነ፣ አሁን እኛ የጸናውን ወንጌል ማመን እንጂ ምልክቱ አያስፈልገንም ይላሉ። መጠየቅ ያለበት ሁነኛ ጥያቄ ግን፣ በዚያ ወቅት ካስፈለገ ዛሬ የማያስፈልግበት ምክንያቱ ምንድን ነው። ለኢየሱስና ለሐዋርያቱ ብቻ ከሆነ፣

ክሐዋርያቱ ውጪ ያሉ ለምች ይህ ተአምራዊ ስጦታ ለምን ታየባቸው ለምሳሌ ፊልጶስና አስጢፋኖስ *(1ቆሮ. 12÷8-20)*።

7) በርካታ ሊቃውንት የተአምራት ስጦታ ዛሬም እየታየ መሆኑን፣ በሕክምና የተረጋገጠ ለነድ እያቀረቡ ነው[33]።

8) በርካታ ሊቃውንት የተአምራት ስጦታ እንዳለ ማመናቸው ብቻ ላይሆን፣ ይህ ስጦታ በሕይወታቸው እየሠራ እንደሚገኝ በይፋ ገልጸዋል[34]።

9) የተአምራት ስጦታዎች ወንጌልን ለማጽናት ብቻ ሳይሆን፣ እግዚአብሔርንም ለማክበር እንደሚያገለግሉ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል (ዮሐ. 2÷11፤ 9÷3፤ 11÷4፤ 11÷40፤ ማቴ. 15÷29-31)።

10) የተአምራት ስጦታዎች የወንጌልን አውነተኛነት ለማጽናት ጥቅም ላይ ውለዋል (ሐሥ. 9÷32-42)።

---

[33] ለምሳሌ የሚከተለውን መጽሐፍ ይመለከቷል:— *Craig Keener, Miracles: The Credibility of the New Testament Accounts Vol 1 and 2. (Grand Rapids, MI.: 2011).* መጽሐፉ ብዙ ሽልማቶችን አግኝቶአል፣ ለምሳሌ:— *Christianity Today 2013 Book Award Winner. 2011 Book of the Year, Christianbook.com's Academic Blog.*

[34] ፕሮፌሰር ክሬክ ኪነር፣ "ሚራክል" በሚል ርእስ በጻፋቸው ሁለት ቅጽ ተከታታይ መጻሕፍት፣ በመቶዎች የሚቈጠሩ ለመ ጥር የነገረ መለኮትና የፍልስፍና ሊቃውንትን ለም ዝርዝር ጠቅሷል። እነዚህ ሊቃውንት ጴንጢቈስጣዊ አቋም ያላቸው ብቻ ሳይሆኑ፣ የተአምራት ስጦታዎች ዛሬ እንዳሉ የሚቀበሉ አንዳንዶቹም እነዚህ ስጦታዎች አሉን የሚሉ ናቸው። የዚህ መጽሐፍ ጸሓፊም፣ እነዚህ የተአምራት ስጦታዎች አሉ ከሚለው ጽኑ አቋሙም ባሻገር፣ የእነዚህ ስጦታዎች ተቋዳሽ ነኝ የሚል እምነት አለው።

11) ምጋቤያዊ/ኖሎታዊ ግብርም አለው፤ ይኸውም ፍቅርንና ክብካቤን ለማሳየት ግልጋሎት ላይ ውሏል (ማቴ. 14÷14፤ ማር. 1÷40-41)።

12) የተአምራት ስጦታዎች ለማነጽ ጥቅም ላይ ውለዋል *(1ቆሮ. 12÷7፤ 1ቆሮ. 14÷3-5÷26)*።

5. የዛሬዎቹ ነቢያት የመሳሳት ፈቃድ ተሰጥቶአቸዋልን?

አንዳንድ ለምች የመጽሐፍ ቅዱስ ነቢያት በሚያስተላልፉት ትንቢት አንዳችም አንከን የለም፤ ዘመነኞቹ ግን ሊሳሳቱ ይችላሉ፤ ባይሆን በፍቅር ማቅናትና ማሳደግ ይጠበቅብናል የሚል አስተያየት አላቸው፤ ይህ አስተሳሰብ ለምን ስሕተት እንደ ሆነ ልምግት:—

1) እውነተኛ ነቢያት መልእክታቸው እውነት እንዲሆን ይጠበቃል (ዘዳ. 18÷15-22)። መጽሐፍ ቅዱስ፣ በየትኛውም የታሪክ ጊዜ የሚኖሩ ነቢያት፤ የመሳሳት ፈቃድ አንዲኖራቸው መጽሐፍ ቅዱስ አንዳችም ፈቃድ አልሰጠም። ዘመነኞቹ ነቢያት ቢሳሳቱ ችግር የለውም ለሚለው ሙግታቸው በመጽሐፍ ቅዱስ የተደገፈ ማስረጃ የማቅረብ ኀላፊነት አለባቸው (አባክዎን እነዚህን ክፍሎች በጥሞና ያንብቧቸው—ሕዝ. 13÷9፤ ኤር. 23÷16፤ ሉቃ. 6÷24፤ ማቴ. 24÷24፤ 16÷11-12፤ 7÷15-202፤ 1ጢሞ. 4÷3-4፤ ሐሥ. 20÷28-30፤ 2ጴጥ. 3÷14-18፤ 1ዮሐ. 4÷1-6፤ 2ጴጥ. 1÷12-21፤ 2÷1-22፤ ቲቶ 1÷6-16)። የመጽሐፍ ቅዱስ ነቢያት ለምች እንጂ መላእክት አልነበሩም። "ክለው ለሕተት ክብረት ዝገት"

የሚባሰው ብሂል ግን ሲፈቀድላቸው አልታየም። ታዲያ ዘመነኞቹ ነቢያት ሰው አስክ ሆንን ድረስ የመሳሳት፣ "ፈቃድ" ይስጠን የሚሰው ሙግታቸው ከየት የመጣ ይሆን?

2) በትንቢቱ ማሰትም በመልእክቱ ላይ አንጂ፣ በነቢያቱ ላይ አንድንፈርድ መጽሐፍ ቅዱስ አያዝም፤ ይህ ደግሞ በሐዲስ ኪዳን ነቢያት እንዲሳሳቱ ፈቃድ መስጠቱን ያሳያል የሚል ሙግት የሚገጥመ ሰዎች አሉ (1ቆሮ 14÷29-32፤ 1ተስሎ 5÷19-20)። ይህ የተሳሳተ የሙግት አካሄድ ነው። በብሉይ ኪዳንም ሆነ በሐዲስ ኪዳን የአንድን ሰው ትንቢት የምንመዝነው መልእክቱን ይዘት በመገምገም አንጂ፣ የግለሰቡን ቅመት ወይም ክብደት በመስፈር አይደለም። ብሉይ ኪዳንም ሐሰተኛ ነቢያትን ገምግሙ የሚል ትአዛዝ የስጠው፣ የሚናገሩትን ነገር ታሳቢ ባደረገ መልክ ብቻ ነው።

3) አንዳንድ ስዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ነቢያት የተሳሳቱበት ሁኔታ ስላለ፣ ለዛሬዎቹም ነባዮች ይህ የመሳሳት ዕድል ሊሰጥ ይገባል ይላሉ። በመሳሳት ረገድ ከሚጠቀሱ ስዎች መኻል ከብሉይ ኪዳን ነቢዩ ናታን በሐዲስ ኪዳን ደግሞ አጋቦስ ናቸው። አንደኛ እነዚህ ስዎች የተሳሳተ ትንቢት ቢያስተላልፉ እንኳ፣ እነርሱ እንደ ተሳሳቱ እኛም የመሳሳት ዕድል ይሰጠን ብሎ መከራከር፣ ከሙግት አካሄድ አንጻር ስሕተት ነው። ከቅዱሳት መጻሕፍት ሌቦችን ጠቅሶ፣ ሌብነት ሊፈቀድ ይገባዋል ማለት ይቻላልን? ወይም ዳዊት አመንዝሯል፣ ገድሏል ዋሽቷል ስለዚህ "ልበ እግዚአብሔር"

የሆነው ዳዊት ይህን እስካደረገ ድረስ፣ እኔም ማድረግ ይኖርብኛል ማለት ትክክል ነውን?

ሁለተኛ እነዚህ ስዎች የተሳሳተ ትንቢት አልተናገሩም። "የይሖዋ ምስክሮች" እውነት ሲሆኑ ያልታዩ በርካታ ትንቢቶችን ተናግረዋል። በተሰይ የአርማጌዶን ጦርነት ይሆናል በሚሰው ያወጧቸው የጊዜ ሰሌዳዎች አንዳቸውም እውን መሆን አልቻሉም። ማስተባበያቸውን ይቀረቡት ግን የዘመኑ ነባዮች በሚሟገቱበት መንገድ ነው። ይኸውም የመጽሐፍ ቅዱስ ነቢያት የተሳሳተ ትንቢት ተንብየዋል፣ አኛስ የተሳሳተ ትንቢት መተንበያችን ለምን እንደ ትልቅ ጥፋት ይታያል የሚል ነው። "ይሖዋ ምስክሮች" እንዲሁም የዘመኑ አባይ ነባዮች በዚህ ረገድ እዘወትረው የሚጠቅሱት የነቢዩ ናታንን ታሪክ ነው።

ንጉሥ ዳዊት ቤተ መቅደስ ማነጽ ፈልጎ ነቢዩ ናታንን ምክር ሲጠይቀው በልብህ፣ "ያሰብኸውን ሁሉ አድርግ" የሚል ቃል ስጠው። ኋላ ግን ቤተ መቅደሱን የሚያንጸው እርሱ ሳይሆን ልጁ እንደ ሆነ ተናገረ። ናታን ለዚህ አድራጎቱ ተግሣጽ አላገኘውም።

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት የተከተለ አስተያየት አይደለም። ናታን መጀመሪያ የተናገረው የግል አስተያየቱን ነበር።

> "ናታንም ለዳዊት፣ "እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ስለ ሆነ፣ ያሰብከውን ሁሉ አድርግ" ሲል መለሰለት" (1ዜና 17÷2)

ጌላ ግን የአምላክ ቃል ሊመጣለት የመጀመሪያው አስተያየቱ ልክ አንዳልሆነ ገልጿል። ከዚህ የነቢዩን የግል አስተያየት እንደ ትንቢት ማቅረብ ስሕተት ነው።

> "3. በዚያም ሌሊት የእግዚአብሔር ቃል ወደ ናታን መጥቶ እንዲህ አለው፤ 4 "ሂድና ለባሪያዬ ለዳዊት እንዲህ ብለህ ንገረው፤ 'እግዚአብሔር የሚለው ይህን ነው፤ እኔ የምኖርበትን ቤት የምትሠራልኝ አንተ አይደለህም...15. ናታንም የዚህን ሁሉ ራእይ ቃል ለዳዊት ነገረው" (1ዜና 17)።

ስዘመነኞቹ አባይ ነባሮች ነገረ መለኮታዊ ሽፋን ለመስጠት የሚውተረተሩ አንዳንድ ስዎች፣ በሐዲስ ኪዳን አጋቦስን ለመጥቀስ ይሞክራሉ። ይህ የሚያስሄዳቸው አይደሰም። ስአጋቦስ፣ ሐዋርያት ጳውሎስ በአይሁድ ተይዞ ስሮማውያን ተላልፎ እንደሚሰጥ መተንበዩ አሙን ነው (ሐሥ 21÷10-11)። ልክ እንደ ተናገረውም ሐዋርያት ጳውሎስ በአይሁድ ተይዞ ስሮማውያን ተላልፎ ተሰጥቷል፣ ሐዋርያውም የትንቢቱን እውነተኝነት መስክሯል (ሐሥ. 28÷17)። አጋቦስ መሳሳቱን የሚያሳይ አንዳችም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንባብ ላስክ ሌሰ ድረስ፣ ግስሰቡ ተሳስቶ ነበር አኛም አንድንሳሳት ይፈቀድልን ማለት ስሕተት ነው (ሐሥ. 11÷28፤ 21÷11)።

4) አንዳንዶች ደግሞ፣ "በሐዲስ ኪዳን አጅግ በርካታ ትንቢቶች ተነግረዋል፣ ነገር ግን ትንቢቶቹ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ አልተካተቱም። ይህ የሆነበት ምክንያት ትንቢቶቹ የተሳሳቱ ስለሆኑ ነው። ክዚህም የተነሣ በዘመነ ሐዲስ ለመሳሳት ፈቃድ ተሰጥቶአል" ባይ ናቸው። ይህ ስሕተት ነው። ልክ ነው በሐዲስ ኪዳን፣ ተተንብየው ነገር ግን

የትንቢቶቹ ይዘት በመጽሐፍ ቅዱስ ያልተካተቱልን በርካታ ትንቢቶች አሉ። ይህ ማስት ግን፣ ትንቢቶቹ የተሳሳቱ ነበር ወደሚለው ድምዳሜ አንድንደርስ የሚያደርጉን አይደሉም። ትንቢቶቹም ስሕተት አንደ ነበሩ የሚገልጽ ወይም ፍንጭ የሚጠቁም አንዳችም ነገር የለም። ያስመካተታቸውን ምክንያት በአርግጠኝነት ማወቅ የሚቻል አይመስለኝም። አምላክ ስምን አንዳይካተቱ አንደ ፈለገ በግልጽ አልነገረንምና። ነገር ግን መገመት ይቻላል፤ ስምሳሌ ትንቢቶቹ ስወቅቱ ለምች ብቻ የሚሆን ወቅታዊ መልአክት ስሳላቸው ሊሆን ይችላል። በብሉይ ኪዳንም በርካታ ነቢያት አንደ ነበሩ ነገር ግን ትንቢታቸው ተመዝግቦ አልተላለፈልንም።

አብድዩ፣ አልዛቤል ነቢያትን ስመጨፍጨፍ በተነሣች ጊዜ አንድ መቶ ነቢያትን በዋሻ ሸሽጎ አንጀራና ውሃ ይመግባቸው አንደ ነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል (1ነገ 18÷4)። ነገር ግን የእነዚህ ነቢያት ትንቢት ተጽፎ አልተቀመጠልንም። ተጽፎ ያስመቀመጡ ስሕተት መሆኑን ያሳያል የሚለው አማራጭ ግን ፍጹም ስሕተት ነው። ምክንያቱም በብሉይ ኪዳን ነቢያት የተሳሳተ ትንቢት ቢናገሩ አንዲገደሉ በግልጽ ያዛልና።

> "19. ማንም ለው ነቢዩ በስሜ የሚናገረውን ቃሌን ባይሰማ፣ እኔ ራሴ በተጠያቂነት እይዘዋለሁ። 20. ነገር ግን እንዲናገር እኔ ያላዘዝሁትን ቃል በድፍረት በስሜ የሚናገርም ሆነ በሌሎች አማልክት ስም የሚናገር ነቢይ ይገደል።' 21. አንተም በልብህ፣ 'እግዚአብሔር (ያህዌ) ያልተናገረውን መልእክት እንዴት ማወቅ እንችላለን?'

ብትል፣ 22. ነቢዩ በእግዚአብሔር (ያህዌ) ስም የተናገረው ካልተፈጸመ ወይም እውነት ሆኖ ካልተገኘ፣ መልእክቱ እግዚአብሔር (ያህዌ) የተናገረው አይደለም። ያ ነቢይ በድፍረት ተናግሮታልና እርሱን አትፍራው" (ዘዳ 18)።

"14. እግዚአብሔርም እንዲህ አለኝ፣ "ነቢያቱ በስሜ የሐሰት ትንቢት ወይም ራእይ፣ (ከንቱ) ሟርት ይናገራሉ፣ እኔ አልላክኋቸውም፣ አላዘዝኋቸውም፣ አልተናገርኋቸውምም። የሐሰት ራእይ፣ ሟርት፣ ከንቱ ነገርንና የልባቸውን ሽንገላ ይተነብዩላችኋል። 15. ስለዚህ በስሜ የሐሰት ትንቢት ስለሚናገሩ ነቢያት እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ እኔ ሳልልካቸው፣ 'ሰይፍና ራብ በዚች ምድር ላይ አይመጣም' የሚሉ እነዚህ ነቢያት በሰይፍና በራብ ይጠፋሉ፣ 16. ትንቢቱ የተነገረለትም ሕዝብ ከሰይፍና ከራብ የተነሣ በኢየሩሳሌም አደባባዮች ይወድቃል፣ እነርሱንም ሆነ ሚስቶቻቸውን ወይም ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸውን የሚቀብራቸው አይገኝም። ሰበደላቸው የሚገባውንም ቅጣት በላያቸው አወርዳለሁ" (ኤር. 14)።

ስለዚህ ነቢያት የመሳሳት ፈቃድ ሊለጣቸው ይገባል የሚሉ አንዳንድ ተከራካሪዎች፣ በዚህ አግባብ ሙግታቸው ፍጹም ስሕተት ነው። ከአምላክ የተገኘ ነው በሚል በአምላክ ስም ለሚነገር፣ ነገር ግን ከአምላክ ላልሆነ ትንቢት ድጋፍ ለጥተዋልና አካሄዳቸው ውጉዝ ነው። ትንቢቱም ለሚያመጣው (ለሚያስከትለው) አሉታዊ ውጤት ተጠያቂዎች ናቸው።

ክፍል ሰባት

መርገም ከምዝላት፣ ከእንጅላት[1]...ይተላለፋልን?



ከየት መጣሁ?
ዴሬክ ፕሪንስ፣ ማርኪን ሄኪ፣ ጀን ኤክሃርት

"መርገም ከዘር ማንዘር ይተላለፋል፣ ይህም መርገም

[1] የአማርኛ ቋንቋ ዐዋቂዎች የዘር ሐረግ ቁጠራ፣ በዚህ መልክ እንደሚዔድ ያስረዳሉ፦— አባት/እናት፣ አያት፣ ቅድመ አያት፣ ቅም አያት፣ ቅማንት፣ ሽማት፣ ምዝላት (መንዥላት)፣ እንጅላት (እንዥላት)፣ ፍናጅ፣ ቅናጅ፣ አስልጥ፣ አመለጥ፣ ማንትቤ፣ ደረባቴ። መርገም ይተላለፋል የሚሉ ሰዎች፣ ይተላለፋል የሚሉት እስከ ሦስተኛና አራተኛ ትውልድ ነው፣ ማለትም እስከ ቅድመ አያትና ቅም አያት ድረስ ነው። ምዝላትና እንጅላት ግን በትውልድ ሐረጉ ውስጥ ሰባተኛና ስምንተኛ አጽቅ ናቸው። እኔ "ምዝላት፣ እንጅላት" የሚለውን በርእስ የመረጥሁት፣ በዘር ሐረግ ቁጠራ ብዙ የተለመደ አነጋገር ስለመሰለኝ ነው። ስለዚህ በዚህ ጽሑፍ "ምዝላት እንጅላት" ማለት፣ "ዘርዐ ሐረግ" የሚለውን ትርጉም የሚወክል ብቻ እንደ ሆነ ልብ ይሏል።

ብትል፣ 22. ነቢዩ በእግዚአብሔር (ያህዌ) ስም የተናገረው ካልተፈጸመ ወይም እውነት ሆኖ ካልተገኘ፣ መልእክቱ እግዚአብሔር (ያህዌ) የተናገረው አይደለም። ያ ነቢይ በድፍረት ተናግሮታልና እርሱን አትፍራው" (ዘዳ 18)።

"14. እግዚአብሔርም እንዲህ አለኝ፣ "ነቢያቱ በስሜ የሐሰት ትንቢት ወይም ራእይ፣ (ከንቱ) ሟርት ይናገራሉ፣ እኔ አልላክኋቸውም፣ አላዘዝኋቸውም፣ አልተናገርኋቸውምም። የሐሰት ራእይ፣ ሟርት፣ ከንቱ ነገርንና የልባቸውን ሽንገላ ይተነብዩላችኋል። 15. ስለዚህ በስሜ የሐሰት ትንቢት ስለሚናገሩ ነቢያት እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ እኔ ሳልልካቸው፣ 'ሰይፍና ራብ በዚች ምድር ላይ አይመጣም' የሚሉ እነዚህ ነቢያት በሰይፍና በራብ ይጠፋሉ፣ 16. ትንቢቱ የተነገረለትም ሕዝብ ከሰይፍና ከራብ የተነሣ በኢየሩሳሌም አደባባዮች ይወድቃል፣ እነርሱንም ሆነ ሚስቶቻቸውን ወይም ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸውን የሚቀብራቸው አይገኝም። ሰበደላቸው የሚገባውንም ቅጣት በላያቸው አመርዳለሁ" (ኤር. 14)።

ስለዚህ ነቢያት የመሳሳት ፈቃድ ሊሰጣቸው ይገባል የሚሉ አንዳንድ ተከራካሪዎች፣ በዚህ አግባብ መግታቸው ፍጹም ስሕተት ነው። ከአምላክ የተገኘ ነው በሚል በአምላክ ስም ሰሚነገር፣ ነገር ግን ከአምላክ ላልሆነ ትንቢት ድጋፍ ስጥተዋልና አካሄዳቸው ውጉዝ ነው። ትንቢቱም ስሚያመጣው (ሰሚያስከትለው) አሉታዊ ውጤት ተጠያቂዎች ናቸው።

ክፍል ሰባት

መርገም ከምዝካት፣ ከአንጅካት[1]...ይተላለፋልን?



ከየት መጣሁ?
ዴሬክ ፕሪንስ፣ ማርኪን ሄኪ፣ ጀን ኤክሳርት

"መርገም ከዘር ማንዘር ይተላለፋል፣ ይህም መርገም

[1] የአማርኛ ቋንቋ ዐዋቂዎች የዘር ሐረግ ቁጠራ፣ በዚህ መልክ እንደሚሄድ ያስረዳሉ፦— አባት/እናት፣ አያት፣ ቅድመ አያት፣ ቅም አያት፣ ቅማንት፣ ሽማት፣ ምዝላት (መንዥላት)፣ እንጅላት (እንዥላት)፣ ፍናጅ፣ ቅናጅ፣ አስልጥ፣ አመለጥ፣ ማንትቤ፣ ደረባቴ። መርገም ይተላለፋል የሚሉ ስዎች፣ ይተላለፋል የሚሉት እስከ ሦስተኛና አራተኛ ትውልድ ነው፣ ማለትም እስከ ቅድመ አያትና ቅም አያት ድረስ ነው። ምዝላትና እንጅላት ግን በትውልድ ሐረጉ ውስጥ ሰባተኛና ስምንተኛ አጽቅ ናቸው። እኔ "ምዝላት፣ እንጅላት" የሚለውን በርእስ የመረጥሁት፣ በዘር ሐረግ ቁጠራ ብዙ የተለመደ አነጋገር ስለመሰለኝ ነው። ስለዚህ በዚህ ጽሑፍ "ምዝላት እንጅላት" ማለት፣ "ዝርዐ ሐረግ" የሚለውን ትርጉም የሚወክል ብቻ እንደ ሆነ ልብ ይሳ.ል።

በክርስቲያኖች ላይ እውናዊ ተጽእኖ አሰው" የሚለውን ትምህርት የቀመሩት፣ ደርዝ ባሰው መንገድ ያደራጁት እንዲሁም በጊዜ ሂደት እጦልብተው ሰዓለም ያስተዋወቁት፣ እንግሊዛዊው ስባኪ ዴሬክ ፕሪንስ እንደ ሆኑ ይነገርላቸዋል[2]። እስተምህሮው በኢትዮጵያ ውስጥ ሰመግነኑ ግን፣ እርሳቸውን ጨምሮ በርካታ ሰዎች የመሪውን ድርሻ ሲወስዱ የሚችሉ ይመስለኛል—ማርሲን ሄኪና ጆን ኤክሃርት፣ ከፕሪንስ ባልተናነስ መልኩ በዚህ ረገድ እሻራቸውን፣ በኢትዮጵያ ወንጌላውያን እብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የጣሱ ሰዎች ናቸው[3]።

[2] አንዳንድ ጸሐፍያን የአስተምህሮው ጠንሳሽ ዴሬክ ፕሪንስ *(Derek Prince)* ናቸው ሰሉ ጽፈዋል። በተለይ ወደ አሜሪካን መጥተው፣ ከአሜሪካውያኑ *Don Basham, Bob Mumford, Charles Simpson* እንዲሁም *Ern Baxter* ጋር በነበራቸው ግንኙነት፣ አስተምህሮው ዳብሮ የአሁኑን መልክ እንዲይዝ ተደርጓል የሚሉ ጸሐፍያን አሉ። እንደ ጉርጉሮሳውያኑ የዘመን ቀመር በ1970ዎቹ ላይ፣ እነዚህ ሰዎች *"covenant relationship"* የሚል "የኪዳን ጥምረት" መሥርተው፣ *"New Wine"* የሚል መጽሔት ማሳተም በጀመሩበት ጊዜ፣ አስተምህሮው በዓሰም ዙሪያ የመስፋፋት ዕድል አግኝ። *"Derek Prince Legacy Radio"* የሚባለውም የራዲዮ ፕሮግራም፣ ሰአስተምህሮው ሥርጭት ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ነው። ዴሬክ ፕሪንስ *(Derek Prince 1915-2003)* ከእንግሲዛውያን ቤተ ሰቦች በሕንድ አገር የተወሰዱ ሲሆን፣ በእንግሲዝ የጦር ሰራዊት ውስጥ አገልግለዋል። የዕብራይስጥ፣ የግሪክ፣ የአረማይስጥና የላቲን ቋንቋዎችን እንደሚያውቁ ይነገርላቸዋል። ይህ ምን ያህል እውነት ነው እንዲሁም ዕውቀታቸው እስከ ምን ድረስ ይዘልቃል የሚሰውን ጉዳይ፣ በነጻ ምንጭ አረጋግጦ ሰዚህ ጽሑፍ ማድረስ አልተቻሰም። ስሰዚህ *"Everybody presumed innocent until proven guilty beyond the reasonable doubt"* በሚሰው አካሄድ፣ ሰጊዜውም ቢሆን ይህንኑ መረጃ ይዘን እንቀያስን።

[3] በኢትዮጵያ ውስጥ ይህን አስተምህሮ በማስተማር ዘስፋት የሚታወቁት፣ ከሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ወጥተው፣ "ዐርነት ቤተ ክርስቲያንን" የተከሰቱት፣ እነመጋቢ የማነብርሃን እንዳሰ ናቸው። የእንቅስቃሴው ዕውቅ መምህር ግን፣ አቶ ጌታቸው መኩሪያ እንደ ነገሩ ብዙዎች ይስማማሉ። ከአቶ ጌታቸው መኩሪያ ጋር በነገረ መሰኮት ዙሪያ የመወያያት ዕድል ባላገኝም፣ ግሰሰቡን በቅርበት የሚያውቋቸው ወዳጅቼ ግን፣ አቶ ጌታቸው እጅግ ትልቅ ዕውቀት እንዲሁም የማስተማር ክሂሎት ያላቸው ኢትዮጵያዊ ምሁር እንደ ሆኑ ይገልጻሉ። እንዲያውም ሁለት ወዳጅቼ፣

እነዚህ ሦስት ሰዎች፣ በርእስ ጉዳዩ ላይ የጻፏቸው መጻሕፍት፣ በአማርኛ ቋንቋ ተተርጕመውና በብዙ ሺህ ቅጅ ተባዝተው፣ በአገሪቱ ውስጥ ተሠራጭተዋል። የዴሬክ ፕሪንስን መጻሕፍት በመተርጕምና አስተምህሮአቸውን በኢትዮጵያ ውስጥ በማስፋፋት የሚታወቁት የቀድሞው፣ "የዐርነት ቤተ ክርስቲያን" መጋቢ፣ መጋቢ የማነብርሃን እንዳለ ናቸው[4]።

"በሳቸው መጠን ያለ ዐዋቂና አስተማሪ አይቼ ሰምቼ አላውቅም" ብሰውኛል—የሚገርም ምስክርነት ነው። ይህ እንዳለ ሆኖ፣ ዛሬ ያሰችው የዐርነት ቤተ ክርስቲያን ይህ ዐይነት አቋም ይኑራት አይኑራት፣ እቅጩን ማወቅ አልተቻሰም። ነገር ግን ከመጋቢ የማነብርሃን ቡኋላ፣ ቤተ ክርስቲያኒቱን በመጋቢነት የሚመሩት፣ መጋቢ ዳርሰማ አስፋ፣ ነገረ መሰኮትን በወጉ የተማሩ ሰው መሆናቸውን እንዲሁም ቤተ ክርስቲያኒቱ ይህን መሰል አስተምህሮ እንደማታምን አስታውቃ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናትን ጎብረት መቀላቀሏን በመጥቀስ፣ ቢያንስ በቤተ ክርስቲያን ደረጃ ነባሩ አቋም እንደ ሌሰ አንዳንዶች ይገልጻሉ። እንቅስቃሴው አብዮ በነበረበት በ1970ዎቹ መጨረሻ አካባቢ፣ እኔን መሠረታዊ የክርስትና ትምህርት ያስተምረኝ የነበረን ወንድም ጨምሮ፣ አንጋፋ የአጥቢያችን (ኮልፌ ቃሰ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን) የሙሉ ጊዜ አገልጋይ፣ ወደ እንቅስቃሴው በይፋ ገብተዋል፣ ቤተ ክርስቲያኒቱንም ትተው ሂደዋል። የሚገርመው ግን በዚያን ወቅት በእንቅስቃሴው ውስጥ የነበሩ በርካታ ሰዎች፣ ዛሬ የእንቅስቃሴውን መሠረታውያን ትምህርቶች እንደማያቀበሱ በይፋ እየገለጹ ነው። አስተምህሮውን በንባብ የተቀበሱ ሰዎች በንባብ ተመልሰዋል። ነገር ግን በሰብአውያን የማስተማር ክሂሎት ተደንቀው፣ በዕውቀታቸው ጥልቀት ተደመው ወደ እንቅስቃሴው የገቡ ሰዎች፣ ተጽእኖ ያስከተሱባቸው ሰዎች ስብእና በልባቸው እስኪደበዝዝ ድረስ፣ አስተምህሮውን መተው ሲከብዳቸው ይችላል።

[4] በእንግሊዝኛ፣ *"Blessing or Curse You can Choose"* በሚል ርእስ ዴሬክ ፕሪንስ የጻፉትን መጽሐፍ፣ በኢትዮጵያውያን የዘመን አቈጣጠር 1989 ዓ.ም ላይ፣ "በረከት ወይስ መርገም አንዱን ምረጥ" በሚል ወደ አማርኛ የመሰሱት፣ ያሳተሙት እንዲሁም ያሠራጩት፣ መጋቢ የማነብርሃን እንዳለ ናቸው። በመጀመሪያው ዕትም፣ ዐሥር ሺህ ቅጅ ተባዝቶ እንደ ተሠራጨ በመጽሐፉ መግቢያ ላይ ተገልጾአል። የትርጉምና የኅትመት ወጪውን የሸፈነው፣ *"Derek Prince Ministries International"* የሚባለው የዴሬክ ፕሪንስ ድርጅት እንደ ሆነ፣ ውስጥ ዐዋቂ ምንጮች ያስረዳሉ።

በርካታ የጆን ኤክሃርትን መጻሕፍት እየተረጐሙና አያተሙ የሚያሠራጩት ደግሞ ቀድሞ፣ "ክሩሴደር ቤተ ክርስቲያን" አሁን "የክርስቲያኖች መቅደስ ቤተ ክርስቲያን" የሚባለውን ቤተ እምነት በኢትዮጵያ ያቋቋሙት፣ መጋቢ ኢዮብ ማሞ ናቸው[5]።

መጋቢ የማነብርሃን እንዳለ፣ የፐሪንስን በርካታ መጻሕፍት ተርጕመው በማሠራጨት በስፋት ይታወቃሉ። እነዚህንም መጻሕፍት በማሰተምና የትርጕም ወጪያቸውን በመሸፈን፣ የተባበረው የፐሪንስ ድርጅት እንደ ሆነ ይነገራል። ግለሰቡም ሆነ አርሳቸው በመጋቢነት ያገለግሉባት የነበረችው ቤተ ክርስቲያን፣ ከወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ጎብረት የለያትን ይህንና ይህን መስል ትምህርት ትቻለሁ፣ ተሰስቼ ነበር በማለት የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ጎብረትን እንደ ተቀሳቀሰች ይታወቃል። ነገር ግን ጎብረቱን ከተቀሳቀሰችም በኋላ (ቢያንስ የቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢ የማነብርሃን እንዳለ) የፐሪንስን ትምህርት በማስተማርም ሆነ በማስፋፋት ቀዳሚውን ቦታ እንዳላቸው ይታወቃል። በእንጻሩ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በጎብረቱ አመራር ውስጥ ያገለግሉ እንደ ነበር ይታወቃል። እንግዲህ የአስተምህሮን በተመለከተ የጎብረቱ አንዱ ምፀት ይህ ነው። ጎብረቱ አባይ ነባሮችን አሰመልክቶ በቅርቡ የጀመረው የአስተምህሮ ተቋርቋሪነት ብዙዎችን አስገርሟል፣ ተስፋም ሰጥቶአል። ይህ ጉዳይ ወደ ፊት ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም እናምናለን፣ እንጸልይማለን። ጎብረቱ በውስጡ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት መሠረተ እምነታቸው ሳይዛነፍ፣ ይዘው መቀጠላቸውን፣ ዕለት ዕለት የመመርመር ኀላፊነት ያለበት ይመስለናል።

[5] "መርገምን መሻር" የሚለውን መጽሐፍ ጨምሮ፣ "ሐዋርያ ነኝ" የሚሉትን የአሜሪካዊውን የጆን ኤክሃርትን *(John Eckhardt)* መጻሕፍት ወደ አማርኛ ቋንቋ ተርጕመው፣ በአገሪቱ ውስጥ ያሠራጩት መጋቢ ኢዮብ ማሞ ናቸው። ምናልባትም በኢትዮጵያ የሚገኘውን ቀድሞ፣ "ክሩሴደር" አሁን "የክርስቲያኖች መቅደስ ቤተ ክርስቲያን"፣ የሚባለውን ቤተ እምነት በኢትዮጵያ እንዲቋረቁር የገንዘብ ድጋፍ ያደረጉት፣ ጆን ኤክሃርት ሳይሆኑ አይቀርም። እስከ ቅርብ ጊዜም ድረስ የመጋቢ ኢዮብን ደመወዝ ይከፍሉ የነበሩት፣ እኚሁ አስተማሪ እንደ ነበሩ አንዳንድ ምንጮች ያስረዳሉ። ምናልባት የቤተ ክርስቲያኒቱ የሰም ሰውጥ፣ መጋቢ ኢዮብ ከግስቡ ጋር ከተጋጨ በኋላ፣ እውን የሆነ ነው የሚል አስተያየትም አለ። በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ላይ ጥናት የሚያካሂዱ ወገኖች እንዲሁም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን ሰውጥ በንቃት የሚከታተሉ ሰዎች፣ ወደ ፊት በዚህ እንዲሁም በዚህ

ትልቁ ምፀት ግን አሜሪካዊቷ ሰባኪ፣ ማርሲን ሄኪ *(Marilyn Hickey)*፣ "የትውልድን መርገም መስበር" *"Breaking Generational Curses"* በሚል ርእስ የጻፉትን መጽሐፍ፣ ተርጕሞና ዐሳትሞ ያሠራጨው የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ጎብረት የመሆኑ ሐቅ ነው[6]። የመጽሐፉን የትርጕም ሥራ አንዲሁም የኅትመት ወጪ ሙሉ በሙሉ የሸፈነው፣ መቀመጫውን አሜሪካን አገር ያደረገው የማርሲን ሄኪ ድርጅት ነው[7]። በወቅቱ ማርሲን ሄኪን ወደ ኢትዮጵያ በመጋበዝ አንዲሁም መጽሐፋቸውን በመተርጐም፣ በማሳተምና በማሠራጨት የጎብረቱ ጽሕፈት ቤት ያደረገውን እድራጎት ብዙዎች ነቅፈዋል[8]።

ነገር ግን የቱንም ያህል ጥረት ቢደረግ፣ መጽሐፉ እንዳይሠራጭ ግስስቢም ወደ ኢትዮጵያ መጥተው የጀማ ስብከት እንዳያካሂዱ ማስቆም አልተቻስም። ምናልባት በወቅቱ የነበረው ውትወታ የፈየደው ነገር ቢኖር፣ ግለስቢ በአዲስ አበባ ከተማ የጀማ ስብከት እንዳያካሂዱ መደረግ ብቻ ነው። በናዝሬት የነበራቸው የጀማ ስብከት ግን፣ በተያዘለት መርሐ ግብር አንዲካሄድ ተደርጓል። መጽሐፉ በብዛት የተሠራጨው እንዲሁም ግስስቢ በስፋት እንዲያስተምሩ የተፈቀደላቸው በናዝሬት ነበር።

የዚህ መጽሐፍ ጸሓፊ በወቅቱ የነበሩትን የጎብረቱን ዋና ጸሓፊ፣ ግስስቢ የእምነት እንቅስቃሴ አስተምህሮ *("Word of Faith*

መስል ጉዳይ ላይ ሚዛናዊነትን የተላበስ፣ ጥም ቁራጭ ጽሑፍ እንደሚያስነብቡን ተስፋ እናደርጋስን።

[6] በኢትዮጵያውያን የዘመን አቈጣጠር በ1994 ዓ.ም።

[7] *Marilyn Hickey Ministries*

[8] ግለስቢ ወደ በጕርጕሮሳውያኑ አቈጣጠር ሚያዝያ 2014 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ በመሄድ፣ በተሰያዩ አካባቢዎች ስብከት እንዳካሄዱ ይታወቃል። ይህ መጽሐፍ የሚያወራው ግን በኢትዮጵያውያን ዘመን አቈጣጠር በ1994 ዓ.ም የተካሄደውን ታሪክ ነው።

Movement") ሰባኪ መሆናቸውን እንዲሁም ተተርጕሞ ለንባብ የቀረበው መጽሐፍ፣ ከወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት መሠረተ እምነት ጋር ከፉኛ የሚጋጭ መሆኑ ግለሰቧን ወደ ኢትዮጵያ የማስመጣቱን ግብዣ ስሕተት እንደሚያደርገው በቃልም ሆነ በጽሑፍ ለማስረዳት ሙከራ እድርጓል። ነገር ግን ጽሕፈት ቤቱ፣ ድርጊቱን ማስቆም አልችልም ያለው፣ የሚከተሉትን ምክንያቶች በመዘርዘር ነው፦— *(1)* ግለሰቧ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ ግብዣ የቀረበው፣ ትምህርታቸው በውል በማይታወቅበት ጊዜ ነው፤ *(2)* ግለሰቧ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው እንዲስብኩና ጽሑፋቸውን እንዲያሠራጩ ሙሉውን ወጪ የሸፈነው ድርጅታቸው ነው፤ *(3)* ግለሰቧ የጀማ ስብከት የሚያካሂዱበት ስፍራ ተወስኗል፤ የማስታወቂያና የቦታ ክፍያ ተካሂዷል፣ *(4)* የግለሰቧ ድርጅት መጽሐፉን በማስተርጐምና በማሳተም ከፍተኛ ወጪ እድርጓል። ይህ ሁሉ እውን ባሆነበት በመጨረሻው ሰዓት ላይ፣ "እታገለግሉም" እንዲሁም "መጽሐፉ እይሠራጭም" ማለት አግባብነት ይጐድለዋል። ከዚህ የተነሣም፣ ስሕተት ነው የተባለው መጽሐፍ እንዳይሠራጭ እንዲሁም ለግለሰቧ የተዘጋጀው የጀማ ስብከት እንዲቋረጥ ማድረግ አልተቻለም[9]። የግለሰቧ አስተምህሮ ስሕተት መሆኑ በውል ከታወቀ

[9] እዚህ ጋ ሁለት ሁነኛ ጥያቄ ማንሣት አግባብ ይሆናል፣ ይኸውም፦— *(1)* ቀድሞውንስ ቢሆን፣ የግለሰቧ ትምህርት በውል ላይታወቅ ግብዣው እንዴት ሊካሄድ ቻለ? *(2)* የመጽሐፉ አስፈላጊነትና ጤናማነት በውል ላይመረመር የትርጕም ሥራው እንዲሠራ እንዴት ተወሰነ? ምናልባት ይህ ጉዳይ የነብረቱን ጽሕፈት ቤተ የሚመራው፣ "የአስተምህሮ አቋም ወይስ የነዋይ ልንም?" የሚል ጥያቄ ይጭራል። ተሰፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር፣ እያንዳንዱ ቤተ እምነት እንዲሁም አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን፣ ነገረ መለኮት መርማሪ ማዕከል ወይም የዐቅብተ እምነት አገልግሎት በርፍ ሊኖረው ይገባል የሚለው በዚህ መሰለ ዐቢይ ምክንያት ነው። የቤተ ክርስቲያንን የአስተምህሮ ንጽሕና መጠበቅና ማሰጠበቅ ከሚቻልባቸው ሁነኛ መንገዶች ወስጥ ይህ አንዱ ነውና።

በኋላ እንኳ፣ እንዳችም ዕርምት ወይም ማስተካከያ ያለመደረጉ፣ ክሥተቱ በብዙ ጐኑ እንዲተረጐም በር ይከፍታል[10]።

"ክርስቲያን ከመርገም መጠበቅ አለበት!"

ክርስቲያን በትውልድ መርገም ውስጥ ሊወድቅ ይችላል የሚለው ትምህርት አስተምህሮውን የሚያስተዋውቀው በሚከተለው መንገድ ነው፦—

> "ከንቱነትና የተስፋቢስነት ስሜት፣ ሕይወትህን ተጫጭኖት ይሆን? ሕይወትህ በእንቅፋትና በመጥፎ አጋጣሚስ የተሞላ ይሆን? በብዙ ዘመን የደከምህበት ልፋትህ ከንቱ ሆኖ ዐመድ አፋሽ ስትሆን፣ የእግዚአብሔር በረከት እንዳልጐበኘህ ይሰማህ ይሆን? እነዚህን እንቅፋቶች የበሰጠ ከባድና አስጨናቂ የሚያደርጋቸው፣ ***አንተ ክርስቲያንና ጌታን የምትወድ ሆነህ ሳለ ስለደረሰብህ ነው።*** ስመሆኑ ዳግም የተወለደ እና መንፈስ ቅዱስን የተሞላ ክርስቲያን፣ ከእርግማን በታች ይኖር ዘንድ ይገባዋልን? እንዲህ ከሆነ ***አንድ ክርስቲያን ከመርገም እንዴት ሊገላገል ይችላል? እንዴትስ ነጻ ወጥቶ በእግዚአብሔር ሙሉ በረከት ሊራመድና ሊኖር ይችላል?***[11]

[10] "አለባበስው ቢያርሱ በአረም ይመስሉ" ይላል የአገራችን ስው። ይኸው፣ "ምንም አይደል"፣ "ለክፉ አይስጥም"፣ "እኔ ምንተዳዩ"...የተባሉ ጉዳዮች፣ እነሆ ዛሬ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናትን ህልውና በጥያቄ ላይ ከተዋል። ይህ በምንም መልኩ ለወቀሳ ወይም በዚያን ወቅት የነበሩ መሪዎችን ለማሳጣት የተደረገ ጥረት አይደለም። ነገር ግን ከዚህ ዐይነቱ ተሞክሮ፣ ብዙ የምንማረው ነገር እንዳለ ለማስታወስ እንጂ። "ከታሪክ የምንማረው ከታሪክ ያለመማራችንን" ቢሆንም።

[11] ይህ የማንንም ልብ የሚሰብ ትልቅ ጥሪ ነው። ምክንያቱም ስኬትን የማይፈልገው የሰው ልጅ የቱ ነው? በተለያዩ የሕይወት ፈርጆች፣ በሕይወቱ ተደጋጋሚ ኪሳራ ያላጋጠመው ፍጡር የቱ ነው (ቢያንስ አፍሪካ በምትባለው ምድር ተወልዶ ያደገ)? ቢያንስ፣ "ለክፉ ለደጉ ፈጦ መድነት ነው" በሚለው አካሄድ፣ ማንኛውም ስው ለመከራ ሊጋለጥ ይችላል፣ ከዚህም የተነሣ፣ አስተምህሮውን ሊቀበል ተግባራዊነቱን ሊከተል እንደሚችል አያጠራጥርም። በተሞክሮም ሆነ በዕንስ ሐሳብ ደረጃ፣ አስተምህሮው ስሑት እንደ ሆነ ግን እንመሰክራለን።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እነኝህን ጥያቄዎች በተመለከተ...ማብራሪያ ሰጥተዋል"[12]::

"ቅዱሳን ድነታቸውን ክተቀበሉም በኋላ በእርግማን ሊጠቁ ይችላሉ:: በቅዱሳን ሕይወት ውስጥ እርግማኖች ተነጥሰው ታውቀው መሰበር አሰባቸው:: የእርግማን መሰበር አጋንንት የሚገለገሉበትን መብትና ሥልጣን ይነጥቃል:: የተደላደሉበትን መብት ከመንጠቅ በኋላ፣ አጋንንትን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም መግሰጥ፣ ማሰወጣትም ቀላል ነው"[13]::

የአስተምህሮው ቀዳማይ አመንጪ እንደ ሆኑ የሚነገርላቸው ዴሬክ ፕሪንስ፣ እርግማን እንድም ከእግዚአብሔር፣ በሌላ መልኩ ከሰይጣን ሊመጣ እንደሚችል ይገልጻሉ፣ "ከእግዚአብሔር የሆነው ሁሉ ሕጋዊ ሲሆን፣ ከሰይጣን የሆነው ሁሉ ግን ሕገ ወጥ ነው"[14] የሚል አስተያየት አላቸው:: ክርስቲያን "ሕጋዊ" የሆነውም ሆነ "ሕገ ወጥ" የሆነው መርገም አንዳይመጣበት፣ መጠንቀቅና አስፈላጊውን ቅድመ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚያስፈልገው ያስጠነቅቃሉ[15]:: አንቅሰቃሴው "ክርስቲያን ማነው?" የሚለውን ጉዳይ የሚያብራራው "ጌታን የሚወድ"፣ "ዳግም የተወለደ"፣ "መንፈስ ቅዱስ የተሞላን" ሰው በማለት ነው[16]::

የዴሬክ ፕሪንስም ሆኑ ባልደረቦቻቸው፣ ትምህርታቸውን በሦስት መልክ ቢያዋቅሩትም፣ ትምህርቱ ግን በሁለት

[12] ጆን ኤክሃርት፣ *መርገምን መሻር!* (የክርስቲያኖች መቅደስ ቤተ ክርስቲያን፣ 2001 ዓ.ም)፣ ገጽ 1፣ አትኮሮት የእኔ:: ይህን መጽሐፍ በቀጥታ የጠቀስነው፣ በመጽሐፉ ላይ በጉልን ሚታዩትን የሆህያት፣ የሥርዐተ ነጥቦችና የስዋስው ስሕተቶች አርመን ነው::

[13] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 33::

[14] ዴሬክ ፕሪንስ፣ *በረከት ወይስ መርገም አንዱን ምረጥ—የሞንቱት ሕይወት ከመመራት የመላቀያው ዘይ*፣ (የማነብርሃን እንዳለ፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ፣ 1989 ዓ.ም)፣ ገጽ 50::

[15] ዝኒ ከማሁ::

[16] ጆን ኤክሃርት፣ *መርገምን መሻር!* ገጽ 1::

መሠረታውያን ነጥቦች መጠቃለል የሚችል ይመስለኛል:: ይኸውም:—

ሀ. ክርስቲያን በመርገም ውስጥ እንዳለ እንዴት ማወቅ እንደሚችል ገለጻ ያቀርባል፣
ለ. ክርስቲያን ከመርገም ለመላቀቅ ምን ማድረግ እንደሚጠበቅበት ያስረዳል[17]፣

በዚሁ ቅደም ተከተል የእንቅስቃሴውን ጽሑፍ በቀጥታ በመጥቀስ የአስተምህሮውን ከንቱነት አንመረምራለን:: ኋላም አስተምህሮው ለንድፈ አሳቡ ማዕከል ያደረጋቸውን ዋነኛ ምንባባት በለፋት እንተነትናለን::

ሀ. ክርስቲያን በመርገም ውስጥ እንዳለ እንዴት ማወቅ ይችላል?

በዚሁ ርእስ ጉዳይ ላይ የእንቅስቃሴው ዕውቅ መምህራን የሚለጡትን ጽሑፍ በቀጥታ እንጥቀስ:—

"'እርግማን' ሰው እግዚአብሔርን ሲያሳዝን፣ ክፋት ሲፈጽም፣ በደልን፣ ግፍን ሲሠራ፣ ክእግዚአብሔር አምላኩ የሚቀበሰው የበደል ውጤት የሆነ ቅጣት ነው:: ይህ ቅጣት በግሰሰቡ፣ በቤተሰቡ ወይም ሁለትና ሦስት ትውልድ ክዚያም በላይ በመሄድ፣ አለበለዚያም አገርን ባካለለ መልክ ሊፈጸም ይችላል"[18]::

አንድ ሰው በእርግማን ውስጥ መውደቁን እንዴት ያውቃል የሚለውን ጉዳይ ጆን ኤክሃርት ራሳቸው በቀጥታ የጠቀሱት፣ ዴሬክ

[17] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 21:: የዴሬክ ፕሪንስ መጽሐፍ አስተምህሮውን ያዋቀረው በሚከተሉት ሦስት መንገዶች ነው:— *(1)* በሕይወታችን ውስጥ መርገም ሚና በመጫወት ላይ ሳለ መሆኑ እንደምን ለማወቅ እንችላለን? *(2)* ከመርገም ለመላቀቅና ከሚያስከትለውም የከፋ ሕይወት ለማምለጥ ምን ልናደርግ ይገባናል? *(3)* የእግዚአብሔርን በረከት እንደምን መጋራት እንችላለን"

[18] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 4::

ፕሪንስን ነው[19]። እኛም ፕሪንስን በቀጥታ ጠቅሰን፣ የኤክሃርትን ጭማሪ እናስከትላለን፦—

> "በግሌ ካካሄዱሁት የረጅም ጊዜ ጥናትና ከተለያዩ ለምኞች ካካበትሁት ግንዛቤ በመነሣት፣ የመርገምን ምልክቶች በለባት የተለያዩ ገጽታዎች ለመከፋፈል ችያለሁ[20]። እነኚህን እኔ ያዘጋጀኋቸውን ዝርዝሮችና ሙሌ ያቀረባቸውን መግለጫዎች ላወዳድራቸው እጅግ ተቀራራቢና ተመሳሳይ በመሆናቸው መደነቄ አልቀረም።"[21]
>
> 1. "የእእምሮ ወይም የስሜት መታወክ
> 2. በተደጋጋሚ ለበሽታ መጋለጥ (በተለይ በውርስ የተላለፈ ሲሆን)
> 3. መካንነት በተለይም ከውርጃና ከመሳለለው ሁኔታ ጋር የተያያዘ ሲሆን፣
> 4. ያላቋረጠ የገንዘብ ዕጥረት፣
> 5. የጋብቻ መፍረስና የቤተሰብ መከፋፈል፣
> 6. ያላቋረጠ የገንዘብ ዕጥረት (ችግር)፣
> 7. ለአደጋ 'በተደጋጋሚ' የተጋለጡ መሆን፣ በቤተሰብ ውስጥ ተደጋግሞ የደረሰ ሕይወትን በገዛ እጅ የማጥፋት ታሪክ ወይም ያለ ዕድሜ መቀሠፍ።"[22]

እነዚህን የዴሬክ ፕሪንስን ሰባት ነጥቦች፣ በጉዳዩ ላይ መጻሕፍት ያሳተሙ እንዲሁም በርእሰ ጉዳዩ ላይ ትምህርት የሚሰጡ ለምኞች ሁሉ አዘውትረው የሚጠቅሷቸው ነጥቦች ናቸው። ጆን ኤክሃርት ራሳቸው እነዚህን ሰባት ነጥቦች ከፕሪንስ በቀጥታ ከጠቀሱ በኋላ፣ የራሳቸውን ተሞክሮ በእማኝነት በመጥቀስ ሁለት ተጨማሪ ነጥቦችን ያከሳሉ (ያስተዋውቃሉ)፦—

> "እኔ ደግሞ በአገልግሎታችን ዘመን ካየሁት በመነሣት[23]፣ ተጨማሪ ሁለት ምልክቶችን ጨምራለሁ። እነዚህም፦—
>
> 1. በሌሎች ለምኞች ፊት ሞገስ ማጣት፣ እእምሮአዊ፣ አካላዊ፣ ወሲባዊ፣ ጉዳትና መወገድን ይጨምራል። ሞገስ እልባ መሆን፣ መጠላት፣ መገለል።
> 2. ተቅበዝባዥነት፣ መባከን፣ ዕረፍት የለሽ ሕይወት መኖር፣ ከአንዱ ቤት ወደ ሌላው፣ ከከተማ ከተማ፣ አንዱን ሥራ ለቆ ሌላውን፣ ከአንዱ ጎብረት ወደ ሌላው

[19] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 14። ነገር ግን እኛ ከተጠቀሰው ከምንጠቅስ ፕሪንስን በቀጥታ በመጥቀስ የኤክሃርትን ጭማሪ ደግሞ ከራሳቸው መጽሐፍ እንወስዳለን።

[20] አንባቢያን ልብ ሊሉት የሚገባ ነጥብ፣ ይህ ጉዳይ የግለሰቡ የግል ተሞክሮ መሆኑን ነው። ክርስቲያን አስተምህሮውን በግለሰቦች ተሞክሮ ላይ ሲመሠርት እንዴት ይችላል? ቅዱሳት መጻሕፍት በግልጽ የሚያስተምሩትን ትምህርት በተሞክሯችን ማዋዛት፣ ትክክለኝነቱን በግል ልምምዳችን ማድመቅ ተገቢ ነው። ነገር ግን የሰዎችን የግል ተሞክሮ የሕይወት መመሪያ ማድረግ፣ በዕንሰ ሐሳብ ደረጃ ስሕተት ነው። መጽሐፍ ቅዱስም ይህ ዐይነቱን አካሄድ አይደግፍም።

[21] የነገረ መለኮት ሰዎች፣ "exegesis" እንዲሁም "eisegesis የሚሏቸው መ·ያዊ ቃላት አሏቸው። የመጀመሪያው መጽሐፍ ቅዱስን እንበቦ፣ ትምህርቱን በትክክል በመፈከር/በመተንተን ወደ አንድ ድምዳሜ ላይ መድረስ ነው። ሁለተኛው ግን የራስን ሐሳብ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ እየሸነቀሩ ማስገባት ነው። እስቲ ይህን አሳብ ዴሬክ ፕሪንስ እያሉ ካሉት ጋር ያነጻጽሩ።

[22] ጸሐፊው፣ በቀጣዩቹ ተከታታይ ምዕራፎች እነዚህን ጉዳዮች በስፋት ይዘረዝራሉ። ፕሪንስ ከእነዚህ ውስጥ የትኛው ወይም ምን ያህሉ፣ በምን ያህል መጠን ተደጋግሞ ሊከሠት አንድ ክርስቲያን በመርገም ውስጥ ነው እንድንል ያደርገናል በሚለው ጉዳይ ላይ ሞርጥ ያሉ መልስ ያልሰጡት። ነገር በእያንዳንዱ ሰው የግል አስተያየት ላይ የሚወድቅ አሻሚ ምላሽ እንዲህ ሲሉ ሰንዝረዋል፣ "ከእነዚህ የመርገም ምልክቶች አንዱ ወይም የሁሉቱ በአንድ ሰው ላይ መታየት ያንን ሰው በመርገም ሥር እንዳለ አድርጎ ሊያስቈጥረው አይችልም። ዳሩ ግን አብዛኞቹ ምልክቶች ሲታዩ ወይም በተደጋጋሚ ሲደርሱ ስለዚያ ሰው ሁኔታ በመጠኑም ቢሆን ስለመናገር እንችላለን። ሆኖም በእርግጠኝነት ስለመናገር የምንችለው በመንፈስ ቅዱስ ስንመራ ብቻ ነው" ዴሬክ ፕሪንስ፣ *በረከት ወይስ መርገም*፣ ገጽ 34።

[23] እነዚህ ሰዎች አስተምህሮ የሚያዋቅሩት፣ ኩተምክሯቸው በመነሣት እንደ ሆነ ልብ ይሏል።

ኅብረት መባከን፣ አዘወትሮ የዘላንነትና የተቅበዝባዥነት ሕይወት መኖር"[24]።

አጭር ቀጭን ግምገማ

"ክርስቲያን በወላጆቹ መርገም ውስጥ ሊወድቅ ይችላል" የሚለውን አስተምህሮ ሙሉ ለሙሉ ብንቀበል እንኳ፣ እነዚህ ዴሬክ ፕሪንስ የዘረዘሯቸው ስባት ነጥቦች እንዲሁም ጆን ኤክሃርት ያከሉባቸው ሁለት ጭማሪዎች፣ "በርግጥ እንድ ሰው በመርገም ውስጥ ነው ብለን በቊርጥ መናገር የሚያስችሉን ናቸውን?" የሚለውን ጥያቄ በብርቱ እንድንጠይቅ የሚያስገድዱን ናቸው። በአፀደ ሥጋ የሚኖር የሰው ልጅ ሁሉ፣ ክርስቲያንም ሆነ የሌላ ሃያማኖት ተክታይ፣ ኢአማኒም ሆነ ሀልዎተ እግዚአብሔርን የሚጠራጠር ጠርጣሪ...ሊያጋጥሙት የሚችሉ የሕይወት ገጠመኞች ናቸው። እንድም ሰው ከእነዚህ ነገሮች ሁሉ ጽዱ ነኝ። አንዳቸውም ገጥመውኝ አያውቁም ማለት የሚችል አይመስለኝም። ምናልባትም የእንቅስቃሴው አስተማሪዎች ራሳቸው ከዚህ ሐቅ እምልጠዋል ማለት እጅግ ሲበዛ አስቸጋሪ ነው። ሕይወታቸውን በቅርበት ባናውቅም እንኳ፣ ከሰው ልጅ ተሞክሮ ይህ ይሆናል ብሎ ለማሰብ ወፈር ያለ አውር እምነት ይፈልጋል።

ይህ አስተሳሰብ በዘርዝር ያላብራራውን ነገር ግን ታሳቢ አድርገን ያስፍንውን ሌላ የነገረ መለኮት ፅንሰ እሳብ መሰስ ብለን እንድንመረምር የሚያስገድደን ነው። ይኸውም፦— *(ሀ)* በርግጥ ክርስቲያን ችግር የሌለበት ምድራዊ ሕይወት እንደሚኖር መጽሐፍ ቅዱስ ዋስትና ሰጥቶአልን? *(ለ)* በምድራዊው ኑሮ ክርስቲያን የገንዘብ ችግር እንዲሁም የበሽታ ጣጣ እንደማይጐበኘው መጽሐፍ ቅዱስ ማረጋገጫና ተስፋ ሰጥቶአልን? እነዚህ በወጉ መተንተን ያለባቸው መሠረታውያን የነገረ መለኮት ጭብጦች ናቸው። በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ፣ "አባሪ" በሚል ርእስ እነዚህን ሁነኛ ጥያቄዎች

[24] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 14-15።

እንነጋገርባቸዋለን። ለእሁኑ ግን ሁለት መሠረታውያን ነጥቦችን ጠቀም በማድረግ፣ እነዚህ ዘጠኝ ዝርዝር ሐተታዎች ስሕተት መሆናቸውን ልሞግት[25]፦—

1. **መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቲያኖች በተለያዩ ችግሮች ውስጥ ሊያልፉ እንደሚችሉ በግልጽ ይናገራል፤**
   በናሙናነት የተወሰኑ ክፍሎችን እንመልከት፦—

> "35. ሌቶች ሙታናቸው ተነሡላቸው። ሌሎቹ ደግሞ የተሻለውን ትንሣኤ ለማግኘት ሲሉ፣ መትረፍን ንቀው ስሞት ስሚዳርግ ሥቃይ ራሳቸውን ሰጡ፣ ከዚህም ነጻ ስመውጣት አልፈለጉም። 36. አንዳንዶቹ መዘባበቻ ሆኑ፣ ተገረፉ። ሌሎቹ ደግሞ ታስረው ወደ ወህኒ ተጣሉ፣ 37. በድንጋይ ተወገሩ፣ በመጋዝ ሰውስት ተሰነጠቁ፣ ድንጋይ ተወገሩ፣ ሰፈተና አልፈው ተሰጡ፣ በሰይፍ ተወግተው ሞቱ፣ አየተጉሳቈሉ፣ አየተሰደዱና እየተንገላቱ የበግና የፍየል ቈዳ ሰብሰው ዞሩ፣ 38. ዓለም ሰእነርሱ አልተገባቻቸውምና። በየበረሓውና በየተራራው፣ በየዋሻውና በየጕድጓዱ ተንከራተቱ። 39. እነዚህ ሁሉ ስለ እምነታቸው የተመሰከረላቸው ቢሆኑም ከእነርሱ ማንም የተስፋውን ቃል የተቀበለ የለም። 40. አግዚአብሔር ስእኛ የሚበልጥ ነገር ስላዘጋጀ፣ ያለ እኛ ፍጹማን ሲሆኑ አልቻሉም" (ዕብ. 11)።

> "21. እኛ ግን ለዚያ እጅግ ደካሞች መሆናችንን አያፈርሁ እናገራለሁ። ማንም በድፍረት በሚመካበት ነገር ሁሉ እኔም ደፍሬ

[25] ልብ ልናደርጋቸው የሚገቡ ሁለት መሠረታውያን ነጥቦች ያሉ ይመስለኛል፦— *አንደኛው*፣ በዝርዝሩ ውስጥ የተካተቱት ነገሮች ሁሉ የመርገም ውጤት ናቸው ብለን ብንቀበል *ሁለተኛ*፣ ክርስቲያን በመርገም ውስጥ ይሆናል የሚለውን አስተምህሮ ብናምን እንኳ፣ የግለሰቦቹ ትምህርት በፍጹም ትክክል ሊሆን አይችልም። ከዚህ በታች የዘረዘርኋቸው ትችቶች እነዚህ ሁለት ነጥቦች ትክክል ናቸው ብዬ ባሰብ እንኳ የሚከተለውን ዝርክርክ ውጤት ነው።

መመካት እንደምችል አንደ ሞኝ እናገራለሁ። 22. እነርሱ ዕብራውያን ናቸውን? እኔም ነኝ፤ እስራኤላውያን ናቸውን? እኔም ነኝ፤ የአብርሃም ዘር ናቸውን? እኔም ነኝ። 23. የክርስቶስ አገልጋዮች ናቸውን? አንደ አበደ ሰው ልናገርና እኔ እበልጣቸዋለሁ፤ ደግሞም ብዙ ጊዜ በሥራ ደክሜአለሁ፤ ብዙ ጊዜ ታስሬያለሁ፤ ብዙ ጊዜ ተገርፌአለሁ፤ ብዙ ጊዜ ለሞት ተቃርቤአለሁ። 24. አይሁድ ለአርባ ጅራፍ አንድ የቀረው አምስት ጊዜ ገርፈውኛል። 25. ሦስት ጊዜ በዱላ ተደብድቤአለሁ፤ አንድ ጊዜ በድንጋይ ተወግሬአለሁ፤ ሦስት ጊዜ የመርከብ አደጋ ደርሶብኛል፤ አንድ ሌሊትና ቀን በባሕር ላይ አድሬአለሁ፤ 26. ብዙ ጊዜ በጕዞ ተንከራትቻለሁ፤ ደግሞም ለወንዝ ሙላት አደጋ፣ ለወንበዴዎች አደጋ፣ ለገዛ ወገኖቼ አደጋ፣ ለአሕዛብ አደጋ፣ ለከተማ አደጋ፣ ለገጠር አደጋ፣ ለባሕር አደጋ እንዲሁም ለሐሰተኞች ወንድሞች አደጋ ተጋልጬ ነበር። 27. ብዙ ጥሬአለሁ፤ ብዙ ደክሜአለሁ፤ ብዙ ጊዜ እንቅልፍ አጥቻለሁ፤ ተርቤአለሁ፤ ተጠምቻለሁ፤ ብዙ ጊዜ ምግብ ሳልቀምስ ኖሬአለሁ፤ በብርድና በራቍትነት ተቈራምጃለሁ። 28. ሌላውን ነገር ሳልቈጥር፤ ዕለት ዕለት የሚያሰጨንቀኝ የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ሐሳብ ነው። 29. ደካማ ማን ነው? አኔስ አብሬ አልደክምምን? በኀጢአት የሚሰናከል ማን ነው? እኔስ አልቈጭምን?" (2ቆሮ 11)።

"32. እነሆ፤ ሁላችሁም በየፊናችሁ የምትበታተኑበት ጊዜ ይመጣል፤ ያም ጊዜ አሁን ነው። አኔንም ብቻዬን ትተውኛላችሁ፤ ይሁን እንጂ አባቴ ከእኔ ጋር ስለ ሆነ ብቻዬን አይደለሁም። 33. "በእኔ ሰላም እንዲኖራችሁ፤ ይህን ነግሬአችኋለሁ። በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዞአችሁ፤ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ" (ዮሐ. 16)።

"18. "ዓለም ቢጠላችሁ፤ ከእናንተ በፊት እኔን እንደ ጠላኝ ዕወቁ" (ዮሐ. 15)።

"22. የደቀ መዛሙርቱንም ልብ በማበረታታትና በእምነታቸው ጸንተው እንዲኖሩ በመምከር፤ "ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት በብዙ መከራ ማለፍ አለብን" አሏቸው" (ሐሥ 14)።

እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ክርስቲያን በችግር ውስጥ ሊያልፍ እንደሚችል የሚናገሩ ናቸው። እርግጥ ነው ክርስቲያን አንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የተመቻቸ ሕይወት ውስጥ ሊኖር ይችላል፤ በእንጻሩ ደግሞ በችግር፣ በሀማም፣ በሥቃይ፣ በዕጦት፣ በበሽታ ወዘተ ውስጥ ሊያልፍ ይችላል። ይህ መፍቀሬ ንዋይ ለሆነው የለው ልጅ፣ በተለይ ደግሞ ለድኅረ ዘመናዊው ትውልድ የሚጣፍጥ አሳብ እይደለም። ቃለ እግዚአብሔር ግን፣ "ችግር የለም" ሳይሆን የሚለን፣ "ችግር አለ" "ነገር ግን፣ በችግር ውስጥ ትልቁ እግዚአብሔር አብሮን አለ"። "ከችግሮቹ ይልቅ ከእኛ ጋር ያለው ጌታ ብርቱ ነው"። "ክርስቲያን ችግርን የሚፈራ ሳይሆን፣ ችግርን በቍርጠኝነት የሚጋፈጥ ለማዕት ነው"... የሚለውን አሳብ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቲያን በመሆናችን ብቻ ከሌሎች ሰዎች የተሻለ ምድራዊ ሰኬት እንደሚያጋጥመን አይናገርም፤ ዋስትናም አይሰጠንም። ባይሆን በምናልፍባቸው ሁኔታዎች ውስጥ ሁሉ፣ ልዑል እግዚአብሔር አብሮን እንደሚሆን፣ እንደሚያጽናናን፣ ክጊዜያዊ ችግር የሚያልፍ ደስታና ሐሴት በልባችን እንደሚያኖር ወዘተ ዋስትና አለን።

2. ከዝርዝሮቹ መኻል አንዳንዶቹ እንደ መርገም የሚታዩ ሳይሆኑ፣ እንደ በረከት የሚቈጠሩ ሊሆኑ ይችላሉ።

ለምሳሌ ጆን ኤክሃርት ሥራ መቀያየር፣ የመኖሪያ ቦታ መቀያየር፣ በሥራ መጠመድ ወዘተ እንደ መርገም ጠቅሷቸዋል፤ እነዚህ ነገሮች እንደ በረከት አይቈጠሩም ቢባል እንኳ፣ እንደ

መርገም ግን ሊታዩ የማይችሉባቸው ብዙ አጋጣሚዎች ይኖራሉ። እንዲያውም አንዳንድ ሰዎች እነዚህን በተቃራኒው መልክ እንደ በረከት ሊቁጥሯቸው ይችላሉ። ሰለዚህ አንድን ነገር መጥፎ ነው ወይስ ጥሩ ነው የሚለውን ጉዳይ ለመበየን፣ "በማን አይታ?" "በየትኛው መሰፈርት?" የሚሉትን መሠረታውያን ጥያቄዎች ያስነሣሉ። እነዚህ ጉዳዮች፣ በብዙ መልኩ አንጻራዊ ምልከታዎች እንጂ ነባራዊ መሠረት ያላቸው አይደሉም። ሰለዚህ ሥራ መቀያየር፣ ቤት መቀያየር፣ ሰፈር መቀያየር ወዘተ ለጀን ኤከሃርት መርገም ቢሆኑ ሌላው ደግሞ እንደ በረከት ሊቁጠሩ የሚችሉ ናቸው።

3. የቀረቡት ዝርዝሮች፣ መርገምን በቅርጥ ለመወሰን የሚያስችሉ መሰፈርቶች አይደሉም።

እኛ እንደ "መርገም" ያየናቸውን ነገሮች፣ እንደ ኪላራ የሰፈርናቸው ገጠመኞች...የትልቅ ሰኬት፣ የትልቅ በረከት ምክንያት የሆኑባቸው እጅግ በርካታ ገጠመኞች አሉን። በአንድ ወቅት ያሰሰቀሰን ጉዳይ፣ የኋላ ኋላ የትልቅ በረከት ምንጭ ሆኖ አይተናል። ለዚህም ነው መጽሐፍ ቅዱስ በሕይወታችን የሚያልፉ ነገሮች ሁሉ፣ "ሰበኛ" ዐላማ መጥተው የሚሄዱ ነገሮች እንደ ሆኑ አበክሮ የሚገልጸው። እንዲያውም መጽሐፍ ቅዱስ መጠናቸውንና ዐይነታቸውን ሉዓላዊው ጌታ እንደሚቈጣጠራቸው ይገልጻል። ውጤቱም ሆነ ዐላማው እኛ ቢገባንም ሆነ ባይገባንም (የሚከተሉትን ምንባባት በናሙናነት ይመለከቷል—ሮሜ 8÷28:35-39፤ 2ቆሮ. 4÷15፤ ሮሜ 5÷34፤ ዘፍ. 50÷20፤ ዘዳ. 8÷2:3:16፤ መዝ. 46÷1-2፤ ኤር. 24÷5-7፤ 2ቆሮ. 5÷1፤ ፊልጵ. 1÷19-23፤ 2ተሰ. 1÷5-7፤ ዕብራ 12÷6-12፤ ያዕ. 1÷3-4፤ 1ጴጥ. 1÷7-8)።

4. በመሰፈርቱ ውስጥ የተካተቱት እንዳንዶቹ ነጥቦች የሰውን ባሕርይ እንዲሁም የሰው ልጅ የሚኖረውን ሕይወት በትክክል ያገናዘቡ አይደሉም።

ማነው ላይፈራ ላይቸር የሚኖር? "የአእምሮና የሰሜት መታወክ" ላይገጥመው የሚችል ሰብአዊ ፍጡር የቱ ነው? በርግጥ ይህና ይህን መሰል ሁኔታዎች በሕይወታችን እውን የማይሆኑ ከሆነማ፣ ወገኖቼ ያለንው መንግሥተ ሰማይ ነው ማለት ነው። "እንባዎችን ሁሉ ከዐይናቸው ላይ ያብሳል" በተባለበት፣ ነገር ግን ይመጣል ብለን በምንጠብቀው መጻኢ ዓለም ላይ አየኖርን ነው ማለት ነው።

ዴሬክ ፕሪንስ "በተደጋጋሚ ሰበሽታ መጋለጥ (በተለይ በውርስ የተላለፈ)" መርገም ነው ብለውናል። ከወላጆቻችን የሚተላለፉ በሽታዎች መኖራቸው እሙን ነው፤ ነገር ግን የበሽታ ዕዳ ብቻ ላይሆን፣ ብዙ በረከቶችን ከቤተሰቦቻችን እንወርሳለን፤ ለምሳሌ አካላዊ ውበት፣ ሰል የሆነ ጭንቅላት ወዘተ። ስለዚህ መርገም ተላለፈ እንደ ተባለው ሁሉ በዚህ መልክ የሚመጣውንስ በረከት እንዴት ልናስላው ይሆን? በርግጥ አነዚህን ነገሮች ቃለ እግዚአብሔር መርገም ይላቸዋል? የሚላቸው ከሆነ እነዚህን መርገም የሚላቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የት ቦታ ነው የሚገኘው? ይህን ጉዳይ ኋላ ዘለግ አድርገን እንመለከተዋለን።

5. በዝርዝሩ ውስጥ ከተካተቱት መኻል አንዳንዶቹ በእኛ መልካምነት እውን የሚሆኑ ነገሮች ላይሆኑ ይችላሉ።

ለምሳሌ ትዳርን ያለማፍረስ፣ በእኛ መልካምነት ብቻ የሚወሰን ላይሆን ይችላል። ተጣማሪው ወገን አልፈልግም፣ አሻፈረኝ ብሎ ትዳር ሊያፈርስ ይችላል። አንዱ ወገን በወስደው አሉታዊ አካሄድ ሌላው ወገን እኔ በመርገም ውስጥ ነኝ ማለት እንዴት ይችላል? በአንድ አገር ኋላቀርነት፣ ጦርነት፣ አድሎ፣ መሰና ወዘተ ለናኝ የሚችለው፣ በእኛ መልካምነት ላይሆን በአገር መሪ

ፖለቲከኞች እኩይ አስተዳደር ሊሆን ይችላል። አሜሪካን አገር የተወለደ ልጅ ኢትዮጵያ ውስጥ ከተወለደው ይልቅ ጥሩ ዕድል አንዳለው ይገመታል። ስለዚህ ኢትዮጵያውያን በመርገም ውስጥ ናቸው አሜሪካውያን በበረከት ውስጥ ናቸው ማለት እንዴት ይቻላል?

እንዲያውም እንደ ላውዲ ዐረብያ ያሉ የዓለማችን ሀብታም አገሮች፣ የአስልምና ሃያማኖት ተከታዮች ናቸው። እንደ ጃፓን በሀብትና በሥልጣኔ የናጠጡ አገሮች የሺንቶና የቡድሃ ሃያማኖት ተከታዮች ናቸው። በቅርቡ በወጣ አንድ መረጃ፣ 47 በመቶ የሚሆነው የቻይና ነዋሪ አምላክ አለ ብሎ እንኳ አያምንም። በተመሳሳይ መንገድ 31 በመቶ ጃፓናዊ በህልውተ እግዚአብሔር አያምንም[26]። የቻይናውን አንኳ ብንተወው፣ ቢያንስ አንድ ጃፓናዊ ከመደበኛው አትዮጵያዊ፣ ዐሥራ ስድስት ዕጥፍ የተሻለ ሕይወት እንደሚኖር ለልካችንን በመጠቀም ማጣራት አንችላለን[27]። ጣያት አምልኮ ወይም በእግዚአብሔር መኖር ያለማመን ለመርገም አንዱና ትልቁ መስፈርት ከሆነ፣ ይህን የዴሪክ ፕሪንስ አስተምህሮ፣ ከዓለማችን ነባራዊ እውነታ ጋር እንዴት ማደላደል ይቻል ይሆን?

በአጠቃላይ እነዚህን መስፈርቶች ተከትሎ አንድ ሰው በመርገም ውስጥ ነው ወይስ አይደለም፣ የሚለውን ጉዳይ ለመበየን እጅግ ሲበዛ አስቸጋሪ ነው። ለዚህም ላይሆን አይቀርም ዴሬክ ፕሪንስ፣ አንድ ሰው በመርገም ውስጥ መሆኑን ወይም ያለመሆኑን "በአርግጠኛነት ለመናገር የምንችለው፣ በመንፈስ ቅዱስ ለንመራ ብቻ

[26] *The Washington Post May 23, 2013*
https://www.washingtonpost.com/news/worldviews/wp/2013/05/23/a-surprising-map-of-where-the-worlds-atheists-live/?utm_term=.a2cfff4f80b0

[27] *OECD Better Life Index* የአንደ ጃፓናዊ የዓመቱ አማካኝ ገቢ *28,641* ዶላር ሲሆን፣ አንደ *World Bank Open Data* በ2016 ዓ.ም የአንድ ኢትዮጵያዊ ዓመታዊ ገቢው በአማካኝ *1730* ዶላር ነው።
https://data.worldbank.org/indicator/NY.GNP.PCAP.PP.CD

ነው"[28] የሚል መሿለኪያ ያበጁት[29]። ይሻላቸዋል! መስፈርታቸው ነባራዊ ሊሆን በጭራሽ አይችልም።

በዝርዝሩ ውስጥ ያካተቷቸው ነገሮች ሁሉ፣ የመርገም ውጤት ናቸው ብለን ብናምን እንዲሁም ክርስቲያን በመርገም ውስጥ ይሆናል የሚለውን አስተምህሮ ትክክል ነው ብለን ብንቀበል እንኳ፣ እኔ ከዚህ በላይ የዘረዘርኋቸው አምስት ነጥቦች። መስፈርቱ ከበዙ አንጻር ቢሆን ስሕተት ባይሆን አንጻራዊ መሆኑን አመላካች ነው።

ለ. ክርስቲያንን መርገም ውስጥ ይጥሉታል እንዲሁም ከመርገም ለመውጣት ማድረግ ያለበት የተባሉትን ነገሮች ደግሞ እንመልከት

በመርገም ውስጥ የሚጥሉን፣ "ጣያትን ማምለክ"፣ መናፍቃዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ መግባት[30]፣ "የግብረገብ ችግር" (ለምሳሌ ወላጆችን ያለማክበር አንዲሁም ከትዳር ውጪ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ)[31]፣ "ፀረ አይሁዳዊነት"[32]፣ "ሕግ አክራሪነት

[28] ዝኒ. ከማሁ፣ ገጽ *34*።

[29] ነገሩን ምን ያህል አንጻራዊ/ጎሰናዊ ብያኔ እንዳደረጉት አንባቢ ልብ ይበል። አንባቢዎቹን የማበረታታው ሌላው ነገር፣ *(1)* በዝርዝሩ ውስጥ የተካተቱት ነገሮች ሁሉ የመርገም ውጤት ናቸው ብለን ብንቀበል *(2)* ክርስቲያን በመርገም ውስጥ ይሆናል የሚለውን አስተምህሮ ትክክል ነው ብለን ታሳበ ብናደርግ እንኳ፣ የግለሰቦቹ ትምህርት በናጹም የተሳከረ መሆኑን ለመረዳት እያንዳንዱን መስፈርት ቆም ብለው እንዲመረምሯቸው ነው።

[30] መርገም ውስጥ ይከታሉ የተባሉት መናፍቃዊ እንቅስቃሴዎች፣ የይሖዋ ምስክሮች፣ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያንና የሞርሞን ሃይማኖት ይገኙበታል ገጽ *52*።

[31] ዝኒ. ከማሁ፣ ገጽ *57* እስከ *61*።

[32] ዝኒ. ከማሁ፣ ከ62 እስከ *68*። ይህ ጉዳይ ራሱን የቻለ ትልቅ ጥራዝ የሚያጽፍ ትችት ሊወጣው ይችላል።

ወይም ሥጋዊነት”[33]፣ “ስርቆት፣ እጭበርባሪነት፣ እግዚአብሔርን ማታለል”[34]፣ አሉታዊ ንግግር[35]።

ልብ እንበል፣ “ክርስቲያን በመርገም ውስጥ ሊወድቅ ይችላል” ተብሎ፣ “ጣያትን ማምለክ” እንዲሁም “መናፍቃዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ መግባት” የሚለው ገለጻ፣ በርካታ ጥያቄ ይጭራል። አንደኛ፣ ክርስቲያን አንዴት‹ና በምን አግባብ ጣያትን ሊያመልክ አንዲሁም መናፍቃዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ገብቶ “ክርስቲያን” ሊባል ይችላል? የአንቅስቃሴው መምህራን ራሳቸው “ክርስቲያን ማነው?” ለሚለው የለጡት ገለጻ፣ “ጌታን የሚወድ”፣

[33] ለዚህ አንደ ምሳሌ ከቀረቡት ውስጥ፣ “ከእግዚአብሔር መገለጥ ምስጢር ይልቅ፣ ለሥነ መለኮት ትምህርት አዘውሮት መስጠት...በእምነት ከመጓዝ ይልቅ በአእምሮ ምሪት መተማመን...ከፍቅር ይልቅ ለሕግ መገዛት” ዴሬክ ፕሪንስ፣ *በረከት ወይስ መርገም*፣ ከገጽ 69 እስከ 76። አእምሮን የአምላክ ባላንጣ አድርጎ ማቅረብ፣ የብዙ ስሕተት ትምህርቶች ዐይነተኛ መለያቸው ነው። መጽሐፍ ቅዱስን የሰጠን አምላክ ነው አእምሮንም የሰጠን። ከአንሰላ የለየን ትልቁ የአምላክ በረከት አእምሮ ነው። አነዚህ ሰዎች ግን ይህን ትልቅ በረከት በማለጣል አንሰላ ጉራ ሊቀላቅሉን ይፈልጋሉ። ስው አእምሮውን ከጣለ ምን ሊተርፍለት ይችላል፣ አንሰላ ከመሆን በቀር።

[34] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 77 እስከ 80።

[35] ዝኒ ከማሁ፣ ከገጽ 90 እስከ 99። ለረጅም ጊዜ ዴሬክ ፕሪንስ፣ ከእምነት እንቅስቃሴ አስተምህሮ ጋር ንክኪ ያላቸው አይመስለኝም ነበር። ኋላ ግን በግልጽ የተገነዘብሁት፣ ከአስተምህሮውም ሆነ ከእንቅስቃሴው አንጋፋ መምህራን ጋር ወዳጅነት እንደ ነበራቸው ነው። ለምሳሌ በወርኀ ሐምሌ 1976 ዓ.ም ኬኔት ኮፐላንድና ዴሬክ ፕሪንስ በአሜሪካን አገር በጥምረት የጀማ ሉበክትና የትምህርት ዐውደ ጥናት አዘጋጅተው ነበር። ስለመርገም ትንታኔ ያቀረቡበት መጽሐፋቸው፣ ክርስቲያን ቱጃር መሆን አለበት እንዲሁም መታመም የለበትም የሚለውን አስተሳሰብ ታሳቢ ያደረገ ነው። ልክ እንደዚሁ ሁሉ፣ አምንታዊ ንግግሮች አምንታዊ ውጤት አንደሚያስከትሉ አሉታዊ ንግግሮችም አሉታዊ ውጤት እንደሚያመጡ በርካታ ቦታ ገልጸው እናነባለን። አጋንንትን ማስወጣት በተመለከተ ኬኔት ሃጊን ቃል ከተናገርሁ ይበቃል ባይ ሲሆኑ፣ ዴሬክ ፕሪንስ ግን በቂ ጊዜ ሰጥቶ መጸለይ...ያስፈልጋል ባይ ናቸው። ምናልባት ልዩነቱ ይህ ብቻ ሳይሆን ይቀራል?

“ዳግም የተወለደ”፣ “መንፈስ ቅዱስ የተሞላ”[36] ብለው ነው። ታዲያ በምን አግባብ ነው የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የሆነ፣ ጌታን የሚወድ...ስው ጣያትን የሚያመልከው። ሁለተኛ፣ ቤተሰቦቹ ጣያትን በማምለካቸው ምክንያት፣ ግለሰቡ መርገም ውስጥ የሚወድቅበት አንዳችም ምክንያት የለም። ይህን ጉዳይ ኋላ በስፋት እንመረምረዋለን።

ንጢአት ሁሉ በአምላክ ፊት ጸያፍ ተግባር ነው። ነገር ግን አማኝ በንጢአት በወደቀበት ጊዜ ሁሉ በመርገም ውስጥ ይወድቃል ስማለት የሚያስችል፣ አንዳችም የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ የለም። በመሠረቱ የእንቅስቃሴው መምህራን ራሳቸው፣ “አዱብ ወቅዱስ” ነን ንጢአት ዝር ብሎብን አያውቅም የሚሉ አይመስሰኝም። መጽሐፍ ቅዱስ፣ “ንጢአት የለብንም ብንል አግዚአብሔርን ሐስተኛ እናደርገዋለን” ይላል (1ዮሐ. 1÷8-10፤ እንዲሁም የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል ኢዮ. 15÷14፤ 25÷4 ኤር. 2÷35፤ ዮሐ. 3÷33፤ 1ዮሐ. 5÷10)። ይህ አውነት ከሆነ ደግሞ፣ የአንቅስቃሴው መምህራን ራሳቸው በየቀኑ በመርገም ውስጥ እየወደቁ፣ በየቀኑ ይነሣሉ ማለት ነው።

አነዚህ መርገሞች የሚሰበሩት በሚከተለው አምስት መልኩ አንደ ሆነ ዴሬክ ፕሬንስ ያስረዳሉ:—

1. “በክርስቶስ ስለ ማመንህና ስለ አንተም መሥዋዕት ሆኖ ስለ መሞቱ መስክር (ዐውጅ)”[37]፣
2. “ስለ ዐመፀኛነትህና ስለማንኛውም ጎጢአቶችህ ንስሓ ግባ”[38]፣
3. “ስለ ማንኛቸውም በደሎችህ ይቅርታን ጠይቅ”[39]፣
4. “የበደሉህን ሁሉ ይቅር በል”[40]፣

[36] ዴሬክ ፕሪንስ፣ *በረከት ወይስ መርገም* አንዱን ምረጥ፣ 1989 ዓ.ም፣ ገጽ 50።

[37] ዴሬክ ፕሪንስ፣ *በረከት ወይስ መርገም* አንዱን ምረጥ፣ ገጽ 141።

[38] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 142።

[39] ዝኒ ከማሁ።

5. "ከአስማትና ጥንቁላ ጋር ያለህን ግንኙነት ፈጽሞ እቋርጥ"[41]::

ክርስቲያን፣ የክርስቶስ ሞትና ትንሣኤን በመመስከር ሰዎች ወደ ድነት እንዲመጡ ማበረታታት እንዳለበት እሙን ነው:: ነገር ግን በሥራ መደራረብም ሆነ በሌላ የተለየ ምክንያት ይህን ባለማድረጉ መርገም ውስጥ ይወድቃል ብሎ ማስተማር፣ ሊበዛ እንግዳ ነው:: ታላቁ ተልእኮን ያለመከወኑ ኀጢአት ሊሆን ይችል ይሆናል፣ ነገር ግን ከዚያ ባለፈ ይህን ያለማድረግ መርገም ውስጥ ይጥላል ማለት ፍጹም ስሕተት ነው::

ክርስቲያን ለሰማናቸውም ኀጢአት፣ ንስሓ መግባት እንዳለበት ሁላችንንም ያስማማል:: ነገር ግን ይህ አስከሚሆን ግለሰቡ በመርገም ውስጥ ይወድቃል ማለት ስሕተት ነው:: በተጨማሪ ዳግም የተወለደ ክርስቲያን አስማትና ጥንቁላን እንዴት ሊለማመድ ይችላል? ይህን የሚያደርግስ ክርስቲያን በምን መስፈርት ክርስቲያን ነው ማለት እንዴት ይቻላል?

በአጠቃላይ ክርስቲያንን በመርገም ውስጥ ይጥሉታል እንዲሁም እንድ ክርስቲያን በመርገም ውስጥ እንደ ወደቀ ምልክት ናቸው የተባሉት ዝርዝሮች መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደሉም:: እንዲያውም በሰዎች አንጻራዊ ምልከታ ላይ መሠረት ያደረጉ አስተሳሰቦች ናቸው:: ከዚህ ባለፈም ክርስቲያን በክርስቶስ ኢየሱስ በማመኑ ባገኘው ትልቅ ዐርነት ላይ እንዳይጓደድ የሚያደርጉ ሰብእውያን ቀንበሮች ናቸው::

መርገምና ከወላጅ የሚተላለፉ በሽታዎች

ይህን ርእስ ከላይ በስፋት እንደምንነጋገርበት ገልጸን ነበር፣ አሁን በቅርበት እንመርምረው::

[40] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 143::

[41] ዝኒ. ከማሁ::

በቤት ለቤት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ላይ፣ ፕሮግራም መሪው ከታዳሚው የጸሎት ርእስ መጠየቅ ጀመረ:: እንዲት እኅት፣ "ወገኖቼ መርገም እንዲሰበር ጸልዩልኝ" አለች:: ብዙዎቻችን በግብዓውያኑ መሚ እንደ ደረቀ እስከሬን ክው ብለን ቀረን:: "ምን ማለት ፈልገሽ ነው?" አለ መሪው፣ መገረምንና ግራ መጋባትን በቀላቀለ ፈገግታ:: "እባቴ ክፋኛ ይቈጣ ነበር" አለች እኅታችን ደልደል ብላ:: "ታዲያ ቊጣው የነደደ ጊዜ፣ እንኳን ስው ተስባሪ ዕቃ እንኳ በፊቱ የመቆም መብት የሰውም፣ በቻይና ካራቴ እየተወናጨፈ እምሽክ ያደርጋቸዋል:: ስውም ቢሆን ዕጣ ፈንታው ከዕቃዎቹ እይለይም:: ይህ የቊጣ መርገም በእኔም ሆነ በታላቅ እኅቴ ላይ ሰፍሮብናል:: ስንቈጣ የምንሆነውን ነገር፣ የሚያደርገንን ነገር በውል እናውቀውም፣ ምላጭ ከሚያስውጠው እልዛችን ጋር ተደምሮ ለምንም ነገር የምንመለስ ስዎች እንሆንም":: ፕሮግራም መሪው፣ "መቈጣት የሥጋ ሥራ እንደ ሆነ፣ በገላትያ 5÷16:20 ላይ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይናገራል:: ከዚህ ባለፈ ግን በመርገም ውስጥ ነኝ የሚለው እነጋገርሽ ግልጽ እይደለም" አላት:: የወንድማችን መልስ እኅታችንን ሊያረካት እልቻለም:: "ግድ የላችሁም እየሰበራችሁ ጸልዩልኝ! ከዘር ማንዘር ሊንከባለል የመጣ የቊጣ እርግማን እኔና እኅቴን እየተጫወተብን ነው"::

ይህ፣ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለዘመናት የተዘራ ክፉ ዘር ነው:: አረሙ ለረጅም ጊዜ ሳይነቀል የመቆየቱም ምክንያት እንደ ርቱዕ ትምህርት እየታየ ነው:: እንዲያውም የዚህ ተቃራኒው ትምህርት እንደ ኑፋቄ እየታየ መምጣቱ ነው ብል ግነት አይሆንም::

ብዙ ሳይንሳዊ ጥናቶች፣ የወላጆች ተጽእኖ በልጆች ላይ ከፍተኛ እንደ ሆነ ያስረዳሉ—እምንታዊውም ሆነ አሉታዊው:: ወላጆች ቤታቸውን ገነት እንዲሁም ገሀነም የማድረግ ከሂሎታቸው እጅግ ትልቅ ነው:: ስዚህም ነው መጽሐፍ ቅዱስ ወላጆች ልጆቻቸውን ሳያስልሱ እንዲመክሩ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን እንዲያስተምሩ፣ የበጉ ምግባር ተምሳሌት እንዲሆኑ የሚያስገነዝበው (ዘዳ. 6÷7-9፤ ኤፌ. 6÷4)::

አባቶችን በተመለከተ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እንዲህ ይላሉ:—

"ትክክለኛና ቀና የሆነውን በማድረግ የአግዚአብሔርን (ያህዌ) መንገድ ይጠብቁ ዘንድ ልጆቹንና ከእርሱ በኋላ ቤተ ሰቦቹን እንዲያዝ መርጬዋለሁ፤ ይኸውም እግዚአብሔር (ያህዌ) ለአብርሃም የሰጠው ተስፋ ሁሉ እንዲፈጸም ነው" (ዘፍ. *18÷19*)።

"አባቱም፣ 'ሰምን አንዲህ ታደርጋለህ?' ብሎ ገሥጾት አያውቅም ነበር፤ አዶንያስም እጅግ መልከ መልካምና የአቤሴሎም ታናሽ ወንድም ነበር" *(1ነገ. 1÷6)*።

"ንጉሡም እጅግ አዘነ፤ በቅጽር በሩ ዐናት ላይ ወዳለችው ቤት ወጥቶ አለቀሰ፤ ሲሄድም፣ "ልጄ አቤሴሎም ሆይ! ልጄ አቤሴሎም! በአንተ ፈንታ ምነው እኔ በሞትሁ ኖሮ! አቤሴሎም ሆይ፣ ልጄን፣ ጠየው ልጄን!" ይል ነበር" *(2ሳሙ. 18÷33)*።

ሐዲስ ኪዳን የእናቶችን ተጽእኖ በተመለከተ እንዲህ ይላል:—

"ግብዝነት የሌለበት እምነትህን አስታውሳለሁ፤ ይህ እምነት ቀድሞ በአያትህ በሎይድ እንዲሁም በእናትህ በኤውንቄ ዘንድ ነበረ፤ አሁን ደግሞ በአንተ አንዳለ ተረድቻለሁ" *(2ጢሞ. 1÷5)*።

"ልጅቷም በእናቷ ተመክራ፣ 'የመጥምቁ ዮሐንስን ራስ በላሕን ላይ አድርገህ አሁኑኑ ስጠኝ' አለችው...የተቁረጠውንም ራስ በላሕን ላይ አድርገው ለልጅቱ ሰጧት፤ ልጅቱም ወስዳ ለእናቷ ሰጠች" (*ማቴ. 14÷8;11*)።

የወላጆች ብቻ ሳይሆን፣ የእካባቢና የባልንጀራም ተጽእኖ በልጆች ሕይወት ውስጥ እጅግ ከፍተኛ እንደ ሆነ ይታወቃል። ነገር ግን ዴሬክ ፕሪንስና ባልደረቦቻቸው፣ ከጓደኛ የሚወረስ መርገም ከእካባቢ የሚወረስ መርገም ባስማለታቸው እናመሰገናቸዋለን።

ተጽእኖና እርግማን

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፣ "ከዘር ማንዘር የሚተላለፍ እርግማን" *("generation curse")* የሚል ቃል እንደ ሌሰ ስንቶች እናውቅ ይሆን። ያን ዐይነት አሳብ የያዘ የቅዱሳት መጻሕፍት ምንባብ

የለም። አንድ ወዳጄ፣ "'ከዘር ማንዘር የሚተላለፍ እርግማን' የሚለው ትምህርት ብዙ ተቀባይነት ያገኘው፣ ስዎች ላደረሱት ጥፋት፣ ላስከተሉት በደልና ግፍ ሙሉ ኀላፊነት ላለመውሰድ በሚያደርጉት ትንቅንቅ፣ እንደ መሸፈኛ ስለሚያገለግላቸው ነው" የሚለው አባባሉ፣ በተወሰነ ደረጃም እንኳ ቢሆን እውነትነት ያለው ይመስለኛል። የሥነ ልቡና ምሁራን፣ "ማንኛውም ሰው የማኅበረሰቡ፣ የእካባቢው፣ የባልንጀሮቹ እንዲያው በአጠቃላይ የአስተዳደጉ ውጤት ነው" የሚለው እነጋገራቸው፣ በብዙ መልኩ እውነትነት አለው። እንዲያውም አንዳንዶች ይህን እውነት ቀመስ አባባል ያለልክ በመለጠጥ፣ "ነጢአተኛ የሚባል ለው የለም ነጢአተኛ አስተዳደግ እንጂ" ይሉናል። ማንም ሊክደው በማይችል መንገድ አስተዳደጋችን በሕይወታችን ውስጥ ትልቅ ለውጥ አስከትሏል፤ ማንነታችንን ይቀርጻል—በጥሩም ሆነ በመጥፎ ጐኑ። ግን ይህን እውነት ይዞ፣ ወላጆቹ ላይ ይታይ የነበረ ሥነ ምግባራዊ እክል ነው መርገም ሆኖ እኔ ላይ የዘመተው ማለት በፍጹም ስሕተት ነው።

የዚህ አስተምህሮ ቀማርያን "መተላለፍ" ተብሎ በአማርኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጆች ላይ የተተረጐመውን ቃል፣ (በእንግሊዝኛው *iniquity)* "ክትውልድ የሚተላለፍ እርግማን" ተብሎ መተርጐም ይችላል ባይ ናቸው። ለምሳሌ ወይዘሮ ማርሲን ሄኪ፣ "ነላፊ የማትሆንበት፣ ነገር ግን የወረስኸው እርግማን ሊኖርብህ ይችላል"[42] ይላሉ። እንዲያውም "ነጢአት ተደጋግሞ ከተሠራ ነጢአት ብቻ ሳይሆን መተላለፍ *'iniquity'* በመሆን በዘረ ሐረግ ደም ውስጥ ይዛመታል፤ የወላጆችህ መተላለፍም ወደ እንተ ደምም ዘልቆ ሊሄድ ይችላል"[43] የሚል አስተምህሮ አላቸው።

በርግጥ በአማርኛችን፣ "መተላለፍ" (በእንግሊዝኛው *"iniquity")* ተብሎ የተተረጐመው የዕብራይስጥ ቃል፣ "ወይዘሮዋ

[42] *Break the generational Curse,* ገጽ 15።

[43] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 12 እና 50።

የሚሉትን ዐይነት ትርጉም አለውን?" የሚለውን ጕዳይ፣ ዘለግ አድርገን አንመርምር። በብሉይ ኪዳን ቅዱላት መጻሕፍት፣ ኀጢአት የሚለውን ቃል ለመወከል ሦስት የዕብራይስጥ ቃላት ጥቅም ላይ ውለዋል። አነርሱም፦— "ሀምን/አቮን" (עָוֹן)፣ "ሀታ/ኻታ" (חָטָא) እንዲሁም "ፓሻ" (פֶּשַׁע) ናቸው፡ የመጀመሪያው ቃል ማለትም "አቮን" (עָוֹן) በአንግሊዝኛው በአማርኛ ትርጉሞች ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ፣ "መተላለፍ" ተብሎ ተተርጕሟል (ለምሳሌ የሚከተሉት የእንግሊዝኛ ትርጉሞች "አቮን" የሚለውን የዕብራይስጥ ቃል "መተላለፍ" ማለትም *"iniquity"* ብለው ተርጕመውታል *KJV, ESV, NASV, WEB)*[44]። "ሀምን" በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ 229 ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን፣ ዐቢይ ትርጕሙም ስሕተት ማለት ነው። ተኳሽ ሊመታ ያለበውን ዐላማ ሲለት፣ ጥይቱ ዐላማውን ስቶ/ተላልፎ ሲሄድ፣ አንደ ማለት ነው። ለለዚህ መተላለፍ ማለት ዐላማን ከመለት አንጻር አንጂ፣ ከአንዱ ሰው ወደ ሌላው ሰው መሻገርን/መዛመትን በሚያላይ መልኩ አይደለም የተጠቀሰው (ለምሳሌ የሚከተሉትን ምንባባት ይመለከቷል ዘፍ. *4÷13*፤ *1ሳሙ. 20÷1:8*፤ *25÷24)*።

ሁለተኛው ቃል፣ "ኻታ" (חָטָא) ነው። በብሉይ ኪዳን 595 ጊዜ ግልጋሎት ላይ የዋለ ሲሆን፣ የተጠበቀውን መስፈርት ያለማሚላት፣ ከመስፈርቱ ማጠር/ጕድሎ መገኘት ማለት ነው (ለምሳሌ የሚከተሉትን ምንባባት ይመለከቷል ኢዮ. *5÷24*፤ *2ነገ. 18÷14*፤ ዘፀ. *5÷16)*[45]።

[44] *C. R. Cover, "Sin, Sinners (OT)", The Anchor Bible Dictionary, (Vol. 6 pp. 31-40, 1992), 31.*

[45] ለበለጠ መረጃ የሚከተለውን መጽሐፍ ይመለከቷል— *James Swanson, Dictionary of Biblical Languages With Semantic Domains: Hebrew (Old Testament), electronic ed. (Oak Harbor: Logos Research Systems, Inc., 1997).*

ሦስተኛው ቃል፣ "ፓሻ" (פֶּשַׁע) ሲሆን፣ በብሉያት ቃሉ *135* ጊዜ ያህል ጥቅም ላይ ውሏል። ትርጕሙም ማመፅ፣ አሻፈረኝ ማለት፣ ሕግን ያለመታዘዝ ነው[46]።

እነዚህ ቃላት ኀጢአት የተለያየ ባሕርይ እንዳለው የሚያሳዩን ቢሆኑም እንኳ፣ አንዳችም የትርጕም ልዩነት ላይኖራቸው በተወራራሽነት ግልጋሎት ላይ የዋሉባቸው ቦታዎች ግን አጅግ ብዙ ናቸው (መዝ. *32÷5*፤ ዕብ. *10÷17*፤ ሉቃ. *13÷27)*። የቃላትን አማራጭ ትርጕም ተከትለው የሚሄዱ የአስተምህሮ ቅመራዎች፣ አጅግ ብዙውን ጊዜ ስሕተት ሆነው የሚገኙት በዚህ ምክንያት ነው።

በዘፀአት *20÷5* ላይ "አቮን" (עָוֹן) በአማርኛችን "መተላለፍ" ተብሎ የተተረጕመው ቃል፣ ግልጋሎት ላይ የዋለው፣ ሁለተኛውን ሕግ ያለመታዘዝ፣ ሕጉን ለቶ/አፍርሶ መሄድ በሚለው ትርጕሙ አንጂ ማርሊን ሄክ እንደሚሉት፣ ከወላጅ ወደ ልጅ መዛመትን ለማመልከት አይደለም[47]።

ዘፀአት *20÷5-6* በተመለከተ ልብ ልናደርገው የሚገቡን ቁም ነገሮች አሉ፤ ይኸውም **1.** እርግማን የሚል ቃል በዚህ ቦታ ተጠቅሶ አናገኝም። ከፍሉ ከሦስት እስከ አራት ትውልድ ይተላለፋል የሚለው አርግማንን ላይሆን፣ ጣዖትን በማምለክ አግዚአብሔርን መበደል ነው። **2.** አግዚአብሔር አምላክ በአንክሮ የሚያስጠነቅቀው ጕዳይ፣ ጣዖትን ማምለክ በተከታታይ ትውልዶች ውስጥ ከፍተኛ ተጽእኖ እንደሚያስከትል ነው። **3.** የጣዖት አምልኮው የሚቀጥል ከሆነ፣ የሚያስከትለውም መዘዝ በሦስትና በአራት ትውልድ የሚቆም አይሆንም። **4.** ፍርዱ ይተላለፍባቸዋል የተባሉ ሰዎች፣ ጣዖትን በማምለክ ለአምላክ ያላቸውን ጥላቻ የሚገልጹ ሰዎችን ነው። **5.** አስከ ሦስትና አስከ አራት ትውልድ ይተላለፋል በተባለበትም ዐውደ

[46] ዝኒ. ከማሁ።

[47] ማርሊን ሄክን ጨምሮ ብዙዎቹ የእንቅስቃሴው መምህራን፣ ነገረ መለኮትን ኮሌጅ ንብተው በሥርዐቱ የተማሩ ሰዎች ያለመሆናቸውን ልብ ይሏል።

ምንባብ ውስጥ፣ የአምላክ ምሕረት እስከ ሺህ ትውልድ ይተላለፋል ተብሏል (ሮሜ 5÷20)።

በአዳምም ኀጢአት፣ የለው ልጅ ሁሉ በኀጢአት እንደ ወደቀ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያስተምራል (ኤፌ. 2÷3፤ ሮሜ 5÷12)። በዚህም አግባብ የለው ልጅ ከውልደቱ ጀምሮ ኀጢአተኛ ነው (መዝ. 51÷5፤ ሮሜ 5÷13፤ 7÷9)። ኀጢአት በለው ልጆች ሕይወት ውስጥ የገባው በአዳምና ሔዋን ኀጢአት በኩል፣ ብቻ እንደ ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል (ሮሜ 5÷17-19፤ 1ጢሞ 2÷14፤ 17÷26)። የአዳም ኀጢአት ወደ ለው ሁሉ እንዳለፈ (1ቆሮ. 15:45)፣ በክርስቶስም ቤዛዊ/ወጂዊ ሥራ ቤተ ክርስቲያንም በክርስቶስ ደም ተገዝታለች፣ ታጥባለች፣ ጸድቃለችም (ሐሥ. 20÷28፤ ሮሜ 5÷9፤ 9÷22)።

የመርገም ይተላለፋል አስተምህሮ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግምገማ

ከዚህ በመቀጠል፣ "መርገም ከአናትህ፣ ከአባትህ ... ይተላለፍብሃል" የሚሉ ለዎች፣ አብዝተው የሚጠቅሷቸውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንባባት በቅርበት እንመረምራለን፤ ከፍሎቹ አነሆ:—

> "5. አትስገድላቸው፤ አታምልካቸውም፤ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ (ያህዌ ኤሎሂም) የሚጠሉኝን ልጆች ከአባቶቻቸው ኀጢአት የተነሣ፣ እስከ ሦስትና አራት ትውልድ ድረስ የምቀጣ ቀናተኛ አምላክ (ኤሎሂም) ነኝ፤ 6. ነገር ግን ለሚወዱኝና ትእዛዛቴን ለሚጠብቁ እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ፍቅርን የማሳይ ነኝ" (ዘፀ. 20)።
>
> "9. ስለዚህም አምላክህ እግዚአብሔር (ኤሎሂም ያህዌ) አምላክ (ኤሎሂም) መሆኑን ዕወቅ፤ እርሱ ለሚወዱትና ትእዛዞቹን ለሚጠብቁት የፍቅሩን ኪዳን እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ የሚጠብቅ ታማኝ አምላክ (ኤሎሂም) ነው። 10. ነገር ግን፣ የሚጠሉትን ዐይናቸው እያየ ይበቀላቸዋል፤ የሚጠሉትን ዐይናቸው እያየ ለመበቀል አይዘገይም" (ዘዳ. 7)።

ከሃምሳ ዓመት በፊት የተጻፉ የነገረ መለኮት መጻሕፍት[48]፣ እነዚህን ምንባባት በመጥቀስ መርገም ከቅድመ አያቶቻችን ይተላለፋል፤ ክርስቲያኖች ከዘር ለሚተላለፍ መርገም ለለባ መሆን ይችላሉ የሚል ትምህርት አላስተማሩም። ከላይ ለማየት እንደ ሞከርነው የዚህ አስተምህሮ ቀዳማይ አመንጪ ዴሬክ ፕሪንስ ናቸው። ከሃምሳ ዓመት ወዲህ፣ "የትውልድን መርገም መሰበር" በሚል ርእስ በብዛት አየታተሙ የሚወጡ ጽሑፎች ግን፣ ክርስቲያን በወላጆቹ የዘር ሐረግ መርገም ሥር ሊወድቅ ይችላል ከማለትም ባሻገር፣ ይህን መርገም እንዴት መስበር አንደሚቻል በስፋት የሚያትት ለፊ መድብል አቅርበዋል፤ ቀመር አበጅተዋል።

አስተምህሮዎች ሁሉ ከቅዱሳት መጻሕፍት አንጻር ይመሳከሩ አንዲሁም የትምህርቶቻችን ሁሉ ማዕከል ቅዱስ ቃሉ ብቻ መሆን አለበት የምንል ለዎች፣ እነዚህን ስውር ምንባባት ለመተንተን አእምሮአዊ ስንፍናን ወግድ ማለት የግድ ይኖርብናል። አለያ ግን የሐሰት አስተምህሮ ማራገፊያ ከመሆን በጭራሽ አናመልጥም።

የአበው ኀጢአት

ጣዖትን የማምለክ ኀጢአት፣ እስከ ሦስተኛውና አራተኛው ትውልድ ደረስ መዘዝ ሊኖረው ይችላል፣ የሚለው አሳብ በመጀመሪያ ተጠቅሶ የሚገኘው በዐሥርቱ ትእዛዛት ውስጥ ነው፣ "እኔ እግዚአብሔር አምላክህ (ያህዌ ኤሎሂም) የሚጠሉኝን ልጆች ከአባቶቻቸው ኀጢአት የተነሣ እስከ ሦስትና አራት ትውልድ ድረስ የምቀጣ፣ ቀናተኛ አምላክ (ኤሎሂም) ነኝ" (ዘፀ. 20÷5)። ይህ ክፍል ከእግዚአብሔር ውጪ ያሉ ማናቸውም ዐይነት ጣዖታትን ማምለክ፣ የሚያስከትለው ቅጣት ምን አንደ ሆነ ይናገራል።

[48] ረዘም አድርጌ ገምቼ ነው።

አንዲያውም ከእስራኤላውያን ታሪክ በግልጽ የምንማረው፣ እስራኤል አምላኪ እግዚአብሔርን ትታ ፊቷን ወደ ጣዖት አምልኮ ስታዞር፣ አምላክ የተለያዩ ቅጣቶችን ያመጣባት እንደ ነበር፣ ከመላው የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እንማራለን። በዚህ ቦታ ልብ ልንላቸው የሚገቡ ሦስት መሠረታውያን ጉዳዮች አሉ። ይኸውም አንደኛ፣ እግዚአብሔር በርኅራኄው ታላቅ ስለሆነ ምሕረቱን እስከ ሺህ ትውልድ አንደሚያኖር፤ ሁለተኛ፣ ሲቈጣ ደግሞ ኀጢአትን/መተላለፍን ("አቮን" עָוֹן) እስከ አራት ትውልድ አንደሚቀጣ። ሦስተኛ፣ በዚህ ቦታ "መርገም" ይተላለፈል የሚል አንዳችም ቃል የለም። ከፍሉ ይተላለፋል የሚለው "ኀጢአትን" እንጂ መርገምን አይደለም። አራተኛ፣ ኀጢአት የሚያስከትለው ዳፋ/ውጤት ይከተላችኋል የተባሉት ደግሞ፣ ንስሓ ያልገቡ አንዲሁም ፊታቸውን ከእግዚአብሔር መልሰው ወደ ጣዖታት ዘወር ያደረጉትን ነው። አምላክን መሻትና ንስሓ መግባት የኀጢአት ሥርየት ቢሆንም፣ ይህን ሲያደርጉ ግን አይታይም።

በደብረ ሲና (በሲና ተራራ)፣ እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ኪዳን አንደ ገባ እንመለከታለን። ከዚህም የተነሣ እስራኤል የእግዚአብሔር ሆነች። እስራኤል ይህን ኪዳን የመጠበቅ ሙሉ ኀላፊነት ነበረባት። ነገር ግን አምላኳን በመውደድም ሆነ በመታዘዝ ኪዳኗን መጠበቅ አልቻለችም። ጣዖታትን በማምለክ ኪዳኗን አፈረሰች። ይህ ደግሞ "መንፈላዊ ዝሙት" በሚል ገለጻ ቀርቦ እንመለከታለን። ብዙ መዘዝ አንደሚያስከትልም በተደጋጋሚ ተነግሯል። ነገር ግን እስራኤል በተደጋጋሚ ሰትወድቅ እንመለከታለን። ይህ ኀጢአት ድርጊቱን በፈጸሙት ሰዎች ላይ ብቻ የሚቆም ሳይሆን፣ ልጆቻቸውንም የሚነካ ብርቱ ጉዳይ እንደ ሆነ ተነግሯል።

ይህ ኀጢአት፣ "እስከ ሦስትና አራት ትውልድ የሚተላለፍ" ነው ሲባል ምን ማለት ነው? እንዲያው በግልቡ ሲታይ አምላክ በአባቶች ኀጢአት ምክንያት፣ ልጆቹ ባለደረጉት ኀጢአት እንደሚጠይቃቸው፣ እንደሚቀጣቸው የሚናገር ይመስላል። ዘዳግም

24÷16 ይህን አማራጭ ትንታኔ ግን ይቃወማል፣ "አባቶች ስለ ልጆቻቸው፣ ልጆችም ስለ አባቶቻቸው አይገደሉ፤ አያንዳንዱ በራሱ ኀጢአት ይገደል"።

በርካታ የቅዱሳት መጻሕፍት ሊቃውንት፣ ልጆች ወደ አግዚአብሔር የሚመለሱ ከሆነ፣ ይህን መቅሠፍት ሙሉ ለሙሉ መቀልበስ ይችላሉ የሚል አቋም አላቸው። ምሳሌ ትልቁ የመጽሐፍ ቅዱስ መምህር ጆን ካልቪን፣ ዘፀአት 20÷5 በተመለከተ እንዲህ ይላል:—

> "እግዚአብሔር አምላክ የአባቶችን ኀጢአት ወደ ልጆች ጉያ አመልላለሁ ሲል፣ ድርጊቱን ባልፈጸሙ ልጆች ላይ የአባቶችን ኀጢአት አመጣለሁ ማለቱ አይደለም። ምክንያቱም ልጆች ባላደረጉት ነገር ሊጠየቁ አይገባቸውምና። ነገር ግን እግዚአብሔር በአባቶቻቸውና ከእነርሱ በፊት በነበረው ትውልድ ኀጢአት የሚጠይቃቸው የእነርሱን መንገድ ከተከተሉ ነው"[49]

ልክ አንደ ጆን ካልቪን ሁሉ፣ አሜሪካዊ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ሊቅ ዋልተር ካይዘር እንዲህ ይላሉ:—

> "ልጆች የአባቶቻቸውን ኀጢአት የሚደግሙ ከሆነ፣ እነርሱም እንደ ወላጆቻቸው በግል እግዚአብሔርን የመጥላታቸው ምልክት ነው"[50]

ስለዚህም ፕሮፌሰር ካይዘር፣ "የሚጠሉኝ" የሚለው ሐረግ አባቶችን ብቻ ሳይሆን ልጆችንም አመላካች ነው ባይ ናቸው።

ከዚህ ጋር ተመሳሳይ መልእክት ያለው በትንቢተ ኤርምያስ ላይ የሚገኝ ምንባብ እንዲህ ይላል:—

> 16. አባቶች ስለ ልጆቻቸው፣ ልጆችም ስለ አባቶቻቸው አይገደሉ፤ አያንዳንዱ በራሱ ኀጢአት ይገደል። 17. "አቤት፣ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተ ስማያትንና ምድርን በታላቅ ኀይልህና በተዘረጋች ክንድህ ፈጥረሃል፣ የሚሳንህም አንዳች ነገር የለም።

[49] *John Calvin, Harmony of the Law, Vol. 2, "Exposition of the 2nd Commandment"*
[50] *Walter Kaiser, "Commentary on Exodus" in The Expositors Bible Commentary, Vol. 2 (Zondervan: Grand Rapids, MI.: 1990), 423.*

18. ፍቅርና ቸርነትን ለአልፍ አለላፍ ታሳያለህ፤ ይሁን አንጂ የአባቶችን በደል ከአነርሱ በኋላ በሚነሡ ልጆቻቸው ጦያ ትመልሳለህ፤ ስምህ የለራዊት ጌታ አግዚአብሔር የሆነ፣ ታላቅና ኀያል አምላክ ሆይ፤ 19. ዕቅድህ ታላቅ፣ በሥራም ብርቱ ነህ፣ ዐይኖችህ የሰው ልጆችን መንገዶች ሁሉ ያያሉ፤ ለእያንዳንዱም አንደ መንገዱና አንደ ሥራው ትከፍለዋለህ"።

በአይሁድ የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት የተዘጋጀ አንድ የትርጓሜ ሐተታ፣ "የአባቶችን በደል ከአነርሱ በኋላ በሚነሡ ልጆቻቸው ጦያ ትመልሳለህ" የሚለውን ክፍል በተመለከተ (ኤርምያስ 32÷17-19) አንዲህ ይላል፦—

"የአባቶች ኀጢአት ልጆችን ሊነካ የሚችለው፣ ልጆችም ልክ አንደ አባቶቻቸው በጣያት እምልክ ውስጥ ሊወድቁ ብቻ ነው። ምክንያቱም ቁጥር 16 ሁሉም በራሱ ኀጢአት ተጠያቂ መሆን እንዳለበት አንዲሁም ልጆች በአባቶቻቸው ኀጢአት መወቀስ አንደሌለባቸው ይገልጻል። ከዚህ በተጨማሪ ቁጥር 19፣ 'ለእያንዳንዱም አንደ መንገዱና አንደ ሥራው ትከፍለዋለህ' ማለቱ አባቶችንና ልጆችን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ስለሆነ፣ በአባቶች ኀጢአት ልጆች መጠየቅ የለባቸውም"[51]።

የሚገርመው ደግሞ ከዚህ ምንባብ ጋር ተጓዳኝ ሐሳብ ባላቸው የብሉይ ኪዳን ክፍሎች ላይ ሁሉ ትኩረት የተሰጠው የአግዚአብሔር ቁጣ ሳይሆን፣ የአግዚአብሔር ይቅር ባይነት ነው (ዘኍ. 14÷17-20፤ ዘፀ. 34÷6-7 ፤ 20÷5-6፤ ዮና. 4÷1-2፤ ዘዳ. 7÷9-10፤ 5÷9-10፤ 6÷5)። ቁጣው ከሦስት አስከ አራት፣ ምሕረቱ ግን አስከ ሺህ ትውልድ ይዘልቃል።

"1. ዮናስ ግን ፈጽሞ አልተደሰተም፤ ስለዚህም ተቁጣ። 2. ወደ አግዚአብሔርም አንዲህ ብሎ ጸለየ፤ 'አግዚአብሔር ሆይ፤ በአገሬ ሳለሁ የተናገርሁትስ ይህን አልነበረምን? ፈጥኜ ወደ ተርሴስ

[51] *From— shamash.org/tanach/tanach/commentary/j_seminar/volume4/v4n22 Copyright ©1997 Sephardic Institute.*

ለመኰብለል የተነሣሁትም ለዚህ ነበር፤ አንተ ቸርና ርኅሩኅ፤ ምሕረትህ የበዛ ከቊጣ የራቅህ አምላክ፣ ጥፋትንም ከማምጣት የምትመለስ አንደሆንህ ዐውቃለሁ" (ዮና 4)።

ምሕረቱ ኪዳኑን መሠረት ያደረገ በመሆኑ፣ ይቅርታ የሚገኘው ወደ ኪዳኑ በመግባት፣ መቅሠፍትም የሚመጣው ከኪዳኑ በመራቅ ነው። ከግብፅ የወጡት አይሁድ፣ በጣያት አምልኳቸው ምክንያት በምድረ በዳ ሊቀሩ፣ ልጆቻቸውና የልጅ ልጆቻቸው የተስፋውን ምድር የወረሱት በዚህ አግባብ ነው። ምክንያቱም አግዚአብሔር በአባቶች ኀጢአት ልጆችን አይቀጣምና። የኀጢአት ክፍያ ኀጢአቱን ካደረጉ አባቶች ኀጢአቱን ወዳላደረጉ ልጆች ይተላለፋል ቢባል አንኳ፣ ይህ አውን የሚሆነው ከኪዳኑ ውጪ ባሉና ኪዳኑን ባፈረሱ አንጂ በኪዳኑ ውስጥ ባሉት ላይ በጭራሽ አይደለም[52]።

አበው የበሉት ፍሬ የልጆችን ጥርስ አጠረሰ!

2. "ስለ አስራኤል ምድር፣ 'አባቶች ጮምዛዛ የወይን ፍሬ በሉ፤ የልጆችንም ጥርስ አጠረሰ' አያላችሁ የምትመስሉት ተምሳሌት ምን ለማለት ነው? 3. 'በሕያውነቴ አምላለሁ ይላል ልዑል አግዚአብሔር፤ ከአንግዲህ ይህን ምሳሌ በአስራኤል ምድር አትመስሉም። 4. እነሆ ነፍስ ሁሉ የአኔ ናት፤ የአባት ነፍስ የአኔ አንደ ሆነች ሁሉ የልጁም ነፍስ የአኔ ናት፤ ኀጢአት የምትሠራ ነፍስ አርሷ ትሞታለች" (ሕዝ 18)።

በአስራኤል ታሪክ ውስጥ፣ አግዚአብሔር ፍትሓዊ ባልሆነ መልኩ በአባቶች ኀጢአት ልጆችን ይቀጣል፣ የሚለው አስተሳሰብ በብዙዎች ዘንድ አንደ ነበር እንመለከታለን። በሕዝቅኤል ዘመን የነበሩ ለምች ያን ዐይነት አስተያየት አንዲያድርባቸው ምክንያት የሆኑ ነገሮች አሉ። ይኸውም ይህ ትውልድ በባቢሎናውያን ምርኮ የተጋዘ ትውልድ ነው። ይህ ግዞት እንደሚሆን በተለያየ ጊዜ

[52] ዝኒ ከማሁ።

የተለያዩ ነቢያት ተናግረዋል። ከዚህም የተነሣ ብዙ ትውልድ በጣዖት አምልኮ ውስጥ ኖሯል። "ከዚህም የተነሣ አዲሱ ትውልድ እኛ ይህ ዕጣ ፈንታ የደረሰብን፣ በአባቶቻችን ኀጢአት ነው የሚል አቋም ነበረው"[53]።

ይህ ግን ስሕተት እንደ ሆነ ሕዝቅኤል በግልጽ ይናገራል፦—

"19. 'እናንተ ግን፣ 'ልጅ ስለ አባቱ ኀጢአት ለምን አይቀጣም?' ትላላችሁ። ልጁ ቀናና ትክክለኛውን ነገር ስላደረገ፣ ሥርዐቴንም ሁሉ በጥንቃቄ ስለ ጠበቀ በሕይወት ይኖራል። 20. መሞት የሚገባት ኀጢአት የሠራችው ነፍስ ናት። ልጅ በአባቱ ኀጢአት አይቀጣም፣ አባትም በልጁ ኀጢአት አይቀጣም። ጻድቁ የጽድቁን ፍሬ ያገኛል፣ ኀጢአተኛውም የኀጢአቱን ዋጋ ይቀበላል። 21. 'ኀጢአተኛ ከሠራው ኀጢአት ሁሉ ተመልሶ ሥርዐቴን ሁሉ ቢጠብቅ፣ ቀናና ትክክለኛውን ነገር ቢያደርግ ፈጽሞ በሕይወት ይኖራል እንጂ አይሞትም። 22. በደሉ ሁሉ አይታሰብበትም፣ በጽድቅ መንገድ ሄዶአልና በሕይወት ይኖራል። 23. በውኑ ኀጢአተኛ ሲሞት ደስ ይሰኛልን? ይላል ጌታ እግዚአብሔር። ይልቁን ከመንገዱ ተመልሶ በሕይወት ሲኖር ደስ አይለኝምን?"

(ሕዝ 18)።

ይህ የሕዝቅኤል ክፍል፣ ምንም እንኳ በአባቶቻቸው ኀጢአት ምክንያት ወደ ግዞት ቢወርዱም፣ በእውነተኛ ንስሓ የሚመለሱ ሰዎች በግዞት ምድር እንኳ፣ የአምላካቸው ቅሬታዎች/ትሩፋን መሆን እንደሚችሉ ይገልጻል።

በግዞት ምድር ለአምላካቸው ትሩፋን ከሆኑ ጻድቃን መኻል ዳንኤል አንዱ ምሳሌ ነው። ዳንኤል፣ "አባት የበላው ፍሬ የልጅ ጥርስ አጠረሰ" ከሚለው አስተሳሰብ ጋር የሚቃረን ሐሳብ እንደ ነበረው የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከታል፦—

[53] *Ralph Alexander, "Commentary on Ezekiel" in The Expositors Bible Commentary, Vol. 6 (Zondervan: Grand Rapids, MI.: 1986), 823.*

"1. የሜዶናዊው የአርጤክስስ ልጅ ዳርዮስ በባቢሎን በነገሠ በመጀመሪያው ዓመት፣ 2. በዘመነ መንግሥቱ በመጀመሪያው ዓመት፣ እኔ ዳንኤል ለነቢዩ ለኤርምያስ በተሰጠው የእግዚአብሔር ቃል መሠረት፣ የኢየሩሳሌም መፈራረስ ለባ ዓመት እንደሚቈይ ከቅዱሳት መጻሕፍት አስተዋልሁ። 3. በለዚህ ማቅ ለብሼ፣ በራሴም ላይ ዐመድ ነስንሼ፣ በጾምና በጸሎት፣ በምልጃም ፊቴን ወደ ጌታ አምላክ አቀናሁ። 4. ወደ አምላኬ ወደ እግዚአብሔር እንዲህ ብዬ ጸለይሁ፣ ተናዘዝሁም፣ 'ከሚወዱህና ትእዛዝህን ከሚፈጽሙ ሁሉ ጋር የፍቅር ቃል ኪዳንህን የምትጠብቅ፣ ታላቅና የተፈራህ አምላክ፣ ጌታ ሆይ፣ 5. እኛ ኀጢአት ሠርተናል፣ በድለናልም፣ ክፋትን አድርገናል፣ ዐምፀናልም፣ ከትእዛዝህና ከሕግህ ዘወር ብለናል። 6. ለንጉሦቻችን፣ ለልዑሎቻችንና ለአባቶቻችን እንዲሁም ለምድሪቱ ሕዝብ ሁሉ በአንተ ስም የተናገሩትን አገልጋዮችህን ነቢያትን አልሰማንም።

7. 'ጌታ ሆይ፣ አንተ ጻድቅ ነህ፣ ነገር ግን ለአንተ ታማኞች ባለመሆናችን እኛን በበተንህባቸው አገሮች ሁሉ የምንገኝ የይሁዳ ሰዎች፣ የኢየሩሳሌምና የመላው እስራኤል ሕዝብ፣ በሩቅም ሆነ በቅርብ ያለን በዚህ ቀን በኀፍረት ተከናንበናል። 8. እግዚአብሔር ሆይ፣ እኛና ንጉሦቻችን፣ ልዑሎቻችንና አባቶቻችን በአንተ ላይ ኀጢአት ስለ ሠራን በኀፍረት ተከናንበናል። 9. ምንም እንኳ በእርሱ ላይ ያመፅን ብንሆን፣ ጌታ አምላካችን ይቅር ባይና መሐሪ ነው። 10. እግዚአብሔር አምላካችንን አልታዘዝንውም፣ ደግሞም በአገልጋዮቹ በነቢያት በኩል የሰጠንን ሕግ አልጠበቅንም፣ 11. መላው እስራኤል አንተን ባለመታዘዝ ሕግህን ተላልፎአል፣ ዘወርም ብሎአል። 'በአንተ ላይ ኀጢአትን ስለ ሠራን፣ በእግዚአብሔር አገልጋይ በሙሴ ሕግ የተጻፈው መሐላና ርግማን ፈሰሰብን። 12. ታላቅ ጥፋት በእኛ ላይ በማምጣት፣ በእኛና በገዦቻችን ላይ የተነገረውን ቃል ፈጸምህብን፣ በኢየሩሳሌም ላይ የተደረገውን የሚያህል ከሰማይ በታች ከቶ የለም።

13. በሙሴም ሕግ አንደ ተጻፈው፣ ይህ ሁሉ ጥፋት በእኛ ላይ ደረሰ፣ ሆኖም ክኀጢአታችን በመመለስና እውነትህን በመከተል ከአምላካችን ከእግዚአብሔር ምሕረትን አልፈለግንም 14. አምላካችን እግዚአብሔር በሚያደርገው ሁሉ ጻድቅ ነውና፣ በእኛ ላይ እግዚአብሔር ጥፋት ከማምጣት አልተመለሰም፤ እኛም አልታዘዝነውም።

15. 'አሁንም ሕዝብህን ከግብፅ ምድር በብርቱ እጅ ያወጣህ፣ እስከዚህም ቀን ድረስ ስምህ እንዲታወቅ ያደረግህ፣ ጌታ አምላካችን ሆይ፤ እኛ ኀጢአትን ሠርተናል፤ አንተንም በድለናል። 16. ጌታ ሆይ፤ ቀድሞ እንዳደረግኸው የጽድቅ ሥራህ ሁሉ፣ ከከተማህ ከኢየሩሳሌም፣ ከቅዱስም ተራራህ ቍጣህን መልስ፤ በእኛ ኀጢአትና በአባቶቻችን በደል ምክንያት ኢየሩሳሌምና ሕዝብህ በዙሪያችን ባሉት ዘንድ መሣለቂያ ሆነዋል።

17. 'አሁንም አምላካችን ሆይ፣ የአገልጋይህን ጸሎትና ልመና ስማ። ጌታ ሆይ፤ ስለ ስምህ ስትል ፊትህን ወደ ፈረሰው መቅደስ መልስ። 18. አምላክ ሆይ፤ ጆሮህን አዘንብለህ ስማ፤ ዐይንህን ገልጠህ መጥፋታችንንና ስምህ የተጠራበትን ከተማ ተመልከት። ልመናችንን የምናቀርበው ስለ ጽድቃችን ሳይሆን፣ ስለ ታላቅ ምሕረትህ ነው። 19. ጌታ ሆይ፤ አድምጥ! ጌታ ሆይ፤ ይቅር በል! ጌታ ሆይ፤ ስማ! አድርግም፤ ስምህ በከተማህና በሕዝብህ ላይ ተጠርቶአልና አምላኬ ሆይ፤ ስለ ስምህ ስትል አትዘግይ"

(ዳን. 9)።

ትንቢተ ዳንኤል ከአምላክ ጋር ሊኖረን ስለሚገባው ኪዳናዊ ግንኙነት፣ ትልልቅ ቍም ነገሮችን ይናገራል። አሰራኤል ወደ ባቢሎን የመጋዟ ምስጢር፣ ለረጅም ዓመታት በጣዖት አምልኮና በዐመፅ ውስጥ የመኖሯ ውጤት ነው። ምንም እንኳ በአባቶቻቸው ኀጢአት በግዞት ቢወድቁም በግዞት በተወለዱበት ምድር እንኳ፣ ኪዳናቸውን ለሚጠብቁ ቅሬታዎች/ትሩፋኖች፣ እግዚአብሔር ቸር እንደ ነበር፣ ከነዳንኤል ሕይወት ማየት እንችላለን።

30. 'ልጆቹ ሕጌን ቢተዉ፣ ደንቤን ባይጠብቁ፣ 31. ሥርዐቴን ቢጥሱ፣ ትእዛዜንም ባያከብሩ፣ 32. ኀጢአታቸውን በበትር፣ በደላቸውን በጅራፍ እቀጣለሁ። 33. ምሕረቴን ግን ከእርሱ አላርቅም፤ ታማኝነቴንም አላጓድልበትም። 34. ኪዳኔን አላፈርስም፣ ከአፌ የወጣውንም አላጥፍም። 35. አንድ ጊዜ በቅድስናዬ ምያለሁና፣ ዳዊትን አልዋሸውም" (መዝ. 89)።

እግዚአብሔር ለዳዊት፣ አንዳች ቅድመ ሁኔታ የሌለባትን ኪዳን አቀሞለል። ይኸውም ከእርሱ ዘር ዘላለማዊ የሆነ ንግሥና እንደሚያቆም—ንጉሥ ከዘሩ እንደማይጠፋ (ለምሳሌ የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል— 2ሳሙ 7÷13-14፤ ኢላ. 9÷7፤ ኤር. 33÷15-21)።

ሐዲስ ኪዳን

የአባቶች ኀጢአት፣ "ሦስትና አራት ትውልድ" ይተላለፋል የሚለው ብሉይ ኪዳን ትምህርት የተነገረው፣ የእግዚአብሔር ምሕረት "ለአንድ ሺህ ትውልድ" ይዘልቃል በሚለው ዐውድ ውስጥ ነው። ይኸውም የአግዚአብሔር "አንድ ሺህ ትውልድ" ምሕረት፣ በኪዳኑ ውስጥ ታማኝ ሆኖ መኖርን እንዲሁም ኀጢአት አሉታዊ ውጤት እንደሚያስከትል፣ ቅድመ ሁኔታ ሆኖ በቀረበበት ዐውደ ምንባብ ውስጥ ነው። የአውነተኛ በረከት መሠረቱ፣ ከእግዚአብሔር ጋር በኪዳን መጋመድ/መጣመር ነው። እንደ ሐዲስ ኪዳን ትምህርት፣ ይህ እውን መሆን የሚችለው ደግሞ፣ ክርስቶስ ኢየሱስን አንደ ግል አዳኝ አድርጎ በመቀበል፣ በእርሱ ቤዛዊ/ወጇዊ ሥራ በፍጹም ልብ በማመን ነው።

ክርስቶስ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኙ የተቀበለ ሰው፣ በምንም ዐይነት መልኩ፣ በወላጆቹ መርገም ሥር ሊወድቅ አይችልም።

6. አስተ አብርሃምን አስቡ፤ 'አርሱ አግዚአብሔርን አመነ፣ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት።' 7. አንግዲህ እነዚያ የሚያምኑት የአብርሃም ልጆች እንደሆኑ አስተውሉ። 8. መጽሐፍ፣ አግዚአብሔር አሕዛብን በአምነት እንደሚያጸድቅ አስቀድሞ በማየት፣ 'አሕዛብ ሁሉ በአንተ ይባረካሉ' በማለት ወንጌልን

ለአብርሃም አስቀድሞ አስታወቀው። 9. ስለዚህ በእምነት የሆኑት፣ የእምነት ለው ከሆነው ከአብርሃም ጋር ቡሩካን ናቸው" (ገላ. 3)።

እሕዛብ፣ በአብርሃም ዘላለማዊ ኪዳኑ ውስጥ መግባት የቻሉት በክርስቶስ ቤዛዊ ሥራ በማመናቸው እንደ ሆነ ሐዋርያው ጳውሎስ ብሉያትን ጠቅሶ ይሞግታል፦—

"13. 'በዕንጨት ላይ የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው' ተብሎ ስለ ተጻፈ፣ ክርስቶስ ስለ እኛ ርግማን ሆኖ ከሕግ ርግማን ዋጅቶናል፤ 14. ለአብርሃም የተሰጠው በረከት፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ለአሕዛብ እንዲደርስ ዋጅቶናል፤ ይኸውም በእምነት የመንፈስን ተስፋ እንድንቀበል ነው" (ገላ. 3)።

"3. የሚባርኩህን እባርካለሁ፣ የሚረግሙህን እረግማለሁ፣ በምድር የሚኖሩ ሕዝቦች፣ በአንተ አማካይነት ይባረካሉ'" (ዘፍ. 12)።

እንዲያውም ሐዲስ ኪዳን በረከት፣ በዘር ሳይሆን በአምነት በሚቆም ኪዳን እንደሚገኝ በግልጽ ያስረዳል፦—

"9. 'አብርሃም አባት አለን' በማለት ራሳችሁን አታታሉ፤ እግዚአብሔር ከእነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆች ሊያስነሣ ይችላል እላችኋለሁና" (ማቴ. 3 እንዲሁም የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከታል— ገላ. 3÷22፤ 4÷20÷ ዘፍ. 18÷18፤ 22÷18፤ 26÷4፤ ኤር. 4÷2፤ ሮሜ 3÷28-30፤ 9÷17፤ ዮሐ. 7÷38-42፤ 19÷37)።

የትውልዳችሁ መርገም በክርስቲያኖች ላይ አውን መሆን ይችላል የሚሉ ሰዎች፣ መርገምን ለመለበር በክርስቶስ ኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ ማመን ብቻ በቂ አይደለም ማለታቸው እንደ ሆነ ልብ ልናደርገው ይገባል። በገላትያና በቈላስይስ አብያተ ክርስቲያናት ታያቶ የነበረው ኑፋቄ፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ማመን በጣም ጥሩ ነገር ነው፤ ነገር ግን ብቻውን በቂ አይደለም የሚል ነበር። ልዩ የሆነ ዕውቀት ወይም ደግሞ ሃይማኖታዊ ልምምድ ካልታከለበት (ካልተጨመረበት) በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ማመን ብቻ ፋይዳ የለውም ወይም ሙሉውን የድነት በረከት አያስገኝም ባዮች ነበሩ።

ዘፀአት 20÷4-5 በመጥቀስ፣ "ከትውልዳችሁ መርገም ሥር ናችሁ" የሚሉን ሰዎች በሌላ መንገድ በክርስቶስ ቤዛዊ/ወጂዊ ሥራ

ማመናችሁ ብቻ በቂ እይደለም እያሉን ነው[54]። እንዲያው ጌታ ያልሰበረውን መርገም የትኛው የሰብእውያን ቀመር ወይም የትኛው ጾግና ሊሰብረው ይችላል? እንስበርላችሁ የሚሉስ ሰዎች፣ የእኛን እነርሱ ይሰብሩልናል ግን የእነርሱን መርገም የሰበረላቸው ማን ይሆን?

የዚህ ትምህርት እስተማሪዎች መርገምን የሚያመጣው ለይጣን ነው ባዮች ናቸው[55]። ነገር ግን ዘፀአት 20÷4-5 ላይ ያለው እንዲሁም ተዛማጅ ምንባባት መርገም የሚያመጣው ከሰይጣን ነው አይሉም። በምንባባቱም ዐውድ ውስጥ፣ ለይጣንም ሆነ አጋንንት በስም አልተጠቀሱም። ኪዳናቸውን የሚያፈርሱትን ሰዎች የሚቀጣው ራሱ እግዚአብሔር ነው። ምክንያቱም የሕጉ እጋጊም (ደንጋጊም) ሆነ የሕጉ አስጠባቂ ራሱ እግዚአብሔር ነውና (ሕጉን የሚያስከብር የሕጉ ባለቤት ነው)።

በተጨማሪም ክርስቶስን በማመናችን ከሥልጣናት፣ ከኀይላት፣ ከገዢዎች ወዙተ ቍጥጥር ውጪ እንደሆንን መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይናገራል።

"10. እናንተም የገዥነትና የሥልጣን ሁሉ ራስ በሆነው በክርስቶስ ሙሉ ሆናችኋል" (ቈላ. 2)።

እንደ ማርሊን ሄክ ያሉ የእንቅስቃሴው መምህራን፣ ዐሥራት ያለመስጠት ራሱ መርገም እንደሚያመጣ ይገልጻሉ፤ ለዚህ አሳብ ማስደገፊያ አድርገው የሚጠቅሱት ሚልክያስ 3÷9 ነው። በአሮጌው ኪዳን፣ የአምልኮ ሕግ በመባል የሚታወቁትን አነዚህን ትእዛዛት መተላለፍ መርገም የሚያስከትል ከሆነ፣ በአምልኮ ሥርዐተ

---

54 ዴሬክ ፕሪንስ፣ *በረከት ወይስ መርገም አንዱን ምረጥ—የጭንቀት ሕይወት ከመመራት የመገላገያው ዘዴ*፤ (የማነብርሃን እንዳለ፤ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ፤ 1989 ዓ.ም)። *Neil T. Anderson, The Bondage Breaker, (Harvest House: Eugene, Or.: 1990).*

55 ዴሬክ ፕሪንስ፣ *በረከት ወይስ መርገም አንዱን ምረጥ—የጭንቀት ሕይወት ከመመራት የመገላገያው ዘዴ*፤ (የማነብርሃን እንዳለ፤ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ፤ 1989 ዓ.ም)፤ ገጽ 61-63። *Marilyn Hickey, Break the Generation Curse, (Denver: Marilyn Hickey Ministries, 1988).*

ሕግ የተዘረዘሩትን 613 ሕጎች ያስማክበራችንም በመርገም ውስጥ ይከተናል ማለት ነው፤ ምክንያቱም ዐሥራት ከእነዚህ 613 ሕግጋት አንዱ ሕግ ነውና[56]።

ልጆች የወላጆቻቸውን መጥፎ ጠባይ ሊወርስ እንደሚችሉ ይታወቃል። በአንጻሩ ልጆች ከወላጆቻቸው የተለያዩ ዐይነት በሽታዎች ሊተላልፉባቸው እንደሚችሉ ግልጽ ነው (ለምሳሌ፦ የስኳር በሽታ፣ ኤች.አይ.ቪ.)። በአንጻሩ ደግሞ ወላጆች ልጆች ከወላጆቻቸው ጥሩ ጠባይም ሆነ ውብ ተክለ ሰውነት ይወርሳሉ። ይህን ጉዳይ መርገም ይተካሰፋል ከሚለው ጋር ስማመሳሰል ምንም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃ አናገኝም[57]።

ማጠቃለያ

ማጅራት መቺዎችና ኪስ አውላቂዎች፣ ዐላማቸውን ከዳር ለማድረስ ተገን የሚያደርጉት አሳቻ ቦታዎችን፣ ግራ አጋቢ ሁኔታዎችንና ስዎች በቀላሉ የሚዘናጉባቸውን ወቅቶች ነው። የአባይ ነባዮችም ሆነ የመናፍቃን አካሄድ የዚህ ግጣም ነው—አንዳችም ልዩነት የለውም።

ሕዝበ ክርስቲያኑ ቅዱሳት መጻሕፍት የአምላክ አፈጮተ ቃል ናቸው፣ የአስተምህሮአችንም ሆነ የሥነ ምግባራችን መልህቅ ናቸው የሚል አምነት አለው—በዝርዝር ጉዳዮች ላይ ያለው አቋም በደምሳሳው የሚታይ ቢሆንም። ከዚህም የተነሣ ትምህርቶችንም ሆነ አካሄዶችን፣ በቅዱስ ቃሉ መመዘን አማራጭ የሌለው አካሄድ ነው የሚል መግባባት፣ በክርስቲያኑ ማኅበረሰብ ዘንድ አለ። ይህ ቋሚና ነባር አካሄድ፣ ለመናፍቃኑም ሆነ ለአባይ ነባዮቹ አንበዛም አክል አይፈጥርባቸውም። ለዚህ ማነቁ ሁነኛ የመሸሸጊያ ብልጎት

[56] የተለያዩ ድረ ገጾች የእነዚህን 613 ሕጎች ዝርዝር ይገልጻሉ፣ ይመለከቷቸው።

[57] ከላይ፣ መርገምና ከወላጅ የሚተላለፉ በሽታዎች በሚል ርእስ ያነሣናቸውን ነጥቦች ይመለከታል።

አበጅተውለታልና፣ በዚህም ጥበባቸው ብዙ ባይተዋር ትምህርቶችን አስርገው ማስገባት ችለዋልና። እነዚህ የማሸሸጊያ አካሄዶች የሚከተሉት ናቸው፦—

- ቅዱሳት መጻሕፍት ከአኛ ትምህርት አንጻር አየተገናዘቡ ይተርጐሙ፣
- ቅዱሳት መጻሕፍት በአኛ የሥነ ትርጓሜ መርሖ አንጻር ይተንተኑ፣
- እጅግ ስውርና ለመተርጐም አስቸጋሪ የሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባትን የአስተምህሮአችን መሠረት አድርገን አንገሰገልባቸዋለን።

አባይ ነባዮችም ሆኑ መናፍቃን፣ እነዚህን ሦስት አካሄዶች እንደ አስፈላጊነቱና እንደ አዋጭነቱ አቀላቅለው ይጠቀሙባቸዋል። ቅዱሳት መጻሕፍትን ከአናት ቋንቋቸው ማስትም ከበኩረ ጽሑፉ በቀጥታ ተርጕመን ነገር ግን ከአኛ አስተምህሮ ጋር አስማምተን/አዋድደን አናቅርብላችሁ የሚለው አካሄድ ጠንካራ የገንዘብ ዐቅም ይፈልጋል። ገንዘብ ያስፈለገው፣ የትርጕሙን ሥራ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ለመከወን ሳይሆን፣ መጽሐፍ ቅዱስን ከራሳቸው አስተምህሮ አንጻር አያደላደሉ ለመተርጐም እንዲሁም ትርጕማቸው በሕዝቡ ዘንድ ተቀባይነት አንዲያገኝ ማስቻል ብዙ ድካም የሚፈልግ ነው። ዐቅማቸው የፈቀደላቸው ግን ይህን ማድረግ ችለዋል። ለምሳሌ፣ "የይሖዋ ምስክሮች" መጽሐፍ ቅዱስን ከራሳቸው አስተምህሮ ጋር አንዲታረቅ አድርገው ተርጕመውታል[58]—በአማርኛ ቋንቋ ያዘጋጁት መጽሐፍ፣ "የአዲስ

[58] እንዲያውም አሁን አንደ *NIV* ያሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጕሞች "ሰይጣናዊ ናቸው"፣ "ግብረ ሰዶማውያን የዘጋጇቸው ናቸው"፣ "የነው ኤጅ ተከታዮች የተሳተፉባቸው ናቸው" ወዘተ የሚል አሉባልታ በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ተከታዮች መኻል እያናፈሱ ነው። ክርስቲያኑ ማኅበረሰብ ግን ይህን በውል ሳይረዳ፣ አሉባልታውን በማኅበራዊ መገናኛ ብዙኃን ላይ እየነዛው ይገኛል። የሚገርመው ግን በመጽሐፍ ቅዱስ የትርጕም ዝግጅት ታሪክ፣ እንደ *NIV* ከመቶ ያላነሱ ሊቃውንት የተካፈሉበት እንዲሁም እጅግ ስመ ጥር ምሁራን የተካተቱበት የትርጕም መጽሐፍ

ዓለም ትርጉም" በመባል ይታወቃል። በአሁኑ ጊዜ ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በኢትዮጵያ ውስጥ በስፋት እየተሠራጨ ይገኛል። ሁለተኛውና ሦስተኛው እካሄድ ግን፣ ብልጣብልጥነትን እንጂ፣ የገንዘብ ዐቅም አይፈልግም።

የተሳሳተ የሥነ ትርጓሜ እካሄድ መከተል፣ በሁሉም እባይ ነባዮችና መናፍቃን ላይ የሚታይ ቋሚ ችግር ነው። ከዚህ በተጨማሪ፣ እስተምህሮአቸውን ግልጽ ባልሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት ላይ ማስደገፍ ተመራጭ እቀራረባቸው ነው። ይህ ምዕራፍ ትኩረት ያደረገበት ርእስ፣ ለመረዳት አዳጋች የሆኑና በርካታ የትርጓሜ እማራጭ ያላቸውን ክፍሎች በመጠቀም፣ ለምች ባይተዋር ትምህርታቸውን እንዴት አድርገው በሕዝቡ ልብ እንደሚያሠርጹ የሚያሳይ ነው።

የእምነት እንቅስቃሴንና እንዳንድ "የዐርነት" አገልግሎት እናገለግላለን የሚሉ ለምች፣ ስውር ምንባባትን አብዝቶ የመጠቀም ልማድ እላቸው። በተለይ አሻሚ ከመሆናቸው የተነሣ በርካታ የትርጓሜ እማራጭ የሚቀርብላቸው ክፍሎች፣ በዚህ ረገድ እጅግ ተወዳጅ ሆነውላቸዋል[59]። ምክንያቱም እነዚህ ምንባባት፣ እስተምህሮአቸው እርቃኑ እንዳይታይ፣ ነፍረት መሸፈኛ ሆነውላቸዋልና፣ ሥነ ምግባራቸው እንዳይጋለጥ ይጋርዱላቸዋልና። ማንም ተነሥቶ፣ "ትምህርታችሁም ሆነ አኗኗናችሁ እንደ ቃሉ እይደለም" የሚለውን ከስ ቢያቀርብ፣ "ከቃሉ አልራቅንም እንዲያውም ቃሉን በጥልቀት ያመሳከረ ሕያወት አለን" የሚሉት፣

እንደ ሌለ በአካዳሚ ጆርናሎች ላይ እየተነገረ ነው። በዚህ አጋጣሚ ክርስቲያኑ ማኅበረሰብ የአንዳንድ አሉባልታዎችን ምንጭ ምን እንደ ሆነ መመርመር፣ የቤተ ክርስቲያን አስተማሪዎችን መጠየቅ፣ እንዲሁም የሚባለው አሉባልታ ምን ያህል እውነት ነው የሚለውን ጉዳይ በትርበት መመርመርን ወይም ማስመርመርን መልመድ እንዳለበት መግለጽ እወዳለሁ።

[59] ይህን ስል ግን አንዳንድ ሰዎች በዚህ ዐይነቱ ትምህርት ውስጥ የገቡት ሆነ ብለው ሳይሆን፣ እነርሱ ራሳቸው ተሳስተው እንደ ሆነ መግለጽ እፈልጋለሁ—በዚህ ረገድ እኔ ራሴ የማውቃቸው በርካታ ገጠመኞች አሉኝና።

እነዚህን ስውር ምንባባት፣ ከወዲህ ከወዲያ እያጠናበሩ በመጥቀስ ነው።

በርካታ ለምች እነዚህን የኑፋቄ ማራገፊያ ከፍሎች በጥልቀት ለለማይመረምሩ፣ ስሕተቱን ፊት ለፊት የመቃወም ኀይል አይኖራቸውም። ከበረታም እነርሱ ራሳቸው ኑፋቄውን ታቅፈው ይኖራሉ።

እባክዎን የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት በጥሙና ያንብቧቸው፦—

> "16. ስለዚህ ከአሁን ጀምሮ ማንንም በውጫዊ ነገር አንመዝንም፣ ከዚህ ቀደም ክርስቶስን በዚህ መልክ መዝነነው ነበር፣ ከእንግዲህ ግን እንደዚህ አናደርግም። 17. ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፣ አሮጌው ነገር አልፎአል፣ እነሆ፣ አዲስ ሆኖአል። 18. ይህ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው፣ እርሱ በክርስቶስ አማካይነት ከራሱ ጋር አስታረቀን፣ የማስታረቅንም አገልግሎት ሰጠን፣ 19. እግዚአብሔር በክርስቶስ ዓለምን ከራሱ ጋር ሲያስታርቅ የሰዎችን በደል አይቈጥርባቸውም ነበር፣ ለእኛም ደግሞ የማስታረቅ ቃል ሰጠን" (2ቆሮ 5)።
>
> "1. ስለዚህ በክርስቶስ ኢየሱስ ያሉት አሁን ኵነኔ የለባቸውም፣ 2. ምክንያቱም የሕይወት መንፈስ ሕግ በክርስቶስ ኢየሱስ ኵነኒትና ከሞት ሕግ ነጻ አውጥቶአችኋል" (ሮሜ 8)።
>
> "13. ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን"
>
> (ገላ. 2)
>
> "15. ነገር ግን ስጦታው እንደ በደሉ መጠን አይደለም፣ በአንድ ሰው መተላለፍ ብዙዎቹ ከሞቱ፣ የእግዚአብሔር ጸጋና በአንዱ ሰው፣ ይኸውም በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የመጣው ስጦታ ለብዙዎች እንዴት አብልጦ ይትረፈረፍ! 16. ደግሞም የእግዚአብሔር ስጦታ አንደ አንዱ ሰው የኀጢአት ውጤት አይደለም፣ ምክንያቱም ፍርዱ የአንድን ሰው ኀጢአት ተከትሎ ኵነኔን አመጣ፣ ስጦታው ግን አያሌ መተላለፍን ተከትሎ ጽድቅን አመጣ (ሮሜ 5)።

9. እናንተ ግን፣ የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጣችሁ የሚኖር ከሆነ፣ በሥጋ ሳይሆን በመንፈስ ናችሁ። ማንም የክርስቶስ መንፈስ ከሌለው፣ እርሱ የክርስቶስ አይደለም። 10. ነገር ግን ክርስቶስ በውስጣችሁ ካለ፣ ሰውነታችሁ ከኀጢአት የተነሣ የሞተ ቢሆንም፣ መንፈሳችሁ ከጽድቅ የተነሣ ሕያው ነው። 11. ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው የእርሱ መንፈስ በእናንተ የሚኖር ከሆነ፣ ክርስቶስን ከሙታን ያስነሣው፣ በውስጣችሁ በሚኖረው በመንፈሱ ሟች ሰውነታችሁ ሕይወትን ይስጣል" (ሮሜ 8)።

"31. ታዲያ ስለዚህ ምን እንመልሳለን? እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ፣ ማን ሊቃወመን ይችላል? 32. ስገዛ ልጁ ያልሳሳለት፣ ነገር ግን ስሁላችንም አሳልፎ የሰወው እርሱ፣ ሁሉንስ ነገር ከእርሱ ጋር እንደ ምን በልግስና አይሰጠን? 33. እግዚአብሔር የመረጣቸውን የሚከስ ማን ነው? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው፤ 34. ታዲያ የሚኰንን ማን ነው? የሞተው፣ እንዲሁም ከሞት የተነሣው፣ በእግዚአብሔር ቀኝ የተቀመጠው ክርስቶስ ኢየሱስ፣ ስለ እኛ ይማልዳል። 35. ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየን ማን ነው? ችግር ነው ወይስ ሥቃይ፣ ወይስ ስደት፣ ወይስ ረሀብ፣ ወይስ ዕራቍትነት፣ ወይስ አደጋ ወይስ ሰይፍ?" (ሮሜ 8)።

"30. በክርስቶስ ኢየሱስ ስመሆን የበቃችሁት ከእርሱ የተነሣ ነው፤ እርሱ ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበባችን፣ ጽድቃችንና ቅድስናችን፣ ቤዛችንም ሆኖአል። 31. እንግዲህ፣ እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ ነው፤ "የሚመካ በጌታ ይመካ'" (1ቆሮ 1)።

አባሪ

ክርስትና ለጤንነትና ለሀብት ዋስትና አልሰጠም!

ከጌታ ጋር ስረጅም ዓመት የኖረች እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በትጋት አምላኪን የምታገለግል ክርስቲያን እኅት፣ "ክርስቲያን ቱጃር መሆን አለበት" የሚሰውን ስብከት ከመጥገቢ የተነሣ፣ "የሚሸተን ዶሮ ወጥ ነው፤ ሽሮ እንኳ በወጉ እያገኘን ግን አይደለም" የሚለው ንግግሯ ትዝ ይለኛል።

ዶሮ ወጥ ያሸተቱን የዘመኑ የዶሮ ወጥ ስባኪዎች እንጂ፣ ቅዱሳት መጸሕፍት አይደሉም። መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ምድር ዐልጋ በዐልጋ የሆነ ሕይወት ይገጥማችኋል የሚል ዋስትና አልሰጠንም። ባይሆን አምላካችን እግዚአብሔር፣ "ሰሽሮ" በማይመጥን ሕይወት ውስጥ፣ "ዶሮ ወጥ" ከሚስጠን ደስታና ፍሥሓ የተሻለ ሐሴት በመንፈስ ቅዱስ እንደሚያጐናጽፈን፣ ሰላማችን የተትረፈረፈ እንደሚሆን ቃል ኪዳን ሰጥቶናል።

በተመሳሳይ መንገድ፣ አንድ ወዳጄ ማቴዎስ 4÷23፤ 9÷35 ጠቅሶ ሁሉም "ይፈወሱ ነበር"፣ "ክርስትና በሽታ ሁሉ እንደሚፈወስ ዋስትና ሰጥቷል" የሚል ሙግት በፈስቡክ ሊገጥመኝ ሞክረ። እባክህ ተው መጽሐፍ ቅዱስ ይህ ዐይነቱን ዋስትና አልሰጠም ብሰው ሲሰማኝ በፍጹም አልቻሰም።

ይህ አስተሳሰብ ወደ ኢትዮጵያ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት የገባው፣ "በእምነት እንቅስቃሴ" መምህራን አማካይነት ነው። ግሰሰቡ የዚህ ትምህርት ሰለባ መሆኑን በትክክል የሚያወቅው አይመስለኝም (ማሰቱን እንጂ የሚሰው ነገር ከየት እንደ መጣ በትክክል አልተረዳውም)።

"የታመመ ሁሉ መፈወስ አለበት" የሚሰው የእንቅስቃሴው ትምህርት አስተምህሮውን የሚያጸናበት ሁሰት የአካሄድ አቅጣጫዎች አሉት። "በክርስቶስ ወጂዊ ሥራ ውስጥ አካላዊ ፈውስ ምሳሽ ሰላገኘ፣ ሰዎች ሁሉ መፈወስ አለባቸው" የሚሰው አንደኛው አካሄድ ሲሆን፣ ሁሰተኛው ደግሞ "በወንጌላውያኑ ትረካ ውስጥ የታመመ ሁሉ ተፈውሰዋል" የሚሰው ነው።

የሁሰተኛው አካሄድ የመረጃ ማሳከር ብቻ ሳይሆን፣ ትልቅ የሆነ የሥነ ትርጓሜ ችግር አለበት። ይኸውም በአንድ ታሪካዊ አጋጣሚ አንድ

ነገር እውን ሆነ ማለት፣ ሁል ጊዜ ነገሩ እውን ይሆናል ማለት አይደለም። ከትምህርታዊ ምንባባት ተነሥተን ታሪክን አጣቅሰን አስተምህሮ እንመሠርታለን እንጂ፣ በተገላቢጦሹ ምንጨታዊ ምንባባት አንዳችም አስተያየት ባልሰጡበት ጉዳይ፣ ከትረካዎች ተነሥተን አስተምህሮ አናዋቅርም። ለምሳሌ ጌታ ተራራ ላይ ወይም በታንኳ ላይ ተቀምጦ በየብስ ላሉ ሰዎች ትምህርት ስጥቶአል ማለት፣ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት በሚያስተምሩበት ጊዜ ተራራ ላይ ይውጡ ወይም ታንኳ ላይ ይቀመጡ ማለት አይደለም። ዘማሪው፣ "ጻድቅ ሲራብ ዘሩም አህል ሲሰማን አላየሁም" (መዝ. 37÷25) ብሏልና እኛም አናይም ማለት ትክክል አይደለም፣ ቢያንስ ይህ አስተምህሮ በሐዲስ ኪዳን ነገረ መለኮት ውስጥ ትክክል አይደለም።

የሚገርመው ግን በወንጌላት የፈውስ ትረካ ውስጥ ወደ ጌታ የመጡ ሰዎች ሁሉ ሲፈወሱ ወይም ስፈውሳቸው እምነት ወይም ሌላ ጉዳይ በቅድመ ሁኔታ ሲጠየቅ አንመለከትም። ከዚህ አንድ ክፍል ጠቅሰ መላው የሐዲስ ኪዳን አስተምህሮ በዚህ መልክ ይሰፈርልኝ ማለት ትክክል አይደለም።

ይህን ጉዳይ በተመለከተ፣ "የእምነት ወይስ የክህደት አንቅስቃሴ" በሚለው የአኔና የወንድም ምኒልክ አስፋው መጽሐፍ (ገጽ 57-70) ስፊ ማብራሪያ የቀረበበት ቢሆንም፣ የምዕራፉን አጥርጥር እንዲሁም ክመጽሐፉ አጠቃላይ መግባት አንጻር የሚከተለውን ወደዚህ አምጥቻለሁ።

ሀ. ክርስትና ሰጤንነት ዋስትና አልሰጠም!

1. በአራቱ ወንጌላት ውስጥ 48 የፈውስ ታሪኮች ተዘግበው እናገኛለን። ነገር ግን የተጓዳኝ ምንባባቱን ድግግሞሽ ስናቀናንስ፣ በወንጌላት ውስጥ 26 የፈውስ ታሪኮችን እናገኛለን።
2. ኢየሱስ ወደዚህች ምድር የመጣው የሰው ልጆችን ሁለንተና ማለትም ነፍሳቸውን ሥጋቸውን ለመፈወስ ነው። ጌታ ይህን ማድረጉ ሁለት ዐቢይ ምክንያቶችን አለው፣ አንደኛው እርሱ እንደ አባቱ ሁሉን የማድረግ ችሎታና ሥልጣን እንዳለው

ለማስየት/ስማሳወቅ (ዮሐ. 5÷17-22)። ሁለተኛ፣ በክርስቶስ እውን የሚሆነው መንግሥት ምን ዐይነት መገለጫ እንዳለው ስማሳለብ/ስማስገንዘብ ነው (ማቴ. 4÷23-25)። ይህ መንግሥት የጽድቅ፣ የሰላም፣ የዕረፍት፣ በጥቅሱ የበረከት ዘመን መንግሥት ነው።

3. በክርስቶስ ኢየሱስ የፈውስ አገልግሎት ውስጥ፣ ተፈዋሹ ስው እምነት ያለው መሆኑ በቅድመ ሁኔታ ውስጥ ገብቶ እንመለከትም። ከ26ቱ የፈውስ ታሪኮች ውስጥ፣ 4ቱ ብቻ የፈውሱ ምክንያት ምን እንደ ሆነ አልተገለጸልንም። በተቀሩት በ22ቱ የፈውስ ታሪኮች ውስጥ ግን የፈውሱን ጥያቄ ያቀረበው ወይም ፈውስ እውን ይሆናል ብሎ እምነት የነበረው ግን እንደ ነበር ተገልጸአል። ክዚህ መረጃ የምናየው በሕመምተኞቹ ጠያቂነት ያውም ጥያቄውን ያቀረቡት እምነት ኖሯቸው ነው ብንል እንኳ ክ22 ውስጥ እምነት የተጠየቀው በ12ቱ ብቻ ነው። ይኸውም፦—

ወንጌላት	በኢየሱስ ጠያቂነት	በደቀ መዛሙርቱ ጠያቂነት	በሕመምተኞቹ ጠያቂነት	በዘመዶቹ ጠያቂነት	በሕመምተኞቹ ወደዳጆች ጠያቂነት	በኢየሱስ ተቃዋሚ ምች ጠያቂነት	ባልታወቁ ሰዎች ጠያቂነት
ማቴዎስ	—	—	1	—	1	—	2
ማርቆስ	—	1	4	3	1	—	2
ሉቃስ	3	—	2	—	—	2	—
ዮሐንስ	1	1	—	2	—	—	—

4. ጌታ ኢየሱስ ሁሉን ማድረግ ቢችልም፣ የታመሙትን ሁሉ ግን ያልፈወሰም (ዮሐ. 5÷3-5)፣ የተጠየቀውን ሁሉ ያላደረገበት ትእይንቶች ነበሩ፣ ለምሳሌ ምልክት እንዲያሳያቸው ስለመኑት ሁሉ ምልክት አላደረገም (ማቴ. 12÷38-40)። ስዚህ ደግሞ ምክንያቱ ኢየሱስ ለሰዎች የሚፈውሰው (ምልክት፣ ድንቅንና

ተአምራትን የሚያደርገው) ሰማያዊ ዐላማውን በሰዎች ልብ ሰማድረስ ብቻ እንደ ነበር የሚያስገነዝበን ነው። እርግጥ ነው ሰዎች ከሥጋዊ አስራታቸው ሲፈቱ ደስ ይሰዋል። ይህ ግን ወሳኝ ጉዳይ ሆኖ አልቀረበም። ወሳኙ ጉዳይ ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝ መሆኑን አምነው፣ አርሱን አንደ ግል አዳኛቸው መቀበላቸው ነው። ሰለዚህ ጌታ ሁሉን ማደረግ መቻሉ እሙን ቢሆንም ሁሉን ሲያደርግ ግን አንመለከትም። ሰለዚህ ችሎታውን ከሉዓላዊ ፍላጎቱ/ዕቅዱ ጋር መቀየጥ የለብንም።

5. ኢየሱስ ዘንድ የመጡ ሰዎች የተፈወሱት፣ ኢየሱስ አርሱ ሁሉን ቻይ፣ ሰሰዎች ግድ የሚሰው...አምላክ መሆኑን ሰማሳየት ነው። በዚህም መንፈስ የተራቡ ሰዎችን መግቧል (ማቴ 15÷32፤ ማር. 8÷2)፤ መሪ ያላላቸውን (ማቴ. 9÷36፤ ማር. 6÷34)፤ ተጨንቀው የነበሩትን (ሉቃ. 7÷13)፤ በደዌ የተመቱትን (ማር. 9÷22) ሰዎች አይቶ አዝኗል። የግለሰቦቹ እምነት ሳይሆን፣ የአርሱ ርኅራኄ ሰፈውሱ ምክንያት ሆኖ የቀረበባቸው አራት የፈውስ ታሪኮች አሉ (የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከታል ማቴዎስ 20÷34፤ 14÷14፤ ማርቆስ 1÷41፤ ሉቃስ 7÷13)።

6. "የዳዊት ልጅ ሆይ ማረን" በማለት ለዕርዳታ የጮኹትን ሰዎች ፈውሷል (ማቴዎስ 9÷27፤ 15÷22፤ 17÷15፤ 20÷30፤ ሉቃስ 17÷13)። እንዲሁም አምነታቸውን አይቶ የፈወሳቸው አሉ (ማቴ. 8÷10፤ 9÷28-29፤ 15÷28፤ ማር. 2÷5፤ 5÷34፤ 9÷24፤ ሉቃ. 17÷19፤ 18÷42)። ቅዱሳት መጻሕፍት እምነት በኀጢአት የወደቀው የሰው ልጅ ከልቡ የሚያመነጨው ጉዳይ ሳይሆን፣ የአምላክ ነጻ ሰጦታ አንደ ሆነ ይናገራሉ (ሰምሳሌ የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከታል ኤፌ. 2÷8፤ ዮሐ. 6÷28-29;44-45፤ ሮሜ 12÷3፤ ሐሥ. 12÷3፤ 3÷16፤ ፊልጵ. 1÷29፤ 2ጴጥ. 1÷1)። ሰሰዚህ እምነት የፈውስ ወይም የድነት ቅድመ ሁኔታ ነው ማለት አስቸጋሪ ነው።

7. ኢየሱስ ሰዎችን ይፈውስ የነበረው ክብሩን ለመግለጥ ነው (ዮሐ. 1÷14፤ 2÷11÷4፤ 17÷5:22:24)። የአርሱን ማንነት አሰመልክቶ ውዝግብ ሲነሣ ምግባሩን አይተው ማንነቱን እንዲሰዩ ጥሪ ያቀርበላቸው ነበር (ዮሐ. 5÷36፤ 10÷25፤ 14÷11፤ 15÷24)። እርሱ የመጣው ሰዎችን ለማስገረምና ሰማሰደነቅ አይደለም (ዮሐ. 4÷48)፣ ነገር ግን በሚያደርጋቸው ምልክቶች (ግሪክ ሴሚያ) ሰዎች የአርሱን ማንነትና ተልእኮ አንዲያውቁ ማድረግ ነው። በሉቃስ ወንጌል፣ ኢየሱስ የፈወሳቸው ሰዎች እግዚአብሔርን ሲያከብሩና ሲያመሰግኑ እንመለከታለን (ሉቃ. 5÷25፤ 13÷13፤ 17÷15፤ 18÷43)። ሰዎቹ በተአምራቱ ብቻ ሳይሆን የተገረሙት፣ ተአምራቱ በሚያሰተላልፈው ወሳኝ መልእክት አንጂ—ይኸውም አምላክ ይራራልናል፣ ቸርነቱ ከእኛ ጋር ነው በሚለው ብርቱ መልእክት እንጂ።

ኢየሱስ ሰዎችን የፈወሰው ትንቢትን ሰመፈጸም ነበር። የብሉይ ኪዳን ነቢያት ኢየሱስን በተመለከተ ከ300 በላይ ትንቢቶችን ተናግረዋል። ኢየሱስ ያ የሚጠበቀውና ነቢያት የተናገሩለት መሲሕ መሆኑን ለማስረገጥ ተአምራትን አድርጓል። በሉቃስ ወንጌል ላይ ኢየሱስ በነቢዩ ኢሳይያስ የተነገረውን ትንቢት ካነበበ በኋላ፣ "ዛሬ ይህ መጽሐፍ በጆሮአችሁ ተፈጸመ" አለ (4÷21)። ሰለዚህ ፈውስ ክርስትና የትንቢት ፍጻሜ አንደ ሆነ እመላካች ነው። ኢየሱስ አጁ የለለችውን ሰው ከፈወለ በኋላ፣ በነቢዩ ኢሳይያስ የተጻፈው ይፈጸም ዘንድ መሆኑን ወንጌላዊው ማቴዎስ ነግሮናል (12÷17-21)። ኢየሱስ የምድራዊ አገልግሎቱ መሲሑ ሲመጣ የሚከውነው ነገር አንደ ሆነ ተናግሯል (ሉቃ. 7÷21-23)።

ከእነዚህ መሠረታውያን ነጥቦች የምንማረው ቁም ነገር የተአምራት ቀዳማይ ዐላማ እግዚአብሔርን ማክበር አንደ ሆነ። አንዲሁም ክርስትና ለምች ሁሉ ከአማማቸው ይፈወሳሉ የሚል ጥቅል ዋስትና አልሰጠም።

ሰ. ክርስትና ለሀብት ዋስትና አልሰጠም!

መጽሐፍ ቅዱስ ምድራዊውን ብልጽግና ሳይሆን፣ ሰማያዊውን ብልጽግና አጥብቀን እንድንሻ ያሳስበናል። መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች ምድራዊ ንዋይ እንዴት ይስበስባሉ የሚሰውን ጉዳይ እያስተምርም። ባንጻሩም ግል ለድኾች የተሰየ አምላካዊ ትኩረት ተሰጥቶ አናነባለን። መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ቀን እጦትም ሆነ አጥረት የማይኖሩበት ዘመን አንደሚመጣ በግልጽ ይናገራል። አግዚአብሔር ሁሉን ነገር አዲስ በሚያደርግበት ጊዜ ሁሉም ነገር የአኛ ይሆናል—ቢያንስ የሚያስፈልገን ነገር ሁሉ በሚያስፈልገን መጠን ይኖረናል። ይህን ደግሞ እግዚአብሔር ራሱ፣ በራሱ የጊዜ ሰሌዳ አውን ያደርገዋል። አስከዚያ ቀን ድረስ መስጠት (ብድራት ሳይጠብቁ መስጠት) የእግዚአብሔር ዘይቤ እንደ ሆነ ሁሉ፣ የአኛም ዘይቤ መሆን አለበት። መስጠት የእግዚአብሔር ባሕርይ ነው። አግዚአብሔር ሁል ጊዜ ሰጭ ነው። አኛም በዚህ ባሕርይ ልንወረስ ይገባል። ገንዘብና ምድራዊ ሀብት ከአኛ ጋር ለዘላለም አይኖሩም፣ የገንዘብም ሆነ የምድራዊ ሀብት ፋይዳው ውሱን ነው። በመሆኑም ገንዘብና ምድራዊ ሀብት አየተጉዱ በመስጠት ለሚልቀው ፋይዳ እንዴት ሊውል ይችላል ብሎ መጠየቅ ያስፈልጋል።

በዘመኑ ብልጽግና እንደ ወንጌል ቢቁጠርም በአውነተኛው ወንጌል ግን አይደለም። የብልጽግና ወንጌል የሰዎችን ሁሉ ችግር አይፈታም። የብልጽግና ወንጌል ባለጠጎች ዘንድ ሊደርስ ይሽመደመዳል፣ ምክንያቱም ምኑን ያበለጽጋቸዋል፣ አነርሱ ራሳቸው

ሥነ ድሮ ባለጠጎች ናቸው። የብልጽግና ወንጌል ባለጠጎችን አያንገም። የብልጽግና ወንጌል የሚያንገው ምስኪን ድኾችን ብቻ ነው[60]።

በመሠረቱ የሰዎች ትልቁ ችግር ማግኘትና ማጣት አይደለም፣ ወይም ሀብትና ድኽነት አይደለም። የሰዎች ትልቁ ችግር ኀጢአትና መዘዙ ነው። በዚህ ረገድ ሰዎች ሁሉ—ሀብታምም ሆኑ ድኾ—እኩል ናቸው። ሀብታሞችም ሆኑ ድኾች ኀጢአተኞች ናቸው፣ እናም ለድኾች ኢየሱስ እንደሚያስፈልግ ሁሉ ለሀብታሞችም ኢየሱስ ያስፈልጋቸዋል። ሰዎች ሁሉ ኀጢአተኞች ከሆኑ ኢየሱስ የማያስፈልገው ምድራዊ ፍጡር በጭራሽ ሊኖር አይችልም። ጳውሎስ "ሰዎች ሁሉ ከኀጢአት በታች" መሆናቸውን ሲናገር "ጻድቅ የለም አንድ ስንኳ፣ አስተዋይም የለም፣ እግዚአብሔርንም የሚፈልግ የለም፣ ሁሉም ተሳስተዋል፣ በአንድነትም የማይጠቅሙ ሆነዋል" ይላል (ሮሜ 3÷9-11)። ጳውሎስ ችግራችን ምን አንደ ሆነ ከነገረን በኃላ መፍትሔውንም ነግሮናል። "አሁን ግን በሕግና በነቢያት የተመሰከረለት የአግዚአብሔር ጽድቅ ያለ ሕግ ተገልጧል፣ አርሱም ለሚያምኑ ሁሉ የሆነ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘው ጽድቅ ነው" (ሮሜ 3÷21-22)።

ምንም ተብለ ምን ክርስቲያኖች ከክርስቶስ የተነሣ ባለጠጋ ናቸው። አግዚአብሔር አንዲመረምረን መፈለግ ትልቅ ነገር ነው። ነቢዩ አንዲህ ብሎ ይጠይቃል፣ "ምን ይዤ ወደ አግዚአብሔር ፊት ልምጣና በልዑል አምላክ ፊት ልስገድ? የሚቃጠለውን መሥዋዕት፣ የአንዱን ዓመት ጥጃ ይዤ በፊቱ ልምጣን? አግዚአብሔርስ በሺህ አውራ በጎች ወይስ በእልፍ የዘይት ፈሳሾች ደስ ይሰዋልን? ወይስ

[60] *Bradley A. Koch, The Prosperity Gospel and Economic Prosperity: Race, Class, Giving, and Voting (Indiana University: PhD Diss, 2009) 14-21.*

የበኩር ልጄን ስለ በደሌ የኽዴንም ፍሬ ስለ ነፍሴ ኀጢአት እሰጣለሁን? ለው ሆይ፤ መልካሙን ነግሮሃል፤ እግዚአብሔር ከአንተ ዘንድ የሚሻው ምንድር ነው? ፍርድን ታደርግ ዘንድ፤ ምሕረትንም ትወድድ ዘንድ፤ ከአምላክህም ጋር በትሕትና ትሄድ ዘንድ አይደለምን?" (ሚል 6÷6-8)።

አንደ ሱዓሳዊ ፈቃዱ አምላካችን እግዚአብሔር ቱጀር ሊያደርገን ቢችልም ክርስትና ግን አማኞች ሁሉ ባለጸጋ ይሆናሉ የሚል ዋስትና አልሰጠም። መጽሐፍ ቅዱስ የዕለት አንጀራችንን መጠየቅ እንደምንችል ነግሮናል፤ በመጠን በመኖር ክርስቶስን የሕይወታችንና የኑሮአችን ማዕከል አንድናደርግ መመሪያ ተሰጥቶናል። በምናልፍባቸው ማናቸውም ዐይነት ጉዳናዎች፣ እርሱን በማክበርና በመፍራት የእርሱ አንደ ራሴ ሆነን እንድንኖር ተጠይቀናል። አምላክ በሰጠን ዕውቀት፣ ገንዘብ፣ ጤንነት፣ ጊዜ፣ ክሂሎት ወዘተ ክርስቶስን መሰበክና ቅዱሳንን ማገልገል ይጠበቅብናል። ክብር ሁሉ ለአምላካችን ለእግዚአብሔር ይሁን።

ክፍል ሰምንት

ክርስቲያን አጋንንት ይገቡበታልን?



እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ፣ "ክርስቲያን አጋንንት ይገባበታል" የሚለው አስተሳሰብም ሆነ አስተምህሮ፣ እንደ ትልቅ ኑፋቄ ይታይ ነበር። የቤተ ክርስቲያናችን አንጋፋ ወንጌላዊ፣ ይህን ትምህርት በድብቅ ተቀብለው፣ የተማሩትን በስውር ሲያስተምሩ፣ ቤተ ክርስቲያኒቱ እጅ ከፈንጅ[1] ያዘቻቸው።

[1] ትምህርቱ እንደ "ፈንጅ" ይታይ ነበር።

በወቅቱ የነበሩት የቤተ ክርስቲያኒቱ ሽማግሌዎች፣ ነገረ መስክት ቀመስ (አንዳንዶቹም ጠገብ) ነበሩና፣ ግለሰቡ የማርከሻ ትምህርት ስተከታታይ ወራት እንዲማሩ፣ በማኅበረ ምዕመናኑ ፊት ቆመው የነገረ መስክት ንስሓ እንዲገቡ፣ ስተወሰኑ ወራትም ከማናቸውም አገልግሎት ታግደው፣ በጸምና በጸሎት ራሳቸውን እንዲመረምሩ ቍርጥ ብያኔ ተላለፈባቸው።

ምክንያቱም ክርስቲያን አጋንንት ይገቡበታል የሚለው ትምህርት፣ ሰወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት መሠረተ እምነት፣ ሊበዛ አንግዳ እንዲሁም ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ ነው። በተገላቢጦሹ ዛሬ፣ "ክርስቲያን አጋንንት አይገባበትም" የሚል ሰው ቢገኝ፣ ከቤተ ክርስቲያን አባልነት ባይሰረዝ እንኳ፣ እንደ ትንግርት እንደሚታይ አያጠያይቅም—ቢያንስ በአብዛኞቹ አብያተ ክርስቲያናት። እንዲያውም ይህን አግድም ዐደግ ትምህርት ስሕተት ነው የሚሉ ሰዎች ወየውላችሁ—"የአእምሮ ሰው"፣ "አውቃለሁ ባይ"፣ "የመንፈስ ቅዱስ ተቃዋሚ"፣ "መንፈሳዊ ነገር የማይገባው ሥጋዊ ክርስቲያን"፣ "የመንፈስ አሠራር የማይረዳ"...የሚል መታወቂያ ይሰጠዋል (ይወጣለታል)።

መቼም አሮጌ አስተምህሮ ሁሉ ትክክል ነው፣ አዲስ ትምህርት ሁሉ ስሕተት ነው የምል ሞኛሞኝ ሰው አይደለሁም። "አሮጌ" እንዲሁም "አዲስ" የሚለው፣ ዕድሜን ብቻ እንጂ ይዘትን ታሳቢ ያላደረገ ገለጻ እንደ ሆነ አረዳለሁ። ስለዚህ "አሮጌም" ሆነ "አዲስ" ትምህርት፣ አይነቀስም አይገሠሥም ብለን በተቀበልንው በቃለ እግዚአብሔር መመዘን፣ መገናዘብ፣ መመሳከር...ይኖርበታል።

ክርስቲያን አጋንንት ይገባበታል የሚለው ትምህርት፣ ሰወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናትም ሆነ፣ ለፕሮቴስታንቱ መሠረተ እምነት አዲስ ነው። "መርገም ከምንዝላት፣ ከእንጅላት ይተላለፋል"

እንደሚለው ትምህርት፣ "ክርስቲያን አጋንንት ይገቡበታል" የሚለውም ዘመን አመጣሽ ትምህርት ነው። ካልተሳሳትሁ በቀር፣ የሁሉቱም ትምህርቶች ቀዳማይ አመንጪና አስተዋዋቂ ዶሬክ ፕሪንስ ናቸው። እነዚህም ሁለት ጣምራ ትምህርቶች አስተማሪዎቻቸው፣ "የዐርነት አገልግሎት" በማለት ያጠሯቸዋል። ክርስቲያኑን ማኅበረሰብ፣ "ከዘር ከሚመጣ መርገም ነጻ ማድረግ" እንዲሁም "ከአጋንንት ቍጥጥር ዐርነት ማውጣት"።

አንደ አሜሪካዊው ፒተር ዋግነር *(Charles Peter Wagner)* ያሉ ሰዎች ደግሞ፣ በዚሁ እስተምህሮ ላይ፣ "የግዛት መናፍስት" *("Territorial Spirits")* የሚሰውን ትምህርት አክለውበት ብቅ አሉ (ለግዛት መናፍስት የሚጠቀሱት ጥቅሶች አነሆ:— ዳን. 10፤ ዮሐ. 12÷31፤ 14÷30፤ 16÷11፤ ማር. 5÷10፤ ኤፌ. 6÷12[2]። ከዚያም በየአብያተ ክርስቲያናቱ ሁሉ፣ የስንበት አምልኮ ከመጀመሩ በፊት፣ "በዐየር ላይ ያሉትን አርኩስ የግዛት መናፍስት እየተቃወምን እንጸልይ!" መባል ተጀመረ። "ስም ... ስም ... ልቀቅ ... በስሜን ... በደቡብ ..."። ቤተ ክርስቲያን የሥርዐት ሳይሆን፣ የሁከት ማዕከል ሆነች። የአልቃይዳ አጥፍቶ ጠፊ የገባበት አዳራሽ መሰለች[3]። ሐዋርያው ጳውሎስ ያላመኑ ሰዎች ወደ ጉባኤያችሁ

[2] ይህ አስተምህሮ በአንዳንድ አካባቢ መንፈስ ቅዱስ እንዳይወርድ፣ ጸሎታችን ምላሽ እንዳያገኝ የሚገዳደሩ እንዲያውም የሚከሰክሱ የተግዳሮት መናፍስት አሉ። አንዳንድ አካባቢ ደግሞ እግዜር፣ ሳይጠራ ከተፍ ይላል። ምክንያቱም ዐየሩ ነጻ ነውና። የሚል ትምህርት ነው።

[3] በዚህ ውጥንቅጥ መካከ፣ ወደ ቤተ ክርስቲያን የገፋው የዜድሁት የአትቱ ልጅ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ባየው ሁከት ምክንያት መንፈሱ እጅግ ታወከ፣ ጎሲናው ተበጠበጠ፣ "ይህ ነገር ምንድን?" ነው ሲል ወደ ጆሮዬ ጠጋ ብሎ በሰሆሳስ ደጋግሞ ጠየቀኝ። "አይዞህ ሰጥቂት ይቀቃ ነው ይቆማል" አልሁት። ነገሩ ከመቼም ይልቅ እየተባባሰ ቀጠለ። እንዲያውም አንዳንዶች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው፣ በልሳን መናገር ጀመሩ። አንዳንዶቹ እየተንዘፈዘፉ ወደቁ። "እባክህ አልተመቸኝም" አለኝ፣

ቢገቡ "ዐበዳችሁ አይሉምን?" የሚለው ትምህርት በመላት ተፈጸመብን። ሃይ ባይ ባጡ አንግዳ ደራሽ ትምህርቶች፣ ቤተ

በሚያሳዝን ድምፀት፣ በተማጽኖ መንፈስ። እንዴት ላረጋጋው እንደምችል ማሰብ ጀመርሁ፤ አንዳችም መላ ሊመጣልኝ አልቻለም፤ ምን ዐይነት መላ ሲገኝ ይችላል? እንኳን በዚያ ቅጽበት እስከ ዛሬ መፍትሔ ልናገኝለት መቼ ቻልንና? "ኃላ ይህ የመንቀጥቀጥና የማንራት ነገር ወደ እኛ ሊመጣ ይችላል፤ እኔ ይህን በፍጹም አልፈልግም" አለ። እጅግ በጣም ደነገጠ። "ከቤተ ክርስቲያኒቱ አስወጣኝ" ሲል ደጋግሞ ተማጸነኝ—በእኔ ሃይ ባይነት ካልሆነ በስተቀር መናፍስቱ ዘለው የሚሰፍሩበት መሰለው። "እኔ አይዞህ ይቆማል" በሚለው ምላሼ ጸናሁ፤ ከብዙ ዓመት ልፋት በኃላ ያመጣሁት ሰው በዚህ መልክ እንዴት ይሂድብኝ? ኃላ ፈትለክ ብሎ ወደ በሩ እየሮጠ ሄደ። ከረጅም ዓመት ያላሰለሰ ጉትጎታ በኃላ፣ እሺ ብሎኝ ወደ ቤተ ክርስቲያን የመጣ ሰው፣ በዚህ መንገድ ወደ ቤተ ክርስቲያን ዳግም ተመልሶ ላይመጣ፤ በዚያው ዓመት በድንገተኛ ሕመም አሸለበ። ከክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ሥርዐት የለሽነትና ሁከት የተባረረው ወንድሜ፣ ያለክርስቶስ ኢየሱስ በሞት ተጠናቀቀ። "በአምልኳችሁ ሥርዐት ይኑራችሁ"፣ "የማያምኑ ሰዎች በመከሰላችሁ ቢመጡ አይታነጹበትም"፣ "ዐበዳችሁ ይላሉ"፣ "እግዚአብሔር የሥርዐት አምላክ ነው" የሚለው የሐዋርያው የጳውሎስ ምክር፣ ከማንም ይልቅ በእኔ መስል ሕይወት ውስጥ ላለፉ ሰዎች ይገባናል፤ ምጡና ጣሩ ጉልቶ ይለማናል። ዛሬ በየአብያተ ክርስቲያናቱ የሚታየው ሁከት እንኳን ላላመነው፣ አማኝ ነኝ ለሚለው፣ ለረጅም ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ለተመላለሰውም ሰው፣ እጅግ ሲበዛ ግራ የሚያጋባ ነው። መንፈስን ያጣልቃል፤ ነፍስን ያውካል። ሐዋርያው ጳውሎስ ተርጓሚ ከሌለ፣ "ልሳን አትናገሩ" የሚለውን ግልጽ ምንባብ ጠቅሶን ሃይ ማለት አልቻልንም። "ሐዋርያት"፣ "ነቢያት"፣ "የእግዚአብሔር ሰው" የሚባሉ ሰዎች በግልጽ ስለሚያደርጉት፣ እኛ ምን ሆነን የሚሰማን ይኖኛል? የሌላውን አላውቅም እኔ ግን አዳዲስ ሰዎችን ወደ ቤተ ክርስቲያን ይዞ መሄድ የማልችልበት ደረጃ ላይ ደርሻለሁ። እንኳን ሰው ይዘን ለመሄድ እኛም መሄድ በብዙ መልኩ ችግር ሆኖብናል። ስሜት ጣራ ያልነካበት ንባሌ ፊልጎ ማግኘት አስቸጋሪ እየሆነ ነው። ከአንጡ ወይም ከመሰል ነፋቁ ጋር ያልተቀላቀለ ንጹሕ መንፈል የሚሰበክበት ዐውደ ምሕረት አለ ማለት በማይቻልበት ደረጃ ተደርሶአል። ለዚህ ነው የዘማሪ ዶክተር ደረጀ ከበደ መዝሙር፣ እጅግ ትልቅ ትርጉም ይዞ ከተፋ፣ የሚለው—ሥርዐት የሌለበት፣ ገደብ የሌለበት...ሰው ተግተሉተለ፣ እንክርዳዱ ስንዴ ተከሳው በግ መሰለ...አወይ ነ—ዳ—ነ—ት !

ክርስቲያን መታወክ ጀመረች፤ የአስተምህሮ መዋቅሮችዋ ሁሉ ታዛ አልባ ሆኑ። ይኸው በዚህ ውጥንቅጥ አለክ ዛሬ አለን!

"የዐርነት" አገልግሎት የሚባለው፣ "የክርስቲያኖችን መርገም መስበር" አንዲሁም "አጋንንት ያለባቸውን ክርስቲያኖች በውስጣቸው ካለው አጋንንት ነጻ ማድረግ" ነው[4]። የዘመኑ አባይ ነባሮች በእኛው መካከል ዐድገው የገሰበቱ አንጂ፣ ከሌላ ምድር የመጡ ስዎች አይደሉም። ባይሆን እነዚህን አስተምህሮዎች ስብስበውና

[4] የእንቅስቃሴው መምህራን፣ "demon possessed" እና "demonized" የሚሉትን የእንግሊዝኛ ቃላት በሁለት የተለያዩ መንገዶች ይጠቀመብቸዋል። "demonized" የሚባለው በአጋንንት በውስጡ አድሮ፣ ሙሉ ለሙሉ በቍጥጥራቸው ሥር ያደረጉትን ሰው የሚያመለክት ሲሆን፣ "demon possessed" ደግሞ አጋንንት በክርስቲያን የተወሰነ ወይም በመላ አካሉ ውስጥ ያድራል የሚለው ነው። አንዳንዶች ይህን አካሄድ አገላብጠው ይጠቀማሉ። ዞሮ ዞሮ ግን የእንቅስቃሴው አራማጆች፣ "ዳግም ልደት ያገኘ ክርስቲያን አጋንንት ሊያድርበት ይችላል፤ ስለዚም በክርስቲያን ውስጥ የሚያድረውን አጋንንት በዐርነት አገልግሎት ማስወጣት ያስፈልጋል ባይ ናቸው"። ግሪክ ሊክሲኮንም (lexicon) ሆኑ፣ የነገረ መለኮት መዝገበ ቃላት፣ "ዳይሞኒዞማይ" (δαιμονίζομαι) የሚለውን የግሪክ ቃል፣ በአጋንንት መያዝ ("to be possessed by a demon") ብለው ነው የተረጐሙት (δαιμονίζομαι; 1 aorist passive participle δαιμονισθείς; (δαίμων): to be under the power of a demon)። የእንግሊዝኛ መዝገበ ቃላት "demon possession" የሚለውን ቃል የተረጐሙት፣ "to gain or exert influence or control over; dominate" (American Heritage Dictionary, 3rd ed.)። ከዚህ የተነሣ "demon possession" የሚለውን ቃል፣ በቍጥጥሩ ወይም በተጽእኖው ውስጥ መኖር ብሎን ልንተረጉመው እንችላለን (ማቴ. 4÷24፤ 8÷16፡28፡33፤ 9÷32፤ 12÷22፤ 15÷22፤ ማር. 1÷32፤ 5÷15፤ ዮሐ. 10÷21)። የግሪኩን ቃል አጠቃቀም በተመለከተ የሚከተሉትን ሁለት መጻሕፍት ይመለከቷል:— Louw and Nilda, *Greek-English Lexicon of the NT Based on Semantic Domains* (New York: United Bible Society, n.d.), 1:147. Bauer, Ardnt, Gingrich, Danker, *A Greek-English Lexicon of the New Testament* (Chicago: University of Chicago Press, 1979), 169. የነገረ መለኮት መዝገበ ቃላት:— Gerhard Kittel, ed., *Theological Dictionary of the New Testament* (Grand Rapids, MI.: Eerdmans, 1964), 2:19. Colin Brown, ed., *New International Dictionary of New Testament Theology* (Grand Rapids, MI.: Zondervan, 1986), 1:453.

አቀናጅተው፣ በአለባበስና ባረማመድ አምረውና ደምቀው "ተገለጡልን" እንጂ።

ክርስቲያኖች በለይጣንም ሆነ በአጋንንት፣ ጥቃት እንደሚደርስባቸው እሙን ነው። በዚህም አግባብ መጽሐፍ ቅዱስ ነቅተን እንድንኖር አበክሮ ያስገነዝባል (ነህ. 9÷6፤ ሉቃ. 2÷13-15፤ ኤፌ. 6÷12፤ ቄላ. 1÷15-16፤ 2ነገ. 6÷11-17፤ ዳን. 10÷7-17)። ከዚህ ባለፈ ግን፣ ዳግም የተወለደ ክርስቲያን፣ የመንፈስ ቅዱስ እንጂ፣ የአጋንንት ማደሪያ ሊሆን በጭራሽ አይችልም።

ከዚህ በመቀጠል፣ "ክርስቲያን አጋንንት ሊገቡበት ይችላሉ" ለሚለው አስተምህሮ ማስደገፊያ፣ ተዘውትረው የሚጠቀሱትን ዋና ዋና የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት እንዲሁም ሙግቶች ለማየት እንሞክራለን። ለሙግቶቹም አግባብነት አላቸው የምላቸውን ምለሾች አስከትላለሁ።

ሙግት አንድ

አጋንንት በክርስቲያን ውስጥ ሲገባ ይችላል ለሚለው ትምህርት ተዘውትሮ የሚጠቀለው ማስረጃ፣ ንጉሥ ሳኦል የተቀባ የእግዚአብሔር አገልጋይ ሆኖ ሳለ፣ አጋንንት ገብተውበታል (1ሳሙ. 18÷10-11፤ 19÷9-10)፤ በዚህ ትልቅ የእግዚአብሔር ባለሟል ውስጥ የሚገቡ ከሆነ፣ በእኛ የማይገቡበት አንዳችም ምክንያት የለም። የተጠቀሱትን ክፍሎች አንብበን ወደ ምላሹ እንዘልቃለን፦—

> "10. በማግስቱም ከእግዚአብሔር የታዘዘ ክፉ መንፈስ በሳኦል ላይ በኀይል መጣበት፣ በዚህ ጊዜ ዳዊት ወትሮ እንደሚያደርገው ሁሉ በገና ሊደረድር፣ ሳኦል በቤቱ ሆኖ ትንቢት ይናገር ነበር። ሳኦል በእጁ ጦር ይዞ ነበር፤ 11. እርሱም፣ 'ዳዊትን ከግድግዳው ጋር

> አጣብቀዋለሁ' ብሎ በማሰብ ጦሩን ወረወረበት፣ ዳዊት ግን ሁለት ጊዜ ከፊቱ ዘወር አለ" (1ሳሙ. 18)።
>
> "9. ነገር ግን ሳኦል ጦሩን ይዞ በቤቱ ተቀምጦ ሳለ፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ ክፉ መንፈስ መጣበት፣ ዳዊት በገናውን ይደረድር ነበር፣ 10. ሳኦልም ከግድግዳው ጋር ሊያጣብቀው ጦሩን ወረወረበት፣ ነገር ግን ዳዊት ዘወር በማለቱ ሳኦል የወረወረው ጦር በግድግዳው ላይ ተሰካ። በዚያች ሌሊት ዳዊት ሸሽቶ አመለጠ" (1ሳሙ. 19)።

ይህ ሙግት አራት መሠረታውያን ችግሮች አሉበት፦—

አንደኛው፣ ከትረካ መጻሕፍት ተነሥቶ አስተምህሮ ማዋቀር፣ አጅግ ሲበዛ ስሕተት አንደ ሆነ በዚህና በተለያዩ መጻሕፍት ላይ በስፋት ሞግቻለሁ። የትረካ ወይም የታሪክ መጻሕፍት ስለአንድ ክሥተት መናገራቸው፣ ያን ሁኔታ አኖም አንድንቀበለው ወይም በየዘመናቱ ለሚኖሩ ለምች መመሪያ እንዲሆን ተብሎ አይደለም። ሥነ ምግባራዊም ሆነ አስተምህሮአዊ መሠረቶችን የምናዋቅረው፣ ከታሪክ መጻሕፍት ሳይሆን፣ ምንጨታዊ (የትምህርት) ምንባባት ነው። ባይሆን ከምንጨታዊ ምንባባት የተማርናቸውን መርሖች፣ በታሪክ መጻሕፍት ውስጥ አንዴት ተግባራዊ ሆነው አንደ ቀረቡ በግልጽ አንመለከታለን። ስለዚህ በንጉሥ ሳኦል አንድ ነገር መከሠቱ፣ ስለተከሠተው ጉዳይ ዝርዝር (ማለትም ለምን፣ አንዴት፣ ወዘተ የሚል) መረጃ ስላልተሰጠን፣ ክዚያ ቊንጽል አሳብ ተነሥተን ወደ ድምዳሜ መድረስ ሲበዛ አስቸጋሪ ይሆናል።

ሁለተኛ፣ በአምላክ በተቀባ ጊዜ የእግዚአብሔር ሰው እንደ ነበር አንመለከታለን *(1ሳሙ. 10÷1+)*። የኋላ ኋላ የታየው ግን ሰውጡ እውነተኛ ሰውጥ እንዳልነበር የሚያሳይ ነው። "ወንድሞቼ ሆይ፣ አንድ ሰው እምነት አለኝ ቢል ሥራ ግን ባይኖረውምን ይጠቅመዋል? እንዲህ ያለው አምነት ሊያድነው ይችላልን?" *(ያዕ. 2÷14)* የሚለው አሳብ፣ በአምላክ መመረጡና አምላክ አርሱን መጠቀሙ፣ እውነተኛ አማኝ ነበር ወደሚለው ድምዳሜ አያደርሰንም። እግዚአብሔር አረማዊ የሆነውን ንጉሥ፣ ንጉሥ ቂሮስን የእግዚአብሔርን ዐላማ እንዲያስፈጽም አምላክ ቀብቶ እንዳስነሣው መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይናገራልና *(ኢሳ. 45÷1)*።

ሦስተኛ፣ በብሉይ ኪዳን መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ሕይወት ውስጥ የሚያድረው በጊዜያዊነት ሊሆን *(መዝ 51÷11፤ መሳ. 13÷25፤ 1ሳሙ. 16÷14፤ ኢሳ. 63÷10-11)*፣ በሐዲስ ኪዳን ግን በቋሚነት በአማኙ ሕይወት ውስጥ ይኖራል *(1ቆሮ. 3÷16፤ 6÷19፤ 2ቆሮ. 6÷16፤ 2ጢሞ. 1÷14፤ ሐሥ. 6÷5፤ ኤፌ. 5÷18፤ ሮሜ 8÷9;11:15፤ ዮሐ. 16÷13፤ ገላ. 4÷6፤ 1ዮሐ. 2÷27)*። በብሉይ ኪዳን በአማኙ ውስጥ በጊዜያዊነት ብቻ ስለሚኖር የአምላክ መንፈስ በተለየው ጊዜ፣ እርኩሳን መናፍስት ሊያድሩበት ይችላሉ። በሐዲስ ኪዳን ግን መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ውስጥ በቋሚነት መኖሩ፣ እርኩሳን መናፍስት በአማኙ ሕይወት ውስጥ እንዲያድሩ ዕድል አይሰጥም። የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ከእርኩሳን መናፍስት (ከቡዔልዜቡል) ጋር አንዳችም ኅብረት እንደሌለው፣ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያስተምራል (የሚከተለውን ምንባብ ይመለከቷል ማቴዎስ *12÷24-35*)።

አራተኛ፣ የነገረ መለኮት ምሁራን፣ በሳኦል ላይ አጋንንት መምጣታቸውና መሄዳቸው፣ አጋንንት በእርሱ ውስጥ ማደራቸውን

በጭራሽ አያሳይም ባዮች ናቸው። ለምሳሌ ቶማስ አይስና ሮበርት ዲን፣ "የዕብራይስጡ ምንባብ፣ በሳኦል ላይ እርኩስ መንፈስ እንደ መጣበትና ኋላም ከእርሱ እንደ ሄደ ይገልጸሉ። ይህ ማለት ግን በሳኦል ላይ አጋንንት ገባበት ማለት በጭራሽ አይቻልም"[5] ባዮች ናቸው። ስለዚህ "መጣበት" ማለት "ገባበት" ወይም "ዐደረበት" የሚለውን አሳብ የሚያጸና አይደለም። ስለዚህ የንጉሥ ሳኦል ታሪክ፣ ክርስቲያን ላይ አጋንንት ይገባሉ ለሚለው አስተምህሮ፣ በጭራሽ ድጋፍ ሊሆን አይችልም።

ሙግት ሁለት

በሉቃስ *13÷10-17* ባለው ክፍል፣ "የአብርሃም ልጅ" ተብላ ስለተጠራች ሴት እናነባለን። ነገር ግን "የድካም መንፈስ" እንደ ነበረባት መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። እንዲያውም ሰይጣን ለ*18* ዓመት እንዳሰራት ተገልጸአል (ቍጥር *16*)[6]። የክፍሉን ሙሉ ዐውደ ኳነበብን በኋላ ወደ ግምገማው እንሄዳለን፦—

> "*10.* ኢየሱስ በሰንበት ቀን በአንድ ምኵራብ ያስተምር ነበር። *11.* በዚያም የድካም መንፈስ ዐሥራ ስምንት ዓመት ሙሉ አካሉ ስንኩል ያደረጋት አንዲት ሴት ነበረች፣ እርሷም ከመጮበጧ

[5] *Thomas Ice and Robert Dean, Jr., Overrun by Demons: The Church's New Preoccupation with the Demonic (Eugene, OR: Harvest House Publishers, 1990), 125.*

[6] አንዳንድ ጸሐፍያንም ይህቺ ሴት አማኝ ነበረች ብለው ጽፈዋል። ለዚህ ማስረጃ አድርገው የጠቀሱት *አንደኛ፣* በምኵራብ እግዚአብሔርን ማምለኳ፣ *ሁለተኛ፣* በፈውሷ ምክንያት እግዚአብሔርን ማመስገኗ፣ *ሦስተኛ፣* የአብርሃም ሴት ልጅ የሚለው ቃል ከዘኪያስ ትረካ ጋር ሲነጻጸር ድነት ያገኘች ሴት እንደ ነበርች ያሳያል *(ሉቃ. 19÷9)*። *C. Fred Dickason, Demon Possession and the Christian: A New Perspective (Chicago: Moody Press, 1987), 124-125.* እነዚህ ሴቲቱ ክርስቲያን ነበረች ለማለት አሳማኝ ነጥቦች ላለመሆናቸው፣ በቀጣዮቹ ተከታታይ ገጾች ላይ የቀረበውን ምላሽ ይመለከቷል።

የተነሣ ፈጽሞ ቀና ማለት አትችልም ነበር። 12. ኢየሱስም ባያት ጊዜ ጠራትና፣ 'አንቺ ሴት፣ ከሕመምሽ ነጻ ወጥተሻል' አላት፣ 13. እጁንም በላይዋ ጫነ፣ እርሷም ወዲያው ቀጥ ብላ ቆመች፣ አግዚአብሔርንም አመሰገነች። 14. የምኩራቡ አለቃ ግን፣ ኢየሱስ በሰንበት ቀን ስለ ፈወሰ ተቈጥቶ ሕዝቡን፣ 'ሥራ ሊሠራባቸው የሚገባ ሰድስት ቀኖች አሉ፣ ስለዚህ በእነዚያ ቀኖች እየመጣችሁ ተፈወሱ እንጂ በሰንበት ቀን አይደለም' አላቸው። 15. ጌታም መልሶ እንዲህ አለው፣ 'አናንት ግብዞች፣ ከአናንተ መካከል አንድ ሰው በሬውን ወይም አህያውን በሰንበት ቀን ከማደሪያው ፈትቶ ውሃ ሊያጠጣ ይወስደው የለምን? 16. ታዲያ፣ ይህች ሴት የአብርሃም ልጅ ሆና ሳሰች ዐሥራ ስምንት ዓመት ሙሉ በሰይጣን ታስራ ስትኖር፣ ከዚህ አስራት በሰንበት ቀን መፈታት አይገባትምን?' 17. ይህን በተናገረ ጊዜ ተቃዋሚዎቹ ሁሉ ዐፈሩ፣ ሕዝቡ ሁሉ ግን አርሱ ባደረገው ድንቅ ሥራ ሁሉ ደስ አላቸው" (ሉቃስ 13)።

ይህ ሙግት እያስሄድም። *አንደኛ፣* "የአብርሃም ልጅ" መባሏ፣ የይሁዲ ወገን መሆኗን አንጂ፣ ክርስቲያን መሆኗን የሚያሳይ አይደለም። ጌታ ዘኬምስን፣ "የአብርሃም ልጅ" ማለቱ፣ እውነተኛ እይሁድና የአሮጌው ኪዳን አባል መሆኑን የሚያሳይ ነው። ይኸውም የሮማውያን ቀረጥ ሰብሳቢ ሆኖ ማገልገሉን በሚያነጻጽር መልኩ[7]።

ሁለተኛ፣ ግለሰቧ በምኩራብ ማምለኪና ለፈውሷ እግዚአብሔርን ማመስገኗ፣ ክርስቲያን ነች ወደሚል ድምዳሜ የሚያደርስን እይደለም። ፈሪሳውያንና ለዱቃውያን በምኩራብ

[7] ይህ ሐሳብ የተወሰደው፣ ከሚከተለው የግሪክ ሌክሲከን ነው፦— *Joseph H. Thayer, Thayer's Greek-English Lexicon of the New Testament (Grand Rapids, MI.: Baker Book House, 1977), 292.*

ያመልካሉ፣ አምላክን ያመስግናሉ፤ ነገር ግን እውነተኛ እማኞች ነበሩ ማለት አንችልም።

ሦስተኛ፣ "የድካም መንፈስ" ነበረባት ማለት፣ በሽታውን ያስከተለው መንፈስ ነው ማለት እንጂ፣ ራሱ የድካም መንፈስ አድሮባታል/ገብቶባታል ማለት ሳይሆን ይችላል። እንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች፣ "በመንፈስ ምክንያት የመጣ በሽታ" ሲሉ ተርጉመውታል ለምሳሌ *(NAS—"Sickness caused a spirit" NIV* ደግሞ፣ *"Crippled by a spirit"* ብሎታል)። ነባሩ ትርጉም፣ "የድካም መንፈስ *ያደረባት*" ብሎ ይተርጉመው እንጂ፣ አዲሱ መደበኛ ትርጉም፣ እንደ እንግሊዝኛቹ፣ "አካሉ ስንኩል *ያደረጋት*" ሲል ተርጉሞታል[8]።

አራተኛ፣ በዚህ ዐውደ ምንባብ ውስጥ ልናስተውለው የሚገባን ሌላው ነጥብ፣ ጌታ ከበሽታዋ እንደ ፈወሳት እንጂ፣ አጋንንት እንዳወጣላት ያለመነገሩ፣ እርኩስ መንፈስ የበሽታው ምክንያት እንደ ሆነ እንጂ፣ እርኩስ መንፈስ ያደረባት ሴት እንዳልሆነች ሊያሳይ ይችላል[9]።

[8] በኮረ ጽሑፉ፣ "καὶ ἰδοὺ γυνὴ πνεῦμα ἔχουσα ἀσθενείας" ይለዋል። የውይይቱ ማዕከል "ኤከሜናስ" (ἐχόμενος) የሚለው ቃል ነው። ቃሉ፣ "ኤከ" (ἔχω) ከሚለው ዘር አንቀጽ የተገኘ ሲሆን፣ ቃሉ በርካታ አማራጭ ትርጉሞች ሊወክል ይችላል። ይኸውም 1. አንድ ዕቃ/ንብረት *አለኝ* ማለት (ማቱ 14÷17)፣ 2. አንድ ነገር በእጅ *መጨበጥ* (ራእ 6÷5)፣ 3. የተወሰነ አመለካከት *መያዝ* (ማቱ. 14÷5፣ ሉቃ. 14÷19) 4. ልብስ *መልበስ* (ማቱ. 3÷4)፣ 5. ችሎታ *ማግኘት* (ኤፌ.. 4÷28፣ 2ጴጥ. 1÷15)፣ *James Swanson, Dictionary of Biblical Languages With Semantic Domains: Greek (New Testament), electronic ed. (Oak Harbor: Logos Research Systems, Inc., 1997).*

[9] ለዚህም ይመስላል ከላይ የጠቀስነው ጸሐፊ፣ "አፋችንን ሞልተን ሌትየዋ አጋንንት ነበረባት ማለት አንችልም" የሚለው። ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 127።

ሙግት ሦስት

አጋንንት በክርስቲያኖች ውስጥ ያድራሉ የሚለው አስተምህሮ፣ አቋሙን እንዲያጸናለት ከሚያቀርበው ሙግት ውስጥ የሚከተሰው ትልቅ ቦታ የሚይዝ ነው። በሐዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ናቸው። ነገር ግን የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ብዙ ክፍሎች እንዳሉት ማወቅ አለብን። በብሉይ ኪዳን የነበረው ቤተ መቅደስ የደጁ አደባባይ፣ ቅድስትና ቅድስተ ቅዱሳን ከሚባሉ ሦስት ዋነኛ ክፍሎች የተዋቀረ ነበር። ጽላቱ/ታቦቱ የሚቀመጠውም ሆነ፣ እግዚአብሔር የሚገለጸው በቅድስተ ቅዱሳን እንጂ በአደባባዩ አልነበረም። በተመሳሳይ መንገድ አኛ ክርስቲያኖች የአምላክ ቤተ መቅደስ ነን። ነገር ግን አኛም አንደ ብሉይ ኪዳኑ ቤተ መቅደስ ሦስት ክፍሎች አሉን፤ ይኸውም:— ሥጋ፣ ነፍስና መንፈስ። በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር መንፈስ፣ በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ እንደሚያድር፣ በአዲሱ ኪዳን ደግሞ፣ በሰው መንፈስ ውስጥ ብቻ ነው የሚያድረው። በአደባባዩ ኀጢአታቸውን የሚያስተሰርዩ ሰዎች እንደሚሰበሰቡ ሁሉ፣ በሥጋችንም አጋንንት "ሊንጠላጠሉ"[10] ይችላሉ።

ይህ ሙግት በበርካታ ምክንያቶች ድምዳሜውን ማለትም ክርስቲያን አጋንንት ሊገባበት/ሊያድርበት ይችላል የሚለውን አቋም ሊደግፍ አይችልም። *አንደኛ*፣ ክርስቲያኖች የሕያው የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ናቸው ሲል፣ መንፈስ ቅዱስ በመንፈሳቸው ብቻ ነው የሚያድረው በሚለው ሂሳብ አይደለም። በሁለመናቸው እንጂ፣ (በዋቢነት የሚከተሉትን ክፍሎች ያነቧል:— ሮሜ 8÷9፤ 1ቆሮ. 3÷16፤ 2ቆሮ. 6÷16፤ ያዕ. 4÷5)።

[10] ከዚያው አካባቢ, *ያገኘሁት* ቃል ነው።

ሁለተኛ፣ አንዲያውም በሚያስደንቅ መልኩ፣ መንፈስ ቅዱስ "በሥጋችን" (ግሪክ "ሶማ" σῶμα) ውሰጥ እንደሚኖር መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይናገራል[11]። የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከታል:— "ቤተ መቅደስ ሊል ግን፣ ስለ ገዛ ሰውነቱ መናገሩ ነበር" (ዮሐ. 2÷21)። በዚህ ዐውድ፣ ጌታ "አፍርሱት" ያለውና አነርሱም ያፈረሱት፣ ኋላ ግን እርሱ፣ "ከሦስት ቀን በኋላ" ስላስነሣው ቤተ "መቅደስ" ነው የሚናገረው። ይህ ደግሞ "ቤተ መቅደስ" የሚለው ቃል፣ ቍሳዊ አካሉን አመላካች እንደ ሆነ የሚያሻማ አይደለም። መንፈሱን ወይም ነፍሱን "አላፈረሱትምና" (አልሞተምና)። በዚህ ምንባብ ቤተ መቅደስ የተባለው የክርስቶስ ቍሳዊ አካል ነው።

"ስመሆኑ፣ ሰውነታችሁ በውስጣችሁ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን? ይህም መንፈስ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት ነው። እናንተም የራሳችሁ አይደላችሁም" (1ቆሮ. 6÷19)። አዲሱ መደበኛ ትርጉም፣ "ሰውነታችሁ" ያለውን፣ ነባሩ ትርጉም፣ "ሥጋችሁ" ይሰናል። በብዙ የሐዲስ ኪዳን ምንባባት "ሶማ" (σῶμα ማለትም "አካል") እና "ሳርክ" (σάρξ, ወይም "ሳርክስ" σαρκός ማለትም "ሥጋ") የሚሉት ቃላት በተሰዋዋጭነት ጥቅም ላይ ውሰው አናገኛለን—አንዳችም የትርጉም ልዩነት ሳይኖራቸው። ስለዚህ ነው፣ "ሶማ ሳርክ ነው፣ ሳርክም ሶማ ነው" የሚባለው[12]። ይህም እንደ ዮሐንስ 2÷21 ግሪኩ፣ "ሶማ"

[11] "ሶማ" (σῶμα) የሚለው የግሪክ ቃል የሚጨበጠውን፣ የሚዳሰሰውን ቍሳዊ አካል የሚያመለክት እንደ ሆነ ልብ ይሰኝ። *James Swanson, Dictionary of Biblical Languages With Semantic Domains: Greek (New Testament), electronic ed. (Oak Harbor: Logos Research Systems, Inc., 1997).*

[12] ለበለጠ መረጃ የሚከተሉትን ስመ ጥር መጻሕፍት ይመለከቷል:— *Louw and Nilda, Greek-English Lexicon of the NT Based on Semantic Domains (New York: United Bible Society, n.d.), 1:147. Bauer, Ardnt, Gingrich, Danker, A Greek-English*

(σῶμα) የሚለው ቃል ነው በዚህም ቦታ ግልጋሎት ላይ ውሉ የምናገኘው። ይህ ደግሞ ቤተ መቅደስ የተባለው ቊሳዊው አካል አንደ ሆነ ያሳያል።

"ደግሞም፣ 'ምግብ ለኾድ ነው፣ ኾድም ለምግብ ነው' እግዚአብሔር ግን ሁለቱንም ያጠፋቸዋል። ሰውነት ለጌታ ነው እንጂ፣ ለዝሙት አይደለም፣ ጌታም ለሰውነት ነው" (1ቆሮ. 6÷13)። ለዝሙት ግልጋሎት ላይ የሚውለው አካል (ግሪክ "ሶማ" σῶμα) "የጌታ ነው" ይለናል። ይህ ደግሞ ቊሳዊው አካል የጌታ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ በግልጽ የሚያሳይ ነው። በአጠቃላይ ሁለመናችን የጌታ መንፈስ ቅዱስ ማደሪያ እንጂ፣ የተወሰነ ክፍላችን አጋንንት የሚያድሩበት በተወሰነው ደግሞ ጌታ ከአጋንንት ጋር በደባል የሚኖርበት አካል የለንም።

ሦስተኛ፣ ጌታ ስለ ብርቱ ሰው በተናገረበት ምሳሌ ላይ፣ "'አንድ ሰው ወደ ጎይለኛ ሰው ቤት ገብቶ ንብረቱን ለመዝረፍ ቢፈልግ፣ አስቀድሞ ያንን ጎይለኛ ሰው ሳያስር አንዴት አድርጎ ይሳካለታል? ኋላም ቤቱን መበዝበዝ ይችላል" (ማቴ. 12÷29 አንዲሁም ሉቃስ 11÷2122 ይመለከቷል)። ለመበዝበዝ ማሰር ወሳኝ ነው ማለት ነው። በሐዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ መሆናቸው እሙን ከሆነ፣ አኛን ለመበዝበዝ በአኛ ውስጥ ያለውን ማሰር የግድ ነው ማለት ነው። እንግዲያው አኛን ለመበዝበዝ፣ በአኛ ውስጥ ያለውን ጎያሉን መንፈስ ቅዱስ የሚያስር ማን ነው?

Lexicon of the New Testament (Chicago: University of Chicago Press, 1979), 169. James Swanson, *Dictionary of Biblical Languages With Semantic Domains: Greek (New Testament)*, electronic ed. (Oak Harbor: Logos Research Systems, Inc., 1997).

አራተኛ፣ በብሉይ ኪዳን፣ በአደባባዩ ላይ ይሆናሉ የተባሉት የእግዚአብሔር ሕዝቦች፣ በሥጋ ላይ ይንጠላጠላሉ ከተባሉት አጋንንት ጋር የተመለሱበት አግባብ ምንድን ነው? ይህን ምስስል ለማበጀት ታሳቢ ያደረግነው ወይም ድጋፍ የሆነን ፅንሰ አሳብ ምን አንደ ሆነ በዝርዝር መጠቀስ ይኖርበታል።

አምስተኛ፣ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስና የሰይጣን ቤተ መቅደስ አንዳችም ግንኙነት እንደሌላቸው መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጻል፣ "የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ከጣዖታት ጋር ምን ስምምነት አለው? እኛኮ የሕያው እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነን፣ አግዚአብሔርም አንዲህ ሲል ተናግሮአል፣ 'ከእነርሱ ጋር አኖራለሁ፣ በመካከላቸውም አመላለሳለሁ፣ አምላካቸው አሆናለሁ፣ እነርሱም ሕዝቤ ይሆናሉ'" (2ቆሮ. 6÷16)። ታዲያ እግዚአብሔር በመንፈሳችን፣ አጋንንት ደግሞ በሥጋችን ውስጥ በደባልነት ሊኖሩ የሚችሉት አግባብ ምንድን ነው? በዚህ የደባል አስተምህሮ ውስጥስ የቤቱ የበላይ ተጠሪ ማን ይሆን?

ሙግት አራት

ከፍተኛ የሆነ የመደባደብ፣ የዝሙት፣ የመጠጥ፣ የስርቆት፣ የቅናት፣ የቊጣ፣ ወዘተ ፍላጎት በአንድ ሰው ውስጥ መኖር፣ አጋንንት እንዳሉበት የሚያመለክት ነው የሚል አስተሳሰብ አለ። ለዚህ አስተሳሰብ ግን የሚጠቀስ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ ወይም ደግሞ የሚቀርብ ሙግት አላውቅም። በሰዎች ሕይወት ውስጥ ይህ ዐይነቱ ጽኑ ፍላጎት ሊከሠት እንደሚችል እሙን ነው። ነገር ግን ይህ ጉዳይ በግለሰቡ ውስጥ አጋንንት አድረዋል ወደሚለው ድምዳሜ እንዴት ሊያደርስ ይችላል? አንድን ነገር መናገርና ለተናገሩት ነገር አጥጋቢ የሆነ ማስረጃ ማቅረብ ደግሞ የተለያዩ ነገሮች ናቸው። ይህ

ዐዋጅ እንጂ ሙግት አንዳልሆነ ልብ ይሏል። እሰካሁን መልሰ የሰጠንው ለሙግት እንጂ፣ መረጃ ሳልቀረበለት አቋም አይደለም። ቢሆንም ነገሩ ክንቱ አሉባልታ መሆኑን በማስረጃ ልሞግት።

ጠንካራ የሆነ ኢሥነ ምግባራዊ ፍላጎት በሰዎች ውስጥ መኖሩ፣ የሰዎችን የንጢአት ጥማት ሊያመለክት ይችላል። ምናልባትም ኢአማኒያን በሆኑ ሰዎች ሕይወት ውስጥ፣ አጋንንት የመኖራቸው ምልክት ነው ሊባል ይችል ይሆናል (ይህንንም ለማለት ማስረጃ ማቅረብ የግድ ያሰፈልጋል፤ ነገር ግን የውይይታችን ርእሰ ሰላልሆነ በወዲህም ሆነ በወዲያ መሞገት አያስፈልገኝም)። ክዚህ ባለፈ ግን፣ ግለሰቡ ላይ የሚታየውን አዘንብሎት ምክንያት በማድረግ አጋንንት አድረውበት ነው ማለት ሰሕተት ነው። ምናልባትም ነውር ነው!

ሰንደኛ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህ የሥነ ምግባር አክሎች የሥጋ ሥራ ሲል ይጠራቸዋል (ሮሜ *8÷13*፤ ቈላ. *2÷8*፤ ገላ. *5÷16*)። ይህ ደግሞ በክርስቲያኖችም ሊታይ ይችላል። በዚህ ረገድ "ሥጋውያን ናችሁ" የተባሉትን የቆሮንቶስ ክርስቲያኖችን በዋቢነት ማየት እንችላለን (ክርስቲያኖች ለመሆናቸው *1*ቆሮንቶስ *1÷2-9* መግለጫ ክቀረበ በኋላ፣ በመካከላቸው መለያየት፡— ክምዕራፍ *1-4*፤ ዝሙት፡—ክምዕራፍ *5-7*፤ መንፈሳዊ አንጭጭነት፡— ክምዕራፍ *8-14*፤ የአስተምህሮ ችግር፡—ምዕራፍ *15* እንደ ነበረ በዝርዝር ተነግሯል)።

እነዚህ ሥነ ምግባራዊ እክሎች፣ በብዙ ምክንያት የእኛ ጠባይ ሊሆኑ ይችላሉ (ክአስተዳደግ፣ ክቤተሰብና ክባልንጀራ ተጽእኖ፣ ካለፍነባቸው መጥፎ ታሪክች ወዘተ)። ነገር ግን ክርስቶስን በመምሰልና እውነተኛ የደቀ መዝሙር ሕይወት በመኖር፣ ክርስቶስን ወደ መምሰል ዕለት በዕለት አያደግን እንሄዳለን። ሥነ ምግባራዊ ለውጦች በሂደት የሚመጡ እንጂ፣ አንድ ሰው ክርስቲያን በሆነበት

ማግሥት እንደ እንጉዳይ በአንድ ጀንበር የሚፈሱ አይደሉም። ለለዚህ በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ የሥነ ምግባር ጉድለቶች መታየታቸው፣ ግለሰቡ አጋንንት እንዳለበት ማስረጃ ነው ማለት ስሕተት ነው።

ሁለተኛ፣ ምናልባት በሰይጣንና በአጋንንት ተጽእኖ፣ ክርስቲያኖች አግባብ ያልሆነ ነገር ሊያደርጉ ይችላሉ። ለዚህም ነው ክርስቲያን በንቃት የአጋንንትን ሽንገላ መመከት እንደሚኖርበት መጽሐፍ ቅዱስ የሚያሰገነዝበው (ኤፌ. *6÷10-18*)። ክርስቲያን በአጋንንት ተጽእኖ ሥር ሊወድቅ እንደሚችል አሙን ነው። ይህ ማለት ግን ክርስቲያን አጋንንት ይገቡበታል ወደሚለው ድምዳሜ የሚያደርስ አይደለም።

ሦስተኛ፣ ዓለም የራሷ የሆነ ሽንገላ እንዳላት መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ዓለም እውነተኛ ደስታ፣ ዘላቂ ርካታ፣ ታላቅ የሆነ ሰላም ወዘተ እሰጣለሁ የሚል ሰብከት አላት። በገንዘብ ብዛት፣ በዕውቀት ብዛት፣ በቍሳቍስ ብዛት ወዘተ ምድራዊ ሕይወት ፍጹም በሆነ ተድላና ፍሥሐ እንደሚሞላ ይታሰባል። በዚህ ሂደት ውስጥ ሰዎች በስሕተት ኢሥነ ምግባራዊ በሆነ ሕይወት ውስጥ ሊወድቁ ይችላሉ (*1*ዮሐ *2÷15*፤ *5÷19*፤ ዮሐ. *2÷1517*፤ ያዕ. *4÷4*፤ ገላ. *5÷17*፤ ሮሜ *722*፤ *1*ጴጥ. *211*)።

ቅዱሳት መጻሕፍት የሰው ልጅ ሙሉ ለሙሉ በንጢአት እንደ ተበላሸ በግልጽ ይናገራሉ። በክርስቶስ ኢየሱስ በተገኘውም አዲስ ሕይወት፣ ሰዎች በምድራዊ ሕይወታቸው ወደ ፍጽምና ይደርሳሉ ተብሎ አይታሰብም። ለለዚህ የሰዎችን ክንቱ ምግባር አይቶ ብቻ፣ አጋንንት አድሮብሃል ማለት ስሕተት ነው።

ሙግት አምስት

ክርስቲያን በተመሳሳይ ኀጢአት ተደጋግሞ ሊወድቅ፣ አግዚአብሔር ራሱ ይቀጣው ዘንድ ለሰይጣን አሳልፎ ሊሰጠው ይችላል *(1ቆሮ. 5÷5፤ 2ቆሮ. 2÷10-11፤ ኤፌ. 4÷26-27)*። "ለሰይጣን መስጠት" ማለት፣ "አጋንንት ይዝቡበታል ማለት ነው" የሚል ሙግት የሚሰነዝሩ ሰዎች አሉ። ክላይ አንዳየናቸው ሁሉ ይህም ሙግት ብዙ የሚያላውሳቸው አይመስልም።

አንደኛ፣ "ለሰይጣን አሳልፎ መስጠት" ወይም "ለሰይጣን ተላልፎ መስጠት" የሚለው ሐረግ በሁለት ቦታዎች ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ ተጠቅሞባቸው አናገኛለን *(ይኸውም:— 1ቆሮ. 5÷5፤ 1ጢሞ. 1÷20)*። በአንደኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 5 ላይ የምናገኘው ሰው፣ የታየበት ችግር ክአባቱ ሚስት ጋር ወሲብ መፈጸሙ ነው *(1ቆሮ. 5÷1-13)*። ይህ ድርጊት በብሉይ ኪዳን የአይሁድ የጋብቻ ሕግ ተኰንኖ አናገኛለን (ዘሌ. 18÷81-13፤ ዘዳ. 22÷22)። ይህ ተግባር፣ በአረማውያኑ ሮማውያን ሕግም የተወገዘ ተግባር ነው። በአንደኛ ጢሞቴዎስ ምዕራፍ 1 የምናገኛቸው ደግሞ፣ ሄሜኔዎስና አሰክንድሮስ የተባሉትን ሰዎች ነው *(1ጢሞ. 1÷18-20፤ 2ጢሞ 2÷17-19)*። የእነዚህ ሰዎች ችግር የተሳሳተ ትምህርት በማስተማር የሰዎችን አምነት ገልብጠዋል *(2ጢሞ 2÷17-19)*።

በርካታ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ምሁራን፣ "አሳልፎ መስጠት" የሚለውን ቃል የሚያብራሩት በሚከተለው መንገድ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ሰይጣንን የገለጸው፣ "የዚህ ዓለም አምላክ" *(2ቆሮ. 4÷4)* አንዲሁም "በዐየሩ ላይ የሚሠራ አለቃ" *(ኤፌ. 2÷2)* አድርጎ ነው። ዓለማችን ደግሞ በሥልጣናትና በኀይላት ቍጥጥር ሥር ወድቃለች *(ቈላ. 2÷15)*። አንደ ጳውሎስ ትምህርት ክርስቶስ በሞቱ ሥልጣናትንና ኀይላትን ሽሯል *(ቈላ. 2÷14-15፤ 1÷13)*።

በአንጻሩ የክርስቶስ አካል በሆነችው በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ አሠራር አለ *(ሮሜ 12÷5-21፤ 1ቆሮ. 12÷12-27፤ ኤፌ. 4÷1-16፤ ቈላ. 1÷18-24)*። ስለዚህ "ለሰይጣን ተላልፈው ይሰጡ" የሚለው ሐረግ፣ ከቤተ ክርስቲያን ኀብረት ይባረሩ ማለት ነው[13]። ስለዚህ በመስክ ምሁራን አስተያየት፣ ግለሰቡ አጋንንት ይገባበታል ማለት አይደለም፤ ከቤተ ክርስቲያን ኀብረት መገለል አንጂ። ከዚህ በተጨማሪ፣ "መንፈሱ በጌታ ቀን ትድን ዘንድ" የሚለው ሐረግ፣ ግለሰቡ ክቤተ ክርስቲያን ቢባረርም፣ በሉዓላዊ ጥበቃው አግዚአብሔር አብሮት አንዳለ የሚገልጽ ነው። ስለዚህ "በጌታ ቀን ድነት የሚያገኘውን" ሰው፣ አጋንንት ቤተ መቅደሱ አድርጎት ነበር ማለት አንዴት ይቻላል?

ሁለተኛ፣ "ለሰይጣን ዕድል ፈንታ አትሰጡት" የሚሉትን ሐረጎች ከዚህ ክፍል ጋር በማያያዝ፣ "አጋንንት ይገባባችኀል ማለት ነው" ብለው የሚያስተምሩ ሰዎች አሉ። ነገር ግን ይህን ሐረግ በዚህ መልኩ ያብራራ የሐዲስ ኪዳን መምህር እኔ አላውቅም *(2ቆሮ. 2÷10-11፤ ኤፌ. 4÷26-27)*። የክፍሎቹ ዐውደ ምንባብ በግልጽ እንደሚያስረዳው ግን፣ በመቈጣት እንዲሁም ይቅር ባለማለት፣ ሰይጣን ክፉ ነገር እንዳያደርግ ዕድል ፋንታ አትሰጡት ማለት ነው።

ሙግት ስድስት

አብዛኛውን ጊዜ ክርስቲያን አጋንንት ሊገባበት ይችላል ለሚለው ትምህርት በማስረጃነት የሚቀርበው፣ የሰዎች የግል

---

13 "ሥጋው ጠፍቶ መንፈሱ በጌታ ቀን ትድን ዘንድ፣ እንደዚህ ዐይነቱ ለሰይጣን ይሰጥ" *(1ቆሮ. 5÷5)*። ማለት፣ "ተቀጪው ሰው የሚንዘበት ኢምግባራዊ አካሄድ ትልቅ ውድቀት/ጥፋት እንደሚያስከትል እንዲገነዘብ ማለት ነው" *W. C. Kaiser, Davids P. H, FF Bruce, Brauch MT, Hard Sayings of the Bible, (Chicago, IL.: Intervarsity Press, 1996).*

ተሞክሮ ነው። ይህንን ይመስላል:— "በመዘምራን ቡድን ውስጥ የምታገለግል ነባር ክርስቲያን፣ አጋንንት ጣላት"፣ "ለብዙዎቻችን ተምላሌት የሆነ ወንድም አጋንንት ዐደረበት" ወይም "የቤተ ክርስቲያናችንን ነባር ዲያቆን አጋንንት ጣለው" ወዘተ። ይህ ዐይነቱ ሙግት ከብዙ አንጻር ስሑት ነው። ዋና ዋና የምላቸውን እነሆ:—

አንደኛ፣ ይህ አካሄድ መሠረታዊ ችግር አለበት። አስተምህሮ የምናዋቅረው ቅዱሳት መጽሐፍትን መነሻ አድርገን እንጂ፣ ተሞክሯችንን መሠረት አድርገን መሆን የለበትም። ተሞክሯችን ከቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት ጋር ተመላለስው ሲገኙ፣ የመጽሐፍ ቅዱሱን ትምህርት በተሞክሮ አዋዝቶ ማቅረብ አግባብ ነው። ነገር ግን ተሞክሮውን መሠረት አድርጉ፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚጻረር ትምህርት ማስተማር ስሕተት ነው። ምክንያቱም መመሪያችን መጽሐፍ ቅዱስ እንጂ፣ የስዎች ተሞክሮ አይደለም። ሌላው እኛ ስለ ጉዳዩ ያለን ዕውቀት ውስን መሆኑ፣ ትምህርታችንን ያልተሟላ ያደርገዋል።

ሁለተኛ፣ አንድ ሰው ስረጅም ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አገልግሏል ማለት፣ ክርስቲያን ነበር ማለት ላይሆን ይችላል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መኖር ስድነት ዋስትና አይደለምና። እግዚአብሔር ብቻ ነው ማን ድነት እንዳገኘ እንዲሁም ማን ድነት እንዳላገኘ የሚያውቀው። በሌላ አገላለጽ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የሆነው ስው ማን ነው የሚለውን ጉዳይ በግልጽ የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነው *(2ጢሞ. 2÷19፤ 1ሳሙ 16÷7፤ ማቴ. 13÷24-30:36-43)*። እኛ ድነት ለማግኘታችን መንፈስ ቅዱስ ስመንፈሳችን እንደሚመለከር ግን አሙን ነው *(ሮሜ 8÷16)*።

ጌታ ለመስቀል ሞት አሳልፎ ሰሰሚስጠው ስው ሲናገር፣ ደቀ መዛሙርቱ፣ "አኔ አሆንን" የሚለውን ጥያቄ ጠየቁ እንጂ፣

"አርሱማ ይሁዳ ነው" ሲሉ አንመለከትም። ምናልባትም ይሁዳን ገንዘብ ያዥ ያደረጉት፣ ጥሩ/ጨዋ ስው ነው ብለው በማስብ ነው። ስለዚህ አንድ ስው ምግባሩን በማየት ድነት ያገኘ ነው ወይም ያላገኘ ነው የሚለው አስተያየት፣ የስዎችን የዕውቀት ውስንነት ያላገናዘበ፣ ልኩን የጣለ አነጋገር ነው።

ሦስተኛ፣ ስዎችን የሚጥሰው አጋንንት ብቻ ናቸው ብሎ ማስብ ስሕተት ነው። ሰዎች በተለያየ ምክንያት ሊወድቁ ይችላሉ። በተስያዩ ዐይነት በሽታዎች፣ የምግብ መበከል፣ በቂ ምግብ ያስመብላት፣ በከፍተኛ ሐዘንና ድንጋጤ ውስጥ መውደቅ ወዘተ ስዎችን ድንገት ሊጥላቸው ይችላል ስዎችን ስለሚጥሉ የበሽታ ዐይነቶች ለፊ ማብራሪያ ከፈለጉ፣ የሕክምና ባስሙያዎችን ይጠይቁ። ስለዚህ የወደቀ ሁሉ አጋንንት ይዘውታል ማለት በእውነቱ የጉድ ነው! ቢያንስ በዛያ አንደኛው መቶ ክፍስ ዘመን የሚኖር ዘመናዊ ስው፣ እንደዚያ ማለብ በፍጹም የለበትም።

አራተኛ፣ የእኛ የኢትዮጵያውን ባህልና አስተዳደግ፣ ነገሮችን ከመንፈስ አንጻር ብቻ የማብራራት፣ በአንጻሩ አአምሮንና የአአምሮ ውጤቶችን የማጥላላት አዝምሞት አስው[14]። ይህ ደግሞ መውደቅን ሁል ጊዜ ከመንፈስ ጋር ብቻ እንድናያይዝ ምክንያት ሆኖናል። በተለያየ ምክንያት የወደቁትን ስዎች አጋንንት እንዳደረባቸው በማስብ ብዙዎችን ክፉኛ ጉድተናል። የወደቁበት ችግር ሳያንስ፣ ምን ይሉኛል በሚል ለቄቃ ውስጥ ከተናቸዋል። ስለዚህ በተስያዩ ምክንያቶች፣ መውደቅን ሁል ጊዜ ከክፉ መንፈስ ጋር ብቻ ማያያዝ

[14] ባህላችን ነገሮችን ከመንፈስ አንጻር መተንተን የሚወድ፣ ምስጠራ ክፉኛ የተጫነው ባህል እንደ ሆነ፣ "ቃለ አንክሮ—ዐደራ ይህን ያንብቡ" በሚለው፣ በተለይ ከገጽ 5 እስከ ገጽ 24 ላይ በስፋት ምገተንበታል።

ትክክል አይደለም። በዚህ አንጻር ክርስቲያኖች ፍጹም ጠንቃቃ መሆን ይጠበቅባቸዋል።

ክርስቲያን አጋንንት ይዝቡበታል የሚሉ ሰዎች፣ ትምህርታችን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው ስማሰት የሚጠቅሷቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባትና የሙግት አካሄዶች ስሑት መሆናቸውን፣ በአስሳ መልክም አንኳ ቢሆን ስማየት ሞክረናል። ክርስቲያኖችም ምንም ዐይነት የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ የሌለውን አንዲያውም መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ የሚያስተምረውን አስተምህሮ የሚቃረን ይህ ዐይነቱን ትምህርት ያስምንም ማቅማማት፣ ወግድ ሊሉ ይጠበቅባቸዋል። አጋንንት፣ ሰይጣን፣ ዳያብሎስ፣ እርኩሳን መናፍስት...ያለ ሁሉ፣ የእርኩሳን መናፍስት ባላንጣ አንዲሁም የአምላክ ባስሚል ነው ብሎ ማሰብ ትክክል አይደለም።

"የዘር ማንዘርሽን መርገም ልስበርልሽ"፣ "የቀጣ መንፈስ ላስወጣልህ"፣ "ስይጣን ስኬት አንዳታገኚ እየተዋጋሽ አንደ ሆነ መንፈስ ቅዱስ ይናገረኛል" ወዘተ የሚሉት ንግግሮች ሁሉ፣ አንዳችም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የላቸውም። ቢያንስ አስካሁን በሁለት ተከታታይ ምዕራፎች ያየናቸው ነጥቦች፣ ይህን አስተሳሰብ በፍጹም አንዳንቀበል አንዲያውም አስተምህሮውን በግልጽ አንድንቃወም የሚያስገነዝቡን ናቸው።

ክፍል ዘጠኝ

በአባይ ነባዮችና በመናፍቃን ተዘወትረው የሚታዩ ባሕርያት የትኞቹ ናቸው?



ሀ. የአባይ ነባዮችና የመናፍቃን አስተምህሮአዊ ባሕርይ

በዚህ ክፍል ስማየት የምንሞክረው፣ በአብዛኞቹ አባይ ነባዮችና መናፍቃን ዘንድ ተዘወትረው የሚታዩትን አስተምህሮአዊ ባሕርያት ነው[1]።

[1] የዚህ ክፍል መሠረታዊ የመግት ጭብጥ በአብዛኛው የተወሰደው፦— *Alan W. Gomes, Unmasking the Cults (Grand Rapids: Zondervan, 1955)* ላይ ነው።

ትክክል አይደለም። በዚህ አንጻር ክርስቲያኖች ፍጹም ጠንቃቃ መሆን ይጠበቅባቸዋል።

ክርስቲያን አጋንንት ይገቡብታል የሚሉ ስዎች፣ ትምህርታችን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው ለማለት የሚጠቅሷቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባትና የሙግት አካሄዶች ስሑት መሆናቸውን፣ በአሰሳ መልክም አንኳ ቢሆን ለማየት ሞክረናል። ክርስቲያኖችም ምንም ዐይነት የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ የሌለውን እንዲያውም መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ የሚያስተምረውን አስተምህሮ የሚቃረን ይህ ዐይነቱን ትምህርት ያለምንም ማቅማማት፣ ወግድ ሊሉ ይጠበቅባቸዋል። አጋንንት፣ ስይጣን፣ ዲያብሎስ፣ እርኩሳን መናፍስት...ያለ ሁሉ፣ የእርኩሳን መናፍስት ባላንጣ እንዲሁም የአምላክ ባለሟል ነው ብሎ ማሰብ ትክክል አይደለም።

"የዘር ማንዘርሽን መርገም ልስበርልሽ"፣ "የቀጣ መንፈስ ላስወጣልህ"፣ "ስይጣን ስሌት እንዲታገኚ እየተዋጋሽ እንደ ሆነ መንፈስ ቅዱስ ይናገረኛል" ወዘተ የሚሉት ንግግሮች ሁሉ፣ አንዳችም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የላቸውም። ቢያንስ እስካሁን በሁሰት ተከታታይ ምዕራፎች ያየናቸው ነጥቦች፣ ይህን አስተሳሰብ በፍጹም አንዳንቀበል እንዲያውም አስተምህሮውን በግልጽ እንድንቃወም የሚያስገነዝቡን ናቸው።

ክፍል ዘጠኝ

በአባይ ነባዮችና በመናፍቃን ተዘወትረው የሚታዩ ባሕርያት የትኞቹ ናቸው?



ሀ. የአባይ ነባዮችና የመናፍቃን አስተምህሮአዊ ባሕርይ

በዚህ ክፍል ለማየት የምንሞክረው፣ በአብዛኞቹ አባይ ነባዮችና መናፍቃን ዘንድ ተዘወትረው የሚታዩትን አስተምህሮአዊ ባሕርያት ነው[1]።

[1] የዚህ ክፍል መሠረታዊ የመግት ጭብጥ በአብዛኛው የተወሰደው፦— *Alan W. Gomes, Unmasking the Cults (Grand Rapids: Zondervan, 1955)* ላይ ነው።

ክፀሓይ በታች ያሉትን የተሳሳቱ ትምህርቶች ሁሉ አጥንተን ልንዘልቅ አንችልም፤ ነገር ግን የአስተምህሮአቸውን ተመሳሳይ ጠባይ ማወቅ፣ ራሳችንን ከመናፍቃን አንቅስቃሴ ለመጠበቅና በአንቅስቃሴው ውስጥ ያሉትን ስዎች ወደ ትክክለኛው መሠረተ እምነት ለማምጣት ትልቅ ቦታ አለው።

የሐስተኛ መምህራንን አስተምህሮአዊ ባሕርይ ስናጠና፣ ሁሉም አባይ ነባዮችና መናፍቃን ሁሉንም ባሕርያት በአኩል ደረጃ ይጋራሉ ማለት አይደለም[2]። ነገር ግን አባይ ነባይ የሆኑት ከክርስትና ትምህርትና ሥነ ምግባር ስላፈነገጡ፣ አስተምህሮውንም ፊት ሰፊት ስለተቃወሙ ነው። አንዳንድ ክርስቲያኖች ከመሠረታዊ አምነታቸው ይልቅ፣ ለልምዳቸው ትኩረት ይስጣሉ። አንዲሁም አንዳንድ ክርስቲያናዊ ተቋሞች፣ የተሳሳተ የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጐም ዘዴ ይከተላሉ። ይህ አካሄዳቸው መሠረታዊውን የክርስትና ትምህርት እስካልተቃረነ ድረስ አንዲሁም የክርስትናን ስም እስካሳጐደፈ ድረስ ልንታገሠው አንችላለን። ምክንያቱም ሁላችንም ብንሆን በማደግ ላይ ያለን ክርስቲያኖች እንጂ፣ ዐድገን ያበቃን አንዲሁም በክርስቲያናዊው አስተምህሮ ላይ ፍጹም የሚባል ዕውቀት የተጐናጸፍን ስዎች አይደለንም።

[2] መናፍቃን መሠረታዊ/ዐበይት የሚባሉ የክርስትና ትምህርቶችን አንድ ወይም ከአንድ በላይ መካድ ሲሆን፣ አባይ ነባዮች ግን መሠረታዊ የሚባሉትን ክርስቲያናዊ አስተምህሮዎች እናምናለን የሚሉ፣ ነገር ግን ንዑሳን ትምህርቶችን የሚክዱ እንዲሁም ክርስትናን በሥነ ምግባራቸው እያስነቀፉ የሚገኙትን ስዎች ነው። ለሰፊ ማብራሪያ፣ "የመሠረታዊ ቃላት ፍካሬና እማሬ" የሚለውን ክፍል ይመለከቷል።

ለ. የአባይ ነባዮችና የመናፍቃን አስተምህሮአዊ ባሕርያት

1. አስተምህሮተ ሥላሴን መካድ

ርቱዕ (ትክክለኛ) የሆነው መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ፣ በአንዱ የአግዚአብሔር ባሕርይ ሦስት ዘላለማዊ አካላት ይኸውም አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ አሉ ብሎ ያምናል። ምናልባት ሁሉም መናፍቃን የሥላሴን አስተምህሮ ይክዳሉ ቢባል ስሕተት አይሆንም። አንዳንድ መናፍቃን የሥላሴን አስተምህሮ ከአረማውያን የመድብለ አማልክት አስተሳሰብ ጋር ሲያመሳስሉት፣ አንዳንዶች ደግሞ አስተምህሮውን አንደሚቀበሉ ያውጃሉ፤ ነገር ግን አስተምህሮውን የሚያብራሩበት መንገድ ክቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት አጅግ የራቀ ነው።

በአንጻሩ የዘመኑ አባይ ነባዮች፣ "እግዚአብሔር ማን ነው?" የሚለው ወሳኝ ጥያቄ፣ የመናፍቃኑን ያህል ሲያሳስባቸው አይታይም። አንዲያውም ለአንዳንዶች ይህ ዐይነቱ ውይይት ጊዜ ማቃጠል ነው። ምክንያቱም ቀዳማይ ትኩረታቸው የመሠረተ አምነት ንጽሕና ላይሆን፣ ንዋይና ዝና መስብሰብ ነውና። በመሠረቱ ብዙ አባይ ነባዮች መሠረታዊውን የክርስትና ትምህርት በቅጡ አያውቁትም። ይህን ለማጣራት አነርሱን በቅርበት ማወቅ አያስፈልግም፤ በማኅበራዊ መገናኛ ብዙኃን ላይ የሚለጥፉትን ስብከት ስዐሥር ደቂቃ ማዳመጥ ብቻ ክበቂ በላይ ነው። አንዲያውም አንዳንዶቹ የት ቤተ ክርስቲያን አንደ ነበሩ አንዲሁም ማን ደቀ መዝሙር አድርጎ አንዳሳደጋቸው የሚታወቅ አንዳችም ነገር የለም። ይህ ደግሞ አስተምህሮአቸው ብቻ ሳይሆን፣ ሥነ ምግባራቸውም ከምርመራ አንዱት አንደ ተደበቀ የሚያሳይ ነው።

አስረጅ

ከምሥረታው በመን ጀምሮ እስከ አሁን፣ የሥላሴን አስተምህሮ በቀጥታ የሚቃወመው "የይሖዋ ምስክሮች" ድርጅት ነው[3]። እንደ ድርጅቱ አስተምህሮ፣ የሥላሴ ትምህርት አረማውያን በክርስትና አምነት የጣሉት አሻራ እንደ ሆነ ይገለጻል[4]።

የሥላሴን አስተምህሮ ከሚክዱ መናፍቃዊ ድርጅቶች መ'ክል "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" ሌላው የሃይማኖት ተቋም ነው። እንደ ድርጅቱ አስተምህሮ አብ እውነተኛው አምላክ ሲሆን፣ ኢየሱስ ደግሞ ወልድ ወይም ልጅ ተብሎ የሚጠራው የራሱ ማንነት የሌለው አብ ላይ የተሰጠፈው ሥጋ ነው። መንፈስ ቅዱስ ደግሞ፣ የአብ ሌላው ስም ነው። አንደ ድርጅቱ ትምህርት "ኢየሱስ ክርስቶስ"፣ "ጌታ ኢየሱስ" ማለት አብና ወልድ ማለት ነው። ኢየሱስ አምላክ ላይሆን፣ አምላክ የተጠቀሰለበት (የተሸፈነበት) ስው/ሥጋ ነው[5]።

ሞርሞኖች የሥላሴን አስተምህሮ እንደሚያምኑ ይገልጻሉ፣ ነገር ግን ስትምህርቱ በሚያቀርቡት ማብራሪያ፣ አምላክን ሦስት አድርገው ያቀርቡታል። እንደ ድርጅቱ አስተምህሮ፣ "ከዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት መካከል አንዱ" የሆነው ጀምስ ታልማግ፣ "አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ሚች እንደ ሆኑት ስብዓዊ ፍጡራን የተለያዩ አካላት

[3] ድርጅቱ "በሥላሴ ማመን ይገባሃልን?" በሚል ርእስ መለስተኛ መጽሐፍ አሳትሞ አሠራጭቷል። የዚህ መጽሐፍ ጸሓፊ "አርዮሳውያን" እንዲሁም "ትምህርተ ሥላሴ መሠረታውያን" በሚል ርእስ ባዘጋጃቸው መጻሕፍት ይህን መጽሐፍ ተችቷል።

[4] "በሥላሴ ማመን ይገባሃልን" (ኒውዮርክ፣ የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር 1989) ገጽ 8-12።

[5] በዚህ የሃይማኖት ተቋም ላይ ሰፊ ማብራሪያ ከፈለጉ የዚህ መጽሐፍ ጸሓፊ "ሰባልዮሳውያን" በሚል ርእስ ያዘጋጀውን ሁለት ቅጽ መጽሐፍ ይመለከቷል።

ናቸው" ይላል[6]። እንደ ድርጅቱ ትምህርት ኢየሱስ አምላክ ሳይሆን፣ አምላክ የሚኖርበት (ያደረበት) ወይም በአምላክ ላይ የተሰጠፈ ሥጋ (ቁሳዊ አካል) ነው።

ሜሪ ቤከር ኤዲ የምትባለው አሜሪካዊት ወይዘሮ የመሠረተችውና "ክርስቲያን ሳይንስ" በመባል የሚታወቀው መናፍቃዊ ድርጅት፣ የክርስቶስን አምላክነት በመካድ የሥላሴን አስተምህሮ ይቃወማል። ወይዘሮዋ— "ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ አይደለም፣ ነገር ግን እርሱ ራሱ አንዳስተማረው የአግዚአብሔር ልጅ ነው"[7] ትላለች። ለእርሷ የእግዚአብሔር ልጅ ማለት አምላክ ማለት ሳይሆን፣ ከአምላክ ያነሰ ማለት ነው።

ዛሬ በዙሪያችን እንደ አንጉዳይ የፈሉት አባይ ነባሮች፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ፣ "የእምነት እንቅስቃሴ" በሚባለው አግድም ዐደግ ትምህርት ክፉኛ የተበከሉ ናቸው። በየስብከታቸው መ'ክል ሁሉ አያፈተለከ የሚወጣው ግልጠታቸውና ትንቢታቸው፣ ታሳቢ ያደረገው የእምነት እንቅስቃሴን አስተምህሮ ነው። ብዙ አባይ ነባሮች፣ "ስው አምላካዊ ባሕርዮት አለው" ወይም ከስብአውያን ከፍ ያለ "ደርዝ"[8] አለን ባዮች ናቸው። እንዲያውም አንዳንዶች በድፍረት እኛ አምላክ ነን አያሉን ነው[9]። ይህ ደግሞ ቅዱላት መጻሕፍት፣

[6] Gomes ገጽ 25 ከ*James Talmage, A Study of Articles of Faith* (salt Lake City: The church of Jesus Christ of Latter-day Saints, 1976), አንቀጽ 1 ገጽ 29-51 ጠቅሶ እንደ ጻፈው።

[7] Gomes ገጽ 26 ከ*Mary Baker Eddy. Science and Health with Key to the Scriptures (boston Trustees Under the Mary Baker G. Eddy, 1934)* ገጽ 361 ጠቅሶ እንደ ጻፈው።

[8] *"dimension"* ለሚለው የእንግሊዝኛ ቃል፣ አነርስ ራሳቸው የሰጡት የአማርኛ ስያሜ ነው። በዚህ ጉዳይ ኤልያስ አብጤ የተባለው አባይ ነባይ በቅርቡ በማኅበራዊ መገናኛ የሰጠውን መግለጫ ይመለከቷል።

[9] ነይሉ ዮሐንስ የተባለውም መናፍቅ፣ እኔ አምላክ ነኝ ሲል በኤልሻዳይ ቱሌቪዥን የተከራከረውን ቪዲዮ በናሙናነት ይመለከቷል።

"እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም የለም" የሚለውን አስተምህሮ በቀጥታ የሚቃረን ነው። ስይጣን "በልዑል እመስላለሁ" እንዳለው፣ አዳምና ሔዋንንም "እንደ አርሱ አንዳትሆኑ ፈልጎ ነው" ብሎ አንዳሳታቸው፣ ዛሬም ሳይጣን በግልጽ፣ "ለው አምላክ ነው" የሚል ትምህርት ይዞብን ብቅ ብሏል። ይህ የአባይ ነባሮች ትምህርት ከትምህርተ ሥላሴ ጋር በጽኑ የሚቃረን ነው።

2. ድነት በእምነት አማካይነት በጸጋ መሆኑን መካድ

ቫን ባስን የተባለው ዐቅብተ እምነት፣ የሁሉም መናፍቃን የትምህርታቸው ማእከል፣ "ራስህን ማዳን አለብህ" የሚለው አስተምህሮ ነው ይላል። ይህ ደግሞ የመናፍቃኑ ብቻ ሳይሆን፣ የአባይ ነባሮቹም ትምህርት ነው። ለአግዚአብሔር ጸጋ የከንፈር አገልግሎት ብቻ እንዲሰጡ ያደረጋቸው፣ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ያከናወነውን (የፈጸመውን) የድነት ሥራ ስለሚያቃልሉ ነው። የክርስቶስ የድነት ሥራ በራሱ ሙሉ በሙሉ የማያድን ከሆነ፣ የጐደለውን በሥራ ማካካስ ወይም መመላት የግድ ይሆናል።

አንዳንድ መናፍቃን የክርስቶስ የማዳን ሥራ፣ አንድ ሰው ወደ አምነት ከመምጣቱ በፊት ያለበትን ነጢአት የማጠብ ኀይል አለው። ነገር ግን ወደ አምነት ከመጣ በኋላ ራሱን ማዳን ያለበት አርሱ ራሱ ወይም የአርሱ ድርጅት ወይም ደግሞ የድርጅቶቹ የአመራር አካላት በሚሠሩት ሥራ እንደ ሆነ አጠንክረው ያስተምራሉ። አንዳንዶች ደግሞ፣ የክርስቶስን የማዳን ሥራ ትናንሽ ነጢአቶችን ብቻ እንጂ፣ ትላልቅ ነጢአቶችን እንደማይጨምር ይገልጻሉ። የተቀሩት ደግሞ የክርስቶስ የድነት ሥራ ለሰው ልጆች ሁሉ እንደማይሆን፣ ነገር ግን እርሱ የጀመረውን ሥራ አነርሱ ከዳር እንደሚያደርሱ ይናገራሉ።

አስረጅ

"ስይሖዋ ምስክሮች"፣ ድነት ለመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ሙሉ በሙሉ ከመገዛትና በሚያወጣቸውም ፕሮግራሞች ተካፋይ ከመሆን ውጪ የሚታሰብ አይደለም[10]።

አንደ ሞርሞኖች ደግሞ አንድ ሰው ድነትን ማስብ ያለበት፣ አምኖ ንስሓ ከገባ በኋላ፣ መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል በድርጅቱ ሰዎች እጅ ተጭኖ ከተጸለየለት በኋላ ነው። እንደ "ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" አስተምህሮ ኢየሱስ፣ አብ ነው ብሎ ማመን (በአብና በወልድ መካከል የማንነት ልዩነት የለም) አንዲሁም በትክክለኛው የጥምቀት ቀመር መጠመቅ ለድነት ወሳኝ ጉዳይ ነው[11]።

ዴቪድ ኮረሽ የተባለው መናፍቅ፣ የኢየሱስ ክርስቶስ የማዳን ሥራው ሕያው የሚሆነው፣ እስከ 31 ዓ.ም ብቻ እንደ ሆነ ገልጸአል። ስለዚህ ከ31 ዓ.ም በኋላ ላለው የሰው ልጆች ኀጢአት አርሱ መሞት አንዳለበት ያስረዳ ነበር[12]።

ጥር 6 ቀን 1920 ዓ.ም በኮርያ የተወለደውና በኮርያ ተራራ ሥር፣ ከራሱ ከክርስቶስ ራእይ ተቀብያለሁ የሚለው ሳን ማዮንግ ሙን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ የአካልና የመንፈስ ድነት ማምጣት ስላልቻለ ይህን ነገር ከዳር አንዲያደርስ አርሱ እንደ ተመረጠ፣ ይህንንም

---

10 ለበለጠ ማብራሪያ የዚህ መጽሐፍ ጸሓፊ፣ "አርዮሳውያን" በሚል ርእስ ያዘጋጀውን መጽሐፍ ይመለከቷል።

11 ድርጅቱ አስተምህሮ ትክክለኛው የጥምቀት ቀመር፣ "በኢየሱስ ክርስቶስ ስም" ነው፣ ይህም ለድነት መሠረት ነው ይላል።

12 Gomes፣ ገጽ 27 ከTalmage. A Study of the Articles of Faith. አንቀጽ 4 ገጽ 107-108 ላይ ጠቅሶ እንደ ጻፈው።

ያበለረው ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ እንደ ሆነ ይገለጻል[13]። ኢየሱስ ክርስቶስ እውን ያደረገው ወይም በሞቱና በትንሣኤው የፈጸመው መንፈሳዊውን ድነት ብቻ ሲሆን፣ ሙን ደግሞ አካላዊውን ድነት ወይም ዐርነት እውን እንዲያደርግ የተመረጠ ሰው ነው።

በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን ውስጥ እኛ "ነቢያት ነን"፣ "ሐዋርያት ነን" የሚሉ ብዙዎች፣ "ከዘር ማንዘር የሚተላለፍ መርገም" እንዳለ እንዲሁም ይህ መርገም በእነርሱ "ቅባታዊ" አገልግሎት እንደሚሰበር ይገልጻሉ። እንዲያውም አንዳንዶች "ቅባታችን የመሰበር ቅባት ነው" ሊሉ ተደምጠዋል። በርግጥ ክርስቶስ ኢየሱስ፣ በጉልኮታ ጣሩ በመስቀል ህማሙ ዕዳችንን ካልከፈለ፣ መርገማችንን ካልሰበረ የክርስቶስ ቤዛዊ ወጀ የተሟላ አልነበረም ማለት ነው። ስለዚህ የሚከተሉትን ተያያዥ ጥያቄዎች መጠየቅ አግባብ ከምንሰውም በላይ ነው:— *(1)* ክርስቶስ ይህን መርገም ካልሰበረው፣ የትኛው ጉበዝ የእኛን መርገም ሊሰብር ይችላል? *(2)* ስእኛስ እነርሱ ይሰብሩልናል ብለን እናስብ፣ ነገር ግን የእነርሱን መርገም የሚሰብርላቸው ወይም የለበረላቸው ማን ነው? *(3)* የአባቱንም ሆነ የቅድመ እያቶቹን የዘር ሐረግ በውል የማያውቅ ክርስቲያን፣ የመርገሙን ዐይነት በምን ዐውቆ ወደ ለበራው ምዕራፍ ሊሸጋገር ይችላል? *(4)* መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ፣ "እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት እሁን ኵነኔ የለባቸውም"፣ "ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን" *(ገላ. 2÷13)* እንዲሁም "ክርስቲያኖች ከዘላለም ሞት ወደሚደነቅ ብርሃን መጥተዋል"፣ "ዳግም በመወለድ የእግዚአብሔር ልጆች ሆነዋል"፣ "የእምላክ ቤተ

[13] ዝኒ. ከማሁ፣ ከ*Samples eta., Prophets of the Apocalypse* ገጽ 205 ጠቅሶ እንደ ጸፈው።

ማደሪያ/መቅደስ ሆነዋል" ወዘተ በሚልበት ዐውድ (ሮሜ 8÷1፣ 1ዮሐ 3÷14፣ 1÷12፣ 3÷16)[14] እነዚህ ስዎች፣ ከሥጋ ወላጆቻችሁ እየተንከባለሰ የሚመጣ መርገም አለባችሁ እንዴት ሊሉን ይችላሉ?

3. የአካል ትንሣኤን መካድ

የክርስቶስ የአካል ትንሣኤ የክርስትና እምነት ያረፈበት ታሪካዊ መሠረት ነው *(1ቆሮ. 15)*። መናፍቃን ደግሞ መሠረታዊ የሆኑትን ክርስቲያናዊ ትምህርቶች ማጣመም ተቀዳሚ ተግባራቸው ነው። ትንሣኤን መንፈሳዊ የሚያደርገው ትምህርት በዚህ ረገድ ዋነኛው ነው። ይህ ትምህርት፣ ክርስቶስ ከሙታን የተነሣው ሬቂቅ መንፈስ ሆኖ ነው የሚል ዐዋጅ አለው። ለዚህ ክሕደት ጥሩ አስረጅ የሚሆኑት "የይሖዋ ምስክሮች" ናቸው። እንደ መጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር፣ "ንጉሥ ክርስቶስ ኢየሱስ በሥጋ ሞቶ፣ የማይታይ ፍጥረት ሆኖ ከሙታን ተነሥቶአል"[15] ይህ ብቻ አይደለም የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት፣ የክርስቶስን ትንሣኤ አስመልክቶ እንዲህም የሚል ግምት አለው፣ "የኢየሱስ ክርስቶስ አካል ወደ ጋዝነት ተሰውጦአል፣ ወይም ለእግዚአብሔር ፍቅር ታላቅ መታሰቢያነት በእንድ ስፍራ ተጠብቆ ነው ያለው"[16]። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ክርስቶስ በአካሉ ሥጋ ከሙታን እንደ ተነሣ ይናገራል[17]።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ፣ ክርስቶስ በ70 ዓ.ም መጥቷል የሚሉ ስዎች

[14] ይህን ጉዳይ (በዚሁ ክፍል) ጎላ በስፋት እንተችበታለን።

[15] *Let God Be True* (1946)፣ ገጽ 22።

[16] *Studies in the Scripture*፣ ገጽ 129፣ ቅጽ 2።

[17] በሙታን ትንሣኤ ላይ ሰፊ ማብራሪያ ከፈለጉ፣ የዚህ መጽሐፍ፣ ጸሐፊ፣ "በሥጋ ትንሣኤ አምናለሁ..." በሚል አርስ ያዘጋጀውን መጽሐፍ ይመለከቷል።

ተነሥተዋል። ክርስቶስ በ70 ዓ.ም ከመጣ ምጽአቱን ተከትሎ እውን ይሆናሉ ከሚባሉት ክሥተቶች መኻል አንዱ ትንሣኤ ሙታን ነው። እነዚህ ግለሰቦች የክርስቶስ ዳግም ምጽአት በ70 ዓ.ም እውን ሆኗል ብቻ ሳይሆን፣ ትንሣኤ ሙታንም ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ነው እያሉ ነው። የክርስቶስን ዳግም ምጽአት በተመለከተ የነገረ መለኮት ምሁራን የተለያየ አስተያየት እንዳላቸው እሙን ነው። ነገር ግን ምጽአቱ በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን ተጠናቋል የሚለውን ትምህርት ለማጽናት፣ ዐበይት የሚባለውን የትንሣኤ ሙታንን አስተምህሮ መካድ ትልቅ ስሕተት ነው፤ ኑፋቄ ነው።

በርካታ አባይ ነባዮች ቍስ አካል እርኩስ መንፈስ ደግሞ ቅዱስ ነው የሚለውን የጥንት ኖስቲኮችን ኑፋቄ ይዘው መጥተዋል። ሥጋ ትንሣኤን የሚጠብቅ በክርስቶስ የተዋጀ የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ/ማደሪያ ሳይሆን፣ ነፍስና መንፈስ የታለፉበት ከርቸሌ/አስር ቤት ነው። "ሰው መንፈስ ነው፤ ነፍስ አለው፤ በሥጋ ውስጥ ይኖራል" ባዮች ናቸው። አባይ ነባዮቹ፣ "አንተ በሥጋ ውስጥ የምትኖር እንጂ ሥጋ አይደለህም" የሚለው ትምህርታቸው ለሥጋ ትክክለኛ ዐቃ ያለመስጠታቸው ብቻ ሳይሆን፣ ሥጋ ማደሪያዬ አንጂ ማንነቴ ካልሆነ፣ "በሥጋ የምሠራው ማናቸውም ኀጢአት እኔን ሊነካኝ ወይም በተጠያቂነት ውስጥ ሊጥለኝ አይችልም" ከሚለው የኖስቲኮች አሮጌ ኑፋቄ ጋር አንድ ዐይነት ነው።

4. መጽሐፍ ቅዱስ ፍጹም ሥልጣናዊ ቃል መሆኑን መካድ

አባይ ነባዮችና መናፍቃን፣ መጽሐፍ ቅዱስ በስሕተት እንደ ተሞላ ይናገራሉ። አንዳንዶች ደግሞ ሥልጣናዊ ቃልነቱን በመቀነስ፣ "አሮጌው ብርሃን" በማለት ይጠሩታል። ይህም፣ "አዲሱ ብርሃን" ከሚሉት ከእነርሱ አስተምህሮ ማነሱን ስለማሳየት ነው።

ሌሎች ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ሥልጣናዊ ቃል እንደ ሆነ ቢናገሩም፣ መጽሐፍ ቅዱስን "የሚተረጕሙት" ከራሳቸው አስተምህሮ ጋር አንዲስማማ አድርገው ነው። አንዳንዶች ደግሞ የመጽሐፍ ቅዱስን ሥልጣናዊነት የሚያቃልሉት፣ ከራሳቸው አስተምህሮ ጋር እንዲጣጣም አድርገው በማብራራት ነው፤ እነዚህ የማብራሪያ ጽሑፎች ደግሞ ከመጽሐፍ ቅዱስ በላይ ይታያሉ።

አስረጅ

"የይሖዋ ምስክሮች" መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ሥልጣናዊ ቃል እንደ ሆነ፣ የአስተምህሮና የሥነ ምግባር መሠረት እንደ ሆነ ይገልጻሉ፤ ነገር ግን ከድርጅቱ አስተምህሮ ጋር እንዲጣጣም ተደርጎ የተዘጋጀው መጽሐፍ (የአዲሱ ዓለም ትርጉም) ድርጅቱ በተደጋጋሚነት የሚያውጀውን ዐዋጅ ከልብ እንዳልተቀበለው የሚገልጽ ነው። የአዲሱ ዓለም ትርጉም ያለምንም ቃለ እግዚአብሔርና የታሪክ ማስረጃ ያህዌ (ጀሆቫ) የሚለውን ስም በአዲስ ኪዳን ምንባባት ውስጥ 237 ጊዜ በላይ መጠቀሙ፤ ድርጅቱ ኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነትና የሥላሴን አስተምህሮ ስመቃወም ምን ያህል እንደ ጠቀመው፤ ቃሉን በተጠቀሙባቸው ዐቃዎች ሁሉ በግልጽ መረዳት ይቻላል።

የሞርሞን ቤተ ክርስቲያን መሥራች የሆነው ዮሴፍ ስሚዝ፣ የእርሱን መምጣት የሚያበሥር "ትንቢት" ይሆን ዘንድ፤ በዘፍጥረት ምዕራፍ 50 ላይ 14 ቍጥሮችን ጨምሮበታል። የሞርሞን የእምነት አንቀጽ፤ "መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል ከተተረጐመ፤ የእግዚአብሔር ቃል ነው፤ እንዲሁም የሞርሞኖች መጽሐፍ የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሆነ አናምናለን"[18] ይላል። ይህ ብቻ

[18] *Gomes* ገጽ 30 ከ*Articles of Faith Article 8* ጠቅሶ እንደ ጻፈው።

አይደሰም ዋልተር ማርቲን፣ ሞርሞኖች መጽሐፍ ቅዱስን ስራሳቸው መጽሐፍ ጋር አንኳ አኩል አንደማያዩት ያስረዳል። ሞርሞኖች ቃለ አግዚአብሔርን የሚያዋርዱት ከመጽሐፍ ቅዱስ እኩል የሚታይ መጽሐፍ በመጨመር፣ ከእነርሱ መጽሐፍ ጋር በማይታረቅበት ቦታ ሁሉ አንዲጣጣም ተደርጎ አንዲተረጉም ከማድረግ ባሻገር፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጨማሪ ምዕራፍና ቊጥር በመጨመርም ነው።

በኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ያሉት ነባሮች፣ "አዲስ መገለጥ አንንገራችሁ ወይስ ስጥቊሩ መጽሐፍ አሮጌ መገለጥ እናንብብላችሁ" ማለት ጀምረዋል። ይህ ቅዱሳት መጻሕፍት ዛሬም ሲናገሩን፣ ሊመክሩን፣ ሊገሥጹን ወዘተ ሕያው/ትኩስ ናቸው የሚለውን መሠረታዊ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት መሠረተ አምነት በቀጥታ የሚጻረር ትምህርት ነው። አንዳንዶች ደግሞ አስተምህሮዎችም ሆኑ ግለሰቦች መመዘን ያለባቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ላይሆን፣ በእነርሱ መንፈሳዊ "ከፍታ" አንጻር አንደ ሆነ በመግለጽ ላይ ናቸው። "እኔ ስባተኛ ክልል ነኝ ስለዚህ አናንተ ስመመዘን ብቃት የላችሁም፣ ያን ዐይነት ምዘና ማካሄድ የሚኖርብን፣ ከፍ ብሰን የምንገኘው እኛ ነን"[19] አያሉ ነው። ይህ አካሄድ የአንድን ትምህርትና የአንድን ግለሰብ አካሄድ የሚመዝነው፣ ቀኖናዊ መጻሕፍት የሆኑት ቅዱሳት መጻሕፍት ሳይሆኑ፣ ግለሰቦች ናቸው ማለት ነው። ይህ የአስተምህሮና የሥነ ምግባር መመሪያ መጽሐፍ ቅዱስ ነው ከሚለው መሠረታዊ የክርስትና አስተምህሮ ጋር በቀጥታ የሚጋጭ ነው።

[19] አባይ ነባይ ኤልያስ አብሔ በቅርቡ ያሠራጨውን ቪዲዮ ይመለከቷል።

5. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላትን፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባልሆነ መንገድ መተርጐም

አብዛኛውን ጊዜ መናፍቃን ለክርስቲያናዊ ቃላት አዲስ ትርጓሜ መስጠት ይወዳሉ። ስለዚህም ነው መጽሐፍ ቅዱስ በ2ቆሮ 11÷4 ላይ፣ ሐዋርያት ከሰበኩት የተሰየ (ገላ 1÷6-9) "ሌላ ክርስቶስ"፣ "ሌላ መንፈስ"፣ "ሌላ ወንጌል" የሚለውን አጠቃቀም ሲጠቀም የሚስተዋለው። አባይ ነባዮችና መናፍቃን ስለ ክርስቶስ፣ ስለ ወንጌል፣ ስለ ድነት ወዘተ አብዝተው ይናገራሉ፣ ነገር ግን እነዚህን ቃላት የሚጠቀሙት መጽሐፍ ቅዱስ ቃሉን በሚተረጉምበት መንገድ አይደለም። ዋልተር ማርቲን እንደሚለው፣ "ብዙውን ጊዜ ከመናፍቃን ጋር የምናደርገው ውይይት ፍሬ አልባ የሚሆነው፣ ስምንወያይባቸው ጉዳዮች ትክክለኛውን ትርጉም (ገለጻ) ባለመጠየቃችን ነው"[20]። ክርስቲያኖች ከመናፍቃን ጋር የሚያደርጉት ውይይት ስኬታማ ሊሆን የሚችለው፣ መናፍቃኑ ቊልፍ የሆኑ ቃላትን እንዴት እንደሚመለከቷቸው አስቀድመው የሚያውቁ ከሆነ፣ አለያም በውይይቱ ወቅት እንዲብራሩላቸው በመጠየቅ ብቻ ነው።

አስረጅ

"የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" አማኞች በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን ይላሉ። አንደ ድርጅቱ አስተምህሮ አብ አግዚአብሔር፣ ወልድ ሰው ብቻ፣ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ የአብ ሌላው ስም ነው። ስለዚህ አንድ "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" አባል በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ አምናለሁ ቢሰን፣ ግለሰቡን በሥላሴ አማኒ ነው ማለት አንዳልሆነ ልብ ልናደርግ ይገባል።

[20] *Martin, Kingdom of the Cults* ገጽ 10።

"ይሖዋ ምስክሮች" ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ መሆኑን እናምናለን ይላሉ፤ ይህን ማለታቸው ግን "ስይጣን የዚህ ዓለም አምላክ"፣ "ሙሴ የፈርዖን አምላክ" በተባለበት ሒሳብ እንጂ፣ "እንደ አብ ሁሉን ቻይ አምላክ ማለት አይደለም" ይላሉ። ስለዚህ "የይሖዋ ምስክሮች" ኢየሱስን አምላክ ቢሉ፣ አምላክ ነው ስትሉ ምን ማለታችሁ ነው የሚል ማብራሪያ እንዲሰጠን መጠየቅ አለብን።

የአምነት እንቅስቃሴን አስተምህሮ የተቀበለ ሰው፣ "ዳግም ተወልደሃል" ብሎ ቢጠይቅ፣ የእግዚአብሔር ልጅ ሆነሃል ማለቱ ሳይሆን፣ "የእግዚአብሔርን ባሕርይ ገንዘብ በማድረግ፣ እግዚአብሔር ሆነሃል" ማለቱ ነው[21]።

6. አባይ ነባሮችና መናፍቃን ድርጅቶቻቸውና መሪዎቻቸው የእግዚአብሔር ብቸኛ እንደራሴዎች እንደ ሆኑ ይናገራሉ

አባይ ነባሮችም ሆኑ የመናፍቃዊ ድርጅት መሪዎች፣ የአግዚአብሔር ብቸኛ ወኪሎች፣ ድርጅታቸውም በአምላክ የሚመራ ብቸኛ ድርጅት፣ አግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የሚገናኝባቸው ድልድዮች፣ የአግዚአብሔር ሥልጣናዊ መገለጥ ተቀባዮች አድርገው ራሳቸውን ያቀርባሉ።

ነገር ግን ይህን የመናፍቃን ዐዋጅ ክርስቶስ፣ "እኔ መንገድና ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም" ከሚለው ወይም የክርስቶስ ሐዋርያት፣ "መዳንም በሌላ በማንም የለም አንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ

[21] ለበለጠ ማብራሪያ የዚህ መጽሐፍ ጸሓፊ ከወንድም ምኒልክ አስፋው ጋር፣ "የእምነት ወይስ የክህደት እንቅስቃሴ?" በሚል ርእስ ያዘጋጁትን መጽሐፍ ይመለከቷል።

የለምና" (ሐሥ 4÷12) በማለት ኢየሱስ ክርስቶስን የአግዚአብሔር ብቸኛ እንደ ራሴ (ወኪል) ከማድረጋቸው ጋር በማነጻጸር፤ ዐዋጁን ወግድ ከማለትም ባሻገር፤ አስተምህሮውን በግልጽ ልንቃወመው ይገባል። ይህ የአምላክን የድነት መንገድ የሚጻረፍ፣ አኩይ ትምህርት ናውና።

አስረጅ

"የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር" በመባል የሚታወቀው "የይሖዋ ምስክሮች" ድርጅት፤ የአምላክ ፍጹም ብቸኛ ድርጅት እንደ ሆነ ይገልጻል። የድርጅቱ ሥልጣናዊ መዋቅር "ታማኝና ልባም በሆኑ ባሮች" እንደ ተሞላ፤ እነዚህም "ባሮች" ወቅታዊ የሆነውን መንፈሳዊ ምግብ ከአምላክ በወቅቱ እንደሚያወርዱ፤ የእግዚአብሔር እንደ ራሴዎች ይታያሉ[22]። ሁሉም "የይሖዋ ምስክር" ያለምንም ጥያቄና ቅድመ ሁኔታ ትምህርታቸውን መቀበልና መታዘዝ ይጠበቅበታል።

"የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" በመባል የሚታወቀው መናፍቃዊ ድርጅት፤ ስዎች የዘላለምን ሕይወት የሚያገኙት፤ በአነርሱ ቤተ ክርስቲያን ጥላ ሥር ሲጠለሉ ብቻ እንደ ሆነ ያስተምራል። ትክክለኛ ትምህርት ባላት እንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አባል መሆን፣ የታላቁን ተልእኮ ሥራ ለማከናወን እንዲሁም በክርስቶስ ኢየሱስ ሕይወት ለማደግ ጠቃሚ ጉዳይ መሆኑ ቅቡል ነው። ይህ ማለት ግን በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያልታቀፈ ሰው ድነት አያገኝም ማለት አይደለም። በየትኛውም የሃይማኖት ድርጅት ጥላ ሥር መጠለል፣ ድነት የማግኛ ቅድመ ሁኔታ አይደለም፤ ክርስቶስ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኝ አድርጎ መቀበል እንጂ።

[22] *You can Live Forever in Paradise on Earth (1982)* ገጽ 191-195።

በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን ውስጥ የምናገኛቸው በርካታ ነባሮች፣ የእነርሱን ፕሮግራም መካፈል አንዲሁም የእነርሱን የቴሌቪዥን ፕሮግራም መከታተል፣ ለመንፈሳዊ ዕድገት ቁነኛ ጉዳይ ከመሆኑም ባሻገር፣ ለሎች "መንፈሳዊ ቅባት የሚቀቡት"፣ "ከዘር ማንዘር መርገም የሚያመልጡት" የእነርሱን ፕሮግራም በአንክሮ በመከታተል እንደ ሆነ ይገልጻሉ። በእንጻሩ ፕሮግራሞቻቸውን ያለመካፈል፣ ከትልቅ የአምላክ በረከት መጉደል ነው።

አንዲያውም በቅርቡ፣ አባይ ነባሮቹ በበርካታ የአሜሪካን ክፍለ እገሮች ቤተ ክርስቲያን በመትከል ለሎች የአገልግሎታቸው ተጠቃሚ እንደሚሆኑ መግለጻቸው፣ ከዚህ አሳብ ጋር የሚጐዳኝ ነው። በርካታ ተከታዮቻቸውም እነዚህን ግለሰቦች፣ "እባት" በማለት መጥራታቸው ሳያንስ፣ ያለእነዚህ ግለሰቦች ክርስትና ሕይወት የማይሞከር ጉዞ እንደ ሆኑ በመግለጽ ላይ ናቸው።

7. ከአስተምህሮአቸው ጋር የሚቃረኑ እውነቶችን፣ ከቁጥ አይቈጥሯቸውም

በርካታ መናፍቃን ከቦዋጃቸው ጋር የሚቃረኑ አውነቶችን ትኩረት አይሰጡአቸውም፣ ወይም አናንቀውና አድበስብሰው ያልፏቸዋል።

አስረጅ

"የይሖዋ ምስክሮች" ሲፈጸሙ (እውነት ሲሆኑ) ያልታዩ በርካታ የሐሰት ትንቢቶችን ተንብየዋል፣ ነገር ግን ይህንን አስተምህሮ እንዲያቁቅሩ ያደረጓቸውን የነቢያት መጻሕፍትን የሚተረጕሙበትን ዘዴ አሁንም አልቀየሩም። የአርማጌዶን ጦርነት በ1914 ዓ.ም ይሆናል ተብሎ ነበር፣ በዚህ ወቅት ሲሆን ሳይችል በመቅረቱ ቀኑ ወደ 1915 ዓ.ም ከዚያም 1975 አና 1981 ዓ.ም

ተሸጋገረ[23]። ነገር ግን ይህን መሰሉን ትንቢት የተናገረው ድርጅት አሁንም ራሱን ከአምላክ አውነተኛ ትንቢት ተቀባይ አድርጎ ይቈጥራል።

ሞርሞኖች "የሞርሞን መጽሐፍ" የተባለውን መጽሐፋቸውን 3,913 ጊዜ ስሕተቱን አርመዋል[24]። ነገር ግን አሁንም ይህ መጽሐፍ የእግዚአብሔር ሥልጣናዊ ቃል፣ "በምድር ላይ ፍጹም ስሕተት የሌለበት መጽሐፍ"[25] ይባላል።

ክርስቲያን ሳይንስ የተባለውን መናፍቃዊ ድርጅት የመሠረተችው ሜሪ ቤከር ኤዲ፣ በሽታ እውነትነት የሌለው ሕልም (ቅዠት) ነው ብትልም፣ እርሷ ራሷ ታማ በዶክተር ትረዳ እንደ ነበር፣ የሕመም ማስታገሻ መርፌ እንደምትወጋ፣ አጥርታ አንድታይ የሚረዳት መነጽር ታደርግ አንደ ነበር፣ በሕመም ምክንያት ብዙ ጥርሶቿን አንዳጣች ይታወቃል[26]። ነገር ግን ዛሬም የኤዲ ተከታዮች በሽታ አውነትነት የሌለው ቅዠት ነው የሚል አቋም አላቸው[27]።

በውስጣችን ያሉ በርካታ አባይ ነባሮች፣ ተከታዮቻቸው ቁጫር እንደሚሆኑ፣ እንዳችም በሽታ እንደማያገኛቸው፣ አርግማናቸው ስለተሰበረ በተትረፈረፈ ሀብት ውስጥ እንደሚዋኙ ይገልጻሉ። ነገር ግን ተከታዮቻቸው ጊዜያዊ የስሜት ብፍታ ካልሆነ በስተቀር እውነተኛ የሆነ ለውጥ በዚህ ረገድ አንዳላገኙ እየታየ ነው። ቁጫር ሲሆኑ የታዩት አባይ ነባሮቹ አንጂ፣ የአባይ ነባሮቹ አገልግሎት ተጠቃሚ አይደለም። ነገር ግን ትላንት የተታለለው

---

[23] *የመጠበቂያ ግንብ* (ሚያዝያ 1 ቀን 1972)። በወቅቱ የነበሩ ብዙ "የይሖዋ ምስክሮች"፣ በዚህ ምክንያት ድርጅቱን ለቀው ወጥተዋል።

[24] *Martin, Kingdom of the Cults* ገጽ 29።

[25] በ1991 ዓ.ም የታተመው "የሞርሞኖች መጽሐፍ" መግቢያ ላይ፣ ጆሴፍ ስሚዝ ያለፈረው ዐረፍተ ነገር ነው።

[26] *Martin, Kingdom of Cults* ገጽ 29።

[27] ዝኒ ከማሁ።

ስው፣ ምናልባት ዛሬ እውነት ሊሆን ይችላል በሚል ይከተላቸዋል። አነርሱም "አንተ እምነት ሰለሌለህ ነው" ወይም "ወፈር ያለ ዐሥራት ስላልሰጠህ ነው" ወይም "ፈውስህ ቀስ በቀስ ይበቅላል ስለዚህ ታገሥ" በሚሉ ወሬሻዎች እየታሹ፣ አብረዋቸው በመዝለቅ ላይ ናቸው። እንዲያውም እንዳንድ አባይ ነባዮች በውል የሚታይ የዐይንና የአካል ችግር እያለባቸው እኛ ዘንድ የመጣ ይፈወሳል እያሉ በድፍረት ያውጃሉ።

8. የዘላለም ኮነኔን (ቅጣት) መካድ

በርካታ አባይ ነባዮችም ሆኑ መናፍቃን፣ የእግዚአብሔር ቃል ስለ ዘላለም ቅጣት የሚያስተምረውን እውነታ አይቀበሉም። አንዳንዶች ለምሳሌ የመላለማዊ *(universalism)* ትምህርት አራማጆች፣ የሰው ልጆች ሁሉ የዘላለምን ሕይወት እንደሚያገኙ ሊያስተምሩ ለሌሎች ደግሞ፣ አምላክ ኀጢአተኞችን ወደ አለመኖር ደረጃ ይወስዳቸዋል ("ብን ብለው እንዲጠፉ *annihilate* ያደርጋቸዋል" ይላሉ)።

አስረጅ

"የይሖዋ ምስክሮች" በድርጅት መልክ ተዋቅረው መንቀሳቀስ ከጀመሩ 120 ዓመት ይሆናቸዋል። በእነዚህ ዘመናት ሁሉ ኀጢአተኞች ዘላለማዊ ቅጣት ይጠብቃቸዋል የሚለውን ትምህርት አጥብቀው ሲቃወሙ ኖረዋል። የድርጅቱ ሁለተኛ ፕሬዝዳንት የነበረው ጆሴፍ ፍራንከሊን ራዘርፎርድ፣ "የዚህ [የዘላለም ቅጣት] እግዚአብሔርን የማያከብር አስተምህሮ ጠንሳሽ ሰይጣን ነው። ይህንን ያደረገበትም ምክንያት፣ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል

እንዳያነቡ ለማስፈራራት እግዚአብሔርን እንዲጠሉ ለማድረግ ነው"[28] ብሎአል።

ዩኒቴሪያን ዩኒቨርሳሊስት የተባሉት መናፍቃን፣ የሥላሴን አስተምህሮ ብቻ ሳይሆን፣ የዘላለም ኮነኔንም ይቃወማሉ። እንዲያውም የድርጅቱ መሠረተ እምነት ሰው ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዳለው ይገልጻል[29]።

በርካታ አባይ ነባዮች በኀጢአት ውጤት ወይም የተፈጥሮ ሕግጋት በሆኑት በመንሥኤና በተገብሮ አንኳ የሚያምኑ አይደሉም። ማጣትንና ህማምን ሁል ጊዜ የሚያብራሩት ከመርገም ጋር እያይዘው ብቻ ነው። ስንፍና፣ እባካችነት፣ ያለማወቅ/ያለመማር፣ መልካም አስተዳደር ያለመኖር፣ የሰላም ዕጦት ወዘተ የድኽነት ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ።

9. ከአስተምህሮአቸው ይልቅ ሰልምምዳቸው ትኩረት መስጠት

መናፍቃንም ሆኑ እባይ ነባዮች፣ ከእውነትና ከምክንያታዊ አስተሳሰብ ይልቅ፣ ለስሜት ከፍተኛ ቦታ ይሰጣሉ። በዚህ መሰረ እንቅስቃሴ ውስጥ ያሉ ሰዎች፣ አስተምህሮአችን ከእግዚአብሔር ቃል የመነጨ ነው ወይ? ለሚለው ጥያቄ ሳይሆን፣ ጥሩ ስሜት ተሰምቶኛል ወይ? ከቀድሞ ልምምዴ ጋርስ ይስማማል ወይ? ለሚለው ትልቅ ትኩረት ይሰጣሉ። ስሜትና የግል ልምምድ መጥፎ ነው ለማለት አይደለም። ነገር ግን ስሜትም ሆነ ልምምድ ተገቢ

---

[28] *Rutherford, Let God Be True* ገጽ 79። በቅንፍ ያለውን አይጨምርም። ይህን ትምህርት አስመልክቶ ያለውን የድርጅቱን ትምህርት ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር ገጽ 98-100፣ 168-175፣ 375-379፣ 382-383 እንዲሁም *You Can Live Forever in Paradise on Earth* ገጽ 76-89 ይመልከቱ። ይህን ርእሰ ጉዳይ ጸሓፊው "አርዮሳውያን" በተሰኘው መጽሐፉ በሰፋት መርምሮታል።

[29] *Mather and Nichols, Dictionary* ገጽ 286።

የሆነውን ስፍራ መያዝ አለባቸው። ይኸውም ለቃለ እግዚአብሔር ትምህርት እንዲሁም ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ለሚጣጣሙ ላይንላዊና ምክንዮአዊ ማስረጃዎች መገዛት አለባቸው፦—

"እግዚአብሔር አምላክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም ሐሳብህ *(mind)* ውደድ" ይላል (ዘዳ. 6÷5፤ ማቴ. 22÷37፤ ማር. 12÷30፤ ሉቃ. 10÷27)። ይህ ዐይነቱም አምልኮ እውነትን ከስሜት ጋር አጣምሮ የያዘ ነው። የክርስትና፣ እውነት የተመሠረተው በማይነቀሉ በማያገሠሡ እውነታዎች ላይ እንጂ፣ በስሜት ላይ እንዳልሆነ ሊጠፋን አይገባም።

አስረጅ

የእባይ ነባዮችን አስተሳሰብ አስተምህሮ በስፋት የቀረጸው፣ "የአምነት እንቅስቃሴ ትምህርት" ዕውቀትን "የስሜት ዕውቀት" እና "የመገለጥ ዕውቀት" ብሎ በመክፈል፣ ሃይማኖታዊ እውነታዎች በአምስቱ የስሜት ሕዋሳቶቻችን የምንገበያቸው ሳይሆኑ፣ በመገለጥ ብቻ የምናውቃቸው እንደ ሆኑ ያስተምራል። እንዲያውም ወደ "መገለጥ ዕውቀት" ለመግባት በስሜት ሕዋሳቶቻችን የሚታወቁትን እውነታዎች "መካድ" እንደሚያስፈልግ አጠንክሮ ያስረዳል። እንደዚህ እንቅስቃሴ ትምህርት ከሆነ፣ የስሜት ሕዋሳቶቻችንንም ሆነ አእምሮአችንን መጠቀም ሥጋዊነት ነው፤ የእግዚአብሔር እውነት በአእምሮ አንዲሁም በስሜት ሕዋሳት ፈጽሞ እይታወቅም ባይ ነው። ከዚህ የተነሣም ክርስቲያናዊ እውነቶችን በቃለ እግዚአብሔር መመርመር አይፈቀድም[30]። በእንቅስቃሴው ተከታዮች ዘንድ አንደ ትልቅ የእግዚአብሔር ለው የሚቈጠሩት ኬኔት ሐገን፣ አት·ተች፤ ግን "እግዚአብሔር እንዲገልጥልህ ጸልይ"[31] የሚለው አነጋገራቸው

[30] *Kenneth Hagin, I Believe in Visions (Old Tappan N. J.: Fleming H. Revell, 1972).*

[31] *Kenneth Hagin, The Voice of Healing (Apr. 1963).*

በጽሑፋቸው ተደጋግሞ የሚዘወተረው፣ መንፈሳዊ እውነትን በእእምሮአችን መረዳት አንችልም ስለሚሉ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በስሜት ሕዋሳቶቻችን የምናውቃቸው ዕውቀቶች፣ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊው መገለጥ ጋር ይቃረናሉ የሚል ትምህርት የለውም። አንዲያ ከሆነ በስሜት ሕዋሳቶቻችን የምናውቃቸው ዕውቀቶች ሁሉ ቅዠት ናቸው ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስን አንብበን የምንረዳውም በስሜት ሕዋሳቶቻችን አንጂ፣ በመንፈስ እይደለም[32]።

ሞርሞኖች፣ "መጻሕፍትንም ሲከፍትልን ልባችን ይቃጠልብን አልነበረምን" (ሉቃ 24÷32) የሚለውን ጥቅስ በመጥቀስ፣ እውነት እውነት መሆኑ የሚረጋገጠው፣ "ልባችን የሚቃጠልብን" ከሆነ ብቻ ነው ይላሉ። ለሞርሞኖች የእውነት መመዘኛው ሚዛን "የልብ መቃጠል" እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ ወይም ደግሞ እመክንዮ አይደለም።

ብዙ ክርስቲያኖች የትምህርተ ወንጌልንም ሆነ የስብከተ ወንጌልን ትክክለኝነት የሚያጸድቁት፣ በወቅቱ በሚለማቸው ስሜት ነው። በተሰይ እሳት ልሶ እሳት ጉርሶ የሚያወራ ስው ሁሉ በመንፈስ እንደ ተነዳ ይታሰባል።

10. ከእግዚአብሔር በቀጥታ ተቀብለናቸዋል ለሚሏቸው መገለጦችና ራእዮች ከፍተኛ ትኩረት መስጠት

እባይ ነባዮች አንዲሁም መናፍቃን በተሰይም የእንቅስቃሴው መሪዎች፣ ከእግዚአብሔር ጋር አስን ከሚሉት ቀጥተኛ ግንኙነት የተነሣ፣ ራእይና መገለጥ እንደሚወርድላቸው እንዲሁም እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚሆነውን መንፈሳዊ ምግብ የሚሰጠው

[32] በዚህ ረገድ ነይሉ ዮሐንስ አንዲሁም የእምነት እንቅስቃሴ መምህራን የሚያስተምሩትን ትምህርት፣ ከድረ ገጾች ላይ፣ በስፋት መመልከት ይቻላል።

በእነርሱ በኩል ብቻ አንደ ሆነ ይገልጻሉ። አብዛኛውን ጊዜ መገለጦቻቸውና ራእዮቻቸው ትኩረት የሚያደርጉት የመጨረሻውን ዘመን በተመለከተ ሲሆን፣ የእነርሱ ዕጣ ፈንታም ምን እንደ ሆነ፣ ከራእዩና ከትንቢቱ ጋር ተያይዞ ይቀርባል። ይኸውም እነርሱ ዋና ተዋናይ እንደ ሆኑ፣ ተከታዮቻቸውም በሂደቱ ውስጥ ቁልፍ ሚና እንዳላቸው የሚያስረዳ ነው። ቃለ እግዚአብሔር፣ "ሁሉንም መርምሩ፤ መልካሙን ያዙ" *(1ተሰ 5÷21)* ይሰናል፤ የተነገረው ትንቢት እንደ ተባለው ካልተፈጸመ፣ ትንቢቱም ሆነ ነቢዩ ከእግዚአብሔር አይደሉም *(ዘዳ 18÷22)*። የአንድ ትንቢት ወይም መገለጥ ትክክለኛነት የሚረጋገጠው ትንቢቱ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር በመስማማቱ እንዲሁም ተፈጸሚነት በማግኘቱና ባለማግኘቱም ጭምር ነው (ኢሳ. *8÷20*)።

አስረጅ

የሞርሞንን እምነት የመሠረተው ጆሴፍ ስሚዝ፣ በ*1820* ዓ.ም ላይ እግዚአብሔር አብን እንዲሁም ወልድን በራእይ አንደ ተመለከተ ይገልጻል። ስሚዝ በዚህ ራእይ፣ ከየትኛውም ሃይማኖታዊ ድርጅት ጋር እንዳትገጥም ተብያለሁ ባይ ነው። ምክንያቱም፦— "ሁሉም የሃይማኖት ድርጅቶች የተሳሳቱ ሰለሆኑ" እንዲሁም "የሃይማኖት መግለጫቸው ሁሉ ጸያፍ ነው"[33] ባይ ነው። በመስከረም *21* ቀን *1823* ዓ.ም ሞሮናይ የተባለው መልአክ አንደ ተገለጠለትና፣ የሞርሞን መጽሐፍ ምን መሆን እንዳለበት የሚገልጹ የወርቅ ሳሕኖች አንደ ሰጠው ተናገረ። ሞሮናይ የተባለው መልአክ በ*1827* ዓ.ም ዳግም ይገለጥለትና ሳሕኖቹን ቁፍሮ በማውጣት የትርጉም ሥራ አንዲጀምር ፈቃድ ይሰጠዋል። በወርኀ ግንቦት *1829*

[33] *Gomes* ገጽ *37* ከ*Pearl of Great Price (1851, rev. ed, salt Lake City: Church of Jesus Christ of Latter-day saints, 1981):* 19 ላይ. ጠቅሶ እንደ ጻፈው።

ዓ.ም መጥምቁ ዮሐንስ፣ ሰሰሚዝና ሰኦሊቨር ኮድሪ ይገሰጥሳቸውና አሮናዊ ክህነት አንደ ተሰጣቸው ያረጋግጥላቸዋል[34]። ጆሴፍ ስሚዝ ከሞተ በኋላ፣ ድርጅቱን የመምራት ኀላፊነት የተረከበውና "የዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት" መሪ የሆነው ብሪጋሃም ያንግ፣ "እኔ ሰሰራሴ ያየሁትና የሰማሁት በርካታ መገለጥ አለኝ፤ እነዚህም ነገሮች አውነት እንደ ሆኑ ዐውቃለሁ፤ በምድር ላይ የሚኖር አንድም ሰው እነዚህን ነገሮች ትክክል አይደሉም ማለት አይችልም"[35] ሲል ይገልጻል።

ይህ ብቻ አይደለም የሞርሞን ሐዋርያት፣ አውን ሲሆኑ ያልታዩ በርካታ ትንቢቶችን ተናግረዋል። በአሜሪካን አገር ተከሥቶ ሰለነበረው የእርስ በርስ ጦርነት፣ ጆሴፍ ስሚዝ ታሳቋ ብሪታንያ ከለሜኑ ክፍል ጋር ተሰልፋ የደቡቡን ክፍል እንደምትወጋ የሚገልጽ ትንቢት ተናግሮ ነበር፤ ከጦርነቱ በኋላ ግን ትንቢቱ ፍጹም ሐሰት መሆኑ ተረጋግጦአል[36]።

"የይሖዋ ምስክሮች" ከ*1935* ዓ.ም ጀምሮ የስብከት አቅጣጫቸውን በመቀየር፤ "ምድር ገነት ትሆናለች" አንዲሁም "ሰማያዊውን አካል የሚወርሱት የቅቡዓን (የ*144* ሺህ) ቊጥር ሞልቶአል" ማለት ጀምረዋል። ይህን ማለት የጀመሩት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ ሰላላቸው ሳይሆን፣ የድርጅቱ ፕሬዚዳንት የነበረው ጆሴፍ ፍራንክሊን ራዘርፎርድ፤ በ*1935* ዓ.ም "የቅቡዓን ቊጥር

[34] መጽሐፍ: ቅዱስ አሮናዊ ክህነት የተሰጣቸው ለሌዊ ልጆች ብቻ እንደሆነ ይነግረናል (ዘፀ. *4÷14፤ 29÷1*)። እግዚአብሔር አምላክ ይህን የክህነት አገልግሎት ለሌዊ ልጆች የሰጣቸው፣ የእስራኤል ልጆችን ወክለው ለእግዚአብሔር መሥዋዕት እንዲያቀርቡ ነው (ዕብ. *5÷1-3*)። ከኢየሱስ ሞት በኋላ ሌዋዊም ሆነ አሮናዊ ክህነት አያስፈልግም።

[35] *Gomes* ገጽ *38*።

[36] *Mc Dowell and Stewart, The Deceivers,* ገጽ *104-122*።

ሞልቶአል፣ ከአሁን በኋላ "የይሖዋ ምስክር" የሚሆኑ ስዎች የሚወርሱት ምድርን ነው" በማለት ስለተናገረ ብቻ ነው[37]።

የዩኒፊኬሽን ቤተ ክርስቲያን መሥራች የነበረው ስን ምዮንግ ሙን፣ በ1936 ዓ.ም ኢየሱስ እንደ ተገለጠለትና ኢየሱስ የጀመረውን ሥራ አርሱ ከዳር እንደሚያደርስ እንደ ተነገረው ይገልጻል[38]።

የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናትን በማመስ ላይ የሚገኙት ዘመነኞቹ አባይ ነባዮች፣ ትንቢታችሁ ለምን አልተፈጸመም የሚለውን ጥያቄ የሚያዳፍኑት፣ "እኛ ከደረስንበት መንፈሳዊ ዓለም አልደረሳችሁም"፣ "ብንነግራችሁም አይገባችሁም" እያሉ ነው። አንዳንዶች ደግሞ፣ "የነቢይን ትንቢት መመርመር የሚችለው ነቢይ ብቻ ነው" እንዲያውም "በእኩል መንፈሳዊ ደርዝ/ደረጃ የሌለ ነቢይ"፣ ከእርሱ በላይ የሆነውን ትንቢት አንኳ መመርመር አይችልም ይላሉ[39]። ይህ ነገሩን ፍጹም ምስጢራዊ በማድረግ፣ ራሳቸውን ከመጽሐፍ ቅዱስ ምርመራ ለመደበቅ የሚያደርጉት ጥረት እንደ ሆነ፣ አማኙ ማኅበረሰብ በግልጽ ሊረዳ ይገባዋል። መጽሐፍ ቅዱስንም መሠረት በማድረግ ግብራቸውንም ሆነ ትንቢታቸውን በጥልቀት መመርመር ይጠበቅበታል።

11. ለድንቆች፣ ለምልክቶችና ለተአምራት ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣሉ

ሁሉን ማድረግ የሚችለው አግዚአብሔር፣ በእውነተኛ ክርስቲያኖች አማካይነት ድንቅና ተአምራትን ሊያደርግ ይችላል። ነገር ግን መሠረታዊውን የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ የሚክዱ ስዎች በአግዚአብሔር ኀይል ተአምራትን ሊያደርጉ በፍጹም

[37] ተስፋዱ ሮበሌ፣ *አርዮሳውያን*።

[38] *Gomes* ገጽ 38።

[39] የኤልያስ አብሴን ቪዲዮ ይመለከቷል።

አይችሉም (ዘዳ. 18÷22፣ ኢሳ. 8÷22)። ነገር ግን ተአምራትን ካደረጉ ተአምራቱ ከአግዚአብሔር ሳይሆን፣ እንደ ሐዋርያው ቃል፣ "በሐስተኞች ድንቆችም በዐመፅም መታለል ሁሉ እንደ ስይጣን አሠራር ነው" (2ተስ. 2÷9-10)።

አስረጅ

ክርስቲያን ሳይንስ የተባለው መናፍቃዊ ድርጅት፡— ፈውስ ሊካሄድ የሚችለው፣ "በክርስቲያን ሳይንሶች ቀመር ብቻ ነው" የሚል አስተምህሮ አለው። ድርጅቱ፣ "ኤ ሴንችሪ አፍ ክርስቲያን ሳይንስ ሂሊንግ" በግርድፉ ሲተረጐም፣ "የክርስቲያን ሳይንሶች ፈውስ በአንድ ምዕተ ዓመት" በሚል ርእስ አዘጋጅቶ እያሠራጨ ባለው መጽሐፍ፣ በክርስቲያን ሳይንሶች የፈውስ ቀመር ተፈወሱ የተባሉትን ግለሰቦች፣ "ምስክርነት" አቅርቦአል[40]።

"የሕዝቦች ቤተ መቅደስ" (ፒፕልስ ቴምፕል) የተባለው መናፍቃዊ ድርጅት መሥራች የሆነው ጂም ጆንስ፣ ከ40 የሚበልጡ ለምኖን ከሙታን እንዳስነሣ ይገልጻል[41]። ጆንስ በቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ ውስጥ በሚገኘው የመኪኖች ማቆሚያ ላይ ተኮስ እንደ ተከፈተበት፣ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ የነበሩትም ስዎች ተኮሱን እንደ ስሙ፣ ከዚያም በደም የተጨማለቀና ሁለት ቀዳዳ ያለበት ሸሚዝ በእጁ ይዞ፣ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ለነበሩት ስዎች፣ ሁለት ጊዜ በጥይት ተመትቶ ከሞተ በኋላ ራሱን ከሞት እንዳስነሣ ገልጾአል[42]። ከጆንስ ጋር በእዚያ የነበሩ ስዎች ራሳቸው፣ ባደረጉት

[40] *Gomes* ገጽ 39 ላይ ከ*A Century of Christian Science Healing* (Boston: Christian Science publishing Society, 1966) ጠቅሶ እንደ ጻፈው።

[41] *Gomes* ገጽ 39 ከ*Sparks, The Mindbenders,* ገጽ 264-265 ጠቅሶ እንደ ጻፈው።

[42] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 39።

ይህ ማስተባበያ አዋጪ ብቻ ሳይሆን፣ ስሕተት መሆኑንም ቢቢሲ በስፋት ተሳልቄበታል። የሚያሳዝነው ግን፣ ግለሰቡ ትክክል ሊሆኑ ያልታዩ ትንቢቶችን በርካታ ጊዜ እንደ ተናገረ፣ የመገናኛ ብዙኃን ገልጸዋል (ለምሳሌ የእንግሊዝ ፕሪምየር ሊግ የእግር ኳስ ጫወታን በተመለከተ ያስተላለፈው "ትንቢት" ሊይዝለት አልቻለም፤ ለመሆኑ ግን፣ የእግር ኳስ ጫወታን በተመለከተ ትንቢት የሚያመጣው አምላክ ምን ዐይነት ነው? ይህስ ሁኔታ ለዎችን ወደ ድነት ወይም ወደ መንፈሳዊ ብስለት እንዴት ሊያመጣቸው ይችላል?)። ዛሬም ግን በርካታ ኢትዮጵያውያንን ጨምሮ እጅግ ብዙ ለዎች፣ ግለሰቡ ትክክለኛ ነቢይ ነው የሚል አቋም አላቸው። እንዲያውም ከሁለት ዓመት በፊት፣ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ባርኩቱን ይስጠን፣ ችግራችንን ይፍታልን የሚሉ ለዎች ጥያቄ አቅርበው፣ አብያተ ክርስቲያንንና አገልጋዮችን ብዙ እንዳሚገተ የምንረሳው አይደለም። የወንጌላውያን እብያተ ክርስቲያናት ጎብረት፣ ይህን ሰው ለመጋበዝ ቊርጥ ውሳኔ ከማድረጉ የተነሣ፣ የጎብረቱ አባል የሆነችው የመሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን፣ "ይህ ሰው ተጋብዞ የሚመጣ ከሆነ፣ ከጎብረቱ ጋር ያለኝን አባልነት አቋርጣለው" የሚል ማስጠንቀቂያ በመስጠቷ የግለሰቡ ግብኣ እንደ ተሰረዘ ውስጥ ዐዋቂ ምንጮች ይገልጻሉ።

በዚህ በአሜሪካን አገር የሚኖሩ ኤልያስ አብጤ የተባሉ አባይ ነባይ፣ የባልንጀራቸውን (እንዲያውም "መንፈሳዊ እባቱ ነኝ" የሚሏቸውን) የአስራኤል ዳንላ ትንቢት (ማለትም ነባዮች በኢትዮጵያ ጋ'ርላማ በመግባት በአገሪቱ ዕጣ ፈንታ ላይ ይወስናሉ የሚለውን ትንቢት) ለምን አልተፈጸመም የሚለውን ጥያቄ በተመለከተ የለጠው ማብራሪያ፣ ልክ እንደ ቲ.ቢ. ጆሽዋ ይህን ማብራሪያ ለመሸከም፣ "መንፈሳዊ ዐቅማችሁ አይፈቅድም፣ አርሱን መመርመር የምችለው አኔ ብቻ ነኝ፣ ምክንያቱም እኔ ለባተኛው ክፍታ ላይ ደርሻለሁ" ብለውናል።

በመሠረቱ "በአፍቅሮተ ነባይ" የተለከፈን ሰው፣ በቃሉ ሥልጣናዊነት ታምኖ መጽሐፍ ቅዱስን መመሪያው አድርጎ መኖር አጅግ አንደሚከብደው ከላይ በስፋት ሞግቻለሁ። ማንን ለማባ፣ ወደ ፊት ክሌጅ ገብቼ ምን ዐይነት ትምህርት ላጥና፣ ለሙሉ ጊዜ አገልግሎት ራሴን መለየት አለብኝ ወይስ የለብኝም ወዘተ የሚሉ ጥያቄዎችን በተመለከተ፣ ቃለ አግዚአብሔርንና የበላል ለዎችን ምክር እንዲሁም ጸሎት እንጂ፣ ትንቢት መመሪያ ማድረግ እንደማይገባ በዚህ አጋጣሚ በግልጽ መናገር እፈልጋለሁ።

"ጌታ እገሊትን ለጥቶሃል፣ አግባት"፣ "እምላክ ሥራሽን ትተሽ እንድታገለግዪው ይፈልጋል" ወዘተ የሚለውን ትንቢት ለምተው የማታ ማታ ቀኑ የጨለመባቸው፣ ከፍተኛ ተስፋ መቊረጥ ውስጥ የወደቁ እጅግ በርካታ ለዎችን አውቃለሁ። ወገኖቼ የአባይ ነባዮች ትንቢት በጀማም ሆነ በእያንዳንዱ ምዕመን ሕይወት ውስጥ ያመጣው ውድመት እንዲህ በቀላሉ ተነግሮ፣ ተዘክሮ የሚያልቅ እንዳይደለ በግልጽ ሊታወቅ ይገባል። የሠላሳ ሁለት ዓመት የክርስትና ሕይወቴ እንዲሁም የሃያ እምስት ዓመት የሙሉ ጊዜ የወንጌል አገልግሎት ቆይታዬ በዚህ ረገድ ያስተማረኝ ትምህርት እጅግ የትዬለሌ ነው። የብዙ ለዎችን እንባና ጸጸት አይቻለሁ። ይህን የምልበት ቀዳማይ ምክንያት ነባዮቹን ለማሳጣት ሳይሆን (ቀድሞውንስ በእኩይ ምግባራቸው የሚጸጸቱ ለዎች መች ሆኑና?)፣ ክርስቲያኑ ማኅበረሰብ ከፍተኛ ጥንቃቄ እንዲያደርግ የመግለጽ ክርስቲያናዊ ኀላፊነት አለብኝ ከሚለው ጽኑ እምነቴ የመነጨ ምክር ነው። ወገን የሚሊዮኖች እንባና ለቄቃ ትምህርት ሊሆነን ይገባል። በምድር ላይ ለመኖር የተለጠንን ምጥን ሕይወት፣ የጸጸትና የቊጭት ማለ ልናደርጋት አይገባም። ባወጣው ያውጣው እየተባለ የሚጠለዘው የአባይ ነባዮች ትንቢት፣ ክቡር ሕይወታችን መበላሸት የለበትም። እነርሱ ያሻቸውን ብለው ያለአንዳች ጸጸት ይኖራሉ፤

ይብላኝ ትንቢታቸው ትክክል ነው በሚል፣ የሕይወቱን ቢጋር በዚያ አንጻር ለሚያደራጀው ምስኪን።

አስረጅ

"የይሖዋ ምስክሮች" የአርማጌዶን ጦርነት 1914 ከዚያም 1915 ከዚያም 1918 በኋላም 1975 ዓ.ም ይሆናል ብለው ነበር[47]። "የይሖዋ ምስክሮች" ከዐሥራ አራት የማበልጡ ይህን መሰል ትንቢቶች አስተላልፈዋል[48]። ነገር ግን አንዱም አውነት ሆኖ አልታየም።

"የዳዊት ሥር" *(Branch Davidians)* የሚባለውን መናፍቃዊ ድርጅት የመሠረተውና ከአርሱ ሞት በኋላ የድርጅቱ ነቢዩት የሆነችው ፍሎረንስ የምትባለው ባለቤቱ፣ ሚያዝያ 22 ቀን 1959 ዓ.ም በራእይ 11 ላይ የተጠቀሰው የ1260 ቀናት መጠናቀቂያና ሕዝቅኤል 9 ላይ የተጠቀሰው የፍርድ ቀን መጀመሪያ ይሆናል ብላ ነበር[49]። ከፍሎረንስ ትንቢት የተነሣ ከ1000 የሚበልጡ የድርጅቱ አባላት ያላቸውን ሽጠው፣ ገንዘባቸውን ለቤተ ክርስቲያን ከለጡ በኋላ፣ በቀርሜሎስ ተራራ ላይ ተሰብስበው ነበር[50] (ትንቢቱ አውነት የሚሆን ከሆነ፣ ገንዘቡን ለቤተ ክርስቲያኒቱ መስጠት ምን ፋይዳ አለው? ዓለም ፍጻሜ ካገኘች በኋላም ገንዘብ ፋይዳ አለው ማለት ነው?)። ኋላ ትንቢቱ ለሕተት እንደ ነበረ የተገነዘቡ በርካታ ለዎች ድርጅቱን ለቀው ወጥተዋል።

የሕዝቦች ቤተ መቅደስ የሚባለውን ድርጅት የቈረቈረው ጂሚ ጆንስ፣ ኢንዲያና ፖሊስ በተባለችው ከተማ ሐምሌ 15 ቀን

47 ተስፋዬ ሮበሌ፣ *አርዮሳውያን*።

48 *McDowell and Stewart, The Deceiver* ገጽ 26-27።

49 *Gomes* ገጽ 40 *CRI "The Branch Davidians, Statement Number DD-025" prepared by Richard Abanes (11 March 1993)* ገጽ 2 ጠቅሶ እንደ ጸፈው።

50 ዝኒ ከማሁ።

1967 ዓ.ም በኒዩክሊየር ጦርነት ያጠፋል የሚል ትንቢት ተንብዮ ነበር[51]።

የእግዚአብሔር ልጆች *(Children of God)* የሚባለውን መናፍቃዊ ድርጅት ያስተዳድር የነበረው ሞሰስ ዴቪዲ፣ ከሆቴክ የሚባል ጅራታማ ኮከብ በ1974 ዓ.ም አሜሪካንን ያጠፋል የሚል ትንቢት ተንብዮ ነበር[52]።

በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን ውስጥ የፈሉት አባይ ነባዮች ብዙ ውድመት ሲያደርሱ አይቻለሁ። በውል የማያውቋትን ልጅ አግባ የተባሉ፣ ተፈውሳችኋል ተብለው ከበሽታቸው ጋር የሚኖሩ፣ አንዲያውም አንዳንዶች በተያዙበት በሽታ ያሸለቡ፣ ለአገልግሎት ውጣ የሚለውን የአባይ ነባይ ጥሪ ሰምተው ሥራቸውን በመልቀቅ ከፍተኛ እንግልት የደረሰባቸው፣ አባይ ነባይ ካደረሰባቸው ማታለል የተነሣ ጌታንም ሆነ ክርስትናን ተሰናብተው የሄዱ፣ ዛሬ ላይ ቆመው አባይ ነባዩን፣ "እግዚአብሔር ይይለት ሕይወቱን አበላሸ" የሚሉ እጅግ በርካታ ሰዎችን አውቃለሁ።

ጌታ የራሳችንን ጉዳይ በመጀመሪያ በግልጽ የሚናገረው ለእኛ ለባለጉዳዮቹ ነው። ቋሚ የሆነ ፍላጎት በእኛ ውስጥ በማኖር፣ ይህንኑ ጉዳይ ጌታ ለቤተ ክርስቲያን፣ ለባልንጀሮቻችን፣ ለቤተሰቦቻችን፣ ለመጋቢዎቻችን፣ ለተሰያዩ አገልጋዮች ወዘተ በመናገር ጉዳዩን ያስረግጥልናል። ጌታ በአገር በዘመድ የሌለ እንግዳ ነገር ዱብ አያደርግም። በጊዜያዊ መነሣሣትም ቋሚ ሕይወታችንን አያመሳቅልም። ወገኖቼ ይህ ነው ጤናማውና መደበኛው የክርስትና ሕይወት። ቢያንስ እኔ የገባኝ የክርስትና ሕይወት ይህ ነው።

51 *Gomes* ገጽ 41 ከ*Sparks, The Mindbenders* ገጽ ጠቅሶ እንደ ጸፈው።

52 ዝኒ. ከማሁ። *Moses David, "40 Days and Nineveh Shall Be Destroyed" Tract published in 1973.*

13. የአማኞችን ክህነት ይክዳሉ

መጽሐፍ ቅዱስ ምዕመናን ሁሉ ካህናት መሆናቸውን ያስተምረናል (1ጴጥ 2÷4-10፤ ራእ 1÷6፤ 5÷10)። ይህም ማለት እያንዳንዱ አማኝ ያለምንም ሰብአዊም ሆነ መንፈሳዊ አካላት (ለምሳሌ መላእክት) መካከለኛነት፣ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ብቻ፣ ከአግዚአብሔር ጋር በቀጥታ መገናኘት ይችላል ማለት ነው (ዕብ 4÷16)።

በርካታ አባይ ነባዮችና መናፍቃን፣ በዙሪያቸው ያሉ ሰዎች ይገዙላቸው ዘንድ አማኝ ሁሉ ካህን ነው፣ አማኝ ከአምላኩ ጋር በቀጥታ መገናኘት ይችላል የሚለውን የአማኞችን ክህነታዊ መብት በመካድ ሰዎች የእግዚአብሔርን እውነት የሚረዱት በእኛ አማካይነት ብቻ ነው ይላሉ (1ዮሐ. 2÷26-27)።

አስረጅ

"የዳዊት ሥር" በመባል ይታወቅ የነበረው መናፍቃዊ አንቅስቃሴ መሥራች የነበረው ዴቪድ ክሬሽ፣ ለተከታዮቹ መጽሐፍ ቅዱስን ማብራራት (መተርጎም) የሚችለው አርሱ ብቻ እንደ ሆነ ገልጾአል[53]። "የይሖዋ ምስክሮችን" ድርጅት የመሠረተው ቻርልስ ታዝ ራስል፣ "ስተዲስ ኢን ዘ ስክሪፕቸርስ" በተባለው መጽሐፉ፣ "የተገነዘብነው ነገር ቢኖር፣ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ብቻ አንብበው መለኮታዊ ምሪትን ማግኘት እንደማይችሉ ነው። ስተዲስ ኢን ዘ ስክሪፕቸርስ መጠቀም ክጀመረ በኋላ ጥቂት ተጠቅሞባቸው፣ ተረድቶአቸው፣ ለዐሥር ዓመት እንኳ ካነበባቸው በኋላ የሚተዋቸውና ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ የሚመለስ ሰው፣ ከተሞክሮአችን የተረዳነው ነገር በሁለት ዓመት ውስጥ ወደ ጨለማ

[53] *Gomes ገጽ 41 ከAbanes, ጠቅሶ እንደ ጻፈው።*

አንደሚሄድ ነው"[54] ብሎአል። ድርጅቱ እስከ አሁን ድረስ መለኮታዊ አውነትን ለመረዳት፣ ለመጠበቂያ ግንብ ማኅበር መገዛት የግድ አስፈላጊ እንደ ሆነ ይገልጻል[55]።

የዩኒፊኬሽን ቤተ ክርስቲያን መሥራች የሆነው ሙን፣ "ሙሴ በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔርን አውነት የገለጠበት፣ በአዲስ ኪዳን ዘመን ኢየሱስ የእግዚአብሔርን አውነት የገለጠበትና ሁለቱ ኪዳናት የሚቋጩበት (የሚደመደሙበት) የሙን ዘመን"[56] በሚል፣ የሰብአውያን ታሪክ በሦስት ትልልቅ ክፍሎች እንደሚከፈል ያስተምራል። ሙን "መለኮታዊ ሕግጋት" በሚል ርእስ የጻፈው መጽሐፍ፣ "በዘመኑ መጨረሻ ላይ አግዚአብሔር የዓለማትንና የሕይወትን መሠረታዊ ጥያቄ ለመመለስ መልእክተኛውን ላክ። ስሙም ሰን ሙዮንግ ሙን ይባላል"[57]።

በዙሪያችን የፈሉትም አባይ ነባዮች አምላክ አነርሱን አፍ ለአፍ እንደሚያናግር፣ በእንድ ጉባኤ ሺህ ስማንያ መገለጥ አንሚያወርድላቸው አያየን ነው። ይህ እውነት ክሆነ ጌታ ለራሳችን ጉዳይ ቢያንስ አንድ ጊዜ እንኳ አንዴት ሹክ ሳይለን (ይቀራል በቃሱ በህልም ወዘተ)? ጸጋን መካፈል ክርስቲያናዊ ትምህርት ቢሆንም ክርስቲያኖችን በአንድ ግለሰብ ዙሪያ ማክማችት፣ አምላክ በቋሚነት የሚናገራችሁ በእኔ አማካይነት ስለሆነ ቤተ ክርስቲያናችሁን ለቃችሁ እኔ ወዳለሁበት ወይም እኔ ወደ ቄሪቄርሁት ቤተ ክርስቲያን ኑ የሚለው ጥሪ፣ የአማኞችን የክህነት መብት በጽኑ የሚጻረር ነው። በመሠረታዊው የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት

[54] *Anthony A. Hoekema, The Four Major Cults (Grand Rapids: Eerdmans, 1963) ገጽ 227።*

[55] *You Can Live Forever in paradise on Earth (1982) ገጽ 191-95። ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር (1994) ገጽ 281-283።*

[56] *Gomes ገጽ 42።*

[57] *ዝኒ. ከማሁ።*

ትምህርት፣ ቤተ ክርስቲያን የምትመሠረተው የዳኑ ለዎች በቃሉ ዙሪያ በሚያደርጉት ኅብረት እንጂ በግለሰቦች ማንነት አይደለም።

14. ትክክለኛውን የቅዱሳት መጻሕፍት አፈታት መንገድ አይከተሉም

መናፍቃን ትክክለኛ ያልሆነውን አስተምህሮአቸውን የሚያጸኑት፣ ትክክለኛ ያልሆነ የቅዱሳት መጻሕፍትን አፈታት መንገድ በመከተል ነው[58]። አብዛኛውን ጊዜ ይህ አውን የሚሆነው፣ አንድን ክፍል ወይም ጥቅስ ከዐውደ ምንባቡ አላቀው በመተርጐም ነው። ለሰዋሰው አወቃቀሩ፣ ለቃላት አሰካኩ፣ ለክፍሉ ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጽ/ጸታ (ዘውግ)፣ ለዐውደ ምንባቡ፣ ለነገረ መለኮታዊ ፍካሬው አንዳችም ቦታ አይሰጡም። መናፍቃን፣ መናፍቃን የሆኑበት ዋነኛው ምክንያት ይኸው ነው። አንቀበለዋለን የሚሉትን የሥነ አፈታት መርሖ ወጥነት ባለው ሁኔታ አንኳ ሊጠቀሙበት አይታይም።

በአባይ ነባሮች ተዘውትሮ የሚታየው የአፈታት መንገድ፣ ምስጥሮታዊ (ትርጉም ፈልቅቅ ትርጓሜ *alegorization)* የሚባለውን የአተረጓጐም ሰልት ነው[59]። ዐውድን መሠረት ያደረገ ትርጓሜ አይመቻቸውም። መጽሐፉ ለተጻፈበት መቼት እንዲሁም ሥነ ጽሑፋዊ ጸታ (ዘውግ) አንዳችም ቁብ የላቸውም። የሚሹትን ነገር ጮኽ ብሎ የሚናገርላቸው አሰክ መሰላቸው ድረስ፣ መዥረጥ አድርጎ መውጣቱን ይችሉበታል፤ ባይሆን ጉባኤው የሥነ ትርጓሜአቸውን ሕጸጽ እንዳያስተውል፣ ንግግራቸውን በአልልታና በሆታ ያሳጅባሉ፣

[58] ቅዱሳት መጻሕፍትን የምንተረጕመው እንዴት ነው የሚለውን ጉዳይ በግልጽ ለመረዳት ከፈለጉ፣ ወንድም ምኒልክ አስፋው፣ *መጽሐፍ ቅዱስና የትርጓሜ ሥልቱ* በሚል ርእስ ያዘጋጀውን መጽሐፍ እንዲያነቡ እናበረታታለን።

[59] መናፍቃን ቃለ እግዚአብሔርን እንዴት እንደሚያጠናብሩ በትክክል ለማረዳት የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ በተለያዩ መናፍቃን ላይ የጻፋቸውን መጻሕፍት ይመለከቷል።

"የገባው አሜን ይበል"፣ "አጠገብሽ ያለውን ምስጢሩ ገብቶኛል በዩው" በዚህ ረገድ ነባር ሰልታቸው ነው።

15. ቅይጥነት

ቅይጥነት የሚለውን ቃል የተጠቀምሁት፣ ሁለት የተለያዩ፣ አብዛኛውን ጊዜ ተቃራኒ የሆኑ ነገሮችን አብሮ መቀየጥ ወይም መደባለቅ የሚለውን ትርጉም እንዲይዝልኝ ነው። አብዛኞቹ መናፍቃን የቅይጣዊነት ችግር እንብዛም አይታይባቸውም። ነገር ግን ከሩቅ ምሥራቅ ትምህርት አስተሳሰብ (ከኮንፊሽስና ከቡድሃ አምነት) ጋር የተዳበሉ ትምህርቶች እንዲሁም በዙሪያችን የፈሉት አባይ ነባሮች ይህ ዐይነቱ ችግር በግልጽ ይስተዋልባቸዋል።

አስረጅ

እንደ "ክርስቲያን ሳይንስ"፣ ብዙ አባይ ነባሮችን የተጣባቸው "የእምነት እንቅስቃሴ" ትምህርት እንዲሁም የዩኒፊኬሽን ቤተ ክርስቲያን የቅይጥነት ችግር በሰፋት ይታይባቸዋል። እንደነዚህ መናፍቃን ትምህርት ለማያዊ የሆነውን የእግዚአብሔር ዕውቀት በስሜት ሕዋሳቶቻችንና በአዕምሮአችን ልንደርስበት እንችልም፤ እንዲያውም በዚህ መልክ የምናውቀውን አውነት ካልኮነንን (ካልካድን) በቀር ወደ ለማያዊው የዕውቀት ደጅ መድረስ (ማግኘት) አንችልም ይላሉ። እንደነዚህ መናፍቃን ትምህርት መንፈሳዊውን አውነት የምንገበየው በመገለጥ ዕውቀት ብቻ ነው። ይህ ደግሞ ኖስቲሲዝም ከሚባለው የጥንት ኑፋቄ የተቀዳ አረማዊ ትምህርት ነው። በዚህ ረገድ አባይ ነባሮች፣ ክርስቲያን ሳይንስና የዩኒፊኬሽን ቤተ ክርስቲያን አንድ ዐይነት አስተሳሰብ ይጋራሉ።

16. ከመናፍስቱ ዓለም ጋር መገናኘት ወይም ጥንቈላ

አብዛኞቹ አባይ ነባዮችና መናፍቃን ከመናፍስት ዓለም ጋር የመገናኘት ችሎታ እንዳላቸው ይናገራሉ።

አስረጅ

ለምሳሌ "የእግዚአብሔር ልጆች" የሚባለውን መናፍቃዊ ድርጅት ይመራ የነበረው ሞስስ ዴቪድ፣ ዛሬ በአፀደ ሥጋ ከሌሉት እንደ ማርቲን ሉተር ካሉ ለምች ጋር ይነጋገር እንደ ነበር ገልጾአል[60]።

የዩኒፊኬሽን ቤተ ክርስቲያን መሥራች የሆነው ሙን፣ "ዛሬ በዓለማችን ላይ በርካታ ለምች ከመንፈሳዊው ዓለም ጋር መገናኘት ችለዋል፤ ይህም የሐሥ 2÷17 ፍጻሜ ነው"[61] ባይ ነው። ሙንም ሆነ ባለቤቱ እንዲሁም ተከታዮቹ፣ በጸሎት ጊዜ ከመንፈሳዊው ዓለም ጋር መገናኘት ይችሉ እንደ ነበር ይገልጻሉ[62]።

የሞርሞን ቤተ ክርስቲያን መሥራች የነበረው ጆሴፍ ስሚዝ፣ ጠጠር እንደ መጣል ዐይነቱን ጥንቈላ ይከተል እንደ ነበር፣ መጻሕፍት ያስረዳሉ[63]።

ለሞኑን በመገናኛ ብዙኃን የወር ባለተራ የሆነው፣ አባይ ነባይ ኤልያስ አብጤ፣ "በአንድ ጊዜ ሁለት ቦታ መገኘት ካልቻልን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ ነው እንዲሁም ሙታንን ክሞት ማስነሣት ይችላል ማለት አንችልም" ሲል ተደምጧል። ይህ በጥንቈላው ዓለም አውን እንደሚሆን የሚነገርለት ከአካል ወጥቶ መሄድ፣ "አስትራል

[60] Gomes ገጽ 44 ከAllan, *Shopping for a God,* ገጽ 149 ጠቅሶ እንደ ጻፈው።

[61] ዝኒ. ከማሁ ገጽ 44 ከMoon, *Divine Principle* ገጽ 177 ጠቅሶ እንደ ጻፈው።

[62] *McDowe and Stewart, The Deceiver,* ገጽ 177 ጠቅሶ እንደ ጻፉት።

[63] ለምሳሌ:— *Kurt Ven Gorden, Mormonoism. D. Michael Quinn's Early Mormonism and the Magic World.*

ፕሮጀክሽን" *(Astral Projection)*፣ ለብሉያትም ሆነ ለሐዲሳት እጅግ ባይተዋር ትምህርት ከመሆኑም ባሻገር፣ በርካታ የአምነት አበው፣ ይህ ዐይነቱ አስተሳሰብ አረማዊ ነው ሲሉ ጽፈዋል።

17. መናፍቃዊ እንቅስቃሴአቸውን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ አስቀድሞ እንደ ተነበየላቸው ይገልጻሉ

አንዳንድ አባይ ነባዮችና መናፍቃን እነርሱ ከመምጣታቸው በፊት መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እነርሱ መምጣት አስቀድሞ የምሥራች እንደነገረላቸው ይገልጻሉ። ይህ ከቅዱሳት መጻሕፍት የአፈታት መርሖ ጋር እንዴት እንደሚቃረን መገመት ይቻላል።

አስረጅ

"የይሖዋ ምስክሮች" በሉቃስ 12÷42 ላይ፣ "ልባምና ታማኝ ባሪያ" የተባለው ቃል የድርጅታችንን የአመራር አካላት የሚያሳይ ትንቢት ነው ባዮች ናቸው።

"የአግዚአብሔር ልጆች" በመባል የሚታወቀው መናፍቃዊ እንቅስቃሴ አባላት፣ "የአግዚአብሔር ልጆች" *(1ዮሐ. 3÷10፤ 5÷2)* የሚለው ሐረግ በቀጥታ ስለ እነርሱ ድርጅት እንደ ተናገረ ይገልጻሉ[64]።

ጆሴፍ ስሚዝ በዘፍጥረት ምዕራፍ 50 ላይ 14 ቊጥሮችን በመጨመር ስለ እርሱና ስለ ድርጅቱ (የሞርሞን ቤተ ክርስቲያን) የሚናገር ትንቢት እንደ ሆነ ገልጾአል[65]።

"የዳዊት ሥር" የሚባለው መናፍቃዊ እንቅስቃሴ መሥራች ዴቪድ ኮሬሽ፣ በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበረው ንጉሥ ዳዊት

[64] Gomes ገጽ 45።

[65] ዝኒ. ከማሁ።

ተምሳሌት *(antitype)* እንደ ነበረ ገልጸአል[66]። ይህ ብቻ አይደለም ኮሬሽ በኢሳይያስ 45 ላይ የተጠቀሰው የንጉሥ ቂሮስ ተምሳሌት እንደ ሆነም ያስተምር ነበር (በዕብራይስጥ "ቂሮስ" ማለት ኮሬሽ ማለት ነው)። ስለዚህ ዴቪድ ኮሬሽ የሚያደርገው ነገር ሁሉ እንደ ኢሳ. 45÷13 መሠረት በእግዚአብሔር ምሪት ነው[67]። ኮሬሽ በራእይ 6 ላይ የተጠቀሰው በግ እርሱ እንደ ሆነም ገልጸአል[68]።

ብዙ አባይ ነባዮች፣ መጽሐፍ ቅዱስ ለኢትዮጵያ ልዩ ትኩረት እንደ ሰጠ እየነገሩን ነው። በዚህም ሂደት ውስጥ እነርሱ ከኢትዮጵያ የሚነሣውን የመጸኢ ዘመን ጦር እንደሚቀቡ በመግለጽ ላይ ናቸው። በዚህ ረገድ መጋቢ በቀለ ወልደ ኪዳንና ቄስ በሊና ሳርካ በእስረጅነት የሚጠቀሱ ንምቱ አበው ናቸው[69]። እነዚህ ሰዎች በዛሬዪቱ ቤተ ክርስቲያን ላይ እያመጡ ያሉት ውድመት ራሱን የቻለ መጽሐፍ የሚወጣው ነው። መጋቢ በቀለ ወልደ ኪዳን በተለያየ ጊዜ እያሠራጫቸው ያሉ ትምህርቶች እንዲሁም ቄስ በሊና ሳርካ በየቦታው እየሄዱ የሚተነብዩት ትንቢትና የሚያፈሱት ዘይት ከምንገምተው በላይ ትልቅ ጉዳት አያመጣ ነው። በዚህ ረገድ

[66] ገዘ. ከማሁ።

[67] ገዘ. ከማሁ። ከ*Abanes, "The branch Davidians"* ገጽ 4 ጠቅሶ እንደ ጻፈው።

[68] ዝኒ. ከማሁ።

[69] ጋሼ በቀለ ወልደ ኪዳን በዚህ መጠን መስመር ስቶ መውጣቱ፣ በዚህም መጠን የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ በሚጉዳ ተግባር ላይ በመሠማራት የአባይ ነባዮች አፈ ቀላጤና ዐቅብተ ነባይ ሆኖ ብቅ ማለቱ አስደንቆኛል። "መጨረሻችንን..አንተው አብጅልን" የሚለው የጥንት ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች መዝሙር ትልቅ ትርጉም ይዞ የሚከሠተው በዚህ ዐይነቱ ገጠመኝ ውስጥ ነው። ጋሼ በቁ የቀድሞ ድካምህን እናደንቅልን፣ በአንጻሩ ደግሞ አሁን ያለህበት ጉዳና በተለይ ደግሞ አባይ ነባዮችን ግብር ለማጽደቅ የምትሄድበት አካሄድ ፍጹም ስሕተት መሆኑን መግለጽ እንወዳለን። እንድትመለስም እንጸልያለን።

ወንድም ዘላለም መንግሥቱ በተለያዩ ጊዜያት በእነዚህ ግለሰቦች ላይ ያዘጋጀውን ጽሑፍ እንድታነቡ አበረታታለሁ[70]።

18. ለደቃቅ አስተምህሮዎች ከፍተኛ ትኩረት መስጠት

እባይ ነባዮችና መናፍቃን ዐበይት ከሆኑት የክርስትና ትምህርቶች ይልቅ ለጥቃቅን አስተምህሮዎች ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣሉ። ለምሳሌ ለአሰባበስ፣ ለአመልኮ ቀናት፣ ለክብረ በዓላት፣ ለባንዲራ ሰላምታ ስለመስጠት፣ ስለልደት ቀናት ወዘተ።

አስረጅ

መቼም በዚህ ዘመን እንደ እባይ ነባይ የሚሰብስ፣ በሥልት ጠጉሩን የሚቈረጥ የውበት ተወዳዳሪም ሆነ የልብስ አስተዋዋቂ ያለ እይመስሰኝም። ቆንጆ ሆኖ መታየት አግባብ ነው፣ ነገር ግን ይህ ሁሉ ለምን አስፈለገ ለሚለው ብዙዎቹ የሚመልሱት ምላሽ፣ "የምለብሰው ለቅባቱ ክብር ነው" የሚል ነው። ይህ የተሳሳተ አሳብን የሚያጸድቅ ብቻ ሳይሆን፣ ንውስ ትምህርትን ዐበይ የሚያደርግ ነው። ይህ ደግሞ ራሳቸውን በገበያው ላይ ጥሩ ተወዳዳሪ እድርጎ አቅርቧቸዋል።

በየንግግራቸው ጣልቃ፣ "አጠንብህ ያለውን አንዲህ በለው" የሚሰው፣ አንዲያው ጉባኤ ማድመቂያ ሳይሆን፣ "የእሱታዊ ንግግር

[70] ጌታ በፈቅድና ዕድሜውንና ጤናውን ቢሰጠኝ፣ "የውስጥ ቦርቧሪ" በምላቸው የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት አስተማሪዎች ላይ፣ ራሱን የቻለ መጽሐፍ ለማዘጋጀት ወጥኛለሁ። ምናልባትም ዛሬ እንደ፣ "ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን"፣ እንደ "ይሖዋ ምስክሮች" ዐይነቶቹ "የውጭ ወራሪዎች" ይልቅ፣ ትልቅ ጉዳት በማስከተል ላይ የሚገኙት የውስጥ ቦርቧሪዎቻችን ናቸው። አሁን ብዕራችንን ወደ እነዚህ ሰዎች ማነጣጠር ያስበት አይመስላችሁም?

ጎይል” ከሚለው የእምነት አንቅስቃሴ አስተምህሮ የተቀዳ ነው። ካልተናገርህ/ካላወጅህ አታገኝም።

“የይሖዋ ምስክሮች” ባንዲራን መሳለም ውጉዝ ነው፣ የሕዝብም ሆነ ሃይማኖታዊ በዓላትን ማክበር ጣዖትን ማምለክ ነው፣ የሚለው ትምህርታቸው ስሕተት መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ለደቂቃን ትምህርቶች እጅግ ከፍተኛ ትልቅ ትኩረት ማድረጋቸውን የሚያሳይ ነው።

ማጠቃለያ

ከላይ ለመጠቆም እንደ ሞከርንው፣ ከፀሓይ በታች ያሉትን አባይ ነባዮችና መናፍቃን ሁሉ፣ አጥንተንም ሆነ መርምረን አንዘልቅም—ያን ያህል ጊዜም ሆነ ዕቅም ሊኖረን አይችልም። በየጊዜው ደግሞ አዳዲስ አቀራረቦችና አስተምህሮዎች እንደሚቀፈቀፉ አያጠራጥርም። ስለዚህ መናፍቃን አዘውትረው የሚጥሷቸውን መሠረታውያን ትምህርቶችና አቀራረቦች ጠንቅቆ ማወቅ፣ ግብራቸውንም ሆነ አስተምህሮአቸውን በቀላሉ ለመለየት ትልማ ዕገዛ አለው።

እነዚህ ዐሥራ ስምንት ነጥቦች በየጊዜው የሚነሡትንና አሁንም ያሉትን አባይ ነባዮችና መናፍቃን፣ አስተምህሮአቸውን የመመዘኛ መስፈርት አድርገን ልንጠቀምባቸው እንችላለን። ጥሩ ትምህርት አውነትን ከውሸት፣ ሠናዩን ክእኩይ የሚለይ ብቻ ሳይሆን፣ የምንለይበትንም መስፈርት የሚሰጠን ነው። በዚህ አንጻር እነዚህ ዐሥራ ስምንት ነጥቦች ትልቅ ጠቀሜታ አላቸው።

ክፍል ዐሥር

“በኢየሱስ ክርስቶስ ስም” ማለት ምን ማለት ነው?



በዚህ በአሜሪካን አገር፣ በማኅበር የሚካሄድ ምህላ (የማኅበር ጸሎት) በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መቅረብ የለበትም የሚል፣ የጦፈ ክርክር ይካሄድ ነበር—በተወሰነ ደረጃም እንኪ ቢሆን፣ ውዝግቡ እስከ ዛሬዋ ቀን የቀጠለ ይመስለኛል። በቤተ ክርስቲያንና በነገረ መለኮት ተቋማት አካበቢ ብዙ ያወያየው ግን፣ “በርግጥ በክርስቶስ ስም መጸለይ ማለት ምን ማለት ነው?” የሚለው መሠረታዊ ነጥብ ነው።

የክርክሩ መነሻ የኖርዝ ካሮላይና ስቴት ስለነበርች፣ በርእስ ጉዳዩ ዙሪያ የዱክ ዩኒቨርስቲ የነገረ መለኮት ሊቃውንት ቃለ መጠይቅ ተደርጓላቸው እንደ ነበር አስታውሳለሁ። "በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መጸለይ ማለት በጸሎታችን ማጠናቀቂያ ላይ፣ 'በኢየሱስ ስም አጸልያለሁ' ብሎ ጸሎትን ማላረግ አያደለም" የሚል አስተያየት ለጥተው ነበር። ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ "አብ በወልድ እንዲከብር በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ፤ ማንኛውንም ነገር በስሜ ብትለምኑኝ እኔ አደርገዋለሁ" (ዮሐንስ *14÷13-14*) ብሎ ባስተማረበት ዐውድ፣ የእነዚህ ምሁራን አስተያየት እንዴት ይተነተናል? በርግጥ "በኢየሱስ ክርስቶስ ስም" መጸለይ ማለት ምን ማለት ነው?

በቅርቡ ኢትዮጵያውያኑን አባይ ነባዮች፣ የነገረ መለኮት ድጋፍ እሰጣለሁ እንዲሁም ነባዮቹ መንፈላዊ አባታችን ነህ የሚሉት ለው፣ የነባዮቹ ተኣምራት እውነተኛ የአምላክ አስተርእዮ ነው፣ ለሚለው ሙግቱ እንደ ዋነኛ መከራከሪያ ነጥብ አድርጎ ያቀረበው፣ "ተኣምራቶቹ፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ሲጠራ እውን የሚሆኑ ስለሆኑ፣ ከኢየሱስ ክርስቶስ እንጂ ከሌላ ባዕድ መንፈስ ጣልቃ ገብነት የተገኙ ናቸው ማለት በጭራሽ አይቻልም" ሊል ክርክር ገጥሞአል። ይኸውም ስሙ ተጠርቶ የተከወነ ተኣምር ስለሆነ፣ ከስሙ ጀርባ እርሱ መኖሩን፣ የተኣምራቱም ባለቤት እርሱ ራሱ መሆኑን መጠራጠር የለብንም ማለቱ ነው።

በርግጥ፣ "በኢየሱስ ክርስቶስ ስም" መጸለይ ማለት ወይም "የክርስቶስን ስም መጥራት" ማለት ምን ማለት ነው? ይህ መሠረታዊ ነጥብ በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት አገልጋዮችና ምዕመናን ዘንድ ትክክለኛ ቦታውን የያዘ አይመስለኝም። ይህም ሁኔታ በብዙ ረገድ ለመታለል ያጋለጠን ይመስላል። ይህ ክፍል

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እንዲካተት የተደረገው በዚህ አግባብ ነው። አንግዲያው፣ "በርግጥ የአምላክን ስም መጥራት (ስሙን ማክበር፣ ማወደስ፣ ማግነን፣ ለስሙ መስገድ ወዘተረፈ) ማለት ምን ማለት ነው?" የሚለውን ጉዳይ ለመመርመር ሙከራ አናደርጋለን[1]።

ለዚህ ጽሑፍ መነሻ የሆነኝ ግን፣ በማቴቴስ መጽሔት ቁጥር *14* ላይ፣ "ስሙን መልሱልን" በሚል ርእስ የወጣው መጣጥፍ ነው፤ ይህ መጣጥፍ ለዚህ ጽሑፍ መነሻ ይሁን እንጂ መድረሻ ግን አይደለም—መነሻው ማቴቴስ መድረሻው ደግሞ አባይ ነባዮች ናቸው። የጸሓፊው የወንድማችን ሰሎሞን አበበ ገብረ መድኅን ሙግትና ሐሰ ያነጣጠረው፣ በአምላክ ስም አጠቃቀም ላይ ነው—በንግረትም ሆነ በክትበት። ጸሓፊው ክርስቲያኑ ማኅበረሰብ እግዚአብሔር የሚለውን ስም፣ "እግ/ር"፣ "አ/ር"፣ "አግ."፣ "እግዚ" በሚል ምኅጻር አሳጥሮ መጻፉ፣ ተገቢ ያለመሆኑን ይሞግታል።

እንዲሁም አጋንንትን ለመቃወም፣ "በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም" በማለት ፈንታ፣ "ቱ! ቱ!"፣ "ቱም! ቱም!"፣ "እ...ስ...ስ...ስ...ም" ማለት ትርጉም የለሽ ቱማታ እንጂ፣ አንዳችም የቅዱላት መጻሕፍት ድጋፍ የለውም፤ እንዲያውም ይህ ዐይነቱ አካሄድ ለበቀልንበት ማኅበረሰብና ላደግንበት ባህል ፍጹም ባይተዋር ከመሆኑ ባሻገር፣ ጸያፍነቱ እንደሚበረታ ወንድም ሰሎሞን በስፋት ይሞግታል። በጽሑፉ ሊያስተላልፈው በፈለገው መሠረተ ሐሳብ ላይ መቶ በመቶ ተስማምቻለሁ—በርግጥም የወንድማችን ጽሑፍ፣ ትክክለኛና ወቅታዊ ጽሑፍ ነው! ወገኖቼ አባካችን[2] በዚህ

[1] ይህን ሐሳብ በወረቀት ላይ እንዳሰፍር ያበረታታኝ እንዲሁም የመጀመሪያ ረቂቆቹን በማንበብ፣ ብሎ ማኑላበቻ አሳቦችን እንድጨምር ያበረታታኝን መጋቢ ዮሐንስ መሐመድን ከልብ አመሰግናለሁ፤ ዕድሜና ጤና ይስጥልኝ!

[2] በተግሣጹና በቃል አራርሆው ውስጥ አንባብያኑን ብቻ ሳይሆን፣ ራሱንም መክተት ፈልጌ ነው። "አባክህ"፣ "አባክሽ"፣ "አባክም" የሚለው ሁለተኛ መደብ እንጂ፣

ረገድ ልንታረም ይገባናል አላስሁ። በአንዳንድ ጕዳዮች ላይ ግን ከወንድሜ የተለየ አሳብ አለኝ። በተወሰነ ደራጃም ቢሆን፣ ይህ ልዩነት የዚህ ጽሑፍ ማዕከል ነው። በዚህ ጽሑፍ፣ የአምላክን ስም በተመለከተ ልናውቀው የሚገባን መሠረታዊ ነገር ምን እንደ ሆነ፣ እቅጣጫ ጠቋሚ አሳቦችን ለማመላከት እሞክራለሁ።

ወደ አሳቤ ያንደረደረኝም ዘንድ፣ እግዚአብሔር አምላክ ስሙን ለመጀመሪያ ጊዜ ያስተዋወቀበትን የብሉይ ኪዳን ምንባብ በቀዳሚነት ላንሣ፦—

> “ደግሞም እግዚአብሔር ሙሴን የአባቶቻችሁ የአብርሃም አምላክ፣ የይስሐቅ እምላክ፣ የያዕቆብ አምላክ የሆነው አግዚአብሔር ወደ አናንተ ልኮኛል፤ ስሜም ለዘላለም ይኸው ነው፤ ወደ ፊት በተከታታይ በሚነሣው ትውልድ ሁሉ የምታስበው በዚህ ስም ነው ብለህ ለእስራኤል ልጆች ንገራቸው አለው” (ዘፀአት 3÷15)።

በዚህ ዐውደ ምንባብ ውስጥ አምላክ ስሙን እንዳስተዋወቀ እንዲሁም እግዚአብሔር ክትውልድ ወደ ትውልድ ሁሉ የሚዘክረው (የሚታሰበው) በዚህ ስም አንደ ሆነ ይገልጻል። በዚህ ስፍራ የተገለጠው የእግዚአብሔር የተጻውዖ ስም፣ “ያህዌ” (יהוה) የሚለው ስም አንደ ሆነ ልብ ይሏል። ይህ ስም በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት

አንደኛ መደብ ብዙ ቍጥርን ማለትም “እኛን” ለማመልከት “አባካችን” እንዲሁም አንደኛ መደብ ነጠላ ቍጥርን ማለትም “እኔን” ለማመልከት “አባኬ” የሚሉ ቃላት በአማኞችን ውስጥ የሉም። በዚህ መልክ በማላመድ ቤተኛ ብናደርጋቸው፣ ለቃላትና ለስዋሰው መዳበር አንዲሁም አሳብን በአቅጩ ለመናገር ዕገዛ የሚያደርጉ ይመስለኛል።

ውስጥ 6,828 ጊዜ የምናገኘው ሊሆን፣ በመዝሙር መጽሐፍ ላይ ብቻ አንኳ 700 ጊዜ ያህል ተደጋግሞ ጥቅም ላይ ውሏል[3]።

አንዲያውም እኛ ባለንበት የታሪክ ዘመን፣ የዚህ የአምላክ ስም ትክክለኛ ንበት የቱ አንደ ሆነ (አንዴት እንደሚነበብ) የትኛውም የአምነት ተቋም ወይም የትኛውም ሰው በርግጠኝነት አያውቅም። ይህ ስም በአንዳች ግለሰብ ወይም የሃይማኖት ተቋም ያልታወቀበትን ዐቢይ ምክንያት ምን አንደ ሆነ ማብራሪያው እነሆ፦—

ክአንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ፣ የጥንት ዕብራውያን ያህዌ (יהוה—*YHWH*) የሚለውን የእግዚአብሔርን የተጻውዖ ስም[4] መጥራት ስለሚፈሩ፣ ያህዌ በሚለው ስም ፈንታ አዶናይ (אֲדֹנָי—*Adonai*) የሚለውን የወል ስም (አዶናይ ማለት “ጌታ” ማለት ነው)፣

[3] ያህዌ በሚለው የአምላክ ስም ላይ እንዲሁም ይህ ጽሑፍ በሚያነሣው ጭብጥ ላይ ስፊ ማብራሪያ ከፊስነ ተስፋዱ ሮበሌ፣ *አርዮሳውያን፣ የይሖዋ ምስክሮች አስተምህሮ በቃስ እግዚአብሔር ሲመዘን፣* (ተስፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር፣ ሎጋንቪል፣ ጆርጂያ፣ 2016 ዓ.ም) ይመስከ፲ል።

[4] በአማርኛ ሰዋስው ሕያዋንም ሆኑ ግዑዛን የሚጠሩበት መጠሪያ ሁሉ “ስም” ይባላል። እንደ ታላቁ የአማርኛ ሰዋስው ምሁር እንደ ብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፣ ስም አምስት ዐይነት ምድቦች አሉት። እነርሱም *(1)* የተጸውዖ ስም፣ *(2)* የወል ስም፣ *(3)* የጥቅል ስም፣ *(4)* የቁሳቍስ ስምና *(5)* የነገር ስም ናቸው። እኔ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የጠቀስሁት፣ የተጸውዖ ስምና የወልን ስም ብቻ ነው። የተጸውዖ ስም ማለት፣ ሰው ወይም አምላክ የሚጠራበት፣ የግሉ የሆነና እርሱ ብቻ ተሰይቶ የሚጠራበት መጠሪያ ማለት ነው። ያህዌ ወይም ኤልሻዳይ የሚሉት ስሞች የአምላክ የተጸውዖ ስም ናቸው። የወል ስም ግን ዐይነቱ አንድ የሆነ ነገር ሁሉ የሚጠሩበት የጋራ መጠሪያ ነው። በዕብራይስጥ አዶናይ የሚሰው ስም፣ በአማርኛችን “ጌታ” ማለት ስለሆነ፣ በወል ስም ፈርጅ ውስጥ ይመደባል። በግሪክ ደግሞ “ኩሪዮስ” እና “ኩራዮስ” የሚሉት ስሞች እንደ ቅደም ተከተላቸው እግዚአብሔርና ጌታ የሚል ትርጉም ስላላቸው፣ በወል ስም ውስጥ ይከተታሉ።

ያህዌ በሚለው ስም ምትክ ተክተው ይጽፉ አንዲሁም ይናገሩ ነበር። ይህን የአምላክ ስም መጥራት አንዲፈሩ ያደረጋቸው ዋነኛ ምክንያት፣ "የአግዚአብሔር የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ" የሚለው፣ ከዐሥርቱ ትእዛዛት መ'ኻል ሦስተኛውን ሕግ በተሳሳተ መንገድ በመረዳታቸው ነው። ይኸውም ተሳስተን ባልሆነ መንገድ ስሙን ጠርተንው ከሆነ፣ ቅሥፈት ያጋጥመናል የሚል ፍርሓት። ይህ ብቻ አልነበረም፣ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ያባዙ የነበሩት ጸሓፍት (አንዳሁኑ የማተሚያ መሣሪያ በወቅቱ ስላልነበር) ያህዌ የሚለው የአምላክ ስም በሚገኝበት ቦታ ሁሉ፣ እጃቸውን በሣሙና ሙልጭ አድርገው ይታጠቡ አንዲሁም ብዕራቸውን በንጹሕ ውሃ ያለቀልቁ ነበር። ይህ ማለት ደግሞ፣ አንድ ጸሓፊ ብሉያትን ገልብጦ እስኪጨርስ ድረስ ወደ ስባት ሺህ ጊዜ ያህል አጁንና ብዕሩን በዚህ መልክ ያጸዳ ነበር ማለት ነው። ይህ ሁሉ ድካም የአምላክን ስም በከንቱ ላለመጥራት እንዲሁም ለስሙ የሚገባውን ትልቅ ክብር ለመግለጽ ነው። ስለዚህ የአምላክህ የአግዚአብሔር ስም በከንቱ አትጥራ የሚለውን ሕግ ላለማፍረስ በሚያደርጉት ትንቅንቅ/ጥንቃቄ፣ ያህዌ የሚለውን የተጸውዖ ስም ከመጠቀም ይልቅ፣ አዶናይ የሚለውን የወል ስም ተክተው በመጠቀም ጀመሩ። በዚህም መንገድ ያህዌ የሚለውን ስም ከሃይማኖት ሥርዐታቸው ውስጥ አስወጡ።

የጥንት ዕብራውያን ድምፅ ተቀባይ ፊደላትን *(consonants)* ብቻ በመጻፍ፣ በሚያነቡበት ጊዜ ብቻ ድምፅ ስጪ ፊደላትን *(vowels)* አያስገቡ ጽሑፋቸውን ያነቡ ነበር። በስድስተኛውና በስባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ፣ የዕብራይስጥ ቋንቋ አያደገ ስለመጣ፣ ድምፅ ተቀባይ ፊደላትን ከድምፅ ስጪ ፊደላት ጋር አስባጥሮ መጻፍ ተጀመረ። ማሶራውያን *(Masoretes)* የሚባሉት የዕብራይስጥ ቋንቋ ሊቃውንት፣ ለዕብራይስጥ ፊደላት አናባቢ ምልክቶችን በመፍጠር፣

አነዚህን ምልክቶች ከተናባቢ ሆህያት ጋር አቀናጅተው መጻፍ ሲጀምሩ፣ ያህዌ ለሚለው ስም ግን አናባቢ ሳያበጁለት ቀሩ— ምክንያቱም ያህዌ የሚለው ስም ባለባቸው ቦታዎች ሁሉ፣ "አዶናይ" (יְהוָה) የሚለውን ስም ተክቶ የመናገር ጠንካራ ልማድ ነበረና፣ ለዚህ ስም አናባቢ ማበጀት አላስፈለጋቸውም[5]። "ልማድ ሲለምጥን ቀኖና ይሆናል" ይሏል ይኸው ነው። ይህ አናባቢ ያልተበጀለት ያህዌ የሚለው ስም ድምፅ ተቀባይ ፊደላት— יהוה–*YHWH* ቴትራግራሞቶን በመባል ይታወቃል።

ነገር ግን አይሁዶች ያህዌ የሚለውን ስም አግዚአብሔርን ከመፍራትና ስሙን ከማክበር የተነሣ ስለማይጠሩት፣ ቋንቋው ሲያድግ የቀድሞውን ትክክለኛ አነባበብ አዲሱ ትውልድ ሳያውቀው ቀረ። ይህን ችግር ለመፍታት ዕብራውያን አዶናይ (יְהוָה–*Adonai*) በሚለው የአምላክ ስም ላይ የሚገኙትን ድምፅ ስጪ ሆህያት ማለትም *"a, o, a"* ያህዌ በሚለው ድምፅ ተቀባይ ፊደላት (ቴትራግራማቶን) ውስጥ በመጨመር፣ *YaHoWaH* ወይም

[5] ይህ ለዕብራይስጥ ብቻ ሳይሆን፣ ለአብዛኞቹ ጥንታውያን ቋንቋዎች እውነት የሆነ ከሥተት ይመስላል። ለምሳሌ የግእዝ ቋንቋ አናባቢ ሆህያት የተቀመሩለት ከጊዜ በኋላ እንደ ሆነ መረጃዎች ይጠቁሚሉ። ቀሲስ ዶክተር ምክረ ሥላሴ ገ/አማኑኤል፣ *"በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በግእዝ ቋንቋ"* በሚል ርእስ አዘጋጅተው ያሳተሙት መጽሐፍ ይህን ጉዳይ በተመለከተ እንዲህ ይላል፣ "በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በቅዱስ ፍሬምናጦስ (አባ ሰላማ) ጊዜና ከአብርሃ ወአጽብሐ ዘመን ወዲህ ነው፣ እንጂ ከዚያ በፊት ፊደሉቱ ቢኖሩም አናባቢ ምልክቶች ሳይኖሩአቸው የነበረው ግእዙ ፊደል ብቻ በመሆኑ ፊደሎቹ ስላስቸገሯቸው ለክዕበ፣ ለሣልስ፣ ለራብዕ፣ ለሐምስ፣ ለሳድስና ለሳብዕ የሚሆኑ የፊደላቱን ድምፆች የሚለዋወጡ አናባቢ ምልክቶችን ጨምረው እያንዳንዱ ፊደል ስባት ዐይነቶች እንዲሆኑ አዘጋጅተው ለአጻጻፍና ለድምፅ አሰጣጥ እንዲመች አድርገውልናል" (ገጽ 5)።

YaHWaH ተብሎ እንዲነበብ አደረጉ። ይህ አንግዲህ የማሶራውያኑ ፈጠራ እንደ ሆነ ልብ ይሏል።

በዚህ ቦታ ልናስተውሰው የሚገባን ትልቁ ቁም ነገር፣ ቴትራግራማቶንን ምንም ብለን ማንበብ ያለመቻላችንን ነው። ምክንያቱም የድምፅ ተቀባይ ፊደላት ቅንጅት ብቻ ስለሆነ፤ ለማንበብ ደግሞ ድምፅ ሰጪ ፊደላት የግድ ያስፈልጋሉ። ከዚህ ሐቅ የተነሣም ነው፣ ያህዌ የሚለው ስም ሰው ሠራሽ ስም ነው የሚባለው[6]። ነገር ግን ያህዌ የሚለው ስያሜ ቴትራግራማቶን ሊነበብበት ከሚችልባቸው አጅግ በርካታ አማራጮች መኻል አንዱ መሆኑን ልብ ይሏል[7]።

ከዚህም ይልቅ አስደናቂ የሆነው ክሥተት፣ የቴትራግራማቶን ንበት በትክክል በሚታወቅበት ዘመን፣

[6] "የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር" በመባል የሚታወቀው "የይሖዋ ምስክሮች" ድርጅት፣ ለው ድነት የሚያገኘው ይህን የአምላክ ስም በመጥራት እንደ ሆነ እንዲሁም በምድር ላይ ይህን ስም ለፍጥረት ሁሉ በማስተዋወቅ ላይ የሚገኘው ይኸው ድርጅት እንደ ሆነ ያስረዳል። በአንጻሩ ደግሞ ይህ የአምላክ ስም ትክክለኛ አነባበብ እንደማይታወቅ፣ አሁን ያሉት አማራጭ አነባበቦች ("ጀሆቫ" ወይም "ያህዌ" የሚሉት ስያሜዎች) ለው ሠራሽ እንደ ሆኑ ገልጾአል። በዚህ ረገድ ድርጅቱ እያተመ ከሚያወጣቸው ጽሑፎች መኻል የሚከተሉትን ሁለት መጻሕፍት ይመለከቷል—*Aid to Bible Understanding* ገጽ 884-885። *ክቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር*፣ ገጽ 195። ትክክለኛውን የአምላክ ስም ማወቅ ለድነት እጅግ ወሳኝ ጉዳይ ነው እንዲሁም የአምላክን ስም ለፍጥረት ሁሉ የምናሳውቅ ብቸኛ የምድር ወኪል ነን እየተባሰ፣ በአንጻሩ ደግሞ የአምላክ ስም ትክክለኛ ንበት አይታወቅም ማለት ትልቅ ተቃርኖ ነው። እንግዲያው የድርጅቱን ተከታዮች ሊጠየቁ ከሚገባቸው ጥያቄዎች መኻል አንዱ፣ "እንዴት የማይታወቅ ስም ዕወቁ እንባላለን፣ እንዴትስ ለው ሠራሽ የሆነ ስም ድነት ለማግኘታችን ቅድመ ሁኔታ ሊሆን ይችላል?" የሚለው ነው።

[7] በቴትራግራማቶን ላይ የቀረበው ትንታኔ በአብዛኛው የተወሰደው ጸሓፊው፣ *አርዮሳውያን* በሚል ርእስ ካዘጋጀው መጽሐፍ ነው።

ከዕብራይስጥ ወደ ግሪክ ቋንቋ የተተረጐመው የሰብዓ ሊቃናት ትርጉም፣ ይህን ስም አንዳችም ጊዜ እንኳ ያለመጠቀሙ ነው። በዘመነ ብሉይ (ከ300 ዓ.ቅ.ክ[8] እስክ 200 ዓ.ቅ.ክ ባለው ጊዜ) ከዕብራይስጥ ወደ ግሪክ ቋንቋ የተተረጐመው የሰብዐ ሊቃናት ትርጉም፣ ያህዌ የሚለውን የእግዚአብሔር የተጻውዖ ስም በጽርዕ (በግሪክ ቋንቋ) "ቴዎስ" (θεὸς ማለትም እግዚአብሔር) አንዲሁም "ኩሪዮስ" (κύριός ማለትም ጌታ) በሚለው የግሪክ የወል ስያሜ ነው የተረጐመው።

አስደናቂ የሆነው ሌላው ጉዳይ፣ የሐዲስ ኪዳን ጸሓፍት በጽሑፎቻቸው ውስጥ አንድም ጊዜ ይህን የአምላክ የተጻውዖ ስም በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ያለመጥቀሳቸው ብቻ ሳይሆን፣ ለትምህርታቸው አማኝነትና ማጐልበቻ ብሉያትን እጅግ በርካታ ጊዜ ሊያጣቅሱ[9]፣ ይህን የአምላክ ስም በሐዲስ ኪዳን በዕረ ጽሑፋት ውስጥ አንድም ጊዜ እንኳ ያለመጥቀሳቸው ነው[10]።

በዚህ ቦታ ልንጠይቀው የሚገባን መሠረታዊ ጥያቄ፣ የሐዲስ ኪዳን ጸሓፍያን ምን ነክቷቸው ነው ይህን ስም በጽሑፋቸው ውስጥ

[8] "ዓ.ቅ.ክ" የሚለው ምኅጻረ ቃል፣ ዓመት ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ወይም ከክርስቶስ ልደት በፊት ማስት እንደ ሆነ ልብ ይሏል።

[9] የብሉይ ኪዳን 295 ክፍሎች በ352 ሐዲስ ኪዳን ምንባባት ውስጥ ተጣቅሰው የሚገኙ ሊሆን፣ እንደዚህ ስሌት 4.4 ከመቶ የሐዲስ ኪዳን ምንባባት ብሉያት ናቸው ወይም 22.5 የሐዲስ ኪዳን ምንባባት ውስጥ አንድ የብሉይ ኪዳን ምንባብ ይገኛል እንደማለት ነው። ስበለጠ መረጃ *Roger Nicole, Revelation and the Bible, ed. Carl. F.H. Henry (Grand Rapids: Baker, 1958)*, ገጽ 137-151 ይመለከቷል።

[10] "የይሖዋ ምስክሮች" 237 ጊዜ ያህዌ የሚለውን ስም በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ የጨመሩ ቢሆንም፣ ለዚህ አድራጐታቸው ግን አንዳችም አጥጋቢ ማስረጃ ማቅረብ አይችሉም። እንዲያውም በሐዲስ ኪዳን ምንባባት ውስጥ ይህን ቃል መጠቀማቸው ስምት፣ "ኢየሱስ አምላክ አይደለም" ወደሚለው አስተምህሮአቸው እንዲሳቡ አድርጓል።

ሳይጠቅሱ ያሰፉት—ቢያንስ አንድ ጊዜ እንኳ ይህን ስም መጥቀስ አንዴት አልቻሉም? ይህ ብቻ አይደለም፣ እግዚአብሔር የተጠራባቸው የብሉይ ኪዳን የተጻውዖ ስሞች በርካታ ቢሆኑም፣ አንዱም ስም ግን በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ጥቅም ላይ ውሎ አይገኝም። በሐዲስ ኪዳን ግሪክ ቋንቋ፣ በአምላክ የወል ስምነት ተደጋግመው የተጠቀሱት ስሞች "ቴዎስ" (θεός—እግዚአብሔር) እንዲሁም "ኩሪዮስ" (κύριός—ጌታ) የሚሉት ስሞች ናቸው። ክዘመነ ክርስትና በፊት፣ እነዚህ ስሞች የግሪክ ጣዖታትን ሰማመልከት ጥቅም ላይ ይውሉ የነበሩ ስሞች መሆናቸውን የመስኩ ምሁራን በግልጽ ያስረዳሉ።

በኦሮምኛ "ጎፍታ/ዋቀዮ"፣ በጉራጊኛ "ጐይታ"፣ በሲዳምኛና በጌዴኦኛ "መገኖ"፣ በትግርኛ "አምላክ"፣ በወላይትኛ "ጦላ"፣ በአማርኛ "እግዚአብሔር" ወዘተ የሚሉት ስሞች፣ የወል ስም መሆናቸው ብቻ ሳይሆን፣ ሰባዕድ አምልከም ሆነ ሰመጽሐፍ ቅዱሱ አምላክ ያላንዳች ጥያቄና ማመንታት ተጠቅመንባቸዋል፣ እየተጠቀምንባቸውም እንገኛለን[11]።

[11] በአንድ ወቅት በኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ጎብረት ዋና ጽሕፈት ቤት ውስጥ፣ "አላህ" የሚለውን የዐረብኛ የወል ስም "እግዚአብሔር" በሚለው የአማርኛ የወል ስም ተክተን እንጠቀም ወይስ አንጠቀም የሚል የሁለት ወገን ክርክር ቀርቦ እንደ ነበር አስታውሳለሁ። በእኔ አተያይ ይህ መግት ሊፈታ የሚችለው፣ በዚህ ጽሑፍ ጭብጥ ነው የሚል አቋም አለኝ። ክርክሩ በቀረበበትም ወቅት የለጠሁት አስተያየት ይህንኑ የተከተለ ነበር። ይህ ጽሑፍ ግን የጎበረቱ ጽሕፈት ቤት ገብቶበት የነበረውን ውዝግብ ለመፍታ ጥሩ መደላድል የሚያደርግ ይመስለኛል፣ ይኸውም የአምላክን ስም አጠቃቀም በተመለከተ ማለቱ እንጂ፣ ነገረ መለኮት ስያሜዎችን በተመለከተ ግን፣ እያንዳንዱ ስያሜ በተናጠልና በጥሙና መመርመር ያለበት ይመስለኛል። ምክንያቱም የእስልምናና የክርስትና ነገረ መለኮት ዕንሰ አሳቦች እጅግ የተለያየ ፍካሬና እማሬ ስላላቸው።

ጌታ ሰደቀ መላሙርቱ ባስተማረው ጸሎት ላይ፣ "ስምህ ይቀደስ በሉ" ወይም "ስሙን ቀድሱ" ተብሰን ነበር (ማቴዎስ 6÷9)። ታዲያ አንዴት ነው ስሙን ላናውቅ ስሙን ልንቀድስ የምንችሰው? አምላክ በየትውልዱ ሁሉ ሰዘላለም አጠራበታሰሁ ያሰው ስም አንዴት በዚህ መልክ መና ይቀራል? አንዳንድ ለምች ሰዚህ ታሪካዊና ነገረ መለኮታዊ ክሥተት የሚሰጡት ትንታኔ፣ ሐዲስ ኪዳን ከአብ ይልቅ ሰወልድ ትልቅ ስፍራ ስሰሚሰጥ ጸሓፍያኑ፣ ሆነ ብሰው ያደረጉት ነገር ነው የሚል ነው። ይኸውም ሐዲስ ኪዳን፣ "በቃልም ሆነ በተግባር የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ስም አድርጉት" (ቈላስይስ 3÷17) ይላል። ሁሉን ነገር በጌታ በኢየሱስ ስም ማድረግ ማለት ደግሞ ምን ማለት እንደ ሆነ፣ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በሚከተለው መንገድ ያብራራሉ፦

- በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተሰብሰቡ (ማቴዎስ 18÷20፤ 1ቆሮንቶስ 5÷4)።
- በጌታ ስም አጋንንትን አውጡ (ሉቃስ 10÷17፤ ሐዋርያት ሥራ 16÷18)።
- በኢየሱስ ስም ንስሓና የኀጢአት ይቅርታ አንዲሁም ድነትን ስበኩ፣ (ሉቃስ 24÷47፤ ሐዋርያት ሥራ 4÷12፤ ዮሐንስ 1÷12፤ ሐዋርያት ሥራ 10÷43፤ 1ዮሐንስ 3÷23፤ 5÷13)።
- ጸሎታችሁን በኢየሱስ ስም አድርሱ (ዮሐንስ 14÷13-14፤ 15÷16፤ 16÷23-24)።
- መንፈስ ቅዱስ የሚላክላችሁ በኢየሱስ ስም ነው (ዮሐንስ 14÷26)።
- በኢየሱስ ስም ሕመማንን ፈውሱ፤ ሽባውን ተርትሩ (ሐዋርያት ሥራ 3÷16፤ 4÷7-10:30)።

- በሰማይም ሆነ በምድር አቻ የለሌው ስም የኢየሱስ ስም ነው (ኤፌሶን 1÷21፤ ፊልጵስዩስ 2÷9-11)[12]።

ልክ ነው ሐዲስ ኪዳን ለጌታችን ለመድኀኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ትልቅ ቦታ ይሰጣል። አንዲያውም ከስሞች ሁሉ በላይ የሆነ ስም ያለውና ጉልበት ሁሉ የሚንበረከክለት ስም፤ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ስም አንደ ሆነ ይናገራል (ፊልጵስዩስ 2÷9-11፤ ኤፌሶን 1÷21)።

ነገር ግን የኢየሱስ ስም ታላቅ ስም መሆኑ የአብ የተጸውዖ ስም እንዲጠፋ ምክንያት ሊሆን አንዴት ቻለ? የሚለው ጥያቄ አጅግ መሠረታዊ ጥያቄ ነው። የሚከተሉትን የብሉይ ኪዳን ክፍሎች ልብ ይሏል፦—

- "እኔ አግዚአብሔር ነኝ፤ ለሜ ይህ ነው፤ ክብሬን ለሌላ ምስጋናዬንም ለተቀረጹ ምስሎች አልስጥም" (ኢሳይያስ 42÷8)።
- "ስሜም ለዘላለም ይኸው ነው፤ ወደ ፊት በተከታታይ በሚነሣው ትውልድ ሁሉ የምታስበው በዚህ ስም ነው ብለህ ለአስራኤል ልጆች ንገራቸው አለው" (ዘፀአት 3÷15)።

እነዚህና አነዚህን መሰል ምንባባት አንዴት ይተነተናሉ የሚለው ጉዳይ፤ አሁንም ቋሚ ጥያቄ ሆኖ ይቀጥላል። ይህን ጥያቄ አጥጋቢ በሆነ መንገድ የሚተነትነው ነገረ መለኮታዊ አንድምታ የሚከተለው ነው።

በጥንት አስራኤላውያን ባህል የተጸውዖ ስም፤ ግብርን (ሥራን)፤ ባሕርይን (ተፈጥሮን) አንዲሁም ሥልጣንን የሚያሳይ ነው። አቢግያ ስለባልዋ አዙይ ምግባርና ጠባየ ብልሹነት ስትናገር፤

[12] ይህ ክፍል በቀጥታ የተወሰደው ተስፋዩ ሮበሌ፤ *አርዮሳውያን፣ የይሖዋ ምስክሮች አስተምህሮ በቃለ አግዚአብሔር ሲመዘን*፤ ላይ ነው።

"ጌታዬ ያን ባለጌ ስው ናባልን ከቁም ነገር አይቊጠረው፤ ስሙ ራሱ ጅል ማለት ስለሆነ፣ ስውየውም ልክ እንደ ስሙ ነው፤ ጅልነትም አብሮት የኖረ ነው" (1ሳሙኤል 25÷25) ማለቷ ስም ግብርንና ባሕርይን አንደሚያመላክት የሚያስተምር ነው። የጥንት ዕብራውያን ስም የሚያወጡት ግለሰቡ እንዲሆን የሚፈልጉትን አልያም ከታሪካቸው ጋር አገናዝበው ነው። ልክ እንደዚሁ ሁሉ፤ የአግዚአብሔር ስሞች በሙሉ፤ የአግዚአብሔርን ግብር፤ ባሕርይና ሥልጣን የሚያሳዩ ናቸው። በሌላ አነጋገር የአምላክ መለኮታዊ ስሞች የማንነቱ ነጸብራቅ ናቸው። በዚህ ረገድ አንዳንድ አሰረጆችን ላቅርብ፦—

ኤሎሂም (אֱלֹהִים) ወይም ኤሎዋሃ (אֱלוֹהַּ) የሚለው የወል ስም፤ "አምላክ" ወይም "ጌታ" የሚል ትርጓሜ ሲኖረው፤ ከሌሎች የአምላክ ስሞች ጋር ተጫፍሮ ሲቀርብ፤ በተገናኝ ትርጓሜው የአግዚአብሔርን ባሕርይ ወይም ሥራ ያውጃል፤ ለምሳሌ ኤልኤልዮን (עֶלְיוֹן אֵל) "ልዑል (ምጡቅ) አግዚአብሔር" ማለት ነው (ዘፍጥረት 14÷18:19; 20:22)። ኤልኦላም (אֵל עוֹלָם) "ዘላለማዊ አምላክ" ማለት ነው። ኤልሮኂ (אֵל רֹאִי) "የሚያይ/የሚመለከት አግዚአብሔር" ማለት ነው። አግዚአብሔር ሥሉጥ ላዕለ ኵሉ ነው፤ ዘላለማዊ ጌታ ነው፤ ችግረኞችን ከነችግራቸው መንጥሮ የሚመለከት አምላክ ነው። ለናሙናነት በቁነጠርኂቸው በአነዚህ ሰሞች ውስጥ የምናስተውለው ቁም ነገር ለም ባሕርይን፣ ግብርንና ሥልጣንን አመላካች ስንደቅ አንዲሁም ዐላማ መሆኑን ነው። ለዚህም ነው ብሉያት አግዚአብሔር የተጠራባቸው ስሞች ሁሉ፤ የአግዚአብሔርን ባሕርይና ሥራ ያትታሉ ያልንው።

በሚከተሉት ምንባባት ውስጥ የእግዚአብሔር ስም ከእግዚአብሔር ባሕርይና ግብር ጋር በተለዋዋጭነት አንዴት አንደ ቀረበ ልብ ይሏል፦—

- "አቤቱ ስለዚህ በአሕዛብ ዘንድ አመሰግንሃለሁ፤ ***ለስምህም*** እዘምራለሁ" (*መዝሙር 18÷49*)።
- "ለእግዚአብሔር ተቀኙ፤ ***ለስሙም*** ዘምሩ፤ ወደ ምድረ በዳ ለወጣም መንገድ አድርጉ፤ ***ስሙ*** እግዚአብሔር ነው" (*መዝሙር 68÷4*)።
- "ይህን ፍጥረትህን አስብ፤ ጠላት እግዚአብሔርን ተላገደ፣ ሰነፍ ሕዝብም ***ስሙን*** አስቈጣ" (*መዝሙር 74÷18*)።
- "አቤቱ አምላኬ ሆይ፤ በልቤ ሁሉ አመሰግንሃለሁ፤ ለዘላለምም ***ስምህን*** አከብራለሁ" (*መዝሙር 86÷12*)።
- "***ስምህን*** ለወንድሞቼ እነግራለሁ፤ በጉባኤም መካከል አመሰግንሃለሁ" (*መዝሙር 22÷22*)።
- "***ስምህን*** ለወንድሞቼ እነግራቸዋለሁ፤ በጉባኤም መካከል ምሰጋናህን እዘምራለሁ" (*ዕብራውያን 2÷12*)።

በእነዚህ ምንባባት የእግዚአብሔር ስም ከእግዚአብሔር ባሕርይ፤ ግብርና ሥልጣን ጋር መሳ ለመሳ ተነጻጽሮ ቀርቧል። መዝሙረኛው፣ "ለስሙ ዘምሩ" ወይም "ለስምህ እዘምራለሁ" ወይም ደግሞ "ስምህን አከብራለሁ" ሲል፣ ከእግዚአብሔር በተለየ መልክ ለስምህ ብቻ ማጎሴተ እግዚአብሔር እቆማለሁ እያለ አያደለም። "ለሰነፍ ሕዝብ የእግዚአብሔርን ስም አለቈጣ" ማለት፣ ራሱን እግዚአብሔርን አለቈጣ ወይም እግዚአብሔርን አዋረደ ማለት አንጂ፣ ከእግዚአብሔር በተለየ መልኩ ስሙ ብቻውን ይቈጣል፣ ይዋረዳል ወይም ይከብራል ማለት አይደለም።

ዕብራውያን 2÷12 ላይ ያለው ምንባብ በቀጥታ የተጠቀሰው ከመዝሙር 22÷22 ላይ ነው። መዝሙር 22 ደግሞ ጻድቅ ስለሚገጥመው መከራና በመጻኢው ዘመን ስላለው ተስፋ ይናገራል። ጻድቅ በሚያልፍባቸው መከራዎች ውስጥ ሁሉ ግን፣ የእግዚአብሔር እንደ ራሴነቱ አይዛነፍም። የዕብራውያን ጸሓፊ ከዚህ ጻድቅ ስለሚገጥመው መከራ ከሚናገረው ክፍል ውስጥ፣ ኢየሱስ የእኛን ሥጋነትና አበሳ ለመሸከም እንደኛ ሰው መሆን እንዳስፈለገው፣ ይህም የክርስቶስ ኢየሱስ ሰው (ትስጉት/ትስብእት) የመሆን ጉዳይ፣ የአምላክን ስም እንደ ማስተዋወቅ ተደርጎ ተወስዷል።

ልብ እንበል በእነዚህ ምንባባት፣ የአምላክ ስም ያህዌ ነው፤ ይህን ስም ለድነታችሁ ዋስትና ነውና ቋጥራችሁ ያዙት አልተባልንም፤ ወይም ወደዚያ የሚያንደረድር አንዳችም ጠቋሚ አሳብ አልቀረበም። በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ፣ ኢየሱስ የትኛውንም የብሉይ ኪዳን ስመ አምላክ በመጥራት ለደቀ መዛሙርቱ አይናገር አንጂ፣ ኢየሱስ በሕይወቱም ሆነ በሞቱ አባቱን በሚገባ መንገድ ተርኩታል (*ዮሐንስ 1÷18*)። አኖም፣ "ከአባቱ ዘንድ የመጣውንም የአንድያ ልጅን ክብር አይተናል" (*ዮሐንስ 1÷14*)።

ከእነዚህ መረጃዎች በግልጽ የምንረዳው ቁም ነገር፣ የአምላክን የተጻውዖ ስም አላወቅንም ማለት ስሞቹ የሚወክሉትን አምላክ አናውቅም ማለት አይደለም። የተጻውዖ ስሞች ንበት ጠፋብን ማለት፣ አምላክ ተስወረብን ማለት አይደለም። ስለዚህ ለስምህ እለግዳለሁ ስንል፣ ለተጻውዖ ስምህ አደገድጋለሁ ማለታችን አይደለም። ነገር ግን የተጻውዖ ስሙ ባለቤት የህልውናዬ ቦልፋና ያሚጋ ነው ማለታችን እንጂ። ያህዌ የሚለው ስም ትርጓሜው፣ የእግዚአብሔርን ታዳጊነትና በድነት ውስጥ ያለውን ሉዓላዊ ቦታ

የሚያሳይ ነው። ስለዚህ ያህዌ ማለት በሁሉ ላይ ሉዓላዊ ሥልጣን ያለው ታዳጊ እምላክ ማለት ነው። ቴትራግራማቶን እንዴት እንደሚነበብ አይታወቅ እንጂ፣ ይህ የአብርሃም፣ የይስሐቅ፣ የያዕቆብ እምላክ ታዳጊና ልዑል አምላክ እንደ ሆነ የሐዲስ ኪዳን ምንባባትም በዝርዝር ያስረዳሉ። ቅዱሳት መጻሕፍት አግዚአብሔርን ማንነትና የድነት መንገድ እጅግ በተፍታታ መንገድ ገልጸውልናልና።

ስም የሚለውን ቃል በጥሬው በመተርጎም ከመንገድ የሳቱት፣ "የይሖዋ ምስክሮች" ብቻ አይደለሁም። "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን"[13] በመባል የሚታወቀው ሃይማኖታዊ ድርጅት መምህራንም ጭምር እንዲሁም የዘመኑ አባይ ነባዮች አንጂ። "የአንሲ ጂሰስ" መምህራን በዮሐንስ 5÷43 ላይ፣ "እኔ በአባቴ ስም መጥቼ አልተቀበላችሁኝም፣ ሌላው በራሱ ስም ቢመጣ ግን ትቀበሉታላችሁ" የሚለውን አሳብ በመጥቀስ፣ "ኢየሱስ በአባቴ ስም መጣሁ" ሲል "ኢየሱስ ራሱ አብ ሆኖ መምጣቱን"፣ "የኢየሱስ ስም ማለት የአብ ስም መሆኑን"፣ "እብና ወልድ እንድ አካል

[13] በኢትዮጵያ ውስጥ በስፋት የሚታወቁት "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" በሚለው ስማቸው ሲሆን በተለምዶ ግን "አንሲ ጂሰስ" በሚለው ስም በስፋት ይታወቃሉ። "አንሲ ጂሰስ" የሚለው ስያሜ የመጣው ድርጅቱ የሥላሴን አስተምህሮ በመካድ አብም፣ ወልድም፣ መንፈስ ቅዱስም አንድ አካል ናቸው የሚለውን ትምህርት በማራመዱ ነው። ይህ ትምህርት በኒቂያ ጉባኤ አበው፣ "ውጉዝ ከመሰባልዩስ" ተብሎ ተወግዞአል። "አንሲ ጂሰሶች" በምዕራቡ ዓለም በተለያየ ስም ይጠራሉ፣ በአሜሪካን አገር የሰባልዮስን አስተምህሮ በማራመዱና የኢትዮጵያውን "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" በመቄርቁሩ ምክንያት በስፋት የሚታወቀው፣ "ዩናይትድ ፔንቴክስታል ቸርች" (UPCI) የሚባለው ድርጅት ነው። ይህ መናፍቃዊ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ ውስጥ ወደ ሁለት ሚሊዮን አባላት እንዳሉት ጥናቶች ያሳያሉ፣ የወቅቱ የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስቴርም የዚሁ ድርጅት አባል እንደ ሆኑ ይነገራል።

መሆናቸውን" ያሳያል ይላሉ። ይህ ፍጹም ስሕተት ነው። በዚሁ ዐውደ ወስጥ ኢየሱስ ራሱ፣ "እኔ ብቻዬን ክራሴ ምንም ማድረግ እልችልም፣ የምፈርደው የምስማውን ብቻ ነው፤ የላከኝን እንጂ የራሴን ፈቃድ ስለማልሻም ፍርዴ ትክክል ነው። 'እኔ ስለ ራሴ ብመስክር፣ ምስክርነቴ ተቀባይነት እይኖረውም። ስለ እኔ የሚመለክር ሌላ አለ፣ አርሱ ስለ እኔ የሚስጠውም ምስክርነት አውነት እንደ ሆነ ዐውቃለሁ'" (ዮሐንስ 5÷30-32)። ኢየሱስ፣ "ስለ እኔ የሚመስክር ሌላ አለ" የሚለው አነጋገሩ ምስክር በሁለት ወይም በሦስት ይጸናል የሚለውን የብሉይ ኪዳን ክፍል ታሳበ. ያደረገ ነው (ዘጉልቊ 35÷30፣ 17÷6፣ 19÷15)።

ኢየሱስ ራሱ አብም ወልድም ከሆነ፣ እርሱ ራሱ ስለራሱ መስክሮአልና አርሱ ራሱ አንደ ተናገረው ምስክርነቱ እውነት ሊሆን እይችልም። ነገረ ግን አብና ወልድ የተለያዩ አካላት በመሆናቸው አንዱ የሚመስክርለት ሌላው ደግሞ የሚመስክር ሆኖ ቀርቧል። አንዲሁም በዚሁ ዐውድ ውስጥ፣ "ከራሴ ምንም ማድረግ አልችልም"፣ "የምፈርደው የምስማውን ብቻ ነው"፣ "የላከኝን እንጂ የራሴን ፈቃድ ስለማልሻ"፣ ወዘተ የሚሉት አነጋገሮች እብና ወልድ የተለያዩ እካላት መሆናቸውን ፍንትው እድርገው የሚያሳዩ ናቸው— የሚያይ ዐይን ላለው ዐይናማ ማለቴ ነው።

በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ስም የሚለው ቃል 156 ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን፣ እንደ ብሉይ ኪዳኑ ሁሉ በእነዚህም መጻሕፍት ስም ባሕርይን፣ ግብርንና ሥልጣንን የሚያመለክት ሆኖ ነው የቀረበው። በሌላ እነጋገር "በ__ስም" ማለት "በ__ሥልጣን" ማለት ነው። በዚህ አንጻር አንድ ክፍል እንመልከት፦—

"ዳዊትም ፍልስጥኤማዊውን እንዲህ አለው፤ አንተ ሰይፍ፣ ጦርና ጭሬ ይዘህ ተምጣብኛስህ፤ እኔ ግን አንተ በተገዳደርኸው የእስራኤል ሰራዊት አምላክ በሆነው፣ ሁሉን በሚችል በእግዚአብሔር ስም እመጣብሃለሁ" (1ሳሙኤል 17÷45)።

በዚህ ክፍል ዳዊት፣ "በእግዚአብሔር ስም እመጣብሃለሁ" ሲል፣ ስሜ እግዚአብሔር ተብሎ ወይም እኔና እግዚአብሔር እንድ አካል ሆነን እመጣብሃለሁ ማለቱ ሳይሆን፣ በተገዳደርኸው በእግዚአብሔር ሥልጣን እመጣብሃለሁ ማለቱ ነው። ልክ እንደዚሁ ሁሉ ኢየሱስ፣ "በአባቴ ስም መጣሁ" ሲል፣ "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" መምህራን እንደሚያስተምሩት የአብና የወልድ ስም እንድ ነው ወይም አብና ወልድ እንድ አካል ናቸው ለማለት ተፈልጎ ሳይሆን፣ በአባቴ ሥልጣን ወይም አባቴን ወክዬ መጥቻለሁ ማለቱ ነው።

ከላይ ለማየት እንደ ሞከርንው፣ "ይሖዋ ምስክሮች" ያህዌ የሚለውን ስም በጥሬው በመተርጉም፣ ትልቅ የነገረ መለኮት ኪሣራ ውስጥ እንደ ወደቁ ሁሉ፣ "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" መምህራንም ኢየሱስ የሚለውን የተጻውዖ ስም በተሳሳተ መንገድ በመተርጉም ከእውነተኛው እስተምህሮ ስተው ወጥተዋል። እነዚህ "የአንስ. ጂስስ መምህራን"፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ብቻ መጠመቅ እስባቸው የሚለው ትምህርት የመነጨው በትምህርተ ሥላሴ ላይ ካሳቸው መስመር የሳተ እስተምህሮ ብቻ ሳይሆን፣ በኢየሱስ ስምም ላይ ካሳቸው ስሑት ነገረ መለኮት የመነጨ ነው። የድርጅቱ መምህራን ሰዎች፣ "በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም" መጠመቅ የስባቸውም የሚለውን ሙግት ያዋቀሩት፣ "አብ፣ ወልድና መንፈስ

ቅዱስ" የሚሉት ስሞች፣ የኢየሱስ የማዕረግ ስሞች ናቸው ከሚለው እስተሳሰብ በመነሣት ብቻ ሳይሆን፣ ኢየሱስ በሚለው የተጻውዖ ስም ላይ የተዛባ አመለካከት መያዛቸው ነው።

"ኢየሱስ ክርስቶስ" የሚለው የእግርኛ ስያሜ ከግሪክ አቻው በቀጥታ የተወረሰ ነው። "ኢየሱስ" (በዕብራይስጥ የሹዋ יֵשׁוּעַ በግሪክ የሱስ Ἰησοῦς) ማለት "እግዚአብሔር ያድናል" ማለት ሲሆን፣ "ክርስቶስ" (በዕብራይስጥ ማሺያኽ מָשִׁיחַ፣ በግሪክ ክርስቶስ χριστός) ማለት ደግሞ የተቀባ ማለት ነው።

ኢየሱስ የሚለው ስም በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን ሰዎች በብዛት ይጠሩበት የነበረ ስም ነበር። "ኢየሱስ" ስሚለው የግሪክኛና የእግርኛ ስያሜ የዕብራይስጥ አቻው፣ የሹዋ ወይም ኢያሱ የሚለው የተጻውዖ ስም ነው—በድምፅትም በትርጉምም። ጌታ በተወለደበት በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ ከየትኛውም የዕብራይስጥ ስም ይልቅ ኢየሱስ የሚለው ስም የብዙ ሰዎች መጠሪያ እንደ ነበር ምሁራን ያስረዳሉ። የፍልስፍናና የነገረ መለኮት ምሁሩ ፕሮፌሰር ጌሪ ሃበርማስ፣ በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን ከዘጠና ዘጠኝ ስሞች መካል ሃያ ሁስቱ ኢየሱስ የሚለው ስም እንደ ሆነ በማስረጃ ይሞግታል። ይህ ማለት ከአምስት ሰዎች መካል አንዱ፣ ስሙ ኢየሱስ ወይም የሹዋ ነው ማለት ነው[14]።

በፊልጵስዩስ መልእክት ላይ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ከመስቀል ሞቱና ሞትንም ድል አድርጎ ከተነሣ በኋላ፣

[14] በሚከተለው ድረ ገጽ ላይ ይህን መረጃ የወሰድነው ወርኀ ጥቅምት 2013 ዓ.ም ላይ ነው።
www.garyhabermas.com/articles/The_Lost_Tomb_of_Jesus/losttombofjesus_response.htm

"እግዚአብሔር እጅግ ከፍ አደረገው፤ ከስምም ሁሉ በላይ የሆነውን ስም ሰጠው፤ ይኸውም በሰማይና በምድር፣ ከምድርም በታች፣ ጕልበት ሁሉ ለኢየሱስ ስም ይንበረከክ ዘንድ፣ ምላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ ይመስክር ዘንድ ነው" *(2÷9-11)* የሚል ቃል እናነባለን።

በዚህ ቦታ ኢየሱስ የሚለው ስም፣ ጌታ ወደ መስቀል ከመሄዱ በፊት ይጠራበት የነበረው ስም ነው። ይህ ምንባብ እየተናገረ ያለው ኢየሱስ ስለሚለው የተጻውዖ ስም ሳይሆን፣ ኢየሱስ ሞትን ድል አድርጎ በመነሣት ከፍተኛ ክብር እንደ ተጐናጸፈ የሚያሳይ ነው (ኤፌሶን *1÷21*፤ ዕብራውያን *1÷4-5*)። ምክንያቱም ኢየሱስ የሚለው ስም ቀድሞውኑ ይጠራበት የነበረ ስም ነውና። ንጉሥ ዳዊት፣ "አቤቱ ስለዚህ በአሕዛብ ዘንድ አመሰግንሃለሁ፤ ለስምህም እዘምራለሁ" (መዝሙር *18÷49*) እንዲሁም "ለእግዚአብሔር ተቀኙ፤ ለስሙም ዘምሩ፤ ወደ ምድረ በዳ ለወጣም መንገድ አድርጉ፤ ስሙ እግዚአብሔር ነው" (መዝሙር *68÷4*) ሲል፣ አምላክ ሰሚጠራበት የተጻውዖ ስም አዘምራለሁ ማለቱ አንዳልሆነ ሁሉ፣ ጕልበት ሁሉ የሚንበረከለት ስም የኢየሱስ ስም ነው ማለት የተጻውዖ ስሙ፣ ከኢየሱስ በተለየ መልኩ ስግደት ይቀርብለታል ማለት አይደለም።

ከላይ በስፋት ለመመልከት እንደ ሞከርንው ስም፣ የስሙ ባለቤት ያለውን ባሕርይ፣ ግብርና ሥልጣን የሚያመለክት ስያሜ ነው። ስለዚህ በክርስቶስ ስም ተሰብስቡ ማለት በምትሰበሰቡበት ጊዜ በኢየሱስ ስም በሉ ማለት ሳይሆን፣ በእርሱ ሥልጣን ሥር ስብሰባችሁን አካሂዱ ማለት ነው (ማቴዎስ *18÷20*፤ *1*ቆሮንቶስ *5÷4*)።

ድነትን ወይም ንስሓና የኀጢአት ይቅርታን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ስበኩ ማለት፣ ኢየሱስ ስለዎች ድነት ያደረገውን ገድል ተርኩ ወይም ሞትና ትንሣኤውን ስበኩ ማለት ነው (ሉቃስ *24÷47*፤ ሐዋርያት ሥራ *4÷12*፤ ዮሐንስ *1÷12*፤ ሐዋርያት ሥራ *10÷43*፤ *1*ዮሐንስ *3÷23*፤ *5÷13*)። በአጭሩ ስም የስሙ ባለቤት ካለው ባሕርይ፣ ግብርና ሥልጣን የተለየ ፋይዳ ያለው ነገር አይደለም።

እንግዲያው እውነቱ ይህ ከሆነ፣ በጸሎታችን ማጠናቀቂያ ላይ፣ "በኢየሱስ ክርስቶስ ስም" ብለን ጸሎታችንን ማሳረግ የለብንም ማለት ነው? የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል። ተገቢ ጥያቄ ነው።

"በኢየሱስ ክርስቶስ ስም" መጸለይ ማለት፣ እንደ ክርስቶስ አስተምህሮና አንደ እርሱ ፈቃድ በመጸለይ የእርሱን ክብር መሻት እንደ ሆነ ከላይ ስማየት ሞክረናል፤ "ማንኛውንም ነገር እንደ ፈቃዱ ብንለምን እርሱ ይሰማናል" *(1*ዮሐንስ *5÷14)*። ስለዚህ አንድን ጸሎት ክርስቲያናዊ ጸሎት የሚያለኘው በጸሎቱ መቋጫ ላይ "በኢየሱስ ክርስቶስ ስም" ማለታችን ላይሆን፣ ከጸሎቱ ጅማሬ እስከ ጸሎቱ ፍጻሜ የክርስቶስን አሳብ የሚወክልና የእርሱን ክብር የሚሻ መሆን ይኖርበታል። መጽሐፍ ቅዱስ በኢየሱስ ስም ጸልዩ ሲለን፣ ቀዳማይ መልእክቱ ይኸው ነው። ይዘቱ እርሱን የሚያስከብር ከሆነ፣ በጸሎቱ ማጠናቀቂያ ላይ "በኢየሱስ ስም" ማለታችን አንዳችም ክፋት የለውም—ለእርሱ ያለንን አክብሮት የሚያሳይ እስከ ሆነ ድረስ አግባብ ነው።

"በኢየሱስ ክርስቶስ ስም" ብለን አጋንንትን ማውጣት የለብንም ማለት ነው? ይህም ሊጠየቅ የሚገባው ተገቢ ጥያቄ ነው። ይህን ጥያቄ በአግባቡ ለመመለስ አንድ ሁነኛ የሆነ ጥያቄን ገፋ አድርገን እንመርምር። ይኸውም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተጻውዖ

ስምና (ለምሳሌ ሙሴ፣ ማርያም፣ ኢየሱስ፣ ገብርኤል፣ ያህዌ)፣ በማዕረግ ስም[15] (መቶ አለቃ፣ ጌታ፣ ንጉሥ፣ እግዚአብሔር ወዘተ) መካከል፣ የስዋስው ስያሜ ልዩነት ካልሆነ በስተቀር፣ አንዳችም የፅንስ ሐሳብ (የይዘት) ልዩነት ያለመኖሩን ነው። ዘመነኞቹ የስዋስው ምሁራን ስሞችን በተለያየ ፈርጅ መድበዋቸዋል። ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ግን አጠቃቀማቸውን በተመለከተ በተጻውዖ ስምና በማዕረግ ስም መካከል አንዳችም ልዩነት አላደረጉም። በዚህ ረገድ አንዳንድ አስረጆችን እንመልከት፦— *(1)* ክላይ ለማየት እንደ ሞከርንው ያህዌ የሚለው የተጻውዖ ስም፣ በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትና በሰብዐ ሊቃናት ትርጉሞች ላይ፣ አምላክና አግዚአብሔር በሚሉ የወል ስሞች ተተክቶአል–አንዳችም የትርጉም ልዩነት ሳይኖራቸው። *(2)* ብሉያትም ሆኑ ሐዲሳት በተጻውዖ ስምና በማዕረግ ስም መካከል አንዳችም ልዩነት አላበጁም። በዚህ ረገድ የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል፦—

- “ቀናተኛ” የሚለው ስም የእግዚአብሔር “ስም” እንደ ሆነ ተገልጸአል (ዘፀአት *34÷14*)።
- “ድንቅ መካር”፣ “ኀያል አምላክ”፣ “የዘላለም አባት”፣ “የሰላም አለቃ”፣ የሚሉት ቅጽሎች የመሲሑ “ስም” ናቸው ተብሏል (ኢሳይያስ *9÷6*)።
- “ቅዱስ” የሚለው ቅጽል የእግዚአብሔር “ስም” እንደ ሆነ ተነግሮናል (ኢሳይያስ *57÷15*)።

[15] ብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፣ *የአማርኛ ሰዋስው* በሚለው መጽሐፋቸው፣ እኔ የማዕረግ ስም ያልሁትን፣ እርሳቸው የወል ስምና የጥቅል ስም በሚለው ጐራ ውስጥ ፈርጀውታል፤ ገጽ *17-22* ይመለከቷል።

- “አዳኝ” የሚለው “ስም” ነው (ኢሳይያስ *63÷16*)።
- “ክርስቶስ” “ስም” ነው (ማቴዎስ *24÷5* ከ*1*ጴጥሮስ *4÷14* ጋር ያነጻጽሯል)።
- “የእግዚአብሔር ቃል” “ስም” ነው (ራእይ *19÷13*)።
- “የነገሥታት ንጉሥ”፣ “የጌቶች ጌታ” ስም ነው (ራእይ *19÷13*)።

“አምላክ”፣ “ጌታ” እና “እግዚአብሔር” በሚሉት ስሞች ላይ “የእኛ” (“የእኛ አምላክ”)፣ “የእስራኤል” (“የእስራኤል አምላክ”) ወዘተ የሚሉት ቅጽሎች ተቀጽለውበት የሚገኙ ስለሆነ፣ ቃሉ የማዕረግ ስምን ማለየቱ እሙን ነው። ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፣ ይህ ዐይነቱ የማዕረግ ስም የተጻውዖ ስም ሆኖ ሊያገለግል እንመለከታለን። በዕብራይስጥ “መሲሕ” (ማሻሽ)፣ በግሪክ “ክርስቶስ” የሚለው ቃል፣ የማዕረግ ስምን በሚያሳይ መልኩ ጥቅም ላይ ውሎአል (ለምሳሌ ማቴዎስ *16÷16*፤ ሉቃስ *24÷46*፤ ዮሐንስ *1÷41*)። በአንጻሩ ደግሞ “ክርስቶስ” የሚለው ይኸው ቃል፣ የተጻውዖ ስምን በሚያመለክት መልኩ በአብዛኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ላይ አገልግሎአል (“ኢየሱስ ክርስቶስ” እንዲሉ)። ክዚህ የምንማረው ትልቁ ቁም ነገር፣ ቅዱሳት መጻሕፍት በተጻውዖ ስምና በማዕረግ ስም መካከል አንዳችም የትርጉም/የፅንሰ ሐሳብ ልዩነት ያለማድረጋቸውን ነው።

“የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን” መምህራን (“እንሊ ጂሰሶች”) በተጻውዖ ስምና በማዕረግ ስም መካከል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ ልዩነት በማኖራቸው ምክንያት፣ ማቴዎስ *28÷19* ላይ የምናገኘውን፣ “አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ” የሚለውን የጥምቀት ቀመር፣ ስዎችን በማጥመቅ ሂደት ውስጥ ተፈጻሚ ልናደርገው አንችልም

ባይ ናቸው። ለዚህ ምክንያታቸው ደግሞ፣ "አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ" የሚሉት ቃላት የተጸውዖ ስም ሳይሆኑ፣ የማዕረግ ስም ናቸው። በማዕረግ ስም ደግሞ ማጥመቅ በትክክል፣ እግዚአብሔርን እያመለክትም (በግእዝ ቋንቋ "አብ" ስንል "አባት" ማለታችን፣ "ወልድ" ደግሞ ስንል "ልጅ" ማለታችን ነውና። ብዙ አባቶች ብዙ ልጆች ባሉበት ምድር በዚህ ዐይነት መልኩ ጥምቀትን ማካሄድ ስሕተት ነው) ባዮች ናቸው[16]።

በብሉይ ኪዳንም ሆነ በሐዲስ ኪዳን፣ በተጸውዖ ስምና በማዕረግ (በወል) ስም መካከል አንዳችም የይዘት ልዩነት እንደ ሌለ ከላይ ተመልክተናል። ይህ እንደኛውና መሠረታዊው ነጥብ ነው። ሁለተኛው ነጥብ፣ በማቴዎስ *28÷19* ጌታ፣ "በአብ፣ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም" አጥምቁ ብሎናል። እነርሱ እንደሚሉት በማዕረግ ስምና በተጸውዖ ስም መካከል የይዘት ልዩነት ቢኖር ኖሮ፣ ጌታ በማዕረግ *ስም አጥምቁ* የሚል ትእዛዝ አይሰጠንም ነበር[17]።

በአጠቃላይ በማዕረግ ስምና በተጸውዖ ስም መካከል ያለው ልዩነት የሰዋሰው ስያሜ ልዩነት እንጂ፣ የፅንስ ሐሳብ (የትርጉም) ልዩነት አንዳልሆነ በግልጽ መረዳት ይኖርብናል። ስለዚህ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም መጠመቃችን ወይም ማጥመቃችን፣ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ሥልጣን ሥር ማደራችንን የሚያሳይ ነው።

[16] ተክለ ማርያም ገዛኸኝ፣ *አድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል አዲስ ልደት!* (አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ) ገጽ *117*።

[17] ይህ መናፍቃዊ ድርጅት በጥምቀት ላይ የሚያስተምረውን የተሳሳተ ትምህርት በስፋት ለመመርመር ከፈለጉ፣ የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ፣ *ሰባልዮሳውያን* በሚል ርእስ ያዘጋጃቸውን ሁለት ተከታታይ ትጽ መጻሕፍት ይመልከቷል።

ስለዚህ ስይጣንን "በኢየሱስ ክርስቶስ ስም" ብቻ ሳይሆን፣ "በወልድ ስም"፣ "ድንቅ መካር፣ ኀያል አምላክ፣ የዘላለም አባት፣ የሰላም አስቃ ስም"፣ "በአዳኙ ስም"፣ "በክርስቶስ ስም" ወዘተ ብሎን በመቃወም ማባረራችን አግባብ ነው። እነዚህ ስሞች ሁሉ የሚያመለክቱት ያው አንዱን ክርስቶስ፣ አንዱን ጌታ ነውና።

እነዚህ ሁሉ ስሞች የኢየሱስ ስሞች እንደ ሆኑ የነገሩን ቅዱሳት መጻሕፍት፣ ይጠራባቸው ዘንድ እርሱን ስለሚመጥኑት፣ ባሕርዩንም ስለሚያመለክቱ ነው። "መቶ አለቃ" የሆነን ወታደር፣ "ሣምሳ አለቃ" ወይም "ሻለቃ" ወይም ደግሞ "ኮሎኔል" ብሎ መጥራት ስሕተት ነው። ሣምሳ አለቃ የሚለው ማዕረግ የግለሰቡን ሥልጣን የሚያሳንስ ሲሆን፣ ሻለቃ ወይም ኮሎኔል ብሎ መጥራት ከግለሰቡ ሥልጣን በላይ ስለሆነ ስሕተት ነው። ኢየሱስ በተሰያዩ ስሞች የተጠራው ስሞቹ ሁሉ በትክክል እርሱን ስለሚመጥኑት ነው። ይህ እውነት ከሆነ ደግሞ፣ አንዱን የጌታ ስም ክሌላው ስም ማበላለጥ ትክክል አይደለም።

ዳዊት ጎልያድን፣ "ዳዊትም ፍልስጥኤማዊውን እንዲህ አለው፣ አንተ ሰይፍ፣ ጦርና ጭሬ ይዘህ ትመጣብኛለህ፣ እኔ ግን አንተ በተገዳደርኸው የእስራኤል ስራዊት እምላክ በሆነው፣ ሁሉን በሚችል በእግዚአብሔር ስም እመጣብሃለሁ" *(1ሳሙኤል 17÷45)* ሲለው፣ ዳዊት የውክልና ጦርነት እንደሚዋጋ የሚያሳይ እንጂ፣ ወንጭፉን ባስወነጨፈ ጊዜ ሁሉ የአምላክን ስም መጥራቱን የሚያመለክት እይደለም። የመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ መልእክት ይህ ሆኖ ሳለ፣ የያህዌን ስም (የኤልሻዳይን ወዘተ ስም) ጠርቶ ወንጭፉን ቢያስወነጭፍ ደግሞ አንዳችም ስሕተት ያለበትም፣ ሊኖርበትም አይችልም። ስለዚህ የክርስቶስን ስም እየጠራን

አጋንንትን ማስወጣት እንችላለን፤ ነገር ግን የጌታን ስም ጥሩ የሚሰውን ቃል ከመሠረታዊ ትርጕሙና መጽሐፍ ቅዱስ ሊያስተላልፈው ከሚፈልገው ትምህርት በወጣ መልክ ልንረዳው አይገባም።

መጽሐፍ ቅዱስ "በስሜ አጋንንትን" እውጡ ሊለን[18]፤ የዚህ ዓለም ገዢ በሆነው በዲያብሎስና በጭፍሮቹ ፊት ክርስቶስን ወክላችሁ ቅረቡ ማለት ነው—ከላይ ባየነው ከፍል ዳዊት፤ ያህዌን ወክሎ በጎልያድ ፊት እንደ ቀረበው ማለት ነው። "የኢየሱስን ስም" መጥራት ብቻ በራሱ ተአምር የሚያደርግ ቢሆን ኖሮ፤ ክርስቶስ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው ያልተቀበሉ አይሁድ፤ የኢየሱስን ስም በመጥራት አጋንንትን ለማውጣት ያደረጉት ሙከራ እይከሸፍም ነበር። እንዲያውም ይህን ለማድረግ ሙከራ ባደረጉት ሰዎች ላይ እርኩስ መንፈስ ያደረበት ሰው ክፉኛ እንዳጠቃቸው ከዚህም የተነሣ፤ የነበሩበትን ቤት ዕርቃናቸውን ጥሰው እንደፈረጠጡ እንመለከታለን። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ፤ "ኢየሱስ" የሚሰውን የተጻውዖ ስም መጥራት ላይሆን፤ በዚህ ስም የሚጠራውን ታላቅ ጌታ በእምነት ወክሎ የመቅረቡ ጕዳይ፤ ዋነኛ ነገር እንደ ሆነ የሚያሳስብ ነው።

> "እየዞሩ አጋንንትን ያስወጡ ከነበሩት አይሁድ አንዳንዶቹ፤ 'ጳውሎስ በሚሰብከው በኢየሱስ ስም እንድትወጡ እዛችኋለሁ!' እያሉ የጌታን የኢየሱስን ስም ርኩሳን መናፍስት በያዟቸው ሰዎች ላይ ለመጥራት ሞክሩ፤ የአይሁዳዊው የካህናት አለቃ የእስቄዋ ሰባት ወንዶች ልጆችም ይህንኑ ያደርጉ ነበር። ርኩስ መንፈሱም፤ 'ኢየሱስን ዐውቀዋለሁ፤ ጳውሎስንም ዐውቀዋለሁ፤ እናንተ ግን እነማን ናችሁ?' አላቸው። ከዚያም ርኩስ መንፈስ ያደረበት ሰው ዘሎ ያዛቸው፤ በረታባቸውም፤ እጅግ ስላየሰባቸውም ቤቱን ጥሰው ዕራቍታቸውን ሸሹ" (ሐዋርያት ሥራ 19÷13-16)።

ማጠቃለያ

በዚህ ክፍል ቅዱሳት መጻሕፍት የአምላክን የተጻውዖ ስም በተመለከተ ያላቸውን ትምህርት ለመዳሰስ ሞክረናል—በተለይ ከርእሰ ጕዳዩ ጋር በተገናኘ፤ ትልቅ የእስተምህሮ አደጋ ሊጋርጡ የሚችሉትን አንኳር አንኳር መሰናክሎች ከመንገድ ላይ ገለል ያደረግናቸው ይመስለኛል። በቅዱሳት መጻሕፍት ስም ባሕርይን፤ ግብርንና ሥልጣንን የሚያመለክት ሁነኛ ሰንደቅ ዐላማ ነው።

የእንድ ተጻውዖ ስም ታላቅነት የሚወሰነው፤ የስሙ ባለቤት ማን ነው በሚለው ማመሳከሪያ እንደ ሆነ ሁሉ የአምላክ ስም ታላቅ፤ ከቡር...የሆነው አማዚአብሔር እምላካችን ክቡርም ትልቅም ስለሆነ ነው። "የያህዌን ስም ከፍ ማድረግ" ማለት፤ እግዚአብሔርን በኑሮአችንና በአገልግሎታችን የበላይ ማድረግ ማለት አንጂ፤ እምላክን በተጻውዖ ስሙ መጥራት ማለት እይደለም።

"በክርስቶስ ስም መጸለይ" ማለት በጸሎት ማጠናቀቂያ ላይ "በኢየሱስ ስም" ማለት ላይሆን፤ አንደ ክርስቶስ አሳብና ፈቃድ ጸሎትን ማድረስ ማለት ነው። በክርስቶስ ስም መሰብሰብ፤ ለክርስቶስ

[18] መጽሐፍ ቅዱስ፤ "በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ" (ማርቆስ 16÷17) የሚለውን ክፍል፤ "በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አጋንንትን ያወጣሉ" ብለን ልናነበው አይገባም። ስለዚህ የኢየሱስ የሆኑ ስሞችን ሁሉ እርሱን የሚመጥኑት ከሆነ፤ እነዚህን ስሞች ሁሉ በመጥራት አጋንንትን ብናወጣ ተሳስታችኋል ልንባል አንችልም።

ስም መሰገድ ወዘተረፈ ማለት፣ በእርሱ ሥልጣን ሥር መዋቀር፣ በእርሱ ማዕከልነት መደራጀት፣ በእርሱ ጥላ ሥር መጠለል፣ በመጠጊያነቱ ውስጥ ማደር፣ ለእርሱ አምልኮተ ስግደት ማቅረብ፣ እንደ ቃሉ መኖር ወዘተ ማለት ነው። እንግዲያው የእግዚአብሔርን ስም የምንቀድሰው፣ ኑሮአችንንና አስተላለባችንን በእርሱ አሳብና ፈቃድ ውስጥ በመክተት እንጂ፣ በአንድ ግብር መጨረሻ ላይ የተጸውዖ ስሙን በመጥራት ወይም ባለመጥራት አይደለም።

አባይ ነባሮች ያሻቸውን አድርገው፣ በድርጊታቸውም መጨረሻ "በኢየሱስ ስም" ማለታቸው፣ ግብራቸውን አያጸድቅም አስተምህሮአቸውን ርቱዕ አያደርገውም። "ኢየሱስ" የሚሰው ስም መጠሪያ እንጂ፣ ምትሐታዊ ቀመር አይደለምና።

እንዲያውም መጽሐፍ ቅዱስ በመጨረሻው ዘመን አባይ ነባሮች "እኔ ኢየሱስ ነኝ" እያሉ በስሙ እንደሚመጡ ጌታ ራሱ ነግሮናል፣ "ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፣ ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ። ብዙዎች እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉና፤ ብዙዎችንም ያስታሉ...ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉና፤ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያላያሉ" (ማቴ. 24÷4-5፡24)። ወገን ስማ—የኢየሱስን ስም የጠራ አባይ ነባይ ሁሉ፣ ከእግዚአብሔር ነው ማለት ስሕተት ነው።

ክፍል ዐሥራ አንድ

የአባይ ነባዮችና የመናፍቃን መበራከት ምስጢር ምንድን ነው?



ሀ. ሰዎች አባይ ነባዮችን እንዲሁም መናፍቃንን ለምን ይከተላሉ?[1]

አጠቃላይ አስሳ

የእንድን ክሥተት ትክክለኛ መንሥኤ ማወቅ፣ የመፍትሔው አስተንትኖት ቀዳማይ አርምጃ ነው።

[1] የክፍሉ ጭብጥ በአብዛኛው የተወሰደው፣ ከሚከተለው መጽሐፍ ነው:— *Alan W. Gomes, Unmasking the Cults (Grand Rapids: Zondervan, 1995), 81-85.*

ስም መስገድ ወዘተረፈ ማለት፣ በእርሱ ሥልጣን ሥር መዋቀር፣ በእርሱ ማዕከልነት መደራጀት፣ በእርሱ ጥላ ሥር መጠለል፣ በመጠጊያነቱ ውስጥ ማደር፣ ለእርሱ እምልኮተ ስግደት ማቅረብ፣ እንደ ቃሉ መኖር ወዘተ ማለት ነው። እንግዲያው የእግዚአብሔርን ስም የምንቀድሰው፣ ኑሮአችንንና አስተሳሰባችንን በእርሱ አሳብና ፈቃድ ውስጥ በመክተት እንጂ፣ በአንድ ግብር መጨረሻ ላይ የተጻፈውያ ስሙን በመጥራት ወይም ባስመጥራት አይደለም።

አባይ ነባሮች ያሻቸውን አድርገው፣ በድርጊታቸውም መጨረሻ "በኢየሱስ ስም" ማሰታቸው፣ ግብራቸውን አያጸድቅም አስተምህሮአቸውን ርቱዕ አያደርገውም። "ኢየሱስ" የሚሰው ስም መጠሪያ እንጂ፣ ምትሐታዊ ቀመር አይደለምና።

እንዲያውም መጽሐፍ ቅዱስ በመጨረሻው ዘመን አባይ ነባሮች "እኔ ኢየሱስ ነኝ" እያሉ በስሙ እንደሚመጡ ጌታ ራሱ ነግሮናል፣ "ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፣ ማንም አንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ። ብዙዎች እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉና፣ ብዙዎችንም ያስታሉ...ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉና፣ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ" (ማቴ. 24÷4-5:24)። ወገን ስማ—የኢየሱስን ስም የጠራ አባይ ነባይ ሁሉ፣ ከእግዚአብሔር ነው ማስት ስሕተት ነው።

ክፍል ዐሥራ አንድ

የአባይ ነባዮችና የመናፍቃን መበራከት ምስጢር ምንድን ነው?



ሀ. ለምች አባይ ነባዮችን እንዲሁም መናፍቃንን ለምን ይከተላሉ?[1]

አጠቃላይ አሰሳ

የአንድን ክሥተት ትክክለኛ መንሥኤ ማወቅ፣ የመፍትሔው አስተንትኖት ቀዳማይ እርምጃ ነው።

[1] የክፍሉ ጭብጥ በአብዛኛው የተወሰደው፣ ከሚከተለው መጽሐፍ፣ ነው:— *Alan W. Gomes, Unmasking the Cults (Grand Rapids: Zondervan, 1995), 81-85.*

አንግዲያው ለምች አባይ ነባሮችን አንዲሁም መናፍቃንን ለምን አንደሚከተሉ አንመርምር።

1. የግል ፍላጎት ምክንያት ሊሆን ይችላል

ወደድንም ጠላንም፣ ማንኛውም ለው የራሱ የሆነ ፍላጎት አለው—መጠኑና ዐይነቱ ቢለያይም አንኳ። የአዳም ዘር፣ ዐቅሙ በፈቀደ መንገድ ሁሉ፣ አነዚህን ፍላጎቶች ቢሆን በቋሚነት ባይሆን በጊዜያዊነት ለማርካት የተቻለውን ትንቅንቅ ይገጥማል። ሰብአዊ ፍጡር ሊያሟላ የሚፈልገው ትልቅ ፍላጎት አንዳለው፣ ከማንም ይልቅ በውል የተረዱት በዙሪያችን የፈሉት አባይ ነባሮችና መናፍቃን ናቸው።

ይህን የለው ልጅ ፍላጎት እጅግ ቀላል፣ አጅግ ፈጣን አንዲሁም አጅግ ፍቱን ወይም ዘላቂ በሆነ መንገድ መፍታት የሚያስችል መፍትሔ፣ በአነርሱ እጅ ብቻ እንደሚገኝ አጠንክረው ይገልጻሉ። ይህ ሁኔታ ለምች በቀላሉ ወደ አባይ ነባሮችና መናፍቃን አንዲሳቡ ምክንያት ይሆናል። ችግሩ አንዲፈታለት የማይፈልግ ማነው? ችግር በሌለበት ሕይወት ውስጥ መኖር የማይፈልግ ሰብአዊ ፍጡር ማን ነው?

ኩርት ቫን ጎርደን የሚባሉ ስመ ጥር ዐቃቤ እምነት፣ "መናፍቃንን በወንጌል መድረስ" በተባለው መጽሐፋቸው ላይ፣ ለምች አባይ ነባሮችንና መናፍቃንን በመከተል ሊያረኳቸው የሚሻቸውን ፍላጎቶች በአራት ከፍል መድበዋቸዋል። ይኸውም:— አአምሮአዊ ፍላጎት፣ ማኅበራዊ ፍላጎት፣ ስሜታዊ ፍላጎትና መንፈሳዊ ፍላጎት ናቸው[2]። ማንኛውም ለው አነዚህ ፍላጎቶች በተለያየ መጠን

[2] ዝኒ ከማሁ *Kurt van Gorden, "Unity School of Christianity" in Evangelizing the Cults* ገጽ 140 ጠቅሶ አንደ ጸፈው።

ስላሉት፣ ፍላጎቶቹ በራሳቸው መጥፎ አይደሉም። አነዚህንም ተገቢ ፍላጎቶች በአግዚአብሔር ቃል አውነት ያለማርካት፣ ለምች በመናፍቃዊ አንቅስቃሴ ውስጥ አንዲሳቡ ወይም አዲስ መናፍቃዊ አንቅስቃሴ አንዲጀምሩ ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ።

አባይ ነባሮችና ሉላዊነት *(globalization)* የሚባለው የምጣኔ ሀብት ፍልስፍና፣ በአንድ ሁነኛ መንገድ ይመሳሰሉብኛል። ሉላዊነት አዳዲስ ምርትን ካስተዋወቀ በኋላ፣ ኋላ ምርቱን መጠቀም በሕይወት ለመኖር ወሳኝ ጉዳይ አንደ ሆነ ለምች አምነው አንዲኖሩ ያስገድዳል። አንድ ምሳሌ ልጥቀስ፣ በቀድሞ ጊዜ በአገራችን ኢትዮጵያ ስኳር በጭራሽ አይታወቅም ነበር—ያውም በእኔ ዕድሜ (ወደራ ዕድሜዬን አንዳልጠየቅ)። ደቾች (የሆላንድ አገር ለምች) በመተሐራና በወንጂ የስኳር ፋብሪካዎችን ከፍተው ስኳር ቢያመርቱም፣ ሕዝቡ ግን ለምርቱ አንዳችም ቊብ አልነበረውም። በወቅቱ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ብርቅ ስለነበር፣ አነዚህ ድርጅቶች ምርታቸውን ያስተዋውቁ የነበሩት ጥሩንባ ነፊ፣ ነጋሪት ጉሳሚ በየመንደሩ በመነስነስ ነበር።

የአነዚህ ፋብሪካዎችም ሎጎ ዝሆን ነበር—ስኳር አንደ ዝሆን ያፋፋል፣ ያጠነክራል ለማለት ተፈልጎ ይመሰለኛል ዝሆን አንዲመረጥ ምክንያት የሆነው። አስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በአገራችን በኢትዮጵያ ውፋሮ፣ አንደ ትልቅ ሰማያዊ በረከት አንደ ልዩ የአምላክ ጸጋ ይታይ ነበር—የዛሬን አያድርገውና።

ከፋብሪካው ግንባታና ከምርታማነቱ ይልቅ፣ የፋብሪካውን ባለሀብቶች ያደከማቸው ስኳርን ለኢትዮጵያውያን ማቅመስ ነበር። ዛሬ ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለስኳር መኖር አንዳሰቸገረው፣ የስኳር ጉዳይ ትልቅ የፖለቲካ አጀንዳ አንደ ሆነ አየታየ ነው። የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር፣ "ስኳር የተወደደው ገበሬው ስኳር ስለቀመሰ፣

ጣዕምናውን ስላጣጣመ እንጂ፣ ምርቱ ስለተጓደለ አይደለም" የሚል መከራከሪያ፣ ፓርላማው ዘንድ ይዘው ቀርበው እንደ ነበር አስታውሳለሁ። እነሆ ዛሬ ስኳር የምቾትና ይጥፍጥና ሁሉ ቀኖና ሆኖ ያገለግላል።

በአንድ ወቅት በዓለማችን፣ ኢንተርኔት/ዋይ ፋይ[3] አገልግሎት አይታወቅም ነበር። ዛሬ የዓለማችን ነዋሪ ሕይወቱ በብዙ ረገድ የተቈራኘው ከዚሁ ዘመን አመጣሹ ኢንተርኔት ጋር ነው። ይኸው ዛሬ ያለተንቀሳቃሽ ስልክ፣ ያለኢሜል፣ ያለፊስቡክ፣ ያለቴሌቪዥን፣ ያለሬዲዮ መኖር እጅግ አስቸጋሪ እየሆነ ነው። ምናልባትም ያለእነዚህ መኖር የማይቻልበት ዘመን ላይ ደርሰናል ቢባል ግነቱ መጠነኛ ነው። በአንድ ወቅት እነዚህን ነገሮች አንጠቀምም ነበር፤ አንዲያውም መኖራቸውንም አናውቅም ነበር። ዛሬ ግን በዐጸደ ሥጋ ስመኖር ዋነኛ ጉዳዮች ሆነው ቀርበውልናል።

የሉላዊነት የምጣኔ ሀብት ፍልስፍናንና አባይ ነባዮችን የሚያመላለሳቸው፣ በሰው ሕይወት ውስጥ ፍላጎት በመፍጠር እንደ ዋዛ ያስገቡት "ሸቀጥ"፣ ኋላ ደስ እኔ ምድራዊ ህልውና ሊኖራችሁ አይችልም ይላል።

እንደ አንጉዳይ በዙሪያችን የፈሉት አባይ ነባዮች፣ "ትፈወሳለህ...አሜን በል!"፣ "የያዝኸው የረዘዝኸው ሁሉ ይባረካል...ጕንህ ላለው ዐውጅለት!"፣ "በድል ላይ ድል በጸጋ ላይ ጸጋ ትጐናጸፋለህ...የገባው አሜን ይላል!" በሚለው ስብከታቸው በክርስቶስ ትመጣለች የምትባለውን መጻኢ ዘመን፣ አሁኑኑ ከጕናችን ይከሥቷታል። ልክ ነው በግዳጅ ካልሆነ በቀር፣ ከችግር ጋር መኖር ማን ይፈልጋል? ፍላጎቱ ተሟልቶለት አምሮ ደምቆ መኖር ማን ይጠላል? ስለዚህ የአባይ ነባዮች ስብከት የማያማልለው፣

[3] "ዐውደ መረብ" የሚል ስም ወጣለት ልበል?

ዐዋጃቸው ጕምን መጨበጥ፣ መርዝን መጨለጥ እንደ ሆነ የተረዳ "ተራማጅ"[4] ብቻ ነው።

አባይ ነባዮችና የሉላዊነት ፍልስፍና ፍላጎት በመፍጠር ወይም በመጫር ረገድ አንድ ዐይነት ጠባይ ቢኖረውም፣ መፍትሔንና እርካታን በማምጣቱ ረገድ ግን፣ የአባይ ነባዮቹ ስብከት ህልም ነው፤ ቅዠት ነው። አባይ ነባዮችና መናፍቃን የተከታዮቻቸውን ፍላጎት ለጥቂት ጊዜ ሊያሟሉ ይችሉ ይሆናል፤ ይሁን እንጂ ለችግሮቹ የሚሰጡት መፍትሔ ዘላቂነትም ሆነ እውነተኛነት ሊኖረው አይችልም። ምክንያቱም ለሰዎች ችግር ትክክለኛና ዘላለማዊ መፍትሔ ከሚሰጠው ከእውነተኛው ወንጌል ርቀዋልና። ከዚህም የተነሣ የተከታዮቻቸውን ፍላጎት ማርካት ይሳናቸዋል። የሰዎችን ፍላጎት ዘላቂ በሆነ መልኩ ማርካት የሚችለውና ጥያቄዎቻቸውን መመለስ የሚችለው መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነውና።

ወደድንም ጠላንም፣ ክርስትናም ሆነ ቅዱሳት መጻሕፍት የታመመ ሁሉ ይፈወሳል፣ የተቸገረ ሁሉ ከችግሩ ነጻ ይወጣል፣ ያጣ የነጣ ሁሉ ቱጃር ይሆናል የሚል ትምህርት በጭራሽ የላቸውም[5]። አምላክ ሊፈውስን፣ ከብሩን በእኛ ሊገልጥ ቢፈልግ የእኛ ነቢያትን ማሳደድ አንዳችም ፋይዳ የለውም። አምላካችን ልዑል መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ፈቃዱም አውን አንዳይሆን የሚከለክለው አንዳችም ምክንያት የለም። የአምላክ ልዑላዊ ፈቃድ በአድራሻችን ያገኘናል። ሊፈውስን ከፈለገ አድራሻችን ሊጠፋው አይችልም። ባይሆን እንኳ የተሻለውን ትንሣኤ ተስፋ በማድረግ ወደ መጻኢው

[4] ያልባነነውን ከ"አድሃሪ" ጋር ለማነጻጸር ነው።

[5] ለበለጠ ማብራሪያ፣ "ክርስትና ለጤንነትና ለሀብት ዋስትና አልሰጠም" (ገጽ 197-204) የሚለውን ክፍል ይመለከቷል።

ሕይወት እንሰበሰባለን (ዕብ. *11÷35-40*)። ችግርና ሕማም ቢኖር አንኳ፣ ነይሌ በድካምህ ይገሰጻል፤ ጸጋዬ ይበቃኻል ወዘተ የሚሰውን የጀግኖች ሐዋርያትና ነቢያትን አምነት ኖረን፣ በእምነት ጀግነን ልናልፍ አንጂ፣ የአባይ ነባዮች መጫወቻ ልንሆን እይገባም (ዕብ. *11÷35-40*፤ ማቴ. *8÷20*፤ *1*ቆሮ. *4÷9-13*፤ *2*ቆሮ. *11÷23-27*፤ *12÷10*፤ ያዕ. *5÷10-11*)።

2. አስተምህሮ ምክንያት ሊሆን ይችላል

ሰዎች ትክክለኛውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ ከተረዱ በኋላ፣ የተረዱትን አውነት ትተው መናፍቃዊ እንቅስቃሴ ውስጥ አይገቡም ብሎ ማሰብ አግባብ ላይሆን ይችላል። ነገር ግን በአንጻራዊነት ሊታይ፣ በዚህ መልኩ መናፍቃንን የሚከተሉ ሰዎች በጣም ጥቂት ናቸው። በአሜሪካን አገር በተደረገ አንድ ጥናት መሠረት፣ አብዛኞቹ ስዎች የሞርሞንን አምነት የሚቀበሉት፣ ሞርሞኖች ምን ዐይነት አምነት እንዳላቸው እሰቀድመው ካወቁ በኋላ ነው።

3. ቤተ ክርስቲያን ማሟላት ያለባትን ሳታሟላ ስትቀር

ሰዎች ቤተ ክርስቲያን እንድታሟላላቸው የሚፈልጉትን ነገር ተሟልቶ ካላገኙት፣ መናፍቃዊ እንቅስቃሴ ሊጀምሩ አሊያም በተጀመረው እንቅስቃሴ ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ። ሦስት አራተኛ የሚሆኑት የሞርሞን ቤተ ክርስቲያን አባላት፣ በአንድ ወቅት

የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን አባላት የመሆናቸው[6] ጉዳይ፣ ይህንኑ እውነት የሚያጠናክር ነው።

የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያንን በእጅጉ እያሳሰቡ የሚገኙት አብዛኞቹ አባይ ነባዮች ከቤተ ክርስቲያን የወጡ ናቸው። "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" በመባል የሚታወቀውን የኑፋቄ ድርጅት የመሠረቱት ቢሾፕ ተክለማሪያም ገዛኸኝ በአንድ ወቅት የሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ወንጌላዊ ነበሩ። ነገር ግን እንድ በራሪ ጽሑፍ/ትራክት በማንበብ የድርጅቱን አስተምህሮ እንደ ተቀበሉ እንዲያውም የኑፋቄ ድርጅቱ ፊታውራሪ እንደ ሆኑ ይታወቃል[7]። "የይሖዋ ምስክሮች" ድርጅት መሥራች የነበረውም ቻርልስ ታዝ ራስል በአንድ ወቅት የወንጌላውያን ቤተ ክርስቲያን አባል ነበር።

ቫን ባለን መናፍቅነትን፣ "ያልተከፈለ የቤተ ክርስቲያን ዕዳ"[8] ብሎ ይጠራዋል። ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን መመላት ያቃታትን ባደነት፣ መናፍቃን እየሞሉ ብዙዎችን በማሳሳት ላይ ስለሚገኙ ነው። ከጊዜ ወደ ጊዜ የመናፍቃን ቍጥር እየጨመረ መምጣት፣ የቤተ ክርስቲያንን ጉድለት የሚያሳይ ነው። ይህ ሊባል ግን፣ ቤተ ክርስቲያን የሰዎችን ተገቢ ፍላጎት ማርካት የምትችለው፣ የምእመናኑ ፍላጎት ሊታከልበት አንደሆነም መዘንጋት የለብንም፤ ቢሆንም ግን ቤተ ክርቲያን የአባሎቿን መንፈሳዊ፣ እእምሮአዊ፣

---

[6] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ *152* *Josh Mc Dowell and Don Stewart, Assisted by Kurt Van Gorden The Deceivers.*

[7] ለበለጠ ማብራሪያ የዚህ ጽሑፍ ጸሓፊ፣ "ስባልዮሳውያን" በሚል ርእስ ያዘጋጀውን ሁለት ቅጽ መጽሐፍ ይመለከቱ።

[8] ዝኒ ከማሁ ገጽ *152* *Van Baalen, Chaos of the Cults* ገጽ 390 ጠቅሶ እንደ ጻፈው።

ማኅበራዊና አካላዊ ፍላጎት አንደ እግዚአብሔር ቃል የማርካት ታላቅ ኀላፊነት አለባት።

ዛሬ ለያዥ ለገራዥ ያስቸገረው የአባይ ነባሮች ጉዳይ፣ በአንድ ጀንበር ወደ ቤተ ክርስቲያን የነባ ችግር አይደለም። ለረጅም ዓመታት፣ "ለክፋት አይለጥም" የሚባሉ ትምህርቶችና አካሄዶች ናቸው ዛሬ ተጠረቃቅመው ድንገት ደራሽ ጐርፍ ሆነው ከተፍ በማለት፣ ቤተ ክርስቲያንን ታላ አልባ ያደረጓት። ዛሬም ይህ ችግር፣ በአንድ ጀንበር አልባት ያገኛል ብሎ ማሰብ ቂልነት ነው። ቀስ በቀስ አንደገባ፣ ቀስ በቀስ ነው የሚወጣው። በተቀናጀ አኩይ ጥረት እንደ ገባ፣ በተቀናጀ ሠናይ ጥረት ነው የሚወጣው። ለመግባት ጊዜ አንደ ፈጀበት ሁሉ ለመውጣትም ጊዜ ይፈልጋል።

ሰ. ሰዎች አባይ ነባሮችንና መናፍቃንን በመጠጋት ሊያሟሏቸው የሚሹአቸው ፍላጎቶች

1. ፍቅር

ለዎች አባይ ነባሮችንም ሆነ መናፍቃንን ከሚጠጉባቸው ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ፍቅርና ክብካቤ ፍለጋ ነው። ይህን በበቂ ሁኔታ ካገኙ ባገኙባቸው ስፍራዎች እስከ መጨረሻው ለመቆየት ይገደዳሉ። የአባይ ነባይ ተከታዮችንም ሆነ መናፍቃንን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት አዳጋች ከሚያደርጉአቸው ምክንያቶች ውስጥ ይህ አንዱ ነው። ለዎች፣ "ዩኒቲ ስኩል አፍ ክርስቲያኒቲ" በሚባለው መናፍቃዊ ድርጅት አንዲሳቡ የሚያደርጋቸው፣ ድርጅቱ ለፍቅር ከፍተኛ ስፍራ ስለሚሰጥ ነው[9]።

[9] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 153 ከMc Dowell & Stewart, The Deceivers ገጽ 18 ጠቅሶ አንደ ጸፈው።

2. ቤተ ሰብ

ወጣቶች አባይ ነባሮችንና መናፍቃንን ከሚከተሉባቸው ምክንያቶች አንዱ፡— ለጊዜውም ቢሆን የሚንከባከባቸው ቤተ ሰብ ስለሚፈልጉ ነው። የቤተ ሰብ መፍረስ፣ በወላጆችና በልጆች መካከል የማያቋርጥ ጠብ መኖር እንዲሁም አግባብ ባልሆነ መልኩ ልጆችን መቅጣት፣ ወጣቶች አዲስ ቤተሰብ አንዲፈልጉ ያደርጋቸዋል።

በተለይ ዛሬ በርካታ አባይ ነባሮች ፕሮግራሞቻቸውን በቴሌቪዥን ማስተላለፋቸው በርካታ ወጣቶች በመርዛቸው እንዲመረዙ ምክንያት ይሆናል። በቤተ ክርስቲያን አካባቢ የተጠናከረ የወጣቶች የሰንበት ትምህርት ቤት ያለመኖር፣ ወጣቶች በቴሌ ቪዥን የሚተላለፉ የአባይ ነባሮች ፕሮግራም ትክክል ነው ብለው አንዲያስቡ ሊያደርጋቸው ይችላል። መሠረታዊውን የክርስትና እምነት የማያውቁ ከሆነ፣ ትምህርቶችን የመመርመር ዐቅማቸው ደካማ ይሆናል።

3. ተፈላጊነትና ከበሬታን ማግኘት

ለዎች በጎብረተሰቡ ውስጥ ተቀባይነት ካጡ ወይም ቤተሰባዊነት የማይሰማቸው ከሆነ፣ አላዛኝ በሆነ ሁኔታ ለአባይ ነባሮችና ለመናፍቃን እንቅስቃሴ ተጋልጠዋል ማለት ነው። ምክንያቱም ተፈላጊነትን፣ ተቀባይነትንና ክበሬታን እናገኝበታለን ብለው ወደሚያስቡበት ስፍራ ሁሉ ለመሄድ አያቅማሙምና። ብዙ አባይ ነባሮች በተለይ ደግሞ መናፍቃን ተፈላጊነትን፣ ተቀባይነትንና ክበሬታን ያለገደብ እንደሚሰጡ ያውጃሉ። ታዲያ እነዚህን ነገሮች አጥብቆ ሲፈልጋቸው የነበረው ለው በቀላሉ ይወሰዳል።

መናፍቃን ለተራው አባላቸው እንኳ የአገልግሎት ስፍራ ይሰጣሉ። ይህም የእያንዳንዱን አባል አስፈላጊነት ከፍ ያደርገዋል። ሞርሞኖች፣ "ክህነታዊ ሥራ" የሚሉትን አገልግሎት ትኩረት

ይለጡታል። ወጣቶቻቸው የራሳቸውን ወጪ በመሸፈን የሁለት ዓመት ሚስዮናዊ አገልግሎት ያገለግላሉ። "የይሖዋ ምስክሮች" አባሎቻቸውን የመጠበቂያ ግንብ ድርጅትን ወንጌል ይሰብካሉ፤ ጽሑፉንም ያሠራጫሉ[10]።

4. አካላዊ ፍላጎትን ማርካት

አንዳንድ መናፍቃን የምግባረ ሠናይን ተግባር ሲያከናውኑ ይታያሉ፤ ይኸውም የተራበን ያበላሉ፤ የታረዘን ያለብሳሉ፤ ቤተ ሰብ የሌላቸውን ልጆች በማደጎ ወስደው ያሳድጋሉ።

ለትምህርት ያላቸው ዕቅድ፤ ድርጅቶቻቸውን ለማስታወቅ የሚጠቀሙበት መንገድና ዘዴ እንዲሁም የመገናኛ ብዙኃን አጠቃቀማቸው፤ ክእኛ እጅግ ብዙ ርቀው እንዲሄዱ አድርጓቸዋል። ዛሬ የመገናኛ ብዙኃንን በስፋት አየተጠቀሙበት የሚገኙት አባይ ነባሮቹ ናቸው። ቤተ ክርስቲያን በዚህ ጉዳይ ብዙ መሥራት ብዙ ማሰብ ይኖርባታል[11]።

5. መንፈሳዊ ፍላጎትን ማርካት

አንዳንድ ለምቾ አባይ ነባሮችንና መናፍቃንን የሚከተሉት መንፈሳዊ ረሃባቸውን ለማጥገብ ነው። መንፈሳዊ ረሃብ በማጥገብ ረገድ ብዙ አባይ ነባሮች የተለከፉበት፤ "የእምነት እንቅስቃሴ"

[10] እያንዳንዱ "የይሖዋ ምስክር" ይህን ሥራ ስለሚሠራ፤ "አስፋፊ" የሚል ስም ተሰጥቶታል።

[11] እያንዳንዱ አብያተ ክርስቲያን በዚህ ረገድ የሠለጠነ ሰው መቅጠር የሚያስፈልገው ይመስለኛል። ከዘመኑ ጋር መዝመን ከመንፈሳዊነት የሚያኮደል ሳይሆን፤ ዘመናዊውን ሰው ባሰበት አድራሻ እንዲሁም ይገባኛል በሚለው መንገድ ማነጋጋል ነው።

ትምህርት በዚህ ረገድ ትልቅ ቦታ የሚይዝ ነው[12]። ብዙ ወጣቶች ትምህርታቸውን ሳይመረመሩ በአምልኮ ዘይቤአቸው ተታለው ተወስደዋል፤ ይበልጡን የሚያሳዝነው የትምህርቱን ሰንኮፍ ከለሰለሰባቸው ልብ ነቅሎ ለማውጣት እጅግ አዳጋች መሆኑ ነው።

አባይ ነባሮችና መናፍቃን የአነርሱን ሥርዐተ አምልኮ መክተልና ፕሮግራማቸውን በተከታታይ መካፈል፤ ለመንፈሳዊ አርካታ ዋነኛ ጉዳይ አንደ ሆነ ይናገራሉ።

6. ለአእምሮ ጥያቄዎች መልስ መስጠት

ለምቾ በተለይም ወጣቶች መናፍቃንን የሚከተሉት ለጥያቄዎቻቸው መልስ ለማግኘት ብለው ነው፤ በዚህ ረገድ "የይሖዋ ምስክሮችን" መጥቀስ እንችላለን። "የይሖዋ ምስክሮች" የመጽሐፍ ቅዱስን ሥልጣናዊነት ያለምንም ገደብና ቅድመ ሁኔታ አንደሚያምኑ ይናገራሉ። ሆኖም የግሪክና (ጽርዕ) የዕብራይስጥ ጽሑፎች እንዲሁም የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ለአስተምህሮአቸው በሚመች መልኩ አጣመው ያቀርባሉ[13]። የአቀራረባቸውም ስልት ማራኪና በጎብረ ቀለማት ያሸበረቀ ስለሆነ፤ ዕውቀት ፈላጊው ለው በዚህ ሁኔታ በቀላሉ ይታለላል።

እንደ ቀድሞው ዘመን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ፤ ዐውደ ጥናቶችን በማዘጋጀት ጥናታዊ ጽሑፎች እንዲቀርቡ ያለማድረጋችን ወይም በመድረክ ውይይቶች ላይ ጠንካራ ርእሰ ጉዳዮች

[12] የዚህ መጽሐፍ ጸሓፊ፤ "የእምነት ወይስ የክህደት እንቅስቃሴ?" በሚል ርእስ ከወንድም ምኒልክ አስፋው ጋር ያዘጋጀውን መጽሐፍ ይመለከቷል።

[13] ተስፋዬ ሮበሌ፤ *የትምህርተ ሥላሴ መሠረታውያን*፤ ያዘጋጀውን መጽሐፍ ይመለከቷል።

አንዲንሸራሸሩ ያለመፍቀዳችን እንዲሁም ወጣቶች እውነትን ከውሸት የሚለዩባቸውን የአስተሳሰብ አካሄዶች *(logic/critical thinking)* ያለማሳወቃችን በብዙ ረገድ ጐድቶናል።

ለማንበብ ፍላጎት ያላቸውን ወጣቶች የሚመጥን፣ በተለያየ ርእሰ ጉዳይ ላይ የሚያጠነጥን መጽሐፍ ያለመኖሩም ወጣቶቻችን መንፈሳዊ ዕውቀታቸው ደረጃውን ጠብቆ እንዳይጐለብት እክል ፈጥሯል።

7. ሁለገብ የሆነ አኗኗር

አንዳንድ ለምኞ አባይ ነባሮችን እንዲሁም መናፍቃንን የሚከተሉት በአኗኗራቸው ፈጣን ለውጥ ወይም መሻሻል ስለሚያሳዩ ነው። የአባይ ነባሮች ጉባኤ በስሜት የነደደ መሆኑ፣ ወጣቶች ፈጣን የሆነ የጠባይ ለውጥ (ነገር ግን ሥር የሌለው) እንዲያሳዩ ምክንያት ሊሆን ይችላል። የሲጋራ፣ የመጠጥና የአደንዛዥ ዕፅ ሱስ ያለበት ለው በአባይ ነባሮች ጉባኤና በመናፍቃን ግብረ ገብ ሊሳብ ይችላል። ምክንያቱም አባይ ነባሮች ችግርን በደቂቃ እንፈታለን ስለሚሉ እኩይ ምግባር ልማድ ሆኖ ያስቸገረው ሰው በወጥመዳቸው ውስጥ ሊገባ ይችላል። መናፍቃንም ቅድስናን አድርግና አታድርግ በሚል ቅድመ ሁኔታ ስለሚመለከቱት በእኩይ ግብረ ገብ የተቸገረ ለው በእንዲህ ዐይነቱ የሥራ ቅድስና ትምህርት በቀላሉ ሊሳብ ይችላል።

ክፍል ዐሥራ ሁለት

የአባይ ነባሮችንና የመናፍቃንን ዕድገት ከመቀነስ ልንወስዳቸው የሚገቡ ርምጃዎች የትኞቹ ናቸው?



ሀ. ለምኞች አባይ ነባሮችንና መናፍቃንን እንዳይከተሉ እንዴት ልንጠብቃቸው እንችላለን?[1]

ለምኞች አባይ ነባሮችን ከመከተላቸው እንዲሁም መናፍቃዊ አንቅስቃሴ ውስጥ ገብተው ከመንፈቃቸው በፊት፣ ወደዚያ የሚወስዳቸውን መንገድ ማጠር ከብዙ አንጻር ጠቀሜታው እጅግ

[1] የዚህ ክፍል የመግቢያ ጭብጥ የተወሰደው፦— *Alan W. Gomes, Unmasking the Cults (Grand Rapids: Zondervan, 1995), 86-90.* ከሚባለው መጽሐፍ ነው።

ታላቅ ነው። ሰዎች በአባይ ነባዮችም ሆነ በመናፍቃን ተታለው ከመመለሳቸው በፊት፣ ልንመለሳቸው የሚገቡ መሠረታዊ ርምጃዎች አሉ። በመሠረቱ ከዚህ በታች የምንመለከታቸውን ዘዴዎች ብንጠቀም እንኳ፣ ሰዎች አባይ ነባዮችን ወይም መናፍቃንን ሊከተሉ አይችሉም ማለት አዳጋች ነው። ሰዎች መናፍቃንን እንዲከተሉ የሚያስገድዷቸውን ሁኔታዎች ማጥበብ ይቻላል፤ ነገር ግን ፈጽመን መዝጋት ወይም ማጠር አንችልም። የምንኖረው ሰይጣን በሚሠራበት፣ ሰዎች አኩይ ፍላጎታቸውን አንዳሻቸው እውን በሚያደርጉበት ዓለም ነውና።

ለ. አባይ ነባዮችና መናፍቃን ሐሰተኞች መሆናቸውን ሰቤተ ክርስቲያን ማሳየት

1. ቤተ ክርስቲያን ከአባይ ነባዮችና ከመናፍቃን ልትማር ይገባታል?

መናፍቃን ሐሰተኞች ስለሆኑ፣ "ከእነርሱ የምንማረው አንዳች ነገር የለም" ብሎ ማሰብ ተላላነት ነው። መናፍቃን ሰዎችን መሳብ የቻሉት (እየሳቡም ያሉት) እውነት ባይሆንም አንኳ፣ ሰዎች የሚፈልጉት ነገር በእነርሱ ዘንድ ስላለ ነው።

አባይ ነባዮችም ሆኑ መናፍቃን፣ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጡት በቤተ ክርስቲያን ደካማ ጐኖች ላይ ስለሆነ፣ ለእነርሱ ዕድገት ምክንያት የሆኑትን ነገሮች በመመርመር፣ ቤተ ክርስቲያን ድካሟን እሻሽላ መቅረብ አለባት። ብዙ ሰዎች አባይ ነባዮችን ወይም መናፍቃንን የሚከተሉት በሕይወታቸው ለሚገጥማቸው ተገቢ ጥያቄ መልስ ለማግኘት እስከ ሆነ ድረስ፣ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህን ፍላጎቶች በሚመልስበት (በሚያረካበት) መልኩ ስመመለስ

መዘጋጀት አለባት። ቤተ ክርስቲያን፣ "ሰዎች ካቤተ ክርስቲያን ይልቅ በአባይ ነባዮችና መናፍቃን ዘንድ ስጥያቄዎቻቸው መልስ ያገኙት ለምንድን ነው?" ብላ ራሷን በብርቱ መጠየቅ ይገባታል። ቤተ ክርስቲያን፣ አባይ ነባዮችና መናፍቃን ለሰዎች ጥያቄ የሚሰጡትን መልስ ልትሰማ፣ እነዚህን ጥያቄዎች ጌታ በመለሰበት መንገድ ልትመልስ ይገባታል።

ሰዎች መናፍቃንን የሚከተሉት ተገቢ የሆነውን እእምሮአዊ፣ ማኅበራዊ፣ ስሜታዊና መንፈሳዊ ፍላጎታቸውን ለማርካት እስከ ሆነ ድረስ፣ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህን ፍላጎቶች በሚያረካበት መንገድ በማርካት፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊውን ክርስትና በቤተ ክርስቲያን ማኖልበት አለብን።

2. የአባሎቻችንን አእምሮአዊ ፍላጎት ማርካት አለብን

ክርስቲያን የሚያምነውን እንዲሁም ለምን በዚህ መልኩ ማመን እንደሚገባው ጠንቅቆ ማወቅ አለበት። ዋልተር ማርቲን እንደሚለው ብዙ ሰዎች የሚያምኑትን ይወቁ እንጂ፣ ለምን በዚህ መልኩ ማመን እንደ ተገባቸው በጭራሽ አያውቁም። እንዲያውም የበለጠ ቁጥር ያላቸው ምን እንደሚያምኑም ሆነ ለምን በዚህ መልኩ ማመን እንዳለፈለጋቸው ጨርሶ አያውቁም።

ክርስቲያን በእምነት ላይ ሲተከል፣ ጸንቶም ሲቆም ይገባዋል። ማንኛውም ክርስቲያን እስተምህሮተ ሥላሴን፣ የክርስቶስን ፍጹም ሰብእዊነትና እምላካዊነት፣ ክርስቶስ በአካለ ሥጋ ከሙታን መነሣቱን እንዲሁም ድነት በእምነት እማክይነት በጸጋ ብቻ የሚሰጥ መሆኑን ከቃለ እግዚአብሔር የተደገፈ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል። ከዚህ በተጨማሪ ክርስቲያን በዙሪያው ያሉ አባይ

ነባዮችና መናፍቃን እዘወትረው ስሚያነሟቸው ጥያቄዎች አጥጋቢ የሆነ መልስ መስጠት እሰበት።

ክርስቲያን ምን እንደሚያምንና ለምን በዚህ መልኩ እንደሚያምን ከመጽሐፍ ቅዱስ መከላከያ ነጥብ ማቅረብ ካልቻለ፣ እደገኛ በሆነ መልኩ፣ ለአባይ ነባዮችና ለመናፍቃን እንቅስቃሴ የተጋለጠ ነው። ዋልተር ማርቲን እንደሚለው፣ "ከመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር ለዘጠና ቀን የቆየ 'የይሖዋ ምስክር' መካከለኛ ዕውቀት ያለውን *(average)* ክርስቲያን በዐሥራ አምስት ደቂቃ ውስጥ እምነቱን ሊያስጥለው (በእጅ ሊያስገባው) አሊያም ክፉኛ ሊያደናግረው ይችላል"። እውነት ጠልቆ የገባው አማኝ በማስረጃ ተብዬዎቹ እይሞኝም።

ክርስቲያን ከፀሓይ በታች ያሉትን የአባይ ነባዮችንና የመናፍቃንን እስተምህሮ ሁሉ ማወቅ አያስፈልገውም። ነገር ግን ዋና ዋና እንዲሁም ተመሳሳይ ባሕርያትን ማወቅ፣ ወንጌልን ለመመስከርም ሆነ ራስን ከመናፍቃን ለመከላከል ጠቀሜታው ከፍ ያለ ነው።

ቤተ ክርስቲያን በጥቃቅን ጉዳዮች ላይ ትኩረት ስትሰጥና በአባይ ነባዮች እንዲሁም በመናፍቃን ለተጐዱት ሰዎች የማገገሚያ ትምህርት ስታስተምር [አሁን ይህም እየተረሳ እንደ መጣ ይታያል]፣ ጊዜዋንና ጉልበቷን በከንቱ ስታባክን፣ አባይ ነባዮችና መናፍቃን የብዙዎችን እምነት ሰብረው መግባታቸው ብዙ ላያስደንቅ ይችላል።

ሰዎች እምነታችንን በተመለከተ የሚጠይቁንን አአምሮአዊ ጥያቄ በበቂ ሁኔታ መመለስ ካልቻልን፣ ከባድ እጣብቂኝ ውስጥ እንደምንገባ ማወቅ አለብን። ዋቢ ይሆነን ዘንድ እንድ ምሳሌ እንጠቀም፤ እንዲት እኅት ለእንድ ሙስሊም ጐረቤቷ፣ ስለ ክርስቶስ

አዳኝነት ልትነግረው ፈለገች እንበል፤ ሙስሊሙ፣ አምላኳ እንዴት አንድ በእንጻሩ ሦስት እካል እንዳለው እንድታብራራለት ፈለገ። አርሷም፣ "ሥላሴ ልታምነው የሚገባህ ጉዳይ ነው። ነገር ግን ይህ ትምህርት እንዲገባህ በጸም በጸሎት፣ በእግዚአብሔር ፊት ስትወድቅ እግዚአብሔር ራሱ ይገልጽልሃል" አለችው።

ከዚህ ውይይት ብዙ ነገር መመልከት ይቻላል። አንደኛው ልጅቱ የሥላሴ ትምህርት ስሜት የማይሰጥ፣ የትምህርተ መለኮትም ሆነ የእመክንዮ መሠረት የሌለው፣ ነገር ግን ጭፍን በሆነ እምነት የሚታመን ነው ያደረገችው። ሌላው፡— "በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያት ስሚጠይቋችሁ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ" *(1ጴጥ. 3÷15)* የሚለውን አምላካዊ ትእዛዝ እልኖረችበትም።

ቤተ ክርስቲያን ስለ አባይ ነባዮችና ስለ መናፍቃን እስተምህሮ ተግታ ማስተማር ያስፈልጋታል። ቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ የሆኑትን ክርስቲያናዊ እስተምህሮዎች ቅድሚያ በመስጠት፣ የአባይ ነባዮችንና የመናፍቃንን መሠረተ እምነት እንዲሁም የተለያዩ ሃይማኖታዊ ድርጅቶች ምን እንደሚያምኑና ለምን በዚያ መልኩ እንደሚያምኑ ማስተማር ይገባታል። ይህም ትምህርት ክርስቲያኖች ለምስክርነት ብቁና ዝግጁ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። ተቃውሞአቸውንም ለመመለስ የምናጠናው ጥናት፣ እምነታችንንም ሆነ ዕውቀታችንን ያጠነክረዋል።

ቤተ ክርስቲያን፣ ሰዎች በጥልቀት እንዲያስቡ የሚረዳቸውን እንደ ሥነ አመክንዮ *(logic)* ያሉ ትምህርቶችን ልታስተምር ይገባል። ምናልባት ምን ማመን እንዳለባቸውና የትኛውን ማመን እንደሌለባቸው ማስተማር ብቻ በቂ ላይሆን ይችላል፤ ነገር ግን

በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ እውነቱን ከውሸት የሚለዩበትን ዘዴ ማለወቅ እጅግ ጠቃሚ ነው።

ክርስቲያን እውነትን የሚገመግምበትን፣ ሐሰትን በቀላሉ ነቅሶ የሚያወጣበትን ከሂሎት ካላገኘ፣ "በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያት ለሚጠይቋችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ" የሚለውን ትእዛዝ ተግባራዊ ማድረግ አይችልም።

"እንደ ስሕተት ሽንገላ ባለ ተንኮል በለምችም ማታለል ምክንያት በትምህርት ነፋስ ሁሉ እየተፍገመገምን ወዲያና ወዲህ አየተንሳፈፍን ሕፃናት መሆን ወደ ፊት አይገባንም" (ኤፌ. 4÷14)።

3. የአባሎቻችንን ማኅበራዊና ሰሜታዊ ፍላጎቶች ማርካት አለብን

የቤተ ክርስቲያንን አባሎች መንፈሳዊ ጥማት ለማርካት የቤተ ክርስቲያንን መሠረተ እምነቶች አጠናክረን ልናስተምር ይገባል (1ጴጥ. 2÷2፤ 2ጢሞ. 3÷16)። በተጨማሪም አእምሮንና ሰሜትን ሊነካ የሚችል አምልኮ መፍጠር አለብን።

አባይ ነባሮችና መናፍቃን ቅናት (zeal) አላቸው። ነገር ግን ቅናታቸው ያለ አውነተኛ ዕውቀት ነው (ሮሜ 10÷2)። በተቃራኒው እውነተኛ ክርስቲያኖች እውነትን ይዘው ሳለ ዳተኛነት ይስተዋልባቸዋል። በሚዛናዊነት የተሞላው የቃለ እግዚአብሔር ትምህርት ግን፣ ቅናትን ከዕውቀት ጋር ያቀናጀ ነው (2ጴጥ. 1÷3-8)።

ሐ. አባይ ነባሮችም ሆኑ መናፍቃን ሐሰተኞች መሆናቸውን ለልጆችህ ማሳየት

1. ጠንካራ ቤተሰብ ልጆቹን ከሐሰተኞች በመጠበቅ ቁልፍ ሚና ይጫወታል

ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር በማንኛውም ጉዳይ ላይ በግልጽ መወያየትን ባህል ካደረጉ፣ መንፈሳዊውን ነገር ለመወያየት አዳጋች አይሆንባቸውም። በርግጥ ልጆች ስለተለያዩ መናፍቃንም ሆነ ሃይማኖቶች የመስማት ፍላጎት ላይኖራቸው ይችላል፤ ነገር ግን መልካም ግንኙነት ለውይይት ጥሩ መሠረት ነው።

ስለ እምነትህ ከልጆችህ ጋር በግልጽ ተወያይ። ወላጆች ልጆቻቸውን በተመለከተ ከቤተ ክርስቲያን ይልቅ የማስተማርም ሆነ መመሪያ የመስጠት ተቀዳሚ ኃላፊነት አለባቸው (ኤፌ. 6÷4)። ስለዚህ ተቀዳሚ ኃላፊነታቸውን በለንበት ትምህርት አስተማሪዎች ትከሻ ላይ ብቻ መጣል አግባብ አይደለም። ልጆችን በእግዚአብሔር መንገድ እየመሩ ማሳደግ ቀዳሚው የወላጆች ኃላፊነት መሆኑን መገንዘብ ያሻል።

2. እንደ ማንኛውም ግለሰብ ልጆችህን አክብር

ልጆች እንደማንኛውም ግለሰብ እንዲከበሩ ይፈልጋሉ። ከወላጆቻቸውም የተለየ ማንነት አላቸው። ወላጆች ልጆቻቸው ማንነታቸውን ሊገልጹ የሚፈልጉበትን ተገቢውን ነጻነት ሊነፍጓቸው አይገባም። ልጆች ይህን የሚያጡ ከሆነ፣ ወደ አባይ ነባሮችና መናፍቃን እንዲሄዱ ሊገፋፉ ይችላሉ። አባይ ነባሮችንና መናፍቃንን በመከተል ከቤተሰቦቻቸው የተለየ ማንነት እንዳላቸውና የተለየ የአኗኗር ዘይቤ እንደሚከተሉ ማሳያ መንገድ አድርገው ሊጠቀሙበት

ይችላሉ። የአባይ ነባሮችንና የመናፍቃንንም የአኗኗር ዘይቤ በመከተል፣ ራሳቸውን ከቤተሰቦቻቸው ሊለዩ ይችላሉ።

ብልኀ ወላጆች የልጆቻቸውን ማንነት መግለጫ ሊሆኑ የሚችሉ ለምሳሌ አንደ አለባበስ፣ አንደ አበጣጠር ወዘተ... ያሉትን አንዲያደርጉ ይፈቅዱላቸዋል። በነገር ሁሉ ስኬታማ የሚሆኑበትን መንገድ ያመቻቻሉ። ብዙ አባይ ነባሮችና መናፍቃን፣ የስኬታማነትን አጭር መንገድ አናሳያለን ስለሚሉ፣ ልጆች በዚህ ቀንበር ተጠምደው ሊከተሏቸው ይችላሉ።

3. የልጆችህን ጥያቄ በአንክሮ ልትመለከተው፣ አጥጋቢ መልስም ልትፈልግለት ይገባል

አንዳንድ ልጆች ስመንፈሳዊ ጥያቄዎቻቸው መልስ ፍለጋ መናፍቃንን ሊከተሉ ይችላሉ። ልጆች ጥያቄዎቻቸው በአጥጋቢ ሁኔታ ካልተመለስ፣ ጥያቄአቸውን ሊመልሱ ወደሚችሉ መልስ ስጪዎቻቸው አምነትና የአኗኗር ዘዴ መሄዳቸው አይቀሬ ነው። ልጆች ክባድ የሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥያቄ አንኳ ቢጠይቁ፣ ወላጆች የጥያቄውን መልስ ለማግኘት መጣር ወይም በበቂ ሁኔታ ሊመልስላቸው ወደሚችል ሰው ዘንድ መውስድ ይጠበቅባቸዋል[2]።

ልጆች አስደንጋጭ ሊሆኑ የሚችሉ ጥያቄዎችን አንኳ ቢጠይቁ ልንቁጣቸውም ሆነ ልናስደነግጣቸው ፈጽሞ አይገባም።

[2] በዚህ ረገድ የዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ የሚከተሉትን ሦስት መጻሕፍት ለንባብ አቅርቧል፦ *አግዚአብሔርን በተመለከተ ልጆች የሚጠይቋቸው 101 ጥያቄዎችና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልሶቻቸው* (ራእይ አሳታሚ ድርጅት፣ አዲስ አበባ 1992)፡፡ *መጽሐፍ ቅዱስን በተመለከተ ልጆች የሚጠይቋቸው 102 ጥያቄዎችና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልሶቻቸው* (ቃለ ሕይወት፣ 1993)፡፡ *ትክክልና ሰሕተትን በተመለከተ ልጆች የሚጠይቋቸው 103 ጥያቄዎችና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልሶቻቸው* (ራእይ አሳታሚ ድርጅት፣ አዲስ አበባ 1992)፡፡

አግዚአብሔር የት ነው የሚኖረው? እርሱን ራሱን ማን ፈጠረው? መጽሐፍ ቅዱስ የአግዚአብሔር ቃል መሆኑን በምን ዐውቃለሁ? ውሸት ለምን ትክክል አልሆነም? ወዘተ የሚል ጥያቄ ሊያቀርቡ ይችላሉ። ነገር ግን ከምናደርጋቸው ነገሮች ሁሉ በጣም የከፋው፣ ልጆችን ማስደንገጥና ጥያቄዎቻቸውን ማጣጣል ነው።

ወጣቶች መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆነ መልኩ የሚያስቡበትን ነገረ መለኮታዊና ሥነ አመክንዮአዊ አካሄዶችን ልናስተምራቸው ይገባል።

4. ከልጆችህ ጋር ወጥነት ያለው ክርስቲያናዊ ኑሮ ኑር

ልጆች ግብዝነትን ከሩቅ ነቅሰው የማውጣት አስመሳይነትን የመለየት ታላቅ ችሎታ አላቸው። ወጥነት ያለውን ክርስቲያናዊ ሕይወት ከልጆችህ ጋር በጋራ የማትኖር ከሆነ፣ ልጆችህ ክርስትናን ቢያወግዙ አትደነቅ!

ወጥነት ማለት ፍጹምነት ማለት አይደለም። ነገር ግን ወጥነት ያለው ክርስቲያናዊ ኑሮ ማለት፣ ክርስትናን የአኗኗራችን፣ የአስተሳሰባችንና የአነጋገራችን መሠረት ማድረግ ማለት ነው። ልጆች ችግርን እንዴት እንደምትፈታ ካንተው ከአባታቸው[3] ሊማሩ ይገባል። ስምሳሌ፦ ልጆችህ ሊበድሉህ ወይም ሊያጠፉ ለአነርሱ ያለህ ይቅርታ፣ አንተም ስታጠፋ ጥፋትህን በግልጽ በማመን የምትጠይቀው ይቅርታ ለልጆችህ መልካም አርአያ፣ ጥሩም ምሳሌ

[3] በርእሱ ላይ የተባእት ጾታን ስለተጠቀምን፣ በዚህ ዙታ "አባት" የሚለውን ቃል ተጠቅመናል። አባትና እናትን በተለዋዋጭነት ማቅረብ፣ የአሳብ ፍሰቱን የደናቅፋል ብለን ስላሰብን፣ አንዱን ብቻ ነጥለን ተጠቅመናል። ስለዚህ እናቶች "እናት" የሚለውን እየተከ እንዲያነቡ በማክበር ይጠየቃሉ።

እንደሚሆናቸው እሙን ነው። ይህም የእምነትህን እውነተኛነት በጎይል ያገልጠዋል።

5. ልጆች እውነታዎችን የሚመዝኑበት ጥሩ ዘዴ ስጣቸው

ልጆች እውነቱን ከውሸት ሊለዩ የሚችሉበትን ዘዴ ስጣቸው (አስተምራቸው)። ዘዴዎች በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ እውነቱን ከውሸት ልንለይ የምንችልባቸው መሣሪያዎች ናቸው። ምንም አንኳ በእያንዳንዱ አስተምህሮ ሐሰቱንና አውነቱን ጠልቀን ባናስተምራቸውም፣ በሚገጥሟቸው አጋጣሚዎች ሁሉ የሚረዱአቸውን ዘዴዎች ማስተማር በቂ ነው። ዘዴዎች ማንኛውንም ነገር የምንመዝንባቸው መሣሪያዎች ናቸውና።

ክፍል ዐሥራ ሦስት

ጸረ-ተምህሮታዊነት
የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት አብሾ፣ እርሾና ጌሾ



ከአሜሪካን መሥራች አባቶች መኻል አንዱ የሆኑት ቤንጃሚን ፍራንክሊን፣ "ሃያ ሰድስት ወታደሮች ለጡኝ ዓለምን በቍጥጥሬ ሥር አደርጋለሁ" ይሉ እንደ ነበር ይነገራል። ግለሰቡ ሃያ ሰድስት ወታደር የሚሏቸው በወታደራዊ ሳይንስ የሠለጠኑ፣ በጦር ዐውድማ የተፈተኑ፣ ዘመናዊ የጦር መሣሪያ የታጠቁ፣ በጦር ፍልስፍና

የመጠቁ ሾተላይ ወታደሮችን አይደለም። በእንግሊዝኛ የፊደል ገበታ ላይ የተለተሩትን፣ ሃያ ሰድስት የእንግሊዝኛ ሆህያት እንጂ[1]።

የግእዝ ቋንቋ ሊቃውንት፣ ሰዎች "ነባብያን ወንቀኦንን" ናቸው ሲሉ፣ የጎልዩ የነቢብና የገቢር (የአሰተላለብ፣ የንግግር እንዲሁም የምግባር) ባለሀብት መሆናቸውን ብቻ ሳይሆን፣ የሥነ ጽሑፍ ባለቤት መሆናቸውንም የሚያመለክት ነው። እርግጥ ነው፣ የሥነ ጽሑፍን ጎያል ጉልበት፣ ሥነ ጽሑፍ ራሱ ነግሮ ዘክሮ እንደ ማይጨርሰው እናውቃለን። ምክንያቱም ዕውቀትን ከአንድ ጭንቅላት ወደ ሌላ አእምሮ የምናስተላልፍበት (የምናንቄረቀርበት) ሁነኛ ቦይ ሥነ ጽሑፍ ነው።

ኮሚኒስቶች የፖለቲካና የምጣኔ ሀብት ርእዮተ ዓለማቸውን በዓለም ላይ እንዲናኝ ያደረጉት፣ በሰላ ብዕራቸው፣ በቀስቃሽ ጽሑፋቸው ነበር። በዚህ ረገድ፣ በዘመነ ደርግ በአማርኛ ቋንቋ ተተርጕመው ለንባብ የቀረቡትን የካርል ማርክስን ዳስ ካፒታልና ኮሚኒስት ማኒፌስቶ መጻሕፍት ያስተውሷል። በ"ቀዝቃዛው ጦርነት" ወቅት፣ በርካታ አገሮች ከኮሚኒስቷ መስኮብ/ራሻ ተርታ መሰለፍ የቻሉት፣ የርእዮተ ዓለሙ መሪዎች ፍልስፍናቸውን ለአእምሮ ግቡዕ በሆነ ሁኔታ በሥነ ጽሑፍ ከሸነው በማቅረባቸው ነበር።

በዐሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተነሣው የፕሮቴስታንቱ የተሐድሶ እንቅስቃሴ፣ እንደ ምትሐት ሊታይ የሚችል ነውጥ ማስከተል የቻለው፣ ንቅናቄው ትምህርትን ማዕከል እንዲሁም ሥነ ጽሑፍ መር የመሆኑ ሐቅ ነው። የማኅበረሰብን አኗኗርና ለውጥ ይከታተሉ የነበሩ የዘመኑ ደራስያን፣ "የፕሮቴስታንት ተሐድሶን በማይጠፋ እሳት በነዳጅ ያንቀለቀለው፣ የኅትመት መሣሪያ ፈጣሪው ጀርመናዊው ዮሐንስ ጉተንበርግ ነው"

[1] ከወንድም ምኒልክ አስፋው ያገኘሁት ነው።

ሲሉ ጽፈዋል። ከንቅናቄው ቀደም ብሎ ዮሐንስ ጉተንበርግ የማተሚያ መሣሪያ ባይፈጥር ኖሮ፣ የሉተርና የመርሕያነ ተሐድሶዎች ጥረት፣ ከመንደር ጫጫታ ዘለግ ያለ ፋይዳ ሊኖረው አይችልም ነበር።

አትነቀስም እትገሠሥም በተባለችው ካቶሊካዊቷ ቤተ ክርስቲያን ዙሪያ የተኰለኰሉት አውሮፖውያኑ ነገሥታት፣ በዐይን ብሌን የሚመስሉትን ካቶሊካዊት እምነታቸውን ከጥቃት የመከላከል ዕቅም ያጡት፣ ከእነርሱ ጉልበት የሚበረታ ኀይል እንደ ደራሽ ውሃ ድንገት ከተፍ በማለት፣ በእርዳ ተራዳ የቆመውን ነገር ግን ሐዳስያኑ በለላ ሐሰ የሞሸለቁትን ተረት፣ ዳግም በእግሩ ማቆም ባለመቻላቸው ነበር። አስደናቂው ነገር፣ እንደ ሰሚ ሁሉ በነገረ መለኮቷም፣ "ዓለም ዐቀፋዊት ነኝ" ብላ ትኵራራ የነበረችው ካቶሊካዊቷ ቤተ ክርስቲያን፣ በመራሕያነ ተሐድሶዎቹ የዕድሜ ዘመን እንኳ፣ ሊጠገን በማይችል ደረጃ በግማሽ መሰንጠቋ፣ የትምህርትንና የሥነ ጽሑፍን ጉልበት በውል የሚያሳይ ጥሩ ማገናዘቢያ ይመስለኛል።

ከዐሥራ ሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ፣ ከአውሮፓ እንዲሁም ከለሜን አሜሪካ ወደ ኢትዮጵያ የገቡት ሚስዮናውያን፣ ወንጌልን ለመስበክ በሄዱባቸው ቦታዎች ሁሉ፣ ስብከተ ወንጌልና የቀለም ትምህርትን እንደ ነበልባልና እንደ ብርሃን እያይዘውት ዘልቀዋል። ቀደምት ኢትዮጵያውያን ምሁራን፣ ፊደል በመቀጠር በዘመናዊው ትምህርት መሚሸት የጀመሩት፣ በሚሰዮናውያኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ውስጥ እንደ ሆነ ይታወቃል። የቀለም ተቀብዖ አላቸው ያሏቸውንም የበለጠ ትምህርት ያገኙ ዘንድ ከአገር ውጪ ሄደው እንዲማሩ ብዙ ጥረት አድርገዋል። በዚህ አግባብ ነበር አንድ ሰው፣ "ተቀመጥ በወንበሬ ተናገር በከንፈሬ" በሚል

በሚስያናውያኑ ትምህርት ቤት ይሄም የነበረው (እኔም በአብዛኛው የትምህርት ዕድል ያገኘሁት በዚሁ አካሄድ ነው)።

ለዚህ ዐቢይ ምክንያቱ፣ ከዘመነ ተሐድሶ ጀምሮ ለረጅም ዓመታት ቤተ ክርስቲያን ሥነ ጽሑፍን ለአምስት ዐበይት ዐላማዎች ስትጠቀምበት የመኖሯ ሐቅ ነው። ይኸውም፦ *(1)* መሠረተ እምነቷን ከጥቃት ለመጠበቅ፣ *(2)* ተጻራሪ አስተሳሰቦችን ለማምከን፣ *(3)* ወንጌልን ለማሠራጨት፣ *(4)* አባሎችዋን በቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርትና በክርስቲያናዊው ንጽርአተ ዓለም ለማነጽ እንዲሁም፣ *(5)* አምልኮተ እግዚአብሔር ለማካሄድ።

ይህ ግን የነበረ እንጂ አሁን ያለ ሐቅ አይደለም። ዕውቀትና ሥነ ጽሑፍ ከወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ሕይወት እየመነነ፣ ከዐውደ ምሕረቱ እየበነነ የባዕድ አገር ሰው አንደ ሆነ ከማንም የሚሰወር አይመስለኝም። አንዲያውም ቅዱሳት መጻሕፍትን ደርዝ ባለው መልክ መተንተን፣ "የአምሮ ሰው" ወይም "የቃል ሰው" የሚል አሉታዊ ሰያሜ የሚያከናንብ ሲሆን፣ ከዚህ በተቃራኒው አንጻር የቆሙትን ግን፣ "የጸጋ አገልጋዮች" "መንፈሳውያን ሰዎች" የሚል ትልቅ ክብር ያጐናጽፋል። ይህ መቼም ሥነ ጽሑፍ ታሽቶ ባደገበት አገር በዚህ መጠን ምጽአተኛ ሲሆን ማየት፣ በርግጥም ትልቅ ቊጭት የሚፈጥር ነው።

የሰምና ወርቁ ማዕቀፍ

ወደድንም ጠላንም በኢትዮጵያ ውስጥ የተነሣው የአባይ ነባዮች እንቅስቃሴ፣ ክርስቲያኖች ቃለ እግዚአብሔርንና ምርምርን የጉዞ መስመራቸው አንዳያደርጉ እጅግ ትልቅ አክል ፈጥሮአል። ይህ ምን ማለት አንደ ሆነ እንዳብራራ ይፈቀድልኝ። መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት ትልቅ ትዕግሥትና ብዙ ትግል ይፈልጋል። ለዚህ ደግሞ

በርካታ ምክንያቶች አሉ። ከእነዚህ መኻል ተዘውትረው የሚጠቀሱትን ሦስት መሠረታውያን ነጥቦች ልጥቀስ፦ *(1)* መጽሐፉ ጥንታዊ መሆኑ አንብቦ የመረዳቱን ሥራ አስቸጋሪ አድርጎታል። በአኖና በመጽሐፍ ቅዱስ ቀዳማይ ተደራስያን መኻል፣ የብዚ ሺህ ዓመት ርቀት አለ። ብሉያት ከሦስት ሺህ ዓመት በፊት የተጻፉ ሲሆን፣ ሐዲሳት ደግሞ ከሁለት ሺህ ዓመት በፊት ነው የተጻፉት። ይህ ደግሞ በአኖና በቀዳማይ ተደራስያኑ መኻል ያለውን ንጽርተ ዓለም በከፍተኛ ደረጃ አለያይቶታል። የሳይንስ፣ የቴክኖሎጂ፣ የፍልስፍና ወዘተ ምጥቀት የዘመኑን ሰው አመለካከት ከጥንታውያኑ ሰዎች አተያይ በከፍተኛ መጠን አራርቆታል። *(2)* በመጽሐፍ ቅዱስ ጸሓፍያንና በመልእክቱ ቀዳማይ ተደራስያን መካከል ከፍተኛ የሆነ የባህል ልዩነት አለ። ይህም ተግባቡቱ እንዲደነቃቀፍ ትልቅ ድርሻ አለው። *(3)* መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበት ቋንቋ እኛ ከምናውቀው ቋንቋ፣ ዘይቤአዊ አገላለጽ፣ ሥነ ጽሑፋዊ ዘውግ፣ ወዘተ በእጅጉ የተለየ ነው።

ይህ ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱስን አንብቦ በትክክል ለመረዳት ረጅም ጊዜ የሚፈጅ እልህ አስጨራሽ ትግል ፈልጓል። አምላክ አሳቡን ለሰብአውያን ለማስተላለፍ፣ ይህ ዐይነቱን አድካሚ መንገድ ለምን እንደ መረጠ አኔ የማውቀው ነገር የለም። ነገር ግን አንድ ነገር በአርግጠኝነት መናገር እችላለሁ። ይኸውም አምላክ ቅዱሱን መጽሐፍ በመንፈስ ቅዱስ ነድቶ እንካችሁ እንዳለን ሁሉ፣ ዛሬ ደግሞ ይህን የመረዳት ክፍተት የሚሞሉልንን አስተማሪዎች ለቤተ ክርስቲያን ሰጥቶአል። እነዚህ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ለረጅም ዓመት በማጥናት ክፍተቱን ለመሙላት ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል፣ በየቋንቋውም ተርጕመው አቅርበውልናል። ይህ ሁሉ አውን ቢሆንም አንኳ፣ መጽሐፍ ቅዱስን አንብቦ መረዳት ትልቅ ጥረት ይፈልጋል።

ሥነ አፈታትን ማወቅ፣ አናት ቋንቋውን ማወቅ፣ ነገረ መለኮትን ማወቅ፣ ወዘተ። ስለዚህ አንድ ሰው መጽሐፍ ቅዱስን አንብቦ የአምላክን ምክር ለመረዳት ከእነዚህ ሁሉ ተግዳሮቶች ጋር መፋጠጡ አይቀሬ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ያስፈለገበት ዐቢይ ዐላማ፣ አምላክ በግልም ሆነ በጋራ የሚናገረንን ነገር በግልጽ ለመረዳት ነው። የትንቢትም ዋነኛ ዐላማ ይኸው ነው። በተወሰኑ አጋጣሚዎች ውስጥ ዐልፎ ዐልፎ እግዚአብሔር ነቢያትን በማስነሣት በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ለቤተ ክርስቲያን ምሪትን ይሰጣል። ከላይ እንደ ተመለከትነው ይህ በብሉያትም በሐዲሳትም የነበረ ዛሬም ያለ ቋሚ አካሄድ ነው። ነገር ግን አምላክ የየዕለቱን ትምህርትና ምክር የሚሰጠን በቅዱሳት መጻሕፍት አንጂ በነቢያት አይደለም፤ አልነበረምም።

ዛሬ በዙሪያችን እንደ እንጉዳይ የፈሉት አባይ ነባዮች፣ ቢያስፈልግ በቀን ዐሥር ጊዜ፣ በእያንዳንዱ ርእሰ ጉዳይ ላይ አምላክ ሊናገረን የሚፈልገውን ነገር ንገሩን ብንላቸው ይነግሩናል። እንግዲያው አምላክ በነባዮች በዚህን ያህል ቅርበትና በዚህን ያህል መጠን የሚናገረን ከሆነ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን ማጥናት በተለይ ደግሞ ከዚህ ጥንታዊ መጽሐፍ ጋር መታገል ለምን ያስፈልጋል? ይህ ነው የማንበብ ፍላጎታችንን ያለለው፣ የለለበው! ይህ አካሄድ ነው መጽሐፍ ቅዱሳችንን ያስረጀብን!

አንድ ወዳጄን፣ "ጌታ በዚህ መጠን በነባዮች የሚናገረን ከሆነ፣ መጽሐፍ ቅዱስ አስፈላጊነቱ እምኑ ላይ ነው?" አልሁት። እርሱም በኩራት፣ "ሁል ጊዜ አንድ ዐይነት ወጥ ብቻ እንዴት ትበላለህ? ይለለቻል እኮ!...መገለጥና ትንቢት ጥሩ መጽሐፍ እንዳይለለችን አምላክ የለጠን ተለዋጭ ወጥ፣ ያውም የዶሮ ወጥ

ነው" አለኝ። "'በጥሩ መጽሐፍና' 'በዶሮው ወጡ' መኻል በመዳኘት፣ ሚዛናዊ ክርስትናን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የምንመሠርተው እንዴት ነው?" የሚለው ጥያቄ እጅግ ወሳኝ፣ እጅግም አንገብጋቢ ጥያቄ ነው። ለዚህ ሁነኛ ጥያቄ ሁነኛ መልስ ሳንሰጥ ፊታችንን እነርሱ "ጥሩ መጽሐፍ" ወደሚሉት እንመልሳለን ማለት ከቀቢፀ ተስፋ[2] ነው፤ ከንቱ ተምኔት ነው። ይህ ለዘመኗ ቤተ ክርስቲያን የቀረበ ወሳኝ ጥያቄ ነው።

ቀጥለን የማንበብ ባህላችን ምንኛ እንደ ተንኰታኰተ በግልጽ ሊያሳየን እንዲሁም ሊያገናዝበልን የሚችል አንድ ማነጻጸሪያ በናሙናነት ወስደን እንመልከት። ይህ በምን መጠን ተሸረብርበን እንደ ወደቅን በጉልኅ ያሳያል ብዬ አስባለሁ። እነሆ፦—

ለዚህ ጉዳይ የመረጥሁት የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር በመባል የሚታወቀውን "የይሖዋ ምስክሮችን" ድርጅት ነው። የእነርሱ ትጋት ለእኛ ሥጋት፣ የእነርሱ ጥረት ለእኛ ኀፍረት፣ የእነርሱ ከፍታ ለእኛ ዝቅታ ሊሆን እንዴት እንደ ቻለ እንመርምር።

ማኅናዘቢያ

ሀ. ኅትመትና ሥርጭት

ከማንኛውም መናፍቃን ይልቅ የጽሑፍ ውጤቶችን በከፍተኛ ደረጃ በመጠቀም ላይ የሚገኙት፣ "የይሖዋ ምስክሮች" ናቸው። ከ26 ዓመት በፊት ይፋ የሆነ አንድ መረጃ፣ "የይሖዋ ምስክሮች" በዓለም ዙሪያ 33 ታላላቅ ማተሚያ ቤቶች እንዳላቸው ይገልጻል። "ቤቴል" በመባል የሚታወቀው ትልቁ ማተሚያ ቤታቸው ብቻ፣ በቀን

[2] "ቀበፀ" ማለት ቁረጠ ነው። ስለዚህ "ቀቢፀ ተስፋ" ማለት ተስፋ መቁረጥ ማለት ነው።

ርዝመቱ 1,000 ማይል (1,609 ኪሎ ሜትር) የሚያህል ወይም 61 ሚልዮን ገጽ ወረቀት ያትማል[3]። ከዚህ በተጨማሪ በወር 3 ሚሊዮን የአዲሲቱን ዓለም ትርጉም አያተመ ያወጣል። በ1991 ዓ.ም. በእነዚህ ማተሚያ ቤቶች ውስጥ የሚሠሩ 11,000 የሙሉ ጊዜ ሠራተኞች ነበሩ[4]።

አንደ ኮርኮሮሳውያኑ የዘመን ቀመር 2013 ዓ.ም "የይሖዋ ምስክሮች" ጽሑፎቻቸውን 700 ቋንቋዎች በመተርጉም 239 አገሮች ውስጥ አሠራጭተዋል[5]። ከድርጅቱ አስተምህሮ ጋር አንዲጣጣም ተደርጉ የተተረጉመው የአዲስ ዓለም ትርጉም በ2013 ዓ.ም ብቻ፣ በ121 ቋንቋዎች ተተርጉሞ፣ 184 ሚልዮን ቅጅ ተባዝቶ ተሠራጭቷል[6]።

ሁሉቱ የድርጅቱ ዕውቅ መጽሔቶች ማለትም፣ "መጠበቂያ ግንብ" አና "ንቁ" መጽሔት የኅትመት ብዛታቸው፣ የሥርጭት ስፋታቸው አንዲሁም የሚተረጉሙበት የቋንቋ ብዛት በርግጥ አንደ ትንግርት ሊታይ በሚችል ደረጃ ላይ ይገኛል። ለምሳሌ 2013 ዓ.ም "መጠበቂያ ግንብ" 210 ቋንቋዎች በመተርጉም 45 ሚልዮን ቅጅ ተባዝቶ ተሠራጭቷል[7]። "ንቁ" መጽሔት ደግሞ፣ በ99 ቋንቋዎች የተተረጉመ ሲሆን፣ 44 ሚልዮን ቅጅ ታትሞ ተሠራጭቷል[8]። ሥርጭቱም ሪደርስ ዳጀስት እንዲሁም ቲቪ ጋይድ ከሚባሉት መጽሔቶች ካላቸው ሥርጭት ጋር የሚስተካከል፣ ሽያጩም

[3] *CRI "Cult Growth Statistics", Citing the Watchtower (1, Jan.1993): 19b.*

[4] *David A. Reed, Jehovah's Withness Litrature: a Critical Guide to Watchtower Publications (Grand Rapids:Baker, 1993), 9.*

[5] *https://www.jw.org/en/jehovahs-witnesses/activities/publishing/global-printing/*

[6] ዝኒ. ከማሁ።

[7] ዝኒ. ከማሁ።

[8] ዝኒ. ከማሁ።

ከታይምስ፣ ከኒውስ ዊክ፣ ከዩ ኤስ ኒውስና፣ የወርልድ ሪፖርት ጋር የሚወዳደር ነው[9]።

የአዲሲቱ ዓለም ትርጉም በ1990 ዓ.ም ብቻ በ67 ሚልዮን ቅጂዎች የተባዛ ሲሆን፣ በ14 ቋንቋዎች ተባዝቶ ስንባብ ቀርቧል። በአሁኑ ጊዜ ይህ መጽሐፍ አማርኛን ጨምሮ ከ129 በሚበልጡ ቋንቋዎች ተተርጉሞአል[10]።

ይህ የድርጅቱ መጽሔቶች ልዩ ጠባይ ብቻ አይደለም። የመጻሕፍትና የመስስተኛ መጻሕፍት (brochure) ነባር ባሕርይ ጭምር አንጂ። ለምሳሌ፣ "ትክክለኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ምንድን ነው?" በሚል ርእስ የታተመውና የድርጅቱን መሠረተ እምነት ለአዳዲስ ተከታዮች የማስተማሪያ መጽሐፍ (224 ገጽ አሰው)፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ስንባብ የበቃው በ2005 ዓ.ም ሲሆን፣ 240 ቋንቋዎች ተተርጉሞ፣ 214 ሚልዮን ቅጅ ተባዝቶ ተሠራጭቷል[11]።

በቅርቡ፣ "አምላክን ስማ የዘላለም ሕይወት ታገኛለህ" በሚል ርእስ የተዘጋጀው ባለ 32 ገጽ ጥራዝ መለስተኛ መጽሐፍ 400 ቋንቋዎች ተተርጉሞ፣ በ42 ሚልዮን ቅጅ ተባዝቶ ተሠራጭቷል[12]።

በ2012 ዓ.ም ብቻ በድርጅቱ ማተሚያ ቤቶች የታተሙት መጽሔቶች ብዛታቸው 1.3 ቢሊዮን ሲሆን፣ መጽሐፍ ደግሞ 80 ሚልዮን ነው[13]።

[9] *Alan W.Gomes, Unmasking the Cults, 23.*

[10] *https://www.jw.org/en/publications/books/2016-yearbook/highlights/new-world-translation-more-languages/*

[11] *https://www.jw.org/en/jehovahs-witnesses/activities/publishing/watchtower-awake-magazine/*

[12] ዝኒ. ከማሁ።

[13] ዝኒ. ከማሁ።

ኅዳር 1 ቀን 2005 ዓ.ም ለንባብ የበቃው፣ "የመጠበቂያ ግንብ" መጽሔት፣ በገጽ 27 ላይ ድርጅቱ እዘጋጅቶ ያሠራጫቸውን የጎትመትና የቪዲዮ ውጤቶች በሚከተለው መልክ ይፋ አድርጓል።

- 3,168,611 ቪዲዮዎች
- 6,834,740 መለስተኛ መጻሕፍት
- 47,490,247 መጻሕፍት
- 167,854,462 በአንድ ርእሰ ጉዳይ ላይ የሚያጠነጥኑ ብሮሹሮች
- 440,995,740 በራሪ ከጽሑፎች
- 1,179,266,348 (1.2 ቢሊዮን የሚጠጋ መጽሔት)

በጎትመት ብዛት ብቻ ሳይሆን በሥርጭትም ብዛት እንዲሁም በሚተረኮሙባቸው ቋንቋዎች ብዛት የድርጅቱ መጽሔቶች እንዲሁም መጻሕፍት በዓለም የቊጥር እንድ ቦታን ይዘዋል።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ድርጅቱ በብዛት ብቻ ሳይሆን፣ በዐይነትም እጅግ በርካታ መጻሕፍትን ዐትሞ በማሠራጨት ላይ ይገኛል። የጎትመት ጥራታቸው እጅግ የላቀ እንዲሁም በሙሉ ቀለም የታተሙ በመሆናቸው፣ የማንበብን ፍላጎት ይቀስቅላሉ። ከዚህ በተጨማሪ የጎትመት ውበታቸው እምርና ደምቆ መቅረቡ፣ አንባቢው የያዙትም ትምህርት ትክክል ነው የሚለውን፣ የተሳሳተ ግንዛቤ እንዲይዝ አድርገዋል። ይህ ደግሞ ድርጅቱ ለዘመናት ሲጠቀምበት የኖረው ለልት ነው። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እየተዘጋጁ ያሉት መጻሕፍት፣ በምን ያህል ቊጥር ተባዝተው እንደ ተሠራጩ በቊርጥ ማወቅ አልተቻለም። ከዚህ በፊት ግን በመጻሕፍቱ መግቢያ ላይ፣ በምን ያህል ቊጥር ታትሞ እንደ ተሠራጨ ይገልጽ ነበር።

ከዐሥር ዓመት ወዲህ በአማርኛ ቋንቋ የታተሙት መጻሕፍት ወደ 35 ይደርሳሉ (በጣት የሚቈጠሩ የቀድሞዎቹን ጽሑፎች ሳይጨምር)። እነርሱም የሚከተሉት ናቸው፦— "ቅዱሳት መጻሕፍትን በየዕለቱ መርምር"፣ "መጽሐፍ ቅዱስ ምን ያስተምራል?"፣ "ምን ጊዜም ለይሖዋ ታማኝ ሁኑ"፣ "የምርምር መርጃ መሣሪያ ለይሖዋ ምስክሮች" (የ2015 ዕትም)፣ "ወደ ይሖዋ ተመለስ"፣ "ኢየሱስ—መንገድ እውነት፣ ሕይወት"፣ "የእምላክ መንግሥት እየገዛ ነው"፣ "የእምላክ ወዳጅ መሆን ትችላለህ"፣ "የምትወዱት ለው ሲሞት"፣ "ልጆቻችሁን አስተምሩ"፣ "ደስተኛ ቤተሰብ ሊኖርህ ይችላል"፣ "የእምላክ መንግሥት ምንድን ነው?"፣ "ለይሖዋ ዘምሩ"፣ "በእምነታቸው ምሰሏቸው"፣ "መከራ የማይኖርበት ጊዜ ይመጣል?"፣ "የቤተሰብን ሕይወት እስደሳች ለማድረግ ቊልፉ ምንድን ነው?"፣ "ዓለምን እየተቈጣጠረ ያለው ማን ነው?"፣ "ስለ ወደ ፊቱ ጊዜ ምን ይለማሃል?"፣ "ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ምን እመለካከት አለህ?"፣ "የሞቱ ለምች እንደ ገና በሕይወት መኖር ይችላሉ?"፣ "ወጣቶች—በሕይወታችሁ ምን ማድረግ እለባችኋል?"፣ "ከእምላክ ፍቅር አትውጡ"፣ "ወደ ይሖዋ ቅረብ"፣ "ከታላቁ አስተማሪ ተማር"፣ "ስለ እምላክ መንግሥት የተሟላ ምስክርነት መስጠት"፣ "በቲኦክራሲያዊ የአገልግሎት ትምህርት ቤት ከሚለጠው ሥልጠና ተጠቀም"፣ "ትክክለኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ምንድን ነው?"፣ "መጽሐፍ ቅዱስ—የያዘው መልእክት ምንድን ነው?"፣ "እምላክን ስማ"፣ "እውነቱን ማወቅ ትፈልጋለህ?"፣ "ሕይወት የተገኘው በፍጥረት ነው?"፣ "የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ መማሪያ መጽሐፍ"።

የአባላት ብዛት

በሥነ ጽሑፍ የሚታገዘው ሃይማኖት ያስውን ዕድገት ደግሞ አንመልከት። አንደ ጉርጉሮሳውያኑ የዘመን አቁጣጠር በ1997 ዓ.ም. በ232 አገሮች በተደረገው ቁጠራ ንቋ፣ "የይሖዋ ምስክር" ተሳታፊ አባላት ቍጥር 5,599,931 ሲሆን፣ ይህ ቍጥር በ1998 ዓ.ም. ወደ 6 ሚልዮን፣ በ2015 ዓ.ም. ደግሞ 8,220,105 አሻቅቦአል። በ2015 ዓ.ም. በተደረገው የ"መታሰቢያ አገልግሎት"[14] 19,862,783 ሰዎች ፕሮግራሙን ተካፍለዋል[15]። ይህ የሚያሳየን "የይሖዋ ምስክሮች" ክንቍ ተሳታፊ አባሎቻቸው ዕጥፍ በላይ በሆኑ ሰዎች ላይ፣ አምንታዊ ተጽእኖ አንዳላቸው የሚያመለክት ነው። በ1997 ዓ.ም ይፋ የሆነ አንድ ጥናት፣ በዓለም ዙሪያ፣ አንድ ደቂቃ ከ45 ሴኮንድ ውስጥ፣ አንድ ሰው "የይሖዋ ምስክር" አባል አንደሚሆን ገልጾአል[16]። ብዛታቸው ክመጨመሩ አኳያ ዛሬ ድርጅቱን የሚቀላቀለው ሰው ከዚህ ጊዜ በፊጠነ ጊዜ ውሰጥ ነው። በ2015 ዓ.ም በዓለማችን 118,016 "የይሖዋ ምስክሮች" ጉባኤዎች ይገኛሉ[17]።

አሜሪካዊው ዐቅብተ አምነት ዋልተር ማርቲን እንደሚለው 75% የሚሆነው "የይሖዋ ምስክር" በአንድ ወቅት የወንጌላውያን

[14] "የይሖዋ ምስክሮች" የጌታን ሞት የሚያስቡበት ቀን "የመታሰቢያ አገልግሎት"— *"Memorial Servicel"* ብለው ይጠሩታል። የ144 ሺህ አባል ናቸው የሚባሉት ጉበኩቱንና ጽዋውን በመብላትና በመጠጣት ሊያከብሩ፣ ምድር ወራሽ የሆኑት "በጐች" ደግሞ፣ እነዚህ "ቅቡዓን" በማየት ያከብራሉ። ለበለጠ ማብራሪያ፣ አረዮሳውያን የሚለውን የጸሐፊውን መጽሐፍ ይመለከቷል።

[15] *1998 Year book of Jehovah's Witnesses, 31.*

[16] *Alan W. Gomes, Unmasking the Cults, 22.*

[17] *2016 Year Book of Jehovah's Witnesses, 176.* "የይሖዋ ምስክሮች" ስብሰባቸውን "ጉባኤ" ብለው ይጠሩታል።

አብያተ ክርስቲያናት አባልና አገልጋይ የነበረ ነው[18]። ይህ ማስት ባለፉት አንድ ምዕተ ዓመት፣ ከስባት ሚሊዮን ሰው በላይ ከእኛ ወደ አነርሱ ሄዷል ማለት ነው። በኢትዮጵያ የተደረገ ሌላ ጥናት ደግሞ፣ በተመሳሳይ መልኩ 75% የሚሆነው "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" አባል በአንድ ወቅት የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት አባል ነበር። ይህ ማለት፣ "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" ስዎች፣ በየዓመቱ ከ35 ሺህ ሰው በላይ ከእኛ ወደ አነርሱ የሚሄዱ ሰዎችን ያጠምቃሉ።

የዕድገት መጠን

በሥነ ጽሑፍ ፊታውራሪነት የሚተመው፣ "የይሖዋ ምስክሮች" የዕድገት ፍጥነት እጅግ አስደንጋጭ ነው። በ1965 ዓ.ም. 1.1 ሚልዮን የነበረው የንቋ ተሳታፊ አባላት ቍጥር በ1980 ዓ.ም.

[18] *Josh Mc Dowell and Don Stewart, Assisted by Kurt Van Gorden The Deceivers. Walter Martin, The Rise of the Cults (Zondervan, Grand Rapids, 1955).* እንደ *Pew Research Center* ጥናት፣ 63 በመቶ የሚሆኑት "የይሖዋ ምስክሮች"፣ ከዐሥራ ሁለተኛ ክፍል በላይ የተማሩ አይደሉም። እንዲያውም ጥናቱ በአሜሪካን አገር ከየትኛውም የሃይማኖት ክፍል ይልቅ በትምህርት ገፍተው ያልሄዱ ሰዎች በብዛት የሚገኙበት የሃይማኖት ተቋም የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር እንደ ሆነ ይገልጻል። ለዚህ ዐቢይ ምክንያቱ ድርጅቱ ሃይማኖቱን ለማስፋፋት እንጂ፣ ሰዎች ኮሌጅ ሄደው እንዲማሩ ስለማያበረታታ ነው። ብዙ የይሖዋ ምስክሮች በድርጅቱ ያልተጻፉ ጽሑፎችን ማንበብ ሊጀምሩ፣ ሃይማኖቱን ጥሰው እንደሚሄዱ ይታወቃል። ለበለጠ መረጃ የሚከተለውን ድረ ገጽ ይመለከቷል፡—

http://www.pewresearch.org/fact-tank/2016/04/26/a-closer-look-at-jehovahs-witnesses-living-in-the-u-s/

http://www.pewresearch.org/fact-tank/2016/04/26/a-closer-look-at-jehovahs-witnesses-living-in-the-u-s/ft_16-04-26_jehovahswitnesses-1/

https://www.thegospelcoalition.org/article/9-things-you-should-know-about-jehovahs-witnesses/

ወደ 2.2 ሚልዮን፣ በ1992 ዓ.ም ወደ 4.4፣ በ2015 ደግሞ ወደ 8.2 ሚልዮን አሻቅቧል[19]። በ1994 ዓ.ም. በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በሉቭየት ኅብረት ብቻ 27,000 ሰዎችን አጥምቀዋል[20]። በዓለም ዙሪያ በየዓመቱ 50 አዳዲስ ጉባኤዎች ይቋቋማሉ[21]። የድርጅቱን ዓመታዊ እንቅስቃሴ ይፋ የሚያደርገው መጽሐፍ፣ 2016 ዓ.ም የድርጅቱ መሪዎች ራሳቸው በድርጅቱ ዕድገት ከፍተኛ መደነቅ ውስጥ እንደ ገቡ ይገልጻል።

ሚስዮናዊ እንቅስቃሴ

"የይሖዋ ምስክሮች" በ1997 ዓ.ም. ብቻ የድርጅቱን ጽሑፍ ለማሠራጨት 1,179,735,841 ሰዓታትን ተጠቅመዋል[22]። ይህን ቍጥር ለንቑ ተሳታፊ አባሎቻቸው ቍጥር ስናካፍለው፣ አያንዳንዱ አባል ለጽሑፍ ሥርጭቱ በዓመት ከ200 ሰዓታት በላይ መጠቀሙን እንገነዘባለን። በ1997 ዓ.ም. የተከታዮቻቸውን ልጆች ቍጥር ጨምሮ 375,923 ሰዎችን አጥምቀዋል[23]። በ2015 ዓ.ም. ደግሞ 260,273 ሰዎችን አጥምቀዋል[24]። ይህ የሚያሳየን "የይሖዋ ምስክሮች" አንድን ሰው

[19] በየዓመቱ *Year Book of Jehovah's Witnesses* በሚል ስያሜ ድርጅቱ የሚያሳትማቸውን መጻሕፍት ይመለከታል።

[20] *Christian Reasearch Institute, "Cult Growth Statistics," Citing the Watchtower (1 January 1993), 15, 26.*

[21] ዝኒ ከማሁ። *The Watchtower Society Video, Jehovah's Witnesses: the Organization Behind the Name (1990)* ጠቅሶ እንደ ጻፈው።

[22] *1998 Yearbook of Jehovah's Witnesses, 31.*

[23] ዝኒ. ከማሁ፣ ገጽ 31።

[24] *2016 Yearbook of Jehovah's Witnesses, 176.*

የድርጅቱ አባል ለማድረግ፣ በአማካይ 3,500 ሰዓት መጠቀማቸውን ነው[25]።

እንድ ንቑ፣ "የይሖዋ ምስክር" ተሳታፊ አባል በአማካይ በአንድ ወር 18 ሰዓትን ለጽሑፍ ሥርጭት ያውላል[26]። በ1970 ዓ.ም. አንድ ንቑ አባል በዓመት ለመስክ አገልግሎት[27] 150 ሰዓትን ያውል የነበረ ሲሆን፣ ከ1992 ዓ.ም. በኋላ ግን ይህን ሰዓት በማሻሻል አንድ አባል በአማካይ በዓመት 236 ሰዓት በመስክ ምስክርነት ያሳልፋል[28]።

አንድ የምርምር መጽሔት በቅርቡ እንደ ገለጸው፣ አንድ "የይሖዋ ምስክር" በአማካይ አንድ የድግሪ ተማሪ ትምህርቱን ለመከታተል እንዲያነብ የሚጠበቅበትን ያህል አንደሚያነብ ገልጿል።

ንጽጽር

ንጽጽር የሚለው ፅንሰ አሳብ፣ ቢያንስ ሁለት ነገሮችን ማወዳደር ታሳቢ ያደረገ ነው። ተነጻጸረ ስንል አንዱ ከሌላው ጋር ተወዳደረ፣ ተገናዘበ፣ ተመሳከረ ማለት ነው። ከላይ እንደ ተመለከትነው፣ "የይሖዋ ምስክሮች" እመርታ ከላይ ያየነውን ይመስላል።

እንኪን በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን፣ በቤተ እምነት ደረጃ እንኳ የማተሚያ ቤት ያለው ቤተ ክርስቲያን የለም። በብዙ ሚልዮን የሚቈጠር አባል ያላቸው ቤተ እምነቶች፣ እንኪን በማተሚያ ቤት

[25] *Robert M. Bowman, Jr. Jehovah's Withnesses. (Grand Rapids: Zon,1995),14.*

[26] ዝኒ. ከማሁ፣ ገጽ 15።

[27] "የመስክ አገልግሎት" የሚባለው በየመንገድ ዳሩና በየቤቱ የመጠበቂያ ግንብ መንገልን መስበክ እንዲሁም ጽሑፎቹን ማሠራጨት ነው።

[28] ዝኒ. ከማሁ፣ ገጽ 16።

ደረጃ ይቅርና በዘመናዊ መንገድ የተደራጀ የመለስተኛ ጎትመት ሥራ አይሠሩም። በተወሰነ መጠን ጭል ጭል የሚለውን የጎትመት ሥራ እንኳ፣ ቤተ እምነቶቹ የሚያሠሩት፣ በንግድ ማተሚያ ቤቶች ነው። በእነዚህ ማተሚያ ቤቶች ውስጥ ታትመው የሚወጡ አብዛኞቹ መጻሕፍት የጎትመት ጥራታቸው ብቻ ላይሆን፣ የአርትዖት ሥራቸው እንኳ በወጉ የተሠራላቸው አይደሉም—በነገረ መለኮት ያዘታቸውም ሆነ በሥነ ጽሑፍ ቅርጻቸው አጅግ በሚያሳፍር መልክ የወረዱ ናቸው።

አንዳንድ ቤተ እምነቶች፣ አንደ መስቀል ወፍ በዓመት አንዴ ታትሞ የሚወጣ መጽሔት ቢኖራቸውም በሥርጭት፣ በጎትመት ጥራት፣ በጽሑፍ ወቅታዊነት፣ በአርትዖት ሥራ ወዘተ ብዙ ወደ ኋላ የቀሩ ለመሆናቸው ሥራቸው ይመሰክራል።

ጎትመት በሌለበት ንባብ የለም። ንባብ በሌለበትም ዕውቀት የለም። ዕውቀት በሌለበት ደግሞ ብፍታ እንጂ እውነተኛ ዕድገት ሊኖር አይችልም። ለዚህም ነው በርካቶች፣ በከፍተኛ ቁጥር ወደ ስሕተት ትምህርት የሚጐርፉት። በኢትዮጵያ ብቻ እንኳ በየዓመቱ 35 ሺህ ለምች ከወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት በመፍለስ "የአንሊ ጂለስን" ሃይማኖት ይቀላቀላሉ። ከላይ ለማየት እንደ ሞከርነው፣ በአሜሪካን አገር የተካሄደ ጥናት ደግሞ 75 ከመቶ የሚሆኑ "የይሖዋ ምስክሮች" በአንድ ወቅት የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት አባል የነበሩ መሆናቸው ችግሩ ዓለም ዐቀፋዊ ይዘትም አንዳለው የሚያሳይ ነው።

ችግሩን አንዴት መፍታት እንችላለን ለሚለው የተወሰኑ ነጥዐችን ጠቀም አድርጌ ልቋጭ:— (1) ቢያንስ ቤተ እምነቶች

የራሳቸው የሆነ የማተሚያ ቤት እንዲኖራቸው ቢደረግ፣ (2) አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት በጎልማሶች፣ በወጣቶችና በሕፃናት የተደራጀ የሰንበት ትምህርት ቤት እንዲኖራቸው ማድረግ፣ (3) አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት የራሳቸው የሆነ ቤተ መጻሕፍትን እንዲከፍቱ ማስቻል፣ (4) የመጻሕፍት ወር፣ የንባብ ሳምንት ወዘተ በማዘጋጀት ሕዝቡ የንባብ ፍላጎቱ እንዲያድግ ማስቻል፣ (5) ጥሩ ጥሩ መጻሕፍትን በሰንበት አምልኮና በትምህርት ክፍለ ጊዜዎች ላይ ማስተዋወቅ፣

(6) ጥሩ ጥሩ ጸሐፍያንን ዐቅም በፈቀደው ሁሉ ማበረታታት፣ (7) በየወሩ እንዲሁም ዓመታዊ ዐውደ ጥናቶችን በማዘጋጀት በተለያዩ ርእሶች ላይ ጥናታዊ ጽሑፎች እንዲቀርቡ ማድረግ፣ (8) የቤት ለቤት መጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶችን አጠናክሮ መጀመር፣ (9) ለነገረ መለኮት ጥናት አጅግ ጠቃሚ ናቸው የሚባሉ ዋና ዋና መጻሕፍትን በየቋንቋው ተርጉሞ ማቅረብ፣ (10) የመጻፍ ፍላጎቱና ተሰጥኦ ያላቸውን ለምች፣ የልብ ወለድና የኢልብ ወለድ አጻጻፍ ሥልጠና መስጠት፣ እንዲጽፉም ማበረታታት። (11) በየአጥቢያው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶችን መክፈት። አባላት ንብተው እንዲማሩ ማበረታታት። (12) የመጻሕፍት ክለብ በማዘጋጀት አባላት በክበብ እንዲታቀፉ ማድረግ። ጥሩ አንቅስቃሴ የሚያደርጉትንም መሸለም። (13) በየአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ የዐቅብተ እምነት ክበቦችን በማቋቋም በደርዛዊ ነገረ መለኮት፣ በሙግት ጥበብ፣ በመናፍቃን አስተምህሮ ላይ ወዘተ ጉዳይ ላይ ፍላጎቱ ያላቸውን ለምች ማሠልጠን። (14) በቤተ እምነት እንዲሁም በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ደረጃ ልምዶችን መለዋወጥ። (15) የመጻሕፍት ግምገማ፣ የመጽሔት ግምገማ ማዘጋጀት። በተለያየ

ርእሰ ላይ ዕውቀት ያላቸውን ነገር ግን የተለያየ አቋም ያላቸውን ሰዎች ማሟገት።

ሊነበቡ የሚገባቸው መጻሕፍት



ከሌላው ጊዜ በተለየ መልኩ፣ በዋቢ መጻሕፍት ዝርዝር ውስጥ ያካተትኋቸሁ መሠረታዊውን የክርስትና ትምህርት ለመረዳት፣ የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ለማወቅ፣ ዕቅብተ እምነትን ለመተግበር አንዲሁም ለአእምሮ ብስለት ይጠቅማሉ ያልኋቸውን መጻሕፍት ነው። በዚህ መጽሐፍ በዋቢነት የተጠቀምሁባቸውን መጻሕፍት በተመለከተ ግን፣ በየገጹ ያሉትን የጎዳግ መዘክሮች ይመለከቷል።

፩. ደርዛዊ ነገረ መለኮት

ሀ. መሠረታውያን

Erickson, Millard J., Christian Theology, Grand Rapids: Baker, 2013.

Grudem, Wayne, Systematic Thoelogy: An Introduction to Biblical Doctrine. Grand Rapids: Zondervan, 1995.

Frame, John M. The Doctrine of the Knowledge of God: A Theology of Lordship. Phillipsburg, NJ: Presbyterian &Reformed, 1987.

McGrath, Alister E., Christian Thoelogy: An Introduction. Malden: Blackwell, 2016.

Poythress, Vern S. Symphonic Theology: The Validity of Multiple Perspectives in Theology. Grand Rapids: Zondervan Academic, 1987; Phillipsburg, NJ: P&R, 2001.

፪. ትምህርተ ክርስቶስ

Bauckham, Richard. God Crucified: Monotheism and Christology in the New Testament. Grand Rapids: Eerdmans, 1999.

Bock, Darrell L. Blasphemy and Exaltation in Judaism: The Charge Against Jesus in Mark 14:53–65. Grand Rapids: Baker, 2000.

Bowman, Robert M., and J. Ed Komoszewski. Putting Jesus in His Place: The Case for the Deity of Christ. Grand Rapids: Kregel, 2007.

Bray, Gerald. Creeds, Councils and Christ: Did the Early Christians Misrepresent Jesus? Rossshire, UK: Mentor, 2009.

Brown, Harold O. J. Heresies: The Image of Christ in the Mirror of Heresy and Orthodoxy from the Apostles to the Present. Peabody, MA: Hendrickson, 1998.

Evans, Craig A. Fabricating Jesus: How Modern Scholars Distort the Gospels. Downers Grove, IL: InterVarsity, 2006.

Fee, Gordon D. Pauline Christology: An Exegetical-Theological Study. Peabody, MA: Hendrickson, 2007.

Gathercole, Simon J. The Preexistent Son: Recovering the Christologies of Matthew, Mark, and Luke. Grand Rapids: Eerdmans, 2006.

Green, Joel B., and Max Turner, eds. Jesus of Nazareth: Lord and Christ: Essays on the Historical Jesus and New Testament Christology. Grand Rapids: Eerdmans; Carlisle: Paternoster, 1994.

Harris, Murray J. Jesus as God: The New Testament Use of Theos in Reference to Jesus. Grand Rapids: Baker, 1992.

----------. *3 Crucial Questions About Jesus.* Grand Rapids: Baker, 1994.

Hengel, Martin. Studies in Early Christology. Edinburgh: T & T Clark, 1995.

Hurtado, Larry W. Lord Jesus Christ: Devotion to Jesus in Earliest Christianity. Grand Rapids: Eerdmans, 2003.

Komoszewski, J. Ed, M. James Sawyer, and Daniel B. Wallace. Reinventing Jesus: How Contemporary Skeptics Miss the Real Jesus and Mislead Popular Culture. Grand Rapids: Kregel, 2006.

Longenecker, Richard N., ed. Contours of Christology in the New Testament. Grand Rapids: Eerdmans, 2005.

Piper, John. Seeing and Savoring Jesus Christ. Wheaton, IL: Crossway Books, 2004.

Rowdon, Harold H., ed. Christ the Lord: Studies in Christology Presented to Donald Guthrie. Leicester, UK; Downers Grove, IL: InterVarsity Press, 1982.

Witherington, Ben, III. The Many Faces of the Christ: The Christologies of the New Testament and Beyond. Companions to the New Testament. New York: Crossroad, 1998.

፫. ጸጋ ስጦታዎችና አጠቃቀማቸው

Carson, D. A. Showing the Spirit: A Theological Exposition of 1 Corinthians, 12-14, Grand Rapids, Mi.: Baker, 1987.

Deere, Jack The Beginner's Guide to the Gift of Prophecy, Bloomington, Minnesota: Chosen Books, 2001.

----------. *Surprised by the Power of the Spirit: Discovering How God Speaks and Heals Today* Grand Rapids, MI.: Zondervan, 2010.

Grudem, Wayne The Gift of Prophecy in the New Testament and Today, Wheaton, Illinois: Crossway Books, 2000.

Keener, Craig S. Spirit Hermeneutics: Reading Scripture in Light of Pentecost, Grand Rapids, Eerdmans, 2016.

----------. *Miracles: The Credibility of the New Testament Accounts , (Vol I & II)* Grand Rapids, Baker, 2011.

----------. *Gift and Giver: The Holy Spirit for Today,* (Grand Rapids, MI.: Baker 2001).

፬. ታሪካዊ ነገረ መለኮት

Allison, Gregg. Historical Theology: An Introduction to Christian Doctrine. Grand Rapids: Zondervan, 2011.

McGrath, Alister. Historical Theology: An Introduction to the History of Christian Thought. Malden: Blackwell, 2012.

Olson, Roger E., The Story of Christian Theology. Downers Drove: IL.: IVP, 1999.

፭. ማጣቀሻ መጻሕፍት

Bauer, Ardnt, Gingrich, Danker, A Greek-English Lexicon of the New Testament (Chicago: University of Chicago Press, 1979).

Colin Brown, ed., New International Dictionary of New Testament Theology (Grand Rapids, MI.: Zondervan, 1986).

Gerhard Kittel, ed., Theological Dictionary of the New Testament (Grand Rapids, MI.: Eerdmans, 1964).

Louw and Nilda, Greek-English Lexicon of the NT Based on Semantic Domains (New York: United Bible Society, n.d.).

፮. ክርስቲያናዊ ዐቅበተ እምነት

ትምህርቴም ሆነ አገልግሎቴ ክርስቲያናዊ ዐቅበተ እምነት ከመሆኑ አንጻር፣ በዚህ የጥናት ዘርፍ ላይ ዘለግ ያለ ዝርዝር መለጠት አፈልጋለሁ። የጥናት ዘርፉ የተለያዩ ነባቤ ቃላት ያሉት ቢሆንም፣ ማንኛውም ክርስቲያን ቢያነበው ብዙ ይጠቀምባቸዋል የምላቸውን መጻሕፍት ብቻ ዘርዝሬለሁ።

ሀ. የዐቅበተ እምነት መዝገበ ቃላትና መክፈቻ መጻሕፍት

Boa, Kenneth D., and Robert M. Bowman Jr. Faith Has Its Reasons: An Integrative Approach to Defending Christianity. Colorado Springs: NavPress, 2001.

Evans, C. Stephen. Why Believe? Reason and Mystery as Pointers to God. Grand Rapids: Eerdmans, 1996.

Carnell, Edward J. An Introduction to Christian Apologetics. Grand Rapids: Eerdmans, 1948.

Clark, David K. Dialogical Apologetics: A Person-Centered Approach to Christian Defense. Grand Rapids: Baker, 1993.

Cowan, Steven B., ed. Five Views on Apologetics. Grand Rapids: Zondervan, 2000.

Craig, William Lane. Reasonable Faith: Christian Truth and Apologetics. Rev. ed. Wheaton, Ill.: Crossway, 1994.

Craig, William Lane, and Chad Meister, eds. God Is Great, God Is Good: Why Believing in God Is Reasonable and Responsible. Downers Grove, Ill.: InterVarsity Press, 2009.
Dulles, Avery. A History of Apologetics. San Francisco: Ignatius, 2005.
Frame, John M. Apologetics to the Glory of God: An Introduction. Phillipsburg, N.J.: Presbyterian & Reformed, 1994.
Geisler, Norman. Baker Encyclopedia of Christian Apologetics. Grand Rapids: Baker, 1999.
Keller, Timothy. The Reason for God: Belief in an Age of Skepticism. New York: Dutton/Penguin, 2008.
Kreeft, Peter. Fundamentals of the Faith: Essays in Christian Apologetics. San Francisco: Ignatius, 1988.
Kreeft, Peter, and Ronald Tacelli. Handbook of Christian Apologetics. Downers Grove, Ill.: InterVarsity Press, 1994.
Lewis, C. S. Mere Christianity. New York: Macmillan, 1943.
Little, Paul. Know Why You Believe. 5th ed. Downers Grove, Ill.: InterVarsity Press, 2008.
McGrath, Alister E. Intellectuals Don't Need God and Other Modern Myths: Building Bridges to Faith Through Apologetics. Grand Rapids: Zondervan, 1993.
Meister, Chad. Building Belief: Constructing Faith from the Ground Up. Grand Rapids: Baker, 2006.
Moreland, J. P. Scaling the Secular City: A Defense of Christianity. Grand Rapids: Baker, 1987.
Moreland, J. P., and William Lane Craig. Philosophical Foundations for a Christian Worldview. Downers Grove, Ill.: InterVarsity Press, 2003.
Murray, Michael, ed. Reason for the Hope Within. Grand Rapids: Eerdmans, 1999.
Sire, James W. A Little Primer on Humble Apologetics. Downers Grove, Ill.: InterVarsity Press, 2006.
Sire, James. Why Should Anyone Believe Anything at All? Downers Grove, Ill.: InterVarsity Press, 1994.
Sproul, R. C. Defending Your Faith: An Introduction to Apologetics. Wheaton, Ill.: Crossway, 2003.
Strobel, Lee. The Case for Faith. Grand Rapids: Zondervan, 2000.
Taylor, James E. Introducing Apologetics: Cultivating Christian Commitment. Grand Rapids: Baker Academic, 2006.

ለ. ድኅረ ዘመናዊነት፣ አንጻራዊነት እንዲሁም የሃይማኖት ሥነ ዕውቀት

Allen, Diogenes. Christian Belief in a Postmodern World: The Full Wealth of Conviction. Louisville: Westminster John Knox, 1989.
Alston, William P. Perceiving God: The Epistemology of Religious Experience. Ithaca, N.Y.: Cornell University Press, 1991.
Beckwith, Francis, and Gregory Koukl. Relativism: Feet Planted Firmly in Mid-Air. Grand Rapids: Baker, 1998.
Boghossian, Paul. Fear of Knowledge: Against Relativism and Constructivism. Oxford: Oxford University Press, 2007.
Mavrodes, George. Belief in God: A Study in the Epistemology of Religion. New York: Random House, 1970.

Morris, Thomas, ed. God and the Philosophers: The Reconciliation of Faith and Reason. Oxford: Oxford University Press, 1994.
Moser, Paul K. The Elusive God: Reorienting Religious Epistemology. Cambridge: Cambridge University Press, 2008.
Plantinga, Alvin. God and Other Minds. Ithaca, N.Y.: Cornell University Press, 1967.
----------. *Warranted Christian Belief.* Oxford: Oxford University Press, 2000.
Swinburne, Richard. Faith and Reason. Oxford: Oxford University Press, 1981.
Wolterstorff, Nicholas. Reason Within the Bounds of Religion. 2nd ed. Grand Rapids: Eerdmans, 1984.

ሐ. ሀልዎተ እግዚአብሔር

Collins, Francis S. The Language of God: A Scientist Presents Evidence for Belief. New York: Free Press, 2007.
Copan, Paul, and Paul K. Moser, eds. The Rationality of Theism. New York: Routledge, 2003.
Craig, William Lane. Cosmological Argument. New York: Harper & Row, 1979. Reprint, Eugene, Ore.: Wipf & Stock, 2001.
Davis, Stephen T. God, Reason, and Theistic Proofs. Grand Rapids: Eerdmans, 1997.
Dembski, William A. The Design Inference: Eliminating Chance Through Small Probabilities. Cambridge: Cambridge University Press, 1998.
Evans, C. Stephen. Kierkegaard's Ethic of Love: Divine Commands and Moral Obligations. Oxford: Oxford University Press, 2004.
Mitchell, Basil. The Justification of Religious Belief. Oxford: Oxford University Press, 1981.
O'Connor, Timothy. Theism and Ultimate Explanation: The Necessary Shape of Contingency. Malden, Mass.: Blackwell, 2008.
Rea, Michael C. World Without Design: The Ontological Consequence of Naturalism. New York: Oxford University Press, 2002.
Swinburne, Richard. The Existence of God. Oxford: Clarendon, 1979.

መ. የእኩይ ጣጣ

Adams, Marilyn McCord. Horrendous Evils and the Goodness of God. Cornell Studies in the Philosophy of Religion. Ithaca, N.Y.: Cornell University Press, 2000.
Boyd, Gregory A. Is God to Blame? Beyond Pat Answers to the Problem of Suffering. Downers Grove, Ill.: InterVarsity Press, 2003.
----------. *Satan and the Problem of Evil: Constructing a Trinitarian Warfare Theodicy.* Downers Grove, Ill.: InterVarsity Press, 2001.
Carson, D. A. How Long, O Lord? Reflections on Evil and Suffering. Grand Rapids: Baker, 1990.
Feinberg, John. The Many Faces of Evil: Theological Systems and the Problem of Evil. 1st ed. Grand Rapids: Zondervan, 1994.
Kreeft, Peter. Making Sense Out of Suffering. Ann Arbor, Mich.: Servant, 1986.
Peterson, Michael. Evil and the Christian God. Grand Rapids: Baker, 1982.
Plantinga, Alvin. God, Freedom, and Evil. New York: Harper and Row, 1974. Reprint, Grand Rapids: Eerdmans, 1977.
Reichenbach, Bruce. Evil and a Good God. New York: Fordham University Press, 1982.

Swinburne, Richard. Providence and the Problem of Evil. Oxford: Oxford University Press, 1998.
Van Inwagen, Peter. The Problem of Evil. Oxford: Oxford University Press, 2008.
Yancey, Philip. Disappointment with God: Three Questions No One Asks Aloud. Grand Rapids: Zondervan, 1988.

ሠ. የቅዱሳት መጻሕፍት ተአማኒነት

Barnett, Paul. Jesus and the Logic of History. Downers Grove, Ill.: InterVarsity Press, 1997.
Blomberg, Craig. The Historical Reliability of John's Gospel. Downers Grove, Ill.: InterVarsity Press, 2002.
----------. *The Historical Reliability of the Gospels.* 2nd ed. Downers Grove, Ill.: InterVarsity Press, 2008.
----------. *Jesus and the Gospels: An Introduction and Survey.* 2nd ed. Nashville: Broadman & Holman, 2009.
Bruce, F. F. The New Testament Documents: Are They Reliable? Rev. ed. Leicester, U.K.: Inter-Varsity Press, 1960.
Copan, Paul. Is God a Moral Monster? Making Sense of the Old Testament. Grand Rapids: Baker, 2011.
Craig, William Lane. The Son Rises: The Historical Evidence for the Resurrection of Jesus. Eugene, Ore.: Wipf & Stock, 2001.
Davis, Stephen T. Risen Indeed: Making Sense of the Resurrection. Grand Rapids: Eerdmans, 1993.
Habermas, Gary R. The Historical Jesus: Ancient Evidence for the Life of Christ. Grand Rapids: Baker, 1980.
----------. *The Resurrection of Jesus: An Apologetic.* Grand Rapids: Baker, 1980.
Wilkins, Michael J., and J. P. Moreland. Jesus Under Fire: Modern Scholarship Reinvents the Historical Jesus. Grand Rapids: Zondervan, 1995.
Wright, N. T. The Challenge of Jesus: Rediscovering Who Jesus Was and Is. Downers Grove, Ill.: InterVarsity Press, 1999.
----------. *Jesus and the Victory of God.* Vol. 2 of Christian Origins and the Question of God. Minneapolis: Fortress, 1996.

ረ. ከሌሎች ሃይማኖቶች የሚሰነዘሩ ትችቶችን ለመከላከል

Chapman, Colin. Cross and Crescent: Responding to the Challenge of Islam. Downers Grove, Ill.: InterVarsity Press, 2003.
Clark, David, and Norman Geisler. Apologetics in the New Age. Grand Rapids: Baker, 1990.
Corduan, Winfried. Neighboring Faiths: A Christian Introduction to World Religions. Downers Grove, Ill.: InterVarsity Press, 1998.
George, Timothy. Is the Father of Jesus the God of Muhammad? Grand Rapids: Zondervan, 2002.
Sire, James. The Universe Next Door. 4th ed. Downers Grove, Ill.: InterVarsity Press, 2004.
Zacharias, Ravi. Jesus Among Other Gods. Nashville: Thomas Nelson, 2000.

ሰ. ሃይማኖትና ሳይንስ፣ ሃይማኖትና ፍልስፍና

Abraham, William J. Crossing the Threshold of Divine Revelation. Grand Rapids: Eerdmans, 2006.

Bauckham, Richard. Jesus and the God of Israel. Grand Rapids: Eerdmans, 2008.
Beckwith, Francis J. David Hume's Argument Against Miracles: A Critical Analysis. Lanham, Md.: University Press of America, 1989.
Brown, Colin. Miracles and the Critical Mind. Grand Rapids: Eerdmans, 1984.
Copan, Paul, and William Lane Craig. Creation Out of Nothing: A Biblical, Philosophical, and Scientific Exploration. Grand Rapids: Baker Academic, 2004.
Geivett, Douglas, and Gary Habermas, eds. In Defense of Miracles. Downers Grove, Ill.: InterVarsity Press, 1997.
Habermas, Gary R., and Michael R. Licona. The Case for the Resurrection of Jesus. Grand Rapids: Kregel, 2004.
Licona, Michael. The Resurrection of Jesus: A New Historiographical Approach. Downers, Grove, Ill.: IVP Academic, 2010.
Ratzsch, Del. Nature, Design, and Science: The Status of Design in Natural Science. SUNY Series in Philosophy and Biology. Albany, N.Y.: SUNY Press, 2001.
----------. *Science and Its Limits: The Natural Sciences in Christian Perspective.* 2nd ed. Downers Grove, Ill.: InterVarsity Press, 2000.
Wierenga, Edward. The Nature of God. Ithaca, N.Y.: Cornell University Press, 1989.

ሸ. በእምነት እንቅስቃሴ አስተምህሮ ላይ ሒስ የሚሰነዝሩ መጻሕፍት

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በስፋት የሚታየው የዚህ አስተምህሮ ችግር ነው። እነዚህ መጻሕፍት በዚህ ረገድ ትልቅ ጥቅም ያላቸው ይመስለኛል።

Barron, Bruce. The Health and Wealth Gospel. Downers Grove, Ill.: Inter Varsity Press, 1987.
Bawman, Robert M. Jr, The Word Faith Controversy: Understanding the Health and Wealth Gospel. Grand Rapid: Baker, 2001.
Farach, Charles, Jr. From the Pinnacle of the Temple: Faith vs Presumption. Plain Field, N. J: Logos International, 1979.
Fee, Gordon D. The Disease of the Health and Wealtn Gospel. Costa Mesa, Calif The World for Today, 1979.
Hanegraff, Hank. Christianity in Crisis. Eugene, Ore.: Harvest House, 1993.
_____ *Counterfeit Revival.* Dallas word, 1997.
Horton, Michael, ed. The Agony of Deceit. Moody, 1990.
Hunt, Dave, and T.A. Macmahon. The Seduction of Christianity. Harvest House, 1985.
MacArthur, John. Charismatic Chaos. Grand Rapids, MI.: zondervan,1992.
McConnell, D.R. A Different Gospel: A Historical and Biblical Analysis of the Modern Faith Movement. Peabody, Mass.: Hendrickson Publisher, 1995.
Moo, Douglas, gen ed. The Gospel and Contemporary Perspectives: Viewpoints from Trinity Journal Biblical Forum services 2. Grand Rapids: Kregel 1991.

ቸ. በጸሓፊው የተዘጋጁ ሌሎች መጻሕፍት

የትምህርተ ሥላሴ መሠረታውያን፤ መጽሐፍ ቅዱሳዊ፣ ታሪካዊና ምክንያአዊ ትንታኔ፤ አትላንታ ጆርጂያ፤ ተስፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር፤ 2015.

አርዮሳውያን የይሖዋ ምስክሮች አስተምህሮ በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን አትላንታ ጆርጂያ፤ ተስፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር፤ 2016.

ስባልዮሳውያን የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን፤ ቅጽ 1 ትምህርተ እግዚአብሔር፤ አትላንታ ጆርጂያ፤ ተስፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር፤ 2016.

ስባልዮሳውያን የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን ቅጽ 2 ትምህርተ ድኅነት፤ አትላንታ ጆርጂያ፤ ተስፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር፤ 2016.

ውርጃን ሕጋዊ ያደረግነው ለምንድን ነው? አትላንታ ጆርጂያ፤ ተስፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር፤ 2016.

"...በሥጋ ትንሣኤ አምናለሁ..." የአስተምህሮተ ትንሣኤ መጽሐፍ ቅዱሳዊ፣ ታሪካዊና ፍልስፍናዊ ትንታኔ፣ ግራንድ ራፒድስ ሚሺገን፤ ተስፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር፤ 2014.

ትንሣኤ ሙታን የአካል ወይስ የመንፈስ፣ አትላንታ ጆርጂያ፤ ተስፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር፤ 2016.

ከምኒልክ አስፋውና ከዶክተር ተስፋዬ ሮበሌ፤ *የእምነት ወይስ የክህደት እንቅስቃሴ፣* አትላንታ ጆርጂያ፤ ተስፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር፤ 2016.

ማስታወቂያ

ይህን መጽሐፍ እንዲሁም የጸሓፊውን ሌሎች መጻሕፍት ማግኘት ከፈለጉ፣ በሚከተለው ቊጥር በመደወል ማዘዝ ይችላሉ:—

አሜሪካን አገር

+16166174746

አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ

+251911657058

የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ምሁራን፣ ስለዚህ መጽሐፍ ምን ይላሉ?

"...በዚህ ጉዳይ ላይ እስካሁን ተጽፈው ካነበብኋቸው መጻሕፍት መካከል ጥልቀት ያለውና ዕውቀት ያገኘሁበት መጽሐፍ ይህ ነው..."

ንጉሤ ተፈራ (ዶክተር)
ከሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን

******

"በብሉይም ሆነ በሐዲስ ኪዳን፣ ሐሰተኛ ነቢያት እንደ ነበሩ፣ እውነተኞቹም በጽኑ እንደተፋለሟቸው ቅዱስ መጽሐፍ...ይነግረናል...ተስፋዬም ከዚህ የተለየ ዐላማ የለውም:: እኛም ወደዚህ መስመር እንድንዘልቅ አባቶች በቀደዱት ትልም ላይ እንድንጓዝ ይጠራናል::"

ጳድቁ አብዶ (መጋቢ)
የወቅቱ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ፕሬዚደንት

******

"ወንድማችን ዶክተር ተስፋዬ ሮበሌ...ወንጌላዊውን ክርስትና እየሞገተ ላለው እንግዳ ልምምድና ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ያፈነገጠ ትምህርት በማረም፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አቋም እንድንይዝ ተማጽኖ በማቅረብ፣ በምርምር የተደገፈ...መጽሐፍ አቅርቦልናል..."

ኅይሉ ቸርነት (መጋቢ)
የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ኅብረት ቤተ ክርስቲያን በሎስ አንጀለስ—መጋቢ
የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት በሰሜን አሜሪካ የቦርድ ፕሬዚደንት

******

"...ወንድማችን ዶክተር ተስፋዬ ሮበሌ በዚህ መጽሐፉ የሚነግረን (የሚሞግተን)፣ 'ለእምነታችሁ ልትጋደሉ ይገባችኋል፤ ይህ የእውነተኛ ክርስቲያን መገለጫ አንዱ ገጽታ ነውና' የሚለውን ነው:: እስቲ ይህን መጽሐፍ አንብበን ከያለንበት፣ ምናልባትም ከተኛንበት እንንቃ!"

ቴዎድሮስ በየነ
የመሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ፕሬዚደንት

$20.00 U.S.
ISBN 978-1-4951-6107-0
51600>
9 781495 161070



አሳታሚ: ተስፋ ወንጌላዊያን ክርስትና ማኅበር
PUBLISHER: THE EVANGELICAL SOCIETY FOR APOLOGETICS [TESFA]